# ክርስቲያናዊ ሕይወት

## የክርስትና ሥነ ምግባርና ግብረ-ገብ መመሪያ መጽሐፍ

በዮሴፍ ኢምበርይ

# ክርስቲያናዊ ሕይወት

## የክርስትና ሥነ ምግባርና ግብረ-ገብ መመሪያ መጽሐፍ

በዮሴፍ ኢምበርይ

ተርጓሚ

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ሉተራን ቤተ ክርስቲያን
የወንጌል ክፍል
2011 ዓ.ም.

© Rune Imberg 2021
Only to be reprinted / copied after permission through
*Evangelisk Litteraturmission - Scriptura, Sweden*

## በጸሐፊው የተደረሱ ሌሎች መጻሕፍት

1. የሕይወት መንገድ የክርስትና እምነት ዋና ዋና አርእስተ ነገሮች፥ 1987
2. እንጸልይ የቤተ ሰብ የጸሎት መመሪያ፣ 1989

ሁለቱም የታተሙት

በ

STIFTELSEN

EVANGELISK LITTERATU RMISSION,

GOTHENBURG, SWEDEN

© ሩኔ ኢምበርይ፣ 1995

342 34 አልቬስታ፤ ስዊድን

አሳታሚ

STIFTELSEN

EVANGELISK LITTERATURMISSION,

Tores SallInfomedia AB

Vaxjo, Sweden

© ይህን መጽሐፍ ወይም የመጽሐፉን ክፍል ያለተርጓሚው ፈቃድ ማባዛት፣ መገልበጥም ሆነ ማሳተም አይቻልም።

# ማውጫ


ገጽ

መግቢያ .................................................. 5

ምዕራፍ 1
እግዚአብሔር፤ ሰውና ዓለም ........................................ 9

ምዕራፍ 2
የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ተግባር ........................ 27

ምዕራፍ 3
ማኅበረ ሰብና አገር ........................................ 41

ምዕራፍ 4
ሥነ ምግባርና ግብረ ገብ ........................................ 59

ምዕራፍ 5
ዓለማዊ ወይም ክርስቲያናዊ መሠረት ያለው
ሥነ ምግባር ........................................ 83

ምዕራፍ 6
እምነትና ሕይወት ........................................ 98

ምዕራፍ 7
ባልንጀራን ማገልገል ........................................113

ምዕራፍ 8
ሰብዓዊ መብቶች ........................................129

ምዕራፍ 9
ፍቅርና ጋብቻ ........................................148

ምዕራፍ 10
ቤትና ቤተ ሰብ........................................168

ምዕራፍ 11
ሥልጣንና ፍትህ ........................................182

ምዕራፍ 12
መከላከያና ጦርነት ........................................198

ምዕራፍ 13
አብዮት ........................................216

ምዕራፍ 14
ትምህርትና ሥልጠና........................................226

ምዕራፍ 15
ሥነ ጥበብና ሳይንስ ........................................235

ምዕራፍ 16
ሥራና ወሮታው ........................................251

ምዕራፍ 17
ክርስቲያናዊ ምስክርነት ........................................267

ምዕራፍ 18
በሕይወት መንታ መንገዶች ላይ........................................282

ምዕራፍ 19
ሕይወትና ሞት ........................................302

ምዕራፍ 20
ወደ ዘለዓለማዊ ግብ መጓዝ ........................................313

# መግቢያ

ይህንን በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ላይ የሚያተኩረውን ሥራ በማቀርብበት ወቅት የአሳቡን ዳራና ዓላማ ማብራራት ተገቢ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ከሠላሳ ዓመታት ለማያንሱ ጊዜያት ክርስቲያናዊ አስተምህሮን (ዶክትሪን) አስመልክቶ ተከታታይነት ያለው ጥናት ሳካሄድ ቆይቻለሁ። ወደ ኋላ ጥቂት ዘግይቶ ግን ሥነ ምግባርን በሚመለከት ተከታታይነት ያላቸውን ጥናቶች ማድረግ እንደ ነበረብኝ ስረዳ ሥነ ምግባራዊ መርሆዎችና ግብረ ገባዊ አተገባበራቸውን ማብራራት ይቻል ዘንድ ጠንካራ የሆነ የአስተምህሮ መሠረት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተገነዘብኩ። ሥነ ምግባርን በሚመለከት ብዙ ውዝግብ ያለ ቢሆንም ከእርሱ ጀርባ ስለሚገኙት መርሆዎች የሚታሰበው ግን በጥቂቱ ነው። ይህንን እውነታ ሥነ ምግባርና ግብረ ገብ በተሰኙት ቃላት በሁሉም ዘንድ በሚፈጠረው ግራ መጋባት ማረጋገጥ ይችላል። ብዙ ተናጋሪዎች ልዩነቱን የማያውቁ በመሆኑ ሰዎች ጥያቄ እንዳያቀርቡላቸው በመሥጋት ከሁለቱ ስለ አንደኛው ርዕሰ ጉዳይ ላይ እየተናገሩ ባሉበት ጊዜ እንኳ አብዛኛውን ጊዜ በሁለቱም ቃላት ይጠቀማሉ።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማን አስመልክቶ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ላይ መመሥረት ያለበትና ይህ ካልሆነ ግን ከሌሎች አመለካከቶች ወይም አስተምህሮዎች ጋር ከመቀላቀሉም ባሻገር በምድረ በዳ ከሚደረግ ጨኸት ጋር የሚመሳሰል መሆኑን የተቻለውን ያህል ግልጽ አድርጎ ማሳየት አስፈላጊ መሆኑን ተረድቻለሁ። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ወይም አስተምህሮ በተሰኙት ቃላት መካከል ግራ መጋባት የሚፈጠርባቸው ከሆነ ይህንን ዕውነታ የበለጠ ልናብራራ ይገባናል። ክርስቲያናዊ አስተምህሮንና ሥነ ምግባርን እንዲሁም ግብረ ገብን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ የሚያርፉት በክርስቶስ ላይ ነው። እርሱ አስተማሪ÷ አምላክ÷ ጌታና አዳኝም ጭምር ነው። ‹‹ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና›› (ዮሐ. 15÷5)።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ክርስቲያናዊ ሕይወትን÷ ሥነ ምግባርንና ግብረ ገብን በተመለከተ ሕግ ፍጻሜ ብቻ እንደሆነ አድርጎ ማሰቡ ፍጹም ስሕተት ነው። ይህ ብልጣብልጥነት ወደሚመስል ነገር ግን ትክክል ወዳልሆነ ድምዳሜና ወደ ፈሪሳዊነት ይመራናል።

ክርስቲያናዊ ሕይወት ግቡ የሚያደርገው ቅድስናን ሲሆን እርሱንም መቀደስ በሚለው መልኩ ልንረዳው እንችላለን። እርሱም የማያቋርጥ ሥራ ነው። ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም እስካሉ ድረስ ወደዚህ ግብ ሙሉ ለሙሉ ሊደርሱ የማይችሉ ቢሆንም በዚሁ አቅጣጫ ወደ ፊት እንዲጓዙ ተጠርተዋል። ‹‹አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደሆንሁ አይደለም፤ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ›› (ፊልጵ. 3÷12)። ክርስቲያን እንዲህ ዓይነት ነገር ላይ ለመድረስ የሚሳነው በመሆኑ እምነትና ሕይወት በራሱ ጽድቅ ላይ ሊመሠረት አይችልም። እምነቱ÷ ተስፋውና ሕይወቱ የሚደገፈው በክርስቶስ ላይ ነው። እርሱ ጽድቃችንና ማስተሰሪያችን ነው። ይህ የክርስቶስ ክብር በሁሉም ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ሊያበራ ይገባል። ስለሆነም ስለ ክርስቶስ የሚመሰከርበት ተገቢው የምስክርነት ቦታ የክርስቲያኖች የየዕለቱ ሕይወታቸው ነው። እንዲህ ዓይነት ምስክርነት በቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚቀርብልንን ክርስቶስንና ጽድቁን በመቀበል ላይ የሚመረኮዝ መሆኑን ማስተዋስ ይገባል።

ይህንን ሥራ በማቀርብበት ወቅት ይህንን ጽሑፍ በማንበብና ብዙ ጠቃሚ የሆነ ምክር የለገሱኝን ወዳጆቼን ማመስገን እፈልጋለሁ። በተለይም በደቡብ አፍሪካ ጆሃንስበርግ ነዋሪ የሆኑትን ቄስ ብራየንትንና ባለቤታቸውን ወይዘሮ ዲክ ብራየትን÷ ስዊድን ኡፕሳላ ነዋሪ የሆኑትን ቄስ ዶክተር በርግሉንድን ላመሰግን እፈልጋለሁ። ከዚህ በተጨማሪ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን አስመልክቶ መጽሐፍ እንድጽፍ የጠየቁኝን አፍሪካውያንን ለማመስገን እፈልጋለሁ። አንዳንዶቹ

አነስተኛ መጽሐፍ እንድጽፍ የጠየቁኝ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ዳጎስ ያለ መጽሐፍ እንድጽፍ ጠይቀውኝ ነበር። ሆኖም እዚህ ላይ እንደምትመለከቱት መለስተኛ የሆነ መጽሐፍ ለማሳተም ውሳኔ ላይ ደርሻለሁ።

ይህ መጽሐፍ በግላቸው ለሚያነቡና ለአንዳንድ ማኅበረ ምእመናንና ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ግቡን መቷል ብዬ አስባለሁ። ከዚህ ባልተናነሰ መልኩ ‹‹የጌታን መንገድ›› ለማወቅ ለሚፈልጉና ‹‹በመንፈስ መቃጠል›› መሻታቸው ለሆነ ወጣቶችና አዛውንቶችም ጠቃሚ ሆኖ እንዲገኝም ምኞቴ ነው (የሐዋርያት ሥራ 18÷25)።

አልቬስታ፤ ስዊድን ጥቅምት 1994

# ምዕራፍ 1

## እግዚአብሔር÷ ሰውና ዓለም

እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ራሱን ለዓለም ሕዝብ ሁሉ እንዲታወቅ አድርጎአል:: ይህም በሁለት መንገዶች ማለትም በተፈጠረው ዓለምና በሰው ልብ አስረጅነት ግልጽ ሆኖ ይታያል:: ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እግዚአብሔር ብቻ ነበር:: እርሱም ዓለምንና ሰውን በፈጠረ ጊዜ መልካም የሆነውንም ነገር ለሰው አሳይቶት ነበር:: በሰው ውስጥ ያለው ሕሊናም ለዚህ ማረጋገጫ ነው::

እግዚአብሔር የማይታይ ከመሆኑ የተነሣ ማንም ሰው በተፈጥሮ ዐይኑ ተመልክቶት ስለ ሕልውናው ማረጋገጫ መስጠት የማይችል ቢሆንም የእግዚአብሔርን ሕልውና መካድ ተገቢነት ያለው ነገር አይደለም:: በእርግጥ ብዙ ሰዎች በዚች ዓለም ውስጥ እግዚአብሔርን ፈልገው ማግኘት እንዳልተስካላቸው የሚገልጹ ቢሆንም እግዚአብሔርን ለመፈለግ መጣር ራሱ ፍጹም ተገቢነት ያለው ነገር አይደለም:: ይህ የአንድን ቤት ወለል÷ ጣሪያውንና ግድግዳዎቹን በመፈተሽ ቤቱን የሠራውን ሰው ለማወቅ ከሚደረግ ከንቱ ሙከራ ጋር ይመሳሰላል:: እውነቱ ግን ቤቱን የገነባው ሰው በየትኛውም የቤቱ አካል ውስጥ ራሱን ሸሽጎ የማያስቀምጥ መሆኑ ነው:: እርሱ ምን ጊዜም ቢሆን ከሠራው ነገር ውጪና ከፈጠረው ነገር በላይ ነው:: በእግዚአብሔርም ዘንድ ቢሆን እንደዚሁ ነው:: ‹‹እግዚአብሔር በአሕዛብ ላይ ነገሠ፤ እግዚአብሔር በቅድስናው ዙፋን ላይ ይቀመጣል፤ የምድር ኃይለኞች ለእግዚአብሔር ናቸውና ... እርሱንም ከፍ ከፍ አደረጉት›› (መዝ. 47÷8-9):: ሁሉንም እየጠበቀና እየገዛ ስላለው ኃያል አምላክ ሳናስብ ስለ ዓለም ሕልውናና ጥበቃ ማብራሪያ ለመስጠት አንችልም:: ‹‹የማይታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና›› (ሮሜ 1÷20)::

ስለ እግዚአብሔር የሚያስረዳ የመጀመሪያው ግልጽ ማስረጃ እርሱ ራሱን በተፈጥሮ ማለትም በተፈጠረው ዓለም መግለጹ ነው:: ሁለተኛውና ግልጽ የሆነው ማስረጃ የሚገኘው ደግሞ በሰው የሕሊና ድምጽ ውስጥ ነው:: በየትኛውም የዓለም ክፍል በመልካምና በክፉ÷ ትክክል በሆነውና ባልሆነው÷ እውነት በሆነውና እውነት ባልሆነው መካከል ትልቅ ልዩነት መኖሩ በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ አለ:: መልካም ተብሎ ስለሚጠራው ነገር ማስረጃ ሲፈለግ አብዛኛውን ጊዜ የተፈጠሩት ነገሮች ከሚናገሩት በላይ ስለ እግዚአብሔር ሲነገር እናያለን:: በዚህ ዓለም በሚገኙ በማናቸውም ሰዎች ላይ ጥናት ብናካሄድ ትክክልና ስሕተት ስለ ሆኑ ነገሮች ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ ግንዛቤው አላቸው:: አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ቢያሳስቷቸው ወይም በእልከኝነት ስሜት ውስጥ ቢሆኑ ይህ ስሜታቸው ግን አብሯቸው ይኖራል:: በተለያዩ የዓለም ክፍል በሚገኙ ሰዎች ዘንድ የትኛውም ስም ቢሰጠው ይህ ስሜት በክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት የሰው ሕሊና ተብሎ ይጠራል:: እርሱም ሰውንና ዓለምን ለመጠበቅ በራሱ በፈጣሪ የተሰጠ ነገር ነው:: ይህ መልካምና ክፉ÷ ትክክልና ስሕተት የሆኑትን ላይቶ የመገንዘብ ነገር ባይኖር ሰዎችም ለመኖር አይችሉም ነበር::

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በሰው ውስጥ ከፈጠረው ነገር ጥቂቱ ብቻ መቅረቱ ግልጽ ነው:: ይህ ግልጽ የሚሆንልን እውነትና ጽድቅ በሰዎች ዘንድ ምን ያህል ዝቅተኛ ስፍራ እንደሚሰጣቸው በምንመለከትበት ወቅት ነው:: ይህም ቢሆን የምንስማማባቸው ጥቂት ‹‹የቀሩ›› ነገሮች በመኖራቸው ምክንያት አብረን ለመኖር እንችላለን:: ‹‹አምላክ የለሽነት›› ዋና መገለጫቸው በሆኑ አገሮችም ጭምር መሪዎቹ ብዙውን ጊዜ ‹‹እውነትን›› እና ‹‹ቀናነትን›› በተመለከተ ገለጻ ሲያደርጉና ሕዝቦቻቸውንም ይህንኑ እውነት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሲወተውቱ ይደመጣሉ:: ታዲያ እውነትና ቅንነት የሚመነጩት ከየት ነው?

እግዚአብሔርንም ሆነ ተፈጥሮን በሚመለከቱ ጉዳዮች ጥርጣሬዎች እንዲፈጠሩ ማድረግ የሚከብድ ነገር አይደለም::

በሌላ አንጻርም ክፉ የሆኑ ነገሮችን እያሳዩ በእግዚአብሔር ላይ ክፉ መናገር ቀላል ነው:: ‹‹ክፉ ነገሮች ለምን ይኖራሉ? እግዚአብሔር ነው የፈጠራቸው? ክፉ ነገሮች በታዩ ጊዜ እግዚአብሔር ዝም ብሎ ተመለከታቸውን? ከዚህ በተጨማሪም ሰዎች እግዚአብሔር መልካም የሆነውን ነገር የወደደው ያ ነገር መልካም ከመሆኑ የተነሣ ነው ወይስ ‹‹መልካም›› እንዲሆን በማዘዙ ነው?›› የሚል ጥያቄን ያነሳሉ::

## የእግዚአብሔርን ማንነት ወይም ‹‹ባሕርይ›› የሚመለከቱ ጥርጣሬዎች

በዚህ ስፍራ ላይ የተነሱት የመጨረሻዎቹ ጥያቄዎች የሚያጠነጥኑት በእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና በውስጣዊ ማንነቱ ላይ ነው:: እዚህ ላይ መልካም÷ እውነት÷ ትክክለኛ ወዘተ... የሚባሉትን ነገሮች በዚህ መልክ እንዲጠሩ የወሰነው ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ነው ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው:: ነገሩ እንደዚህ ቢሆን ኖሮ የእርሱ ሥልጣን ከእውነት በላይ ስለሚሆን ‹‹እውነት›› የተባለው ነገር በእኛ ዘንድ ኃይል ብቻ ሆኖ ይቀር ነበር ማለት ነው:: በሌላም አንጻር እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች መልካምና ትክክል ብሎ የጠራቸው እነርሱ ከራሳቸው ልዩ ባሕርይ የተነሳ እርሱ ሕጋዊነታቸውን ለመቀበል በመገደዱ አይደለም:: እንደዚያ ቢሆን ደግሞ እነዚያ ነገሮች ከእግዚአብሔር በላይ ስለሚሆኑ እርሱ ‹‹እግዚአብሔር›› ለመሆን አይቻለውም ወይም አምላክ ተብሎ ለመጠራት ብቃት አይኖረውም ማለት ነው:: እነዚህ ነገሮች ሊታዩ የሚገባቸው በተለየ መንገድ ነው:: እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ‹‹መልካም›› ‹‹እውነት›› ‹‹ትክክል›› ወዘተ... ብሎ የሚጠራው ከእርሱ የሚፈልቅ መልካምነትና ትክክለኛነት ስላላቸውና ከእርሱ ጋር የሚስማሙ በመሆናቸው ነው:: መልካሞቹ ነገሮች በተመደበላቸው ልዩ መንገድ በእርሱ የጠለቀ ማንነት ውስጥ ያለውን ‹‹የመለኮትን ባሕርይ››ያንጸባርቃሉ።

## ከቀድሞ ጀምሮ መልካም የሆነ ነገር እንዴት ስፍራ ሊለቅ ይችላል?

ሰው መጀመሪያው የነበረው ስፍራ በዚህ መልክ ሊብራራ ይችላል:: ማብራሪያውም ሰው መልካምና በእግዚአብሔር አምሣል ሆኖ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ባሕርይ ተላብሶ ነበር በእግዚአብሔር የተፈጠረው (ዘፍጥ. 1÷26) የሚል ነው:: እነዚህ ቃላት የሰው ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ፍጹም የሚስማማና የእግዚአብሔርን መንገዶችና ትእዛዛት የሚከተል መሆኑን ያሳያሉ:: ከዚህ በኋላ ግን አንድ ነገር ተከሰተ:: ምን ነበር ተከሰተው? የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በተፈጥሮና በሕሊናቸው ውስጥ ከነበረው የቀድሞ ዕውቀታቸው ጋር ለመኖር ፈቃደኛ አልሆኑም:: እግዚአብሔር ያሳያቸውን መልካም መንገድ በመተው በራሳቸው በሆነው ሌላ መንገድ ሊተኩት ፈለጉ (ዘፍጥ. 3÷5):: ከዚህ የተነሳም ‹‹የራሳቸውን መንገድ የሚከተሉ÷ መልካም ባልሆነ መንገድ የሚጓዙ አመፀኞችና ለመታዘዝ ፈቃደኞች የማይሆኑ ሆኑ›› (ኢሳ. 65÷2)::

ጥያቄ የሚያስነሳው ጉዳይ ያለው እዚህ ላይ ነው:- የክፋት ምንጩ የት ነው? በተለያዩ የእምነት ተቋማትና የፍልስፍና ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ብዛት ያላቸው ሰዎች እግዚአብሔር ከክፋት ምንጭነት ጋር የተያያዘ ምንም ነገር የለውም የሚለውን አሳብ ጨርሶ አይቀበሉትም:: ጥያቄ እንዳያስነሳባቸውም ከዚህ በመቀጠል የሚገኘውን አሳብ ያቀርባሉ:: ከዘለዓለም ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የክፋት ኃይል ከመጀመሪያውኑ ነበረ ይላሉ:: እንደዚህ ዓይነት አስተምህሮዎችን ባለ ሁለት ገፅታ ብለን እንጠራቸዋለን:: ይህም ማለት መልካምና ክፉ የሆነ አማልክት አሉ እንደ ማለት ነው:: ይህ ግን ከክርስትና አስተምህሮ ጋር የሚስማማ አይደለም:: በሌላ በኩል በክርስትና ውስጥም የሁለት ገፅታ አመለካከቶች እንዳሉ መቀበል ይኖርብናል:: እግዚአብሔር እርሱ ብቻ አምላክ ነው፤ዘላለማዊና ፈጣሪ የሆነው እርሱ ብቻ ነው:: በሌላም አንጻር የክፉው ኃይል ዘለዓለማዊ አይደለም::

ከእግዚአብሔር እጅ ከመውጣቱ በፊት መልካም የነበረ ቢሆንም ከጀርባ በመሆን ክፉ ለሆኑ ሥራዎች ሁሉ ዋና ተዋናይ ነው። የተፈጠረውም በእግዚአብሔር ነበር። ወደ ሕልውና በመጣበት ወቅት በታላላቅ ስጦታዎች፥ እጅግ ታላቅ በሆነ ኃይልና በከፍተኛ ዕውቀት ተሞልቶ ነበር። ከተፈጠረም በኋላ ወደ ክፉት ኃይልነት ተለወጠ።

ይህ የማይቻልና ለማመን የሚያዳግት ቢመስልም በዚህ ጉዳይ ላይ አንዳንድ ነገሮችን መነጋገርና ልዩነቶችን መስፈለ-ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ትክክል ያልሆነና ክፉት የሆነ ነገር ሊከሰት የቻለው በአንድ መንገድ መሆን አለበት። ይህም ሊሆን የሚችለው በመፈጠር ወይም በመወለድ ነው። መልካም መንገድም ተጀምሮ ሊሆንም ይችላል። ይህንን ዕውነታ ከሌቦች፥ ከከዳተኞች፥ ከአምባገነኖችና ከጨካኞች ልንማር እንችላለን። እነዚህ ሰዎች ብዙዎቹ መልካም ከሆኑ ብዙ ስጦታዎች ጋር የተወለዱ ነበሩ። ነፃነት መልካም ተግባርን ለማከናወን ምን ጊዜም ቢሆን ጠቃሚ ነገር በመሆኑ ስጦታዎቻቸውን በአግባቡ ለመጠቀም ይችሉ ዘንድ ገደብ የሌለው ግላዊ ነፃነት ተችሯቸውም ነበር። በሚዛና ውስጥ ሆኖ መልካም ነገርን ማከናወን ጥሩ ከለመሆኑም በላይ ከትውንም መልካምን ነገር ማጭለት አይችልም። በሌላም በኩል ነፃነትን መልካም ባልሆነ መንገድም መጠቀም ይቻላል። በዚህ ረገድ የተጨበጠ ማስረጃ ይኖረናል። ብዙት ያላቸው መሪዎች፥ ፈላስፋዎች፥ የአገር መሪዎች ወዘተ... ጅማሬያቸው እጅግ መልካም የነበረ ቢሆንም በሥራቸው ላይ እየቆዩ ሲሄዱ ግን መልካም የሆነውን መንገድ በመተው ክፉዎችና በአንዳንድ ሁኔታዎችም እጅግ የከፉ ሰዎች ይሆናሉ። አንዳንድ ጊዜም ወደዚህ የክፉት ባሕርይ መቼና በምን ሁኔታ ሊለወጡ እንደቻሉ ሊታወቅ የሚችልበት ሁኔታ አለ። በሕይወታቸው ውስጥ አንድ ነገር ወደ ተሳሳተ መንገድ ሲያመራ የግል «ውድቀት» ይገጥማቸዋል።

ይህ በክርስትና እምነት ውስጥ ስለ ክፉት አጀማመር የሚሰጥ አስተምህሮ ነው። መልካም የነበረው የእግዚአብሔር

መልአክ ከመቅጽበት በመለወጥ ክፉ ሆነ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ መኻ[ገ]ገር ሆኖ ይኖራል። በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከልና በተፈጠረችዋ ዓለም ውስጥ ስርቆትን ያከናውናል፤ ሥርዓት እንዲበላሽም ያደርጋል፤ የክፋት ሥራውም የሚቋረጥ አይደለም። ‹‹ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል›› (2 ቆሮ. 11÷14-15)።

ብዛት ያላቸው ሃይማኖቶችና የፍልስፍና አስተሳሰቦች በተለያዩና ባልተለመዱ መንገዶች ለክፋት ሥረ መሰረት መፍትሔ ለማግኘት ብዙ ጥረዋል። አንዳንዶቹ እንዲያውም ‹‹ክፋት›› የሚባል ነገር የለም የሚል አሳብ ያራምዳሉ። ሌሎቹ ደግሞ ‹‹ክፋት›› ተብሎ የሚጠራው ነገር በመሠረቱ የመልካምነትና የጥራት ደረጃው ዝቅ ያለ ቢሆንም መልካም ነገር አለበት፤ ስለሆነም መለስተኛ ስሕተት የሚታይበት ነው የሚል አስተሳሰብ ያኖራቸዋል። ሌሎቹ ደግሞ አሳባቸውን በሌላ ዓይነት መንገድ ይገልጻሉ። ለክፋት ሁሉ ሰበቡ የሰው አካል÷ ከአካሉ÷ ከፍላጎቱና ከምኞቱ የተነሳ አንድ ሰው ክፉ ይሆናል፤ ውስጠኛው የሰው ክፍል የሆኑት አእምሮና ነፍስ ግን ምንም ህፀፅ የሌለባቸው÷ ንጹሕና የዋህነትን የተላበሱ እንደሆኑ ያምናሉ። በዚህ አሳቤ መሠረት ‹‹መልካም ለመሆን›› የሚደረገው ጥረት ከአካል የሚመነጩትን ድክመቶች÷ መሻቶቹንና ፍላጎቶቹን ለመዋጋት የነፍስ ተሳትፎ ይፈለጋል። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር አለ። ይኸውም ነፍስ እንደ ንጹሕና የዋህ ተደርጎ ሲወሰድ አካል ግን ንጹሕ እንዳልሆነና ጥፋተኛ እንደሆነ ተደርጎ መታየቱ ነው። የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብና አስተምህሮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሰርጾ የገባው በቀደመው ዘመን ነው። ይህንን አስተሳሰብ ከሚያቀነቅኑትና ከታወቁት የእምነት ተቋማት መካከል ግኖስቲክና ማኒችያኑስ የተባሉት ይገኙበታል። እስከ ዛሬ ድረስም ቢሆን አንዳንድ አስተሳሰቦቻቸው በቤተ ክርስቲያን

ውስጥ ትልቅ ተግዳሮት መሆናቸው እንደቀጠለ ነው:: እውነተኛ በሆኑ ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ውስጥ ማለትም ከአዲስ ኪዳን ዕይታ አንጻር ዘወትር የሚጠቀሰው ነገር ሰው አንድ ማንነትና ሙሉ ስብዕና ያለውና በአጠቃላይ አካልም ሆነ ነፍስ ለመልካምም ሆነ ለክፉ ኃይላት ተጽዕኖ የተጋለጡ ናቸው ተብሎ ትምህርት ይሰጣል:: ይህ አንድ በሆነ ማንነት ‹‹አካልና ነፍስ›› ወይም ‹‹መንፈስ÷ ነፍስና አካል›› ተብለው በሚጠሩ ሁለት ወይም ሦስት ተባባሪ በሆኑ ክፍሎች እንደተጋጠመ ተደርጎ ይወሰዳል (1 ተሰ. 5÷23)::

የሰውን ማንነት በሁለት የሚከፍለውን አስተሳሰብ የምንከተል ከሆነ ‹‹ነፍስ›› የሰውን አእምሯዊና መንፈሳዊ ነገር የሚመለከት ነው:: በሦስት የምንከፍለው ከሆነ ‹‹ነፍስ›› ተብሎ የሚጠራው ‹‹መንፈስ›› በሚለው የሚተካ ሲሆን ‹‹ነፍስ›› የሚለው ቃል ደግሞ የሰውን አእምሯዊ ክፍል በመወከል የሚቆም ይሆናል::

አንዳንድ ጊዜ ስለ ሰው አእምሯዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች በምናስብበት ጊዜ ‹‹የሰው ልብ›› የሚለውን የተለየ ቃል እንጠቀማለን:: ይህንን የምናደርግበት ምክንያት ማስረዳት ቀላል ነው:: በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ አካላዊው ልብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ከመሆኑ የተነሣ እንደ ‹‹ፍቅር›› ‹‹እምነት›› ‹‹ታማኝነት›› ‹‹ደስታ›› ወዘተ... ስለ መሳሰሉ የሕይወት መገለጫዎች በምናወሳበት ወቅት በዚህ ቃል እንጠቀማለን:: በአንዳንድ ቋንቋዎች ለምሳሌ በአፍሪካ ውስጥ ‹‹ሕሊና›› የሚል ትርጉም ያለው ቃል ላይኖር ይችላል:: በመሆኑም ሕሊናን ስለሚመለከት ነገር በሚያወሱበት ወቅት ‹‹ልብ›› ወይም ‹‹የልብ አሳብ›› የሚሉትን ቃላትን ይጠቀማሉ::

## የሰውን ማንነት የሚገልጹ ሁለት አመለካከቶች

በዛሬው ዘመን አንድ እጅግ ተወዳጅ የሆነ አመለካከት አለ:: እርሱም መጥፎና ክፉ የሆኑ ነገሮች ሁሉ የሚመጡት

ከውጪ ነው ሚል ነው:: ለምሳሌ በተወሰኑ ጥቂት ሰዎች አማካይነት ወይም ‹‹በአካባቢው›› እና ‹‹በየመዋቅሮቹ›› ውስጥ የሚሰገሰጉት ሰዎች በማኅረሰቡ ውስጥ ከሚያሳድሩት መጥፎ ተጽዕኖና ይኸው ተጽዕኖ ሰው ወደ ተሣሣተ አቅጣጫ እንዲሄድ ከመገፋፋቱ ውጪ ሰው በራሱ መልካም ነው፤ መልካምነቱንም እንደጠበቀ ይኖራል ተብሎ ይታሰባል:: ኢየሱስ ግን ‹‹ከልብ ክፉ አሳብ÷ መግደል÷ ምንዝርነት÷ ዝሙት÷ መስረቅ÷ በውሸት መመስከር÷ ስድብ ይወጣልና›› (ማቴ. 15÷19-20) ማለት ፍጹም የተለየ ዕይታ እንዲኖረን ይናገረናል:: ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመላ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ሲሆን እንዲህም ተብሎ ተነግሮአል፤ ‹‹የሰው የልቡ አሳብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነው›› (ዘፍጥ. 8÷21)::

በእርግጥ እንደዚህ ዓይነቱን አመለካከትና ቃላት ብዙውን ጊዜ ከዕውቀትና ከልምድ እጥረት የተነሣ ሰዎች አይረዱትም፤ ወይም ደግሞ አግባብ ባልሆነ መንገድ ይተረጉሙታል:: የተጠቀሱት ቃላት ግባቸው ሁለት ነው:: አንደኛው የሰው ልጆችን መንፈሳዊ የጀርባ ታሪክ የሚዳስስ ነው። ለምሳሌ የራሳችን ረዳት አዳኝ መሆን አለመቻላችንና በተመሳሣይ ሁኔታም በራሳችን ኃይል ብቸኛ አዳኝ ወደ ሆነው ወደ ጌታችንና ወደ መድኃኒታችን ልንደርስ አለመቻላችን ነው:: በአንድ በኩል ይህ ሙሉ በሙሉ የሕግ ሥራ ነው:: እርሱም ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ‹‹የሞግዚትነትን›› ሥራ ያከናውናል (ገላ. 3÷24):: እንዲህ በሚባልበት ወቅት በአእምሯችን ውስጥ ሊቀመጥ የሚገባው ነገር እንደ ራሱ እንደ ክርስቶስ አሳብ ከሆነ አማኝ በሆኑና ባልሆኑ ሰዎችም ውስጥ ብዙ መልካም ነገሮች አሉ:: ለምሳሌ ያህል መልካምና ጽድቅ ስለ ሆኑ ነገሮች ያለው ግንዛቤ አንድ ማስረጃ ነው:: ስለሆነም ኢየሱስ በእርሱ የማያምኑ ሰዎችን ‹‹ራሳችሁ ደግሞ ጽድቅን የማትፈርዱ ስለ ምን ነው?›› ሉቃስ 12÷57፤ እንደዚሁም ‹‹ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ›› ማቴ. 7÷11 የሚለውን ቃል ሲናገራቸው እንመለከታለን::

እዚህ ላይ እየተነጋገርን ያለነው በክርስትና አስተምህሮ ውስጥ ስለሚገኝ መሠረታዊ እውነታ ነው:: ይህንን እውነታ መገንዘብ የሚያዳግተን ወይም ችላ ብለን የምናልፈው ከሆነ ብዙ ነገሮችን ከማጣታችንም ባሻገር በክርስቲያናዊ አስተምህሮ ውስጥ እምነትና ሥነ ምግባርን በሚመለከቱ ብዙ ጉዳዮች ራሳችንን አደጋ ላይ መጣላችንና ዋጋ መክፈላችን አይቀሬ ነው:: የመጀመሪያው መሠረታዊ እውነታው ኃጢአት ነው:: እነዚህ ቃላት በውድቀት ምክንያት የሰው ውስጣዊ ማንነቱ መበላሸቱን የሚያመለክቱ ናቸው (ዘፍጥረት 3)::

የውርስ ኃጢአት በሁላችንም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም ባሻገር እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ አብሮን ይኖራል:: ልንከላከለው ወይም ልንዋጋው የምንችል ቢሆንም በዚህ ሕይወት ውስጥ ሊደበቅም ሆነ ሊወገድ አይችልም:: ሊሸነፍ የሚችለው አማኝ በሆኑ ክርስቲያኖችና በተባረከው «የክርስቶስ ሞት» ብቻ ነው:: የሰው ልጆች ያለባቸው ጉስቁልና በመጀመሪያ በተፈጠሩበት ወቅት አብሯቸው የተፈጠረ የባሕርያቸው አንዱ ክፍል አልነበረም:: ይህ ወደዚህ ዓለም የመጣው ከፍጥረት በኋላ ነበር:: ለዚህ አባባል ማስረጃ የሚሆነን ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በመጀመሪያ እንደነበረውና በኋላም በተካታታይነት እንደታየው የሰውን ባሕርይ ተቀብሏል፣ ወስዷልም:: እርሱ ግን ኃጢአትን አላደረገም:: በውርስ ኃጢአት ላይ ምንም ዓይነት ተሳትፎ አላደረገም:: እርሱ «የሰው ልጅ» ከሚለው ፍቺ አንጻር «የሰው ልጅ» በመሆኑ ኃጢአተኛ ሊሆን አይችልም (ሮሜ 8÷3፤ ፊልጵ. 2÷6):: በዚህም ምክንያት ሰውም ኃጢአት የሌለበት ሰብዓዊ ፍጡር ሆኖ የተፈጠረ ሲሆን ኃጢአት የመጀመሪያ ኃጢአተኞች በሆኑ ሰዎች አማካይነት ሰውን ሁሉ ለኃጢአት ዳረገው:: ከላይ በተጠቀሱት አባባሎች መሠረት ኃጢአተኞች መሆናችንን÷የመዳን ዕድል ያለን መሆኑንና ዳግም ወደ ራሱ ሊመልሰን በመጣው ጌታ አማካይነት የታደሰ ሕይወት ሊኖረን የሚችል ስለ መሆኑ አሳይተናል::

ከሰው ልጅ ውድቀት በኋላ አንዳንድ ክፉ የሆኑ ውጤቶች

አሉ:: ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ሰው ትክክልና ስሕተት የሆኑ ነገሮችን ለይቶ ከማወቅ አንጻር ጉዳት ላይ መውደቁና ለግራ መጋበት መዳረት ነው:: ይህም ሆኖ አሁንም ከፍተኛ የሆነ ዕውቀትና ሥልጣን አለው:: ዓለማዊ በሆኑና እንደ ፍልስፍና÷ አገር አመራር÷ ንግድን ወዘተ... በመሳሰሉ ነገሮች ላይ ግሩም በሆነ ሁኔታ ሥራውን ሊያከናውን ከመቻሉም ሌላ እንደ ደረሰበት የእምነት ደረጃም «መንፈሳዊ ነገሮች» እና «መልካም ነገሮችን» የማከናወን ጥሩ ችሎታ አለው:: በኋላም ቀጣይ ነገሮች የሚተውለት ከሆነ በራሱ መንገድ የሚገነዘባቸው ይሆናል:: በአጠቃላይ ሲታይ ግን ከእግዚአብሔር ጋር ሙሉ የሆነ ግንኙነት ማድረግ ስለማይችል ይሳሳታል:: ከመጀመሪያውኑ ለእግዚአብሔር ካለው ጥላቻ የተነሳ በእግዚአብሔር ላይ ጥርጣሬ ስለሚኖረው «መንፈሳዊ ጉዳዮችን» እንኳ በሚመለከት የእግዚአብሔርን አሠራር ለመቃወም በመጣር የራሱን ዓላማ የሚፈጽምበትን መንገድ ይዞ ይጓዛል:: ሰው በራሱ እግዚአብሔርን የሚወድበት ወይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግበት ነፃነት የለውም:: አድርጌአለሁ ብሎ ሊያስብ ወይም ሊናገር የሚችል ቢሆንም እውነቱ ግን ተቃራኒው ነው:: ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ ሰው ውስጣዊ አካላቱ ማለትም ልቡ÷ ነፍሱና አእምሮው በከፍተኛ ደረጃ ጉዳት የደረሰባቸው መሆናቸው ነው:: ትክክል ያልሆነ ድርጊት ፈጽሟል፤ኃጢአተኛም ነው:: ሆኖም ዳግም መጠቀስ የሚገባቸው ቃላት አሉ:: እነዚህም ቃላት ሰው ከእግአብሔር ጋር በሚኖረው ግኑኝነት ተግባራዊ ሊሆኑ መቻላቸው ነው:: ሰው ዓለማዊ በሆኑ ጉዳዮች በምድራዊ ማኅበረሰብ ውስጥ የተለየ ስፍራ ሊኖረውና መልካም የሆኑ ታላላቅ ነገሮችን ለማከናወን የሚችል ቢሆንም በእግዚአብሔር ፊት በሚቆምበት ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ ባለው እምነት አማካይነት የመቅረብ ዕድል ካልተሰጠው ኃጢአተኛ ነው::

## ክፉ የሆነ መንግሥታዊ አመራር

ሁሉም ሰዎችና ግለሰቦች በውድቀት ምክንያት ክፉኛ

ተጎድተዋል:: ማኅበረ ምእመናን÷ አብያተ ክርስቲያናት÷ የተለያዩ ማኅበረ ሰቦችና መንግሥታትም በዚህ ብልሽትና ኪሳራ ምክንያት ይሰቃያሉ:: በዓለምም ሆነ በሰው ልጆች ውስጥ መልካም ነገር የሚገኝ መሆኑ እውነት ቢሆንም ብዙ ክፉ የሆኑ ነገሮችም መኖራቸውን መካድ አንችልም:: ይህንን ነገር በአግባቡ በመለየትና በእነርሱ አባባል «ሥርዓት ለማስያዝ» መሞከሩ ለብዙ ሰዎች ፈታኝ ሲሆን፤ ካላቸው ደካማ አስተሳሰብ የተነሳ ብዙ ጉዳት እንዲደርስ ከማድረጋቸውም ባሻገር መልካም የሆነውንም ነገር ሲያበላሹ ይታያል:: ስለሆነም ኢየሱስ ይህ «የሥርዓት ዕጦት» «እስከ መከር አብረው ይደጉ፤ በመከር ጊዜም አጫጆቹን እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ፤ በእሳትም ለማቃጠል በየነዶው እሰሩ፤ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ» (ማቴ. 13÷30) ይላል::

ይህ የክርስቲያን አስተምህሮ በተለያዩ ሃይማኖታዊና የፍልስፍና አስተሳሰቦች ዘንድ ተቀባይነትን አላገኘም:: በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ለምሳሌ በክፋት መኖርና በሰው ልጆች መካከል ስላሉ አንዳንድ ሕፀፆች የመግባባት ደረጃ ላይ ቢደርሱም የውርስ ኃጢአትንና የሰው ልጆች ውድቀትን አስመልክቶ ግን አጥብቀው ይቃወማሉ:: እነዚህ ነገሮች ሥነ ምግባርን ከመረዳትና እርሱንም አስመልክቶ ከሌሎች ክፍሎች ጋር ለመተባበር ከፍተኛ እንቅፋትን ይፈጥራል:: ምንም እንኳ ይህንን ችግር አስመልክቶ (በምዕራፍ 5) ላይ የምንነጋገርበት ጉዳይ ቢሆንም በዚህ ስፍራ ከዚህ በታች በሚገለጸው መልኩ የሚቀርብ ይሆናል:: ክርስቲያኖች የተለየ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎችን ለምሳሌ፡- ግዑዝ ነገሮች ነፍስ አላቸው ብለው የሚያምኑትንና እግዚአብሔር የለም ብለው የሚያምኑ ሰዎችን ወዘተ... ሊያስተናግዱ የሚገባው እንዴት ነው? በክርስትና አስተምህሮ መሠረት ከፍጥረታቸው የተነሣ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር በመሆናቸው የየትኛውም ሃይማኖት ወይም እምነት ተከታዮች ቢሆኑም ክርስቲያኖች ሁሉንም ማየት የሚገባቸው እንደ ወንድምና እንደ እኅት ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ሰዎች ሁሉ ትክክልና ስሕተት ስለ ሆነው ነገር የተወሰነ

ዕውቀት ያላቸው በመሆኑ ሕሊናችን በሚነግረን መሠረት ሥነ ምግባርን በሚመለከት ጉዳይ ከእነርሱ ጋር ተባብሮ መሥራት ይቻላል:: ይህም አስፈላጊ ነው:: በሦስተኛ ደረጃ በሰው ልጅ ውድቀት ምክንያትና ከደኅንነት አስፈላጊነት የተነሳ ምን ጊዜም ቢሆን ሁለቱን የሚከፍል መሥመር ይኖራል:: በክርስቶስ ውስጥ የተደረገውን መገለጥና ደኅንነት ብዙዎቹ ክደውታል:: በዚህ ነጥብ ላይ መግባባትና መተባበር አዳጋች ቢሆንም በክርስቲያኖች ዘንድ ሰዎች ሁሉ ስፍራ ሊሰጣቸው÷ ሊከበሩና ሊፈቀሩ ይገባቸዋል:: ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ታላቅ የሆነ ዕውቀት ያላቸው በመሆኑ ክርስቲያኖች ለሰዎች ከፍተኛ የሆነ አክብሮትና ፍቅር ሊያሳዩ ይገባል (1 ዮሐ. 4÷19):: በአራተኛ ደረጃ በሁለቱ አመራሮች መካከል ከፍተኛ የሆነ ልዩነት አለ:: በአንድ በኩል በክርስቶስ የሚገለጥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር መንግሥት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሰይጣን÷ በፈተናዎችና በኃጢአት የሚወከለው የክፋት መንግሥት አለ:: ከዚህ የተነሣ ክርስቲያኖች ሁሉ ‹‹ከዓለም›› ከሚመነጨው ትልቅ አደጋ ራሳቸውን መጠበቅ ይኖርባቸዋል:: ዓለም የተሰኘው ቃል ዓለምን÷ ጠፈርን ይህንን ወይም ያንን ሰው ለማለት ሣይሆን ‹‹የዚችን ዓለም ጥበብ›› ማለትም ‹‹በእግዚአብሔር ላይ መዘበትን›› ለማመልከት የዋለ ቃል ነው (1 ቆሮ. 1÷19):: ከዚህ አንጻር የክርስቲያኖች ጦርነት መሆን የሚኖርበት ከሰዎች ወይም በዓለም ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ ነገሮች ጋር ሳይሆን ከራሳቸው ከክፉ መናፍስትና በራሳቸው ውስጥ ካለው ክፉ ምኞታቸው ጋር ነው:: ‹‹ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው›› (1 ዮሐ. 5÷4)::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ሁሉ በትምህርቶቹ ውስጥ ቀደም ብሎ አሳውቆናል:: ዓለም ሁሉ የእርሱና የእኛ ፍቅር መገለጫ ቦታ እንደሆነች ያመለክታል:: በተመሣሣይ ሁኔታም በወደቀው ዓለምና አዲስ ፍጥረት በመሆን ወደ ልጁ መንግሥት በፈለሱት ሰዎች መካከል ስላለው ልዩነት ይናገራል:: ወደ ልጁ መንግሥት የፈለሱት ምንም እንኳ በዓለም ውስጥ ያሉ ቢሆኑም

በእግዚአብሔር መንግሥትና በተቀደሰችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተካፋይነት አላቸው:: ምንም እንኳ የውጪው ዓለም አንድ ቢሆንም ችላ ተብሎ ሊታለፍ የማይችል ልዩነት አለ:: ‹‹ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር አልላከውምና...ብርሃንም ወደ ዓለም ስለመጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ ፍርዱ ይህ ነው›› (ዮሐ. 3÷17-19):: ይህ ሂደትና ክፍፍል ዘወትር በእኛ መካከል ተግባራዊ ሲሆን እንመለከተዋለን:: ሐዋርያው ጳውሎስ በ2 ጢሞ. 4÷10 ላይ ዴማስን አስመልክቶ ‹‹ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና›› ብሎ የተናገረው ቃል ባለንበት ዘመንም ከዚህ ባልተናነሰ ሁኔታ ብዙ ነገሮች እየተተገበሩ መሆናቸውን መናገር ይቻላል:: አብዛኛውን ጊዜ እየተከናወኑ ያሉትን ነገሮች በምናስተውልበት ጊዜ ብዙ ሰዎች የሚያደርጉትን ነገር እኛ ለማድረግ ሲሳነን እናገኘዋለን:: ከዚህ ዓለም በስተጀርባ ላሉት ‹‹አደጋ›› እና ‹‹ፌዝ›› ለሚሰኙ ቃላት አሳማኝ ያልሆነ ምክንያት መስጠት ይፈልጋሉ:: ከዚህም አልፈው ‹‹ክርስቲያን ያልሆነ›› ‹‹ፍቅር የጎደለው›› ወይም ‹‹ፈሪሣዊነት›› የተሰኙ ቃላትን ይጠቀማሉ:: በግላችን ምንም ብናስብ ወይም ብንናገር ስለ ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ የክርስቶስና የሐዋርያቱ ቃሎች ናቸው::

## እግዚአብሔር ለዓለም ያለው ፍቅር

‹‹እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና›› (ዮሐ. 3÷16) ተብሎ ተጽፎአልና በኃጢአት የወደቀችው ዓለም እንኳ በእግዚአብሔር የምትወደድ ነች:: ስለ ሆነም ቤተ ክርስቲያንና ክርስቲያኖች የተጠሩት ይህንን ፍቅር ለዚች ዓለም ለማካፈል ነው:: ይህ ማለት ግን ቤተ ክርስቲያን ወይም ክርስቲያኖች ከወደቀው ዓለም ጋር ራሳቸውን ማላመድ አለባቸው ማለት አይደለም:: ከእነዚህ አባባሎች ‹‹ዓለም›› ስለሚለው ቃል ሦስት ነገሮችን መገንዘብ እንችላለን:: በቃሉ ውስጥ የሚገኘው አንደኛው አሳብ ‹‹ዓለማትን›› ማለትም የተፈጠረውን ዓለም በአጠቃላይ የሚያመለክት ነው:: ከዚህ አንጻር

ቃሉ ምንም ዓይነት ‹‹የወደቀው ዓለም›› ወይም ‹‹ኃጢአተኝነት›› የሚል ሁለተኛ ትርጉም አይሰጥም:: በቃሉ ውስጥ የሚገኘው ሁለተኛው አሳብ ምድርን፤ ሁሉንም ክፍለ ዓለማት፤ በአንዳንድ ሁኔታዎችም በውስጧ የሚኖሩትንና የሚከሰቱትን ክስተቶች ነው:: በዚህ ረገድ የምንናገረው ስለ መልክዓ ምድራዊ÷ ታሪካዊ÷ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሁኔታዎችና እውነታዎችን ነው:: እዚህ ላይም ቢሆን ስለ ውድቀትና ስለ ኃጢአት የሚነሣም ነገር የለም:: በሦስተኛው የቃሉ አሳብ ላይ ብቻ ነው ‹‹ዓለምን›› በተመለከተ ስለ ውድቀት ማሰብ የምንጀምረው:: ሁሉም ሰው ለውድቀት የተዳረገ ነው፤ ኃጢአተኛ ነው፤ የጉስቁልናም ተጠቂ ነው:: እዚህ ላይ ነው እግዚአብሔር ለዓለም ያለው ፍቅር የሚገለጸው:: ለደህነነታቸው ሲል ልጁን አሳልፎ እስከ መስጠት ድረስ እግዚአብሔር የወደቀችውን ዓለም ማለትም የወደቀውን የሰውን ዘር ሁሉ ወዷል:: ከዚሁ ከሦስተኛው አሳብ ጋር ተግባራዊ የሚሆን ሌላ ዓይነት አሳብም አለ:: እግዚአብሔር ለውድቀቱ መንስዔ የሆነውን መንፈስም ሆነ ከዚህ ጆርባ የነበረውንም ጠላት አይወድም:: ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል÷ ‹‹ዓለምም በመላው በክፉው እንደተያዘ እናውቃለንና›› ‹‹ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ ... ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም›› ‹‹ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው?›› (1 ዮሐ. 5÷19፤ 2÷15፤ 5÷5)::

በሚቀጥሉት ምዕራፎች በሚገኙት በእነዚሁ መዘርዝሮች ውስጥ ይህንን ሦስት የተለያየ ማብራሪያ ማጤኑ አስፈላጊ ይሆናል:: ይህ ከክርስትና የሥነ ምግባር ትምህርቶች ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው:: በዚህ መንገድ ብቻ ሲሆን ነው ሁለቱን የክርስትና አስተምህሮዎችን በሚዛናዊነት መረዳት የሚቻለው:: ይህም ማለት እግዚአብሔር ‹‹የሰማይና የምድር›› በአጠቃላይም የዓለም ሁሉ ፈጣሪ መሆኑ እና ‹‹ከዚህ ዓለም ባይሆኑም›› (ዮሐ. 17÷14-17) የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የሆኑቱ በዚህ ዓለም ውስጥ መኖር ይችላሉ፤ ይኖርባቸዋልም ማለት ነው::

## የ ‹‹ነፃ ምርጫ›› ፈቃድ አለ?

ከሰው ልጅ ውድቀት በኋላ የሰው ዘር የፈለገውን ለመምረጥና መልካም የሆነውን ነገር የማድረግ ሙሉ ነፃነት የለውም:: ለእግዚአብሔር ሊኖረው ከሚችለው ፍቅርና በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ከሚሰጠው ጽድቅ አንጻር ሰው ፈጽሞ ነፃነት የለውም:: ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ይህ አሳብ የማያስደስታቸው በመሆኑና ምላሽም ለመስጠት ነፃነት እንደላቸው አጥብቀው የሚከራከሩ በመሆኑ ይህ ዐረፍተ ነገር ማብራሪያ ሊሰጥበት ይገባል:: ከዚህ በታች የሠፈሩትን ዓይነት ምሳሌዎች በመስጠትም የተቃውሞአቸውን እውነትነት ለማረጋገጥ ይፈልጋሉ:: ‹‹እኔ እዚህ ወይም እዚያ ለመሄድ ብፈልግ አደርገዋለሁ፤ አንድ ንግድ ለመጀመር ብፈልግ÷ ለመስረቅ ወይም ዝሙት ለመፈጸም ብፈልግ ወይም መልካም የሆነ ሥራ እንኳ ለመሥራት ብፈልግ ተግባራዊ አደርገዋለሁ:: ይህንን ከማድረግ ሰው ቀርቶ እግዚአብሔር እንኳ ሊከለክለኝ አይችልም›› ብለው ያስባሉ:: እነዚህ ሰዎች ሁለት ጥያቄዎችን የሚያደባልቁ ከመሆናቸውም ባሻገር ዋናውን ችግር ባለመንካታቸው የተሣሣቱ ስለመሆናቸው በራሳቸው አንደበት ምስክርነት ይሰጣሉ:: የራሳቸውን ውሳኔ መስጠትን በተመለከተ ያቀረቡት የመጀመሪያው ክፍል ትክክል ቢሆንም ውሳኔያቸውን ተግባራዊ ስለሚያደርጉበት ሂደት የተናገሩት ግን ፈጽሞ ስሕተት ነው:: በእርግጥ ሊመኙና አንድን ነገር ለመፈጸም ውሳኔ ሊያሳልፉ ይችላሉ:: ይህ ዓይነት አስተሳሰብና ዕቅድ ገደብ ላይኖረው ይችላል:: ፈጽሞ የተለየ ችግር የሚሆነው ግን፡- ሰዎች ካሰቡትና ካቀዱት አንጻር ስኬታማ ሆነዋል ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው:: ምናልባት በጥቂት ነገሮች ይሁን እንጂ በሁሉም ነገር ስኬታማ ሊሆኑ አይችሉም:: ጥቂት ምሳሌዎች ለዚህ ማስረጃ ሊሆኑ ይችላሉ:: ያቀዱትን ነገር ተግባራዊ ከማድረጋቸው በፊት ሊረበሹ ወይም አንድ ነገር ጣልቃ ሊገባባቸው ይችላል:: በዕቅዳቸው ያሠፈሩትን ነገር ተግባራዊ ለማድረግ በሚሯሯጡበት ወቅት ስርቆት ወይም ዝሙት ሊገጥማቸው ወይም ምናልባት አንድ ወዳጃቸውን ሊያገኙና ወዲት እየሄዱ እንዳሉ ለእርሱ ቃል የማይተነፍሱ

ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ያሰቡትን ነገር ሳይፈጽሙ አብረው በእግር ተጉዘው ወደ ቤታቸው ሊመለሱ ይችላሉ:: ታዲያ በዚህ ሁኔታ ‹‹የፈለጉትን ነገር ተግባራዊ›› አድርገዋል ለ.ባል ይቻላል? በሌላ ሰው ሁኔታ ደግሞ ብንመለከት ያ ሰው የሆነ ነገር ለማከናወን ዕቅድ ካወጣ በኋላ ያቀደውን ሥራ ማከናወን ከመጀመሩ በፊት ይታመማል፤ እጁን ወይም እግሩን ሊሰበር ይችላል:: ይህ ሁሉ የሚያሳየን ዓለማዊ በሆኑ ጉዳዮች እንኳ ያቀድነውን ነገር ሁሉ ለማከናወን እንቅፋት ሊፈጠርብን የሚችል መሆኑን ነው:: ይህም በዓለማዊ አስተሳሰብ እንኳ ሁለት ነገሮችን አደባልቆ መመልከት ተገቢ አለመሆኑን የሚያሳየን ሲሆን እነርሱም የማሰብና የማቀድ ነፃነት በአንድ በኩል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተግባራዊ የማድረግ ነፃነት ናቸው:: ዕቅዶችን ተግባራዊ የማድረጉ ጉዳይ በብዙ መልኩ እንቅፋት ሊገጥመው ይችላል::

በክርስትና አስተምህሮ ውስጥ ትልቅ ችግር ስለሆነው ‹‹ነፃ ምርጫ›› የሚመለከተው ጉዳይ እዚህ ስፍራ ላይ የጠቀስናቸውን ችግሮች ፈጽሞ አይመለከትም:: በመሆኑም ብዙ ጊዜ ለዚህ የሚሰጠው ‹‹ምላሽ›› ፈጽሞ መልስ የለም የሚል ነው:: ከክርስትና ዕይታ አንጻር ማንም ሰው የማሰብ ወይም የማቀድ ነፃነትን ከዓለማዊ ነገሮች ጋር አነጻጽሮት አያውቅም:: ከዚህ ይልቅ ‹‹ነፃ ምርጫ›› በሚሉት ቃላት ውስጥ ያለው ችግር ከዚህ በታች ከተጠቀሰው አሳብ ጋር ይያያዛል:: የወደቀው ሰው በራሱ ፈቃድ እግዚአብሔርን ለማግኘት መሞከር፤ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ማለት÷ ልቡን መስወጥ÷ እግዚአብሔርን ሊወድና በእግዚአብሔር ፊት ጽድቅና መልካም የሆነውን ማድረግ ይችላልን? ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ለዚህ የሚሰጠው ክርስቲያናዊ መልስ ያለጥርጥር አይችልም የሚል ነው::

ይህንን በአእምሯችን መያዙ አስፈላጊ ነው:: ይህ ካልሆነ ግን ‹‹ዓለም›› እና ‹‹የነፃ ፈቃድ ምርጫ›› ወዘተ... የሚሉት ቃላት ብዥታ ያለባቸው ወይም ትርጉም የለሽ ይሆኑብናል::

ባለንና በሌለን ነፃነት መካከል ያለውን ልዩነት በሚመለከት ቅዱስ አውግስጢኖስ በአግባቡ ማብራሪያ ሰጥቶበታል:: ‹‹ምክንያታዊ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ሁሉም ሰው በነፃነት የመወሰን መብት አለው:: እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ጉዳዮች ከሆነ ግን ለመጀመርም ሆነ ‹‹ማንኛውንም ነገር›› ወደ ግቡ ማድረስ ከእግዚአብሔር ዕርዳታ ውጪ ሊከናወን አይችልም:: መልካምም ሆኑ ክፉ ሥራዎችን ብንሠራ የጊዜ ገደቡ በዚች ዓለም ብቻ ነው›› (የኦውግስበርግ ኑዛዜ 18)::

እንግዲህ ተራ የሆኑ ዜጎች ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ስለ ራሳቸው አሁን ምን ያስባሉ? አለ ጥርጥር እንዲህ ብለው ነው የሚያስቡት:- ‹‹ሥራዬንም ሆነ ንግዴን በፈለግሁት ጊዜና ስፍራ ለማከናወን የምችል ሲሆን ከእግዚአብሔርም ጋር በተመሳሳይ መልኩ በፈለግሁት መንገድ ግንኙነት ለመፍጠር እችላለሁ:: ልወደው ወይም ልተወው÷ ላምነው ወይም ልክደው እችላለሁ:: ሁሉንም የምወስነው እኔው ራሴ ነኝ::›› ብዙ ሰዎች በዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ላይ  ከዚህ በታች የተጠቀሰውን ተጨማሪ ነገር ለማከል ይፈልጋሉ÷ ‹‹መሐሪና በፍቅር የተሞላ እንደሆነ የተነገረን በመሆኑ እኔ ጉልበት ወይም ችሎታ በሚጎድለኝ ወቅት እግዚአብሔር በሚያስፈልገኝ ሁሉ ይሞላብኛል›› ይላሉ:: ይህ ሲጀመርም ለአሳቡ ደርዝ ያልተበጀለት ነገር ነው:: በሰዎች መካከል የሚኖረውን መንፈሳዊ ዕውነታና እግዚአብሔር ራሱ በቃሉ የተናገረንን ነገር ፈጽሞ ስፍራ የሚያሳጣና የሚክድ ነው::

ፍጥረታትን በመመልከት ብቻ ስለ እግዚአብሔር በቂ ዕውቀት ልናገኝ አንችልም:: ስለ ውድቀት÷ ስለ ኃጢአታችን ወይም ስለ ድነት መንገድ ከእነዚህ ነገሮች ብዙም ልንማር አንችልም:: ወይም ደግሞ እነዚህ የተፈጠሩት ፍጥረታት አዳኙ ማን እንደሆነ ወይም ወደ እርሱ ስለሚመራን መንፈስ ቅዱስ ምንም ነገር ሊነግሩን አይችሉም:: ሰዎች ሁሉ በተፈጠረው ዓለም ውስጥ ይኖራሉ፤ ፈጣሪን በሚመለከት እጅግ አነስተኛ የሆነ ዕውቀት ሊኖራቸው የሚችል ቢሆንም ወደ እርሱ እንዴት

መምጣትና መኖር እንዳለባቸው ግን ከእነዚህ ፍጥረታት መልስን ሊያገኙ አይችሉም:: ከሕሀሊናቸው ጋር የተያያዘው ጉዳይም ቢሆን ከዚህ ጋር ተመሣሣይነት አለው:: ትክክል የሆነውንና ትክክል ያልሆነውን ነገር እንዲሁም ምን ማድረግ እንደሚገባቸውና ምን ማድረግ እንደማይገባቸው ‹‹በልባቸው›› ውስጥ የሚናገራቸው ድምፅ እንዳለ ይገነዘቡ ይሆናል:: እዚህ ደረጃ ድረስ መልካም ቢሆንም ድምፁ ግን ትክክል የሆነው ነገር እንዴት ሊያገኙት እንደሚችሉ አይነግራቸውም። ከዚህ የተነሳ ሰው አዲስ የሆነ ነገርን ማለትም የበለጠ ግልጽና አሳማኝ የሆነ ነገርን ይራባል:: ይህንን የሚያገኙትና ንብረታቸው የሚያደርጉት እንዴት ነው?

እዚህ ላይ ውድቀቱን ለማካካስ እግዚአብሔር የሠራው ነገር ምንድነው? የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም:: መልሱ እግዚአብሔር መንገድን አዘጋጅቷል የሚል ይሆናል:: ይህም መንገድ የተፈጠረ ነገር አልነበረም:: ትክክለኛ የሚሆነው አባባል፡- ተወልዶ ነበር፤ የተወለደው ግን ዘለዓማዊነት ያለው ነው የሚል ነው:: እግዚአብሔር የወደቀው የሰው ልጅ ዘለዓማዊ ይሆን ዘንድ ያዘጋጀለት መንገድ ራሱን መንገድ÷ እውነትና ሕይወት ብሎ የሚጠራውን ነው (ዮሐ. 1÷14፤ 14÷6):: እኛም ‹‹ብቸኛው የእግዚአብሔር ልጅ እርሱ እንደሆነ፤ ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት ከአባቱ የተገኘ ... ለእኛ ለሰዎችና ለድነታችን ሲል ከሰማይ የወረደ›› (የኒቂያ አጭር የእምነት መግለጫ) ብለን ስለ እርሱ በአፋችን እንመሰክራለን:: እንግዲያውስ በዚህም መንገድ ብቻ ማለትም በዚህ ድነት ውስጥ ብቻ ነው አዲስ ሰው ለመሆን ዳግም ልንወለድ፤ ልንለወጥና ልንታደስ የምንችለው (ገላ. 6÷15):: በዚህ መንገድ ብቻ ነው እንደ ክርስቲያኖች መኖር የምንችለው:: በእነዚህ ቃላት ቁልፍ የሆኑ ዝርዝር አርእስቶችን አስፍረናል:: እነርሱም÷ በክርስትና እምነት ውስጥ ለመኖር እና እንደ ክርስቲያን ሥነ ምግባር ለመመላለስ የሚሉ ናቸው::

# ምዕራፍ 2

# የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ሥራ

እኛ ስለ ራሳችን ስንናገር መንገድ ነን ማለት አንችልም:: እንዲህ ብለን ብንናገር ንግግራችን ትርጉም የማይሰጥ ይሆናል:: በተጨማሪም በዘመናት ሁሉ ለነበሩት ሰዎች መንገድ ነን ብንል አስከፊነቱ ከዚህም የባሰ ይሆናል:: በዚህ ንጽጽር በዮሐንስ ወንጌል 14÷6 ላይ ‹‹እኔ መንገድ ነኝ›› ብሎ ስለ ራሱ በሚናገርበት ወቅት ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ልንገነዘብ እንችላለን:: ‹‹... እውነትም÷ ሕይወትም›› የሚሉትን ቃላት በመጨመር ስለ ሁኔታው የሚናገርበትም መንገድ ተራ አልነበረም:: ይህ የሚያሳየን በእርሱ በኩል ካልሆነ ማንም ሰው ወደ አባቱ ሊመጣ የማይችል መሆኑን ነው:: ይህ እርሱ ካደረጋቸው ከሌሎች ንግግሮችም ጋር የሚጋጭ አይደለም:: ለምሳሌ እርሱና አባቱ አንድ ስለ መሆናቸውና ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በአባቱ ክብር ውስጥ ይኖር እንደ ነበረ ይናገራል (ዮሐ. 10÷30፤ 17÷5)::

የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነትና ታላቅነት የሚያሳዩ ብዙ ቃላትና ስያሜዎች አሉ:: ቃል የሚል ስም አለው:: በዚህ ቃል በኩል በገንዘብ የማይለካ ውድ የሆነ ራእይን ከእግዚአብሔር ከመቀበላችንም ባሻገር ከውድቀት በኋላ ከእርሱ ጋር በእጅጉ ቅርርብ እንዲኖረን አስችሎናል:: ‹‹ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን፤ ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን›› (1 ዮሐ. 1÷2):: በዚህ ስፍራ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በሁለት መንገዶች ማለትም እውነተኛ አምላክና እውነተኛ ሰው ሆኖ ወደ እኛ ስለ መምጣቱ ግልጽ ይሆንልናል:: እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚል ነው:: ይህም ቢሆን ለክርስትና ሥነ ምግባር ትልቅ ጠቀሜታ አለው:: ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ የሚሆንልን ከሆነና በዚህ ዓለምም የሚያግዘን ከሆነ ትክክልና ፍጹም በሆነ መልኩ እርሱ ሰው መሆን ይኖርበታል:: እንደ

እኛው ሰው ባይሆን ኖሮ ስለ እርሱ ለመረዳትና በመንገዱ ከእርሱ ጋር ለመጓዝ ያዳግተን ነበር:: በሌላም በኩል ይህ የወደቀው ዓለም ከመሆኑ የተነሣ ሰዎች ከኃጢአትና ከሞት ለመዳን አዳኝ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑና ዓለምን ሁሉ ሊያድን የሚችለው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ እውነተኛው አምላክም መሆን ነበረበት::

በሚቀጥሉት የክርስትና ሥነ ምግባር መዘርዝሮች በአብዛኛው አስተምህሮንና እምነትን ከምንተነትንበት አካሄድ ወጣ ያሉ ይሆናሉ:: ሆኖም በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውስጥ ተፈላጊ የሆኑ እንደ እምነት ያሉ ጉዳዮች የሚዳሰሱባቸው ይሆናሉ:: በአጠቃላይ ክርስቲያናዊ አስተምህሮን በተመለከተ ሁለት ነጥቦች ልብ ሊባሉ ይገባል:: የመጀመሪያው ነጥብ ክርስቲያን በሆነ ሰው ውስጥ ምን ጊዜም ቢሆን እምነት ከክርስትና ሕይወት ጋር በአንድነት የሚጓዝ ነገር መሆኑ ነው:: ማለትም ሥነ ምግባርም ሆነ የዚህ ሌላኛው ገጽታም ቢሆን ማለት ነው:: ሁለተኛው ነጥብ በክርስቶስ ማመንና እርሱንም መከተል ሙሉ በሙሉ የሚደገፉት በመጽደቅና በጸጋ ላይ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቃችን ነው:: ይህም ማለት ክርስቲያናዊ ለሆነው ኅብረት ሁሉ ምክንያቱና መሠረቱ እርሱ ነው ማለት ነው:: ይህ ኅብረት ምን ጊዜም ቢሆን ሁለት ጎኖች አሉት:: እነርሱም ከክርስቶስና በእርሱ ከሚያምኑቱ ጋር የሚኖረን ኅብረት ናቸው::

ስለ ሆነም በእግዚአብሔር ላይ ያለን እምነትና ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የሚኖረን ግንኙነቶች ሁሉ ከክርስቶስ ጋር የተያያዙ ናቸው:: ከዚህ የተነሳ እርሱ የተለያዩ ስሞች እንዲኖሩት መደረጉና ሥራውና አስፈላጊነቱም ከተለያዩ አቅጣጫዎች እንዲታይ መደረጉ አግባብነት አለው:: ከዚህ አንጻር ኢየሱስ ታላቅ መምህርና ታላቅ ምሳሌ በመሆኑ በሕይወታችን ውስጥ ልንከተለው የሚገባን ትክክለኛ ተምሳሌት እንደሆነ ልንማር እንችላለን:: እንደ አስተማሪነቱ ከነቢያት ሁሉ ይልቃል፤ ‹‹ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ›› እርሱ ነው (ዮሐ. 6÷14):: በዘመናት ሁሉ ይህ ነቢይና አስተማሪ ያስፈገናል:: ሆኖም የምኖረን

ትምህርቱ ብቻ ከሆነ ለውድቀት የምንዳረግና በብዙ መንገዶች የምንስት ሆነን እንገኛለን:: አሁን ግን ተምሳሌት ሆኖ የቀረበልን በመሆኑና የእርሱን ዓይነት የአኗኗር ዘይቤ እንድንኖር መንገዱን ያሳየን በመሆኑ ስሕተት ውስጥ ልንገባ ከምንችልባቸው ብዙ ነገሮች ለመዳን ይረዳናል:: በሌላም በኩል እንደዚህ ዓይነት ምሳሌነት በቂ የማይሆንበት ሁኔታም አለ:: አንዳንድ ሰዎች በቂ ነው ብለው ስለሚያስቡ በሕይወታቸው ልክ እንደ ኢየሱስ መኖር እንችላለን ብለው የሚያምኑ በውጫዊ ሁኔታቸው ሣይቀር እርሱ የኖረበትን ሕይወት ለመኮረጅ የሚጥሩ ሰዎች ይኖራሉ:: በብዙ ምክንያት እንደዚህ ዓይነት አስተሳሰብ የተሣሣተ አመለካከት እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባናል:: መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ዓይነት መንገድ ብንጓዝ ውድቀት የማይቀርልን መሆኑን ይናገራል:: ኢየሱስ ኃጢአተኛ አልነበረም፤ እኛ ግን ነን:: እርሱ አዳኝ ነው፤ እኛ ግን አዳኝ የሚያስፈልገን ነን:: ትልቅ ልዩነት የሚፈጥረውም ይህ ነው::

## አማኞችና ኢ. አማኞች

አማኝ የሆኑ ክርስቲያኖችና አማኝ ያልሆኑ ሰዎች ፈጽሞ ሊስማሙ የማይችሉበት ነጥብ አለ:: አማኝ ያልሆኑ ሰዎች በብዙ መልኩ ማለት ይቻላል የኢየሱስን የሥነ ምግባር ትምህርት እንደሚወዱት ከዚያም አልፎ እንደሚያፈቅሩት ከመናገራቸውም ባሻገር የሥነ ምግባር አስተማሪና ምሳሌአቸው መሆኑንና እርሱንም ለመከተል ዝግጁ እንደሆኑ ይናገራሉ:: ክርስቲያኖች ግን እነዚህ ወገኖች ኢየሱስ ክርስቶስን በከፊል ብቻ መከተላቸውን አይቀበሉትም። ምንያቱም የነዚህ ወገኖች አመለካከት ለክርስቲያኖች ኢየሱስን ወደ ሥነ ምግባር አስተማሪነት ብቻ ዝቅ የሚያደርግ ይሆንባቸዋል። የአብ ልጅ መሆኑንና የዓለም አዳኝነት ሥልጣኑን እንደ መካድ ይቆጥሩታል::

በተመሣሣይ ሁኔታ አማኞች ያልሆኑ ብዙ ሰዎች ከእርሱ የተነሳ እጅግ ብዙ ነገር ስለ ማግኘታቸው ክርስቲያኖች

ከፍተኛ ዕውቅና ይሰጣሉ:: በተጨማሪም የማያምኑ ብዙ ሰዎች ከኢየሱስ ክርስቶስ ያገኙት ብዙ ግንዛቤ መኖሩን ክርስቲያኖች ይቀበላሉ:: በክርስትና ትምህርት ውስጥ ኢየሱስን ለመምሰል ደቀ መዝሙርነትና መቀደስ አስፈላጊ ነገሮች ሆነው ይገኛሉ:: በተለይ የክርስትና እምነትና ክርስቲያን ተብሎ ለመጠራት መመዘኛው ይኸው ነው ብለን የምናስብ ከሆነ አመለካከታችን የተዛባ ይሆናል:: ይህን ያህል ስሕተት ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ምንድነው? ስሕተት ሊሆን የሚችልበት ምክንያት ክፋት በውጪ ከሚደረግብን ተጽዕኖ ብቻ ሳይሆን ሥሩን በጥልቀት ከሰደደበት ከሰው ልብ የሚመነጭ በመሆኑ ነው:: ስለ ሆነም መልካም የሆኑ የሥነ ምግባር ተምሳሌቶች ስላሉንና እነርሱን ለመምሰል በመሞከር ለሥነ ምግባር ችግሮች መፍትሔ ልናመጣ አንችልም:: ከዚህ ይልቅ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ በልባችን ውስጥ ላለው ክፋት ነው:: በሕይወታችን ውስጥ ለሚገኙ ውጫዊና ውስጣዊ ችግሮቻችንና ከሌሎች ሰዎች ጋር ለሚኖረን የኅብረት እንቅፋቶች እልባት ከማግኘታችን በፊት አዳኝ ያስፈልገናል:: አማኝ ያልሆኑ ሰዎች በዚህ አሳብ ፈጽሞ ባይስማሙም ይህ ግን በኢየሱስ ትምህርት መሠረት ‹‹ውጪው ደግሞ ጥሩ እንዲሆን አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን ውስጡን አጥራ›› ማቴ. 23÷26 የሚለው ቃል ክርስቲያናዊ መንገድ ነው::

## የልብ ዝንባሌ

ሁሉንም የሥነ ምግባር ትምህርት አስመልክቶ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ማለትም ስለ አእምሮና ስለ ሰው መንፈስ እንዲሁም ስለ ልብ ዝንዝባሌ ዳሰሳ አድርገናል:: በእርግጥ ውጫዊው ሥርዓት ትልቁን ስፍራ እንዲይዝ በማድረግ የሥነ ምግባር ሥርዓቶችን መፍጠር ይቻላል:: ሰው ስለማንገድል፤ ከበቀል ድርጊት የምንቆጠብ ስለሆነ፤ ኮቶቻችንና አልባሳቶቻችንን ሁሉ ለሰዎች የምንሰጥ በመሆኑና አንድ ምዕራፍ አብረነው እንደንሄድ ከሚያስገድደን ሰው ጋር ሁለት ምዕራፍ የምንሄድ ስለሆነ መልካሞች ነን ብለን ልናስብ እንችል ይሆናል

(ማቴ. 5÷38-42)። መልካም ሥነ ምግባር የሚያካትታቸው እነዚህን ብቻ ነውን? እነዚህን ነገሮች ውጭአዊ በሆነ ሁኔታ ለመፈጸም የምንጥር ከሆነ በልባችን መልካም የመሆናችን ጉዳይስ ምን ያህልስ ርቆ ሄዶአል? ከዚህ ሌላም እነዚህን ነገሮች ልናከናውን የቻልነው በሌላ ሰው ስለ ታዘዝን ከሆነ ወይም ደግሞ ሌሎች ሰዎች ሲያደርጉ አይተን ከሆነ እንዴት መልካምነት ሊኖረው ይችላል? አንድ ሰው ውጪያዊ የሆኑትን እነዚህን ነገሮች የሚያከናውነው ከጫና የተነሣ እንደሆነ በሚሰማው ጊዜ በልቡ ሊያዝን ወይም ሊበሳጭ ይችል ይሆናል፤ ምናልባትም ከራሱ ጋር ከፍተኛ ትግል እያደረገ ሊሆን ይችላል። ፈጽሞ መልካምነት የሌለው ነገር ነው፤ መታዘዙ ሐሰት፤ «መልካምነቱ» ደግሞ ባሩድ እንደሌለው ጥይት ነው።

እነዚህ ምሳሌዎች እጅግ ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያሳዩን መሠረታዊ ስለሆኑት ስለ ክፋት፤ ስለ ኃጢአት፤ ስለ ፀፀት፤ ስለ እውነት፤ ስለ መዋጀት፤ ስለ ድነትና ስለ ቅድስና ጥያቄዎች መልስ ሳንሰጥ የሥነ ምግባር ጥያቄዎችን አስመልክቶ ለሚነሱ ጥያቄዎች ቅንነትና ጥልቀት ባለው መንገድ ምላሽ ለመስጠት አዳጋች እንደሚሆን ነው። በሌላ አባባል በመጀመሪያ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ምን እንደሆነ ከተገነዘብን በኋላ፤ ስለ ሰው ምንነትና ሰው አብረውት ከሚኖሩት ሌሎች ሰዎች ጋር በተያያዘ ምን ሊሆን እንደሚችልና እንዴትም በጋራ ሊኖሩ እንደሚችሉ እንረዳለን።

የልብ ዝንባሌ አስመልክቶ እንደ ኢየሱስ ግልጽ አድርጎ ያቀረበልን ማንም የለም። እርሱ ይህንን ትእዛዝ ሰጥቶናል «ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ» (ዮሐ. 7÷24)። እንደዚህ ዓይነት ፍርድ ሊሠራ የሚችለው እንዴት ነው? በውጭ የሚታው ድርጊት ብቻውን በመልካምና በክፋት መካከል ስላለው ልዩነት መመዘኛ ሊሆን አይችልም። ክፋት መቀመጫውን የሚያደርገው በገዛ ፈቃድ፤ በምኞት፤ በአስተሳሰቦችና በአጠቃላይ በልብ ዝንባሌ ውስጥ ነው። በሌላም መልኩ ክፋት በራሱ በሰው ውስጥ ማለትም በድርጊቱ፤ በአስተሳሰቦቹና በምኞቶቹ ጀርባ

ስፍራ ይይዛሉ:: በክፋት የሚከናወነው ድርጊት በሰው ውስጥ የሚገኘው ዝንባሌ ውጪያዊው መገለጫ ነው:: ሰው በልቡ ውስጥ ከክፋት ፈጽሞ ነፃ የሚሆንበት አንድ ቀን እንኳን የለም:: ማርቲን ሉተር እንደተናገረውና ተወዳጅም እንደሆነ አባባሉ ሰው ወደ ራሱ ውስጣዊ ማንነት የሚያዘነብልና የተጣመመም ነው:: ይህ እጅግ አሳሳቢ የሆነ ጉዳይ ነው:: ሆኖም ከክፋት ለመራቅ ‹‹ሃይማኖተኛ መሆን›› ‹‹ስለ እግዚአብሔር ማሰብ መጀመር›› ወይም ደግሞ ‹‹መንፈሳዊ ዕይታን ማዳበር›› መፍትሔ ሊሆን አይችልም:: እንደነዚህ ዓይነት ነገሮችን በራስ ጉልበት ለማከናወን መሞከር ራስን ከማታለል ውጪ ሌላ ትርጉም ሊኖረው አይችልም:: ይህንን በመገንዘብ ደረጃ ላይ በምንደርስበት ጊዜ ክፍት የሆነ አንድ በር ብቻ እንዳለ ወደ መረዳት መድረስ ይገባናል:: እርሱም ድነትን ለማግኘት ፈቃደኛ መሆን ነው:: ይህ ማለት የፍርድ ሂደት ተካሂዶ ይቅርታን ማግኘት ማለት ነው:: አንድ ሰው ይህንን በሚገነዘብበት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ታላቅ መምህርነቱ ብቻ ሣይሆን ፈጽሞ ውድቀት እንደማይነካው፣ እንደ አዲሱና እንደ ታላቁ አዳምና ከዚህም በላይ እንደሚዋጅና አዳኝ ሆኖ ዕውን ሆኖለታል ማለት ነው:: ሁሉም ነፃ ‹‹በእውነት ነፃ›› ይሆኑ ዘንድ ለሰው ልጆች መዳን ሲል ራሱን ብቸኛና እውነተኛ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበ እርሱ ታላቁ ካህን ነው (ዮሐ. 8÷31-36):: በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርና አማኞች ባልሆኑት የሥነ ምግባር ሥርዓቶች መካከል ያለው ከፍተኛ ልዩነት ይህ ነው:: ይህም ልዩነት በድነት አስተምህሮዎችና በሥነ ምግባር መርሆዎች መካከል ያለውን ትስስር በሚመለከት ነው:: እነዚህን መርሆዎች መሠረት የሚያደርግ ጥበብና የመከወን ኃይል ተግባራዊ ይሆናሉ::

እነዚህን የክርስቲያን ሥነ ምግባር ዝርዝሮች መመልከት በምንቀጥልበት ጊዜ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥቃይ፣መሥዋዕት መሆንና ሞት በሥነ ምግባር መስክም ምን ትርጉም እንዳለው የሚታይ ይሆናል:: ይህ ለክርስቲያኖች ሁሉ በብዙ መመዘኛ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ተምሳሌት ነው:: ከክርስቶስ የምናገኘው ‹‹እንደዚህ ዓይነት አሳብ›› በእኛ መካከል እንዲኖር የምንመከርበት

ምክንያት እርሱ ‹‹ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ አልቆጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ ... ለሞትም ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ›› (ፊልጵ. 2÷5-8) ተብሎ ስለ ተጻፈ ነው:: የእኛ ፍቅር የእርሱን ያህል ጥልቀትና ተጽዕኖ የማሳደር ኃይል የሌለው ቢሆንም በድነታችንና ከእርሱ ጋር ከሚኖረን ግንኙነት የተነሳ ወደዚህ ዓይነት ፍቅር ለመግባት ተጠርተናል:: ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ የራሱ እሆን ዘንድ፤ ከእርሱ ሥር ሆኜ በመንግሥቱ ውስጥ እኖር ዘንድ፤ ከሞት የተነሳውን፤ ሕያው የሆነውንና ለዘላለም የሚገዛውን በጽድቅ፤ በእውነትና በበረከት ውስጥ ሆኜ አገለግለው ዘንድ እኔን የጠፋሁትንና የተፈረደብኝን ሰው ከኃጢአት፤ ከሞትና ከዲያቢሎስ ሥልጣን ነፃ አውጥቶኛል:: ይህ ደግሞ በእርግጥም እውነት ነው (ትንሹ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ)::

## ኢየሱስ ክርስቶስ እውነት ነው

ቅድስና፤ ጽድቅና ፍቅር የእርሱ ባሕርይ እንደሆኑ ሁሉ እውነትም አንዱ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው:: የእግዚአብሔር እውነት የተገለጠልን በቃሉ ነው:: ያለዚህ ቃል የእግዚአብሔር ባሕርይ የሆኑትን እነዚህን ነገሮች ለማወቅ ካለመቻላችንም ሌላ እውነት ምን እንደሆነ በግላችን ለማወቅ አይቻለንም ነበር::

ኢየሱስ ቃሉና መንፈሱ ወደ ‹‹እውነት ሁሉ›› እንደሚመሩን ይናገራል (ዮሐ. 16÷13):: ‹‹የሚሰማውን ሁሉ (መንፈስ) ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል›› ብሎ ስለሚናገር እዚህ ላይ ቃሉ እንዲካተት ሆኗል:: ይሄ የሚያሳየን አብም ሆነ ወልድ ሥራን በሚመለከት በቃሉና በመንፈስ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ ማለት ነው:: ይህንን ሁሉ የገለጸልን ልጁ ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍት ከመጀመሪያው ክፍል ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ስለ ክርስቶስ (መሢሁ) ይናገራሉ:: ክርስቶስ ‹‹አልፋና ያሜጋ መጀመሪያውና መጨረሻው››

(ራእይ 21÷6) ነው:: ‹‹መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ ተረከው::›› ስለዚህ ‹‹ጸጋና እውነት ግን በክርስቶስ በኩል ሆነ›› (ዮሐ. 1÷18-17) ተብሎ ተጽፏል:: ስለሆነም እውነት ነኝ ብሎ ለመናገር ብቃት ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: እውነትን አስመልክቶ ተወዳዳሪ ሊኖረው እስከማይችል ድረስ እውነትን በማስተማርና በመተግበር ዋነኛው ነው:: ይህ ከዚህ በሚከተለው መንገድ አስፈላጊ ይሆናል:: ትምህርታችን ‹‹ክርስቲያናዊ›› ተብሎ የሚጠራና በኢየሱስ ክርስቶስ ሥም የሚቀርብ ከሆነ መሠረት ሊያደርግ የሚገባው ራሱን ኢየሱስ ክርስቶስንና ለእኛ የሰጠን ቃሉን ነው:: ስለሆነም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ስለ እርሱ የተሰጠውን ትምህርት ችላ ልንለው አንችልም:: ቃሉ ሩቅና ከማይታወቅ ዓለም የሚናገር አፈ ታሪክ ወይም ምስጢራዊ የሆነ ነገር አይደለም:: እርሱ አሁንና ባለንበት ሁኔታ በቃሉና በመንፈሱ የሚናገር ሕያው አምላክ ነው::

የዚህን ቃል አስፈላጊነት በብዙ መንገድ ማሳየት ይቻላል:: በኢየሱስ ክርስቶስ ከሚኖረው እምነት ውጭ የክርስትና ሕይወት ሊኖር አይችልም:: በተጨማሪም እርሱ ከእኛ ጋር በሚገናኝበት ወይም የጸጋ መሣሪያው ለእኛ በሚቀርብበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከእርሱ ጋር ኅብረት ሳይኖረን በክርስቶስ የሆነ እምነት ሊኖረን አይችልም:: እነዚህን ሁሉ በሚመለከት በቃሉ ውስጥ ግልጽ የሆነ መረጃ ሰጥቶናል:: ‹‹እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም አርነት ያወጣችኋል›› (ዮሐ. 8÷31-32)::

በመንፈሳዊ ሕይወታችን በጥንቃቄ እንድንኖርና ለእምነታችን መጋደል እንችል ዘንድ ተከታታይ ትምህርትና ግሳጼ በመካከላችን ይኖራል:: ይህ ካለ ያለ እውነት ቃል ማለትም ያለ እግዚአብሔር ቃል ተግባራዊ ሊደረግ አይችልም:: በዚህ መልኩ ማለትም ከእምነት ጋር በጥንቃቄ ተግባራዊ የምናደርገው ከሆነ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ለራሳችን እያደላን ወይም

የራሳችንን ዓላማ እያስፈጸምን አይደለም:: ይህ ሁለት ባሕርይ ያለው የተፈጥሮ አካል ነው:: ሁለቱም ባሕርያት ዘወትር በዚያው ስፍራ መኖር አለባቸው:: አብረውን ካሉ ሰዎች ጋር ትክክለኛ የሆነ ግኑኝነት ሊኖረን የሚችለውና ተገቢ ታማኝነት ለማሣየት የምንችለው በእምነትና በግላችን ጥንቃቄን በማድረግ እንዲሁም በክርስቶስ ውስጥ ያለውን የሚያድን እምነት ለመጠበቅ በግላችን መጋደል ስንችል ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር በግላችን ከመገናኘት ጋር በተያያዘ ወደ እግዚአብሔር መሠውያ በምንቀርብበት ወቅት ከወንድሞቻችንና ከእኅቶቻችን ጋር ያለንን ግኑኝነቶች ልናቆም አንችልም:: ይህ በራሱ በኢየሱስ ግልጽ በሆነ መልኩ ትምህርት የተሰጠበት ጉዳይ ነው (ማቴ. 5÷23-26)::

## የክርስትናን ተጽዕኖ በሌሎች ላይ ማሳረፍ ይፈቀዳል?

ብዙ ሰዎች ይህንን በሚመለከት ከፍተኛ ተቃውሞ አንስተዋል:: እምነታቸውን ወይም የአስተሳሰብ አቋማቸውን በተመለከተ ተጽዕኖ ለማሳደር መሞከር ስሕተት ነው ብለዋል:: የክርስትና ትምህርትንና ተጽዕኖን አስመልክቶ የሚጠቅሱት ምሳሌ በተለይ ልጆችን በሚመለከት ነው:: ‹‹ራሳቸው የመወሰን ዕድሜ ላይ እስኪደርሱ ድረስ›› ከልጆች ፈቀቅ ሊባል ይገባል የሚል አሳብ ያቀርባሉ:: እንደዚህ ዓይነት ተቃውሞዎች ወደ አንድ አቋም ብቻ ያሳያሉ:: አምባገነን አመለካከትና መንግሥታት በነበሩባቸው ብዙ ስፍራዎች ውስጥ ይህ አሳብ በከፋ መልኩ ተግባራዊ ተደርጓል:: በሌላም አንጻር ‹‹ከፕሮፖጋንዳ ለመታደግ›› በሚል እሳቤ ትናንሽ ልጆችን ከወላጆቻቸው ለመነጠል በጣም ትናንሽ የሆኑትን ልጆች ጨምሮ በወጣቶችና በታዳጊዎች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም:: እንደ እውነቱ ከሆነ ‹‹ልጆቹ ለራሳቸው መወሰን የሚችሉበት›› ዕድሜ ላይ እስኪደርሱ ድረስ ሳይነኩ አልኖሩም፡፡ በዚህ ምትክ የዚያ መንግሥት ፕሮፖጋንዳ ተጠቂዎች እንዲሆኑ ተፈረደባቸው:: ከዚህ ዓይነት ጽንፋዊ አስተሳሰብ የዳኑና በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኙ ወላጆች ልጆቻቸውን መልካም ነው ብለው በሚያስቡት

መንገድ ለማስተማርና መረጃ ለመስጠት ሙሉ ነፃነት ነበራቸው:: በሌላም አንጻር ወላጆቹ ይህንን ለማከናወን የማይፈቀድላቸው ሆኖ ሲገኝ ወይም ካለማወቅ ወይም ከራሳቸው ችግር የተነሣ ማከናወን ቢያዳግታቸው ሌሎች ድርጅቶች በምትካቸው እንዲያከናውኑት ይደረጋል:: እነዚህ ድርጅቶች ልጆቹን በሥነ ምግባር፣ በማኅበራዊና በፖለቲካ ዘርፎች ለማስተማርና ለማሠልጠን በፈቃደኝነት የሚሳተፉ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ ግን ከክፋት ጋር የተያያዙ ተግባራትን ያከናውናሉ:: እንደዚህ ዓይነት ጥፋት በሚፈጸምበት ጊዜ ለተካሄደው ጥፋት መፍትሔ እንዲያበጁለት ብዙ ሰዎች ወደ ባለሥልጣናት አቤት ሊሉ ይችላሉ:: በእኛ ዘመን በብዙ ስፍራ የሚደረገው ይህ ነው::

በታዳጊዎችና በልጆች ላይ የሚሠሩ ብዙ ድርጅቶች የሚንቀሳቀሱ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ልትደርስ እስከምትችልበት ርቀት ድረስ ወጣቶችንም ሆነ አዛውንቶችን የማስተማር ግዴታ እንዳለባት ልትገነዘብ ይገባል:: በዚህም ምክንያት በጌታዋና በአምላክዋ ‹‹አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፣ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ›› (ማቴ. 28÷19-20) ተብሎ የተሰጣትን ትእዛዝ መልሳ ልታጤን ይገባታል:: ለዚህ ትእዛዝ ታዛዥ በመሆን ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ፣ እውነትና ሕይወት እንደሆነና በዚች ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም መሪና ደጋፊ እንደሆነ ለማሳየት ትፈልጋለች:: በዚህ መመሪያ መሠረት ሰዎች ለሕይወታቸው ግብ የሚኖራቸው ሲሆን አብረው ከሚኖሩት ሰዎችም ጋር ኅብረት ለመፍጠር እንዲችሉ ጠንካራ መሠረት ይኖራቸዋል::

## የሕይወት ዓላማ

በሁሉም ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውስጥ ‹‹ሕይወት›› ሁለት ገጽታ ያለው መሆኑን አጽንዖት መስጠቱ ተገቢ ይሆናል::

የዚህ ቃል የመጀመሪያው ትርጉም ‹‹ሕልውና›› ማለትም ሕያው መሆን ወይም በሕይወት መኖር የሚል ትርጉም ሲኖረው ሁለተኛው ትርጉም ደግሞ የሕይወት ዓይነት ማለትም በአንድ ወይም በሌላ መንገድ መኖርን የቀጠለ ሕይወትን ያመለክታል:: እነዚህ ሁለቱ ነገሮች የአንድን ነገር ሁለት ገፅታ የሚያሳዩ መሆናቸውን መገንዘቡ ጠቃሚ ይሆናል:: የአኗኗር ዘይቤው የሚያሳየው የራሱን የሕይወት ዓይነትና መልካምነትን ነው:: ስለሆነም ‹‹ክርስቲያን›› ተብሎ በሚጠራው ሰው ውስጥ እውነተኛ የሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወት የማይታይ ከሆነ ክርስቲያናዊ የሆነ የአኗኗር ዘይቤ የለም:: ክርስቲናዊ የሆነ የአኗኗር ዘይቤ ዓላማ ለታይታ የሚደረግ ሳይሆን ብቸኛ ዓላማው እንደ ክርስቲያን መኖርና ክርስቶስን ማክበር ነው:: እርሱ ሕይወት የሰጠን ከመሆኑም በላይ ይህንኑ ሕይወት በየዕለቱ ተግባራዊ ያደርገዋል:: እንደዚህ ዓይነት ሕይወት የማይኖረን ከሆነ ግን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ‹‹ሥራህን አውቃለሁ፤ ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ ሞተህማል›› (ራእይ 3÷1) ተብሎ እንደ ተጻፈው አስመሳይነትና ለታይታ የሚደረግ ነው ማለት ነው:: በእምነትና በሕይወት እንዲሁም በእምነትና በድርጊት መካከል ያለውን ግኑኝነት አስመልክቶ በአዲስ ኪዳን ብዙ የተብራራ ሲሆን ይህ በአጠቃላይም ሆነ በክርስትና ውስጥ ባለው የቃሉ አተረጓገም መሠረት እውነተኝነት ያለው የሥነ ምግባር ዕውቀት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ በመረዳት በአግባቡ ትኩረት እንድንሰጥበት ያግዘናል:: ቀጥሎ ያሉትን ጥቅሶች ተመልከት፤ ‹‹እናንተ የምድር ጨው ናችሁ÷ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም›› (ማቴ. 5÷13) ‹‹የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር÷ ደስታ÷ ሰላም÷ ትዕግሥት÷ ቸርነት÷ በጎነት÷ እምነት÷ የውሃት÷ ራስን መግዛት ነው›› (ገላ. 5÷22)::

## የሕግ ዓላማ

ከውድቀት በኋላ ዓለም ያለ ሕግና ያለ ትእዛዝ ለመኖር አልቻለችም:: በክርስትና ትምህርት መሠረት የእግዚአብሔር

ሕግ ሁለት ተግባራት አሉት:: ሕጉ የተሰጠው ግለሰቦችንና ማኅበረ ሰብን ለመደገፍና እንዲገዙበት ለማድረግም ጭምር ነው:: ቢሆንም ማንም ሕጉን በመተ‌ታዘዝና ትእዛዛትን በመጠበቅ እንዲሁም ሁሉንም ነገሮች ለመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም:: ይልቁንም ድነት የጸጋ ጉዳይ ነው:: ‹‹ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንላለንና›› (ሮሜ 3÷28):: እዚህ ላይ በጸጋ ብቻ መዳን የሚቻለው እንዴት ነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: ይህ የሚሆነው በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በመምጣት ነው:: ይህ ማለት በጸጋው ዙፋን ፊት እንደ ኃጢአተኛ መቅረብ ማለት ነው:: በዚህ ሁኔታ ሕጉ ሥራውን ሰርቷል ማለት ነው:: ሕጉ ኃጢአተኛው ሰው በኃጢአቱ እንዲጸጸትና ጥፋተኛ መሆኑን አምኖ እንዲናዘዝ ያደርገዋል:: በዚህ ረገድ ሕጉ ‹‹ወደ ክርስቶስ የሚያመጣን ሞግዚታችን ሆኖአል›› (ገላ. 3÷24):: ከዚህ በኋላ ምን ይሆናል? ይኸው ሰው በሞግዚትነት ሥርና በክርስቶስ ትምህርት ቤት ውስጥ በሚሆንበት ወቅት በሚቀጥለው ዓላማ ማለትም በኅብረትና በፍቅር ትምህርት ቤት ውስጥ ሕጉ አመራር ለመስጠት ተፈላጊ ይሆናል:: ሚዛናዊ በሆነ የሕሊና ዕገዛ የትኛውም ሰው ቢሆን ፍቅርን፤ ኅብረትንና ‹‹መልካም ሥራን›› አስመልክቶ ክርስቶስ ከእርሱ የሚጠብቅበትን በራሱ ለመናገር አይችልም:: ሁላችንም ብንሆን በዚህ ነጥብና ለዚህ ዓላማ ሕግ ያስፈልገናል:: ሕጉና ትእዛዛቱ የማይመሩን ከሆነ ቢያንስ በምስጢር ራሳችንን ለመውደድና ለራሳችን ጥቅም የምንጥር እንሆናለን::

ብዙ መጋቢዎች፤ አስተማሪዎችና የሥነ መለኮት ትምህርት ቤቶች ሳይቀሩ ቀደም ብሎ በተጻፉት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙትን የትምህርት ዓይነቶች ተቃውመዋል:: በምትኩም ‹‹እውነተኛ ክርስቲያኖች›› ከሆንንና ‹‹ሙሉ በሙሉ የተለወጥን›› ከሆንን ሕጉና ትእዛዛቱ እኛን አይመለከትም የሚል አሳብ ለማራመድ ጥረዋል:: ነገር ግን ትክክል አይደሉም:: ትምህርታቸው ከክርስቶስና ከደቀ መዛሙርቱ ትምህርት ጋር የሚስማማ አይደለም:: ይህን

አሳባቸውን እንዲደግፍላቸው የሚያቀርቡት የመከራከሪያ ነጥብ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 7፥14-15 ባለው ክፍል ውስጥ አማኝ ባልነበረበት ወቅት ይገኝ ስለነበረበት ሁኔታ እንጂ እንደተለወጠ ሰው የነበረበትን ወቅት አያነሳም የሚል ነው:: በሮሜ 7 ላይ የተጻፈው ይህ ትርጉም ተቀባይነት የሌለው ነው:: ከዚህ በተጨማሪም በፊልጵስዩስ 3፥12-16 ባለው ክፍል አንድ ክርስቲያን የሕግን እገዛ የሚፈልግበት ነጥብ ላይ መድረሱን አይገልጽልንም:: ከዚህ በተቃራኒ አንድ ክርስቲያን በክርስትና ሕይወቱ ለመቀጠል ይችል ዘንድ በየዕለቱ መለወጥና መንፈሳዊ መመሪያ የሚያስፈልገው ከመሆኑም ባሻገር መልካም ሥራን አስመልክቶ መበረታታት እንደሚያስፈልገው ያሰየናል:: ስለሆነም ሁለት ገጽታ ያለው የእግዚአብሔር ሕግ ትምህርት ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ጥሩ ትምህርት ለማስተማር ጠቃሚነቱ እጅግ የጎላ ነው:: እዚህ ስፍራ ላይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንገድ፣ስለ እውነትና ስለ ሕይወት ያስተማረንን አንዳንድ ነጥቦች ለማሳየት ሞክረናል:: በሚቀጥሉት ምዕራፎች ውስጥ ደግሞ በተለያዩ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና በአጠቃላይም በማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ ይህ ምን ማለት እንደሆነ የምንመለከት ይሆናል:: ሰዎች እዚያና እዚህ በብዙ ነጥቦች ዙሪያ ሊከፋፈሉ እንደሚችሉ እንገነዘባለን:: አማኝ የሆኑና ያልሆኑ ይኖራሉ፣ አብያተ ክርስቲያናትና ሰበካዎች ይኖራሉ፣ በሌላ አንጻር ደግሞ ዓለማዊ የሆኑ ኅብረተሰቦች ወይም ማኅበረ ሰቦች ይኖራሉ:: ስለሆነም ብዙ የሚያለያዩ መስመሮችና ድንበሮች ያሉ ቢሆንም በአንድ ዓለም ውስጥ የምንኖር በእግዚአብሔር የተፈጠርን የሰው ዘሮች በመሆናችን አንዳንድ ጊዜ ሁላችንም የምንጋራው ተመሳሳይ የሆነ ባሕርይ አለ:: እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮች በሚቀጥሉት ሁሉም ምዕራፎች ውስጥ ይገኛሉ:: እነዚህን አስቸጋሪ ነገሮች ሁሉ ግምት ውስጥ እያስገባን የእነዚህ ዝርዝር እርእሰቶች ዓላማ የክርስትናን አመለካከትና የሥነ ምግባር መርሆዎችን ማሣየት መሆኑ በአእምሮአችን ውስጥ መጠበቅ አለብን::

ክርስቲያኖችና ቤተ ክርስቲያን እስከ ተጠቀሱ ድረስ ሁሉም

ሰዎች በፍጥረታቸው ምክንያት የእግዚአብሔር ሕዝብ ተብለው እንደሚጠሩ ሳይሆን ለየት ባለ ሁኔታ እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ ሊታዩ ይችላሉ:: ክርስቲያኖች ‹‹የእግዚአብሔር ሕዝብ›› ተብለው በሚጠሩበት ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል ብርሃንና በክርስቶስ ቤዛነትና መዋጀት ውስጥ ስለሚመላለሱ የእግዚአብሔር መንግሥት ወይም የክርስቶስ መንግሥት አካል ሆነዋል ማለት ነው:: በዚሁም መሠረት ክርስቲያናዊ አስተምህሮ በዓለም ውስጥ ለሚገኙ የተለያዩ ሕዝቦች ሁሉ እምነትንና ሥነ ምግባርን የሚመለከት የተወሰነ አስተዋጽዖ ያበረክታል:: ስለሆነም ክርስቶስ ‹‹እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ›› ብቻ ሳይሆን ‹‹እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ›› ብሎም ተናግሯል (ዮሐ. 8÷12፤ ማቴ. 5÷14):: ይህ መሲሁ ብርሃን ስለሚያበራበት የጌታ ዘመን ከተነገረው የቆየ ትንቢት ጋር ይስማማል:: ‹‹ኑ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወደ ያዕቆብ ቤት እንውጣ እርሱም መንገዱን ያስተምረናል በጎዳናውም እንሄዳለን ይላሉ›› (ኢሳ. 2÷3፤ ማቴ. 5÷14÷15)::

# ምዕራፍ 3

# ማኅረሰብና አገር

## ሰውና ዓለም

ሰው ምን እንደሆነ ሳንረዳ ይህንን ጥያቄ መመለስ አንችልም:: ብዙ ሰዎች ዓለምና ሰው አብረው ለመኖር የበቁት በአጋጣሚ ነው የሚል አሳብ አላቸው:: ሁኔታው እንደዚህ ቢሆን ኖሮ ሰው ምንም ዓይነት ዓላማ የማይኖረው ከመሆኑም በሻገር የሥነ ምግባር ሕይወቱን በሚመለከት በግለሰብ ደረጃም ሆነ በሚኖርበት ማኅረሰብ ውስጥ ምንም መርሆዎች የሌሉት ፍጥረት ይሆን ነበር::

በክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ዓለም የተፈጠረችው በእግዚአብሔር ነው:: ከዚህ የተነሳ በዓለምና በሰው ሕልውና ጀርባ ዓላማ ያለ ከመሆኑም ባሻገር ለሰው ሕይወት ግብ ተዘጋጅቶለታል::

ሌላው አስፈላጊ የሆነው የሕይወት ክፍል ኅብረት ነው:: ማንም ሰው ከሌላው የሰው ዘር ተለይቶ መኖር አይችልም:: በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መገባደጃ ወቅት ጫካ ውስጥ የጠፋና ለብዙ ዓመታት ለብቻው የኖረ አንድ ወታደር የተገኘው ከአንድ ማኅረሰብ ሲሆን ከጊዜ በኋላም የተመለሰውም ወደዚያው ማኅረሰብ ነው:: ሁሉም ሰው ማለት ይቻላል የተገኘበት ቤተ ሰብ ይኖረዋል:: አብዛኛውን ጊዜ ከዘመዶቻችን÷ ከጎረቤቶቻችንና ከሥራ ባልደረቦቻችን ጋር የተወሰነ ኅብረት አለን:: እንደዚሁም በወረዳ÷ በክፍለ አገርና በአገር እንዲሁም ትላልቅና ትናንሽ በሆኑ ቦታዎች ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች ሕይወት ጋር ተቆራኝን ነን:: በእነዚህ ጉዳዮች አንጻር ምንም ዓይነት እድገትና ለውጥ ቢኖርም አንድ የሆነ አካል መኖሩ የማይታበል እውነት ነው:: በቀደመው ዘመን ሦስት ዓይነት አካላት ማለትም ቤተ ሰብ፤

አለቃና ጥቂት ሽማግሌዎችን የሚያካትት ፍርድ ቤት መሰል ነገር ነበር::

ትላልቅ ወይም አነስተኛ የልማት ድርጅቶች ቢኖሩንም ባይኖሩንም ምን ጊዜም ቢሆን በኅብረት የምንተሳሰረው ከብዙዎች ጋር ነው:: ምን ጊዜም ቢሆን በየዕለቱ በሚካሄዱ የተለመዱ ሥራዎች÷ ፌስቲቫሎች÷ በሥዕልና በእጅ ሙያ÷ ዝማሬና ሙዚቃ÷ ተረትና ምሳሌዎች ወዘተ... ራሳቸውን የሚገልጹ አሉ:: በዓለም ላይ እነዚህ ነገሮች የሌለው ሕዝብ የለም:: እነዚህን ሁሉ አጠቃለን ስንጠራቸው ባህል ወይም ሥልጣኔ በሚል ስያሜ እንጠራቸዋለን። በእነዚህ ነገሮች ሁሉ አንድ ሕዝብ ራሱን÷ ስሜቶቹን÷ ስጦታዎቹን÷ መንፈሱንና መሻቶቹን ለመግለጽ የሚችልበት ዕድል ይፈጠራል። ማንም ግለሰብ ቢሆን የራሱ ሕዝብ መገለጫዎች ከሆኑት ከእነዚህ ነገሮች ራሱን ሊነጥል አይችልም።

## ሰዎችና አገራቸው

ብዙ ጊዜ ሁሉም ሰው የራሱ አገር ያለውና ሊኖረውም እንደሚገባ በእርግጠኝነት እናስባለን። በብዙ መልኩ ግን በዚህ ጉዳይ እንሳሳታለን፤ ምክንያቱም የአገር ድንበርና የሰዎች ድንበር አብዛኛውን ጊዜ ተመሳሳይ ስለ ሆኑ ነው። ለምሳሌ አንድን ሕዝብ ወይም ብሔረሰብ ማለትም ተመሳሳይ የሆነ ቋንቋና ባህል ያላቸውና እርስ በእርሳቸው ግኑኝነት እንዳላቸው የሚያስቡ ሕዝቦች ወይም ነገዶች እንኳ ቢሆኑ በብዙ ክፍሎች ሊከፈሉ ይችላሉ። እነዚህ ክፍሎች በሁለት ወይም በሦስት አገራት በአንዳንድ ሁኔታዎችም ከዚህ በበለጡ አገራት ሊኖሩ ይችላሉ። በሌላም አንጻር በአንድ አገር ውስጥ በፈቃደኝነት ወይም በአመዛኙ በግዳጅ ከአንድ እስከ ሁለት መቶ የሚጠጉ ሌሎች ሕዝቦችና ብሔረሰቦች በአንድ መንግሥት ጥላ ሥር የሚኖሩበት ሁኔታም ይኖራል። ከዚህ የተነሳም ሕዝቡ «ድንበር» የሚለውና «መንግሥት» ድንበር ብሎ የሚጠራው ብዙውን ጊዜ የሚጣጣሙ አይሆኑም:: የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ግን ይህንን ሁኔታ መቃወም ወይም መደገፍ

አይደለም:: ለእኛ `አካሄድ ያመች ዘንድ በአንዳንድ ሁኔታዎች ‹‹አገር›› የሚለው ቃል በአንዳንድ ሁኔታዎች ሰፊ አሳብ በመያዝ ‹‹ሕዝብ›› ሊሆን ይችላል።

ለእኛ አስፈላጊ የሚሆነው ጉዳይ የአንድን ግለሰብና ማኅረሰብ ክንውን ከክርስቲያናዊ ዕይታ አንጻር መረዳታችን ነው። ምናልባትም ከተወሰኑ ሰዎች ወይም አገር ጋር እየኖርን ያለንበት ሁኔታ የሚያረካን ላይሆን ይችላል፤ ይህም የሚሆነው የተለያየ መሠረትና ባህል ያላቸው ሰዎች ‹‹በአንድ አገር›› ውስጥ በአንድነት ከመኖራቸው የተነሣ ከሌሎቹ ጋር አብሮ ለመኖር ስለሚያዳግታቸው ሊሆን ይችላል። ሆኖም ሁሉም አብረው መኖር ያለባቸው በመሆኑ በተቻለው መንገድ ሁሉ ይህንኑ ግንኙነት በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ ይጥራሉ። መፍትሔው አንድን ‹‹አገር›› ወደ ተለያዩ ‹‹አገሮች›› መበታተን ከሆነ ይህ የፖለቲካ ጥያቄ በመሆኑ እኛ ከተነሳንበት ዓላማ ጋር የሚሄድ አይደለም። ይህንን ጉዳይ መመልከት የሚኖርብን ከሥነ ምግባር አንጻር ነው። የተለያዩ ቡድኖች አንድ ላይ የሚኖሩበት ሁኔታ የሚፈጠር ከሆነ ይህንኑ ተግባራዊ የሚደርጉበት የተሻለ ሁኔታ ማመቻቸት በተለይ የክርስቲያን ተግባር ነው። አንዱ ቡድን በሌላው ተጽዕኖ ሥር እንዲወድቅ ወይም የአንዱ ባህል በሌላው ባህል እንዲተካ ማድረግ ፈጽሞ መፍትሔ ሊሆን አይችልም። ሊታሰብ የሚገባው ብቸኛው ነገር መቻቻል፥ የጋራ መግባባትና ትብብር ብቻ ነው። ስለሆነም አብሮ የመኖሩ ጉዳይ ከታሰበ ለሌሎች አክብሮት በመስጠት ላይ ሊመሠረት የሚገባው ነው። ይህ ራስን ከማክበር ጋር በእጅጉ የሚያያዝ ጉዳይ ነው። ሁላችንም በእግዚአብሔር የተፈጠርን እንደመሆናችን የምናካሄዳቸው ልማዶችና ባህሎች በኃጢአት የተተበተቡና የማይጠቅሙ እስካልሆኑ ድረስ እንደ አንድ ሕዝብ ማንነታችንንና ከአባቶቻችን የወረስናቸውን ነገሮች አሳልፈን የምንሰጥበት አንዳችም ምክንያት ሊኖር አይችልም። እኛ ሌሎች እንዲሰጡን የምንፈልገውን ክብር እኛም ለሌሎች ግለሰቦች፥ ቡድኖች ወይም ሕዝቦች እንደየሁኔታው ለመስጠት ዝግጁ መሆን ይኖርብናል (ማቴ. 7፥12)።

## አገር÷ ማኅበረሰብ ወይም ‹‹ባለሥልጣናት››

‹‹አገር›› የሚለው ቃል ብዙ ትርጉም ሊሰጠው የሚችል በመሆኑ ውስብስብ ነው፡፡ ይኸውም የሚሆነው ቃሉ የምንኖርበትን አገር÷ ባለሥልጣናቱንና አገዛዙ ወዘተ... ስለሚመለከት ነው፡፡ ‹‹አገር›› የሚለው ቃል አሳባችንን በእጅጉ ከመማረኩ የተነሳ ብዙዎች ‹‹የአንድ አገር አባል እስካልሆንን ድረስ ፈጽሞ መኖር አይቻልም›› የሚል ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ፡፡ ይህ አባባል ስሕተት ቢሆንም የፈለጉትን እንዲያደርጉ ለብዙ ባለ ሥልጣናት የሌላቸውን ዕድል በመስጠት ብዙ ዜጎች ሊድኑ የሚችሉበት በር እንዲዘጋ አድርጓል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ሰዎች ተሰባስበው እንደ አገር መደራጀታቸው በመሠረቱ የመጨረሻው አስፈላጊ ጉዳይ አይደለም፡፡ ለዚህ ማስረጃ ማቅረብ ቢያስፈልግ በአሁኑ ጊዜ ያሉትን ብዙ የአፍሪካ አገሮችን በምሳሌነት መጥቀስ እንችላለን፡፡ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስና ከዚያ ቀጥሎ ባሉት ዘመናት (በግምት ከ1850 ዓ.ም.) አሁን ባለው ዘመናዊ አተረጓጎም መሠረት ‹‹አገር›› የሚባል ነገር አልነበረም፡፡ ፓርላማዎች÷ መንግሥታት ወዘተ... አልነበሯቸውም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ በቊጥር አነስተኛ በሆኑ የሰዎች ስብስብ ወይም በጎሳ አለቆች የሚገዙበትና እነዚህ በአለቃ ሥር የሚገኙ ሕዝቦች በሽማግሌዎች በሚመራ ባልተጻፈ ሕግና በሕዝቡ ባህል ጥላ ሥር በአንድነት እንዲኖሩ ይደረግ ነበር፡፡ እነዚህ በተለያዩ አለቆች ሥር የነበሩ ብዛት ያላቸው ሕዝቦች በአንድነት እንዲኖሩ በተደረገበት ሁኔታ ነው አሁን በምናውቀው መልኩ ‹‹አገር›› የሚለው ቃል ብቅ እያለ መምጣት የጀመረው፡፡ ቀድሞ የነበረው ሥርዓት በቀጣዮቹ ዓመታትም ታይቷል፡፡ ለምሳሌ ያህል ከፍተኛ ረብሻ በተፈጠረበት ወቅት አገራት እንደ አገር መቆማቸው ያቆመበት ወቅት ነበር፡፡ ትናንሽ የሆኑ አገራትና አህጉራት ሕይወታቸውን ያለ መንግሥት የመሩበት ወቅትም ነበር፡፡ ሰዎች በሚኖሩበት አካባቢ ራሳቸውን በማደራጀትና የየራሳቸውን አለቆች በመምረጥ ‹‹ማኅረሰብ›› እንዲኖርና ሥራው እንዳይቋረጥ ያደርጋሉ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በዚህ መልኩ በተቋቋሙ ማኅረሰቦች መካከል

በተወሰነ ደረጃ ትብብር የሚኖር ቢሆንም ቀድሞ የነበረው ትልቅ አገር ሕልውና አይኖረውም። እንደዚህ ያሉ ሁኔታዎች የሚከሰቱ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በዓለም ዙሪያ ‹‹አገራት›› አሉ። በሌላ አንጻር የተዋጣለት በጎ ነገር ባይሆንም ‹‹አገር›› በመሠረቱ ክፋት ያለው ነገር አይደለም። ሁሉም ነገር የሚወሰነው አገሩ እንዴት እንደተገኘና እንደተደራጀ÷ መልካምም ይሁን ክፉ ምን ዓይነት ተግባር እያከናወነ እንዳለና ዜጎቹ በአገራቸው የሚኖራቸው አስተዋፅዖ ነው። ይህ ‹‹ባለሥልጣናት›› ለሚለው ቃልም ይሠራል። ባለ ሥልጣናቱ ጥሩ ወይም ክፉ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ ‹‹ባለሥልጣናት›› የሚለው ቃል ‹‹አገር›› ከሚለው ቃል ጋር በተወሰነ ደረጃ ተመሣሣይነት ሊኖረው ይችል ይሆናል። እዚህ ላይ አስፈላጊው ነገር ከግለሰቦች÷ ከቤተ ሰቦችና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ከተደራጁ ሌሎች ቡድኖች ጋር ኅብረት ማድረግ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ‹‹ማኅረሰብ›› እያልን የምንጠራው ይህንን ነው። ሰው ሁሉ የሁሉም ጌታ መሆን ወይም ማዘዝ ለሚፈልገው ሰው ሁሉ ትእዛዝ መስጠት የማይችል በመሆኑ አንዳንድ ግለሰቦች የአመራር ኃላፊነትን ወይም ሥልጣንን ከቤተ ሰቦቻቸው የሚወርሱ÷ በተጻፈ ወይም ባልተጻፈ ሕግ መሠረት ለኃላፊነት የሚመረጡ ይሆናሉ። ስለሆነም ‹‹አገራት›› ከመኖራቸው በፊትም ቢሆን ይህ በዓለም ዙሪያ ሁሉ ተግባራዊ ይደረግ ነበር። በዚህም ምክንያት እንደዚህ ብለን ልንናገር እንችላለን፡- አንድ ላይ ለመኖር ያስችለን ዘንድ መንግሥት መመሠረቱ ሊቀር የማይገባው ጉዳይ ነው ብለን የማናምን ቢሆንም አንድ ማኅረሰብ መኖሩ ግን ምን ጊዜም ቢሆን አስፈላጊ ነው።

በዚህ ምክንያት ደግሞ ሌላ ነገር ብቅ ይላል። በእኛ ላይ ‹‹ገዢ›› እንዲሆኑ ሳይሆን ነገሮችን እንዲያደራጁልን፣ እንዲያገለግሉንና በሰላምና በሥርዓት እንድንኖር እንዲያደርጉን ምን ጊዜም ቢሆን ባለሥልጣናት ያስፈልጉናል። ባለሥልጣናት በሚኖሩበት ወቅት ከሠፈር አለቃና ዳኞች ጀምሮ እስከ ፓርላማዎች÷ መንግሥታትና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ከሠፈር ጥበቃዎች ጀምሮ እስከ ፖሊስ ኃይል÷ ጦር ሠራዊትና የአገር

መከላከያ ድረስ ሊኖሩን ይችላል። የዚህ ሁሉ ዓላማው ምንድ ነው? መልሱ ‹‹ለጋራ ጥቅም›› ‹‹ለሕዝብ ደኅንነት›› ወይም ለሌላ ተመሣሣይ ነገር ነው ሊባል ይችላል። ይህ መልካም የሚመስል ቢሆንም መሪዎቹም ሆኑ ‹‹ባለሥልጣናቱ›› ‹‹ለጋራ ጥቅም›› በሚል ሰበብ አንዳንድ ነገሮችን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ግለሰቦች ይጎዳሉ ወይም ‹‹መብታቸው›› እንደተሸረሸረ አድርገው ይገምታሉ። ምናልባት ባለሥልጣናቱ የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንደተወጡ የሚያስቡና የሚናገሩ ቢሆንም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግለሰቦች ግን ይህ ትክክለኛ ነገር መስሎ አይታያቸውም። ከዚህ በተቃራኒው ባለሥልጣናቱ የተሣሣተ ነገር እንደፈጸሙ አድርገው ሊገምቱ ይችላሉ። ይህ በምን ምክንያት ሊሆን ይችላል?

## ግለሰቦችና ባለሥልጣናት

በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ባለሥልጣናት ለአንድ ፓርቲ÷ ለአንድ የፖለቲካ ቡድን ገንዘብን በሚመለከት ወዘተ... ጉዳዮች አድልተው የአንድን ግለሰብ ወይም የተወሰኑ ግለሰቦችን መብት ተጋፍተዋል እንበል። ወይም ደግሞ እውነተኛው ሥልጣን የማን እንደ ሆነ ለማኅበረሰቡ ለማሣየት ሲሉ ብቻ አስቸጋሪዎች ሆነው መታየትን አማራጭ መንገድ አድርገው ሊቆጥሩ ይችሉ ይሆናል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ ማንም ቢሰቃይ ግድ የላቸውም። ጉዳዩ ሌላ መልክም ሊይዝ ይችላል። ምናልባትም አንዳንድ ዜጎች ‹‹መብታችን›› ነው ብለው የሚያስቡት ከራሳቸው ጥቅም አንጻር ብቻ ከመሆኑ የተነሣ ይህ ለግል ጥቅማቸው ያሰቡት ጉዳይ በባሥልጣናቱ ድጋፍ እንዲቸረው በከንቱ ሲለፉ ከርመው ባለሥልጣናቱ ግን እነርሱ ለሚፈልጉት ነገር ፈቃደኝነታቸውን ሳያሳዩ ሲቀሩ ጥቅማቸው ከመነካቱ የተነሳ እነዚህን ባለሥልጣናት ማሳጣት ሊጀምሩ ይችላሉ። ማንም ሰው ቢሆን እነዚህን ነገሮች እንደ ቀላል ሊያያቸው አይገባም። እንዲህ ዓይነት ነገሮች ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በታሪክ ገጾች ይነገራሉ። እነዚህ ችግሮች መፍትሔ የሚያገኙት እንዴት ነው?

በመጀመሪያ ደረጃ ማንም ሰው በሌሎች ግለሰቦች ላይም ሆነ በባለሥልጣናት ላይ የሚያቀርበው ስሞታ ሁሉ ትክክለኛ ነው ለማለት አይቻልም። በሌላም አንጻር ማንም ባለሥልጣን በግለሰቦች÷ በቡድኖችና ማኅበሮች ላይ የሚያቀርበው ስሞታ ሁሉ ትክክል ነው ማለት አይቻልም። ስለ ሆነም በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ባለሥልጣናት የግለሰቦችን አቤቱታና ጉዳዮች ማዳፈን አይገባቸውም። በሌላም አንጻር ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ለሚያቀርቡት ስሞታ በቂ መረጃ ሳይኖራቸው ባለሥልጣናቱን በየምክንያቱ ሊወነጅሏቸው አይገባም። በሌላም በኩል በየትኛውም አገር ቢሆን በየዓመቱ ማለት ይቻላል የናቡቴ ዓይነት ችግር የሚገጥማቸው ሰዎች ቊጥር ቀላል አይደለም (1 ነገ. 21÷1-19)። እንግዲያውስ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የሚገኙ ሰዎች እጅግ ባለጸጋ ስለሚሆኑበት ሁኔታ እንዴት ማስረዳት ይቻላል? በሌላ አንጻር ለእንደዚህ ዓይነት ችግሮች ቀላል የሆኑ መፍትሔዎችን ማመንጨት ከባድ አይደለም። አብዛኛውን ጊዜ በሕዝብ መካከል የሚከሰቱ ችግሮችንና ሁሉንም የሚነካኩ እርካታ የማጣት ስሜቶችን አንዱን ወይም ሌላውን በመደገፍ ለራሳቸው ጥቅም እንዲውል የሚያደርጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ። እነርሱም ‹‹ወደ ሥልጣን እንድንመጣ አግዙንና የባለሥልጣናቱ ጥቅም የሚገፈፍበትን ሁኔታ እናመቻቻለን›› ይላሉ። ወይም ደግሞ ‹‹ሥልጣን ስጡንና ሁሉም ግለሰቦች ጥቅም የሚያገኙበትን ሁኔታ ወይም ሁሉም ነገሮች ለጋራ ጥቅም የሚውሉበትን መንገድ እናመቻቻለን›› በማለት ይናገራሉ። እንደዚህ ዓይነት እወጃዎች በተለይም ሕዝቡን ለማታለል የሚደረጉ ከሆነ ነገሮች እየከፉ እንዲሄዱ ከማድረግ ውጪ የሚፈይዱት ነገር አይኖራቸውም። በጣም የሚገርመው በተለይ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ብቻ በሚያስተዳድርበት አገር ውስጥ ሁሉም ነገር የሕዝብ ንብረት በመሆኑ ግለሰብ ንብረት እንዲኖረው አይፈቀድም የሚል ሕግ ካወጡ በኋላ አንድ የዚህ ሥርዓት መሪ የሆነ ሰው እጅግ ምቾት ያላቸው የስፖርት መኪናዎች ባለቤት ሆኖ መገኘቱ ነው።

እነዚህ ሁሉ ችግሮች የሚመነጩት ከየት ነው? ብዙ

የግልና የባለሥልጣናትን ልብ የሚዘውር በሰው ውስጥ ሥር የሰደደ ገደብ የለሽ ራስ ወዳድነት እና እጅግ ብዙ ክብር የማግኘት ፍላጎቶች ናቸው። ‹‹የግለሰብ ፍላጎቶች›› አብዛኛውን ጊዜ ንጹሕ የሆኑና ራስ ወዳድነት ያልተጠናወታቸው አይደሉም። በአንድ ፓርቲ ብቻ በሚገዙ አገራት የሚገኙ ጥቂት ቊጥር ያላቸው ግለሰቦች ‹‹ከራስ ወዳድነት መንፈስ ርቀው ለሕዝቡ ደኅንነት›› የሚሠሩ ቢመስሉም በአንጻሩ ግን ብዙውን ጊዜ ሕዝብን የሚጎዱ ሆነው ይገኛሉ። ለምሳሌ ያህልም ለራሳቸው ብዙ ንብረትን በመሰብሰብ ዜጎቻቸውን ያደኸያሉ። አንዳንዶቹ ገንዘብ የማጋበስ ሥራቸውን በአገራቸው ውስጥ የሚያካሄዱ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ አስተዳደራቸው የከፋ በመሆኑና በሕዝብ ከመጠላታቸው የተነሣ ሕይወታቸው ስጋት ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ለመሸሽ እንዲያመቻቸው በምሥጢር የባንክ አካውንት በውጪ አገር ይከፍታሉ።

ለእንደዚህ ዓይነት ክፋት መፍትሔ የሚገኘው በአንድ ወይም በሌላ ሥርዓት÷ ወይም ከፍተኛ የዲሞክራሲ አሠራር በሰፈነበት÷ ወይም አምባገነን ሥርዓት በነገሠበት ሁኔታ ውስጥ አይደለም። መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለው እውነተኛና ሚዛናዊ በሆኑ ሕጎችና እነዚህን ሕጎችና ፍትሕ ባለሥልጣናቱ ለግለሰቦች÷ ለቡድኖች÷ ለአንዳንድ ወገኖችና በአጠቃላይም ለሕዝቡ ቅን በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ሲጥሩ ብቻ ነው። የአንድ አገር ዜጋ የሆነ ግለሰብ ጉዳዩን ለፍርድ ቤት የማቅረብ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚቀርብበት ፍርድ ቤት ውስጥ ያሉ ዳኞች ከሌሎች ባለሥልጣናት ተጽዕኖ ፍጹም ነፃ ሊሆኑ ይገባል። አንድ ግለሰብ የራሱን መንግሥትና አገር ፍርድ ቤት ወስዶ እስከ መክሰስ ሊደርስ የሚችልበት መብት ሊኖረው ይገባል። አንዳንድ ‹‹ዝግ የሆኑ አገራት›› ዓለም አቀፍ ሕጎችን የማያከብሩ ከመሆናቸው የተነሳ በተለየ መልኩ ችግር ፈጣሪዎች ይሆናሉ። ሕጋዊ በሆነ መልኩ ይህንን ጉዳይ ተግባራዊ ለማድረግ ዓለም አቀፉን ስምምነት የሚፈርሙ ቢሆኑ እንኳ ከንግግር ውጪ ወደ ተግባር አይለወጡትም። ‹‹ነፃነት ባላቸው

አገሮች›› ውስጥ ግን ይህ በተለየ መልኩ ይገለጻል። እዚያ ቦታ ግን አንድ ግለሰብ ‹‹መብቴ›› ተጥሷል ብሎ የሚያስብ ከሆነ የራሱን አገር ባለሥልጣናትና ከዚህ ሲያልፍም ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት በመሄድ ‹‹አገሩን›› የመክሰስ መብቱ ይጠበቅለታል፤ ይህም ከሃዲ አያሰኘውም። ይህ የሚያሳየው አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሕጎች መከበራቸውን ነው። እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች ተገቢውን ውሳኔ በሚያገኙበት ወቅት ለሌሎች አገሮች ሳይቀር ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ። አንዳንድ ጊዜ የሚያዳግት መሆኑ አሌ የማይባል ቢሆንም ብዙ ሰዎች ፍትሕን ማግኘት ይቻላል ብለው ተስፋ እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል። መልካም የሚሆነው የፍርድ ቤት እገዛን በማንሻበት መልኩ የምንኖር ከሆነ ነው። ጥሩ የሆኑ ሕጎች ወይም በአጠቃላይ ለእግዚአብሔር መታዘዝ እና በፈቃደኝነት ላይ በመመሥረት የጎረቤቶቻችንን መብቶችና ጥቅሞች ማክበር እንደዚህ ዓይነት መልካም የሆነ ኑሮን ለመኖር ይረዳናል።

## ሁለት ዓይነት አገዛዝ

የምንኖርባት ዓለም በሰው ዘር ሁሉ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መልካምና ክፉ ነገሮች የሚገኙባት ናት። እግዚአብሔር ይህንን ሥርዓት አልበኝነት የማይሻው ቢሆንም ከሰው ውድቀት የተነሳ ወደ ዓለም ሊገባ ችሏል። ስለ ሆነም የሰዎች ሕልውና እንዲጠበቅና አብረው ለመኖር ይችሉ ዘንድ እግዚአብሔር ለሰይጣን ገደብ አበጅቶለታል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በዚህ ስፍራ ላይ ከምናጠናቸው ሁለት አገዛዞች በአንደኛው ውስጥ የምናየው እውነታ ነው። ይህ አገዛዝ የሚካሄደው በመንግሥታትና በተለያዩ ዓለማዊ ባለሥልጣናት አማካይነት ነው። እነዚህ አካላት የተፈጠሩት ክፋት የበላይነት እንዳይኖረው ሕዝቡን ከጠላት ለመከላከል÷ ለመጠበቅና ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ ነው። ይህን ዓይነት አገዛዝ ዓለማዊ አገዛዝ ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

የዚህ ተቃራኒ የሆነው አገዛዝ ደግሞ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥራውን የሚሠራበት መንፈሳዊው

አገዛዝ ነው። እነዚህ ሁለት አገዛዞችን በተመለከተ በሚቀጥሉት ክፍሎች ውስጥ የበለጠ በዝርዝር የምንመለከት ቢሆንም ሁለቱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለ መሆናቸው ግን መዘንጋት የለበትም። ከእግዚአብሔር አሳብ አንጻርና ለሕሊናችንና ለደኅንነታችን ስንል ሁለቱንም ልናከብራቸው ይገባናል።

ውጫዊ የሆነውን ዓለማዊ አገዛዝ በአጠቃላይ ‹‹ባለሥልጣናት›› ‹‹ማኅበረሰብ›› ወይም ‹‹መንግሥት›› በሚል ስያሜ እንገልጸዋለን። ይህ ውጫዊ የሆነው ዓለማዊው አገዛዝ ተግባሩ በአንድ አገር ውስጥ ሰላምን ማስጠበቅና ሥርዓት እንዲሰፍን ማድረግ፥ ከተለያዩ ጠላቶች ዜጎችን መጠበቅና ከጊዜው አንጻር በተቻለ መጠን ጥሩ የሆኑ ውጫዊ የአኗኗር ዘይቤን ተግባራዊ ማድረግ ናቸው። ይኸኛው ዓይነት ሥልጣን ከሚያካትታቸው ነገሮች መካከል አንዱ የአንድ ዜጋ መብትና ተግባር በሌላ ሰው ጉዳት እንይደርስበት ከለላ መስጠት ነው። ለምሳሌ አንድ ዜጋ መብቱ በሌላ ሰው ምክንያት ሥጋት ላይ የወደቀ መስሎ ሊታየው ይችል ይሆናል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ መልካም በሆነው ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኘው ሕግ ማንም ሰው ለራሱ በመሰለው መንገድ በሌላው ዜጋ ላይ የራሱን ሥልጣን ሊያሳይ አይገባውም የሚል ይሆናል። ይህንን የሚያደርግ ከሆነ በአንድ ወይም በሁለቱም አካላት ላይ በተሣሣተ መንገድ የሚያደርግ ስለ ሆነ እንደዚህ ዓይነት ፍትህ በማኅረሰቡ ሊታገድ ይገባዋል። ይህንን አንድ ቀላል ምሳሌ የበለጠ ግልጽ ሊያደርገው ይችላል። ምንም እንኳ ፍትህን የሚመለከቱ ጉዳዮችን አስመልክቶ በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ በስፋት የሚዳሰስ ቢሆንም ከዚህ በታች የቀረበው ምሳሌ ‹‹ዓለማዊውን አገዛዝ›› ቋሳያል።

አንድ ሰው ብስክሌቱ በሌባ ይሰረቅበታል። እንዳጋጣሚ ባለቤቱ የጠፋበትን ብስክሌት በአንድ የሆነ ስፍራ ላይ ያገኘውና ምንም ዓይነት የሕግ ሥርዓት ባልተከተለ መልኩ ብስክሌቱን ወደቤቱ ይዞት ይመጣል። ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ጥቂት ሰዎች ይመለከቱት ነበር። ይኸው ሰው በአዲሱ የብስክሌቱ

‹‹ባለቤት›› ብስክሌቱ የእኔ ነው በሚል ፖሊስ ጣቢያ ይከሰሳል። ፍርድ ቤት ቀርቦ መብቱ እንደሆነ ቢከራከርም ንብረትነቱ የእኔ ነው የሚለው ሌላው ግለሰብ ግን ብስክሌቱን ከሱቅ እንደገዛውና ለዚህም ክፍያ ስለመፈጸሙ ደረሰኝ ሊያቀርብ ስለሚችል ብስክሌቱ የተሰረቀበት ሰው ሌባ ነህ የሚል ፍርድ ይተላለፍበታል። ይህ ሁሉ የሚሆነው ለምንድነው? የመጀመሪያው ባለቤት ነኝ ባዩ ሌባ ስለ ነበረ ብስክሌቱን ሰርቆ የራሴ ነው በማለት ለባለ ሱቁ የሸጠለት ሲሆን ባለ ሱቁ ግን ይህ ብስክሌት በእርግጥም የእርሱ ስለ መሆኑ የገዛበትን ደረሰኝ ወይም የባለቤትነት ማስረጃ ባለመጠየቁ ስሕተት ሰርቷል። እነዚህን በሕግ የተደነገጉትን ደንቦች ወይም እውነታዎች ባለማወቁ የመጀመሪያው የብስክሌቱ ባለቤት ፍትሕን በራሱ በመወሰኑ ሌባ ሆኖ ተገኘ። ይህ የሚያሳየን ፍትሕን በራሳችን ለመወሰን የምናደርገው ጥረት ስሕተት ውስጥ የሚከተን መሆኑን ነው። ከዚህ ይልቅ የሕጉን መንገዶችና አሠራሮች ማወቅና የሕግ ባለሙያዎችን ማማከር ይገባናል። በዚህ መልክ በሚፈጸም አካሄድ ብቻ በአንድነትና በሠላም መኖር ይቻላል። በዚህም መንገድ የሕግ ባለሙያዎች በእኛና ባልተግባባናቸው ዜጎች መካከል በመግባት ሽምጋዮችና አስታራቂዎች ይሆኑልናል ማለት ነው። ከላይ በተጠቀሰው ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ‹‹ባለሥልጣናቱ ነገሮችን ከማወሳሰብ ውጪ የሚፈይዱት ነገር የለም›› ለማለት የሚዳዳን ከሆነ እስቲ የብስክሌቱን ጉዳይ ተመልሰን ለማየት እንሞክር። የተገኘው ብስክሌት ከተሰረቀው ብስክሌት ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም ብስክሌቱ ግን እርሱ አይደለም እንበል። ‹‹የብስክሌቱ ባለቤት›› ነኝ ያለው ሰው በስሕተት ሌባ ተደርጎ ቢቆጠርም እውነተኛ ሌባ ነው እንበል። በዚህ ዓለም ላይ አስቸጋሪ ከሆኑ ብዙ ነገሮች መካከል አንዱ ብዙ ሌቦች የሠረቋቸውን ነገሮች እንደገዛ ንብረታቸው መቍጠራቸው ነው። አሁንም ይህ ጉዳይ ዜጎች አንድን ነገር ፍትሕን በራሳቸው መንገድ ለማግኘት የሚጓዙበት መንገድ ሊፈቀድላቸው እንደማይገባ ያሳየናል። ሕጎችና ባለሥልጣናት እዚያ ስፍራ ላይ የሚቀመጡት ለአንድ ወይም ለጥቂት ግለሰቦች ሳይሆን እኛን ለመርዳት፥ የሁሉም ጥቅምና ደኅንነት እንዲጠበቅ

ለማድረግ ነው። እግዚአብሔር እኛን እየተንከባከበ ስለ መሆኑ እውነተኛ ማረጋገጫው ዓለማዊ ለሆነው አገዛዝ ሥልጣንና ኃላፊነት መስጠቱ ነው።

መንፈሳዊው አገዛዝ ፍጹም ልዩ የሆነ አሠራር አለው። የሚሰጠው ለቤተ ክርስቲያን ሲሆን ክንውኑ የሚጀምረውም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል የተሰጡ ሲሆኑ÷ ሁሉን ቻይና ኃያል በሆነው እግዚአብሔር ፊት እንዲቀርቡ ሲደረግና የእግዚአብሔርን ጸጋ እንዲመለከቱና እንዲቀበሉ በሚደረግበት ወቅት ነው። ቤተ ክርስቲያን እኛን የእግዚአብሔር ልጆች÷ የእግዚአብሔር መንግሥት አባላትና የሰማያዊዋ ኢየሩሳሌም ዜጎች ለማድረግ ትሻለች። ይህ መልእክት ምድራዊ በሆነው አገዛዝ በኩል አይመጣም፤ በጸጋና በእምነት ውስጥ ብቻ ይገኛል። ይህንን በሚመለከት ምድራዊ ባለሥልጣናት በጉዳዩ የሚገቡበት ምንም መንገድ የለም።

## በሁለቱ የአገዛዝ ዓይነቶች መካከል ያሉ ግንኙነቶች

የምንኖረው በአንድ ዓለም ውስጥ ብቻ ከመሆኑ የተነሳ በምድራዊውና በመንፈሳዊው አገዛዝ መካከል አንዳንድ ግንኙነቶች መቼም ቢሆን አይቋረጡም። እዚህ ስፍራ ላይ የግንኙነት ማዕከል ሊሆኑ የሚችሉና በጣም ግልጽ የሆኑ ሦስት ነጥቦችን መጥቀስ ይቻላል። የመጀመሪያው የግንኙነት ማዕከል ውጪያዊው ሥርዓት ነው። እንደዚህ ዓይነት ሥርዓትን የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለባቸው ምድራዊ የሆኑ ባለሥልጣናት አማኝ ቢሆኑም ባይሆኑም ሥራቸው ለሰው ልጆች ሕይወት የሚጠቅም በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንም በዚህ ረገድ ተሣትፎ የማድረግ ፍላጎቱ አላት። እንደዚህ ዓይነት ውጪያዊ የሆነ ሥርዓት «መልካሙን የምሥራች» ወይም ወንጌልን ለማሰራጨት አስፈላጊ ነው። ሁለተኛው የግንኙነት ማዕከል የማሰብና የመናገር ነፃነት ነው። ይህ ነፃነትን የሚሸራረፍ÷ እንቅፋት የሚፈጠርበት ወይም ክልከላ የሚደረግበት ከሆነ ለወንጌል መስፋፋት ትልቅ እንቅፋት ይፈጠራል። በሌላም አንጻር እንደዚህ ዓይነት የማሰብና የመናገር

ነፃነት በሰፈነበት ስፍራ የእግዚአብሔር ቃል ሊነበብ÷ ሊሰበክና ሊደመጥ የሚችል በመሆኑ ለማመንና እንደ ክርስቲያን ለመኖር ሙሉ ነፃነቱ ይኖራቸዋል።

ሦስተኛው የግንኙነት ማዕከል እምብዛም ግልጽ ባይሆንም ጠቃሚነቱ ግን ብዙ ነው። ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን በውጪያዊው አመራር ውስጥ ጣልቃ የማትገባ ቢሆንም ከትንቢታዊ ሥራዋ ጋር የሚያያዙ ጉዳዮች ግን አሉ። ለምሳሌ ያህል ፍትሕ ያለ አድልዎ የሚካሄድበት ሁኔታና ጽድቅንና ዕውነትን መሠረት ያላደረጉ ዓለማዊ የሆኑ የሰዎች አስተሳሰብ የሚስተናገዱበት ሁኔታ ነው። በዓለማዊው አገዛዝ ውስጥ ባለሥልጣናት ከሙስናና ከራስ ወዳድነት የተነሣ ፍትሕ÷ ሚዛናዊነትና እውነት ችላ ሊባሉ ከነአካቴውም አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ። በዚህን ወቅት ቤተ ክርስቲያን ትንቢታዊ ተግባሯን ማከናወን ይጠበቅባታል። ይህ ማለት ግን በእያንዳንዱ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ትገባለች ማለት ሳይሆን የሚዛናዊነትን÷ የእውነትንና የፍትሕን መርሆዎች ታስከብራለች ማለት ነው። ይህንን ተግባር የምታከናውን ከሆነ የዓለም ጨውና ብርሃን መሆኗን ታስመሰክራለች ማለት ነው (ማቴ. 5÷13-16)። እንደዚህ ዓይነት ምሳሌዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዛት ይገኛሉ። እዚህ ቦታ ላይ ነቢዩ ናታንን÷ አሞጽንና የኢየሱስ መንገድ ጠራጊ የነበረውን መጥምቁ ዮሐንስን ማንሳት ብቻ ይበቃል። እነዚህ ሦስቱ የሚጠቀሱትና ትኩረትን የሚስቡት ሰዎች ሁሉ ከሕግ ጋር ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት ትግል በማድረግ ነበር። ዓለማዊው አስተዳደር ሕግን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ብቻ ነው የሚያስበው። ከወንጌል ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም። ቢሆንም ሕግን÷ ሰላምንና መልካም አስተዳደርን ከማስከበር አንጻር ዓለማዊው አገዛዝ ለወንጌል ሥራ እገዛ ያደርጋል። በሌላም በኩል መንፈሣዊው አስተዳደር ከሕጎች ሁሉ ራሱን በማግለል በወንጌል ዙሪያ ብቻ የተገደበ አይደለም። መንፈሳዊው አገዛዝ የሕግን ጠቃሚነት አጥብቆ ይደግፋል። ውጪአዊውን የሕግ ሥራ አስመልክቶ ተግባራዊ የማድረግ

ኃላፊነት የምድር ባለሥልጣናት እንደሆነ በጥብቅ ያምናል። በዚህ ዕውነት ላይ ሊታከል የሚገባው መንፈሳዊውን ጉዳይ በሚለመለከት ሕጉ ጠቃሚ የሆነ ሌላ ተግባርም አለው። ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የሚመራ አስተማሪና ሞግዚት ነው። ይህ ተግባር በማናቸውም ምድራዊ በሆኑ ባለሥልጣናት የሚከናወን ነገር አይደለም። ይህ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ተግባር ነው (ገላ. 3፥24)።

## የምንኖርበት ነባራዊ ሁኔታ

አንዳንድ ጊዜ እኛ የምንፈልገው ዓይነት አስተዳደር ለማግኘት የማንችልበት ሁኔታ ይፈጠራል። በብዙ አገራት ውስጥ ሰዎች ፈጽሞ በማይወዱት አገዛዝ ሥር እየኖሩ ይገኛሉ። እንደዚህ ዓይነት አስተዳደር ከፍላጎታቸው ውጪ ተጭኖባቸው ወይም ደግሞ ከቀደሙ ትውልዶች የወረሱት ሊሆን ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ መኖር ምን ያህል ከባድ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ከዓለም አቀፍ አስተሳሰብ አንጻር እነርሱን ከውጪ ሆኖ በመሣሪያ በማገዝ ካሉበት አስከፊ ሥርዓት ነፃ ማውጣት አይገባም። እንደዚህ ዓይነት ጣልቃ ገብነት ‹‹ሁከት መፍጠር›› ወይም ‹‹ጠብ ጫሪነት›› በሚል ሥያሜ ነው የሚታወቀው። ኃይለኛና ጨካኝ በሆነ ምድራዊ አገዛዝ ውስጥ እንዲኖሩ የሚገደዱ ክርስቲያኖች ጉዳይስ? አሳሳቢ ጉዳይ ቢሆንም ጥያቄውን መመለስ የሚኖርብን በዚህ መልኩ ነው። ክርስቲያን ለሆኑ ሰዎች ሁኔታው እጅግም አስቸጋሪ ይሆናል። ይህንን መግለፅ የሚቻለው እንዴት ነው? ቀላሉ መንገድ አንድ ብቻ ነው። ይኸውም ክርስቲያኖች እንደመሆናቸው ክርስቶስ በልባቸው ያለ በመሆኑና እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ዜግነታቸው ደግሞ ዘላለማዊ ተስፋ ያላቸው በመሆኑ ነው (ዕብ. 13፥14)። ምንም እንኳ ውጪያዊ የሆነው ሕይወታቸው እጅግ አስቸጋሪ ሊሆን ቢችልም ለመኖር ግን ፈፅሞ እርባና ቢስ ነው ብሎ መደምደም አይቻልም። ይህንን ሁኔታ በሌላ መልኩ ስናየው ክርስቲያን የሆኑ ሰዎች የበለጠ የሚንገላቱ፥ የሚሰደዱና የሚቀጡ ከመሆናቸው

የተነሣ ለክርስቲያኖች ከሌሎች ወገኖች ይልቅ አስቸጋሪ ወቅት ሊሆን ይችላል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ጥሩ ዜጋ ሆነው ለመቀጠል ይጥራሉ። አገራቸውን በእግዚአብሔር ፊት በማቅረብ አገልግሎት ይሰጣሉ (ኤር. 29÷7)። ይህ ከሐዋርያትና ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማማ ነው (1 ጴጥ. 2÷18-20፤ 3÷13-17፤ ማቴ. 5÷11-12)።

## እንደ ክርስቲያን ማከናወን የሚገቡን ነገሮች

በችግሮች የተተበተቡ ቢሆኑም ምድራዊ ባለሥልጣኖቻችንን መቀበል÷ ማክበርና ማኅበረሰቡን እንዲሁም የአስተደዳደሩን መዋቅሮች መልካም እንደሆኑ ቢያንስ መልካምነት የሚታይባቸው እንደሆኑ አድርገን ልንመለከታቸው ይገባል። እንዲህ የምናደርግ ከሆነ አላስፈላጊ ወደ ሆነ ክስ አንሄድም (ሐዋ. 28÷19)። በእኛና በባለሥልጣናቱ መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ከሆነ በመጀመሪያ ስሕተቱ ምን ላይ እንደሆነ ለማስረዳት መሞከር÷ ለእውነትና ከሕሊናችን አንጻር ራሳችንን መከላከልና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እምነታችንን መግለፅ ሲሆን የዚህ ውጤት ካሰብነው በተቃራኒ ከሆነ ቅጣቱን በትሕትና÷ በብርታትና በደስታ መቀበል አለብን (ሐዋ. 5÷41)። ሌላ ይህንን በሚመለከት ሊዘነጋ የማይገባው ጉዳይ አለ። አሁን የምንነጋገርባቸው ‹‹ጉዳዮች›› ከማኅረሰቡ÷ ከሕጎቹ÷ ከፍርድ ቤቶች÷ ሕዝቡ ከሚያውቃቸው ሥርዓቶች ወይም ከሌላ የሚመነጭ ከሆነ ከሌሎች ዜጎች ጋር በመሆን ለዚህ ጉዳይ ተገቢ የሆነ መፍትሔ ለማምጣት መጣር ይኖርብናል። ይህ ለምሳሌ ያህል የፓርላማ አባላት በሚመረጡበት ወቅት÷ በጋዜጦች ላይ ክርክር በሚካሄድበት ወቅት ወይም ደግሞ በተለያየ ሁኔታ በሕይወታችን በሚከሰቱ ጉዳዮች ላይ ሊሆን ይችላል። በየመንገዱና ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው አደባባዮች ጡጫ÷ ዱላና ጥይቶችን መጠቀም ነገሮችን ከማባባስ ውጪ የሚፈይደው ነገር የለም። የተሻሉ መንገዶች ግን አሉ።

‹‹ሳትቻኩሉ ረጋ ባለ ሁኔታ ውስጥ መሆን ይኖርባችኋል

… በአንድ ሰው ላይ ቅሬታ የሚያድርባችሁ ከሆነ ፍርድ ቤቶችና ጠበቆች በሥራ ላይ አሉላችሁ። ጉዳዩን ለእነርሱ ያቅርቡ። ከዚህ የሚያልፍ ነገር የምትሹ ከሆነ ግን ሕጋዊነት ባለው ሸንጎ የሚወሰን ይሆናል›› (ሐዋ. 19÷36-39)።

እነዚህ ቃላት የተነገሩት ክርስቲያን ባልነበረ ባለሥልጣን ነው። የእርሱ ጥበብ ከክርስቲያኖች የሚልቅ ከሆነ አሳፋሪ ነው የሚሆነው። አብዛኛውን ጊዜ በተለያዩ አገሮች በሚተገበሩ የአገዛዝ ዓይነቶች መካከል ትልቅ ልዩነቶች አሉ። በዚያው አገር ውስጥ እንኳ በተለያዩ ጊዜያት ከፍተኛ ልዩነቶች ሊፈጠሩ ይችላል። እኛ የተጠራነው በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ለራሳችንም ሆነ ከእኛ በኋላ ለሚመጡት ሰዎች ሳይቀር የተሻለ አስተዳደር እንዲኖር ለማስቻል ተባብሮ ለመሥራት ነው። ይህ ከፍተኛ የሥልጣን ባለቤት የሆኑትን ፓርላማዎች÷ መንግሥታት÷ ፍርድ ቤቶች ወዘተ… እና ዝቅተኛ ሥልጣን ያላቸውን እንደ ወረዳ÷ ሸንጎና አውራጃ ምክር ቤቶችን ወዘተ… ይመለከታል። ዜጎች ራሳቸው በሥራው ውስጥ ተሳትፈው መልካም ነገር እንዲመጣ ካልጣሩ የተሻለ ለውጥ ከቶውንም ሊመጣ አይችልም። ለመሆኑ የትኛው ዓይነት ምድራዊ አገዛዝ ነው የሚሻለው? እዚህ ቦታ ላይ ይህንን ጥያቄ በሚመለከት የተለያዩ ማስረጃዎችን በማቅረብ ምላሹን ሙሉ በሙሉ ለመስጠት አንችልም። ይህ ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ የሚችለው አንዳንድ አጠቃላይ የሆኑ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ነው። ስለ ሆነም ቀለል ያለ የአገዛዝ ኃይልን የሚጠቀም አገዛዝ የተሻለ ነው፤ ግድ ከማይሰጠው አገዛዝ ይልቅ ለሰው የሚያስበው አገዛዝ በእጅጉ የተሻለ ነው፤ ራስን በራስ ማስተዳደር አንድ ወንድ ወይም አንዲት ሴት የበላይ ከሚሆኑበት የአንድ ፓርቲ አምባገነን አገዛዝ ይልቅ በእጅጉ ይሻላል የሚሉ አሳቦችን መጥቀስ ይቻላል። ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ዓመታት ካሳለፈችው ልምድ የተቀበለችው ዕውነታ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እጅግ መልካም መሆኑን ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩትን የተወሰኑ የጥንት ጊዜዎችን ብንተዋቸው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እያደገ የመጣው ክርስቲያናዊ በሆኑ የአስተሳሰብ ተጽዕኖዎች÷ ከክርስቲያናዊ ሥነ

ምግባርና ከክርስቲያናዊ ወንድማማችነት የተነሣ ነው። ከዚህ ተጽዕኖ የተነሣ ብቻ ነው «ሰብአዊ መብት» እና «ሰዋዊ እሴት» የሚሉትን አሳቦች በአግባቡ ልንረዳ የምንችለው። በዚህ መስክ ውስጥ ክርስቲያኖች ሁሉ ለምሳሌ ፍትህን÷ ሰብአዊ መብትን÷ የበጎ አድራጎት ሥራን፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን÷ የዕርዳታ ሥራ ወዘተ... በሚመለከቱ ጉዳዮች ለዓለም ከፍተኛ አስተዋፅዖ ሊያደርጉ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ በአግባቡ ከተሠራባቸው ክርስቲያናዊ አስተሳሰቦች ዓለማዊ በሆነው ማኅረሰብ ውስጥ የትሕትናን÷ ከራስ ወዳድነት መንጻትንና ሌላውን የማገዝና የማገልገል አሳብን ያሰርጻሉ። ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ብቻ ነው እንዲህ ዓይነት ነገሮችን ሊያስገኝ የሚችለው። በሌላ መልኩ በዚህ ዓለም ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን ከፖለቲካ ሥርዓት እና ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲና መንግሥት ልንጠብቅ ፈጽሞ አይገባንም። ባለሥልጣናት ሁሉ የሰው ስብስቦች ናቸው። ብዙውን ጊዜ በአስተሳሰባቸውና በድርጊታቸው መዋዠቅ ይስተዋልባቸዋል። አብዛኛውን ጊዜ በሥልጣን ላይ በሚገኙ ሰዎች ላይ የሚታየው ሥጋት ሊያጠቃቸው ስለሚችል ግላዊና ምስጢራዊ የሆነ ምኞታቸው ወይም የዘመዶቻቸው ጉዳይ÷ ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንዲሁም በሌሎች ብዙ ነገሮችና ዘመኑ በሚያመጣው የመጠራጠር ሕይወት ሳይቀር ተጽዕኖ ሊያድርባቸው ይችላል። ቢሆንም ክርስቲያኖች የተጠሩት የዓለም ብርሃን ይሆኑ ዘንድ ነው። ስለ ሆነም ጥሪ የተደረገላቸው ከዚህ አንጻር እንዲሠሩም ጭምር ነው። «ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል፤ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች» (ዮሐ. 9÷4)። ይህ እንግዲህ የክርስቲያኖች ሁሉ አቋም ነው። በምድራዊ አገዛዝ ሥር እንደሚኖሩ ዜጎች ራሳቸውን ለእነዚህ ሕጎችና ባለሥልጣናት ማስገዛት ይኖርባቸዋል። ይህ ተግባር ደግሞ በመንፈሳዊ አገዛዝ ውስጥም እውቅና ማግኘት ይኖርበታል። የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች እንደመሆናቸው መጠን ለእግዚአብሔር መንግሥት ሕጎች ራሳቸውን ማስገዛት የሚኖርባቸው ሲሆን ይህም ተግባር በምድራዊው አገዛዝ ዕውቅና

የማይኖረው ከሆነ የአንድ ወገን አገዛዝ ወይም አምባገነንነት ይሆናል ማለት ነው። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚገኙት ‹‹ተግባሮች›› እና ‹‹ሕጎች›› በሌላ ቦታ ከሚገኙት ሕጎች ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው አድርጎ ማሰብ ስሕተት ነው። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚገኙት ‹‹ሕጎች›› በእግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋ የተቃኙ ሲሆኑ ኃጢአተኛ የሆኑ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገቡና ከእምነት የተነሣ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ የሚያስችል ነው።

# ምዕራፍ 4

# ሥነ ምግባርና ግብረ ገብነት

ብዙ ጊዜ ‹‹ሥነ ምግባር›› እና ‹‹ግብረ ገብ›› የሚሉትን ቃላት በተመለከተ አንዳንድ ግራ መጋባቶች ይታያሉ። በሁለቱ ቃላት መካከል ያለው ልዩነት ወይም አንድነት ምንድነው? አብዛኛውን ጊዜ በአማራጭነት ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያል። ማለትም አንዱ ቃል ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ በሌላኛው ቃል ለመተካት ይቻላል ማለት ነው። ሆኖም በተለያዩ የአነጋገር ደረጃዎች ላይ በሁለቱ ቃላት መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት እንዲኖር ማድረግ እንችላለን። አብዛኛውን ጊዜ ‹‹ሥነ ምግባር›› የሚለው ቃል የድርጊታችንን አካሄዶች የምናስገዛበት መርሆዎችንና ከእነዚህ መርሆዎች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን የሚመለከት ሲሆን እነዚህን የመሳሰሉ መርሆዎችን በግል ሕይወታችን ተግባራዊ ስናደርጋቸው ‹‹ግብረ ገብነት›› ወይም ‹‹ግብረ ገብ›› በመባል ይታወቃል። እዚህ ስፍራ ላይ ነው እንግዲህ እነዚህን ሁለት ቃላት በሚመለከት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የምንገባው። በሕይወታችን የተወሰኑ ክፍሎች ውስጥ ሥነ ምግባራዊ የሆነ ድርጊት ሲታይብን ‹‹ከሥነ ምግባር ጋር የተያያዘ ክንውን›› ብለን የምንጠራው ከሆነ ከዚህ ተቃራኒ የሆነ ነገር ኢ-ግብረገባዊ ነው ማለት ነው። ሆኖም በዛሬው ጊዜ ‹‹ኢ-ግብረገባዊ›› የተሰኘው ቃል እያገለገለ ያለው ከወሲብ ጋር በተያያዘ ከሚታይ መጥፎ የአኗኗር ዘይቤ ጋር ነው። በዚህ ረገድ ያለውን ብዥታ ለማጥራት ጥሩ ደረጃ ላይ ስለማይገኙ የአኗኗር ዘይቤዎች በምናወሳበት ወቅት ‹‹ኢ-ሥነ ምግባራዊ›› ብለን ልንጠራቸው እንችላለን። ከዚህ በኋላ ግራ መጋባትን ለማስወገድ እንችል ዘንድ ‹‹ኢ-ሥነ ምግባራዊ›› የተሰኘውን ቃል ብንጠቀም ይሻላል።

## ‹‹ትክክል›› እና ‹‹ስሕተት›› የሆነውን ነገር የምናውቀው እንዴት ነው?

ብዙ ሰዎች እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ውሳኔ ሊያገኙ

የሚችሉት ከጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ አንጻርና ‹‹አጠቃላይ በሆነ የሥልጣኔ ሂደት›› ወይም በተወሰኑ የፍልስፍና አስተሳሰቦችና እነርሱ ሊጠቅሷቸው በሚፈልጓቸው ተመሳሳይ ነገሮች ውስጥ ነው ይላሉ። ከዚህ ‹‹ዕድገት›› ጀርባ ያለው ማን እንደሆነ በሚጠየቁበት ወቅት ምላሽ ለመስጠት ያዳግታቸዋል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ በአጠቃላይ ስለ ‹‹አስተሳሰቦች›› እና ስለ ‹‹ዕድገት›› ወዘተ... መናገርን ይመርጣሉ።

ምንም ዓይነት ቃላት ብንጠቀምና የትኛውንም ዓይነት አሳብ የመደገፍ አዝማሚያ ብናሳይ በሥራ ላይ ያሉ ሥነ ምግባራዊ መመዘኛዎችና መርሆዎች መኖራቸው ግልጽ ይመስላል። ለመሆኑ እንዴት ነው ተግባራዊ የሚሆኑት? በምን ዓይነት መሠረት ላይ ነው የሚመሠረቱት? ከአንዳንድ እጅግ ተወዳጅ ከሆኑ አስተሳሰቦች በስተቀር አንዳንድ ጊዜ የማይነበብ፣ ለመረዳትና ለማብራራት አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮች ቢኖሩም ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ምዕተ ዓመታት በብዙ የዓለም ክፍሎች ውስጥ ሥነ ምግባራዊ ትምህርትን የቀረጹትንና እንዲያብብ ያደረጉትን ሁለት የአስተሳሰብ ዘርፎች እዚህ ስፍራ ላይ እንመለከታለን።

አንዱ መርህ እንዲህ ይላል፦ ‹‹ለአንድ ሰው ጠቃሚ ሆኖ የሚገኝ ነገር ሁሉ መልካም ነው›› ወይም ‹‹ግለሰብን ለማሳደግ የሚጠቅም ነገር ሁሉ ከሥነ ምግባር አንጻር መልካም ነው።›› ሁለተኛው መርህ ደግሞ እንደዚህ ይላል፡ ‹‹እውነተኛ ርኅራኄን የሚበያረታታ ነገር ከሥነ ምግባር አንጻር መልካም ነው።›› እነዚህ ሁለቱ አስተሳሰቦች በከፍተኛ ደረጃ እርካታን የማይሰጡ ናቸው። እነዚህ አመለካከቶች እጅግ ግላዊነት የሚያጠቃቸው ከመሆኑ የተነሣ በብዙ የዓለም ክፍሎች ውስጥ ለቤተ ሰብና ለማኅበራዊ ሕይወት ተግዳሮት የሚፈጥሩና አስፈሪም እየሆኑ የመጡ ይመስላል። ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ የአስተሳሰብ መሥመሮች ከሌላ አስተሳሰብ አንጻር ፈጽሞ የሚያረካ ነገር የላቸውም፣ መሰጠት ለሚገባቸውም ጥያቄዎችም

ምላሽ አይሰጡም። ይልቁንም የተለያዩ ቃላትን የሚጠቀሙ ቢሆንም ምላሽ ለመስጠት የሚጥሩት ያንኑ በመደጋገም ነው። ሁለተኛውን ጥያቄ ይመልሳል ብለን የምንገምተው ምላሽ በትንሹ ብንለውጠው (ሁለቱን አማራጮች) ይህ ጉዳይ ግልጽ እየሆነልን ይመጣል። ጥያቄ ከጠየቃችሁ በኋላ ምላሽ ስጡና መልሳችሁ አንብቡት። ‹‹ቃሉ እንደሚለው ርኅሩኅ ለመሆን ለሚሻ ሰው መፈጸም የሚገባው ትክክለኛ ነገር ምንድነው?›› ሁሉም ነገር የሚያጠነጥነው ‹‹ርኅሩኅ›› ወይም ‹‹መራራት›› በተሰኙት ቃላት ዙሪያ ነው። ‹‹ርኅሩኅ›› መሆን ‹‹ርኅራኄን›› ያሳድጋል ማለት ነው። እንደዚህ ዓይነት አባባል ብዙም ስሜት ላይሰጥ ይችላል።

ሦስተኛው መርሆ ከዚህ በፊት ከተጠቀሱት ከሁለቱ ጋር ቅርብ የሆነ ግኑኝነት አለው። ‹‹ከሥነ ምግባር አንጻር ትክክል የሆኑና የሰዎችን ደስታ የሚያበዙ ነገሮች ብቻ ናቸው›› ለዚህ መርሆ አማራጭ ይሆን ዘንድ ስሜታዊ ነገሮች ላይ አጽንዖት ይሠጣል። ለምሳሌም በተለያዩ የሕይወት ሂደቶች ውስጥ የሚገኙ የደስታ ልምምዶችን ማለት ነው። ሁለተኛው አማራጭ ደስታን አስመልክቶ በዓለማዊና በአካላዊ ስሜቶች ላይ አጽንዖት የሚፈጥር ልምምድ ነው። በአንዳንድ ሁኔታ በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙት ሦስት ነገሮች ከፖለቲካዊ አመለካት አንጻር ሲታዩ ኖሮአል። ‹‹መርሆው ሊሆን የሚገባው ብዛት ላላቸው ሰዎች ከፍተኛ የሆነ ደስታ ሊያመጣ የሚችል ሊሆን ይገባዋል›› የሚል ነው።

በመጨረሻ ላይ የተጠቀሱት እነዚህ ሦስት አማራጮች በሥራ ላይ ከሚገኙ ብዙ ምሳሌዎች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። ስኬታማ ያልሆኑ ከመሆናቸው የተነሳ ሁሉም ቢሆን ሌላ ላቅ ያለ መርሆ የሚያስፈልግ ስለ መሆኑ በተግባር ያሳያሉ። የሚያረካ ዓይነት ሥነ ምግባራዊ እሴቶችን ለማየት የምንሻ ከሆነ ከዚህ በታች የሚገኘውን ዓይነት ጥያቄ እንመልስ፤ ይኸውም፡ -መስቀልኛ የሆነ የሕይወት መስመር ላይ በምንሆንበት ወቅት ከሥነ ምግባር አኳያ ተገቢ የሆነ ምርጫ ለማካሄድ ይቻለን ዘንድ ምን ዓይነት መርሆ መከተል ነው የሚኖርብን? ለዚህ

ጥያቄ የተሰጡት መልሶች የትኞቹ ናቸው? ብዙዎቹ አመክንዮ የሚል ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ። ከዚያ በኋላ ሰው ከአመክንዮ አንጻር ከራሱ ጋር ሊሟገት የሚችል እንደሆነና ትክክል የሆነውና ያልሆነው ነገር ላይ ለመድረስ እንደሚችል ያስባሉ። ይህ ትክክለኛ የሆነ መነሻ ነው? የራሳችንን ፍላጎትና የሌሎቹን ፍላጎት በማሟላት መካከል እንዲሁም የአጭር ጊዜና የረዥም ጊዜ መሻቶቻችንንና ጥያቄዎቻችንን በተመለከተ ትክክለኛ የሆነ መንገድ ለማግኘት ይቻለናል? እነዚህን መርሆዎች በሚመለከት ባካሄድነው ውይይት ውስጥ የሥነ ምግባር ጉዳይን በተመለከተ በዘመናት ሁሉ እጅግ አስቸጋሪ ስለ ሆነው ጉዳይ ልንወያይ ነው። ላቅ ያለ መርህን በተመለከተ ከላይ የተነሳው ጥያቄ ከዚህ በታች በተመለከተው መልኩም ሊገለፅ ይችላል። በሥነ ምግባር ረገድ የላቀ ነው የሚባለውን መርሆ በሚመለከት ውሳኔ የሚያስተላልፈው ማነው? ራሱ ሕዝቡ ነውን? ለምሳሌ ያህል በአገር ውስጥ ቢሆን በአገሪቱ ውስጥ ያለው የትኛው አካል ነው የሚወስነው? ከዚህ በታች በሰፈረው መልኩ መፍትሔ እንደሆነ የሚያስቡት ጥቂት ሰዎች ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚያ ይልቅ ስለ ‹‹ግላዊ ነፃነት›› ስለ ‹‹ግል ታማኝነት›› ስለ ‹‹አብላጫ ድምፅ›› እና ከእነዚህ ጋር ስለሚመሳሰሉ ነገሮች መናገር ይመርጣሉ። በዚህ ሁኔታ ‹‹የድምፅ ብልጫ›› ማለት ተመሳሳይነት የሆነ ዋጋና ጠቀሜታ ያላቸው ብዙ አሳቦች ተቀባይነት ከማግኘታቸው የተነሳ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ለውድድር እንዲቀርቡ ይደረጋሉ ማለት ነው። ከዚያ በኋላ ጥቂት ቆይቶ ትልቁ ችግር ራሱን ይገልጣል። ለውድድር እንዲቀርቡ የተደረጉት ማናቸውም አሳቦችም ሆኑ ሥርዓቶች መንገዱን የማሳየት አቅም የሌላቸው ወይም በሕዝቡም ሆነ በማኅበረሰቡ ላይ ጤናማ የሆነ ተጽዕኖ አይፈጥሩም። ከዚህ ይልቅ እነዚህ ለውድድር የቀረቡት ብዛት ያላቸው አሳቦች የግብረ ገብ ዝቅጠት ሊኖር በሚችልበት አቅጣጫ በጋራ ሆነው ሥራን ይሠራሉ። ከዚያ በኋላ ምን ሊደረግ እንደሚገባው በማሰብ ሁሉም ተስፋ የመቍረጥ ስሜት ውስጥ ይገባሉ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የሚወድቁ ከሆነ

ሰዎች ሌላ መጥፎ በሆነ አሳብ ተጠቂ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ እንግዲህ ‹‹ጠንካራ የሆነ አመራር›› ይፈልጋል፤ መንግሥትም ትክክል ስለሆነውና ስላልሆነው ነገር ተገቢውን መመሪያ የመስጠት ኃላፊነትን መውሰድ ይገባዋል። ይህ በፖለቲካው ረገድ ሲገለፅ አብዛኛውን ጊዜ ‹‹የሕግና የሥርዓት መኖር›› የሚል ትርጓሜ ይኖረዋል። አብዛኛውን ጊዜ ይህ ለአምባገነንነት የሚሰጥ የሽፋን ሥም ነው። እነዚህ የተከበሩ የሥነ ምግባር መርሆዎች ስፍራቸውን በሚለቁበት ወቅት በብዙ ሕዝብ ላይ የሚፈጸም የአምባገነንነት ሁኔታ ይከሰታል። ከሥነ ምግባር ረገድ ሕዝቦቹ ግራ የመጋባት ስሜት ውስጥ በሚገቡበት ወቅት በአንድ ፓርቲ አገዛዝ ተጽዕኖ ሥር ይወድቃሉ። አዲስ በሆኑት ሁኔታዎች ውስጥ ብዙውን ጊዜ ነገሮች የከፉ ይሆናሉ። የሥነ ምግባር መለኪያዎቹ ካለማደጋቸውም ባሻገር አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም በአደገኛ ሁኔታ እያሽቆለቆሉ ይሄዳሉ። ይህንን አስመልክቶ ጥቂት ግንዛቤ የሚኖረን ከሆነ ተጨማሪ ጥናት ሊያስፈልገው የሚችል ትልቅ የሥነ ምግባር ጥያቄም እንዳለ እንገነዘባለን።

## የሥነ ምግባር ጉዳዮችን በሚመለከት ትክክል ነው ወይም ስሕተት ነው የሚል ውሳኔ የማስተላለፍ ኃላፊነት የተሰጣቸው እነማን ናቸው?

የሥነ ምግባር ጉዳዮችን በሚመለከት መንግሥት ወይም ከፍተኛ የሆኑ ባለሥልጣናት ውሳኔ ሊያሳልፉ ይገባል የሚለው አስተያየት ምንም መፍትሔ ሊያመጣ አይችልም። እንደነዚህ ዓይነት ባለሥልጣናት መርሆአቸውን የሚያገኙት ከየት ነው? ትክክል የሆነውንና ትክክል ያልሆነውን ነገር ለይተው ከወሰኑ በኋላ እነርሱ በወሰኑት መሠረት ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆኑትን ወይም ባህርያቸውን በዚህ ረገድ ያላስተካከሉትን ሰዎች በሙሉ ለቅጣት መዳረግ ተገቢነት ይኖረዋል?ይህ ለብዙ ሰዎች የሚቀላቸው መንገድ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የሌለው ቢሆንም እንደዚህ ዓይነት መፍትሔ ከሥነ ምግባር አንጻር ተቀባይነት

የሌለው በመሆኑ ሊወገድ ይገባዋል። በማኅረሰብ ውስጥ ለሚገኙ ግለሰቦች የተዘጋጀ መርሆ ከሌለና ይህ መርሆ ደግሞ በእነርሱ ተቀባይነት የማይኖረው ከሆነ እንዴት የዚህ ዓይነት መርሆ በአገሪቱ ባለሥልጣናት ዘንድ ሊታወቅ ይችላል? እንደዚህ ዓይነት መርሆ የሥልጣን ጉዳይ ብቻ ነው? እንደዚህ ዓይነት መርሆ የማይታወቅና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት የማይኖረው ከሆነ በአንድ የመንግሥት ቢሮ ውስጥ የሚገኝ ወይም ከተደበቀበት የሚወጣ ከሆነ የሥነ ምግባር መመሪያ አካል ሆኖ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው እንዴት ነው? በማኅበረ ሰቡ ውስጥ በሚገኙ አባላት አስተሳሰብና ሕይወት ላይ በጎ የሆነ ተጽዕኖ ሊኖረው የሚችለውስ እንዴት ነው? በባለሥልጣናቱ አማካይነት ጉዳዩ በጉልበት እንዲጫንባቸው የሚደረግ ከሆነ ዝቅተኛ የሆነ አክብሮት በሚሰጠው መልኩ የሚካሄድ ሲሆን ወደ ከፋ ሁኔታ ከተለወጠም ተቃውሞ የሚገጥመውና ጥላቻ የሚያተርፍ ሊሆንም ይችላል።

መንግሥት ወይም የፖለቲካ ባለሥልጣናት የሥነ ምግባር መርሆዎችን አስመልክቶ ራሳቸው ኃላፊነቱን እንዲወስዱ ማድረግ እውነት ለመናገር ፈፅሞ መፍትሔ ሊሆን አይችልም። በአንድ አገር የሚገኙ ዜጎች ከንቃተ ሕሊናቸው አንጻር ስለ ሥነ ምግባር ምንም ዕውቀት የሌላቸው ከሆነ አንድ መንግሥት ትእዛዞችንና ምክሮችን ከመንግሥት ቢሮዎች በጽሑፍ እያሳተመ ችግሮቻቸውን ሊፈታላቸው አይችልም። በመሪነት ቦታ ላይ የሚገኙትን ጥቂት ባለሥልጣናት ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ፡ ለምሳሌ በሆነው ቢሮ ውስጥ የሚገኙና ‹‹ግብረ ገብ፤ ሕግና ደንብን›› በሚመለከት ከፍተኛ ኃላፊነት በተሰጣቸው ሚኒስትሮች ላይ በመደገፍ የሰዎች አላዋቂነት ተዓምራዊ በሆነ መንገድ በመልካም ሥነ ምግባር ይተካል ብሎ ማሰብ ስሜት የሚሰጥ ነገር አይደለም። ይህ በሌላ አነጋገር በመንግሥት ደረጃ የሚሾሙ ሰዎች በሥልጣን ላይ በመኖራቸው ብቻ ሥነ ምግባርን በሚመለከት ዝቅተኛ የሆነ አስተሳሰብ የላቸውም ማለት ነው። ሥነ ምግባራዊ የሆነ ዕውቀትና ብርታት በእነርሱ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ ምናልባት ይህ ሊሆን የሚችለው ሥነ ምግባርን በሚመለከት ራሳቸው

ባላቸው አቋምና በራሳቸው በሰዎቹ ውስጥ ከተቀመጠው መልካም ነገር የተነሳ ነው ማለት ነው። ስለሆነም ከሁሉም ዜጎች የሚፈለጉ ነገሮች ዕውቀት፣ኃላፊነት፣ትብብርና ከሁሉም በላይ መርሆዎችንና የሕይወትን ግብ የመገንዘብ ችሎታ ናቸው። ‹‹ሕዝብ አሳቡን እንዲሰጥባቸው›› ተብሎ ሥነ ምግባርን ሊመራ የሚችል መርሆን የማውጣት አሳብ ቀርቦ ነበር። ይህ ማለት በጋዜጦች፤ በመጻሕፍት፤ በሬድዮና በቴሌቪዥን አማካይነት ወዘተ... ውይይቶች ይካሄዱ ነበር ማለት ነው። ይህንን እንደ መፍትሔ አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች ያሉባቸውን ችግሮች በዚህ መንገድ በግልጽ የሚወያዩ ከሆነ የትኛው መርሆ በብዙ ሰዎች ሊወደድ እንደሚችል ለማወቅ ይቻላል። ይህ ስልት በጉዳዩ ላይ ውይይት ተደርጎ ሌላ የተሻለ አማራጭ እስኪገኝ ድረስ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ይህ መርሆ ሊያገለግል ይችላል ብለው ሊያስቡ ይችላሉ።

እንደዚህ ዓይነት አስተያየት ግን ችግር ይዞ ይመጣል። በሕዝቡ ዘንድ እየተሠራበት ያለ የሚልቅና የሚገዙለት መርሆ ከሌለ ተከራካሪዎች ምን ዓይነት መርሆዎችን ሊከተሉ ነው? የራሳቸው አሳቦች ከሌሎቹ ይልቅ የበላይነት እንዳላቸው ለማሳመን ምን ዓይነት የመከራከሪያ ሥልት ይጠቀማሉ? በእንደዚህ ዓይነት ውይይቶች ወቅት ሁለት ኃያላን ነገሮች ማጣቀሻ ይሆናሉ። እነዚህም የአመክንዮ ኃይልና አብዛኛውን ሕዝብ የሚወክለው ሥልጣን ነው። ሰዎች ‹‹አመክንዮ›› የተሰኘውን ነገር በሚጠቅሱበት ወቅት ‹‹አመክንዮ›› መደገፍ ወይም ትርፍ ማግኘትን ሁሉ የሚመለከት ፍቺ እንዳለው ይዘነጋሉ። ‹‹አመክንዮ›› በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ለተካሄዱ አስከፊ የሆነ ክንውኖች ተጠያቂ ነው። ለምሳሌ ያህል ሊታገሏቸው ያልፈለጉትን ወይም በዚህ ረገድ ታሳቢ የተደረጉ የሰው ልጆችን ማጥፋት፤

ሰዎች ‹‹የአብዛኛው ሕዝብ ሥልጣን›› በሚሉበት ወቅት የዲሞክራሲ ሥርዓት ማለታቸው ነው። ምናልባትም በዚህ መልክ ይሆናል ሊያስቀምጡ የሚሞክሩት። ማንኛውም ነገር

‹‹መወሰን የሚኖርበት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ነው›› ይህ አሳብ መልካም ቢመስልም ብዙ ችግሮች ግን አሉበት፡፡ ከብዙ ጉዳዮች የተነሳ እነዚህን ለምርጫ ማቅረብ አይቻልም፤ ወይም ሰዎች የሚመርጡት ነገር ካለመኖሩ የተነሳ ምርጫ ማካሄዱ ጊዜን ከማጥፋት ውጪ የሚፈይደው ነገር አይኖርም፡፡ ጉዳዩ ቀደም ሲል ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ሰዎች ጉዳዩን ይቀበላሉ ወይም አይቀበሉትም፡፡ ጥቂት ምሳሌዎች ይህንን ሊገልፁት ይችላሉ፡፡ ሁሉም ሰው ኦክሲጂን የሚያስፈልገው ስለ መሆኑ፤ለዜጎች ሁሉ ምግብና መጠለያ እንደሚያስፈልግ ወይም ደግሞ ሕዝባዊ በሆኑ ጉዳዮች ለምሳሌ እውነትና ታማኝነት ወዘተ... አስፈላጊ ስለ መሆናቸው ምርጫ ማካሄድ አስፈላጊነት የለውም፡፡ ባለሥልጣናቱ ሊወያዩ የሚገባቸው የእነዚህን ጉዳዮች አስፈላጊነት በተመለከተ ሳይሆን እነዚህ ነገሮች በምን መልኩ በሥርዓት መካሄድ እንደሚገባቸው ነው፡፡ ታማኝነትን በተመለከተ ድጋፍ በመሥጠት ስለ እርሱ ከማስተማር ውጪ ኅብረተ ሰቡን ታማኝ መሆን ይሻላል ወይስ ታማኝ አለመሆን ይሻላል በሚል ርዕስ ላይ እንዲከራከሩ ማድረግ የሚያዋጣ አይሆንም፡፡ ይህ ዋና ዋና ለሆኑት ለሁሉም የሥነ ምግባር መርሆዎችም ይሠራል፡፡ ስለ ሥነ ምግባራዊ እሴቶችና አማራጮች በምንነጋገርበት ወቅት ሁሉም ቢሆኑ ክፋትና መልካምነት፤ትክክል የሆነና ያልሆነ ነገር፤እውነት የሆነና ያልሆነ ነገር ይካተትበታል፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ መንፈሳዊ ነገርም በእጅጉ አለበት፡፡ እኛ ሥጋና ቁስ እንደሆንን ብቻ አድርገን በመገመት ሙግት መግጠሙ ተገቢነት የለውም፤ አይገባምም፡፡ ስለሆነም በዚች ምድር ላይ ‹‹በአመለካከቶች›› ‹‹በሙግቶች›› ወይም ‹‹በምርጫዎች›› ውሳኔ ሊደረስባቸው የማይችሉ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ በሚቃወሙትና በማይቃወሙት ሰዎች መካከል በተወሰነ ጉዳይ ላይ ምርጫ እንዲካሄድ ለማድረግ አንችልም፡፡ ይህ ነገር ከፍተኛ ለሆኑ ምድራዊ ባለሥልጣናትም ይሠራል፡፡ ትክክለኛ በሆነና ትክክለኛ ባልሆነ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ከዚህ በታች በሰፈረው መልኩ እንኳ ቢቀመጥ በሌላ ሰው አመለካከት ለመጓዝ

መገደድ የለብንም፤ ‹‹በእኔ መሥሪያ ቤት ቋሚ በሆነ መመሪያ›› መሠረት ሁሉም ዜጎች --- ይኖርባቸዋል›› እዚህ ላይ የተባለው ነገር ትክክልና ስሕተት ከተሰኙት ዋና የሥነ ምግባር መርሆዎች ጋር የተያያዘ እንጂ ለሕጋዊ ባለሥልጣናት የሚሰጠውን ዓለማዊ የሥራ ድርሻ ሁሉ የሚያካትት አለመሆኑ በእጅጉ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል። ዲሞክራሲ በታሪክ ውስጥ በሥራ ላይ መዋል ከጀመረ አጭር ጊዜ ያስቆጠረ ሲሆን ሥነ ምግባር ግን የሥርዓቱን በአገዛዝ ዓይነቶች መካከል ልዩነት ሳያደርግ በዓለም ላይ በሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ ዘንድ ለዘመናት ትምህርት ሲሰጥበት ኖሯል። በየትኛውም ዓይነት የአገዛዝ ሥርዓት ሥር ቢገኙም ሥነ ምግባርና ግብረ ገብ በሰዎች ሁሉ ዘንድ መኖር አለባቸው። ስለዚህ መርሆዎቹ በክርክር ወይም አንዱን በመደገፍና በመቃወም በሚካሄዱ የምርጫ ቆጠራዎች ላይ መደገፍ አይችሉም። ይልቁንም ይህ እውነታ በሰዎች ሁሉ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ይኖርበታል። ትክክለኛ በሆነና ባልሆነ፤መልካምና ክፉ ፤እውነትና እውነት ባልሆነ ነገር መካከል ልዩነት አለ። ከዚህ በኋላ አንድ ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። እርሱም ይህንን ወይም ያንን ጉዳይ በተመለከተ እነዚህ መርሆዎች ከእኛ የሚፈልጉት ነገር ምንድነው? የሚል ነው። ከዚህ አንጻር ልንመራበት የሚገባን መርሆ አስቀድሞውኑ በእጃችን ላይ አለ። ቀድሞውኑ በሥራ ላይ ለሚገኙት መርሆዎች ተገዢዎች ስለሆንን ራሳችንን ለመልካምና ለክፉ ነገሮች ጌቶች እንደሆንን አድርገን እንድናስብ አልተፈቀደልንም።

በዓለም ዙሪያ ሁሉ የታመነበት ነገር ቢኖር ከአገዛዞች ሁሉ ዲሞክራሲ ተመራጭ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ሆኖም ሥነ ምግባራዊ መርሆዎችን የምንቀንስበት ከሆነ ሊንደገፍበት የማንችለው ቀጭን ዘንግ ይሆንብናል። ዲሞክራሲ ራሱ ባዘጋጃቸው ሕጎች መሠረት ራሱን የሚያስተዳድር ሥርዓት ነው። ከዚህ ነጥብ ፈቀቅ የምንል ከሆነ ማለትም ሕዝባዊ ከሆነ አገዛዝ የምናፈገፍግ ከሆነና ከውስጡ የሥነ ምግባር መርሆዎችን የምናስወገድ ከሆነ የራሳችን ጥያቄ እንደ መልስ ሆኖ ሊቀርብልን ይችላል ማለት ነው። ‹‹እንደ ጥያቄው ሁሉ መልሱም እንዲሁ ነው›› ማለት

ነው። በመጨረሻም ይህ በሥነ ምግባር ረገድ ወደ ‹‹ብዛሃነት›› ይለወጣል። ይህም በጣም ተራ ወደ ሆኑት የተለያዩ የትክክልና የስሕተት መለኪያ መርሆዎች ይመራናል፤ በሌላ አነጋገር ምንም ነገር በተለይም ሃይማኖትና ግብረ ገብ ምንም ዋጋ የላቸውም ወደሚለው ጅምላ አመለካከት ይወስደንና ‹‹እኛ ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን ነገር ለማወቅ ስለማንችል በሚመጣው በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ መወሰን አለብን›› ወደሚለው ሁኔታ ያደርሰናል። ይህ አመለካከት አብዛኛውን ጊዜ እንደዚህ ዓይነት አስተሳሰቦች በሚከተለው ሁኔታ ሊገለጹ ይችላሉ፤ ‹‹አንድ ሰው ትክክል በሆነውና ባልሆነው ነገር መካከል ልዩነት ሊያደርግ አይችልም። ሁሉም ነገር የሚወሰነው በሁኔታዎች ነው።››

ዲሞክራሲ በዚህ መልኩ የሚሠራ ከሆነ ማለትም ትክክል የሆነውንና ያልሆነውን ነገር የመወሰን ኃላፊነትን ራሱ የሚወስድ ከሆነ ሊያደርግ የሚችለው አስተዋፅዖ ቢኖር ሥነ ምግባርና ግብረ ገብ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያሽቆለቁሉ በማድረግ በአጠቃላይ ማኅበረሰቡን ለመበታተን አደጋ ይዳርጋል። ከጊዜ በኋላም ይሁን በወቅቱ የዚህ ዓይነት ሁኔታዎች የሚያመሩት መሪዎቹ ከራሳቸው ዕይታ አንጻር ሕዝቡ ትክክል የሆነውን ወይም ያልሆነውን ነገር እንዲቀበል የሚያስገድዱት ሲሆን ሥልጣን ያለተወዳዳሪ የሚያዝ ይሆናል። በዘመናት ውስጥ ለብዙ ዓይነት አምባገነንነቶች መሠረት የሆናቸው የሥነ ምግባር መርሆዎችና እሴቶች ተፈላጊነት ማጣታቸው ነው። የሥነ ምግባር ጉዳዮችን አስመልክቶ ‹‹ለፍፁም ነፃነት›› ይሠሩ የነበሩ ሰዎች የራሳቸውን ፍላጎትና መርሆዎች በግዴታ ሊጭኑባቸው በሚሹ አምባገነኖች ተሸንፈው ባሪያዎች ሆነዋል። የባርነታቸው ትልቅ ምልክትና ‹‹የአዳኞቻቸው›› ታላቅነት በሚገልጸበት መልክ ‹‹ለነፃነታቸውና›› ‹‹ከተጽዕኖ ውጪ›› እንደሆኑ ለመሆናቸው አምባ ገነኖቹን ለማመስገንና ለማሞገስ ይገደዳሉ። ዛሬ በምንገኝበት ዓለም ውስጥ እንኳ ይህንን የሚያደርጉና በላያቸው በጉልበት ስለተጫነው ‹‹ነፃነት›› ምስጋና የሚያቀርቡ አሉ።

ባለፉት ጊዜያትም ሆነ አሁን በምንኖርበት ዘመን ሥነ ምግባርን በተመለከተ እንደዚህ የሚወላውል አቋም እንዳለ የምንገነዘብ ከሆነ ከዚህ ዓይነት ውሸትና ደስታ ከማይሰጡ ነገሮች ይልቅ ሌላ የተሻለ መንገድ ማግኘት ይቻላል? የሚል ጥያቄ መጠየቅ ተገቢነት ይኖረዋል።

## መውጫ መንገድ አለ

ይህንን መንገድ ለማግኘት የምንሻ ከሆነ እውነቱን ለማግኘት መጣርና መጓጓት ይኖርብናል። ከፍተኛ የሆነ ዋጋ ለመክፈልም መዘጋጀት ይኖርብናል። እርሱን በገንዘብ ለመግዛት የማይቻል ቢሆንም በሌላ መንገድ መክፈሉ ግን አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። እጅግ የምንወዳቸውንና ከጊዜው ጋር የሚሄዱ እንኳ ቢሆኑ ቀድሞ በእኛ ውስጥ የተፀነሱትን የራሳችንን አሳቦች ልንተው ይገባናል። እውነትን በምንፈልግበት ወቅት ከጓደኞቻችን ሊለያየንና ቀድሞ ከነበሩን ግንኙነቶች ሊነጥሉን ይችላሉ። እንደዚህ ዓይነት ፍለጋ ሁልጊዜ የሚጀመረው በግለሰቦች ነው። ሁሉም መንፈሳዊና ሥነ ምግባራዊ የተሐድሶ ሥራዎች የተጀመሩት በዚህ መልኩ ነው። አንድ ሰው እውነትን በዚህ መልኩ ማየት ሲጀምር መፈክሮች፡ ተወዳጅነትና በብዙ ሰው ዘንድ የሚኖረው ተደነቀነት እርካታ አይሰጡትም። ብዙ ተወዳጅ የሆኑ አስተሳሰቦች ያለባቸው ችግር ቢኖር ያልበሰሉና ጥልቀት የሚጎድላቸው መሆኑ ነው። መሠረታቸውን የሚያደርጉት ጥልቀት ባለው አሳብ ላይ ሳይሆን ጎዶሎነት ባጠቃው አስተሳሰብ ላይ ነው። ይህንን አሳብ የሚያራምዱ ሰዎች አስተሳሰባቸው ያልበሰለ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ለዚህ ጉዳይ ዋጋ ለመክፈል ያልተዘጋጁ ሆነው እናገኛቸዋለን።

ለዚህ እውነትን የመፈለግ ሥራ የምንሰጠው ስያሜ ግብረገነት ወይም በተገቢው መንገድ መሥራት ብለን ብንሰይመው ልዩነት የለውም። ትልቁ ችግር የሚጀምረው ግን «ሥነ ምግባር» ምን ማለት እንደሆነ ለመወሰን ስንታገል፤ ሥነ ምግባራዊ መርሆዎች መነሻቸው ከየት እንደሆነ ለማወቅ ስንጥርና መልካም

የሆኑ የሥነ ምግባር ድርጊቶች ከየት እንደሚመነጩ ለማወቅ ስንሞክር ነው።

## ደካማ የሆኑ አካሄዶች

ሥነ ምግባራዊ የሆነውን ድርጊት ፍቺውንና ክንውኑን የራስ ማድረግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ እርግጠኛ ሆነው የሚናገሩ ብዙ ደካማ ዓይነት አቀራረቦች አሉ። የአመክንዮን÷ የሙግትንና የዲሞክራሲን ሚና አስመልክቶ ከላይ ስንመለከት ቆይተናል። አንዱና ቀላል የሆነው መንገድ ሁሉም ሰው ሊስማማበት ወደሚችለውና ወደሚያስማማ ስፍራ ለመምጣት መሞከር ነው። በዚህ ስፍራ ላይ የታሰበው መጠነኛ የሆነ ነገር ማድረግ ነው፤ ማለትም ‹‹ብዙም ጥቂት ያይደለ›› ወይም ደግሞ ወደ ቀኝም ሆነ ወደ ግራ አለመጠን የማይለጠጥ ማለት ነው። እንደዚህ ዓይነት አካሄዶች መፍትሔ ሊያመጡ የማይችሉ ስለመሆናቸው ከመጀመሪያው እርግጠኞች ልንሆን ይገባናል። እነዚህ ምንም ጥልቀት የሌላቸው ይሁኑ እንጂ አብዛኛው ሰው የሚደግፋቸው ናቸው። እንደነዚህ ዓይነት አካሄዶች ትክክል ቢሆኑ ኖሮ ሥነ ምግባር የሚያርፍበት ጠንካራ መሠረት የሌለውና ግልጽ የሆነ ግብ የማያስቀምጥ የሚያመቻመች ሳይንስ ነው ማለት ነው። እንደዚህ የሚሆን ከሆነ ሥነ ምግባራዊ የሆነ የክንውን መንገድ መልካምና ክፉ በሆኑት መንገዶች መካከል የሚዋልል መካከለኛ መንገድ ይሆናል ማለት ነው። በሁለት ወገኖች መካከል በሚካሄድ ምርጫ መሠረት መሥመሩን የማስመርና ‹‹አማራጭ›› የማይገኝለትን ተመራጭ ነገር ለመወሰን›› እነዚህ ሰዎች ትክክል ወይም ሐሰት፤ እውነት ወይም ውሸት ስለሆነው ነገር በውስጠኛው ልባቸው የሚያምኑበትን ውሳኔ ወደ ጎን በመተው ሁለቱ ወገኖች ሳይጣሉ የጋራ ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ማለት ነው። በዚህ መልክ ጉዳዩን ማከናወን ከዚህ በታች የተጠቀሰውን ነገር እንደመቀበል ይቆጠራል። ውሸት÷ ስርቆት÷ ዝሙትና መግደል የመሳሰሉትን አንዳንድ ድርጊቶች በዚህ መልክ ለመረዳት የምንዳዳ ከሆነ እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ክፉ አይደሉም ማለት ማለት ሲሆን እነርሱን

የምንመለከትበት መንገድ በማመቻመች ላይ የተመሠረተ መስመር ለማስቀመጥ ፍላጎት ስላለን ነው ማለት ነው። ሁሉም ሰው ሊስማማበት የሚገባው ጉዳይ ቢኖር የሥነ ምግባርን ርዕሰ ጉዳይ በዚህ መልክ ማራመዱ ስሕተት መሆኑን ነው። በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ ስለሆነና ትክክልና ስሕተት የሆነውን÷ መልካምና ክፉ የሆነውን ነገር ስለሚገልጽ ሌላ ነገር ይናገራሉ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሰዎች ነገሮችን መልካም ወይም ክፉ ብለው ማብራሪያ የሚሰጡት በተለየ መልኩ ነው፤ ማለትም ለማንም ወገንተኛ ያልሆነ÷ ጥቁር ወይም ነጭ ያልሆነ÷ ግራጫ የሚመስል ሆኖ ከጥቁር ግራጫ እስከ ፈካ ግራጫ የሚሄድ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከነጭ ቀለም ጋር የሚመሳሰል ክምር ግራጫ ይሆናል ማለት ነው። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ስሜት በማይሰጥ መልኩ ነው ማብራሪያን ሊሰጡ የሚሞክሩት። ይህ ሥነ ምግባርን የሚመለከቱ ጉዳዮችን የምናራምድበት አመቺ መንገድ አይደለም። ሌሎች ሰዎች ደግሞ ከዚህ ተቃራኒ ሊሆን በሚችለውን ተግባራዊ ለማድረግ ይሞክራሉ። መልካምና ክፉ ለሆኑ ችግሮች መፍትሔ የሚፈልጉት ስሕተትና ትክክል ተብለው የሚታሰቡትን÷ ክፉ የሚሏቸውን ነገሮችንና ድርጊቶችን በዝርዝር በመጻፍ ነው። በዝርዝር ባስቀመጧቸው መሠረት ይህ የተከለከለ ነው፤ ይህንን በምንም ሁኔታ ቢሆን ማስወገድ ይኖርብሃል ብለው ይናገራሉ። ብዙ ሰዎች ይህ ናሙና በጣም ጥሩ ነው ብለው ያስባሉ። ከዚህም አልፎ ትክክልና ስሕተት የሆነውን ያለመጠራጠር ለማወቅና ሥነ ምግባራዊ ክንውን የትኛው እንደሆነ በአግባቡ ለማወቅ ይህ የአሠራር ዘይቤ መልካም ነው ብለው ያስባሉ። ነገሩ ግን እንደዚህ አይደለም። ምንም እንኳ ይህ ስልት ለሥነ ምግባር አዎንታዊ የሆነ አስተዋጽዖ የሚያበረክት ቢሆንም ‹‹የክልከላ መንገዶች›› የሚል ስያሜ ሊሰጠው ይችላል። ልናደርግ ስለሚገባን ነገር የሚለው ነገር የሌለው ሲሆን ማድረግ ስለሌለብን ነገር ብቻ ይነግረናል። ይህ አሳብ የጥልቀት ችግር ያለበት ሲሆን ናሙናነቱም በሌላ አንጻር እጅግ አደገኛ ነው። ብዙ ሰዎች በዝርዝሩ ውስጥ ያልተመዘገበ ነገር ሙሉ በሙሉ እንደተፈቀደ አድርገው ሊገምቱ

ይችላሉ። ከዚህ የተነሳ ኃጢአት ተብለው በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያልተካተቱ ነገሮች የተፈቀዱ ናቸው ማለት ነው። በዚህ መልኩ የሥነ ምግባር ትምህርቶችን ማስተማር በብዙ ሃይማኖቶች÷ በአንዳንድ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥና እንዲሁም በተወሰኑ የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች ወቅት ተግባራዊ ሆኖ ነበር። የዚህ ዓይነት አሠራር በእጅጉ እርካታን የማይሰጥ ነገር ነው። ጥልቀት የሌለውና ለሰዎችም ቢሆን ሚዛናዊነት የሚጎድለው ነገር ነው። ጥቂት ምሳሌዎች ለዚህ ማስረጃ ይሆናሉ። ሁለት ሰዎች ተመሣሣይ የሆነ ውጪያዊ ነገር ሲተገብሩ ብንመለከት ድርጊታቸው እኩል በሆነ ሥነ ምግባራዊ ዋጋ ሊተመን ይገባዋል ብለን ልናስብ እንችል ይሆናል። ድርጊቱን ያከናወኑባቸው ሁኔታዎች ፈጽሞ የተለያዩ እንደሆኑ ግን ዘንግተናል። ድርጊቶቹ ሲመዘኑና ዋጋ ሲሰጣቸው የሚገባው ከክንውኖቹ አንጻር መሆን ይገባዋል። ይህ የሚባለው ሥነ ምግባራዊ መለኪያዎችና እሴቶች ስፍራ እንዲያጡ ለማድረግ ሳይሆን ተቃራኒውን ለማሳየት ነው። በመጀመሪያ አንድ ቀላል የሆነ ምሳሌ እንመልከት። በሁለት የተለያዩ ጊዜያት አንድ ሰው ወንዝ አጠገብ ወደሚገኝ መጠለያ ለመግባት መስታወት ይሰብራል። ገመዶችንና የተወሰነ ቊጥር ያላቸው መቅዘፊያዎችን ይዞ ይወጣል። ይህ ሰው ሌባ ነው። በሁለተኛ ጊዜ ደግሞ የቤት ሰበራና የስርቆት ወንጀል እንደሆነ ሰማን። እንደ እውነቱ ከሆነ ሰውየው ዕቃዎቹን የፈለገው አንድን ሰው ከወንዝ መስጠም ለማዳን ነበር። በዚህ ሁኔታ ሰውየው ባለቤቱን አግኝቶ ዕቃዎቹን መለሰለት። ምናልባትም ሰውየው ስላከናወነው የጀግንነት ሥራ ኒሻን ተሸልሞ ሊሆንም ይችላል። ይህንን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ‹‹የተከለከሉናያልተፈቀዱ›› የተባሉት ‹‹ዝርዝር›› ነገሮች ሁሉ እጅግ ሊያሠሩ የማይችሉ መንገዶች ናቸው።

ሌላ ምሳሌ ብንወስድ ደግሞ ከዚሁ ጋር ተመሣሣይነት ያለው ነገርን ያሳየናል። አንድ ወንድና አንድ ሴት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ስለማድረጋቸው ሁለት ጉዳዮች ቀርበዋል ብለን እናስብ። ስፍራው÷ ዕድሜው÷ ሰዓቱና ቀኑ ተቀራራቢነት

ያላቸው ናቸው። ታዲያ እነዚህ ሁለት ጥንዶች ‹‹በዝርዝሩ›› ውስጥ የት አሉ? አንዱ ጉዳይ ሁለቱ ሰዎች የተጋቡ ባልና ሚስት ሲሆኑ ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ የየራሳቸው ትዳር ያላቸው ሆነው የግብረ ሥጋ ግኙኝነት ከፈጸሙት ሰው ጋር ግን ያልተጋቡ ይልቁንም ከሌላው ሰው ጋር የትዳር አጋርነት ያላቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ምንም እንኳ ውጪያዊ በሆነ መልኩ ክንውኑ ተመሣሣይነት ያለው ቢሆንም ከሥነ ምግባር አንጻር ከተመለከትነው ግን ሁለቱ ሰዎች ያደረጉት ድርጊት ተመሣሣይ ነው ለማለት አንችልም። የመጀመሪያውን ክስ የተመለከትን እንደሆነ በትዳራቸው ውስጥ ይህንን ማከናወን ሕጋዊነት ያለው ነገር ሲሆን በሁለተኛው ክስ ግን ሁለቱም ሰዎች የሥነ ምግባርን ሕግ ጥሰዋል። ሁለት ዋና የሆኑ መስመሮች አሉ። ስለ ጋብቻና ስለ ፍቅር በምንነጋገርበት ጊዜ ከእነዚህ ከሁለት መሥመሮች ጎን ለጎን ልናጤናቸው የሚገቡ ብዙ ነገሮች አሉ። ስለዚህ እነዚህ መርሆዎች ዝርዝር በሆኑና ሁሉን ሊሸፍን በሚችል መልኩ ሊቀመጡ አይችሉም።

ሌላ ምሳሌ ብንወስድ ተመሣሣይ የሆነ ነገርን ያሳየናል። ሁለት ሰዎች ስለ አንድ በትክክል ስለተከናወ ታሪክ ቃል በቃል ይነጋገራሉ። ታሪኩ እውነት ቢሆንም የሚያሳዝን ነገር አለው። አንዱ ታሪኩን ሲያወራ እውነትነት ያለው ሲሆን ሌላኛው ግን ታሪኩን ሲያወራ ውሸትነት አለው። ይህ እንዴት ነው ማብራሪያ ሊሰጥበት የሚችለው? የመጀመሪያው ለፍርድ ቤት መረጃ በማቅረብ ነው። ይህ ሰው የዓይን እማኝ ከመሆኑ የተነሳ መረጃ መስጠት አለበት። ይህንኑ እንዲያደርግ በፍርድ ቤት ተጠርቷል። ታሪኩን መናገሩ ደግሞ በሌላም አንጻር መልካም ነው። መረጃ መስጠቱ ማኅበረ ሰቡን ከማገልገሉም ባሻገር ፍርድ ቤቱ ተገቢ በሆነውና ባልሆነው ነገር መካከል ሚዛናዊ የሆነ ፍርድ እንዲፈርድ እገዛ ያደርግለታል። የተደረገው ጥፋት በፍርድ ቤቱ በሚሰጥ ውሳኔ በአግባቡና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መስተናገድ ይኖርበታል። ሌላው ሰው ደግሞ ታሪኩን ለመስማት ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች በሚናገርበት ወቅት ፈጽሞ ውሸት የሆነ

ነገር ይናገራል። የሚናገረው ነገር እርሱን የሚመለከት ሳይሆን በሌሎች ሰዎች ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ሊሆን ይችላል። ለአንድ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች ምናልባትም ለቤተ ሰብ አባላት ሁሉ እንደዚህ ዓይነት ሰው የማይጠቅም ነገር መናገሩ ከሥነ ምግባር አኳያ ተቀባይነት የሌለው ነገር ሲሆን በብዙ መልኩም ስም በማጥፋቱ ምክንያት ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት የሚወሰድበትም ሁኔታ ሊፈጠር ይችል ይሆናል። በዚህ ነጥብ ላይ ብዙ ሰዎች ተቃውሞ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ‹‹የሚናገረው ነገር እውነት ከሆነ ስለ ተናገረ ብቻ ሊፈረድበት አይገባም።›› በእርግጥ መናገር ይችላልና! በየቦታው እየዞሩ አንተ የምታውቀው ነገር እውነት ስለ መሆኑ መናገር አስፈላጊ አይደለም፤ እንደነዚህ ዓይነት ነገሮችን መናገር ሥራህ አይደለም በሚል እሳቤ እውነት የሆኑ ነገሮችን እንኳ ብትናገር ፍርድ እንዲፈረድብህ ገደብ የሚያስቀምጡ ሕጎች ያሏቸው ብዙ አገሮች አሉ። ምናልባትም ጉዳዮቹ የፍርድ ቤት ውሳኔ አግኝተውም ሊሆን ይችላል። ከዚህም የተነሣ ንግግርህ ሌላ ጉዳት ሊያስከትል በሚችል መልኩ እንደተነገረ ሊታሰብ ይችላል። ስለዚህ አንተ የዚህ ዓይነት ዓላማ ባይኖርህ እንኳ ሊፈረድብህ ይችላል። ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ካሳለፈ በኋላ ሰውየውን የዕለት ተዕለት ማኅበራዊ ሕይወቱን በአግባቡ እንዳይመራ እንቅፋት እንደሆንክበት ሊታሰብ ይችላል። ሌሎች ከንግግርህ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ነገሮችን በተመለከተ ወደ ኋላ ላይ የምንመለስበት ይሆናል።

እዚህ ላይ የተሰጡት ምሳሌዎች በብዙ መልኩ ሊብራሩ ይችላሉ። ሁሉም የሚያሳዩት ነገር ቢኖር የሰው ድርጊቶች ውጪያዊ በሆነ ሁኔታ ብቻ ሊመረመሩ ወይም ሊወዳደሩ የማይችሉ መሆኑን ነው። እነዚህን ሁኔታዎች በጥልቀት የመመርመር ፍላጎት የሚኖረን ከሆነ ማድረግ የሚኖርብን ውጪያዊውንና ውስጣዊውን ማለትም ጅማሬያቸውን÷ ዓላማቸውንና ድርጊቶቹ በተከናወኑበት ወቅት ለሁኔታው እገዛ ስለሰጡት ኃይሎች በአግባቡ ማጥናት ነው። አንድ ሰው ከከፍተኛ ጫና የተነሳ ማንኛውንም ተግባር ሊፈጽም ይችላል።

በሌላው በኩል ደግሞ ሌላኛው ሰው ያንኑ ድርጊት በፈቃደኝነት ሊፈጽመው ይችላል። እስቲ ስለ ሁለት ሌቦች የሚናገረውን ምሳሌ እንመልከት። አንደኛው ሰው ጓደኛውን በአጋጣሚ ባገኘበት ወቅት ስለ ታቀደው ዕቅድ የሚውቀው ነገር አልነበረም። ይህ ጓደኛው በእግር እየሄዱ ሳሉ በያዘው መሣሪያ ያስፈራራውና ወደ አንድ ቤት ገብቶ ውድ የሆነ ዕቃዎችን ይዞ እንዲመጣ ያስገድደዋል። እነዚህን ዕቃዎች ይዞ ባይመጣ በሕይወት ሊኖር እንደማይችልም ይነግረዋል። ጓደኛው ከእርሱ ጋር አብሮ በእግር የመጓዝ አሳቡን ሁሉ ሳይቀር ባቀደው ዕቅድ መሠረት ነው ያከናወነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ ፖሊስ ቢመጣና በውጪ ሆኖ የሚጠብቀው ያ ያስገደደው ጓደኛው ቢያመልጥና በቤቱ ውስጥ የሚገኘው ሰው የመያዝ ዕድል ቢገጥመው እንግዲህ ከእነዚህ ከሁለቱ ዋነኛው ሌባ የትኛው ነው?

## የአእምሮና የልብ ሁኔታ

ይህንኑ ጉዳይ በሌላ መልኩ ልናየው እንችላለን። ልክ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሁለት ሰዎች ተመሳሣይ የሆነ መልካም ነገር እያደረጉ ነው ብለን እናስብ። ያከናወኗቸው ተግባራት ደግሞ እኩል የሆነ ሥነ ምግባራዊ ዋጋ ሊሰጣቸው ይገባል ብለን አስበናል እንበል። እንደ ዕውነቱ ከሆነ ብዙ ሰዎች ፍርድ የሚሰጡት ከዚህ አኳያ ነው። ምናልባት እነዚህን ሁለት ሰዎች የመጠየቅ ዕድል ቢገጥመንና ነጥብ በነጥብ ለምንና እንዴት ተግባራዊ ሊያረጉት እንደቻሉ ቃለ መጠይቅ ብናደርግላቸው የሚያስደንቅ ዕውነታ ላይ ልንደርስ እንችላለን። አንደኛው ግለሰብ የእርሱ አስተዋፅዖ እዚህ ግባ ሊባል የማይችል እንደሆነ ሊጠቁም ይችል ይሆናል። ትሕትና በተሞላበት አነጋገር ‹‹ይህ የተለመደ አሠራር ነው›› የሚል ቃል ሊናገር ይችል ይሆናል። ሆኖም እንዴት ይህንን ሊናገር እንደቻለ አጥብቀን ስንጠይቀው ያለኝ ምርጫ ይህ ብቻ ነው ሊል ይችላል። ይህንን እንዲል ያስገደደው ውስጣዊ የሆነ ኃይል ነው። ይህን ዕውነታ ልክ ኤርምያስ ባብራራው መልኩ ሊገለጽ ይችላል። ‹‹እኔም የእግዚአብሔርን ስም አላነሣም፤

ከእንግዲህ ወዲህም በስሙ አልናገርም ብል በአጥንቶቼ ውስጥ እንደገባ እንደሚነድድ እሣት በልቤ ሆነብኝ፤ ደከምሁ መሸከምም አልቻልኩም›› (ኤር. 20÷9)፡፡ ‹‹መልካም የሚሰኙ ተግባራት›› ሊገለጹ የሚችሉት በዚህ መልኩ ነው፡፡ እስቲ አሁን ደግሞ ለውጫዊው ዓይን ተመሳሣይ ስለሚመስል አንድ ሌላ ጉዳይ እንመልከት፡፡ እኛ ላይ አግራሞትን እስኪፈጥር ድረስ ጉዳዩን የሚከውነው አንዱ ሰው እንዲህ ሊለን ይችል ይሆናል፡፡ ‹‹እኔ ይህ ነገር ብዙም ትኩረት የምሰጠው ጉዳይ አልነበረም፤ ሆኖም ይኸኛው ጓደኛዬ ሲያደርገው ስመለከት እኔም ያንኑ ለማድረግ ተገፋፋሁ፡፡ እኔ በበኩሌ ይህ ነገር እንዲሁ ሳሠራ እንዳለ ልተወው ወይም ሌላ ነገር ላደርግ ወይም ፍጹም ተቃራኒ የሆነውን ነገር ማድረግ እችል ነበር፡፡››

ታዲያ ሁኔታው እንደዚህ ከሆነ የሁለት ሰዎች ‹‹መልካም ሥራ›› ተመሣሣይነት አለው ብለን ልናስብ የምንችለው እንዴት ነው? ሁለት የተለያዩ የሥነ ምግባር ድርጊቶችን በምንመዝንበት ጊዜ ምንም ቢሆን በዚያ ሰው ውስጥ ያለውን የአእምሮና የልብ ሁኔታ ልናጤን ይገባናል፡፡ ከዚህ ጋር አክለን ልናይ የሚገባን ሌላ ነገር ቢኖር ‹‹መልካም ሥራ›› ተብለው የሚፈረጁ ነገሮች በግድ የለሽነት ወይም ከሴራ ጋር በተያያዘ መንገድ የሚከናወኑ ከሆነ እነዚህ ነገሮች ከመልካምነት መራቃቸውን መገንዘብ ብቻ ሳይሆን በውሸትና በግብዝነት መፈረጅ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም በመካከላችን ስምምነት እንዳይኖር እንቅፋት ይሆናሉና ነው፡፡ በመግባብት÷ በመልካም ፈቃደኝነትና በፍቅር ላይ መመሥረት በሚፈልግ ኅብረት ወይም ማኅረሰብ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት እውነትና ውሸት ሊዋሐዱ አይችሉም፡፡

ስለሆነም ጥያቄው መልካምና ክፉ የሆነውን ነገር ለማወቅና ለመመዘን መለኪያው የሚመጣው ከየት ነው? የሚል ነው፡፡ ወይም ደግሞ መልካም ተብሎ የሚጠራ ነገር እስከሌለ ድረስ ሰው ‹‹መልካም›› እና ‹‹ትክክል›› የሆነውን ነገር የማያውቅ ከሆነ አንድን ነገር እንዴት ውሸት ነው ወይም ሐሰት ነው ብለን ለመናገር እንችላለን? እናውቅም ወይም ልናውቅ አንችልም በሚል

አሳብ ላይ የሚመሠረት ሙግት ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ነው። በዚህ ነጥብ ላይ ሁላችንም የምንስማማ ቢሆንም ይህ መርሆ ሥነ ምግባርን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ ላይ የሚሠራ ነው። በዚህ ዓለም ላይ ምንም ነገር ትክክል፣ መልካም ወይም እውነት ተብሎ የሚጠራ ነገር እስከሌላ ድረስ ማንም ሰው ቢሆን ነገሮችን መጥፎ ድርጊቶችንና ክንውኖችን ከእውነት የራቁ በማለት ድምዳሜ ላይ ለመድረስ መሞከር የለበትም። እንደ እውነቱ ከሆነ እንደዚህ ዓይነት ልዩነት ስለመኖሩ አናውቅም ብለው ምስክርነት ሊሰጡ የሚችሉት ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው። በሌላም መልኩ የተለያየ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ሁሉ ትክክልና ስሕተት፣ መልካምና ክፉ ስለሆኑ ነገሮች በተደጋጋሚ ይናገራሉ። ነገር ግን ለምን ይህንን እንደሚደርጉ አያውቁም። ስለሆነም እኛ ደግሞ ‹‹ስለ መልካም፣ ስለ ክፉ፣ ስለ እውነትና ስለ ሐሰት የምትናገሩት ከምን ጋር አወዳድራችሁት ነው? መመዘኛው ምንድነው?›› የሚል ጥያቄ ልንጠይቃቸው እንችላለን። ‹‹ስሕተት›› ‹‹ሐሰት›› እና ‹‹ውሸት›› ስለሚባሉት ነገሮች በሚናገሩበት ወቅት የዚህ ተቃራኒ የሆኑት ‹‹ትክክል›› እና ‹‹እውነት›› የሚባሉ ነገሮች ስለመኖራቸው በግልጽ እያሳዩ ነው ማለት ነው። ታዲያ ልዩነቱን መገንዘብ የሚችሉት እንዴት ነው? ይህንን በሚለኩበት ወቅት አንድ መለኪያ ወይም መሳሪያ ተጠቅመው ሊሆን ይችላል። ለእነዚህ ጉዳዮች መለኪያ እስካልተዘጋጀለት ድረስ ስለ መጥፎነት÷ ስለ ክፋትና ስለ ውሸት የሚነገሩ ነገሮች በሙሉ ከነፋስ ጋር ከመነጋገር ጋር ሊመሳሰሉ ይችላሉ።

## በሥነ ምግባር ወስጥ የሕሊና ሚና

በእግዚአብሔር ቃል አስተምህሮ መሠረት እግዚአብሔር ‹‹በልባቸው›› ውስጥ ማለትም በሕሊናቸው አማካይነት በመናገር ራሱን ለሰው ሁሉ ገልጿል። ሁሉም ሰው ቢሆን እንደዚህ ዓይነት በውስጣዊ ማንነቱ ይህንን የሚመስል መሣሪያ አለው። ለምሳሌ ሕሊና በየትኛው የአካል ክፍል ላይ ነው የሚገኘው የሚል ጥያቄ በመጠየቅ ብዙ ሰዎች ይህንን ዕውነታ ይክዳሉ። ይህንን ጉዳይ

የበለጠ ሲያብራሩት የሰውና የአካል ክፍሎች በሙሉ በኬሚካል ምርመራ፣ አጉልቶ በሚያሳይ መነፅር ወዘተ... ተገቢውን ምርመራ ያደረግን ቢሆንም የሕሊና መቀመጫ ሊሆን የሚችል አንዲት ስፍራ እንኳን አላገኘንም ብለው ይናገራሉ። እንደዚህ ዓይነት አባባል እጅግ ደካማ የሆነ ሙግት ነው። ይህንን ጉዳይ በሚመለከት በዚህ መልኩ መልስ ሊሰጥበት ይችላል። በዚሁ መልኩ ከቦታ ቦታ የሚፈልሱ ወፎች ከቦታ ቦታ እንዲፈልሱ የሚያስገድዳቸው ነገር በአካላቸው ውስጥ ስለ መቀመጡ ተገቢውን ጥናት አድርጋችኋል? እንደ አየሩ ሁኔታ ከአንዱ የዓለም ክፍል ወደሌላኛው የዓለም ክፍል የሚጓጓዙ ቢሆንም የሚያስደንቀው ነገር ቢኖር ተመልሰው የተወለዱበት ስፍራ መስፈራቸው ነው። ሌላው እጅግ አስገራሚ የሆነው ነገር ወላጆቻቸው የሄዱበትን ሌላውን ክፍለ ዓለም፣አገር ወይም ስፍራ ፈጽሞ ያልተመለከቱ ትናንሽ ወፎች አብዛኛውን ጊዜ የተወለዱበትን ስፍራ ትተው የሚሄዱት ከቤተ ሰቦቻቸው ተነጥለው ነው። ታዲያ እዚያ መዳረሻቸው ላይ ሊደርሱ የሚችሉት እንዴት ነው? ርቀትንና አቅጣጫን የማወቅ ችሎታ እንዳላቸው ጥርጥር የሌለው ነገር ቢሆንም ታዲያ ይህ መሣሪያ የትኛው ክፍላቸው ላይ ይሆን የሚገኘው? አሁንም ሆነ ከሺህ ዓመታት በፊት በገሃድ ሲሠራ የሚታይ ቢሆንም ይህንን ነገር እጅግ ዘመናዊ በሆነ አጉሊ መነፅር እንኳን ለማየት አይቻልም። እንደዚህ ዓይነት የማይታይ መሣሪያ ስለ ሕሊና፣ ማለትም በሰው ውስጥ በመሥራት ላይ ስላለው ስለማይታየው መሣሪያ ለመግለጽ ጥሩ ማሳያ ነው። ‹‹ሕሊና›› የተሰኘው ቃል ተመሣሣይ በሆነ መልኩ በሁሉም ቋንቋዎች ውስጥ ይገኛል። ቃሉ በእንግሊዝኛ ሁለት ክፍሎች (con-science) ያሉት ሲሆን÷ ትርጉሙም በጋራ ማወቅ (to know together) የሚል ፍቺን ይሰጣል። ጥያቄው ግን የጋራ ዕውቀት ከማን ጋር የሚል ይሆናል። ትርጉሙ የሕሊና ባለቤት ከሆነው ‹‹ከእግዚአብሔር ጋር አንድን ነገር በጋራ ማወቅ›› የሚል ነው። ስለሆነም የዚህ ቃል ትርጉም የሚሆነው የሕሊናችንን ድምፅ በምናዳምጥበት ወቅት ከእግዚአብሔር ጋር መሠረታዊ ስለ ሆነው እውነት፣ ትክክል

ወይም ስሕተት ስለሆነው ነገር፤እውነትና ውሸት ስለሆነው ነገር የጋራ ዕውቀት ይኖረናል ማለት ነው። ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት ዕውቀት የሌላቸው ሕዝቦች በዓለም ላይ የሉም። አንዳንዶቹ ዝቅተኛ የሆነ ዕውቀት ሊኖራቸው ይችል ይሆናል። አንዳንዶቹ ደግሞ ዕውቀታቸውን ፈጽመው ትተው ልዩነቱን ለማወቅ የተቸገሩ ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል። ከጊዜ ብዛት የተነሣ ሥነ ምግባራዊ እሴቶቻቸው ከእነርሱ ተወስዶባቸውም ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ ግብረብነት ከጎደላቸው መሥሪያ ቤቶች ቅስቀሳ የተነሳ አቋማቸው ተለውጦ ሊሆንም ይችላል። ይህም ሆኖ በቀረው አመድ ውስጥ ጭል ጭል የምትል ትንሽ እሳት ልትኖር ትችላለች፤ ወይም በአንድ ወቅት ትክክልና ስሕተት ስለሆነ ነገር ዝግ በሚል ድምፅ ተነግሯቸውም ሊሆን ይችላል። ይህንን ድምፅ ፈጽሞ ጸጥ ለማሰኘት አይቻልም።

ድምፁ የተለየ ሲሆን የሚናገረውም በተለየ ሁኔታና ለተለያዩ ሰዎች ነው። ይህ የሚያሳየው የትኛውም ሕሊና ስሕተት የለሽ አለመሆኑን ነው። ሕሊና መስተካከል የሚያሻው ነገር ነው። አንዳንድ ሕሊናዎች ከባድ በሆኑ ብርሃኖች ውጤት አልባ በሆነ ሁኔታ የበራባቸው ናቸው። በሌላ ሁኔታ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ብቻ ከሚሠሩና በቂ ዕድሳት ካልተደረገባቸው መሣሪያዎች ጋር ይመሳሰላሉ። በአንዳንድ ወቅት ደግሞ ሕሊናውን የተሸከመው ሰው ድርጊቶቹን ከእርሱ በተቃራኒ ከማድረጉ የተነሳ የክንውኑ ሥርዓት ተዛብቶ ሊሆንም ይችላል። አንድ አውቶማቲክ የሆነ መሣሪያ የተሳሳተ ‹‹ማስተካከያ›› ከተደረገለት በኋላ የተሳሳቱ ምስሎችን እንደሚሰጥ ዓይነት ነው። እነዚህ ሁሉ እውነታዎች የሕሊናን ተግባር በምንመረምርበት ወቅት ግንዛቤ ውስጥ ልንከታቸው ይገባናል። የየትኛውም ሃይማኖት ወይም እምነት ተከታዮች ቢሆኑ ሕሊናቸው እውን መሆኑ በክርስቲያኖች ሁሉ ዘንድ እውቅና ሊያገኝ ይገባዋል። ወደ በኋላ ላይ እንደምንመለከተው መግባባትና ትብብር ባለበት ሁኔታ ውስጥ ይህ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ነጥብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ (የሙሴ) ደግሞ ይጠፋሉና፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት

ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል›› (ሮሜ 2÷14) ይላል። ይህ ስፍራ መሠረታዊ ስለሆነው ነገር ማለትም ትክክልና ስሕተት ስለሆነ ነገር፤ ስለ መልካምና ክፉ ነገር በማሳወቅ ሰዎች መስረቅ፤ መግደል ወይም መዋሸት እንደሌለባቸው የማስገንዘብ ኃላፊነትን ይወስዳል። እዚህን የተነሱትን ነጥቦች አስመልክቶ ማንኛውም ሰው ‹‹ዘመናዊ ሥልጣኔ›› ባልደረሰባቸው ወይም የክርስትና አሻራ ባላረፈባቸው ስፍራዎች በመጓዝ ማረጋገጥ ይችላል። በእንዲህ ዓይነት አካባቢዎች የሚገኙ ሕዝቦች የራሳቸው ደኅንነት ሥጋት ላይ እንደወደቀ አድርገው እስካላሰቡ ድረስ ለሕይወት ሕግጋትና ለንብረቶቻቸው አክብሮትን ይሰጣሉ። በብዙ መልኩ እነዚህ ሰዎች በመዝገበ ቃላታቸው ውስጥ ‹‹ሕሊና›› የተሰኘ ቃል የላቸውም። በዚህ ምትክ ሌላ ቃልን ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋሉ። ››ልብ››÷ ‹‹የልብ አሳብ››÷ እየተሰማቸው ስላለ ነገር ወይም በውስጣቸው እያቃሰተ ስላለ አንድ ነገር ሊናገሩ ይችላሉ። ቃላቱ በራሳቸው በጉዳዩ ላይ የወሳኝነት ሚና ይኖራቸዋል ማለት አይደለም። የሚወሰነው ሰዎች ትክክል በሆነውና ስሕተት በሆነው መካከል ያለውን ልዩነት በሚያውቁበት ወቅት ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሕሊና ሁለት ገጽታዎች ይኖሩታል። እነዚህም መልካም ለሆነው ነገር ማረጋገጫ መስጠትና ክፉ የሆነውን ነገር የመኮነን ናቸው። ‹‹እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸውን የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ›› (ሮሜ 2÷15)። ትክክለኛውን ውሳኔ መወሰንን አስመልክቶ በዚህ መልኩ ሊብራራ ይችላል። ‹‹ስለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ›› (የሐዋ. 24÷16)። ምናልባትም በተለያዩ እምነቶችና ሃይማኖቶች ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በዚህ ነጥብ ላይ ጳውሎስ የተናገረውን ሊቀበሉት ይችሉ ይሆናል።

## አመለካከቶች ሲለያዩ

ብዙ ሰዎች የሕሊና መኖርን መኖር በመቃወም በከፍተኛ ደረጃ ይሚገታሉ። ይህ ‹‹በዘመናት መካከል የቆየ አስተሳሰብና ክምችት›› ወይም በቀደሙት ዘመናት ሰዎች

የነበሩባቸው የተለያዩ ፍርሃቶች ማረጋገጫ ነው የሚል ስያሜም ይሰጡታል። እንደዚህ ዓይነት አባባሎች ከታሪክ ምስክርነት ጋር የሚጋጩ ናቸው። የትኛውንም ቅርፅ ይያዝ ከአራት ሺህ ዓመታት ጀምሮ የታወቁና ታሪካቸውን በጽሑፍ ያሰፈሩ ሕዝቦች ሁሉ ትክክልና ስሕተት ስለሆነ ነገር ጥርት ያለ ግንዛቤ ነበራቸው።

አብዛኛውን ጊዜ ግን ‹‹ሕሊና›› ስለ ተሰኘው ቃል ለምን እንደሚያገለግል ሰዎች ብዥታ አላቸው። የራሳቸውን የተለመዱ አሳቦች÷ ቤት ሠራሽ የሆነ አስተምህሮታቸውንና ሌሎችን ሰዎችና አመለካከቶችን በሚመለከት ውሳኔ በሚያደርጉበት ጊዜ ‹‹ሕሊናን›› ማጣቀሻ ያደርጉ ነበር። በዚህ መልክ ‹‹ሕሊናን›› መጠቀሙ ቃሉን ተገቢ ባልሆነ መንገድ መተርጎም ነው። ሕሊና ብለን የምንጠራው መሣሪያ ተግባሩን የሚያከናውነው በትክክልና በስሕተት÷ በክፉና በመልካም÷ በእውነትና በሐሰት መካከል የሚኖረውን ልዩነት ብቻ በሚመለከት ነው። ይህንን ከፖለቲካ አንጻር ምሳሌ በመስጠት ለማሳየት ይቻል ይሆናል። አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ፍትህ በጎደለው መልኩ ለአንድ ሕዝብ አድልዎ ለማድረግ በሚል እሳቤ ሌላውን ሕዝብ በግልጽ የሚጎዳበት ነገር ቢፈጥር ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ አንድ ሰው ከእንደዚህ ዓይነት ድርጊቶች ጋር ለመተባበር ሕሊናዬ አይፈቅድልኝም ቢል ተናጋሪው ትክክል ነው። ነገር ግን በየትኛውም መንገድ ከዚህ የፖለቲካ ፓርቲ ጋር በማንኛውም መልኩ ለመሥራት ሕሊናው እንደማይፈቅድለት ውሳኔ ላይ መድረሱን ቢናገር ስሕተት ነው። ሌላው ፓርቲ በሌሎች ጉዳዮች ላይ መልካም የሆነ ሥራ እየሠራ ካለ ይኸኛውንም ሆነ ሌሎችን ተግባራት እንዳያከናውን ሕሊናው ሊነግረው አይችልም። ተናጋሪው እንዲህ ቢያደርግ የሕሊናን ጉዳዮች ከፖለቲካዊ አስተሳሰቦች ጋር ደባልቆታል ማለት ነው። እንደዚህ ዓይነት የመደባለቅ ተግባር የተለመደ ከመሆኑም ባሻገር ‹‹ሕሊና›› የሚለውንም ቃል በተሣሣተ መንገድ መተርጎምን ያካትታል። እንዲህ ዓይነቱን መደባለቅ በሌሎች የሕይወት ክፍሎችም ውስጥ ማየቱ የተለመደ ነው።

አንዳንድ ሰዎች የሕሊናቸውን ድምፅ የሚሰሙ ሲሆን አንዳንዶቹ ይህንን አያደርጉም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ በማያቋርጥ መልኩ የሚያዳምጡ ሲሆን ሌሎቹ የሚያዳምጡት አልፎ አልፎ ነው፡፡ ስለሆነም የሕሊናቸው ደረጃ በእድገት ይለያያል፡፡ በአንዳንድ ሰዎች ላይ ሕሊናቸው በሥራ ላይ ያለና ሙሉ በሙሉ ንቁ ሊሆንም ይችላል፡፡ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ደግሞ እንደ ቀድመው ዘመን በማንቀላፋት ላይ ሊሆን ይችላል፡፡ ሕሊናው ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ያ ሰው ‹‹መልካም›› እና ‹‹ግልጽ›› የሆነ ህሊና እንዳለው መገንዘብ ይጀምራል፡፡ ከዚያ በኋላ ትክክለኛ የሆነ ነገር ማድረጉን ያውቃል፡፡ በሌላም በኩል ስሕተት የሆኑ ነገሮችን በሚፈፅምበት ወቅት ‹‹መጥፎ›› የሆነና ‹‹የመጸጸት›› ስሜት በሕሊናው ያድርበታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አንድን ነገር ለመፈጸም ሰውየውን ያገዘው ‹‹ሕሊናው›› ነው ብለን እናስባለን፡፡ የሠራው ነገር ስሕተት እንደሆነ ቢያውቅም ድርጊቱን ለመፈጸም ተስማምቷል ማለት ነው፡፡ የአንድ ሰው ሕሊና በማይሠራበት ወቅት በአንድ በሆነ ምክንያት እንዳይሠራ ተደርጓል ማለት ነው፡፡ እነዚህ ዝምታዎች በሚደጋገሙበት ጊዜ ሕሊና ለመሞት የተቃረበ ሲሆን ፈጽሞ ሕይወትም ላይኖረው ይችላል፡፡ ሆኖም በአካባቢው ከሚፈጠር ነገር የተነሳ ሰውየው ሕይወት ሊዘራ ይችላል፡፡ በክርስቲያን ቋንቋ በሚቀጥለው ጥቅስ ላይ እንደ ተጻፈው በእግዚአብሔር ወይም በእግዚአብሔር ቃል ተነክቶ ሊሆንም ይችላል ‹‹ከእንቅልፍ እንደሚነቃ አነቃኝ›› (ዘካ. 4÷1)፡፡

እንዲህ ዓይነት መነቃቃቶች እንደ ማስጠንቀቂያ ደወል በሚያገለግሉ ወዳጆች አማካይነት ሊከናወን የሚችል ይሆናል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ጥልቅ በሆነ መንፈሳዊ እንቅፍል ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ሊያነቃ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ በሚቀጥሉት ምዕራፎች ውስጥ በሚገኙ ልዩ ልዩ ርዕሶች ውስጥ የሕሊናን ተግባርና ሕልውናውን አስመልክቶ ብዙ ምሳሌዎች በማቅረብ በዚህ ጉዳይ ላይ ስለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እንጥራለን፡፡

# ምዕራፍ 5

# ዓለማዊ ወይም ክርስቲያናዊ መሠረት ያለው ሥነ ምግባር

አንዳንድ ጊዜ ሃይማኖተኛ የሆኑ ሰዎች ብቻ ሥነ ምግባራዊ መርሆዎች ሲኖሩአቸው እንደሚችልና ከዚህም የተነሣ ግብረ ገባዊ ድርጊቶችን እንደሚፈጽሙ ይታሰባል። ይህ እውነታዎችን አለመረዳት መሆን አለበት። እግዚአብሔርን የማያምኑ ሆኖም ግን ከፍ ያለ ሥነ ምግባራዊ መርሆዎች ያሏቸውና በዚያው መሠረት ለመኖር የሚሞክሩ ሰዎች የሚተባበሏቸውና የሚያከብሯቸው በርካታ ሥነ ምግባራዊ ሥርዓቶች አሉ። እንደዚህ ያሉ ሥርዓቶች በክርስቲያኖችም ጭምር እውቅናና ዋጋ ሊሰጣቸው ይገባል። ይህም በሁለት ምክንያቶች ነው። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች በአሳባቸውና በኑሮአቸው ሁላችንም በእግዚአብሔር መፈጠራችን

እና በተፈጥሮም በሕሊና እና በተወሰኑ መንፈሳዊ ሕግጋት መሠረት በተወሰነ የአስተሳሰብና የድርጊት ተሰጥዖ የታጠቅን መሆናችንን የሚያንጸባርቁን የክርስትና አስተምህሮ ያሳያሉ። ሁለተኛ በሥነ-ምግባራዊ መርሆዎች መሠረት የሚኖሩትንና አማኝ ያልሆኑትን ጨምሮ ሰዎች ሁሉ ለማኅበረሰቡ እና ለደኅንነቱ መጠበቅ አዎንታዊ አስተዋጽዖ ማበርከትና በዚህም ዓለም ውስጥ ያሉ የጥፋት ኃይላትን በመቃወም ይሠራሉ።

በሌላ በኩል ሌላ እውነትን ማወቅ ይገባናል፤ በዘመናት መካከል የሥነ ምግባር ትምህርት ለሥነ ምግባራዊ እሴቶችና ባሕርያት እንደ መንፈሳዊ ኃይል አድርጎ በክርስቲያኖች ድረስ በሃይማኖት ላይ ተደግፎ ኖሯል። በቅርብ ጊዜያት ግን የተለያዩ ዓለማዊ ወይም «መንፈሳዊ ያልሆኑ» ሥነ ምግባር ዓይነቶች ይበልጥ እየበረታቱ መከሰት ጀምረዋል። መልካሙ ተቀባይነት ያለው፥ ደካማ ወይም መጥፎ ሥነ ምግባራዊ ባሕሪይን ለመለየት እምነቶቻቸው እጅግ ልል ከሆነው ጀምሮ ሙሉ

በሙሉ ጠንካራ እስከሚባለው አሳብ ድረስ በጣሙን ይለያያሉ። በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት ሥርዓቶች በተለያየ ሁኔታ ዋጋ ሊሰጣቸው ይገባል። ምክንያቱም በአጠቃላይ በሥነ ምግባር ማለትም በትክክለኛውና በስሕተተኛው መካከል ባለው ግልጽ ልዩነት ላይ በጽናት እስከ ተናገሩ ድረስ ለማኅበረሰቡ ሕይወት የሚሰጡት አስተዋጽዖ አላቸው። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ባይሩ ኖሮ ማኅበረሰቡ የሚጠብቀው ተስፋ እጅግ ይበልጥ የጨለመ ይሆን እንደነበር መቀበል ይኖርብናል።

## ትክክለኛ የሆነውን ነገር የምናደርገው ለምንድን ነው?

በእግዚአብሔር በሚያምኑ እና እንደዚህ ዓይነት እምነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በመሠረታዊ እሳቤዎች በኩል አስቀድሞውኑም ቢሆን ትልቅ ልዩነት መኖሩ ሊካድ አይችልም። የእግዚአብሔርን ሕልውና የሚክዱ ሰዎች ለምን ትክክለኛ የሆነውን ነገር ማድረግና ስሕተት የሆነውን ከማድረግ መራቅ እንደሚገባ የሚያረካ መልስ መስጠት አይችሉም። በመሆኑም ራሳቸውን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገብተው ያገኙታል። በራሳቸው መልካም የሆኑና ወደ መልካም ዓላማ ያነጣጠሩ ነገሮች እንዳሉ የሚቀበሉ ከሆኑ በመጠኑም ቢሆን የዓላማ መነሻ ነጥባቸውን ትተውታል። ለምን? ምክንያቱም በመለኮታዊ ኃይል ያልተፈጠረ፣ ነገር ግን በእድል ብቻ የታየ ነገር በራሱ ‹‹መልካም›› ወይም ወደ አንድ ግብ የተነጣጠረ ሊሆን ስለማይችል ነው። ለተለየ የተቃራኒ ምክንያት ቢሆንም ከሌላኛው አማራጭ ጋር ተያይዘው የሚመጡትም መሰናክሎቻቸውም ብዙ ናቸው። በራሳቸው ‹‹መልካም›› ተብለው ይጠራሉ? ‹‹መልካም›› ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ እና በራሳቸው አንድ ‹‹ዓላማ›› ያላቸው ነገሮ መኖራቸውን ለመቀበል የሚገደዱ ከሆነ እንግዲያውስ ለምን ‹‹መልካም›› ተብለው ይጠራሉ? ‹‹መልካም›› የሚለው ምልክት የዘፈቀደ ሥራ ብቻ ነው? ጉዳዩ ይህ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ‹‹መልካም›› ወይም ‹‹ሥነ-ምግባር›› ወይም ‹‹ግብረ ገብ›› ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ ነገሮች አለመኖራቸውን መቀበል ይኖርብን ነበር።

ራሳቸውን ኢ-አማንያን ወይም የማያምኑ ብለው የሚጠሩ ሰዎች ከሁለት አሳቦች ለመራቅ የሚመኙ ይመስላል፤ ይኸውም ፈጣሪ መኖሩን እና አስቀድሞውኑም ከፍጥረት ጀምሮ በሥነ ምግባር ጉዳዮች አስተሳሰባችን እና ድርጊታችንን ሊመራ የሚችል ኃይል አለ የሚለውን አሳብ ነው። በሌላ አነጋገር ሊርቁት የሚመኙት ነገር የሕሊና ወይም በሰው ውስጥ አብሮ የተገነባን የትክክልና የስሕተት ነገር እሳቤ ነው። እንደዚህ ያለ ነገር ከመጀመሪያው ጀምሮ እዚያ ሊኖር የማይችል ነው ይላሉ። በእርግጥ እንደዚህ ነው? ከመጀመሪያው አንስቶ የነበሩ ሌሎች እጅግ በርካታ ነገሮችና እሳቤዎች አሉ። በምሳሌነት ሰዎች አብረዋቸው የኖሩዋቸውና ልናስወግዳቸው የማንችላቸውን ሁለት ‹‹ሕግጋት›› መጥቀስ እንችላለን። በመላው ዓለም ላይ በየትም ቦታ ሁለት ጊዜ ሁለት ሦስት ወይም አምስት አይሰጥም። ድንጋዮች ወይም ክዋሶች ወደ ላይ ቢወረወሩ ወደታች ተመልሰው ይመጣሉ። እነዚህ ሁለት ሕግጋት አሁን እንደሚታየው ያልሠሩበት ጊዜ የለም። ለምሳሌ ድንጋዮች ወይም ደቡልቡል ነገሮች በቀደመው ዘመን ወደ ላይ ተወርውረው ጠፈር ውስጥ የጠፉበት ጊዜ እንደነበር አናምንም። እንደ እነዚህ ምሳሌዎች ሁሉ በአጠቃላይ መልኩ መስረቅ ወይም መግደል ትክክለኛ ተደርጎ የተቆጠረበት ወይም ታማኝነት የተከለከለበት ጊዜ እንደ ነበረ ከናካቴው በዓይነ ሕሊናችን ልናስብ አንችልም።

በተመሳሳይ መልኩ ስለ ትክክለኛው መንገድ እና ስሕተተኛ ሌሎች በርካታ ነገሮች በምንናገርበት ጊዜም እንደዚሁ ነው። በመሆኑም የማያምኑ ብለው ራሳቸውን የሚጠሩ ሰዎች አመለካከቶች ምንም ይሁን ምን አሁን እኛ ያለን የሕሊና ሕግጋት በዘመናት ሁሉ የሰዎች ትጥቅ ሆነው እንዳገለገሉ መስማማት ይኖርብናል። አመለካከታቸው ስሕተት ነው፤ ነገር ግን ለሌሎች ምክንያቶች ሲሉ መልካም ለሆነው ነገር ሲቆሙ እናበረታታቸዋለን። በዚህ ነጥብ ላይ ከእነርሱ ጋር መስማማት እንችላለን።

## ክርስቲያናዊና ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ሥነ ምግባሮች መካከል ያለው ልዩነት

ባለንበት ዓለም ውስጥ የምንኖር መሆናችንን መቀበል ይገባናል። ምክንያቱም በሕልሞች ዓለም ውስጥ ብቻ ልንኖር አንችልምና። የምንኖርበት ዓለም የወደቀ ዓለም በመሆኑም በተለያዩ ደረጃዎችና ለተለያዩ ዓላማዎች አንድ ሕግ ያስፈልገናል። ከሁሉ አስቀድሞ በተናጠል፤ በማኅበረሰብና በአጠቃላይ በዓለም ውስጥ ሕይወታችንን ለመምራት ውጫዊ ሕግ ያስፈልገናል። የዚህ ዓይነት ሕግ ሕልውና ከሌለውና የማይሠራ ከሆነ የሰው ሕልውና በሙሉ የማይቻል ይሆናል። ማንኛውም ሰው የሁሉም ሰው ጠላት ይሆናል፤ ሌላ ሰውም ሙግታቸውን ወይም ጠባቸውን ሊያስቆም አይችልም። ውጫዊው ሕግ በልባችን ውስጥ አንድ ተባባሪ አለው። በተጨማሪም ሕጉ ብዙ ጊዜ ወይም በአጠቃላይ መልኩ በሕሊናችን ታግዞ ትክክለኛውን እና ስሕተተኛውን ነገር ይነግረናል። በእነዚህ ነጥቦች ላይ በርካታ የማያምኑ ሰዎች ይስማማሉ። ነገር ግን የሕጉ እና የመታዘዝ ስሜት ከየት እንደሚመጣ በሚያብራሩበት ነጥብ ላይ አይስማሙም። ሆኖም ግን በትክክል እና በስሕተት መካከል ባለው ልዩነት ላይ ይስማማሉ።

ክርስቲያኖች ግን ሕጉን በሌላ መንገድ ይረዱታል። ሕጉ እንድናደርግ የሚነግረንን መፈጸም እንደማንችል በሕጉና በሕሊናችን ሲነገረን ሕጉ ተስፋ እንድንቆርጥ ወይም እርዳታ እንድንፈልግ የሚያስገድደን ጥብቅ እና ኃይለኛ አዛዥ ይሆናል። ይህንን እርዳታ ከአዳኙ ክርስቶስ ከፈለግን ሕጉ ሊረዳን ወደሚችለው ወደ ክርስቶስ የሚመጣን «ሞግዚታችን» ይሆናል (ገላ. 3÷24)። ሕጉን ከእነዚህ ነጥቦች አንጻር የተመለከትነው እንደሆነ ጠላት አይደለም። ይልቁንም እንደ ባልንጀራ እና ረዳት ሊቆጠር ይገባዋል። ሕጉ ጠላት የሚሆንብን በክርስቶስ ምትክ በገዛ ራሳችን መንገድ ጻድቃን ሆነን ለመገኘትና ለሕጉ በመታዛዝ ራሳችንን ለማዳን ጥረት ያደረግን እንደ ሆነ ብቻ ነው።

ከአመለካከቶች ልዩነት የተነሣ በተለያዩ የሥነ ምግባር ሥርዓቶች መካከል ዘወትር ክርክር አለ። ሥርዓታቸውን ‹‹እውነተኛ ሰዋዊ›› ብለው የሚፈጥሩ የተወሰኑ ኢ-አማንያን አሉ። በእነዚህ ቃላት ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ ፍጥረት ከሚመለከቱ አሳቦች ሁሉ ራሳቸውን ለይተው በምትኩ ሥነ ምግባራቸውን ‹‹በሰዋዊ›› እና ‹‹በአመክንዩ መሠረት›› ላይ ለማነጽ ይመኛሉ። በእነዚህ ጉዳዮች በአንድ ክበብ ዙሪያ ይከራከራሉ። በመጀመሪያ ‹‹እውነተኛ ሰዋዊ›› የሆነውን ነገር ያብራሩ እና ከዚያ የሥነ ምግባር ሕግጋታቸውን እሴት ከማብራሪያቸው ጋር በማነጻጸር ያረጋግጣሉ። እንዲህ ዓይነቱ የመከራከሪያ መንገድ ግን ክርክራቸው እውነተኛ መሠረት የሚጎድለው መሆኑን ብቻ ያረጋግጣል። በተመሳሳይ መንገድ ሌላም ሰው ‹‹ሰዋዊ›› ለሚለው ቃል የግሉን ማብራሪያ በመስጠት ሰዋዊነቱን ከገለጻው ጋር በማነጻጸር ማረጋገጥ ይችላል። ከዚሁ ጋር በተግባር ሲታይ በርካታ የማያምኑ ሰዎች ይበልጥ በጥበብ እንደሚኖሩ መቀበል ይገባናል። እንደዚህ ዓይነት ጽንሠ አሳቦችን በመከተል ፈንታ በይፋና በተግባር የሚታዩትንና የሚገለጹትን የትክክለኛ እና የስሕተተኛ አሳቦችን መርህ ይከተላሉ። ይህ ማለት ለፍጥረተ ዓለም መፈጠርና ለሕሊና መኖር ከሚኖራቸው ክህደት በተቃራኒ የሕሊናቸውን አገዛዝ ይከተላሉ ማለት ነው።

በሌላ በኩል ክርስቲያኖች ከዚህ በተለየ መነሻ ነጥብ ያስተምራሉ፤ ያደርጋሉም። የእግዚአብሔርን ሕልውና፤ ፍጥረት በእግዚአብሔር መፈጠሩንና እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ውስጥ ራሱን መግለጡን ይቀበላሉ፤ ያምናሉም። ይህ መገለጥ ‹‹ሥጋ በሆነውና በእኛ መካከል ባደረው›› በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ይገኛል (ዮሐ. 1÷14)።

እንደ እውነቱ ከሆነ እውነተኛው የእግዚአብሔር እውቀት በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ የሚገኝ ከመሆኑ የተነሣ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሥነ ምግባርን ማስተማር ትችላለች የሚለውን አመለካከት የሚያራምዱ ክርስቲያን ሊቃውንት እንደነበሩ አሳይተናል። እንደዚህ ያለው አመለካከት ግን ስሕተት

መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህም ለምን እንደሆነ ቀደም ብለን አሳይተናል (ምዕራፍ 5 መጀመሪያ)። በኃጢአት በወደቀው ሰው ውስጥ እንኳ ትክክልና ስሕተት ስለ ሆኑ ነገሮች የተወሰነ እውቀት አለ። ሕሊና ተብሎ የሚጠራ ጠንካራ ወይም ደካማ ድምፅ ይሰማል። ይህ እውነታ የማያምኑትንም ሰዎች ይመለከታል። ክርስቲያኖች ባልሆኑና በማያምኑ ሰዎች መካከልም አንዳንድ ጊዜ ከፍ ባለ ደረጃ የሥነ ምግባር ሥርዓቶች መኖራቸውንም መቀበል ይገባል። እንደዚህ ዓይነት ሥነ ምግባራዊ አስተሳሰቦች ጥቂት ባልሆኑ አጋጣሚዎች በርካታ ክርስቲኖች በእምነታቸውና በሕይወታቸው ከሚያሳዩት ሥነ ምግባር ይልቃል። ስለዚህ ክርስቲያች ሁሉ በእውነት መልካም ለሆነው ነገር የሚቆምንና ክፋውን ነገር የሚቃወምንና የሚከላከልን ሥነ ምግባራዊ ትምህርትና ተግባር መቀበል ይገባቸዋል።

## አማኝ ላልሆኑ ሰዎች ለምን በሁሉም ነገር እውቅና ሊሰጣቸው እንደማይገባ

በመጀመሪያ ተለያይተው ሊቀመጡ የሚገባቸው ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛው ነገር አማኝ ያልሆኑ ሰዎች በሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው አሳብና ባህሪያቸው ነው፤ በትክክለኛውና በስሕተተኛው መካከል እውነተኛ ልዩነትን የሚያስተምሩና የሚጠብቁ ከሆኑ በእነዚህ ነጥቦች እውቅና ሊሰጣቸው ይገባል፤ ምክንያቱም ክፉን ሁሉ በመቃወም በሚደረገው ተጋድሎ በትክክለኛው ጎራ ውስጥ ናቸውና። ሌላው ነገር የሃይማኖትና የእምነት ጉዳዮችን በተመለከተ ያላቸው አቋም ነው። እነዚህ ወገኖች ሥነ ምግባራዊ አስተምህሮአቸውንና ተግባራቸውን ከሐሰተኛ ሃይማኖት ወይም ከፍጹም ኢአማኒነት ጉዳዮች ጋር ሲቀላቅሉ ይስተዋላል። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ አመለካከቶቻቸውና አስተምህሮአቸው ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም። በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት ትምህርት ካለ ለሥነ ምግባራዊ አስተምህሮአቸው እውቅና መስጠቱ በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ለሚያስተምሩት ነገር እውቅና እንደ መስጠት ተደርጎ ሊምታታና ሊወሰድ

አይገባም፡፡ ሥነ ምግባራዊ ሥርዓታቸውን ክርስትና ስሕተት መሆኑን ‹‹ለማረጋገጥ›› እና ለማምከን ከተጠቀሙበት ‹‹ሥነ ምግባራቸውን›› ወደ ሃይማኖታዊ ሥርዓት በመለወጥ የክርስትና እውነተኛ ጠላቶች ይሆናሉ፡፡ እነዚህ ምሳሌዎች ከሥነ ምግባር ጋር አንዳንድ ጊዜ በሚያያዙበት ጊዜ ሐሰተኛ ሃይማኖታዊ አሳቦቻቸው ሳይሆኑ ሥነ ምግባራዊ መርሆዎቻቸውና የኑሮ ዘይቤዎቻቸው በክርስቲያኖች እውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

ምንም እንኳ የመልእክቱ አራማጆች ራሳቸውን ሃይማኖተኛ እንዳልሆኑ በይፋ ቢናገሩም ብዙ ጊዜ ሃይማኖታዊ አሳቦች ከሥነ ምግባራዊ አመለካከቶች ጋር እንዴት እንደሚደባለቁ ስለምናውቅ እነዚህን መርሆዎች በአእምሮ መያዝ አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህ እውነታዎች እጅግ በርካታ ዓለማዊ የሥነ ምግባር ሥርዓቶች ለምን ዓላማዎቻቸውን ማሳካት እንደማይሆንላቸውና ከዚያም አልፎ ለምን ሥነ ምግባር በጎደለው ባሕርይ እንደሚደመድሙ ያስረዱናል፡፡ አንድ ሥርዓት በመጠኑ ጤናማ በሆነ ሥነ ምግባራዊ መርሆዎች ላይ ከተመሠረተ በኋላ በውስጡ ሁሉንም ሃይማኖቶች÷ እግዚአብሔርንና ዓለምን መፍጠሩን የሚጠላ ከመሆኑ የተነሣ ሥነ ምግባር የጎደላቸውን ከዚያም አልፎ የጭካኔ ድርጊቶችን በመደገፍ ይጠናቀቃል (ሮሜ 2÷14፤ 1÷28-32)፡፡

## ከክርስቲያናዊ የሥነ ምግባር ትምህርት ‹‹የተዋሱ አመለካከቶች››

በርካታ የአስተሳሰብ ሥርዓቶች በሥነ ምግባርም ጭምር በክርስቲያናዊ አስተምህሮ ተጽዕኖ እንደደረሰባቸው የተሰወረ አይደለም፡፡ በመሆኑም በእነዚህ ሥርዓቶች ውስጥ መጀመሪያ ያልነበሩ ‹‹የፍቅር፤›› ‹‹የታማኝነት››÷ ‹‹የልግስና››÷ ‹‹የወንድማማችነት›› ወዘተ... አሳቦች አሉ፡፡ ስለዚህ ክርስቲያናዊ ትምህርት ብዙዎች አሳባቸውን የሚቀዱበት የጋራ ምንጭ ሆኗል፡፡ በ‹‹ሰው ማስተዋል›› ብቻ እንደሚተነተኑ የሚነገርላቸው በርካታ እግዚአብሔር የለሽ የሥነ ምግባር ትምህርቶች ጅማሬአቸው

በኢየሱስ እና በሐዋርያቱ ትምህርት ውስጥ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ የአጀማመሩን ምንጭ ለማሳየት ስለዚህ እውነት መከራከር አስፈላጊ አይደለም፡፡ እውነታውን መቀበልና ክርስቲያናዊ አስተምህሮውን እጅግ ግልጽ በሆነ መልኩ ማቅረብ የተሻለ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ዓለምና የተለያዩ የሥነ ምግባር አመለካከቶች ለመላው የሰው ዘር ጥቅም የሚሆነውን ነገር የሚቀዱበትን ምንጭ በይበልጥ ያገኛሉ፡፡

## መንግሥት÷ ሥነ ምግባርና ግብረ ገብነት

ቀደም ሲል እንዳየነው ሥነ ምግባር ሊገኝ የሚችለው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ ነው ብሎ መናገር ሙሉ በሙሉ ስሕተት ይሆናል፡፡ ሰዎች አማኞች ሆኑ ወይም የማያምኑ ግብረ ገብነት ሊተገበር የሚችለው በግለሰቦች ብቻ ይሁን እንጂ ግብረ ገብንና የሥነ ምግባር መርሆን አስመልክቶ የሚሰጠው ትምህርት የመላው ማኅበረ ሰብ እና ማኅበረ ሰቡ በመንግሥትነት ተደራጅቶ ከሆነ የመንግሥቱም ጉዳይ ነው፡፡

የሥነ ምግባር እና የግብረ ገብ ጥያቄዎች ለሁሉም ሰዎች ሕይወት እጅግ በጣም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ‹‹መንግሥትም እርስ በርስዋ ከተለያየች ያች መንግሥት ልትቆም አትችልም›› (ማር. 3÷24)፡፡ አንድ ሕዝብ እንደ ሕዝብ መቀጠል ከፈለገ የሥነ ምግባር ጉድለትን ለመፍቀድ ወይም ለማበረታታት አደጋ ሊጋለጥ አይችልም፡፡ ነገር ግን በበርካታ የዓለም ክፍሎች ሰዎች እንዲህ ወደ ሆነ ሁኔታ እጅግ መቅረባቸው በጣም የሚያሳዝን እውነታ ነው፡፡ ምናልባት በግልጽ ሳይሆን ይልቁንም ይበልጥ ምስጢራዊ በሆነ ሌላ መንገድ ተደርጎ ይሆናል፡፡ ‹‹ግላዊ ነፃነት››÷ ‹‹ግላዊ ምርጫ››÷ ‹‹ግላዊ አቋም›› ወዘተ... በሚሉአቸው ቃላት ሽፋን ሥር ወይም በይፋም ጭምር ማኅበረሰቡ ምንም ዓይነት ሥነ ምግባራዊ እሴቶችን በአባላቱ ላይ መጫን እንደማይችል እና ሊሞክረው እንደማይገባው ተዘውትሮ ይነገራል፡፡ በመሆኑም ማኅበረሰቡ (‹‹የመንግሥት›› እና የመሳሰሉት) ‹‹ገለልተኛ›› ሆነው መቆየት እንደሚገባቸው ይናገራሉ፡፡ ይህ ደግነት የሞላበትና

ምክንያታዊ ቢመስልም እጅግ በተለየ መንገድ ሊተረጎምም ይችላል። ለምሳሌ ወጣቶችን÷ የመዝናናት ፍላጎታቸውን እና ጥያቄያቸውን ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል የሚሠሩ ኃይላት አሉ። እነዚህ ኃይላት ከባለ ሥልጣናቱ የሚተላለፉ ፍንጭ ጠቋሚ ምልክቶችን ለተጨማሪ ፕሮፓጋንዳ እና ብዝበዛ ይጠቀሙባቸዋል። ይህ በሁሉም ዘመናውያን አገሮች ውስጥ ለአያያዝ እጅግ የሚያስቸግር ነገር ነው። መንግሥታትና ሌሎች ባለ ሥልጣናት በእንደዚህ ዓይነት ኃይላት የሚከናወኑ ጤናማ ያልሆኑ ንግዶችን ለማስቆም እርምጃ እንዲወስዱ ዘወትር ይጠየቃሉ። ነገር ግን ፓርላማዎችና መንግሥታት ሥነ ምግባርን÷ ግብረ ገብን ወይም መልካም ባሕርይን በሰዎች ላይ በኃይል መጫን አይችሉም። ሕግን በማውጣት ይህንን ለማድረግ ከሞከሩ ውሸተኝነትን እና ግብዝነትን ብቻ ያስከትላል። በሌላ በኩል የሕጋዊ ባለ ሥልጣናቱ ‹‹ገለልተኝነትም›› የዚያኑ ያህል ውሸት ይሆናል። ሁኔታው በመላው ዓለም ንግዳቸውን እንዴት እንደሚጠብቁና ሥነ ምግባራዊ አመለካከቶችንና እሴቶችን እንዴት እንደሚሸራርፉ በሚያውቁ ኤጀንሲዎች ይበዘበዛል።

አንዳንድ ጊዜ የሕጋዊ ባለ ሥልጣናት ዓላማ ‹‹ዝቅተኛው የሥነ ምግባር ደረጃ›› ብቻ መጠበቅ እንደሚገባው እና ‹‹የላቀ የሥነ ምግባራዊ ልኬቶች›› እንዲኖር ለመወትወት እና ለመሥራት መስኩ ለግለሰቦች÷ ለመንፈሳዊ ድርጅቶችና ለቤተ ክርስቲያን ክፍት ሆኖ መተው እንዳለበት አሳብ ይቀርባል። ይህ አሳባቸው ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችል ቢመስልም ትልቅ አደጋ አለበት። ባለ ሥልጣናት ‹‹ገለልተኛ›› ሆነው መቆየት እንደሚገባቸው ቀደም ሲል ከተጠቀሰው አሳብ ጋር እጅግ የሚቀራረብ ነው። በተጨማሪም ‹‹ዝቅተኛ ሥነ ምግባር›› የሚለውን ብዙዎች ‹‹በተቻለ መጠን ዝቅ ያለ ልክታ›› አድርገው ሳይገነዘቡት አይቀሩም። እንደዚህ ዓይነት አስተሳሰቦች ያለ ጥርጥር ሥነ ምግባራዊ እና ግብረ ገባዊ ዝቅጠትን ወይም ማሽቆልቆልን ያስከትላሉ። ይህንን ታላቅ ችግር እዚህ ላይ ሙሉ በሙሉ ለማስረዳት መሞከር የማይቻል ነው፤ ነገር ግን ጥቂት ነጥቦችን መጠቆም ይቻላል።

## ሕግ ሊሠራ የሚችልበት መንገድ

ሕግን በመውጣት ሥራ ዓለማዊው ማኅበረሰብ በሕዝቡ ውስጥ መኖር የሚገባውን እጅግ በጣም ጠንካራ የፍትህ ስሜት መግለፅ ይገባዋል። የትኞቹም ሃይማኖተኞች ወይም አማኞች የሆኑ ሰዎች እንደዚህ ዓይነት ሕግጋትን ለአገራቸው በትእዛዝ ማስጻፍ ስለማይችሉ ሕግ አውጪዎች በጎ ፈቃድ በሚኖራቸው ሰዎች የሚፈለገውንና ተቀባይነት ያለውን ነገር መከተል ይኖርባቸዋል። ይህ ማለት ሕግጋቱ በማስተዋል÷ አመክንዮታዊ በሆኑ ሰዎች ሕሊናና በጤናማ የሕይወት ተሞክሮ መሠረት መጻፍ ይገባቸዋል። እንደዚህ ዓይነት መርሆዎች በተባበሩት መንግሥታት ተቀባይነት ባገኘው ‹‹ዓለም ዓቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ›› ውስጥ ይገኛሉ። ይህ ድንጋጌ የሁሉም አገራት ዜጎች እስከ ታቻለ ድረስ እንዲስማሙበት÷ በከፍተኛ ደረጃም ተግባራዊ እንደያያደርጉት እንደ ምሳሌ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። በቀጣይነት ወደ ጥቂት የተወሰኑ ‹‹የሰብዓዊ መብቶች›› ጉዳዮች ተመልሰን መመልከት ይገባል።

እዚህ ላይ በተጠቀሱት ‹‹አንቀጾች›› ውስጥ ‹‹የሕሊና ነፃነት›› መሠረታዊ ነው። መንግሥታት ሕግጋታቸውን በእነዚህና በተመሳሳይነት በቀረቡ አሳቦች መሠረት መጻፍ÷ ከዚያም በፍትህ አካላታቸው ለምሳሌ በፖሊሶች÷ በፍርድ ቤቶች÷ በከፍተኛና የበላይ ፍርድ ቤቶች÷ ወዘተ... አማካይነት ጠብቀው ማቆየት ከቻሉ የሁሉም ሰዎች ነፃነትና አቋም በመጠኑም ቢሆን በሚገባ ሁኔታ ይጠበቃል። በዚህ መንገድ እያንዳንዱ ዜጋ ከሁሉ የተሻሉ ናቸው ብሎ በተቀበላቸው የሥነ ምግባር መርሆዎች መሠረት ማሰብና ተግባራዊ ድርጊት ማከናወን ይቻላል። ይህ ማኅበረሰቡን በሚመለከት ለሥነ ምግባር ጉዳዮች ገለልተኛ መሆን አይደለም፤ ይልቁንም ለሥነ ምግባር እሴቶችና ለከፍተኛ ክብር ልኬታዎች መቆም ነው፤ ይህም በዝርዝር ጉዳዮች በእሴቶቹ ላይ የበላይ መሆን አይደለም፤ ነገር ግን በማኅበረሰቡ ውስጥ ለእነርሱ በቂ ስፍራ መስጠት ነው።

በሌላ በኩል መንግሥታት፥ ፍርድ ቤቶችና የመንግሥት የሥራ ክፍሎች እርምጃ ሊወስዱ፥ ሊያዙ፥ ሊለኩም የሚችሉት ባላቸው ውጫዊ መሣሪያዎች አማካይነት ውጫዊ ጉዳዮችን ብቻ ነው። እንደዚህ ዓይነት ባለ ሥልጣናት የሰዎችን አስተሳሰቦች ወይም ሕሊናዎች አይገዙም። ስለዚህም መንፈሳዊ ጉዳዮች፥ ስሜት ነክ አስተሳሰቦች፥ ዝንባሌዎች፥ ምርጫዎች እና ሕሊና በመንግሥት ባለ ሥልጣናት ሊወሰኑ አይችሉም። ከመንፈሳዊው እይታ አንጻር ትክክለኛው ምን እንደሆነ እንዲመረምሩና እንዲፈትሹ፥ በሚቻልበት ቦታ ሁሉ በጉዳዮቹ ላይ ሌሎቹን እንዲመክሩና እንደዚህ ዓይነት አመለካከቶች ለሕግ አውጪዎችና ለባለሥልጣናት እንዲታወቁ የማድረግን ኃላፊነት እንዲወስዱ እነዚህ ጉዳች ለሚመለከታቸው ግለሰቦች፥ ቡድኖች እና ድርጅቶች እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያንና ለመሳሰሉት መተው ይገባቸዋል። በዚህ መንገድ በማኅበረሰቡ ውስጥ በሥነ ምግባራዊ ምክንያቶች ምን መለወጥ ወይም መሻሻል እንደሚገባው በጥልቀት ለማወቅ ይቻላል። በሌላ በኩል በሕጋዊ መንገድ ሊሠራ የሚችል ሙሉ በሙሉ ፍትሐዊ እና ሥነ ምግባራዊ የሆነ ሥርዓት በዚህ ዓለም አይገኝም። ይሁን እንጂ በዚያ አቅጣጫ መሥራትና መልፋት፥ ጥረትም ማድረግ የሁሉም ግዴታ ነው።

## እነዚህ መርሆዎች የሚያስከትሏቸው ውጤቶች

በማኅበረሰቡ (በመንግሥት) እና በግለሰብ ዜጎች ሥነ ምግባር መካከል ያለው ግንኙነት በበላይና በበታች ሠራተኞች መካከል ያለ ግንኙነት ተደርጎ ሊቆጠር አይችልም፤ አይገባውምም። የባለ ሥልጣናት ሥነ ምግባር ከዜጎች ሥነ ምግባር ከፍ ያለ ነው የሚል አባባል የለም። ባለሥልጣኖችም በማስገደድ የተወሰነ ግብረ ገባዊ ልክታን በማስገደድ ከዜጎቻቸው መጠየቅ ወይም በእነርሱ ላይ መጫን አይችሉም። በሕጎችና መመሪያዎች መሠረት መታዘዝን እና መፈጸምን ከዜጎቻቸው መጠየቅ ይችላሉ። የሥነ ምግባርና የግብረ ገብ ኃይላት ሌሎች መሥመሮችን ተከትለው ይሠራሉ፤ የአንድ ሕዝብ ሥነ ምግባራዊ ልክታዎች ወደላይ

የሚነሱት በተለየ መንገድ ነው። በሕግ÷ በመንግሥት ትእዛዝ ወይም በሕግ አስከባሪነት አይደለም። ጥቂት ምሳሌዎች ይህንን አባባል ለማረጋገጥ ይበቃሉ።

በታሪክ ውስጥ በተወሰኑ ወቅቶች የአንዳንድ ሕዝቦች ሥነ ምግባራዊ ልክታዎች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነበሩ፤ ያን ጊዜ ማጭበርበር÷ ዝርፊያ÷ ጥቃቶች÷ ማመንዘርና ዝሙት የተለመዱ መለያ ባሕሪያት ነበሩ። እነዚያ ሰዎች በዚያ መንገድ እስከ መጨረሻቸው ስላልቀጠሉ ለውጡ እንዴት መጣ? ከለውጦቹ በስተጀርባ ያሉት ሕግ አርቃቂዎች ወይም ባለሥልጣናት አልነበሩም። ባለሥልጣናቱ ሞክረውት ከነበረ ብዙ ጊዜ በከንቱ ነበር የጣሩት፤ ሊሳካላቸው ከጀመረ እና ከተሳካላቸው በሕዝብ መካከል ጥቂት ሕሊናቸው የነቃ ሰዎች ወይም አንድ ነቢይ የማንቂያውን ደወል ገመድ አስቀድመው ሲስቡት መቀስቀስ ስለነበረ ነው። በአንድ ሕዝብ መካከል የሥነ ምግባራዊ ለውጦች ግልጽ ምልክቶች ሲኖሩ በአነስተኛ ደረጃ የሚከሰተው ሁልጊዜ ይህ ነው።

በሕዝብ መካከል መነቃቃት በሚኖርበት ጊዜ ሁሉንም ዓይነት ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች መሸፈን ይገባዋል። በዚህ ነጥብ ላይ በመላው ዓለም ማለት ይቻላል በአሁኑ ጊዜ ትልቅ ችግር አለ። የሚዛናዊነት ስሜቱ የጠፋ ይመስላል። ሥነ ምግባርን በተመለከተ በበርካታ የሥራ ክፍሎች የባለሥልጣናቱ ልጓም ሲላላ ኢኮኖሚያዊና ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ ግልጽ የሆነና የደረቀ መጠናከር አለ። ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች በማኅበረሰቡ ሕይወት በርካታ መስኮች ውስጥ አነሰም በዛ ቸል ሲባሉ የብዙዎቹ የሥራ ክፍሎችና ሌሎች ባለሥልጣናት ጥረት ገቢን በማስታወቅ÷ በግብርና በገንዘብ ልውውጥ እንቅስቃሴ ወዘተ... ላይ ተያይዘው በሚፈጸሙ ‹‹ገንዘብ ነክ ወንጀሎች›› ላይ የተነጣጠሩ ናቸው። ይህ ሕጋዊ ኃይል በሌሎች የሥራ ክፍሎች ካለው ብቃት የለሽ የአሠራር ቅደም ተከተል ጋር አብሮ አይሄድም። ለእነዚህ እውነታዎች የተወሰኑና ግልጽ የሆኑ ማብራሪያዎች ይኖራሉ። አንዱ ‹‹ገንዘብ›› የሚባለው እውነተኛ

ያልሆነ አምላክ በበርካታ ቦታዎች ላይ መግዛቱ ነው፡፡ ሌላው ማብራሪያ የሥነ ምግባር አጠቃላይ አስተምህሮ በብዙዎች ዘንድ÷ በትምህርት መስክ÷ በአብያተ ክርስቲያናት ወዘተ... በመርገቡና በማሽቆልቆሉ ይህንንም አካሄድ ብዙዎች በሕጋዊና በሕገ ወጥ መንገዶች ጥቅማ ጥቅሞችንና ገንዘብን ለራሳቸው ለመሰብሰብ እንደ ጠቋሚ ምልክት ስለ ወሰዱት ነው፡፡ በመሆኑም ደካማ የመንግሥት የሥራ ክፍሎችና ሌሎች ባለሥልጣናት ‹‹አልጋህን እንዳነጠፍከው ልትተኛበት ይገባሃል›› የሚለውን አባባል በራሳቸው ላይ እያረጋገጡት ይገኛሉ፡፡

በወንጀሎች ላይ በሚወሰዱ የተለያዩ እርምጃዎች የተሻለ ሚዛናዊነት እንዲኖር በይበልጥም በሰዎች የልብ ዝንባሌ ላይ እውነተኛ ለውጥ እንዲመጣ ለመሥራት ከፈለግን ግለሰቦች÷ ባለሥልጣናት÷ መንፈሳዊ ድርጅቶች ከሁሉ በላይ ቤተ ክርስቲያን÷ አብረው መሥራታቸው አስፈላጊ ነው፡፡ በመንግሥት ባለ ሥልጣናት÷ በፍርድ ቤቶችና በተቋማት ወዘተ... ሊቀረጽ የሚገባው መመሪያ ሕግጋትን ለመታዘዝ÷ ለማክበር÷ መልካም ሥነ - ምግባራዊ አመለካከትንና ድርጊትን ለመደገፍ÷ በሁሉም ስፍራ መልካም ሕሊና በጥሩ ግምት ለመያዝ የሁሉም ሰዎች ትብብር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ በሁሉም መስክ ሲደረግ ብቻ የአሁኑ ሚዛን የለሽነት በተሻለ ነገር ሊለወጥ ይችላል፡፡

## ክርስቲያናዊ የሥነ ምግባር አስተምህሮ እንዴት ሊቀርብ ይገባዋል?

በሁሉም ዓይነት ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ሕግጋትን አለማቅረብ እጅግ በጣም አፈላጊው ነገር ነው፡፡ ለዚህም ሁለት ጠንካራ ምክንያቶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ በሁሉም የሥራ ዓይነቶች ወይም የሕይወት መስኮች ውስጥ እውነቶቹን በጥልቀት አናውቃቸውም፤ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ በሁሉም ዓይነት ነገሮች ላይ አመለካከታችንን ለመጫን እንሞክርና ክርስትና እንዳይከበር እናደርገዋለን፡፡ ሁለተኛ ለሕይወት ሁኔታዎች ሁሉ ዝርዝር ሕግጋትን ለመጻፍ ከሞከርን የእውነተኛ ክርስትናን

ባሕርይ እንለውጥና ስለ ክርስትና ምንነት የተሳሳተ ግንዛቤን ለሰዎች እንሰጣለን። በዚህ ሂደት ውስጥ አካሄዳችን ሕገኝነት ብቻ ይሆንና ሰዎችም እንደዚያ ይገነዘቡታል፤ አስተምህሮአችንም ለመሸከም የሚከብድ ‹‹ከባድና አስቸጋሪ ሸክም መጫን›› ይሆናል (ማቴ. 23÷4)። ከእነዚህ የተሳሳቱ መንገዶች የትኛውንም ስንከተል በክርስቲያናዊ የሥነ ምግባር አስተምህሮ ውስጥ ልናስብበት የሚገባውን አንድ ነገር እንስታለን፤ ይህ የምንስተው ነገር በሥነ ምግባር እንዲሁም በደኅንነት ወንጌል ውስጥ ሁሉም ነገር በኢየሱስ ክርስቶስ ማዕከልነት ዙሪያ መሆኑን ነው። በአንዱ ነገር ማለትም በደኅንነት እርሱ አልፋና ያሜጋ እንደሆነ ሁሉ በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርም ውስጥ እርሱ አልፋ ያሜጋ ነው።

በወንጌል እና በክርስቲያናዊው ሥነ ምግባር መርሆዎች መካከል ሕያው ግንኙነት አለ። በዚህ ነጥብ ላይ ብዙ ሰዎች በእምነታቸውም÷ በአኗኗር ዘይቤያቸውም ይወድቃሉ። አንዳንዶቹ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው ሊይዙት ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን ሥነ ምግባራቸውንና ግብረ ገባቸውን የራሳቸው ማድረግ ይመኛሉ። ይህም ‹‹ግላዊ ነፃነታቸው›› እና ‹‹አቋማቸው›› ብለው የሚጠሩት ነው። በሌላ በኩል ኢየሱስን እንደ ሥነ ምግባር መምህር አድርገው ሊከተሉት በመፈለግ በግብረ ገብ ተምሳሌነት ሊይዙት የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። ዳሩ ግን እንደ እግዚአብሔር ልጅ እና የሰው ዘር አዳኝ እውቅና ሊሰጡት አይፈልጉም። በተጨማሪም እርሱ ከረጅም ጊዜ በፊት ያስተማረው ትምህርት በብዙ ነጥቦች ላይ ዘመኑ ያለፈበት በመሆኑ ‹‹ይበልጥ ዘመናዊ የሆነው ጊዜ እና ኅብረተሰብ በሚጠይቀው›› ነገር ሊተካ እንደሚገባው ያምናሉ። ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት የነገሮች እሳቤ እንደ ክርስቲያናዊ እይታ ሊቆጠር አይችልም።

ክርስቲያናዊ የሥነ ምግባር አስተምህሮ በጠንካራ ክርስቲያናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ላይ መመሥረት ይኖርበታል። እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ማን መሆኑን÷ ስለ እግዚአብሔር÷ ስለ ራሱና ስለ መንግሥቱ÷ ስለ ሰውና ስለ ዓለም÷ ስለ ጊዜ እና ዘለዓለማዊነት እርሱ ምን እንደሚያስተምር

በመጠየቅ መጀመር ይገባዋል፡፡ ትክክለኛ የሕይወት ምጣኔ እና የሕይወት አቅጣጫ ማግኘት የሚቻለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ከትክክለኛው ነጥብና ከእግዚአብሔር ፈቃድ መጀመር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ያለ ፈቃዱ እውቀት ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር መናገር አንችልም፡፡

ኢየሱስ እንደዚህ ዓይነት መነሻ ነጥብ አሳይቶናል፡፡ ‹‹የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል›› (ዮሐ. 7÷17)፡፡ አንድ ሰው በዚህ መንገድ መጓዝ ሲጀምርና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ሲሞክር÷ ወዲያውኑ ይህን ለማድረግ ምን ያህል እንደምንችል÷ በእግዚአብሔር እና በመሰሎቻችን ፊት በትክክለኛው መንገድ ለመኖር እውነተኛው እርዳታ የት ቦታ ላይ እንደሚያስፈልገን ይረዳል፡፡ በመሆኑም በሥነ ምግባር ወይም በግብረ ገብ ደንቦች ለመኖር የቃሉ ብርሃንን÷ የእርዳታን÷ የብርታትን÷ የደኅንነትን÷ የአዲስ ልደትን÷ ወዘተ... አስፈላጊነት አረጋግጦ ያሳያል፡፡ ይህ ሁሉ በኢየሱስ አስተምህሮ ውስጥ በቃላት÷ በምስሎች÷ በምሳሌዎች እና በድርጊቶች ተካትቷል፡፡ ‹‹እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም፡፡›› ‹‹ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ፡፡›› ‹‹ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም›› (ዮሐ. 14÷6፤ 14÷15፤ 15÷4)፡፡ በመሆኑም በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርና ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒታችን መሆኑን በእውነት በማመን መካከል ያለው እጅግ ተቀራራቢ ግንኙነት አስፈላጊነቱ ተዘውትሮና ተጠናክሮ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አጽንዖት ተሰጥቶታል፡፡ ለምሳሌ በእነዚህ ዓይነት ቃላት ‹‹እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ፤ ሥር ሰድዳችሁ በእርሱ ታነጹ፤ እንደ ተማራችሁትም በሃይማኖት ጽኑ፤ ምስጋናም ይብዛላችሁ›› (ቈላ. 2÷6፤ 7)፡፡

# ምዕራፍ 6

# እምነትና ሕይወት

ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ከእምነት ከተነጠለ እንደሚገባ ልንረዳው ወይም በተገቢ መልኩ ልናደንቀው አንችልም። እምነትና ሥነ ምግባር ሁለቱም ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ላይ ጥገኛ ናቸው፤ ነገር ግን ይህ ግላዊ ወይም የተናጠል ግንኙነት ብቻ አይደለም። ክርስቲያን ሁልጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ አባል ነው፤ ማለትም የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ እና የዓለም አቀፋዊቷ ቤተ ክርስቲያን አባል ነው ማለት ነው። እነዚህ ግንኙነቶች በተለምዶ በ‹‹ቀኖና›› ውስጥ ከሌሎች የክርስቲያናዊ አስተምህሮ ጉዳዮች ጋር አብረው የሚስተናገዱ በመሆናቸው በሥነ ምግባር ጉዳዮችም ውስጥ ለአስፈላጊነታቸው አጽንዖት ለመስጠት ሲባል ብቻ እዚህ ላይ ተጠቅሰዋል።

## የእምነት አስፈላጊነት

ዓለማዊ የሥነ ምግባር ሥርዓቶች ከአንድ ዓይነት እምነት ውጭ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ሲሆን ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ግን እንደዚያ አይችልም። ይልቁንም የሥነ ምግባር መርሆዎች በአንድ ክርስቲያን ድርጊቶችና በአጠቃላይ በሕይወቱ ላይ ተጽዕኖ እንዲያሳድሩ ከተፈለገ እምነት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህን እንዴት ማብራራት ይቻላል? ቀደም ሲል ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግላዊ ግንኙነትና በክርስቲያን ግለሰቦችና በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት ጠቅሰናል። እነዚህ ግንኙነቶች በበርካታ መንገዶችና በተወሰኑ መሳሪያዎች አማካይነት በጠራ ሁኔታ የሚገለጹ ናቸው። እነዚህም መሣሪያዎች ጥምቀት፥ የእግዚአብሔር ቃል፥ መንፈስ ቅዱስ፥ ቅዱስ ቍርባን እና በዚህ ጉዳይ የማኅበረሰብ አካል ከሆኑት ሌሎች ክርስቲያኖች ጋር የሚደረግ ኅብረት ናቸው። መንፈስ ቅዱስ

ደግሞ ዳግም ልደትን÷ እምነትን÷ የመፅደቅ አዋጅን እና ከዚህ በኋላ ተሐድሶንና መቀደስን የሚያስገኝ ወኪል ሠራተኛ ነው። እነዚህን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእግዚአብሔር የሚሰጡ ስጦታዎችን ሰው የሚቀበላቸው በእምነት አማካይነት ነው። በመሆኑም በአማኙ የዕለት ተዕለት ሕይወትና ሥራው ውስጥ የመንፈሳዊ ኃይል ምንጮች የሚከፈቱለት በእምነት አማካይነት በመሆኑ እምነት በሥነ ምግባርም ውስጥ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

እነዚህ እውነታዎች በኦግስበርግ የእምነት መግለጫ መከላከያ ጽሑፍ አንቀጽ III ላይ በሚገባ የተገለጹ ናቸው። ‹‹በእርግጥ እምነት መንፈስ ቅዱስን ከማምጣቱና በልብ ውስጥ አዲስ ሕይወትን ከማስገኘቱ የተነሣ በልብ ውስጥ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን መፍጠር አለበት። እነዚህ እንቅስቃሴዎች ምን እንደሆኑ ነቢዩ ኤርምያስ 31÷33 ላይ ‹‹ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ።›› ሲል ያሳያል። ስለዚህ በእምነት ስንጸድቅና ዳግም ስንወለድ እግዚአብሔርን መፍራትና መውደድ÷ ወደ እርሱ መጸለይ÷ ከእርሱ እርዳታን መጠበቅ÷ እርሱን ማመስገንና ማወደስ÷ በመከራ ውስጥ እርሱን መታዘዝ እንጀምራለን። ልባችን መንፈሳዊና ቅዱስ የሆኑ እንቅስቃሴዎች ስለሚኖሩት ማለትም (በዚህ ጊዜ በክርስቶስ መንፈስ አማካይነት አዲስ ልብ÷ አዲስ አእምሮ እና አዲስ መንፈስ በውስጣችን ስለሚኖር) ባልንጀራችንን መውደድ እንጀምራለን። በእምነት እስካልጸደቅንና ዳግም እስካልተወለድን እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን እስካልተቀበልን ድረስ እነዚህ ነገሮች ሊከሰቱ አይችሉም፤ ምክንያቱም በመጀመሪያ ሕጉ ያለ ክርስቶስ እውቀት (እርሱን አለማወቅ) ሊጠበቅ አይችልምና ነው፤ እንዲሁም ያለ መንፈስ ቅዱስ ሕጉ ሊጠበቅ አይችልም። ጳውሎስ በገላትያ 3÷14 እንደሚናገረው መንፈስ ቅዱስን መቀበል የምንችለው በእምነት ነው። እርሱም በእምነትም የመንፈስን ተስፋ እንድንቀበል የሚል ነው።

## እምነትና መንፈሳዊ በጎነት

አንድ ክርስቲያን ከእግዚአብሔርና ሰው ጋር ሊኖረው የሚገባው ትክክለኛው ግንኙነት በአሠርቱ ትእዛዛት ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል (ዘዳ. 10÷1-7)። ‹‹ዓለም ዓይኖች ፊት ምንም ያህል ታላቅ ወይም የከበረ ቢሆን ከአሠርቱ ትእዛዛት ውጪ የትኛውም ሥራና ነገር መልካም ወይም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሊሆን እንዳይችል÷ መላው ሕይወታችን እግዚአብሔርን ደስ ያሰኝ ዘንድ÷ ለመልካምም ሥራ ምንጭና መተላለፊያ መንገድ እንዲሆን መለኮታዊ አስተምህሮና የተሟላ ጽሑፍ የሆኑት አሠርቱ ትእዛዛት ተሰጥተውናል›› (ትልቁ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ)

ከአሠርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያው ክፍል ከሌሎች የተለየ ቦታ አለው፤ ይህም በሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛው ምክንያት በመጀመሪያ ላይ የተቀመጠ ሲሆን በዚህም ከሁሉም ቀዳሚነቱን ያመለክታል። በሁለተኛ ደረጃ የተቀሩትን ሁሉ ያጠቃልላል። አንድ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር በትክክለኛ ግንኙነት ውስጥ የሚመላለስና በዚህ ትእዛዝ መሠረት በእርግጥ የሚኖር ከሆነ የቀሩት ትእዛዛት ሁሉ ይከበራሉ። ‹‹የመጀመሪያውና ዋናው ትእዛዝ ትርጉምና እውነተኛ ፍቺም ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ የሚለው ነው፤ ሌሎቹ ሁሉ ሊጎርፉበትና ሊከተሉት የሚገባው እርሱ ነው። እጅግ ግልጽ በሆነ ትርጓሜው ከዚህ ያለፈ ሌላ የሚጠይቀን ነገር የለም፤ ‹‹እንደ ብቸኛ እውነተኛ አምላክህ እኔን ፍራ፤ ውደድ፤ በእኔም ታመን። ልብ ወደ እግዚአብሔር እንደዚህ በሚያዘነብልበት ቦታ ይህንንና ሌሎች ትእዛዛትን ሁሉ ይፈጽማል። በሌላ በኩል በሰማይና በምድር ያሉትን ሌሎች ማናቸውንም ነገር የሚፈራና የሚወድ ማንም ሰው ይህንን ወይም የትኛውንም ትእዛዝ አይጠብቅም። በመሆኑም መላው መጽሐፍ ቅዱስ በየቦታው እነዚህን ሁለት ነገሮች ማለትም እግዚአብሔርን መፍራትን እና በእርሱ መታመንን ዘወትር ዓላማው አድርጎ ይህንን ትእዛዝ ይሰብካል÷ ያሰርጻልም።›› (ትልቁ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ)

የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ከሰዎች ትእዛዛት ሁሉ ማስቀደማችን የእውነተኛ መንፈሳዊነት ባሕርይ ክፍል ነው። ይህ አባባል በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ ልንከተላቸው የሚገቡንን በርካታ መመሪያዎችና ደንቦች ወላጆች÷ መምህራን÷ የበላዮች አለቆች÷ ወዘተ... ሲሰጡን ትክክል ሊሆኑ እንደሚችሉ አይክድም። ነገር ግን በተወሰኑ ሰዎች አልፎ አልፎ የሚሰጡትን ልዩ ልዩ ትእዛዛትን በእግዚአብሔር ከተሰጡት ትእዛዛት የማስቀደም ፈተና አንዳንድ ጊዜ ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ ይኖርብናል። በእርግጥ የእግዚአብሔር ትእዛዛት በዘመናት ሁሉ ለሁሉም ሰዎች እና ሁኔታዎች ተገቢ መሆን ይገባቸዋል። በሰዎች መካከል የሚሰጡ ትእዛዛትን በእርሱ ትእዛዛት ብርሃን አማካይነት ብቻ መገንዘብና መገምገም የሚቻል ይሆናል። ማርቲን ሉተር ስለ አሥርቱ ትእዛዛት ትምህርቱን ሲያጠቃልል እነዚህን አስተያየቶች እንደሚከተለው ይጽፋል፤

እዚህ ላይ አንድ ሰው እነዚህን ትእዛዛት ለመጠበቅ ማለትም ጭምትነት÷ ትዕግሥት÷ ጠላቶችን መውደድ÷ ንጽሕና÷ ቸርነት÷ ወዘተ... እና እንደዚህ ዓይነት ሥነ ምግባር የሚያስከትላቸውን ለማድረግ እጆቹ ሙሉ ይሆናሉ (በቂ ነገር ይኖረዋል)። ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ሥራዎች በዓለም ዓይኖች ፊት ዋጋ የሚሰጣቸውና ለታይታ የሚቀርቡ አይደሉም። ምክንያቱም በተወሰኑ ጊዜያት÷ ቦታዎች÷ ወጎችና ሥነ ሥርዓቶች የተገደቡ ልዩና የትዕቢት ሥራዎች ሳይሆኑ አንዱ ጎረቤት ለሌላው ሊያደርጋቸው የሚችል÷ የተለመዱ÷ የዕለት ተዕለት የቅርበት ሥራዎች ናቸው። ስለዚህ ከፍ ያለ ግምት አይሰጣቸውም። ሰዎች ከአሥርቱ ትእዛዛት ጋር የሚስተካከል ሌላ አስተምህሮ ወይም እሴት ከማግኘታቸው በፊት ረጅም ጊዜ ይወስድባቸዋል፤ ምክንያቱም ትእዛዛቱ እጅግ ከፍ ያሉ ከመሆናቸው የተነሳ ማንም ሰው በሰብአዊ ኃይል ሊደርስባቸው አይችልምና ነው። ሊደርስባቸው የሚችል ማንም ሰው ቢኖር እርሱ ሰማያዊ÷ ከምድር ቅድስና ሁሉ በላይ መልአካዊ ሰው ነው። ራስህን ሰጥተህ ልትፈጽም የምትችለውን የመጨረሻውን

ነገር ብታደርግ÷ ኃይልህንና ችሎታህን ሁሉ ብትጠቀም÷ የምታደርገው ነገር እጅግ በዝቶ ከማግኘትህ የተነሣ የትኛውንም ሌላ ሥራ ወይም ቅድስና አትፈልግም፤ ወይም አታደንቅም።›› (ትልቅ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ)

## እምነትና መታዘዝ

የተለያዩ የመታዘዝ ዓይነቶች አሉ። ባሪያ ወይም የማይታዘዝ አገልጋይ በበርካታ አጋጣሚዎች የሚታዘዝ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን በዛቻ ወይም በአስገዳጅነት ሥር የሚፈጸም መታዘዝ ነው። ከእምነት ጋር የተያያዘው መታዘዝ ግን ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ መድኃኒቱ የሚያምን ሰው ‹‹በክርስቶስ›› ነው። እርሱ ‹‹አዲስ ፍጥረት›› ነው (2 ቆሮ. 5÷17)። እንደዚህ ዓይነት ሰው በቀደሙት ግንኙነቶች ትስስር ‹‹በሰንሰለትና በገመድ ማሰሪያ›› ውስጥ በመኖር ፈንታ ወደ አዲስ መተማመንና ሙሉ በሙሉ አዲስ ወደ ሆነ ግንኙነት ውስጥ ገብቷል። ‹‹እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው›› (ገላ. 2÷20)። በአዲሱ ሕይወት ውስጥ አንድ ዓይነት ኃይል ወይም ግፊት አለ፤ ይህ ግን የፍቅር ኃይል ነው። ‹‹የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያውስ ሁሉ ሞቱ፤ በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሳው እንጂ ወደፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ›› (2 ቆሮ. 5÷14-15)።

ይህ መታዘዝ ለሚያምን ክርስቲያን እውነተኛ ምልክት የሚሆን የመታዘዝ ዓይነት ሲሆን እርሱም በብዙ መንገዶች መብራራት ይችላል። ቅዱስ ጴጥሮስ እንደሚለው÷ ‹‹በውድ እንጂ በግድ ባልሆነ›› ሁኔታ የሚፈጸም የፈቃደኝነት መታዘዝ ነው (1 ጴጥ. 5÷2)። ቅዱስ ጴጥሮስ ለሕይወት ዘይቤያችን ክርስቶስ ራሱ የሰጠንን ምሳሌም ይጠቁመናል። ‹‹የተጠራችሁለት

ለዚህ (የመከራ ሕይወት) ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና›› (1 ጴጥ. 2÷21)።

በዚህ ነጥብ ላይ በሁለት ጽንፈኛ አቋሞች መካከል ሚዛናዊነት አስፈላጊ ነው። በአንድ በኩል ሰዎች የመለወጥን÷ የእምነትንና የዳግም ልደትን አስፈላጊነት ችላ እስኪሉ ድረስ ርቀው መታዘዝንና የክርስቶስን መልካም ምሳሌ መከተልን ብዙ ጊዜ አጽንዖት ሲሰጡ ተስተውሎአል። በሌላ በኩል በርካቶች ተቃራኒውን በማድረግ መለወጥንና የእምነትን ወዘተ... አስፈላጊነት ብቻ አጽንዖት በመስጠት የመታዘዝን አስፈላጊነት ችላ ብለዋል። የኋለኛው የአስተሳሰብ መንገድ የሚያስከትለው ውጤት ምን ይሆናል? ቢያንስ ቢያንስ ፍቅር የለሽ እምነት ወይም ‹‹ከሥራ የተለየ እምነት›› ይሆናል። እንደዚህ ያለ ‹‹እምነት›› የሞተ ነው (ያዕ. 2÷26)። ይህም በሌሎች መንገዶች ባገኘናቸው ጽንፈኛ አሳቦች መሠረት ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ በተማርነው መሠረት ማስተማርና ማመን ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ያሳየናል።

የእግዚአብሔርን ሕግ መታዘዝ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ዳሩ ግን ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ በመከተል ክርስቲያን ሊሆን እንደማይችል ሊታወስ ይገባል። ክርስቲያን መሆንና ሆኖም መቀጠል ሁልጊዜ የጸጋ ጉዳይ ነው። በሌላ በኩል የትኛውም ክርስቲያን ከሕግ ሙሉ በሙሉ ነፃ መሆን አይችልም። ሕጉ ባለማቋረጥ ወደ ክርስቶስ ዘወር እንድንል የሚያስገድደን ‹‹ሞግዚት›› መሆንና ሆኖ መቆየት ይገባዋል (ገላትያ 3÷24)። በክርስቶስ የሆነውን አዲስ ሕይወት በምንኖርበት ጊዜ ትሑታን ሆነን እንድንቆይ÷ እንደ ‹‹ሕግ ሥራ ሳይሆን›› አዲሱ ሕይወት በፍቅርና በመታዘዝ ከእኛ የሚጠየቀውን ነገር እንዲያሳየን÷ ይልቁንም የእምነትና የፍቅር ፍሬ ሆኖ ይመራን ዘንድ ሕጉ ያስፈልገናል። ‹‹ሰው በእግዚአብሔር መንፈስ አዲስ ሲወለድና ከሕግ ነፃ ሲወጣ ማለትም ከዚህ ነጂ ኃይል ሲፈታ እና በክርስቶስ መንፈስ ሲመራ በሕጉ ውስጥ በሚገኘው

በማይለወጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት ይኖራል። እንደ ገና በመወለዱም ማንኛውንም ነገር ከነፃ የደስተኝነት መንፈስ ተነስቶ ያደርጋል፤ እነዚህም በተገቢ ሁኔታ የሕግ ሥራዎች ተብለው የሚጠሩ ሳይሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎችና ፍሬዎች ናቸው። ወይም ቅዱስ ጳውሎስ የአእምሮ ሕግ እና የክርስቶስ ሕግ ብሎ የሚጠራው ነው (ሮሜ 7÷23)። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚለው ከእንግዲህ ‹‹ከሕግ በታች ሳይሆኑ ነገር ግን ከጸጋ በታች ናቸው›› (የስምምነቱ መመሪያ)።

ይህ የጉዳዩ አንድ ገጽታ ነው። ሌላኛውን ገጽታ ከተመለከትን የሕጉንና የመታዘዝን አስፈላጊነት እንገነዘባለን። ‹‹የሚያምኑ ሰዎች በውስጣዊ ሰውነታቸው በእግዚአብሔር ሕግ በእርግጥ ደስ ይላቸዋል፤ ነገር ግን በአካላቸው ክፍሎች ውስጥ ያለ ሕግ ከአእምሮአቸው ሕግ ጋር ይቃረናል። በመሆኑም ያለ ሕግ አይደሉም÷ ነገር ግን ከሕግ በታች አይደሉም፤ ነገር ግን በሕግ ውስጥ ናቸው፤ በጌታ ሕግ ውስጥ ይኖራሉ፤ ይመላለሳሉ፤ ሆኖም ከሕጉ አስገዳጅነት የተነሣ የሚያደርጉት ምንም ነገር የለም›› (የመጽሐፈ ስምምነት መመሪያ)።

## ‹‹መንፈሳዊ›› እና ‹‹ዓለማዊ›› የሆኑ ነገሮች

ስለ መታዘዝ በምናወሳበት ጊዜ ቀደም ሲል በአጭሩ ከላይ ወደተመለከትነው ‹‹የአእምሮ እና የልብ ዝንባሌ›› ተመልሰን መምጣት ይኖርብናል። ይህ አመለካከት በሥነ ምግባር ሁሉ አስፈላጊ ነው፤ በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ደግሞ ይበልጥ አስፈላጊ ነው። ይህም በብዙ ምክንያቶች ነው፤ ውጫዊው ሥራ በልባችን እና በሕሊናችን ውስጥ ባሉ መንፈሳዊ ኃይላት ካልተመራና ካልተደገፈ ውጫዊ ሥራ ብቻውን ምናልባት ሐሰተኝነትና የግብዝነት ይሆናል። ለምሳሌ የልግስና ሥራዎች በሰው ልብ ውስጥ ካልተፈጠሩ ብዙም ሳይቆዩ አሰልቺ ድግግሞሽ ይሆናሉ፤ ወይም ፈጥነው ይቋረጣሉ። እንደገናም ለመሰሎቻችን የፍቅርና የልግስና ሥራዎች እንድንፈጽም የሚያደርገን እውነተኛ

ኃይል የፍቅር ውስጣዊ ዝንባሌ ብቻ ነው። የኛ ተፈጥሮአዊ የልብ ዝንባሌ እንዲገዛን ከተፈቀደለት አዘውትሮ በሌላ መንገድ እንድንተገብር ይነግረናል።

በዚህ ቦታ የምንመለከተውና በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውስጥ ያሉት ትክክለኛ ምስጢራት ነው። እነርሱም ከ‹‹ተፈጥሮአዊው ሰው›› መንፈስ በተቃራኒው ያሉት ፍቅርና ክርስቲያናዊ ‹‹መንፈስ›› ናቸው። በእርግጥ ከሌሎች ሰዎች ሁሉ የተሰወሩ በሚሆኑበት መንገድ የተደበቁ አይደሉም። በተቃራኒው ምስጢርነታቸው አብዛኛውን ጊዜ እጅግ ግልጽ በሆነ መንገድ ጉልህ ሆነው ይታያል። ምስጢሩ በሰው ውስጥ እንዴት ሊከሰቱ ይችላሉ? በጭራሽ ወደማይወደዱ ይልቁንም ጠላትነት መሆን ወደሚፈልጉ ሰዎች እንዴት ሊያመሩ ይችላሉ? የሚል ነው። ለእንደዚህ ዓይነት ምስጢራት ብቸኛውን እውነተኛ ማብራሪያ የምናገኘው ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሕይወቱን ለዓለም እስኪሰጥ ድረስ በኃጢአት የወደቀውን ዓለም ወዷል። በመሆኑም ለሁሉም ክርስቲያኖች ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን፤ እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፤›› የሚለው ማሳሰቢያ ሊሰጣቸው ይችላል (ፊልጵ. 2÷5-7)። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱም፡- ‹‹ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና›› ይላል (ማቴ. 11÷29)።

በዚህ ነጥብ ላይ÷ ከውጫዊ ግልባጭ እጅግ በላቀ ሁኔታ÷ ውስጣዊ÷ መንፈሳዊ ብርታትና ኃይላት እንዲሁም ክርስቶስን የመከተል ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በመላው ዓለም ላይ ላሉት ሥነ ምግባራት ሁሉ የሚያበረክተው ታላቅ አስተዋጽዖ አለ። ይህ አስተዋጽዖ በዓለም ላይ ከሚታወቀው አጠቃላይ ትእዛዝና ኢየሱስ በጥልቀት ‹‹ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው›› ብሎ ካስተማረው ቃል ጋር አብሮ

ሊጤን ይገባዋል (ማቴ. 7÷12)። ይህ ሁሉ ‹‹ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም›› ያለው ክርስቶስ እርሱ ከእውነተኛ ሥነ ምግባራት ሁሉ ጀርባ ያለ ብርቱ ኃይል ራሱ ክርስቶስ መሆኑን ይጠቁመናል (ዮሐ. 15÷5)።

## በዓለም እንጂ ከዓለም አለመሆን

በክርስቶስ ያለ እምነትና ክርስቶስን መከተል ‹‹በዓለም ውስጥ›› መተግበር አለባቸው። በመሆኑም አንድ ክርስቲያን ዘወትር የሁለት መንግሥታት ማለትም የመንግሥተ ሰማይና የዓለማዊ መንግሥት ወይም አገር ዜጋ ነው። በዚህ የዜግነት ጉዳይ ላይ በሁለት መንገድ ማለትም አንዱን መርጦ ሌላውን በመተው ወይም ለአንዱ አጽንዖት በመስጠትና ሌላኛውን ቸል በማለት ወይም የተገላቢጦሹን በማድረግ መሳሳት ይቻላል። መንግሥቱን በተመለከተ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዴት እንዲያደርጉ እንደሚፈልግ በግልጽ አስተምሯቸዋል። በአንድ በኩል ‹‹ከዓለም አይደሉም›› በሌላ በኩል ‹‹ወደ ዓለም ልኳቸዋል›› (ዮሐ. 17÷16-18)። ምንም እንኳ ይህ ፈጽሞ ተቃራኒ ቢመስልም የቃላቱ ትርጉም ግልጽ ነው። ደቀመዛሙርቱ ‹‹ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት የፈለሱ›› ስለሆኑ ከዚህ በኋላ የወደቀው ዓለም (ቈላ. 1÷13) አስተሳሰብና መንፈስ ሊኖራቸው አይገባም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር እስከፈቀደ ድረስ በዚህ ውጫዊ ዓለም ላይ መቆየትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሆነውን ነገር ማከናወን ይኖርባቸዋል።

በዚህ ነጥብ ላይ ብዙዎች ክርስቲያኖች ተብለው የተጠሩ ነገር ግን ከክርስቲያን መንገድ ያፈነገጡ ሌላ ነገር አስተምረዋል። ‹‹እውነተኛ ክርስቲያን›› እና እውነተኛ ‹‹መንፈሳዊ›› ለመሆን ‹‹ዓለማዊ›› ግንኙነቶችን ሁሉ ለምሳሌ አገራዊ ሙያዎችንና ሥራዎችን መተው አስፈላጊ ነው ብለዋል። በጥብቅ አነጋገር እንደነዚህ ዓይነት አስተሳሰቦች ከተሳሳተ ግንዛቤ የሚመነጩ ናቸው። በዚህ ምድር የሚኖሩ ሁሉ በሰው አካል ውስጥ መኖር

ስለሚኖርባቸው በዚህ ዓለም ላይ የሚኖር ማንም ‹‹መንፈሳዊ›› ብቻ መሆን አይችልም፡፡

በዓለማዊ ሙያዎችና ሥራዎች መደበኛ ተግባራችን በራሱ ኃጢአት ካልሆነ በስተቀር መልካም ሥራና እግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኝ ነው፡፡ በሕጋዊ የዕለት ተዕለት ሥራችን የተቻለንን ሁሉ በማድረግ እኛንና ለሥራችን የተመቻቸ ሁኔታዎች የፈጠረውን እግዚአብሔርን ማክበርና ማሞገስ እንደዚሁም በምናደርገው ሥራ እኛን የሚመስሉንን ሰዎች ማገልገል እንችላለን፡፡

እንግዲያውስ ክርስቲያን ምን ዓይነት ሥራዎችን መሥራት ይችላል? በአጠቃላይ ‹‹እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን›› ተብሎ ስለ ተጻፈ እውነተኛና ትሑት ክርስቲያን በተሰጠው በማንኛውም ዓይነት የሥራ ደረጃ እግዚአብሔርን ማገልገል ይችላል ለማለት ይቻላል (ኤፌ. 2÷10)፡፡

በእርግጥ በዚህ ዓለም ላይ እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኙና ለየትኛውም የሰው ዘር ምንም ዓይነት ጠቃሚ አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ሙያዎች አሉ፡፡ ይልቁንም በእንደዚህ ዓይነት ሥራዎች ውስጥ የሚሠራው ሥራ ብዙዎችን የሚጎዳና ሄዶ ሄዶ በረጅም ጊዜ ውስጥ አውዳሚ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ ጥቂት ምሳሌዎችን ብቻ ለመውሰድ በወጣቶች መካከል የሚከናወኑ የአልኮል መጠጦች÷ ንግዶችና እፆችን የሚያዘዋውሩ እና የተለያዩ የማጭበርበርና የስርቆት ዓይነት ድርጊቶችን የሚመክሩና የሚያስተዳድሩ ጉዳዮችን መጥቀስ እንችላለን፡፡

በመሆኑም ማን ሰው እውነተኛ ክርስቲያን መሆን የሚፈልግ ሰው ስለ ሥራው ወይም ሙያው ወይም ስለ ዓለማዊ ጥሪው ወይም እንዲያከናውን የሚጠበቅበትን የትኛውንም የተወሰነ ሥራን በሚመለከት ጥርጥር ከገጠመው መንፈሳዊ አማካሪውን በተለይ ካህኑን ማማከር ይገባዋል፡፡ ከገዛ ህሊናው በተቃራኒው ማድረግ ሁልጊዜ ስሕተት ነው፡፡ የቢጤውን ሰዎች ደኅንነት

የሚጎዳ ቢሆን የሰው ዕለታዊ ሥራ ከሙያው አንጻር ትርፍ ቢኖረውም በቅርብ ይሁን ቆይቶ አስከፊ ውጤቶችን የሚያስከትል ይሆናል።

## በወዳጆችና በጠላቶች መካከል

ለፍጥረታዊው ሰው በወዳጅና በጠላት መካከል ግልጽ ልዩነትን ማድረግ የሚፈቀድለት ይሆን ይሆናል። ምናልባትም በዘመዶቹና ከእርሱ ውጪ እንግዳ የሆኑ ሰዎችን በተመለከተ እንደዚህ ዓይነት ነገር ያደርጋል። በእነዚህ ነጥቦች ወደ ክርስቲያን እምነት ሲመጣ ሁሉም ነገር የተለየ ይሆናል። አማኞች ሙሉ በሙሉ አዲስ ከሆነ ግንኙነቶች ጋር ይተዋወቃሉ። ቀድሞ እንደ ጠላት የነበሩ ሰዎች ‹‹እንደ ወንድም÷ እኅት÷ እናት›› ሊቆጠሩ ይችላሉ (ማቴ. 12÷50)፤ በሌላም በኩል እንደ ክርስቲያን ወዳጆች የቆጠርናቸው ሰዎች ‹‹ሐሰተኛ ወንድሞች›› ሆነው ሊገኙ ይችላሉ (2 ቆሮ. 11÷26)። በዚህ በኩል የበለጡ ችግሮች አሉ። ጥቂት ሰዎች እንደ ፍጹም ወዳጅ ባይሆኑም እንደ ውጪ ሰዎች ግን ‹‹የገዛ ሕዝባቸውን ፈርተው በምስጢር›› የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ይሆኑ ይሆናል (ዮሐ. 19÷38)። ይህ ሁሉ በግንኙነቶች ብቻ ሳይሆን በክርስቲያን አማኞች የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ በርካታ ችግሮችን እንደሚፈጥር ግልጽ ነው። ቀጣዩ አንድ ጥያቄ ይህንን ሰው ዛሬ ብናገኘው እንዴት ልንይዘው ይገባናል? የሚል ይሆናል። ሌላው ችግር ክርስቲያኖች ስሜታቸውን በግልጽ ቢያሳዩ ከዚህ ሰውና ከሌሎችም ጋር አዳዲስ ችግሮች ይፈጠሩ ይሆናል።

በአጠቃላይ መንፈሳዊ አቋማቸውን በሚገባ ካላወቅን በስተቀር እምነትን በሚመለከት ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለ ልክ ቁርኝት እንዳንፈጥር ወይም ምሥጢረኛ አለመሆን ይመከራል ማለት እንችላለን። እርግጥ ነው የእምነት ይዞታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ሳንነጋገር ከእንደዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር ባሉን ግንኙነቶች ሩህሩህ መሆን÷ የአእምሮ ክፍትነትና ደስተኛነት

አስፈላጊ ናቸው። በሌላ በኩል የተጠቀሰው ሰው ምክርንና እርዳታን እየፈለገ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ከሰጠህ በእንደዚህ ዓይነት ምልልሶች ውስጥ የተመቻቹ አጋጣሚዎች ይኖሩ ይሆናል። ልምድ ያካበቱ ክርስቲያኖች እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮች በሚቀርቡበት ጊዜ የተለየ ስሜት የሚመስል ማወቂያ ነገር ይኖራቸዋል። በሌላው ሰው በኩል ልባዊ ፍላጎት ከሆነ÷ ጥቂት የምዘና ጥያቄዎች ይነገሩታል፤ እንደዚያ ከሆነ ወደፊት መቀጠልና ይበልጥ በግልጽ መናገር ይቻላል። በእንደዚህ ዓይነት ምልልሶች በመጀመሪያ በመጠኑ እያመነቱ በጉዳዩ ላይ እርዳታና የእግዚአብሔር ምሪት እንደሚያስፈልግህ ተረድተህ በውስጥህ እየፀለይክ ደረጃ በደረጃ ንግግሩን መቀጠል ሁልጊዜ ተመካሪ ነው። ቀደም ብለው ጠላቶች የነበሩ በርካቶች በእንደዚህ ዓይነት ቀን ወይም በኋላ ወደ አደባባይ ወጥተው ወዳጆች መሆን ብቻ ሳይሆን ከዚያ ይበልጥ እውነተኛ አማኞች እንደሆኑ የሕይወት ልምድ አሳይቷል። የመንፈሳዊ እንክብካቤ ታሪክ ስለ ኒቆዲሞስ ምሽቶች የሚናገሩ በርካታ ገጽታዎች አሉት (ዮሐ. 3÷1-15)።

በግል÷ በይፋ ወይም በፍርድ ቤት ስላደረግነው ስብሰባ ወይም የአሳብ ምልልስ በሌሎች ብንጠየቅ በዚህ ዓይነት ጉዳዮች መወሳሰብ ሊመጣ ይችላል። ከዚህ ሰው ጋር የተደረገው ስብሰባ ወይም ምልልስ ግላዊና ምሥጢራዊ ነገሮችን የማይመለከት ከሆነና ለማኅበረሰቡ አስፈላጊ ጉዳይ ከሆነ ምን እንደተከሰተና ምን ተብሎ እንደነበር ለመተረክ የሚቻልና የሚፈቅድ ይሆናል። በምትኩ ግን ምልልሱ እንደ ኃጢአት ኑዛዜ÷ እምነትን ማስታወቅ ወይም በመንፈሳዊ ጉዳዮችና የመሳሰሉ ግላዊ ጉዳዮችን የተመለከተ ከሆነ እና ምልልሱ በምስጢር ጠባቂነት ቃል ኪዳን ሥር ከተከናወነ ምንም ነገር መናገር አይፈቀድም። እነዚህ ጉዳዮች ከልክ በላይ አስፈላጊ ናቸው፤ ለሁሉም ክርስቲያኖች ስለ እነዚህ ጉዳዮች በስብከቶች÷ በትምህርቶች÷ በአነስተኛ ቡድኖች ስብስባ ወዘተ... በሚገባ ትምህርት ሊሰጥባቸው ይገባል። በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ምሥጢርን ለመጠበቅ ባለበት ግዴታ በጥብቅ መገደብ እንዳለበት አጽንዖት ሊሰጠው ይገባል፤ በ‹‹ኃጢአት

ኑዛዜ›› ከሰማው ውስጥ አንዲት ቃል ማስራጨት ቀርቶ መጥቀስ እንኳ አይፈቀድለትም።

## አማኝ ሰው የገዘፉ ችግሮችን የመጋፈጥ ሁኔታ ሲያንዣብብበት

እምነት ለሁሉም ዓይነት ችግሮችና አደጋዎች ከመቅጽበት ማቃለያ እንደሚሆን ወይም እንደ መድኃኒት እንደሚሠራ ተደርጎ በሚያምኑና በማያምኑ ሰዎች መካከል ተቀባይነት እንዳገኘ የሚያሳይ አሳብ አለ። ለእንደዚህ ዓይነት እምነት የእግዚአብሔር ቃል ድጋፍ እንዳላቸው ብዙዎች ያምናሉ። ‹‹የጻድቃን መንገድ የተደላደለች ናት›› (ምሳሌ 15÷19) የሚለውንና ‹‹ለሚያምን ሁሉ ይቻላል›› (ማርቆስ 9÷23፤ 11÷14) ሚሉትን የኢየሱስን በርካታ የተስፋ ቃላት ይጠቅሳሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅሱበት ዘዴ ግን እጅግ ተራና አተረጓጎማቸው ደግሞ ይበልጡኑ የባሰበት ነው። ጥቅሶቹን ከሌሎች በርካታ ጥቅሶችና በራሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰጠን ምሳሌ ጋራ ማነጻጸርን ይረሳሉ። ማብራሪያው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃላት ፍጻሜ ብዙ ጊዜ ከገዛ ራሳችን አሳቦች ፍጹም በተለየ መንገድ መሰጠታቸው ነው። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር መልሱን፦ ‹‹ጸጋዬ ይበቃሃል÷ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና›› በሚለው መልክ ይሰጣል (2 ቆሮ. 12÷9)። ስለዚህ ጉዳይ መናገር ከሚቻለው በላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል እንደ ማማ ጸና ግንብ ሆኖ ቆሞአል። ‹‹አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን›› (ማቴዎስ 26÷39)። የዚህ ዓይነት ጸሎት ውጤቱስ ምንድን ነው? በአንድ በኩል ‹‹እግዚአብሔርንም ስለ መፈራቱ ተሰማለት›› ተብሏል (ዕብ. 5÷7)። በሌላ በኩል ምንም እንኳ ቢሰማለትም መሠቃየትና መሞት ነበረበት፤ ጽዋውንም ጠጣ (ዮሐ. 18÷11፤ 19÷30)።

በሥቃይና በአደጋ ጊዜ የክርስቲያኖች ባሕርይ ለራሳቸው የተለየ እርዳታ በመጠየቅ ላይ ያነጣጠረ አይደለም። እንደዚህ ዓይነት መንፈስ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ሙሉ በሙሉ

የሚቃረን ነው። የኢየሱስ አስተምህሮ እጅግ ግልጽ ነው። ክርስቲያኖች ከተቀሩት የሰው ዘር ጋር አብረው ሊሰቃዩ ይችላሉ (ዮሐ. 9÷3፤ ሉቃ. 13÷1-5)። ጻድቃን ከኃጥአን ጋር አብረው ሊሰቃዩ ይችላሉ። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የአንድ ክርስቲያን የላቀ ዓላማ ራሱን በተመለከተ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈልጎ ማግኘትና ከሁሉ ይልቅ ጠቢብ ለሆነው የእግዚአብሔር ምክር ራሱን ማስገዛት መሆን አለበት። በዚህ ነጥብ ላይ በትክክል ክርስቲያኑን የሚደግፉትና የሚያበረታቱት እጅግ በጣም ጠንካራ የተስፋ ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያገኛል፤ ‹‹በመከራ ቀን ጥራኝ÷ አድንህማለሁም አንተም ታከብረኛለህ›› (መዝ. 50÷15)። ‹‹እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን›› (ሮሜ 8÷28)። በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃልና እርሱን በሚመስል ቅዱስ ምክር ላይ የተመሠረተ ክርስቲያን ጊዜያዊ መከራዎች የእግዚአብሔር ጥላቻ ወይም ቁጣ ምልክቶች እንዳልሆኑ ይታመናል። ይልቁንም ከውድቀት በኋላ ሰው ከእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በታች እንደሚኖርና አንዳንድ ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ የሆነው መልካሙ የእምነት መንገድ (ዮሐ. 14÷6) በመከራና በእንባ ሸለቆዎች በኩል ሊወስደው እንደሚችል ያውቃል (መዝ. 23÷4)። ሊያልፉበት ካለው መከራ ሁሉ በተቃራኒ ‹‹ከአሸናፊዎች በልጠው›› እንደሚወጡ በክርስቲያኖች መካከል ግልጽና የጸና እምነት አለ። (ሮሜ 8÷31-39፤ 11÷33-36)።

## እምነት ሁልጊዜ ግላዊ ሆኖ ይቀጥላል

ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንዳደረግነው አንድ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያን አንድ ብልትና አባል ብቻ ሆኖ ሊኖርና ሊሠራ እንደሚችል ሕይወቱ ግን ሁልጊዜ የማኅበረሰብ እንደሆነ በአጽንዖት ለማሳሰብ በቂ ምክንያት አለ። ይህን አባባል መቃረን የማይቻልና ቸል ሊባል የማይገባ ቢሆንም የጉዳዩ ሌላ ገጽታም እንዲሁ አስፈላጊ ነው፤ ክርስቲያኑ ግለሰብ በግሉ አማኝ መሆን ይገባዋል፤ ለግል ሕይወቱና አቋሙ በእግዚአብሔርም ፊት

ኃላፊነት አለበት። የትኛውም ዓይነት የአንድነት÷ የኅብረት ወይም የማኅበረሰብ መንፈስ ስሜት ይህንን ከክርስትና እምነት እና ሥነ ምግባር ሊያወጣው አይችልም። የክርስቲያንን ማኅበረሰባዊ ሕይወት እና የክርስቲያንን ኅብረት ከልክ በላይ አጋንኖ መናገር ግላዊ እምነትንና ሕይወትን እንዲሁም ማንኛውም ክርስቲያን ውስጥ ሊገኝ የሚገባውን የኃላፊነትን ስሜት የሚጎዳ ይሆናል። ይህ የሚሆን ከሆነ የጋራ ኃላፊነት ስሜትም ይዳከምና ሄዶ ሄዶ በመጨረሻም ይጠፋል። ይህ እውነታ ዓለማዊና መንፈሳዊ ማኅበረሰቦች እጅግ ለበርካታ ጊዜያት ባሽቆለቆሉበትና በመጨረሻም በፈራረሱበት በመላው ዓለም ላይ መጠናት ይችላል። በዚህ ነጥብ ላይ ቤተ ክርስቲያንና ሁሉም ክርስቲያኖች በተናጠልና በጋራ የእያንዳንዱ ግለሰብ ሕሊና መኖሩን እንዲሁም ለእግዚአብሔርና ለሰው ያለበትን ግዴታ መወጣቱን ባለመቋረጥ አጽንዖት በመስጠት የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው። እነዚህ ሁሉ ነገሮች በእግዚአብሔርና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ላይ ካለን ግላዊ እምነት ጋር በቅርበት የተዛመዱ ናቸው። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር «እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ... እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም። ... መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» ብሎ ነግሯቸዋል (ማቴ. 5÷13-16)።

# ምዕራፍ 7

# ባልንጀራን ማገልገል

## እንደዚህ ላለው አገልግሎት ፍቅር ያስፈልጋል

እውነተኛ ፍቅር ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚፈስስ ነው። እጅግ በጣም አስፈላጊውና ብቸኛ የፍቅር ሰነድ የሚገኘው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ነው። እጅግ በጠለቀ ትርጉማቸው ከተረዳናቸው «ማድረግ ይገባሃል» የሚሉ የሕግ አንቀጾችን አልያዙም። ይልቁኑ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃሎች እና ፍቅር ማብራሪያዎች ናቸው። እንደዚህ ዓይነቶቹ ሰነዶች «የተራራው ስብከት» (ማቴ. 5-7) እና «የፍቅር መኃልየ መኃልይ» ናቸው (1 ቆሮ. 13)። ክርስቶስ በፍቅሩ የደቀ መዛሙርቱን ልብ መሙላትና ስርስር መግባት ይፈልጋል። ያን ጊዜ እነርሱም በተራቸው [illegible]

ልታደርጉ አትችሉም» ይላል (ዮሐ. 15፥5)። በኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ በተገለጠው የእግዚአብሔር ፍቅር የክርስቲያን ሥነ ምግባር መሠረታዊ ጭብጥ እናገኛለን። «እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛም እንወዳለን» (1 ዮሐ. 4፥14)። ስለዚህ የዓለማዊ እና የፍልስፍናዊ ሥነ ምግባር ሥርዓቶች ቃል አቀባዮች የክርስቲያንን ሥነ ምግባር መውደዳቸውና መቀበላቸው ነገር ግን «ተያያዥ የድነት መሠረተ እምነቶችንና የመስቀሉን» ለመቀበል እምቢ ማለታቸው መሠረታዊ ስሕተት ነው። በአንድ በኩል እንደዚህ ዓይነት አለመስማማት አንጋር የወጣለት ምኞት ነው። በዓለማዊ ጉዳዮች ላይ፦ «የዚህን ዛፍ ፍሬ እወዳለሁ፤ ነገር ግን ዛፉ ራሱ ባይኖረኝ እመርጣለሁ።» ወይም «የዚህን ጉድጓድ ንጹሕ ውሃ እወዳለሁ፤ ነገር ግን የውሃው ጉድጓድ ራሱ ቢደፈንም ግድ የለኝም» ወደሚለው አባባል ይቀርባል።

ከእውነተኛ ፍቅር ጋር እውነተኛ ትሕትና ይኬዳል። ከእንደዚህ ዓይነት ፍቅር እውነተኛ ክርስቲያናዊ ኅብረትና ልግስና



113

ይፈስሳል። እውነተኛ ፍቅር ከቶም «እኔ ያልኩት ብቻ ካልሆነ» አይልም (1 ቆሮ. 13፥5)። ፍቅር በግዴታ ከቶም ሊፈጠር ወይም ሊወለድ እንዲሁም በውጫዊ ሁኔታዎች ሊያፈራ እንደማይችል ሁሉ ምንጩ በ«እኔ» እና «እንተ» መካከል ባለ ኅብረት ውስጥ ብቻ ይገኛል።

አስቀድሞ ሃይማኖታዊ ባልሆነ የሥነ ምግባርና የማኅበረሰብ ሕይወት ሥርዓቶች ሁሉ የእኛን ዜጎች በሚመለከት በመጠኑም ቢሆን በኋላፊነት እንጠየቃለን። በመሆኑም ይብዛም ይነስም በመላው ዓለም በእንደዚህ ዓይነት መንገድ እየተተገበረ ይገኛል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክርስቲያን ሥነ ምግባር መሠረት «የወንድማማችን ፍቅር» መሆናችንም ይበልጥ በግልጽ አጽንዖት ሊሰጠው ይገባል (1ተሰ. 4፥9)። «ሁላችሁ በአንድ ልብ ሁኑ፥ ... እንደ ወንድሞች ተዋደዱ፥ ርኅሩኆችና ትሑታን ሁኑ» (1 ጴጥ. 3፥8)። በዚህ ነጥብ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት በየትኛውም

የሥነ ምግባር አስተምህሮ ወይም መሠረተ እምነት ተወዳዳሪ ሊኖረው አይችልም። «አንተም በፍጹም ልብህ፥ በፍጹም ነፍስህ፥ በፍጹም ሐሳብህ፥ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ፤ ሁለተኛይቱም ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርሱ ዋነኛም የምትመስል ይህች ናት፤ ከእነዚህም የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም» (ማር. 12፥30-31፤ ማቴ. 7፥12)። ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳደረገው ለእንደዚህ ዓይነት ፍቅር መንፈሳዊ ኃይል ወይም ግፊቱን መስጠት የሚችል አንድም የሥነ ምግባር መምህር የለም። ከእርሱ የሚፈስ ፍቅር፥ ትምህርት እና መልካም ሥራ ይኖራል፤ ይህ ፍሰት ዘወትር በተከታዮቹም ይቀጥላል። እንደነዚህ ዓይነት መልካም ተግባራት ከሰብዓዊ ጥረቶች፥ ከትዕቢት ወይም ከአብሪት ከቶም ሊመነጩ አይችሉም። ከእውነተኛ የፍቅር ምንጭ ብቻ ሊመነጩ ይችላሉ (የሐ. 4፥14)። ይህ «እርሱ አስቀድሞ እኛን የመውደዱን» እውነታ ግልጽ ያሳያል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በሥነ ምግባር መስክ ሌላኛውን የክርስቲያን አስተዋጽዖ አጠንክረን መናገር ይገባናል። ያም



114

«ባልንጀራችን» የሚለው ቃል ነው። ምናልባትም በሁሉም ቋንቋዎች ውስጥ የሚገኘው ይህ ቃል «ጎረቤትን» የሚቀጥለው ቤት ውስጥ የሚኖረውን ሰው» ወይም ቢያንስ የሚቀርበንን ሰው ያመለክታል። በክርስቲያናዊ አጠቃቀሙ ቃሉ እጅግ የበለጠ ትርጉም አለው። ለእርሱ በተለይ ኃላፊነት እንዲኖርብን አድርጎ በተወሰነ መንገድ በእኛ ላይ ጥገኛ የሆነ ሰው ማለት ነው። በርካታ ቋንቋዎች ለምሳሌ ጀርመንኛና የስካንድኔቪያን ቋንቋዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ካለው ይልቅ ይህንን ቃል የሚገልጽ ሌላ ቃል አላቸው። በጀርመንኛ «Der Nachste» የሚለው ሊሆን ትርጉሙም እጅግ በጣም ቀረብ ከየትኛውም የተለመደ «ጎረቤት» የሚበልጥ ሰው ነው። የግድ የቤተ ሰብ ግንኙነት ጉዳይ አይደለም። በዓለማዊ ሥነ ምግባር «ባልንጀራህ» የሚለው ቃል በዚህ መንገድ ተዘውትሮ ይገለጻል። «የሚያስፈልገው የተለየ ነገር ያለው ሰው ባልንጀራህ ነው።» ሉቃስ ምዕራፍ 10 ኢየሱስ ከሁሉ ይልቅ ስለሚቀርበን አጠቃላይ ችግር አዲስ መፍትሔ ሰጥቶናል። ስለ መልካሙ ሰማርያዊ በተናገረው ምሳሌ አጠቃላዩን ጉዳይ

ከላይ ወደታች ገልብጦታል። «ከነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል?» (ሉቃ. 10÷30)። በተለምዶ አመለካከት የተደበደበው ሰው ባልንጀራ ነበር። በእርግጥ ባልንጀራ ነበር፤ ነገር ግን በተጨባጭ እውነተኛ ባልንጀራ መሆኑን በይበልጥ ያረጋገጠ አንድ ነበር፤ እርሱም የሚያስፈልገውን ነገር አይቶ ጣልቃ ለመግባትና ለመርዳት በልቡ ግፊት የተሰማው ሰው ነበር። የኢየሱስ ማብራሪያ የትም ቦታ ቢሆን ተመሳሳይ ደረጃ የማይገኝለት መንፈሳዊ እና ሥነ ምግባራዊ ኃይል አለው። ይህ አስተምህሮ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ በሌሎች ሥነ ምግባራዊ ሥርዓቶች ዘንድ አቻ የሌለው ለዓለም የተሰጠ ስጦታ ነው።

## ፍቅርን መረዳት እና በኃዘን ተካፋይ መሆን

እርግጥ ነው ውጫዊ «መልካም ሥራዎችን» በማድረግና ምናልባትም በመጠን ስራ ይዞት እና በመልካም ውጤቶች ፍቅርን

ማሳየት ይቻላል። እንደዚህ ዓይነት ‹‹መልካሞ ሥራዎች›› አንዳንድ ጊዜ በተወሰነ ደረጃ ጥልቀት በሌለው ሁኔታ ይታያሉ፤ ይመዘገናሉም፤ ይበልጥ በጥንቃቄ ከተመረመሩ ግን ብዙ ጉዳትም እንዳደረሱ ሊታወቅ ይችላል። ለምሳሌ ለልጆችና ለወጣቶች በርካታ ገንዘብ ብንሰጥ አንድ ዓይነት ልግስና እና ፍቅር ይመስል ይሆናል፤ ነገር ግን ጉጉ እንዲሆኑ፥ እንዲያጠኑ፥ ሥራ እንዲሠሩ፥ ራሳቸውን እንዲጠብቁ፥ ወዘተ... ካላስተማርናቸው ገንዘብ በመስጠት ብቻ ትልቅ ጉዳት ልናደርስባቸው እንችላለን። ከሌላም የሥራ መስክ የሚወሰድ አንድ ምሳሌ ተመሳሳይ ነገር ያሳያል። ብዙ ጊዜ ‹‹ያላደጉ አገሮችን›› በተወሰነ ደረጃ የመርዳት ጥረት በቆላማ ቦታዎች በጥልቀት የተቆፈሩ የውሃ ጉድጓዶችን በማቅረብ መልክ ይከናወናል። እርግጥ ይህ የበዛ ቸርነትና ልግስና ሊተገበር በሚገባ የታቀደ ይመስላል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ለመጠጥ ውኃ በጉድጓዶቹ አካባቢ የሚሰበሰቡት በርካታ መጠን ብዙ የቀንድ ከብቶች የአካባቢውን አፈር አራቁተውት ከዓመት ወደ

ዓመት እየጨመረ ወደሚጎዳ ምድረ በዳነት ለውጠውታል። እርዳታ የሚያስብ ‹‹ፍቅር›› ወይም ‹‹እርዳታ›› ወይም ‹‹መልካም ሥራ›› ሁልጊዜ እንደታሰበባቸውም ወይም እንደ መልካም ለሚቆጠሩ መልካም አይደሉም። አብዛኞቻችን ተቀባዮቹንና ሌሎች በርካታ ሰዎችንም ጭምር የሚጎዱ ሊሆኑ ይችላሉ። እውነተኛ ፍቅር ሁልጊዜ በዚቱ የእውቀት መጠን እና ‹‹በዚህ መንገድ ካደረግን ምን ይሆናል? በእርግጥ ሰዎችን እንረዳቸዋለን ወይስ ከምንረዳው የበለጠ እናበላሻለን?›› በሚል ቅድመ ጥንቃቄና አስቢነት የተተኮረ ነው።

በመከራ ጊዜ አንድ ጠቃሚ የሆነ ነገር ግን የማይታይ የእውነተኛ እርዳታ ክፍል ያለ ሊሆን እርሱም በሐዘን ተካፋይ መሆን ነው። የዚህ ቃል እውነተኛ ትርጉም በበሚጌት ብቻ የሚገለጽ አይደለም። ‹‹አብሮ መከራ መቀበል›› ነው። መከራ የሚቀበለውን ሰው ስሜቶች፥ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮቹንና ምናልባትም የመረጸውን መንገድ ለመገንዘብ ራስን በዚያ ሰው ቦታ በማስቀመጥ ልንረዳው ይገባናል። የጓደኛው የመፍትሔው

መንገድ ሁልጊዜ የማይገኝ ቢሆንም ተካፋይነት እጅግ ይረዳል። በዚህ መንገድ ካሰብን «ባልንጀራችንን» ሊጎዳ የሚችል ወይም መከራውን የሚያጨምር ነገር በተቻለ እናስወግዳለን። ይህ ችግር ሌላ ገፅታም አለው። ፍቅር ሁል ጊዜ በውጫዊ ድርጊቶች ለምሳሌ «በመስጠት» እና «በድርጊት» ብቻ አይገለጽም። አንዳንድ ጊዜ አንድን ነገር በመተፈል፥ አብሮ በመሰቃየት ወይም በዝምታ ብቻ በሚገለጽ አብሮነት እና ከልብ ለልብ በሆነ ግንዛቤ ከሁሉ በተሻለ መንገድ ሊገለጽ ይችላል።

የአንድን ሰው ስሜት «መረዳት» እና «አብሮ መሰቃየት» ሁልጊዜ ብዙ ከመናገር ጋር ለምሳሌ ብዙ «የማጽናኛ» ቃላትን ከመናገር ጋር አንድ ዓይነት አይደሉም። አንዳንድ ጊዜ ከሁሉ የሚበልጠው መጽናናት የሚገኘው መቼ ዝም ማለት እንዳለባቸው ከሚያውቁ ወዳጆች ነው። የኢዮብ ወዳጆች ረጅም ንግግራቸውን ማድረግ ከጀመሩበት ጊዜ ይልቅ (ምዕራፍ 4 - 25) ዝም ባሉ ጊዜ የበለጠ መጽናናት እንደሰጡት ግልጽ ነው (2፥13)።

## ከፍቅር ጋር የተያያዘ እምነትና ጥሪ

እንደሌሎች በርካታ ጉዳዮች ሁሉ በዚህም ላይ መሠረታዊው ግንኙነት እንደ ፈጣሪያችንና አባታችን ከእግዚአብሔር፥ እንደ መድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር መሆኑ አጽንዖት ሊሰጠው ይገባል። ክርስቶስ፦ «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤... ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ» ይላል (ዮሐ. 15፥16)። እዚህ ላይ የመጀመሪያው ክፍል በክርስቶስ አማካኝ በዚያም የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን የተደረገው ግለሰባዊ ጥሪ ነው። በመሆኑም የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን የተደረገው ጥሪ ተቀባይነት ሳያገኝ ስለ «ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር» ወይም ስለ «ክርስቲያናዊ ባሕርያት» ወዘተ... ጥሪ መናገሩ ጥቅም የለውም። የፊተኛው (ልጅ ጥሪ በመጀመሪያ ይመጣል። ከእርሱ በኋላ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በተለያዩ ተግባራት እግዚአብሔርን የሚገለገል ጥሪ ይመጣል።



117

ይህ ሁሉ ጸጋ ነው፤ ጸጋን ደግሞ መቀበል የሚቻለው በእምነት ብቻ ነው። «ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፤ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን» (1 ጢሞ. 1፥19)።

ይህ ሙሉ በሙሉ መንፈሳዊ የሆነ ጥሪ ከተጠና በእግዚአብሔር ጥሪ ላይ ወደሚያርፉት ወደ እምነትና አገልግሎት ጉዳዮች ዞር ማለት እንችላለን። «እኔ መረጥኋችሁ፤ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩም ሾምኋችሁ!» ምንም እንኳ እነዚህ ጉዳዮች እርስ በእርሳቸው የተዛመዱ ቢሆንም በቀጥታ እና በሥነ ምግባር መካከል ያለውን ድንበር የምናልፍበት ነጥብ ይህ ነው።

ማንኛውም ክርስቲያን ለእርሱ ክብር በሆነ መንገዶች ሁሉ እግዚአብሔርን፥ ባልንጀራውን፥ ክርስቲያንነትና ጎለማዊውን ማኅበረሰብ እንዲያገለግል ተጠርቷል። ይህ በአብዛኛው በግለሰቡ

ስጦታዎች ላይ የሚመረኮዝ ሲሆን እግዚአብሔር በወሰነውና እርሱ እያንዳንዱን ሰው በግል በሚመራበት ሁኔታ ይወሰናል። የአንድ ሰው ሥራዎችና ጥሪዎች በተለያዩ ጊዜያትና ስፍራዎች የተለያዩ ሲሆኑ፥ እንደገናም በእድሜ፥ በትምህርት፥ በሥልጠና እና በሌሎች ሁኔታዎች ላይ የሚወሰኑ ሊሆኑ ይችላሉ፤ በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል።

በእነዚህ ጉዳዮች ላይ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ከሆኑት ነገሮች አንዱ በዓለም ፊት አንዱ ጥሪ ወይም ሙያ እጅግ በጣም «የተሻለ» ወይም እጅግ በጣም «የከበረ» የመሆኑና ከተቀሩት የላቀ ዋጋ ሊሰጠው ይገባል የሚለው አመለካከት በአእምሮአችን ውስጥ ተደጋሞ ስፍራ የያዘ ነው። ይህ ሊሆን የሚችለውና ተቀባይነት የሚያገኘው በጎለማዊ አነጋገር እስከተናገርን ድረስ በተወሰነ ደረጃ ሊሆን ይችላል። በክርስቲያን አነጋገር ግን የተለየ ነው። ከዚያ ላይ ማንኛውም ነገር በኢየሱስ ክርስቶስ አስተምህሮና አገልግሎት የተለወጠ ሆኗል። እርሱ «በምንሰውም

እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ›› (ፊልጵ. 2፥8)። ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እኛም ‹‹እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ የዓለምን ምናምንቴ ነገር፥ የተናቀውንም ነገር ያልሆነውንም ነገር መረጠ፤ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ›› ይላል (1 ቆሮ. 1፥28-29)።

ከመንፈሳዊና ከሰማያዊ ነገሮች ጋር ሲነጻጸሩ ዓለማዊ ነገሮች እንዴት ያለ ዋጋ ሊሰጣቸው ይገባል? በዚህ ነጥብ ላይ በመንፈሳዊ እና ሰማያዊ ነገሮች ወይም በዓለማዊ ነገሮች ላይ በማተኮር መካከል እጅግ ቀላል ነው። በእርግጥ ዓለማዊ ነገሮች ለአንድ ክርስቲያን ሕጋዊ፥ የተከበሩና ከጌታው ጋር አብረው የሚሄዱ እስከሆኑ ድረስ ከእነዚህ የትኛውንም ቸል ሊል አይገባውም። ‹‹መንፈሳዊ›› እና ‹‹ዓለማዊ›› በሆነው መካከል

ተገቢው ሚዛናዊነት ሊያገኝ የሚፈትለው በእምነት ጽኑ መሠረት ባላቸውና የክርስቲያንነት ግዴታዎቻቸውን ባወቁ ክርስቲያኖች ዘንድ ብቻ ነው። እንደዚህ ዓይነት ጽኑ መሠረት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እውነተኛ እምነት የሚገመግ ትሕትናና ፍርሃት የለሽ አእምሮን ይሰጣቸዋል (1 ጢሞ. 3፥13)።

የዚህ ጉዳይ ሌላው ገጽታ ‹‹ሌሎች የሚያደርጉት›› ነው። ምንም እንኳ እንደ ዛፍ ቅርንጫፎችና እንደ አንድ አካል ብልቶች አብረን ብንመደብም በከፍተኛ ደረጃ እንዳችን በሌላችን ላይ ጥገኛ ያልሆንን ነን (ሮሜ 12፥3-8)። በዚህ ሁኔታ የአንድ ክርስቲያን ተግባር በአብዛኛው በውጫዊው ማኅበረሰብ ዓለማዊ አገልግሎት ውስጥ የሚመደብ፤ ሌላኛው የክርስቲያን ግዴታ ደግሞ ይበልጥ በቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብና ሕይወት መንፈሳዊ አገልግሎት ክፍል ውስጥ ሊመደብ የሚችል መሆኑ ግልጽ ይሆናል። የትም ቦታ ብንሆን ጥሪያችንን፥ ግዴታዎቻችንን እና አገልግሎታችንን ወዘተ... ብንመለከትና በጌታችን ስም በታማኝነት ብንሠራባቸው ‹‹በጌታ ድካማችን ከንቱ እንዳልሆነ›› እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን (1 ቆሮ. 15፥58)።

## በኅብረት ውስጥ ያለ ሕይወት

ለክርስቲያን ግለሰብ እምነትና በእግዚአብሔር ፊት ለሚኖረው ግላዊ ኃላፊነት ደግመን ደጋግመን አጽንዖት መስጠት ይኖርብናል። ይህ ኃላፊነት ሁሉቱንም ማለትም እምነትንና ሥነ ምግባርን ያጠቃልላል። የገዛ ራሱን ሕሊና ድምፅ መስማት የሚችል ግለሰብ ብቻ ነው። በዚያው መጠን ግን በበርካታ መንገዶች በጋራ አስተምህሮና ሥልጠና+ ድጋፍና ማበረታታት ወዘተ... ለክርስቲያን ኅብረት አስፈላጊነትም አጽንዖት መስጠት ይገባናል። ከኢየሱስ የበለጠ እነዚህን ሐቆች በአጽንዖት የተናገረ ሌላ የሥነ ምግባር መምህር የለም።

ምንም እንኳ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ግለሰባዊ ኃላፊነት ያለብን ብንሆንም ፍጹም ግለኝነት ፍጹም መነጠልን እና ብቸኝነትን ስለሚያስከትል ጎጂና ፍሬ ቢስ ይሆናል፤

ራስ ወዳድነትና ስሁብ አለምርን ምናልባትም በሌሎች ላይ መጫኑንም ያበረታታል፤ እንድናገለግላቸው የተጠራነውን ሰዎች ችግሮች እንዳናይም ያሳውረናል።

ሁላችንም በእግዚአብሔር ስለ ተፈጠርን በሰፊ ኅብረት ውስጥ እንዴት ልንተባበር እንደምንችል ኢየሱስ በቃላቱ፣ በምሳሌዎችና በድርጊቶች አሳይቶናል። እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና ሰማያዊ አባታችን ነው። እርሱ ከሁሉ በላይ እና ስለ ሁሉም ግድ የሚለው አምላክ ነው። በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔርን የማያውቁት ሰዎች እንኳ በእርሱ የተወደዱና እንክብካቤ የሚደረግላቸው ናቸው። «እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐዩን ያወጣልና፤ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና» (ማቴ. 5፥45)። በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑ ሰዎች ስለ ሁሉም የሰው ዘር ኅብረት ጥልቅ እውቀት አግኝተዋል። «እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ስለሰጠ ፍቅርን በዚህ አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል» (1 ዮሐ. 3፥16)።

ይህ የአንድነትና የኅብረት መሠረተ እምነት በአዲስ ኪዳን ጽሑፎች ውስጥ በምስሎች ተብራርቷል። አንዱ ምስል የሰው አካልንና ክፍሎቹን ይመለከታል (ሮሜ 12፥4-8)። ሌላው ምስል የቤተ ክርስቲያንን ሕንፃና እስከ ድርድር ድንጋዮች ወይም ጡቦች ድረስ ስለ ክፍሎቹ ሁሉ ያሳየናል (ኤፌ. 2፥2፤ 1 ጴጥ. 2፥4-5)። በበርካታ ሐዋርያት የተሰጡት እንደዚህ ዓይነት ምሳሌዎች በክርስቲያን አስተምህሮ ውስጥ እንግዳ ነገሮች አይደሉም። ምሳሌዎቹ ኢየሱስ ራሱ ካስተማረን ትምህርት ጋር ሙሉ በሙሉ የሚስማሙ ናቸው። እርሱ ስለ ወይንና ቅርንጫፎቹ ተናግሯል። «ቅርንጫፍ በወይን ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንደማይችለው እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም» (ዮሐ. 15፥4)።

ይህ ስለ ኅብረት የሚናገረው መሠረተ እምነት ከዚህ ቀጥሎ በምናጠናው ክፍል ውስጥ ለምሳሌ ትዳርንና ጋብቻን፥ ወላጆቻችን እና ልጆችን፥ አገራችንን፥ ዜግነትን፥ የማኅበረሰብ ሕይወትን፥ ወዘተ... ጉዳዮች ስንደርስባቸው በዝርዝር

ዕይታዎች ማለትም ከአክብሮት፥ ከአሳቢነት፥ ከባለአደራነት፥ ወዘተ... አንጻር መመልከት ይቻላል።

## ለባልንጀራችን አክብሮትና አሳቢነት ያለበት ሕይወት

«ፍቅር» ምን እንደሆነ ለመግለጽ በምንሞክርበት ጊዜ ሁሉ አደጋ አለ። እንደ ወንድማማችነት ኅብረት ያሉ እና ሌሎች ክርስቲያናዊ መልካም ባሕርያትን በምንገልጽበት ጊዜ ተመሳሳይ ነገር ይከሰታል። አደጋው ቢያንስ ሁለት መንገድ ነው። ከፊሉ ምግባር ዕይታ አንጻር ፍቅርና ሌሎች ክርስቲያናዊ መልካም ባሕርያት ከስሜቶች እጅግ በጣም የሚበልጡ መሆን ቢገባቸውም የምንነጋገርበት ጉዳይ «የስሜቶች» ወይም የሌሎች ስሜቶች አጸፋዊ ምላሽ ሊሆን ይችላል። ሌላው አደጋ ከእንደዚህ ዓይነት መልካም ባሕርያት ጋር ተያይዞ ቢጠይቁቸንን በተመሳሳይ ትርጉም ማውጫ ውስጥ እንዲተጨመሩ ግልባጭ ሰዎች አድርገን

በመመልከት መፈተናችን ነው። ሰዎች ክርስቲያኖች ሲሆኑ እጅግ በጣም ተመሳሳይ በሆነ መንገድ እንዲታዩና በባይ ማሳመር እንደሚገባቸው ማሰቡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የቆየ ክፉ ፈተና ነው። በበርካታ የክርስቲያን ክፍሎች ውስጥ ይህ ነፀታ ወደ ፅንፍ ተወስዷል። የአሚሽ ኬሚን ቀበል ያለ ጥናት+ እንደዚህ ዓይነት አሳቦች ለአዲየሱስ ክርስቶስና ለሐዋርያቱ አስተምህሮ ሙሉ በሙሉ እንግዳ መሆናቸውን ሊያሳየን ይችላል።

እነርሱ ያስተምሩት ተቃራኒውን ነው ማለት ይቻላል። ምንም እንኳ ሁላችንም በእግዚአብሔር የተፈጠርን ሰዎች ብንሆንም በብዙ ሁኔታዎች እጅግ የተለያየን ስንሆን ይህ ልዩነታችንም የሚታተበል ይሆናል። ሁላችንም አያንዳንዳችን የተወሰኑ ነፀታዎችና ስጦታዎች ያሉን ግለሰቦች ነን። በአብዛኛው መንገዶች እንኳ በመጠኑ ወይም በእጅግ የተለያዩ ናቸው። የሰዎችን ገጽታዎች ለማስማማት ወይም ለማስተካከል ከሞከርን

እንደ በግ መንጋ ይብዛዛ ሕዝብ አድርገን እንህሰዳቸዋለን። እዚህ ላይ የተባለው ነገር እንደ ባሕርይ+ ስጦታዎችና ክህሎቶች+ ዝንባሌዎች እና ስሜቶች ወዘተ... ያሉትን ተመሳሳይ ውስጣዊ ገጽታዎችንም ይመለከታል። በአንድ ስበ ወይም ማኅበረሰብ ውስጥ አባሊህን በጲዎች በመጠቀም አንድ ዓይነት ልክህ መፍጠር ከፈለግን ያለ ጥርጥር የእግዚአብሔርን ፍጥረት እንበድላለን። ግላዊ ገፅታዎችን+ ስጦታዎችንና ክህሎቶችን መግደል በእግዚአብሔር የተሰጡ በርካታ የሕይወት ዓይነቶችን እና ልዩ ልዩ ነገሮችን መግደል ነው።

ከሰዎች ጋር ባለን ኅብረት እና ከእነርሱ ጋር በምናደርጋቸው መስተጋብሮች ሁሉ በምንችለው መንገድ በውስጣዊና በውጫዊ ገፅታዎቻቸው+ በልዩነታቸውና ግለሰባዊ ስጦታዎቻቸው ወዘተ... እነርሱን ማክበር ክርስቲያናዊ ግዴታችን መሆኑን እዚህ ላይ መናገሩ ዘቱ ነው። መበደላቸው ወይም በአስፈላጊ ነገሮች ላይ በሕጉት መፈጸማቸው ወይም ኃጢአት የሆነውን ነገር ማድረጋቸው በእግዚአብሔር የተፈጠሩና እኛን መሰል ሰዎች የመሆናቸውን መሠረታዊ እውነት አያጠፋውም። በአንዲህ

አይነት አገልግሎቶች እነርሱን መሠከርና በምንችላቸው መንገዶች ሁሉ መርዳት ግዴታችን ይሆን ይሆናል፤ እንደ ዓለማዊውና ክርስቲያን ማኅበረሰብ አባላት ግን በሥራቸውና በአገልግሎታቸው ውስጥ ስራዎችን የምንፈጽመውን ስለ የመንቀሳቀስ ነፃነት ለእነርሱም ልንፈቅድላቸው ይገባል። በመሆኑም በክርስቲያን ሥነ ምግባር ውስጥ እግዚአብሔር ለፈጠራቸው ሰዎች ከበሬታ፣ ለችሎታዎቻቸውና ስለ ስጦታዎቻቸው፣ ለጥሪያቸውና ለማኅበረሰቡ ሕይወት ለሚያበረክቷቸው የተለያዩ አስተዋጽዖዎች እውቅና መስጠት ጽኑ መርህ ሊሆንልን ይገባል። ከሰውነት አካልና ከክፍሎቹ ጋር የተደረገው ንፅፅር ይህን ጥበብ ሙሉ በሙሉ ግልጽ ያደርገዋል (ሮሜ 12፥4-8)።

እንደ እኛው ሰዎች የሆኑትን ስለ ማክበር እና ስለ እነርሱ ማሰብ እዚህ ላይ የተባለው ነገር ሌላ ተመሳሳይ የሆነውን እውነት አይቃረንም። ያም በመካከላችን ሊኖር ስለሚገባው የአንድነት

አስፈላጊነት ነው፤ ይህ እውነታ በእነዚህ ቀና ቀና አሳቦች ውስጥ ከበርካታ ጥያቄዎች ጋር ተያይዞ አጽንዖት ተሰጥቶታል፤ ከላይ በአካል ክፍሎች መካከል ያለው ታላቅ ልዩነት በተገለጸባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ውስጥ ይህ አንድነት በንክር መነገሩን መጠቆም ይበቃል። ስለ አንዱ ብልት ልዩ መሆን አጽንዖት ሲሰጥ እና በዚያው መጠን አካል አንድ ከመሆን የተነሳ በመካከላቸው ያለውን አንድነት በዓይነ ምንም ተቃርኖ የለበትም። «እንዲሁም ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፤ እርስ በእርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን» (ሮሜ 12፥5)።

## ባለ አደራነት እና ኃላፊነት

«ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደተበጁ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. 11፥3)። በመሆኑም ለተፈጠሩት ነገሮችና በአጠቃላይ ለፍጥረት ያለብንን ኃላፊነት በሚገባ እምነት ከሁሉ የበለጠ አስፈላጊ መሆን ይኖርበታል። በእምነትም እግዚአብሔርን በማገልገል ውስጥ ባለ አደራዎች መሆናችንን ለማስታወስ

እንገደዳለን። በዚህ መንገድ ብቻ ነው በተፈጠሩት ነገሮች እና በአጠቃላይ በአካባቢያችን ለምናደርገው ነገር ተጠያቂ ልንደረግ የምንችለው።

እንደ ክርስቲያን መሠረተ እምነት ክፉ የሆነ ነገር ሁሉ ሕልውና ያገኘው በእግዚአብሔር ላይ በተነሳ አመጻ አማካይነት ነው። እንደዚያም ሆኖ የወደቀው ዓለም ምንጩ ከእግዚአብሔር እንደሆነ የሚያሳዩ በርካታ ምልክቶችና ርዝራዦች አሉት። የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ ለወደቀው ዓለም ተስፋ መኖሩን ጭምር ይነግረናል (ሮሜ 8÷19-25)። ይህ ተስፋ ከአዳኙ ጋር በቅርበት የተቆራኘ ነው፤ ምክንያቱም በእርሱ ‹‹የፅድቅ ፀሐይ›› ወጥቶአልና! (ሚል. 4÷2)።

ባለ አደራነትን በሚመለከተው የክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት ዋናው ነጥብ መክሊቶች÷ ስጦታዎች ወይም ሌሎች ነገሮች የእኛ ሳይሆኑ ይልቁንም እንድንጠቀምባቸው በእግዚአብሔር በእጃችን ላይ የተቀመጡ መሆናቸው ነው። በእነዚህ ነገሮች እርዳታ እግዚአብሔርንና ሰውን እንድናገለግል በአደራ የተሰጡን ነገሮች ናቸው። ይህንን እንዴት ማድረግ እንዳለብን ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ በማሰላሰል የራሳችንን ውሳኔዎች ማድረግ እንችል ዘንድ ባለ አደራነት ከታላቅ ነፃነት ጋር ተያይዞአል። ይህም ስለ ባለአደራነት በተሰጡት አንዳንድ ምሳሌዎች ላይ በግልጽ ተብራርቷል (ማቴ. 25÷14-30)።

የግድ በቃላት ባይሆንም በየዕለቱ ሊነሱ የሚገባቸው ጥቂት ጥያቄዎች አሉ። ‹‹እንድጠቀምባቸው የተሰጡኝን እነዚህን ነገሮች ለምሳሌ ችሎታዎቼን÷ ስጦታዎቼን÷ ንብረቴን÷ ገንዘቤን÷ ወዘተ... ከሁሉ በተሻለው ሁኔታ የምጠቀምበት መንገድ ምንድን ነው? በእግዚአብሔርና በሕሊናዬ ፊት ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው የእነዚህ ነገሮች አያያዝ ምን ዓይነት ነው?›› የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች ሌላም ገጽታ አላቸው። እነርሱን እንደ ውጫዊ ዓለማዊ ሕግ ዝርዝሮች ማየት ፈጽሞ የማይቻል ነው፤ በእያንዳንዱ አጋጣሚ ሰው ሁሉ ምን ማድረግ

እንደሚገዛቸው፣ እንደማይገዛቸው በዝርዝር የሚያስረዱትን የተብቅ ሕጋጋት ማወቃቸውንም የማይችል ነው። እንዲህ ዓይነት አሠራር ዘወትር በሌላ ክርስቲያን ተግባር ነበር። ይህ ዓይነት ዝንፈት በሥነ ምግባር ካሱኢስትሪ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን እርሱም ለማንኛውም «ጉዳይ» (ጉዳይ በላቲን ነው) ዝርዝር ደንቦችን ይሰጣል። እንዲህ ዓይነት ዘይቤ ሙሉ በሙሉ ስሕተት መሆኑ ምዕቡን ይገባዋል። ሁላችንም ባሮች ሳንሆን ነፃ ሰዎችና ባለ አደራዎች እንድንሆን ተጠርተናል። በማመዛዘን+ በሕሊናና በሀሳኔ ነጻነታችን መልካሙ+ ተስማሚና+ ተገቢ የሆነውን ማንኛውንም ጉዳይ ማወቅ መቻል ያለብን ሲሆን ሁሉን በዝርዝር በመመልከት+ በመመሪያ ዓይነት+ በክፍሎችና በንዑስ ክፍሎች በመከፋፈል አይደለም። ይልቁንም ጤናማ ሥነ ምግባር ሁሉ በታላላቅ መርሆዎች በመንፈስ የሚገዛ ይሆናል። ይህንን የክርስቲያን ሕይወት ባሕርይና ሥነ ምግባሩን የሚገነዘቡትና እነዚህን መርሆዎች እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ [illegible]

[illegible] ኢየሱስ ራሱ ይህ ጉዳይ በዚህ መንገድ መሆኑት እንዲጸለበት ነግሮናል፤ «ራሳችሁ ደግሞ ጽድቅን የማትፈርዱ ስለ ምን ነው?» (ሉቃስ 12፥57)

**በአጠቃላይ ከፍትሬት ጋር ያለ ግንኙነት**

በሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት የሚገልጥ፤ የማኅበርና የማመሠዘን አስፈላጊነትን አስመልክቶ የምንሰጠው ማብራሪያ እንደ አርምጃ ወይፈት ሊወሰድ ይገባል። ይህም በአጠቃላይ ፍትሬትን ወይም ማኅበር ይሆናል። በአንድ በኩል በትርጓሜ በሩቅ የክህደትን ማንኛውንም ነገር ስለሚያስመለክተው «አካባቢ» ብዙ በሚነገርበት ዘመናችን ይህ እጅግ የታወቀ ጭብጥ ነው። እዚህ ላይ አንዱ ችግር ወይ አንድ ናሙ ያጋደለ የብዙዎች ወገናዊነት ሊሆን ሲችል ሊላው በተለያዩ የሥራ መስኮች ውስጥ ብዙዎች ለሀብትና ለገንዘብ ያላቸው ፍላጎት ነው፤ ይህም ለተፈጥሮና አካባቢ የተለያዩ ክፍሎች አደጋ ሊሆን ይችላል።

---

የተለመደ የአንድ ጥግ ወገናዊነት በየዕለቱ ሊስተዋል ይችላል። ብዙ ጊዜ ሰዎች በተፈጥሮ አያያዝ ይህንን እና ያንን ይቃወማሉ። ምናልባት በነዳናዎች ወይም መናፈሻዎች ላይ ስለ ዛፎች መቁረጥ ወይም ደኖችን ወይም ወንዞችን ከልክ በላይ ስለመበዝበዝ፡ ግድቦችን ወይም የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎችን ወዘተ... ስለመገንባት ሊሆን ይችላል። የተቃውሞአቸው መልካም አላማና ክርክሮችን ማቅረብና የታተዱት ነገሮች መልካም አማራጮችን መጠቀም ከቻሉ እና ተቃውሞዎቹ በሰላማዊ መንገድ እስከተደረጉ ድረስ መቃወም ስሕተት አይደለም። ነገር ግን ኃይልን ከተጠቀሙና ሰዎችን ከጎዱ እንዲሁም ንብረት ካወደሙ ያ ሙሉ በሙሉ ሌላ ነገር ይሆናል። ይህ ድርጊታቸው አንዳንድ ጊዜ ከሚቃወሙት ነገር ይበልጥ የከፉ ነገሮችን እነርሱ ራሳቸው እያደረጉ መሆናቸውን ያሳያል። ሌላ ዓይነት የአንድ ጥግ ወገናዊነትም አለ። ለምሳሌ ተቃዋሚ ቡድኖች ስለ ንጹሕ አየር አስፈላጊነት ስለ «ብክለት» አደጋ እና ተመሳሳይ ነገሮች

እየተከራከሩ ወደ አንድ ቦታ መጡ እንበል፤ ወደ ቦታው የደረሱት እንዴት ነው? በቦታው የደረሱት እነርሱ ከሚቃወሙት ነገር የበለጠ አየሩን እየበከሉ በትላልቅ መኪናዎች ተጓዘው ከሆነ የገዛ ራሳቸውን ክርክሮች በእርግጥም ያለ አግባብ እየተጠቀሙበትና እየተቃረኑት ነው። የዚህ ዓይነት ምሳሌዎች በብዛት ይታያሉ።

በተጨማሪም የአንድ ጥግ ወገናዊነት ሌላም ገፅታ አለው። ብዙ ጊዜ የተቃዋሚ ቡድኖች ፍላጎት እንደ ዛፎች፥ ደኖች፥ ወንዞች እና ሐይቆች ያሉ ውብ ተፈጥሮዎችን በመከላከል ላይ ያተኮረ ይሆንና የሰዎች ውድመት እንበል የሕጻናትና የወጣቶች ጥፋት ግን ሙሉ በሙሉ ችላ ይባላል። ተቃዋሚዎቹ ቡድኖች ተሰብስበው እያለ ሌሎች ቡድኖች ከልክ በላይ አውዳሚ የሆነ በቅርቡ የወጡ መግለጫዎችን ለቦታው ወጣቶች የሚያቀርቡላቸው የእፅ ሻጮች ተወካዮች ወይም የመዝናኛው ንግድ ወኪሎች ያንን መንደር ወይም ከተማ እየጎበኙት ይሆናል። ስለ እንደዚህ ዓይነት «ብክለት» አንድም የተቃውሞ ቃል እንኳ አይሰሙም።

ስለዚህም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የበለጠ ዝርዝር ነገሮች ወደ ጎን መተው ይገባቸዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ «የአካባቢ» ጉዳዮች የተለየ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል፡፡ በመሆኑም ይበልጥ እንክብካቤ ስለሚያስፈልጋቸው አንባቢዎች በጉዳዩ ላይ የተለያዩ ሙያዊ መጻሕፍትን እንዲያነቡ ወደዚያ እንመራቸዋለን፡፡ እዚህ ላይ በተለይ እኛን ግድ የሚለን ከክርስቲያን እይታ አንጻር መርሆዎችን መመልከት ነው፡፡ እነዚህም መርሆዎች «የአካባቢ» ጉዳዮችን ለመረዳት የምንፈልግ ከሆነ ከዚህ በፊት ከተጻፈው ጥረት ይልቅ «መላውን የፍጥረትና የተፈጥሮን መስክ የሚሸፍን እጅግ ሰፊ ክልል ያስፈልጋል» የሚል መሆን ይገባዋል፡፡ ሁሉአቀፍና ውስብስብ ጉዳዮችና ሁኔታዎችን ማሰቡን ይኖርብናል፡፡ ገንዘብንና ንብረትን ብቻ ሳይሆን ስብዕናዊና መንፈሳዊ እሴቶችንም ማሰቡን ይገባል፡፡ ሰውን እንደ ተጠቃሚና ወንጀለኛ ብቻ ወይም እንደተፈጠሩ ነገሮች ጌታ ሳይሆን ከዚያ ይበልጥ እንደ ባለአደራ፣ ኃላፊነት እንዳለበት ሆኖ በእግዚአብሔር እንደተፈጠረ፣ ለገዛ ራሱ ፍላጎት፣ ጥቅም ወይም ትርፍ እዚህ እንደ ተቀመጠ ሳይሆን ፍጥረትን፣

እግዚአብሔርን፣ እና ዓለምን ከዚህም ባላነሰ ሁኔታ የእርሱን ቢጤ ሰው ለማገልገል በተፈጠረው ዓለም ውስጥ ለሰው ማዕከላዊ ቦታ የሚሰጠው ዓይነት ፍላጎት ሊኖረን ይገባል፡፡

ይህ ቤተ ክርስቲያንን፣ መሪዎቿን፣ ሰበካዎችዋንና አባላቶቿን በሚመለከት ጉዳይ እጅግ ከፍተኛ አስፈላጊነት ያለው ተግባር ነው፡፡ ከየትኛውም የቀደመ ጊዜ ይልቅ እነዚህን ጉዳዮችና ሁኔታዎች ማንሳት፣ በጉዳዩ ላይ ፍላጎት ካላቸውና ግድ ከሚላቸው ሁሉ ጋር ጥናትና የተጠናከረ ትብብር ማድረግ እንዲሁም ከምንም ባላነሰ ሁኔታ ማስተዋልና ጥንቃቄ የተሞላበት እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡ በእጃችን ላይ ያለው ጊዜ አጭር ይሆን ይሆናል፤ ምክንያቱም የሰው ዘርን ከሚያሰጉት አደጋዎች ጥቂቶቹ ለመጥቀስም ያህል ሁሉአቀፍ ተፈጥሮ እና የሰው ዘር በአጠቃላይ በብክለት፣ በረሀብ፣ በመብዛት ውስጥ ዕጦት ወደ አልቂት መሄዱ በመላው ዓለም ላይ ያንዣበበ ሥጋት ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ሰው በተፈጠሩ ነገሮች ላይ ካለው የበላይነት አስተምህሮ የተነሳ ቤተ ክርስቲያን «በአካባቢ» ጉዳዮች ውስጥ ላለው ቀውስ ኃላፊ እንደሆነች ተደርጎ ይነገራል። የሚጠቀሰውም ጥቅስ ዘፍጥረት 1+26 ነው። ሐቁ ግን ተቃራኒው ነው። ተፈጥሮን ያለ አግባብ መጠቀምና ያንን ተከትሎ የመጣው ቀውስ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ማመፃቸውን ከመቀጠላቸውና ለተጠሩለት ባለአደራነት ብቁ ባለ መሆን በስግብግብነታቸው የምድር በዝባዦች ከመሆናቸው የተነሳ ነው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ነቢያዊ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ በማንሳት የመጨረሻው ማስጠንቀቂያ መስጠትን ለሰዎች ማስታወስ ይገባታል። «ወደፊት ለእኔ መጋቢ ልትሆን አትችልምና የመጋቢነትህን ሂሳብ አስረክበኝ» (ሉቃስ 16+2)።

# ምዕራፍ 8

# ሰብዓዊ መብቶች

## ሰው ምንድን ነው?

‹‹የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ፥ ጨረቃንና ከዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጎበኘውስ ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?›› (መዝ. 8፥3-4)።

የሚከተሉት ስለ ሰው የተሰጡ አስተያየቶች በእነዚህ ዋና ዋና ሐሳቦች ዝርዝር መጀመሪያ ላይ መቀመጥ ይችሉ ነበር። የዚያኑ ያህል በመጨረሻም ላይ ሊቀመጡ ይችሉ ነበር። ይህ እውነታ ሰውን የሚመለከት ጥያቄ አስፈላጊነት ወይም የሕይወት ተዛማጅነት የሌለው መሆኑን አያረጋግጥም፤ በተቃራኒው እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ በሥነ ምግባር ላይ የተጻፉ ምዕራፎች ሁሉ ስለ እርሱ ያወሳሉ። ነገሮች ሁሉ በሰው ዙሪያ የተማከሉ ናቸው። ይህ በእርግጥ እግዚአብሔርን ከግምት ውጪ ማድረግ አይደለም። ነገር ግን እየተመለከትን ያለነው ቀኖናን ሳይሆን በተለይ ሥነ ምግባርን በመሆኑ ሰውንና የሰዎችን ማኅበረሰብ በልዩ ሁኔታ እናያለን።

ስለ ‹‹ሰው ምንነት›› የሚናገሩ አባባሎች ሁሉ ሰው በእግዚአብሔር ከመፈጠሩ እውነታ መጀመር ይገባቸዋል። እንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎችን በዚህ መጽሐፍ ዋና ዋና ክፍሎች ውስጥ በበርካታ ቦታዎች ላይ አስቀድመን አይተናቸዋል። አሁን ደግሞ በብዙ ስብከቶችና ትምህርቶች ላይ ቸል ወደሚባለው ወሳኝ ነጥብ እንመጣለን። ይህን ነጥብ ሰው ሰውን የሚይዘው እንዴት ነው? መንግሥታትና ባለ ሥልጣናት ሰውን የሚይዙት እንዴት ነው? ሀብታሞች ድሆችን እንዴት ያዩዋቸዋል? የሚል ነው። ሌላ ጥያቄም መጨመር ይገባናል፤ ድሆች እንዴት ነው

ሌሎች ድሆችን የሚይዟቸው? እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ወደ አንድ አቢይ ጥያቄ ይጠቃለላሉ፤ በዓለም ዕለታዊ ሕይወት ውስጥ ሰው ምንድነው? በራሱ ሲመረመር ሰብአዊ ፍጡር ምንድነው? ይህ ዓይነቱ ሕይወት ከልጆች፥ ካልተወለዱትና ቀደም ሲል ከተወለዱት ይጀምራል።

## የልጆች ደኅንነት

ይህም ሁሉ ሆኖ በሚወለዱበት ጊዜ በሐሴትና በደስታ ተቀባይነት የሚያገኙና እንክብካቤ የሚደረግላቸው በርካታ ልጆች አሉ። በሌላ በኩል ሲወለዱ ኀዘንና ተስፋ መቍረጥ የሚገጥማቸው ቍጥራቸው የማይገመት ልጆች አሉ። ወደ ኀዘንና የመጨረሻ የድኅነት ዓለም ይደርሱና ሕይወት ያውም ከቀጠለ፥ በኋላ ላይ ምንም የመሻሻል ተስፋ የሌለው ይሆንባቸዋል።

ይህ በአሁኑ ጊዜ ካሉት የዓለም ታላላቅ ችግሮች መካከል አንዱ ሲሆን በሚመጡት ዓመታትም እንደዚሁ ይሆናል። ብዙዎች በዚህ ምድር ላይ የሚኖሩትን በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን መመገብ የሚችል በቂ ምግብ በዓለም ላይ እንዳለ ይናገራሉ፤ ነገር ግን ምግቡን ወደ ተራቡት ለማድረስ የማጓጓዣው መንገድ ቢያንስ በቂ ወይም የተቀላጠፈ አይደለም። ከእነዚህ ችግሮች መካከል ብዙዎቹ እዚህ ላይ ያልተነሱና በሌሎች ርዕሰ ጕዳዮች ሥር የሚመደቡ ናቸው። እነዚህ የሥነ ምግባር ዋና ዋና አሳቦችን በሚመለከት በአንድ በኩል በወላጆችና በቤተ ሰቦች ኃላፊነቶች እና በሌላ በኩል በማኅበረሰቡ ኃላፊነቶች ላይ ማተኮር ይኖርብናል።

ይህንን ያህል በርካታ ልጆች በከፍተኛ ድኅነት ውስጥ ለማደግ መገደዳቸው በእርግጥ የሚያሳዝን ነው። የዚህ ችግር አንዱ ክፍል ወላጆቻቸው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ማደጋቸውና ሌላ ዓይነት ሕይወት አለማወቃቸው ነው። እነዚህ ሰዎች ሁኔታቸውን ለማሻሻል ሁሉንም እርምጃዎች ራሳቸው እንዲወስዱ ከጠበቅንባቸው እጅግ ብዙ የሆነን ነገር ከእነርሱ

መጠበቅ ይሆናል። እነዚህ ሰዎች ስለ ምን ማሰብ ይችላሉ? አንዱ መውጪያ መንገድ ባለ ሥልጣናት ሁኔታውን በጽናት አጥብቀው መያዝ ሊኖርባቸው ይችላል። የላቁ የመማሪያና የሥልጠና እድሎች÷ አካባቢያዊ ሥራዎች÷ የልጆች ደኅንነት÷ የእናቶች ደኅንነት÷ ወዘተ... የመሳሰሉትን ምሳሌዎች መስጠት ከንቱ መስሎ ይታያል። አጠቃላይ ሁኔታው በአንድ ወይም በሁለት ትውልድ ሙሉ በሙሉ መለወጥ ካልቻለ የሚመለከታቸው የፖለቲካ መሪዎች ፍላጎት እንደሌላቸው ወይም ለሹመታቸውና ለሥራቸው በእርግጥም ብቁ እንዳልሆኑ ሊገመት ይችላል።

እጅግ ከከፋው ድኅነት ይበልጥ የከፋ ነገርም አለ፤ ያም ባርነት ነው። ባርነት በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በዓለም ላይ በበርካታ አገሮች የተደመሰሰ ቢሆንም እስከ አሁንም በብዙ የዓለም ክፍሎች መኖሩ የሚያስገርም ነው። ወላጆቻቸው የራሳቸውን ዕዳ መክፈል ባለመቻላቸው ባሪያዎች ከመደረጋቸው የተነሳ ብዙዎች በባርነት ውስጥ ይወለዳሉ። ዛሬም እንኩዋን ሰዎች ከትንሽ ደመወዛቸው ላይ በቅድሚያ ገንዘብ ብድር ይሰጣቸውና እዳው ሲከማች በድንገት ሙሉ በሙሉ እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ። መክፈል በማይችሉበት ጊዜ ለተቀረው የሕይወት ዘመናቸው ለአስሪያቸው ወይም ለመሬቱ እንዲሠሩ ታስረው ይቀራሉ፤ ልጆቻቸው ደግሞ በወረቀት ላይ እንኳ ላልሰፈረ ውል በኃላፊነት ይያዛሉ። በጥቂት አገራት ልጆች በስድስት ወይም በሰባት ዓመታቸው ባሪያዎች ይሆኑና ከባርነታቸው መቼም ቢሆን ሳይወጡ ይቀራሉ። የሠራተኛ ማኅበራት እንኳ በቀን ውስጥ አሥራ አምስት ወይም ለበለጠ ሰዓታት ከመሥራት አያስቆሟቸውም። እርሻዎች ወይም የከብት ማርቢያዎች ወይም ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ባሪያዎች ባይሆኑ እንኳ በሴተኛ አዳሪነት ተሠማርተው ባሪያዎች ይሆናሉ። የተባበሩት መንግሥታት አባላት በሆኑ አገራት ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች እንዲቀጥሉ አስተዳዳሪዎች ሲፈቅዱ ዓለም ምን ነክቷት ይሆን? ይህንን ጥያቄ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደገና እንመለስበታለን።

## የቤተ ሰብ ደኅንነት

ችግሩ አንድ ዓይነት ቢሆንም የልጆችን ሁኔታ በምንጠቅስበት ጊዜ ቤተ ሰቦችንም መጥቀስ ይገባናል። በእርግጥ ለልጆቹ እጣ ፈንታ ወላጆችና ቤተ ሰቦች የተወሰነ ኃላፊነት አለባቸው፤ ነገር ግን በብዙ አጋጣሚዎች ወላጆችና ቤተ ሰቦች ልክ እንደ ልጆች ተጠቂዎች ናቸው። በመሆኑም ስለ ጉዳዩ ሊያደርጉት የሚችሉት ብዙም ነገር የለም። ከእነዚህ ቡድኖች መካከል አንዱ ለውጥ ካገኘ ለውጡ ሁሉንም ይነካቸዋል። ለውጡ መጀመር ያለበት ከልጆቹ ይሁን ወይም ከወላጆቹ ማንም መናገር አይችልም። ቢያንስ ቢያንስ የለውጥ ተስፋ ተካፋዮች መሆን ይችላሉ።

## የግለሰብ መብት

በተለያዩ ማኅበረሰቦች÷ ሕዝቦች÷ ሃይማኖቶች÷ ወዘተ... መካከል የተወሰነ ልዩነት አለ። ይህ ልዩነት በመንፈሳዊ÷ በማኅበራዊ እና በኅብረተሰብ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛው ስፍራ የሚሰጠው ለግለሰቡ÷ ለሕሊናውና ለእምነቱ÷ ወይስ ለቤተ ሰቡ÷ ለጎሳው እና በአጠቃላይ ለማኅበረሰቡ ነው? በሚለው ጥያቄ ላይ የተመሠረተ ነው።

በሁሉም አጋጣሚዎች አጽንዖት ሊሰጣቸው የሚገባ ሁለት ወይም ሦስት ነገሮች አሉ። ግለሰቡ ተለቅ ያለው ክፍል (ቤተ ሰብ÷ ጎሳ÷ ማኅበረሰብ ወይም ምንም ይሁን ምን) አባል የሆነና በዚያው የሚቀጥል ቢሆንም በገዛ ራሱ መብት ራሱን የቻለ ግለሰብ ነው፤ እንደዚያም ሆኖ መቀጠል ይኖርበታል። በመሆኑም እርሱ ልዩ ሰው ሲሆን እንደ ሰብአዊ ፍጡር እና ኃላፊነት እንዳለበት የማኅበረሰቡ አባል ሊከበር ይገባዋል። አንድም ልጅ ቢሆን እንደዚህ ዓይነት ልዩ ፍጡርና በገዛ ራሱ ማንነት እንደ ታዳጊ ዜጋ ዋጋ ያለው የማኅበረሰቡ አባል ተደርጎ ሊከበር ይገባዋል። ይህ ሁሉ የሚመጣው ልጁ ሰብአዊ ፍጡርና አንድ ግለሰብ ሰው

ከመሆኑ ሐቅ ነው፤ ይህም እውነት ነው። ሁላችንም የተለያዩ ስጦታዎች አሉን። በማኅበረሰብ መካከል መሥራትና መተባበር ይኖርብናል። ነገር ግን ግለሰቦች ካልሆንን እና በገዛ ራሳችን ችሎታ እስካልተንቀሳቀስን ድረስ ይህንን ማድረግ አንችልም። ይህ ችሎታ የሕሊናችንን፥ የአስተሳሰባችንን፥ የእምነታችንን አሠራር፥ በሕይወት ውስጥ በርካታ ነገሮችን የሚመለከት የምርጫ መብታችንን እና ሌሎችንም ያካትታል። በመሆኑም አንድ ሰው በእነዚህ ነጥቦች ላይ መብቱ ሲነካ ወይም ጥሰት ሲደርስበት ድርጊቱ ክብሩን የሚያዋርድ ነው። ከዚህም አንጻር እንደ ባሪያ ሆኖ መወለድ አሳፋሪ ነው። የዚያኑ ያህልም የተወረሱ መጥፎ ሁኔታዎችን ተከትሎም ይሁን በመሰል ፍጡራን ሆነ ተብሎ የሚደርስ ባሪያ የመደረግም አሳፋሪ ድርጊት ነው። አሁን ገና ያልደረስንበት ቢሆንም የሰለጠኑ አገሮች በመላው ዓለም ላይ ግላዊ ነፃነትን በዓለም ላይ በየትኛውም ቦታ ከአደጋ ለመጠበቅ የሚከናወኑ መልካም ሥራዎችን ሁሉ ማበረታታት ግዴታቸው ነው። ለክርስቲያኖች እና ለቤተ ክርስቲያን ደግሞ ይህ የበለጠ ግዴታ ነው።

## ዓለም አቀፋዊ ችግሮች

ሰብዓዊ መብቶችን በሚመለከት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሁሉ ተገቢው ክብር ሊሰጣቸውና እንዲከበሩም በሁሉም መንገድ ሊበረታቱ ይገባል። በመላው ዓለም ላይ ያሉ የሚያምኑም ሆኑ የማያምኑም ሰዎች ሊስማሙ በሚችሉባቸው (የኋለኛውን ቃል ተጠቀሙም አልተጠቀሙ) ምክንያቶችና ሕሊና ላይ የተመሠረቱ ናቸው። እዚህ ላይ ችግሩ ያለው በድንጋጌዎቹ ውስጥ በተጻፈው ነገር ላይ ሳይሆን ስምምነቶቹን በፈረሟቸው ሰዎች ቸል ባይነት እና ምናልባትም በተመሳሳይ ሁኔታ ስምምነቶቹን ለመፈረም ያልተስማሙት አገራት እያደረጉት ያለው ነገር ነው።

በዚህ መስክ ችግሮቹ በርካታ ናቸው። የዓለም አቀፍ ማኅበረሰቡ አባላት ለምሳሌ የተባበሩት መንግሥታት አባላት

እንዲሆኑ ለአገራት መፍቀድ አስቸጋሪ አይደለም፡፡ ሰብዓዊ መብቶችን አስመልክቶ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ መድረስም እጅግ አስቸጋሪ አይደለም፡፡ ብዙዎች ለተፈራረሙዋቸው ስምምነቶች የንግግር ድጋፍ የመስጠቱን እድል ዋጋ እንደሚሰጡት የታወቀ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ከትልልቆቹ ችግሮች አንዱ አገራት ሊከተሉት ቃል የገቡለትን ነገር የመከተልን አስፈላጊነት እንዲያምኑበት ማድረግ ነው፡፡

እዚህ ላይ እጅግ ጽኑ ከሆኑት ችግሮች መካከል ሌላኛው ብቅ ማለቱ አይቀርም፡፡ የአንድ አገር የወደፊት መሪዎች ይሆናሉ ተብለው የሚጠበቁ መሪዎች በአገራቸው ውስጥ እጅግ የከፋውን ሁኔታ ያውቁ ይሆናል፡፡ ለዚያም ችግር መፍትሔ ለመፈለግ እውነተኛ ቅድመ እርምጃዎችን ለመውሰድ ዝግጁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ወደ ሥልጣን ሲመጡ ምንም መሻሻል አይኖርም፤ አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም የባሰ ማሽቆልቆል ይኖራል፡፡ መሰናክሎቹ ምን ነበሩ? ጥቂቶቹን ብቻ ብንጠቅስ ለእውነታው እጅግ እንቀርባለን፡፡ በርካታ የፖለቲካ መሪዎች በብዙ ነገሮችና ሰዎች እጅግ ከመገደባቸው የተነሣ ከትዕይንቶቹ ጀርባ ክሮቹን ለሚጎትቱት የተወሰኑ የማይታዩ ኃይላትና ሰዎች እንደ መሣሪያዎች እንዲያውም እንደ አሻንጉሊቶች ናቸው፡፡ ከትዕይንቱ ጀርባ አሻንጉሊቶቹ እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ክሮቹን የሚስብ ጣኦታትም ይኖሩ ይሆናል፡፡ ምንም እንኳ የማያምኑና አምላክ የለሾች ከነአካቴውም ምንም አማልክት እንደሌሉ አዘውትረው ቢፎክሩም በርካታ ቊጥር ያላቸው ሰዎች ብዙ ጊዜ በአንዱ ጣዖት ቊጥጥር ሥር ናቸው፡፡ ስሙም ‹‹ገንዘብ›› ይባላል፡፡ ‹‹ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም›› (ማቴ. 6÷24)፡፡

በአሁኑ ጊዜ በዚህ ዓለም ላይ ካሉ ትልልቅ ችግሮች መካከል አንዱ ገንዘብን መውደድ ወይም ቁሳዊነት ነው፤ ይህም ዓለም ሊሰጥ በሚችለው የመደሰቻ መንገዶች ሁሉ ያውም የድሃውን ሰው አንዲት ትንሽ ጠቦት በመንጠቅ ፈንጠዚያ በሚደረግበት ጊዜ ነው (2 ሳሙ. 12÷4)፡፡ ሰው ለበለጠ ሀብት ያለው መራብና መጠማት

መርካት የሚችል አይመስልም፡፡ ሰዎች አዘውትረው የሚጠቅሱት ምክንያትም እንደ ቀልድ ይመስላል፡፡ ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን ለቀለባቸውና ድጋፋቸው ሊኖራቸው የሚገባው ነገር ከረሃብ ሳይሆን ከስስት የተነሳ ከአንድ ትውልድ ዕድሜ ባነሰ አጭር ጊዜ ውስጥ ይሰበሰብና ይወገዳል፡፡ ከዚህም የተነሣ ከፍተኛ ደኖች በብዙ ቍጥር ብቻ ሳይሆን ከቶውንም ተመልሰው እንዳይገኙ ተደርገው ይጨፈጨፋሉ፤ ተክሎችና እንስሳት ከምድር ገጽ ይደመሰሳሉ፡፡ ቍጥራቸው ይህ ነው የማይባል ጎልማሶች ሥራ የለሽ ሲሆኑ በነዚያው ከተሞች ውስጥ ያለ ቅጥ አነስተኛ ክፍያ የሚከፈላቸው ልጆች በፋብሪካዎች ውስጥ ይበዘበዛሉ፡፡ ልጆች በሴተኛ አዳሪነት በመበዝበዝ አለ አግባብ ይጎሳቆላሉ፤ ወይም ደግሞ በትልልቅ ከተሞች ለምግብ ፍለጋ የቆሻሻ መጣያ ቆርቆሮዎችን ወይም የቆሻሻ ክምሮችን ያመሳቅላሉ፡፡ ‹‹የተለመደው ጦርነት›› ፈንድቶ ሳይሆን የአንድ ጎሳ ወይም ሕዝብ አዲስና ጠንካራ መሪ በሌሎች ጎሳዎች ወይም ሕዝቦች ክሳራ ለገዛ ራሱ ጎሳ ወይም ሕዝብ በቂ ስፍራ ለማግኘት ሌሎች ጎሳዎች ወይም ሕዝቦች በሙሉ በጭካኔ ጦርነቶች ይወድማሉ፡፡ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች መሬትና ሥራ የለሽ ሆነው እያለ ‹‹ሕዝቡን ለማገልገል ራሳቸውን ሰጡ›› የሚባልላቸው አንዳንድ የአካባቢው መሪዎችና የመሬት ባለቤቶች የበለጠ ንግድ ለማካሄድ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ከተቀማጭ ሒሳባቸው ወይም ከቀበሩበት ስፍራ ያወጣሉ፡፡ ይህንን ሁሉ ማን ሊገነዘበው ይችላል? ብዙ ጊዜ የሚሞገሰው ‹‹ማስተዋላቸው›› የት ነው?

## ማጠፍያው ነጥብ የት ነው?

በእርግጥ መላው ዓለም የሚፈልገው አዲስ መንፈስን እና መስመርን ሁሉ ተከትሎ የሚመጣ መነቃቃት ነው፤ ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ለውጥ እንዴት ሊመጣ ይችላል? የጥቂት መሪዎች ሕሊና የተነካ እንደሆነ÷ ሕዝባቸው ለሚያስፈገው ነገር ሁሉ ማለትም ለረሃባቸውና ለጥማቸው ኃላፊነት ያለባቸው ሆነው ራሳቸውን በእርግጥ ሲያገኙት÷ ብዙ ከመናገር ይልቅ

ጠንክረው ለመሥራት ራሳቸውን ሲሰጡ እና የብዙዎችን ሸክም ለማንሳት በሕሊናቸው ውስጥ ያለው ጫና ሲሰማቸው ብቻ የሚቻል ይሆናል። የተወሰኑ ውጤቶች ጉልህ ሆነው እስኪታዩ ድረስ እንደዚህ ዓይነት እድገት በአንድ አገር ውስጥ ከተጀመረ ወደ ሌሎች አገሮች ይሰራጭና ለበርካቶች ኑሮ ይቀላቸዋል፤ የበለጠ ቊጥር ያላቸው መሪዎችም ‹‹በምስጢር ስመኘው የነበረው ነገር ይህ ነው፤ ነገር ግን ድፍረት አንሶኝ ነበር፤ አሁን ሌላው እንዳደረገው አደርጋለሁ›› ይላሉ፤ ሌሎች በርካቶችም ይከተሏቸዋል።

እነዚህ ሁሉ ችግሮች አንድ መንፈሳዊ መነሻ ስላላቸው ሕግጋትና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እነርሱን ለመፍታት በቂ አይደሉም። በመሆኑም ማኅበረሰቡን፥ ሕዝቦችንና አገራትን ለማንቃት በእሳት የተቀጣጠለ ነፍስ ያላቸው የጥቂት ደፋር ሰዎች ተግባር ይሆናል። ከምንጩ ታላቅ መንፈሳዊ ችግር ስላለበትም ለቤተ ክርስቲያንም ችግሯ ይሆናል። የማይታዩ የጥፋት ኃይላት የሆኑትን ራስ ወዳድነትን፥ ስስታምነትን፥ ቁሳዊነትንና ገንዘብን መውደድን ድብቅ ሥራ መግለጥ የነቢይነት ተግባሯ አንድ ክፍል ይሆናል። በዚህ መንገድ ብቻ ለሰብዓዊ መብቶች በአዲስና ይበልጥ በተነሳሳ መንገድ መሥራት ይቻላል። ክርስቲያኖች ሳይቀሩ ይህንን በፍጥነትና በብርታት እንዲሁም በጥብቅ ታታሪነት ካልሠሩት ጥቂቶቻችን ብቻ ሳንሆን፥ ብዙዎችም ብቻ ሳይሆኑ መላው የሰው ዘር እንዳለ ወደ መንገዱ መጨረሻ መጥተናል።

## ዓለማዊ መሠረት

ለሰብዓዊ መብቶች የሚሰጠው ግምት በአሁኑ ጊዜ በበርካታ የዓለም ክፍሎች የጨለመ ቢመስልም በእርግጥ የተወሰኑ የብርሃን ጭላንጭሎች አሉ፤ እንደዚህ ዓይነት ጭላንጭልን በዲሴምበር 10,1948 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተላለፈውን ‹‹የሰብዓዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ድንጋጌ›› እጅግ በርካታ አገራት በመቀበላቸው እውነታ ውስጥ እንገኛለን።

የእነዚህ ዋና ዋና አሳቦች አንባቢዎች በርካቶቹን የዚህን ድንጋጌ ሙሉ ጽሑፍ ሳያገኙ እና ስለ ድንጋጌውም እጅግ ብዙ ሳያውቁ ስለሚችሉ የተወሰኑ አንቀጾችን ከመጥቀስ ይልቅ ሙሉሁኑን ጽሑፍ መጻፍ ይበልጥ ጠቃሚ ሆኖ አግኝተነዋል። የስምምነቱ ፈራሚ ኃይላት ሁሉንም ኀይነት በፖለቲካው፣ በማኅበራዊው፣ በባሕላዊው፣ በፍልስፍናዊውና በሃይማኖታዊው ካርታ ላይ ያሉ ሰዎችና አገራት እንዲሚወክሉ እዚህ ላይ ሊጤን ይገባል። ይህም ማለት በእነዚህ ሰብዓዊ መብቶች ሁላችንም ልንተባበር ይገባናል ማለት ነው።

# ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ

## መግቢያ

የሰው ዘር አባላት ተፈጥሮአዊ ክብር እና እኩልነት ሊነጠሉ የማይችሉ መብቶች በዓለም ላይ የነፃነት፣ የፍትህና የሰላም መሠረት መሆናቸውን እውቅና መስጠት በማስፈለጉ፣

ሰብዓዊ ፍጡራን አሳብን የመግለጽና የእምነት ነፃነት እንዲሁም ከፍርሃትና ከእጦት ነፃ ሆነው የሚደሰቱበት ዓለም መምጣቱ የብዙሃኑ ሕዝብ እጅግ የላቀ ምኞት ሆኖ በታወጀበት፣ ሰብአዊ መብቶችን ችላ ማለትና መናቅ የሰው ዘርን ሕሊና ያስቆጡ አረመኔያዊ ድርጊቶችን በማስከተሉ፤

ሰው በአምባ ገነንነትና ጭቆና ላይ ማመፅን እንደ

የመጨረሻ የሌለው ምርጫ ለድርጊ በመውሰድ እንዳይገደድ ሰብዓዊ መብቶች በሕግ የበላይነት ከለላ ሊደረግላቸው በማስፈለጉ፤

በሕዝቦች መካከል የወዳጅነት ግንኙነት መዳበርን ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች በቻርተር መሠረታዊ በሰብዓዊ መብቶች፣ በሰብዓዊ ፍጡር ክብር እና ዋጋ፣ እንዲሁም በወንዶችና በሴቶች እኩል መብቶች ላይ ያላቸውን እምነት እንደገና ማጽናታቸውን እና በላቀ ነፃነት ማኅበራዊ እድገትና የተሻለ የኑሮ ደረጃዎችን ለማበረታታት፤

አባል አገራት ከተባበሩት መንግሥታት ጋር በመተባበር ለሰብዓዊ መብቶች እና ለመሠረታዊ ነፃነቶች መከበርና መተግበር ዓለም አቀፍ ማበረታታት ላይ ለመድረስ እርስ በእርሳቸው ቃል ስለገቡ፤ ለዚህ ቃል ኪዳን ሙሉ በሙሉ እውን መሆን የእነዚህ መብቶችና ነፃነቶች የጋራ ግንዛቤ እጅግ በጣም አስፈላጊ

በመሆኑ፣ ጠቅላላ ጉባኤው፣ ለእነዚህ መብቶችና ነፃነቶች መከበር በማስተማርና በማሳወቅ የተቻለውም ግለሰብና የኅብረተሰብ ክፍል ይህንን አዋጅ ዘወትር እንዲያስቡና ደረጃ በደረጃ በብሔራዊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚወሰዱ እርምጃዎች በአባል አገራት፣ በሕዝቦችና በሥልጣናቸው ባሉ ግዛት ሕዝቦች መካከል፣ ለሰዎችና ለሕዝቦች ሁሉ ስምምነት እንደተደረገበት የጋራ ክንውን ልክ ዓለም አቀፋዊ ውጤታማ እውቅና እንዲሰጣቸውና እንዲጠበቁ፤ ይህንን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ያውጃል።

## አንቀጽ 1

ሰዎች ሁሉ ነፃ ሆነው የተወለዱና በክብርና በመብቶች እኩል ናቸው። በማስተዋልና በሕሊና የታደሉ እና ለእርስ በእርሳቸው በወንድማማችነት መንፈስ ግንኙነት ሊያደርጉ

ይገባቸዋል።

## አንቀጽ 2

ሰው ሁሉ ያለ አንዳች ልዩነት ማለትም ያለ ዘር፣ ቀለም፣ ጾታ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ፖለቲካዊ ወይም ሌላ አመለካከት፣ ብሔራዊ ወይም ማኅበራዊ መነሻ፣ ንብረት፣ መወለድ ወይም ሌላ ይዞታ በእዚህ ድንጋጌ የተገለጹት መብቶችና ነፃነቶች አለው።

በተጨማሪም በፖለቲካዊ፣ በአገር ወይም በድንበር ሕጋዊነት ወይም በዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ራሱን በቻለ አገር ውስጥ ቢሆን ወይም በሞግዚትነት በሚተዳደር አገር ውስጥ ቢሆን፣ ራሱን በማያስተዳድርበት ወይም በማንኛውም ዓይነት የሉዓላዊነት ገደብ ሥር ባለ አገር ውስጥ ቢሆን ምንም ልዩነት ሊደረግበት አይገባም።

## አንቀጽ 3

እያንዳንዱ ሰው የሕይወት፥ የነፃነትና የአካል ደኅንነት መብት አለው።

## አንቀጽ 4

ማንም ሰው በባርነት ወይም በተገዢነት መያዝ የለበትም፤ ባርነትና የባሪያ ንግድ በሁሉም መልኩ የተከለከለ ነው።

## አንቀጽ 5

ማንኛውንም ሰው ማሰቃየት፥ ወይም በጭካኔ ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ ማጉላላት ወይም ማዋረድ ወይም መቅጣት አይቻልም።

## አንቀጽ 6

እያንዳንዱ ሰው በየትም ቦታ ቢሆን በህግ ፊት ሰው ሆኖ የመታወቅ መብት አለው።

## አንቀጽ 7

ሰዎች ሁሉ በህግ ፊት እኩል ናቸው። በመካከላቸው አንዳችም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ እኩል የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት አላቸው። ሁሉም ሰዎች ልዩነት እንዳይደርስባቸውና ልዩነት የሚያስከትል ቅስቀሳ እንዳይደረግባቸው የህግ ጥበቃ የማግኘት መብት አላቸው።

## አንቀጽ 8

ማንም ሰው በህግ፥ መንግሥትም ሆነ በሌላ ህግ የተሰጡትን መሠረታዊ መብቶች የሚጥስ ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ሥልጣን ላላቸው የአገሩ ፍርድ ቤቶች አመልክቶ መብቱን የማስከበር መብት አለው።

## አንቀጽ 9

ማንም ሰው በዘፈቀደ በሆነ መንገድ ሊያዝ፣ ሊታሰር ወይም ሊጋዝ አይችልም።

## አንቀጽ 10

ማንኛውም ሰው የተንጸለበትን መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም የተከሰሰበትን ማናቸውንም ወንጀል ለማስወሰን ሙሉ የእኩልነት መብት ተጠብቆ ነፃ በሆነና አድልዎ በሌለበት ፍርድ ቤት ትክክለኛና ግልጽ የሆነ ፍርድ የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 11

1. እያንዳንዱ በወንጀል የተከሰሰ ሰው የቀረበበትን ክስ በሚገባ ለመከላከል የሚያስችሉት ሁኔታዎች ሁሉ ተሟልተውለት

   በህግ መሠረት በግልጽ ችሎት ጥፋተኛነቱ በማስረጃ እስኪረጋገጥበት ጊዜ ድረስ እንደ ንጹሕ ሰው የመቆጠር መብት አለው።

2. ማንም ሰው ድርጊቱ በተፈጸመ ጊዜ በብሔራዊም ሆነ በዓለም አቀፍ ህግ ወንጀል ነው ተብሎ ባልተደነገገ ማናቸውም ተግባር ጥፋተኛ ሊባል አይቻልም። እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ከነበረው ቅጣት የበለጠ ሊወሰንበት አይቻልም።

## አንቀጽ 12

የማንንም ሰው የግል ሕይወት፣ ቤት ወይም ደብዳቤ ከህግ ውጭ በሆነ መንገድ መድፈር አይቻልም።

## አንቀጽ 13

1. ማንም ሰው በአገሩ ክልል ውስጥ በነፃ የመዘዋወርና የመኖር መብት አለው።

2. ማንም ሰው ከራሱም ሆነ ከሌላ አገር የመውጣትና ወደ አገሩም የመመለስ መብት አለው።

## አንቀጽ 14

1. ማንም ሰው በሌሎች አገራት ውስጥ ከስደት ጥገኝነትን የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።

2. ይህ መብት ከፖለቲካ ውጭ በእውነት የመነጩ ክሶች በሚከሰቱበት አጋጣሚዎች ጥያቄ ሊቀርብበት አይችልም።

## አንቀጽ 15

1. ማንም ሰው የዜግነት መብት አለው።

2. ማንም ሰው ከህግ ውጭ የዜግነት መብቱን አይገፈፍም፤ እንዲሁም ዜግነቱን የመለወጥ መብቱን አይነፈግም።

## አንቀጽ 16

1. ዕድሜያቸው ለጋብቻ የደረሰ ወንድና ሴት በዘር፥ በዜግነት ወይም በሃይማኖት ምክንያት ሳይታገዱ ታጋብተው ቤተ ሰብ የመመሥረት ሥብት አላቸው። ጋብቻቸውን ሲመሰርቱ፥ ተጋብተው ሲኖሩና ጋብቻው ሲፈርስም እኩል መብት አላቸው።

2. ጋብቻ የሚፈጸመው ለመጋባት በተፈቃቀዱት ሰዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ብቻ ነው።

3. ቤተ ሰብ የማኅበረ ሰቡ ተፈጥሮአዊና መሠረታዊ የሆነ ክፍል ሲሆን በኅብረተሰቡና በመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 17

1. ማንኛም ሰው ብቻውንም ሆነ ከሌሎች ጋር በመተባበር የንብረት ባለቤት የመሆን መብት አለው።
2. ማንኛም ሰው በዘፈቀደ ንብረቱን እንዲያጣ አይደረግም።

## አንቀጽ 18

ማንኛም ሰው የሃሳብ፥ የህሊናና የኃይማኖት ነፃነት መብት አለው። ይህ መብት ኃይማኖቱን ወይም እምነቱን የመለወጥ፥ ለብቻውም ሆነ ከሌሎች ጋር በኅብረት፥ በግልም ሆነ በአደባባይ ኃይማኖቱን ወይም እምነቱን በማስተማር፥ በማምለክና ህጎቹን በመፈጸም የመግለጽ ነፃነትንም ይጨምራል።

## አንቀጽ 19

ማንኛም ሰው አስተያየት የመስጠትና ሃሳቡን የመግለጽ ነፃነትና መብት አለው። ይህ መብት ማንኛውም ሰው ያለ ምንም ተጽዕኖ አስተያየት እንዲኖረውና በማናቸውም ዓይነት መንገድ፥ ወሰን፡ አልፎም ቢሆን፥ መረጃዎችንና ሃሳቦችን የመፈለግ፥ የመቀበልና የማስተላለፍ ነፃነትንም ይጨምራል።

## አንቀጽ 20

1. ማንኛም ሰው በሰላም የመሰብሰብ ነፃነትና ማኅበር የማቋቋም መብት አለው።
2. ማንኛም ሰው ማኅበር ውስጥ እንዲገባ ማስገደድ አይቻልም።

## አንቀጽ 21

1. ማንም ሰው በቀጥታ ወይም በነፃ ምርጫ በተወከሉ ወኪሎቹ አማካይነት በአገሩ መንግሥት የመሳተፍ መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው በአገሩ ውስጥ እኩል የሕዝብ አገልግሎት የማግኘት መብት አለው።

3. የመንግሥት ሥልጣን መሠረት የሕዝቡ ፈቃድ ይሆናል፤ ይህ ፈቃድ በሁለም አተኛና እኩል የምርጫ መብት እንዲሁም በምስጢር የድምፅ አሰጣጥ ወይም በአቻ ነፃ የመምረጫ አካሄዶች በተወሰነ የጊዜ ገደብ በሚከናወኑና እውነተኛ ምርጫዎች ይገለጻል።

## አንቀጽ 22

እንደ ማኅበረ ሰቡ አባል ማንኛውም ሰው ለማኅበራዊ

[illegible]

ዋስትና እና በብሔራዊ ጥረትና በዓለም አቀፍ ትብብር በእያንዳንዱ አገር አደረጃጀትና ጥሪት መሠረት ለክብሩና ለስብዕናው ነፃ ልማት የግድ አስፈላጊ የሆኑት የኢኮኖሚያዊ፣ የማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች እውን መሆን መብት አለው።

## አንቀጽ 23

1. ማንም ሰው ሥራ የመስራት፣ የቅጥሩን ሁኔታ የመምረጥ፣ ፍትሃዊና ተስማሚ የስራ ሁኔታዎች እና ከሥራ አጥነት የመጠበቅ መብት አለው።

2. ማንም ሰው ያላንዳች አድልዎ ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ የማግኘት መብት አለው።

3. ማንኛውም የሚሰራ ሰው ለራሱንና ለቤተሰቡን ሰብዓዊ ክብር የተገባ ሕልውና የሚያረጋግጥ ፍትሃዊና ተስማሚ

ክብሩ የሚገባትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሌሎች የማኅበራዊ ጥበቃዎች መንገዶች የመደጎም መብት አለው።

4. ማንም ሰው ለፍላጎቶቹ መጠበቅ የሠራተኛ ማኅበርን የመመስረትና የመቀላቀል መብት አለው።

## አንቀጽ 24

ማንኛውም ሰው አሳማኝ የሥራ ሰዓቶች ገደብንና በተወሰነ የጊዜ ገደብ የሚሆኑ በዓላትን ጨምሮ ለማረፍና ለትርፍ መዝናኛ ጊዜ መብት አለው።

## አንቀጽ 25

1. ማንም ሰው ምግብን፥ ልብስን፥ ቤትንና የጤና እንክብካቤን፥ አስፈላጊ የማኅበራዊ አገልግሎቶችን ጨምሮ ለራሱና ለቤተሰቡ ጤንነትና ደኅንነት በቂ ለሆነ የኑሮ ደረጃ፥ እንዲሁም ሥራ አጥነት፥ በሽታ፥ የአካል ጉዳት፥

[illegible] መበለትነት፥ እርጅና ወይም ከቁጥጥሩ ውጪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ የመተዳደሪያ እጦት በሚከሰትበት ጊዜ ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።

2. እናትነትና ልጅነት ለተለየ እንክብካቤና ድጋፍ መብት አላቸው። በጋብቻ ውስጥም ሆነ ውጪ የተወለዱ ልጆች ሁሉ ተመሳሳይ ማኅበራዊ ጥበቃ ይካፈላሉ።

## አንቀጽ 26

1. ማንኛውም ሰው የመማር መብት አለው፤ ትምህርት ቢያንስ ቢያንስ በአንደኛ ደረጃ እና መሠረታዊ ደረጃዎች ነፃ ይሆናል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ግዴታ ይሆናል። ቴክኒካዊ እና ሙያዊ ትምህርቶች በአጠቃላይ ተደራሽ ይደረጉና ከፍተኛ

ትምህርት በተገቢነት መሠረት ለሁሉም በእኩል ደረጃ በቀላሉ የሚደረስ ይሆናል።

2. ትምህርት ለሰው ስብዕና ሙሉ ልማት እና ለሰብዓዊ መብቶችና መሠረታዊ ነፃነቶች መከበር ማጠንከሪያነት ይውላል። በአገሮች ፥ በዘርያዊ ወይም ኃይማኖታዊ ቡድኖች ሁሉ መካከል ግንዛቤን፥ መቻቻልን፥ እና ወዳጅነትን የሚያጠናክርና ለሰላም ተጠብቆ መቆየት የተባበሩት መንግሥታትን እንቅስቃሴዎችን የሚያስቀጥል ይሆናል።

3. ወላጆች ለልጆቻቸው የሚሰጠውን የትምህርት ዓይነት የመምረጥ ቀዳሚ መብት አላቸው።

## አንቀጽ 27

1. ማንኛውም ሰው በማኅበረ ሰብ ባህላዊ ሕይወት በነፃነት የመሳተፍ

መብት፥ ሥነ ጥበብን የመካፈልና በሳይንሳዊ ግስጋሴ እና ጥቅሞቹ የመካፈል መብት አለው።

2. ማንኛውም ሰው እርሱ ያስገኘው የየትኛውም ሳይንሳዊ፥ ሥነ - ጽሑፋዊ ወይም ሥነ ጥበባዊ ውጤት /ሥነ ምግባራዊ እና ቁሳዊ ጥቅሞች ጥበቃ የማግኘት መብት አለው።

## አንቀጽ 28

ማንኛውም ሰው በዚህ ድንጋጌ ውስጥ የተገለጹት መብቶችና ነፃነቶች ሙሉ በሙሉ እውን ሊሆኑ ለሚችሉበት ማኅበራዊና ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት መብት አለው።

## አንቀጽ 29

1. ማንኛውም ሰው የስብዕናው ነፃና ሙሉ ልማት ሊሆን ለሚችልበት ብቸኛ ማኅበረሰብ ግዴታዎች አሉበት።

2. ማንም ሰው የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶች ተገቢ እውቅናና ክብር ለማረጋገጥ ዓላማና የሞራል ምግባር፣ የሕዝብ ሥርዓትንና በዲሞክራሲያዊ ማኅበረ ሰብ ውስጥ የአጠቃላይ ደኅንነትን ፍትሃዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል መብቶቹንና ነፃነቶቹን ሲለማመድ፣ በሕግ የሚወሰኑ ገደቦች ብቻ የሚደረጉበት ይሆናል።

3. እነዚህ መብቶችና ነፃነቶች ከተባበሩት መንግሥታት ዓላማዎችና መርሆዎች በተቃራኒው በምንም መልኩ ተግባራዊ አይደረጉም።

## አንቀጽ 30

በዚህ ድንጋጌ ውስጥ ምንም ነገር፣ የትኛውም አገር፣ ቡድን ወይም ግለሰብ እዚህ ላይ የተጠቀሱትን የትኛውንም [illegible]

መብቶችና ነፃነቶች [illegible] እንዲጠመዱ ወይም ማንኛውንም ድርጊት እንዲፈጽሙ መብት የሚሰጥ ተደርጎ ሊተረጎም አይገባም።

# ምዕራፍ 9

# ፍቅርና ጋብቻ

## ፍቅር እና ሥነ ጾታ

በአጠቃላይ እንጋገር በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ሁለት ክበድ ያሉ ፍንገባዎች በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ዓለም ላይም ትልቅ ጉዳት አድርሰዋል። የመጀመሪያው ፍንገባ ምንጭ አንዳንድ የምሥራቃውን አሳቦች ሲሆን ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ከቤተ ክርስቲያን በተገነጠሉ አንዳንድ ልዩ ልዩ የሃይማኖት ክፍሎች ውስጥ ታይቶአል። እነዚህ ክፍሎች «ግኖስቲሳውያን» ነበሩ (ከላይ ገጽ 107 ይመልከቱ)። እነርሱም በሰው ውስጥ ያለው የክፋት ምንጭ ሥጋ፣ የሥጋ ፍላጎትና ምኞቶች እንደሆኑና የሰው ነፍስ ወይም መንፈስ ከእንደዚህ ዓይነቶች ክፋት ነፃ ስለ [illegible]

[illegible] ነበር። እንደዚህ ዓይነቱ ኃይለኛ አስተምህሮ ወዲያውኑ ሥነ ፆታን ጨምሮ በቤትና በቤተ ሰቡ ሕይወት ውስጥ ያለውን የተለመደና ጤነኛ አካላዊ ሕይወት መናቅ ጀመረ። ሥነ ፆታ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እንደ ክፉ በመቁጠሩ ታፍኖ መያዝ ነበረበት። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የዚህ ዓይነቱ አስተምህሮ ቀሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንዳንድ ክፍሎች በርከት፣ በሌሎች ክፍሎች ደግሞ አነስ ብለው ይታዩ ነበር። በተለይ የበለጠ «መንፈሳዊ» ሃይማኖት ለመፍጠር በመሞከር በተወሰኑ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይህ ዓይነቱ አስተምህሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ ብቅ ብሏል።

እንደዚህ ዓይነቱን አስተምህሮ በከፊል በመቃወም፣ በከፊል ደግሞ «በስ ሁሉም ዓይነት መሠረተ ቢስ ጥላቻ» በሰዎች «ለመገበሬዳት» እና «ነፃ ለማውጣት» የሚደፋፈሩበትን ዓይነት ተከትሎ መጣ በሙሉ አዲስ የሆነ አሳቦች በመላው

ዓለም ላይ ማለት ይቻላል ተሰራጭተዋል። ይህም ከሁለት መቶ ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ በአውሮፓ፥ በአሜሪካና በሌሎችም አገሮች እየጨመረ በሚሄድ ፍጥነት ተገዝቷል። በቅርብ ጊዜያትም አሳቦቹ ወደ አዳዲስ አገሮች ተሰራጭተዋል። እነዚህ አሳቦች በርካታ መዘዞችን ያስከተሉ ሲሆን አንዱ ሥነ ፆታን እንደ መብላትና መጠጣት የተለመደ የአካላዊ ሕይወት መገለጫ አድርጎ የመቁጠርና መቆጠብን ያልተለመደና ለጤና አደገኛ አድርጎ የመቁጠር ዝንባሌ ነው። ይህ አስተሳሰብ ያስከተለው ሌላው መዘዝ የትኛውም ንክኪት ሳይጋቡ አብሮ መኖር፥ ከጋብቻ ሕይወት ጋር እኩል ወይም የሚበልጥ ተደርጎ እስኪቆጠር ድረስ የጋብቻ ሕይወት ቸል መባሉ እና መፈራረሱ ነው። ሦስተኛው መዘዝ ደግሞ የምንዝር፥ የፍቺዎች፥ የልቅ ግብረ ሥጋ ሕይወት፥ የአባላዘር በሽታዎችና በመጨረሻም የኤች አይቪ/ ኤድስ በከፍተኛ ቁጥር መጨመር ነው።

እንደ ክርስቲያናዊ መሠረተ እምነት ሥጋና ነፍስ ሁለቱም በእግዚአብሔር ተፈጥረዋል፤ ሁለቱም የሰውን ውድቀት ይጋራሉ፤ አካላዊ ወይም መንፈሳዊ ማንነት ከነሱ ሁሉ ጋር የሚያደርገውን የሰውን ተጋድሎም ይካፈላሉ። በመሆኑም በሰዋዊ ሕይወት ውስጥ የሚታይ ማንኛውም ነገር፥ አካላዊ ሕይወት፥ መንፈሳዊ ሕይወት፥ ፍቅር፥ ሥነ ፆታ፥ ጋብቻ ለፈቃድ መገዛት አለበት። እዚህ ላይ «ፈቃድ» ማለት የእግዚአብሔር ፈቃድ እና የሰው ፈቃድ ሲሆኑ የኋለኛው ከቀዳሚው የበታች መሆን ማለት ነው። በእግዚአብሔር «ወንድ እና ሴት» ተደርገን የመፈጠራችንን እውነት ሳንቀበል ፍቅርን፥ ወሲብን፥ ጋብቻን ወይም ቤተ ሰብን በሚመለከት የትኛውንም ጉዳይ መገንዘብ ወይም በጥሩ ሁኔታ ማስተዋል አንችልም (ዘፍጥረት 1፥27)።

ሥነ ፆታ እና ፍቅር በራሳቸው እጅግ መልካም ነገሮች ናቸው። በመሆኑም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊስተናገዱ ይገባል። ይህም የሚደረገው ወንዶችና ሴቶች የንጽሕናን፥ የታማኝነትን እና የጨዋነትን ምግባርና ሕግጋት ሲከተሉ ነው።

## «ነፃ ከመውጣት» ጋር የተያያዙ ችግሮች

ከሥነ ፆታ ጋር ተያይዞ «ነፃ መውጣት» ሲባል በተለምዶ «ከተፈጥሮአዊው ነፃነት፣ ከሕጋዊና ሥነ ምግባራዊ ገደቦች ሁሉ ነፃ መሆን» ማለት ነው። ይህ ከክርስቲያናዊ ዕይታ አንጻር የተሰጠ ትርጉም ሳይሆን ይልቁንም የወሲባዊ «ነፃነት» ወኪሎች የሚገልጹት ወይም ቢያንስ ተግባራዊ እንዲሆን የሚሞክሩበት መንገድ ነው። እንደዚህ ዓይነት «ነፃ መውጣት» በአብዛኛው የሚከናወነው ደረጃ በደረጃ ነው። የመጀመሪያው እርምጃ በበርካታ ባህሎች እንደሚተገበረው ወደ ጋብቻ ከመግባቱ በፊት በሚደረግ ወሲባዊ ልምምድ ላይ በመጠን ለዘብተኛ መሆን ነበር። ይህ በጥቂት አጋጣሚዎች በሚደረግበት ጊዜ እና ማኅበረሰቡ እንደ ልቅ አደናርና መጥፎ ልማድ ቆጥሮት አፀፋ ምላሽ ሲሰጥበት ሁኔታው በምንም ዓይነት አሳሳቢ አልነበረም። በወጣቶችና ባልተጋቡ ሰዎች መካከል የሚዘወተር የወሲብ ልምምድን

ወላጆችና ማኅበረሰቡ ሲቀበሉ፣ በክፉል ብቻ ያደጉ ወንዶችና ልጃገረዶች ወሲብ መፈፀማቸው ልማድ እስኪሆን ድረስ እና ወጣቶች ሳይጋቡ አብረው መኖርን እንዲለምዱ የእድሜ ገደብን እያሳነሱ መነገርን እንደ ተገቢ አድርገው ሲቀበሉ ሌላው ቀጣዩ እርምጃ ተከትሏል። በቅርብ ዓመታት ወላጆችና ቤተ ሰቦች በወንዶች ልጆችና በልጃገረዶች መካከል በሚሆነው ነገር ላይ ጭላንት እየተተዋል። ከሥነ ምግባር አንጻር ፍጹም ያልተለመደ ቢሆንም ማንኛውም ነገር «የተለመደ» ነገር ተደርጎ እንደ እውነት ሲገለጥ ወይም ተቀባይነት ሲያገኝ ይታያል።

ይህ እያደገ የሚሄድ ሁኔታ የቤተ ሰብ፣ የትምህርት ቤቶችና የፍርድ ቤቶች ጉዳይ ብቻ አይደለም። በሕይወት ውስጥ እጅግ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች መካከል አንዱ የሆነው ይህ ጉዳይ በመካከሉ የሚከናወን ከመሆኑ የተነሳ የማኅበረሰቡም ጉዳይ ነው። ቀደም ሲል የፍቅርና የጋብቻ ጉዳዮች የኋላ መርሆዎችና ድንጋጌዎች ወዘተ... ጉዳዮች የነበሩ ቢሆንም በአሁኑ ዘመን ግን «ግላዊ የሕይወት ክልል» እየተባሉ በብዙ

መጠን እየተጠቀሱ ይገኛሉ። ይህ በአብዛኛው በዚህ መንገድ ይገለጻል፤ ‹‹ሰዎች በጉርጓ ጊዜያቸው በመዝናኛቸው የሚያደርጉት አንድ ወሲብ እና ፍቅር የመሳሰሉ ጉዳዮች፥ ባለ ሥልጣናትን አይመለከታቸውም›› ይባላል። በተጨባጭነት እንደምንመለከተው ግን እነዚህ ነገሮች በተጨባጭ ባለ ሥልጣናትንና ማኅበረሰቡን በብዙ ይመለከቱታል። በተለይ ደግሞ ‹‹የግል ጉዳዮች›› የሚያስከትሏቸው መዘዞች በገሃድ ሲታዩና ከቁጥጥር ውጪ ሲሆኑ ማኅበረ ሰቡን ይነኩታል። ከሁሉም ነገር አንጻር ሲታይ ይህ ብዙ ጊዜ ራሱን ‹‹እንደሚያውቅና እንደሠለጠነ›› አድርጎ ከሚኩራ ማኅበረሰብ ታላላቅ ችግሮች መካከል አንዱ ነው።

በዘመናዊው ዓለም ውስጥ እየታየ ያለው ሂደት ቀደም ብሎ ሊተወሰኑ ጊዜያት የነበረና ወደ በርካታ ‹‹የባሕል›› ሕይወታችን ክፍሎች በደበልጥ ዘልቆ በመግባቱ ሁላችንም እየተሰቃየንበት [illegible] ነው።

[illegible]
የዚህ አየጨመረ የመጣ ለውጥ ግልጽ ምልክቶች አድርገን ሥነ ጽሑፍን፣ የሕትመት ውጤቶችን፣ ፊልምን፣ ሬዲዮን፣ ቴሌቪዥንን እና የመዝናኛውን ዓለም ሥራ መጥቀስ እንችላለን። በበርካታ አጋጣሚዎች ባለሥልጣናት በጉልህ ከፋ የሆነውን ነገር በይፋ የመቃወም ሥራቸውን ተስፋ ቆርጠው እርግፍ አድርገው ትተውታል፤ ከዚህ የሚከፋው ነገር እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን በመቃወም መሥራት ኃላፊነታቸው እንዳልሆነ መግለጻቸው ነው። በምትክ ጉክክለኛው ወይም ስሕተተኛው ምን እንደሆነ መወሰን የተቋጣጠሬ ኃይላቱ ሊሆን እንደማይችል ያስባሉ። ከዚህ ይልቅ ባለሥልጣናቱ እነዚህ የሚያስከትሉባቸውን ውጤቶች እና በመጨረሻም ኃላፊነቱን መሸከም፣ ብዙ ጊዜ አስፈላጊ የሚሆነውንም የማገልገል ሥራ መስራት ይገባቸዋል።

እየሆነ ያለውን ከፋ ነገር በመቃወም ቤተ ክርስቲያን ድምጿን ስታሰማ ‹‹የለውጥ ተቃዋሚ›› ከዚህም አልፎ በሥነ ምግባራዊ ልክታዎቿ ‹‹ሕዝቡን እንደምታሸብር›› ተደርጋ ትከሰሳለች። እንደዚህ ዓይነት ክሶች በአርግጥ የፈሩቸውን

የተናጋሪዎቹን ሥነ ምግባራዊ እሴት መለኪያን ይገልጣሉ። ከዚህ ቀጥሎ በሚቀርበው አሳብ ውስጥ ያሉ በርካታ ነገሮች ይህንን እውነታ ያረጋግጣሉ።

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ እየጨመረ የሚሄደው እድገት በሚመጡ ዘመናትም መቀጠሉን መናገር ይከብዳል። የተወሰኑ ተስፋ የቆረጡ ጨለምተኞች በዓለም ላይ ሲኖሩ በርካታ ሰዎች ፈጠን ብሎ የሚመጣ ለውጥን ተስፋ ስለሚያደርጉ ምልክቶቹ ተቃራኒ ናቸው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚያንጸውን ነገር በመደገፍና ለግለሰቦችና ለሰዎች የጋራ ሕይወት አፍራሽ የሆነውን በመቃወም ነቢያዊ ድምጿን ከፍ ማድረግ አለባት። በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን ክፉውን ነገር የሚያበረታቱትን እና ትርፍ ለማግኘት ብቻ የሚጣደፉትን ሰዎች ‹‹ነፃ የማውጣት›› ክፋት ልትገልጽ ይገባታል ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ቤተ ክርስቲያን በሁሉም ዓይነት መልካም ሥልጣኔዎች ውስጥ ዘወትር ከፍተኛ ዋጋ የተሰጠውን ነገር፤ ‹‹እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ÷ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ÷ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ÷ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ÷ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ÷ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን›› ልታመሰግነውና ልታበረታታው ይገባታል (ፊልጵ. 4÷8)።

## በወንድና በሴት መካከል ያለ ፍቅር

እርግጥ ነው ፍቅር በሚኖርበት ቦታ ስሜቶች ይሳተፋሉ፤ ነገር ግን በወንድና በሴት መካከል ያለ እውነተኛ ፍቅር ከስሜቶች እጅግ በጣም የላቀ ነው። ፍቅር አእምሮና ነፍስም በከፍተኛ ደረጃ ገብተው የሚሳተፉበት ዓይነት ግለሰባዊ መሳሳብም ጭምር ነው። ፍቅር የስሜት ሕዋሳትን ሁሉ ጨብጦ የሚይዝና ከአሁኑና ከወደፊቱም ጊዜ ከሕይወት እይታና አመለካከት ጋር የተገናኘ ነው። ፍቅር እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን ካላካተተ የመጀመሪያዎቹን ከልክ በላይ የተቀሰቀሱ ስሜቶች በአግባቡ አለመረዳት ተፈጥሮአል

ወይም በትክክል ጥልቀት የሌለው እንደሆነ ያፈራል። በዚህ አይነት ሁኔታ ለረጅም ጊዜ የማይቆዩና ነገር ግን ተዘውትሮ እንደሚሰማው ወዲያው «በአዲስ ፍቅር» የሚተኩ ይሆናሉ። ይህ ማለት «በፍቅር ወድቋል» የነበረው ሰው በድጋሚ «በፍቅር የሚወድቅበት» አዲስ ይበልጥ የሚስብ (የምትስብ) ዕቃ አግኝቷል (አግኝታለች) ማለት ነው።

በአንድ ወንድ እና በአንዲት ሴት መካከል ያለው እውነተኛ ፍቅር እንደተመለከትነው የሁለቱንም ሙሉ ስብዕና ያሳትፋል። በመሆኑም በሕይወት ውስጥ ሁሉንም ነገር እርስ በእርስ ለመከፋፈል ዝግጁ ይሆናሉ። «ፍቅር የራሱን ብቻ ስለማይፈልግ» እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ስለማይል በጋራ ግንኙነታቸው ውስጥ ለመስጠት እና ለመቀበል ዝግጁ ይሆናሉ። ፍቅር «የማይገባውን አያደርግም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሳል፤ ሁሉን ያምናል፤ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፤ በሁሉ ይጸናል» (1 ቆሮ. 13፥5-6)።

እዚህ ላይ የተጠቀሱት ነገሮች «በፍቅር በመያዝ» እና በእውነተኛው ዘላቂ ፍቅር መካከል ትልቅ ልዩነት መኖሩን ግልጽ ያደርጉታል። ፍቅሩ ለ«መጽናናት» ዝግጁ ከሆነ፣ የመጀመሪያዎቹን የፍላጎት ስሜቶች ማለፍና የጊዜያዊ ስሜቶች ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ለሕይወት ዘመን ግለሰባዊ መያያዝ መሆኑንና አለመሆኑን የሚያሳዩ የተወሰኑ ምዘናዎችን አልፏል ማለት ነው።

## የጋብቻ ዝግጅቶች

ልማዶችና ሕጋጋት ከአገር አገር እጅግ በጣም ስለሚለያዩ እዚህ ላይ ዝርዝር ነገሮችን ማብራራት የማይቻል ነው። በአጠቃላይ «ጥሎሽን» የሚመለከቱ ሕጋጋትና ልማዶች ሁሉ በበርካታ አገሮች ምናልባትም በአብዛኞቹ አገራት ተሽረዋል ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ሕግ ነክ እንቅፋቶቹን በተመለከተ ያለው አስፈላጊነት እጅግ አናሳ ቢሆንም «አንድ ዓይነት መተጫጨት» በበርካታ አገሮች ይከናወናል።

በተወሰኑ አገራት ግንኙነታቸውን ልማዶች ሳይበላሹ ተጠብቀው ቆይተዋል፤ ጋብቻ በሚመለከታቸው ወላጆችና ቤተ ሰብ ጠያቂዎች አማካይነት በወጣቱ ሰው ምትክ ወይ ልጃገረዲቱ አባት በሚደረግ አመቻቺነት አስተዳደሩ የሚከናወን ነው።

እዚህ ላይ የቅደም ተከተሉን ዝርዝሮች ሁሉ ወደ ጎን ትተን ሕጋዊ ጋብቻ በወንድየውና በሴቲቱ መካከል ያለው ግንኙነት እጅግ በላቀ ሁኔታ አስፈላጊ መሆኑን መናገር እንችላለን። ይህ ግንኙነት በመካከላቸው ያለውን፥ ልጆችን ካገኙ ደግሞ ለልጆቻቸው ያለባቸውን እንዲሁም ማኅበረሰቡ ለተጋቡት ጥንዶችና ለልጆቻቸው ያለበትን ኃላፊነት ጨምሮ በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ባሕርይ ባላቸው ጉዳዮች ይሸፈናል።

ከዚህ ሁሉ ‹‹እንደ ባል እና ሚስት አብረን መኖራችን የግል ጉዳያችን ነው፤ ማኅበረ ሰቡ በጉዳዩ ላይ ምንም ጉዳይ
[illegible]

[illegible]
ጋብቻ እንደ ይፋዊ ተቋም ከሥነ ሥርዓትነት እጅግ የላቀ ጉዳይ ነው። ሁለቱም ተጋቢዎች ‹‹ወደ እነዚህን የጋራ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች ሙሉ በሙሉ እንገባለን፤ እንቀበላቸውማለን።›› በማለት በመካከላቸውና በማኅበረ ሰቡ መካከል ያለውን ግንኙነት በይፋ የሚያስታውቁበት የጋራ ድርጊት ሁነት ነው። በመሆኑም እዚህ ላይ የቀዳሚው ፍጥምጥም ትጥቂት ወይም ካርድ ማላተም፥ የሆርን ድግስ መኖሩ አለመኖሩ፥ ወዘተ... አስፈላጊነታቸው እጅግ አናሳ ይሆንና ወደ ጎን ሊተው ይችላል። እዚህ ላይ ብቸኛ አስፈላጊ ነገሮች ጋብቻው ራሱና ሕጋዊ ክብሩ፥ አስከትሎም የሚያመጣቸው ሕጋዊ፥ ማኅበራዊና ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮች ይሆናሉ።

ጋብቻ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት በሁሉም ሕዝቦችና ባህሎች መካከል መተግበሩን ማወቅ የሚያስገርመን ትምህርት አለ። በእርግጥ ብዙ ጊዜ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶች እጅግ በጣም በቀለለ መንገድ፥ ለምሳሌ ሙሽራይቱን ሙሽራው፥ የተወሰኑ ታዳሚዎችና የሚመለከታቸውን ወላጆች ወይም ተወካዮቻቸው

ባሉበት በአንድ የንሰሁ መሪ ወይም ሞግዚት ሹም ፊት የሚከናወኑበት ሁኔታ አለ። እዚህ ላይ ምንም ዓይነት ውጫዊ ዝርዝር ጉዳይ አስፈላጊ አይደለም። ቃል ኪዳን መገባባቱ+ ምስክሮችና ይፋዊ ቅደም ተከተሎቹ ብቻ አስፈላጊና ዋጋ ያላቸው ናቸው። ምክንያቱም በጉዳዩ ላይ በሚሳተፉት አካላት መካከል ጽኑ ውል የሚያስገኙት ነገሮች እነዚህ ናቸውና። ከጋብቻ ጋር የተያያዙ ቅደም ተከተላዊ ሥርዓቶች ሁሉ የጥንዶቹን+ ሊወለዱ የሚችሉ ልጆቻቸውን፣ የማኅበረሰቡን ፍላጎትና በአጠቃላይ የሰውን ደኅንነት ከአደጋ ለመጠበቅ ይከናወናሉ፤ ሊከናወኑም ይገባቸዋል።

እዚህ ላይ በታሪክ ውስጥ በግልጽ በሚታወቅ የትኛውም ዘመንና የትኛውም ሰው ያልተመሠረተ ነገር ግን ለመላው የሰው ዘር ጥቅምና ከአደጋ መጠበቅ ማወቅ ከማይችል ጥንታዊ ዘመን ጀምሮ ሕልውና ያለውን ጠቃሚ ተቋም ለማፍረስ ኃላፊነቱን የሚወስድ ማን ነው?

## ቤተ ክርስቲያን የጋብቻን ግንዛቤ ለማሥረጽ የሚኖራት አስተዋጽዖ

ይህ አስተዋጽዖ ሦስት ደርብ ባሕርይ አለው ለማለት ይቻላል። የመጀመሪያው በሁሉም አገሮች ሁሉና እና በሕዝቦች ሁሉ መካከል ጋብቻን እጅግ በላቀ ክብር ለመያዝ አስፈላጊነትና አስገዳጅነት አጽንዖት መስጠት ነው። በመሆኑም ክርስቲያንና አማኝ ያልሆኑ በርካታ አካላትና ሰዎች ጋብቻን እጅግ በላቀ ክብር በያዙበት ወቅት ቤተ ክርስቲያን በጋብቻ ላይ ያላትን መሠረተ እምነትና አብረውት የሚሄዱትን መልካም ልማዶች ብትተው ትልቅ እፍረት ይሆናል።

በቤተ ክርስቲያን ሊሰጥ የሚችለው ሁለተኛው ዓይነት አስተዋጽዖ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚሰጥ ትምህርት ነው። ምንም እንኳ የክርስትና እምነትን ባይቀበሉም በርካታ ሰዎች የሚቀበሏቸውና ሊቀበሏቸው የሚችሉ በርካታ ጠንካራ ነጥቦች አሉ። በመሆኑም ብዙዎች በልባዊና እውነተኛ ፍቅር+

በታማኝነት፥ በሕይወት ዘመን ለሚዘልቅ መሠጠት ወዘተ... ላይ አጽንዖት ለመስጠት ገዝጃ ናቸው። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ነገር ነው፤ «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን» (ዕብ. 13፥4)።

ሦስተኛው ዓይነት አስተዋጽዖ ይበልጥ ቀጥተኛ ያልሆነ ባሕርይ ያለው ዓይነት ይሆናል። ይህ አስተዋጽዖ ከቤተ ክርስቲያንና ከአማኞች ውጪ ምንም ቀጥተኛ ተጽዕኖ ያለው አይመስልም። ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድ ስለ ጋብቻ የሚኖረው ግንዛቤ ላይ የተወሰነ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ይህ መሠረታዊ እምነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደከበረ ድንጋይ ሊያዝና ዋጋ ሊሰጠው ይገባል፤ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ያለው ግንኙነትና ፍቅር ከሁሉ በላቀ ደረጃ ላይ ሲደርስ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል እንደሚኖረው ፍቅር ዓይነት ነው

እንዛቤ ወይም አድማጭ ግልጽ አይደሉም። ምክንያቱም ይህ «ታላቅ ምሥጢር» ነው። እንደ እነዚህ ዓይነት ቃላትን ከሰማን ፍቅርንና ጋብቻን የሚመለከተውን የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ወደ «ዓለም» መርሆዎች፥ ልክታዎችና ልምምዶች ገቅ ማድረግ ከተውንም እንዴት ማሰብ እንችላለን?

## በዓለማዊው ማኅበረ ሰብ ውስጥ የጋብቻ ቦታ

እዚህ ላይ መነሻ ነጥባችን መሆን የሚገባው በተለያዩ የዓለም አገራት ያሉ ሕግጋት፥ ባህሎችና ልማዶች የተለያዩ የመሆናቸው እውነታ ነው። እንደዚያም ሆኖ ግን ጋብቻ «ከመጀመሪያው» ነበረ (ማቴ. 19፥4)። እግዚአብሔር በፍጥረት መጀመሪያ ያቋቋመው ሥርዓት ሲሆን የማያምኑትንም ሆነ የሚያምኑትን ሁሉ የሚመለከት ነው። የጸጋ መንግሥት ክፍል ብቻ ሳይሆን የመላው ዓለም ጋብቻ በመሆኑም ዓለማዊ ሕግ አውጪዎች ጋብቻን በሚመለከት የተወሰኑ ክርስቲያናዊ አመለካከቶችን በመደገፍ ሕግ እንዲያጸድቁ ወይም ዓለማዊ ባለሥልጣናት የቤተ

እንችልም። ይህ በአብዛኛው ባለፉት ዘመናት የተደረገ ቢሆንም በማንኛውም ጊዜና ቦታ ትክክለኛ አካሄድ ሊሆን አይችልም። በእርግጥ ዓለማዊ ባለሥልጣናት በጋብቻ ላይ መሠረታዊ+ እውነተኛ እና ጠቃሚ ሰብአዊ ዕሴታዎች ተብለው ሊቆጠሩ የሚችሉ ነገሮችን ማክበርና መደገፍ ሊጠበቅባቸው ይችላል።

በእርግጥ ጋብቻ ሕዝባዊ እና ማኅበራዊ ገፅታ ስላለው በዓለማዊው ማኅበረ ሰብ ሥልጣንና እንክብካቤ ገደብ ሥር ያርፋል። በመሆኑም የጋብቻ ተቋም ሥልጣንና እንክብካቤ በምንም ዓይነት መንገድ ለቤተ ክርስቲያን ብቻ የተሰጠ ተልዕኮ ተደርጎ መወሰድ አይችልም። ሁሉም ክርስቲያኖች ጋብቻን መልክ የሚያስይዙ ሕጎች እንዲጸድቁና እንዲጠበቁ ራሱ ማኅበረ ሰቡ ኃላፊነት አለበት። ማኅበረ ሰቡ ለዚህ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ፍርድ ቤቶችና ሌሎች ተቋማትን በማዋቀርና ሰዎችን በጋብቻ ጥያቄዎችና ሕጎች ለማስተማር ብቁ የሆኑ አማካሪዎችን በማስቀመጥ ጋብቻ ሁሉም በሚያከብሩትም ጊዜ እንዲፈጸሙ የሚገደድ ኃላፊነትም አለበት። በተጨማሪም ጋብቻን ተከፋ አስቀራሚ ወይም ጎጂ፤ ምናልባትም አውዳሚ ከሆኑ ምክንያቶች መከላከል የእንደዚህ ዓይነት

ባለሥልጣናትና ተቋማት ተግባር ነው። ይህ ሁሉ በእርግጥ ለራሱ ለማኅበረሰቡ ጥቅም ነው፤ ምክንያቱም ማኅበረሰቡ ራሱ የተገኘባቸውና የተገነባባቸው ብቸኛ ነገሮች ጋብቻዎችና ቤቶችና ቤተ ሰቦች ስለሆኑ ነው። ማኅበረሰቡ በተቃራኒው አቅጣጫ መጓዝ በሚጀምርበት ጊዜ ማለትም ለዓቅርና ለቤተ ሰብ ጋብቻ ትክክለኛ አውታር መሆኑን በሚጻረር መልኩ ሥራዎችን በሚሠራባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ራሱን እየጎዳ በራሱ ላይ ችግር እያመጣ ነው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ "ነፃነትን" የሚደግፉ ቡድኖች ከሚያመጡበት ጫና የተነሳ እንደዚያ ማድረግ ጀምር ይሆን ይሆናል። ይህ ከሆነ ማኅበረ ሰቡ ግዴታዎቹንና ኃላፊነቶቹን እንደገና ማጤን ይገባዋል።

አንድ ወንድና አንዲት ሴት አብረው መኖር በሚጀምሩበት ጊዜ ማኅበረሰቡ ራሱ እንዲገባበት እና ሊሳተፍበትም እንደሚገባ ለማሳየት የሚያስፈልገን አንድ ምሳሌ ብቻ ነው። በምሳሌያችንም

በሕጋዊ መንገድ ሳይጋቡ አብረው ለመኖር ወስነዋል እንበል። ይህንን ማድረግ የራሳቸው ጉዳይ እንደሆነ አስታውቀዋል። ‹‹እኛ እርስ በእርስ እንዋደዳለን፤ የምናደርገውን ነገር ለማወቅ የበሰልን ነን፤ ቃል ኪዳናችንን ለራሳችን እንጠብቃለን፤ ታማኞች እንሆናለን፤ ሌላ ማንንም ሰው አይመለከተውም›› ብለዋል። ምናልባት ለተወሰኑ ዓመታት በዚህ ሁኔታ ይቀጥላሉና ምንም ችግር ያለ አይመስልም። ነገር ግን ከዚያ በድንገት አብረው መኖራቸው ያከትማል። ከሁለቱ አንዳቸው ቤታቸውን ይለያል፤ ለዚህ ድርጊታቸው በሌላኛው ወገን በፍርድ ቤት ይካሰሳሉ፤ ስለ ሌሎች ንብረቶችም አንድ ክስ ይመሠረታል፤ ሦስተኛው ክስ ስለ ልጆቻቸው የማሳደግ ኃላፊነት ይሆናል። በፍርድ ቤቱ አንዱ ሌላውን ወገን በማጭበርበር እና ቃል ኪዳን በማፍረስ ይከስሳል። ሌላኛው ወገን በእያንዳንዱ ጉዳይ፡- ‹‹የምን ቃል ኪዳን? መቼ እና የት ነው ቃል ኪዳን የገባሁት?›› በዚህን ጊዜ ማንንም ከአደጋ የሚጠብቁ ሰነዶች÷ ምስክሮች÷ ሕጋዊ የሥነ ሥርዓት ቅደም ተከተሎች÷ አካሄዶች ካለመኖራቸው የተነሳ ምንም ነገር ሊረጋገጥ አይችልም። ምሳሌው ራሱን በራሱ የሚያብራራ ገላጭ ነው። ከጥቂት አስተያየቶች በስተቀር በዚህ ነጥብ ላይ ምንም ተጨማሪ ማብራሪያዎች አያስፈልጉም። በበርካታ ‹‹ምዕራባውያን›› አገሮች÷ በቀድሞ ጊዜያት ይደረጉ የነበሩት የተዘጋጁና ስምምነት ላይ የተደረሰባቸው ጉዳዮች÷ ስምምነቶችና ምስክሮች ወዘተ... መኖራቸውን የሚከታተሉ ተገቢ የሆኑ ባለ ሥልጣናት የነበሩበትን እጅግ የቀለሉ አካሄዶች ማግኘት ቢችሉ ጥንዶቹና ባለ ሥልጣናቱ ራሳቸው ደስተኞች የሚሆኑበት አጋጣሚ ይፈጠር ነበር። አሁን ግን ከዚያ ይልቅ ጋብቻ የማኅበረሰቡ ተቋም መሆኑን የሚቃወም ሰፊ ፕሮፓጋንዳን ተከትለው በመጡት ችግሮች ውስጥ ያለውን እውነት ለይቶ ለማውጣት በመሞከር እጅግ የከበረ ጊዜና ከፍተኛ መጠን ያለው የሕዝብ ሀብት እየባከነ ይገኛል። አንድ ማኅበረ ሰብ ራሱን÷ ፍላጎቶቹንና የራሱን ዜጎች ደኅንነት የሚቃረን የሞኝነት ድርጊት እንዴት ሊፈጽም ይችላል?

## ዓለማዊ ባለ ሥልጣናት ጋብቻን በሚመለከት ማድረግ የሚችሉትና ማድረግ የማይገባቸው ነገሮች

ዓለማዊ ማኅበረሰብ ጋብቻን መደገፍ እና ሰዎች ሳይጋቡ አብረው መኖርን በመለማመድ ፈንታ መጋባትን ማበረታታት እንደሚገባቸው ተገንዝበናል። በዚህ መንገድ ማኅበረ ሰቡ ወላጆችንና ወጣት ጥንዶቹን መርዳት ይችላል። በዚህ መንገድ ማኅበረሰቡ ራሱንም ይጠቅማል።

በሌላ በኩል ዓለማዊው ማኅበረ ሰብ በጋብቻ ላይ የራሱ የሆነ ምንም ዓይነት ዝርዝር መሠረተ እምነቶች ሊኖሩት አይገባም። በጋብቻ ላይ የራሳቸው አይታ ሊኖራቸውና ከጋብቻ ጋር ተያይዞ የፀና እምነታቸውን መከተሉ የዜጎች+ የአስተሳሰብ ዘይቤአቸው፤ የአብያተ ክርስቲያናቸው እና የሃማኖታቸው ወዘተ... ጉዳይ ነው። በተለይ ሕዝቡ በሃይማኖቶች ወይም በሌሎች መንገዶች የተለያዩ [illegible]

[illegible]
ይገባዋል። ዓለማውያን ባለ ሥልጣናት ለአንዳቸው አድልተው ሌሎችን በመቃረን የተወሰኑትን መደገፍ ስለማይችሉ+ ጉዳዩ ሃይማኖታዊ ያልሆኑትን አካላት የሚመለከት ሲሆን እነዚህ ልምምዶች ለአንዳንድ ቡድኖች እስካላደሉ ወይም የጋራ ሕግንና ሥርዓትን እስካልጣሱ ድረስ ሁሉም የእምነትና እምነቶቻቸውን የመለማመድ ነፃነት ሊፈቀድላቸው ይገባል። መሠረታዊው እውነታ ለሁሉም የጋራ የሆነው የጋብቻ ተቋም አስፈላጊነቱ እና ለሁሉም ደኅንነት መጠበቅ የሚያስፈልግ መሆኑ ነው።

በሁሉም ሃይማኖቶችና የአስተሳሰብ ዘይቤዎች ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውና በመልካም ምግባር እና የተፈጥሮ እውቀት ላይ የተመሠረቱ የተወሰኑ መሠረታዊ ሕግጋት አሉ። እነዚህ ደንቦች በሁሉም ዓለማዊ ባለ ሥልጣናት ሊከበሩ ይገባቸዋል። እነዚህ ሕግጋት የጋብቻ ቃል ኪዳን መጠበቅን ጨምሮ እውነተኛነትንና ታማኝነትን+ ልጆችን ከአደጋ መጠበቅንና ደኅንነታቸውን ማረጋገጥን+ መንከባከብንና ማስተማርን ወዘተ... ግለሰቦቹ በሌላው አካል የሚሰነዘሩባቸውን አደጋዎች+ ግላዊ ሉዓላዊነትን

እና የጋብቻ ሕይወታቸውን በሚመለከት እንዳቸው ለሌላቸው የሚሰጡት አቀባበል የሚመለከቱ ናቸው። ሕግጋቱ የንብረትና የውርስ ወዘተ... ጉዳዮችንም ጭምር ይመለከታሉ። በአሁኑ ጊዜ ከእነዚህ ጉዳዮች አብዛኞዎቹ በመጠኑ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች በመደበኛነት ይዳኛሉ። ሆኖም ግን በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ሙሉ ስምምነት ላይ ሊደረስበት አይቻልም፤ ቢያንስ እንደዚህ ዓይነት ግብ ላይ ለመድረስ እጅግ በጣም ረጅም መንገድ የቀረ ይመስላል። በአንዳንድ አገራት በቀዮ ልማድ መሠረት ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት አሁንም ተቀባይነት አለው። በተወሰኑ አገራት እስከ አሁን ባል ሚስቶቹን መቅጣት ሲፈቀድለት በእንደዚህ ዓይነት አጋጣሚ የሚፈቀደው ነገር ዝርዝሩ በሕግ የተሰጠ ሊሆን ይችላል። በተቃራኒው ሚስት ባሏን የምትቀጣበት ሁኔታ ስለመኖሩ ብዙም ተሰምቶ አይታወቅም። በዓለም አቀፍ ስምምነቶች አማካይነት ከእንደዚህ ዓይነት ነገሮች ማምለጥ ካልቻልን ባለ ሥልጣናት ሁሉ ቢያንስ እውነተኛነትን፣ ታማኝነትን፣ መስጠትንና

ጨዋነትን ማበረታታት ይገባቸዋል። በተለይ በአንድ የማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ ልጆችን፣ ወጣቶችን ለመበዝበዝ በረቀቀ ዘዴ የሚሠሩትንና የሃሰት ምግባርን፣ የጨዋነትን ጣዕምና ትርጉም የሚጎዱ በመጨረሻም በማኅበረሰቡ ውስጥ የጋብቻን መሠረታዊ ተቋምነት የሚሸረሽሩ ድርጅቶችን፣ ተጽዕኖ አምጪ ኃይሎችን በማገድ ዓለማዊ ባለ ሥልጣናት ለማኅበረሰቡ መልካምና እጅግ ጤናማ አገልግሎትን መስጠት ይችላሉ።

ከዓለማዊ ባለሥልጣናትና ከጋብቻ አያያዛቸው ጋር በተገናኘ መጠቀስ የሚገባቸው ሁለት ችግሮች አሉ። አንዱ የፍቺዎች ችግር ነው። ይህ ችግር እጅግ ውስብስብና በተለያዩ አገራት የተለያየ ከመሆኑ የተነሣ እዚህ ላይ ሙሉ በሙሉ ማብራሪያ ሊሰጥበት አይችልም። በመሆኑም የትኛውም ዓለማዊ ባለ ሥልጣን የጋብቻን ወይም የማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታት የፍቺ መንገድነትን ማበረታታት እንደማይገባው በአጭሩ መግለጽ ይበቃል። ይህ በትምህርታዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት አማካይነት የሚደረግ ነው። በዚያ ምትክ በችግር ውስጥ ያሉ

ጥንዶችና ቤተ ሰቦቻቸው ችግሮቻቸውን ያለ ፍቺ ለመፍታታቸውን ዓላማቸው አድርገው የሚሊዷቸው አማካሪዎችና አማካሪ አካላት ያሉበትን ሥርዓት ዓለማዊ ባለ ሥልጣናት ሊያመቻቹላቸው ይገባል። እንደዚህ ዓይነት እርምጃዎችን ለመውሰድ በቅርብ ያሉ ቢያንስ ሦስት ምክንያቶች አሉ፤ በአንዳንድ አገራት ከመቶ ሃያ፥ ሰላሳ ወይም አርባ እጅ የሚሆኑት ጋብቻዎች በጥቂት ዓመታት ውስጥ ወደ ፍቺ ያመራሉ። በእንደዚህ ዓይነት አገራት በተወሰኑ ከተሞች አርባ ከመቶ የሚሆኑት ቤተ ሰቦች ከአንድ ወይም ከሁለት ወይም ቍጥራቸው የበለጠ ልጆች ጋር የሚኖረው አንድ ነጠላ ወይም ጎልማሳ ሰው ብቻ ይሆናል። ከእነዚህም ጎልማሳ ሰዎች እጅግ ከፍተኛ ቍጥር ያላቸው አንድ ጊዜ የተፋቱ ምናልባትም በተደጋጋሚ የተፋቱ ናቸው። ሦስተኛው ምክንያት ሳይታሰበበት ወዲያውኑ ማለት ይቻላል ራሱን ብቻ ያደርጋል፤ ከፍተኛ ቍጥር ያላቸው ልጆችና ወጣቶች «እጅግ ከሚያሳዝኑ ሁኔታዎች፥ ከተፋቱ ወላጆች፥ ከተበተኑ ቤተ ሰቦች፥ ከንዴና

ወንበዴዎች የመጡ እና ወደ መጥፎ ሕይወት ወይም ወንጀል፥ ወዘተ... ውስጥ የገቡ ስለሆኑ» በማኅበራዊና በሕዝብ ደኅንነት ባለ ሥልጣናት እንክብካቤ ሊደረግላቸው ግድ ይሆናል።

ከጋብቻ ጋር ተያይዞ ያለ ሌላው የተለየ ችግር የጋብቻ ሕግጋትን ይመለከታል። በበርካታ አገራት በዓለማዊ ባለ ሥልጣናት እና በቤተ ክርስቲያን መካከል ግጭት ታይቷል። እንደዚህ ዓይነት ነገር ተከስቶ ከሆነ የሁለቱም አካላት ጥፋት ይሆን ይሆናል። ምናልባትም የሌላውን አካል ወይም የነዛ ሩሳቸውን ግዴታ እና የድንበር ክልል እንኳ ምን እንደሆነ አልተገነዘቡ ይሆናል። ጋብቻ ዓለማዊ ተቋም ቍምር እስከሆነ ድረስ በዓለማዊ ሕግ ሊስተካከል ይችላል፤ መስተካከልም ይገባዋል። በመሆኑም ዓለማዊው ማኅበረሰብ በጋብቻ ላይ ሕግ ሊያወጣ፥ ተገቢነት ያለው የጋብቻ ሥነ ሥርዓት እንዲኖር እንዲሚፈጸም፥ በውል የታሰረ ጋብቻ ምን መብቶችንና ግዴታዎችን እንደሚያስገኝ ገደብ ሊያደርግ መብት አለው። የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶች ሁሉ በተወሰኑ የማኅበረሰብ ባለ ሥልጣናት ፊት ሊፈጸሙ እንደሚገባቸው ከገለጹም ትክክል

ነው። እንደነዚህ ዓይነት ሕግጋት ሚዛናዊና አሳማኝ ከሆኑ ስለ እነርሱ ለመከራከር ምንም ምክንያት ሊኖር አይገባም። በሌላ በኩል በዚህ መንገድ ቃል በቃል ሕግ ማውጣት አስፈላጊ አይደለም። በዚህ ምትክ ሕግጋቱ አንድ አማራጭ ወይም በርካታ አማራጮችን እንዲያናግሩ ማድረግ፣ ለምሳሌ ሃይማኖታዊ አካላት የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶችን እንዲፈጽሙ መፍቀድና ለዚያ ደግሞ ወዲያውኑ ሕጋዊ እውቅና መስጠት ሊሆን ይችላል። ያን ጊዜ ይፋዊ ያልሆነው የጊዜያዊው ሥነ ሥርዓት በምዝገባ እንደ ተፈጸመው ሕጋዊ ሥልጣን ያለው ይሆናል። ሌላው አማራጭ ደግሞ የሚከተለው ሊሆን ይችላል፤ ዓለማዊው ማኅበረሰብ በማኅበረሰቡ ባለ ሥልጣን ፊት ከሚደረገው ይፋዊ ሥነ ሥርዓት በሻገር ከጋብቻ ጋር የሚያያዝ ሃይማኖታዊና ሥነ ምግባራዊ አይታዎቻቸውን ለመግለጽ ለሚፈልጉ ሰዎች መሻገሪያቸውን ለማሟላት አብያተ ክርስቲያናትና ሌሎች ሃይማኖታዊ አካላት ተጨማሪ ሥነ ሥርዓት እንዲያናግሩቸው ይፈቅዳል። ዓለማዊ ባለ

ሥልጣናቱ ይህን የማይፈቅዱ ከሆነ በግራ ያለሀዊ መብቶችን ሕግጋት ይተላለፋሉ። እንደዚህ ዓይነት መብቶች ከቤተ ክርስቲያን ወይም ተመሳሳይ አካላት በሚነስከሱበት ጊዜ እነዚህን መብቶች እጅግ በጠንከረ መልኩ ለመጠየቅ ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል። ግለሰባዊና ሃይማኖታዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩም ከዓለም ኅብረተ ሰብ እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።

## ከእውነተኛው የፍቅር የጋብቻ መንገድ የከፉ ፍንገጣዎች

እንደ ቀልድም ተደርጎ ብዙ ጊዜ ሴተኛ አዳሪነት ከመጀምሪያ ሁሉ ጥንታዊው ነው ተብሏል። ከሆነ እጅግ ጥንታዊው ኃጢአትም ነው። ነገር ግን በአንዳንድ አገሮች እንደ መደ እውቅና ተሰጥቶትና ተደራጅቶ እንዲሁም ቁጥጥር እየተደረገበት በርካታ ይፋዊ ባሕርያት ማለትም ምዝገባ፣ የጤና ምርመራና ቁጥጥር፣ የግብር ሥርዓትና ያልተገነለ ግብርም ተደንግጎለታል።

ሴተኛ አዳሪነት ይፋዊ እውቅና ተሰጠውም አልተሰጠው

ያሉት አፍራሽ ገጽታዎች ብቻ ናቸው። ለሴተኛ አዳሪዎም ሆነ ለእንግዳዎቹ ለሁለቱም እንደ ሰብዓዊ ፍጡርነታቸው ክብራቸውን የሚያዋርድ ሲሆን ለመላው ማኅበረሰብም ጭምር አዋራጅ ነው። በተጨማሪም ተግባራቸው እጅግ ከፍተኛ የሆነ ከልክ በላይ ባለጠጎች የሆኑ ሰዎች እያሉ ያለ መደበኛ ሥራ ባልተረጋጋ ማኅበራዊ ሁኔታዎች ውስጥ በመሆናቸው በሴተኛ አዳሪነት በጎደፈ ተግባር ተጠምደው የሚኖሩ በርካታ ድሆች በአገሪቱ ውስጥ ይኖራሉ። በአንዳንድ አገራት የአሥር ወይም የአሥራ ሁለት ዓመት ልጃገረዶች ራሳቸውን ለሴተኛ አዳሪነት አሳልፈው የሚሰጡ ሲኖሩ አንዳንድ ጊዜ በራሳቸው ድሃና ሥራ አጥ ወላጆች እንደዚያ ለማድረግ የሚገደዱበት አጋጣሚም አለ። ስለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ማነው? በእርግጥ ለነዚ ራሳቸው ሕዝብ ደኅንነት ግድ የሚላቸው ፖለቲከኞቹና ማኅበራዊ ባለ ሥልጣናት በእርግጥ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ነገር ግን ኃላፊነት ያለባቸው ተጨማሪ ሰዎችም አሉ። ለምሳሌ የገደብ የለሽ ወሲባዊነት

ነቢያት፥ በሰዎች መካከል ይህንን ከልክ ያለፈ ወሲባዊ ረሀብ ያመጡ ሰዎች፥ ልጃገረዶችና ወንዶች ልጆችን ገና ልጅ እያሉ ወደ ማባለግ የሚመሩና እንደዚህ ዓይነት ብልሽቶችን ያመጡ ሰዎችም ኃላፊነት አለባቸው።

ክርስቲያኖችና ቤተ ክርስቲያንስ? በእርግጥ እነርሱም በአንዳንድ መንገዶች ለምሳሌ በማኅበረሰቡ ላይ በተሻለ መንገድ ተጽዕኖ ባለማምጣታቸው ኃላፊነት አለባቸው። ስለ ወሲባዊነትና ፍቅር ክርስቲያኖቹ ይበልጥ በግልጽነትና አጽንዖት በማስተማርና በመምከር መርዳት ይገባቸው ነበር። በአገር ውስጥ የወንጌል ተልዕኮን ተከትለው በመሥራት፤ ለምሳሌ ማኅበራዊ ተቋማትን በማስጀመርና በማደራጀት በትልልቅ ከተሞች ወዘተ... ዝነኛ ጎዳናዎች እየተዘዋወሩ የምሽት ጥበቃ በማድረግ ብዙ ሊረዱ ይችላሉ። ሌላው አስፈላጊ ነገር «ወሲባዊ ድብቅ የንግድ እንቅስቃሴን» ለማስቆም ወይም ቢያንስ ለመቀነስ አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ የማኅበረሰቡ ኃላፊነት ያለባቸውን ባለሥልጣናት መወትወት ነው።

ሴተኛ አዳሪነት እውቅና ሊሰጠው የማይችል፤ ከቶም ሕጋዊ ሊደረግና በየትኛውም መንገድ ሊደገፍ የማይገባው ክፋት ነው። እንዲህ ዓይነት ክፉ ነገር መኖሩ ብቻ በራሱ ሊያስጸጽተን የሚችል ነገር ነው፤ እስካለም ድረስ በጥብቅ ልንከላከለው እና በሚቻል መንገድ ሁሉ ሊፈወስ የሚገባው ነው።

ወሲብንና ፍቅርን በተመለከተ ሁለተኛው ጉልህ ፍንገጣ ግብረ ሰዶማዊነት ማለትም ‹‹ተመሳሳይ ፆታ ለሆኑት ወሲባዊ ፍላጎት›› ሲሆን ባሕርዩ የሚከሰተው ይህንን ፍላጎት ከተከተሉትና ከተለማመዱት ነው። በቀደሙት ጊዜያት ግብረ ሰዶማዊ ዝንባሌ ብዙ ጊዜ የተደበቀ ነበር። ተለማምደውትም ቢሆን ይደረግ የነበረው በምሥጢር ነበር። ዛሬ ዛሬ ግን በበርካታ አገራት ይበልጡኑ ወደ አደባባይ በግልጽ እየወጣ ነው። ራሳቸውን ‹‹የመቻቻል ሰዎች›› እና ‹‹ከድንቁርና ተላቀናል›› ብለው መጥራት በሚመኙ ሰዎች ሳይቀር በስፋትና በኃይል እየተደገፈ ነው። ተዘውትሮም

ላለ ፍቅር›› ‹‹ተፈጥሮአዊ አማራጭ›› እንደሆነ ተደርጎ መግለጫ ይሰጥበታል። በአሁኑ ጊዜ ብዙዎቹ ግብረ ሰዶማውያን ጥንዶች ሕጋዊ መብት ማለትም ሁለት ወንዶች ወይም ሁለት ሴቶች በሕጋዊነት በተመዘገበ ጋብቻ ውስጥ እንዲኖሩ እስከመጠየቅ ድረስ ርቀው ሄደዋል። በእነዚህ ጉዳዮች አሁን ጊዜው በፍጥነት እየሮጠ ነው። በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በተመሳሳይ ፆታዎች መካከል የሚደረገውን ጋብቻ የመባረክን ሥርዓት እንዲፈጽሙ ከፍተኛ ጫና እየተደረገባቸው ነው። ይህ ዓይነት ፍላጎት ያላቸው ጠንካራ ቡድኖች ይህንን እንደ መብት እየጠየቁና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሳይቀር ሥነ ሥርዓቱ እንዲፈጸም እየጠየቁ ናቸው።

ብዙ ጊዜ ስለ ጉዳዩ የሚቀርበው አንዱ ክርክር የግብረ ሰዶማዊ ዝንባሌ በዘር የሚወረስ ስለ ሆነ ሊወገድ የማይችል ነው የሚል ነው። ይህንን የሚቃወም የመጀመሪያው አሳብ እንደዚህ ዓይነት ነገር መኖሩን የሚያረጋግጥ እውነታ በማያሻማ ሁኔታ አልተረጋገጠም የሚል ይሆናል። በሁለተኛ ደረጃ ጥቂት የውጪ

ሰዎች እስኪያስተምሩትና ተጽዕኖ ባላቸው ጥቂት የቤታው ነዋሪዎች አማካይነት በአገራቱ ላይ መስፋፋት እስኪጀምር ድረስ ግብረ ሰዶማዊነት ሙሉ በሙሉ የማይታወቅባቸው አገራት አሉ። በተከሰተባቸው የአሥርተ ዓመታት ጊዜ ሁሉም አንድም ጉዳይ «የተወረሰ ዝንባሌ» ተብሎ ሊጠራ የሚችል አጋጣሚ አልነበረም። በዚያ ትውልድ ውስጥ የተከሰቱት ሁኔታዎች በቃላትና በምሳሌነት የተማሯቸው ነበሩ እንጂ እንደዚያ በመሆናቸው የተወረሱ አልነበሩም።

የዚህን መጽሐፍ ዋና ዋና አሳቦች በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ዝርዝር ማብራሪያ ለመስጠት አይፈቅዱልንም። ቤተ ክርስቲያንና አባላቶቿ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በአራት መስመሮች ቢሠሩ እንደሚጠቅሙ በአጭሩ መናገሩ ብቻ ይበቃል።

1. [illegible] ካደረጉት ወይም ሌሎች በእነርሱ ላይ ካደረጉባቸው ነገር የተነሳ ለሚሰቃዩት የሌላ ሀዘኔታ ሊኖረን ይገባል፤ ሁሉንም ነገር ወይም ሁኔታዎችን ካለማወቃችን የተነሳ እንዲሁም የእነዚህን ሰዎች መንፈሳዊ ታሪክ ስለማናውቅ ከእነርሱ ጋር በማኖረን ግንኙነት በመጀመሪያ ስለ ኃጢአት በመናገር አለመጀመር ነው።
2. ሰዎች ሁሉ ከአደገኛ አኗኗሮች፥ ከመጥፎ ልምምዶች እና እነዚህ ከሚያስከትሏቸው ውጤቶች በሙሉ እንዲርቁ የተቻለውን ሁሉ እርዳታ መስጠት ነው።
3. በምንችልባቸው ቦታዎች ወይም ቢያንስ በተጠያቂነታቸው ቤቶች ሁሉ ተጨባጭ እና እውነተኛ መረጃ መስጠት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥና ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ለወጣቶችና በአደጋ ላይ ሰዎች ጤናማና እውነተኛ ለብንድ ድጋፍ የሚሰጥበት እውነተኛና «ተፈጥሮአዊ የሆነ» መልክም ሥራ ለመፈጸም ድጋፍና እርዳታ የሚያስፈልጋቸው የተለያዩ [illegible]

[illegible]

4. ቀደም ባሉት ነጥቦች መሠረት በምናደርገው በማናቸውም ነገር ውስጥ በእግዚአብሔር ቃል ጽኑ መሠረት ላይ ማረፍ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ግብረ ሰዶማዊነት በሚሰጠው ምስክርነት መሠረት ግብረ ሰዶማዊነት ክፉ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለበትም (ዘሌዋ. 18፥22-25፤ ሮሜ 1፥18-32)፡፡ ይህ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የመደገፍ ሁኔታ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የጥቃት ሰለባ ለሆኑት ሰዎች የስሜት መጎዳት ንቁ መሆንንና የኀዘኔታ አቀራረብን አይከለክልም፡፡

## እውነተኛ ፍቅርና ጋብቻ አንዱ ሌላውን የሚያገለግልበት ጥሪ ስለመሆኑ

ወሲባዊነትን፥ ፍቅርንና ጋብቻን የሚመለከቱ ፍንገጣዎች በሙሉ የራስ ወዳድነትን ዓላማ ማለትም ራስንና ምኞትን ለማርካት

ሁልጊዜ ለሌላው ሰው ጥቅም ሲል ሌላ አካልን ያገለግላል፡፡ በመሆኑም ተጨባጭ ፍቅር የራሱን ምኞት ለማርካት ሌላን ሰብዓዊ ፍጡር እንደ መሣሪያ አድርጎ ሊጠቀም አይችልም፡፡ በዚህ ምትክ እውነተኛ ፍቅር የፍቅሩ ማረፊያ የሆነውን ሰው ደስታና ደኅንነት ማግኘት ይፈልጋል፡፡ ሴተኛ አዳሪነትና ግብረ ሰዶማዊነት ሁለቱም በእነዚህ ነጥቦች ላይ ከንቱ ይሆናሉ፡፡ ከጨዋነትና ከመልካም ምግባር ምልክት በታችም እጅግ ርቀው ይወድቃሉ፡፡

ፍቅር የገዛ ራሱን ፍላጎት ብቻ ማርኪያ መሣሪያ ወይም መንገድ ሊሆን ከቶውንም አይችልም፡፡ ደስታ እና ሐሴት የአጠቃላዩ ነገሮች ክፍል እንጂ በራሳቸው ዋና ስላልሆኑ አነስተኛ ክፍል የሚይዙ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ነገር በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል ያለው ፍቅር፥ ሕይወትን ለማገልገል ግለሰባዊነትና የጋራ ጥሪን ያካተተ በሁለቱ መካከል ያለ ግላዊ ውህደት ነው፡፡ አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ከጊዜያዊ ምኞት እና በሥጋዊ ጉጉት ብቻ ተነሳስተው ሳይሆን እርስ በእርሳቸው ሊዋደዱና

ለወደፊቱ አብረው ለመኖር ሲወስኑ ጋብቻቸው በአካል፥ በአእምሮና በነፍስ በከፊል ሲጋሩ አገልግሎት፥ በከፊል ደግሞ መሰል ሰዎችን፥ ማኅበረሰባቸውንና የሰው ዘርን ሁሉ ለማገልገል የሚረዱበት ቃል ኪዳን ነው። በመሆኑም ውህደታቸው ለሕይወት ጥቅምና አገልግሎት የሆነ ውህደት ነው። ጥልቅ ግንኙነታቸው፥ ደስታቸውና የጋብቻ ሐሴታቸው ለዚህ አገልግሎት እንደ መሣሪያዎች ያገለግላሉ። የአገልግሎት አሳቦችን ሁሉ ካስወጡ እና በዚያ ፈንታ ራሳቸውን ለደስታቸው ብቻ ከሰጡ ግን ይህ ደስታ በጥቂት ይከስማል፤ ይጠፋልም። በተጓዳኝነት «የበለጠ ጠንካራ»፥ «የተሻለ» ወይም «እውነተኛ ደስታ» የሚሉትን ሌላ ደስታ ወዲያውኑ መፈለግ ይጀምራሉ።

በእንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች የበለጠ ደስታና ሐሴት ለማግኘት ሲባል ስለ «አገልግሎት»፥ ሲወለዱ ስለሚችሉ [illegible]

[illegible] ይጠፋል።

ስለ ወሲብ፥ ስለ ፍቅርና ስለ ጋብቻ የሚያስተምር ጤናማ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ሁሌጊዜ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊውና ለተባረከው እይታ እጅግ አጽንዖት ሊሰጥ ይገባዋል። ፍቅርና ጋብቻ ክርስቶስ ለእኛ ያለው ፍቅር አምሳል እና ማብራሪያ ናቸው (ኤፌ. 5፥21-33)። ይህ እይታ በቅርባችን ስለሆነው ሰው፥ ለሚስት ወይም ለባል እንዲሁም የዚህ ዓይነት ፍቅር ፍሬ ስለሆኑትና በአጠቃላይ ለማኅበረሰቡ አገልግሎት ለመስጠት ሁሌጊዜ ያነሳሳል። በዚህ ሁኔታ ፍቅር፥ ቤተ ሰብ እና ቤት እንደ እጽዋት ችግኞች ማፍያና ማሳደጊያ ቦታ ለትንንሽ ልጆች እንደ ዓይነት የመንከባከቢያ ስፍራ ይሆናል። አንድ ቀን እነዚህ እፅዋት ከመንከባከቢያ ጣቢያቸው ተወስደው ግልጽ መሬት ላይ ማደግ ይጀምራሉ። የፍቅር አገልግሎት እንደዚህ ዓይነት ሲሆን ቀጣይ ሕይወትን ያገለግላል።

# ምዕራፍ 10
# ቤትና ቤተ ሰብ

## መሠረታዊ የቤተ ሰብ ክፍል

እያንዳንዱ ግለሰብ የአንድ ቤተ ሰብ መሠረታዊ ክፍል ይሁን እንጂ ግለሰቦች ከመኖራቸው በፊት ግን ቢንድ ማለትም ወላጆች ይኖራሉ። በተጨማሪም አዲሱ ሰው ማንኛውንም ሥራ ከማከናወኑ በፊት ወይም ማንኛውንም ተጽዕኖ ወይም ተጸማጭነት ከማግኘቱ በፊት ዕድገት፥ እንክብካቤ፥ ትምህርትና ሥልጠና ያስፈልገዋል። ከእነዚህ ዝርዝር ነገሮች መካከል የመጀመሪያዎቹ ክፍሎች አብዛኛውን ጊዜ በልጅ በቤተ ሰብ ውስጥ በወላጆች አማካይነት ይከናወናል። ልጆች በቤታቸው ውስጥ የሚያገኙት

የትብብር መንፈስ፥ ትምህርትና ሥልጠና በዓለም ማኅበረ ሰብ ዘንድ ለሚኖራቸው ግንኙነት መሠረት ይሆናል። የቤተ ሰብ ተጽዕኖና አስፈላጊነት ያላረፈበት ሕዝብ ወይም ሥልጣኔ በየትኛውም የዓለም ክፍል ኖሮ አያውቅም። ከዚህ የተለየ መርህ የሚከተል ሕዝብና ሥልጣኔ ኖሮ ከሆነ ለረጅም ጊዜ ዘልቆ አያውቅም።

አንዳንድ ጊዜ ጋብቻዎች፥ ቤትና ቤተ ሰብ በብዙ ጊዜ ሂደት ውስጥ የተፈጠረ እንደ ሆነ አድርገው የሚቀርብ አስተሳሰብ አለ። ይህ አስተሳሰብ ግን የተሳሳተ ነው። ወደ ኋላ የቀሩ ናቸው የሚባሉትን አገሮች እንኳ ብንመለከት ባደጉ አገሮች የሚታየውን ያህል የቤተ ሰብ የኑሮ ዘይቤ አላቸው። ዘመናዊ ነው በሚባለው ዓለም ውስጥ ግን ከልጁ ውልደት አንሥቶ የቤተ ሰብን ኑሮ በመንግሥታዊ የኑሮ ተቋማት ለመለወጥ ጥረት በሚደረግበት ሁኔታ ውስጥ ውጤቱ አሉታዊ ሆኖ ተገኝቶአል። ይህም ማለት በተፈጥሮ ቤተ ሰብና እና ቤት የምንላቸው ተቋማት ሊተኩ ወይም ከመነሻው እንዲኖራቸውም ማለት ነው።

ወላጅነት፣ ስጦታም ኃላፊነትም ነው

በአንዳንድ ነበባት ወላጅ ለመሆን ጥሩ የሆነ መደብና ትምህርት አስፈላጊ ነው የሚል አስተሳሰብ አለ። ጥሩ የኢኮኖሚ ደረጃ ቢኖራቸው ጠቀሜታው የጎላ ነው የሚል አመለካከትም ይኖራል። ይህ ሁሉ አመለካከት በጣም የተጋነነ አመለካከት መሆኑን በኋላ ላይ ተደርሶበታል። ሌሎች አስፈላጊ ነገሮች የሚጎድሉ ቢሆን እንኳ ትምህርትና ገንዘብ በዚህ ምድብ ውስጥ የሚካተቱ መሆናቸው ተረጋግጦአል። ሌሎች አስፈላጊ ናቸው የሚባሉት ነገሮች ፍቅር፣ ሥነ ምግባራዊ መረጋጋት፣ ጠባይ፣ ስለ ራስ የተሟላ አመለካከት፣ የሕይወት ግቦችና የመላመድ ችሎታ ናቸው። ለልጆቻቸው መልካም ነገር ማለትም ገንዘብ፣ ንብረት፣ የናጠጠ የትምህርት ደረጃ መስጠት የሚችሉት ወላጆች የመኖራቸውን ያህል ለልጆቻቸው ምንም መስጠት የማይችሉ ወላጆችም [illegible]

ይኖራሉ። [illegible] አቅም የሌላቸው ወላጆች ታማኝነትን፣ ስጦታም አለመሆንን፣ ትጉህ ሠራተኛ መሆንን እና ስለ አደራነትን በልጆቻቸው ላይ የማሳደር ልምድ ሊኖራቸው ይችላል። እንግዲህ ከእነዚህ ልጆች ከፍ የሆኑ ነገሮችን ለልጆቻቸው የሚያወርሱ የተሻሉ ወላጆች ይሆናሉ? ከሁለቱ ወላጆች ልጆች የትኞቹ ወላጆች ልጆች ናቸው "መልካም ወላጆች ስለ ነበሩኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ" የሚሉት የተሻሉ ወላጆች ይሆናሉ?

የመልካም ወላጅነት ጅማሬ ወላጆች ራሳቸው ልጆች የነበሩበት ጊዜ ነው። ይህም ማለት በወላጆቻቸው ቤት በነበራቸው ሕይወት ውስጥ ነው ማለት ነው። በዚያም ወጣት የሆኑ ሰዎች አንድ ቀን እናት ወይም አባት የመሆንን ዋጋ ይማራሉ ማለት ነው። በእርግጥ ከክፉ ቤተ ሰብ የሚመጡ ልጆች መልካም ወላጆች ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ግን በሌሎች ቤተ ሰቦች መልካም ምሳሌ ተጽዕኖ፣ የሕይወት ተሞክሮ ወይም "በልጅነቴ በሰቦሀብት ክፉ ነገር ውስጥ ቤተ ሰቤን እንዲያልፉ አልፈቅድም" በሚል የግል ተነሳሽነት እና በሌሎች ነገሮች ላይ ሊመረኮዝ ይችላል።

## ልጆች ጠንቅ ወይንስ በረከት ናቸው?

በአብዛኞቹ የሰው ልጅ ሥልጣኔዎች ልጆች በረከት ተብሎ ይታሰባል። በክርስቲያን አመለካከት ውስጥ ‹‹እነሆ÷ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው፤ የሆድህም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው›› (መዝ. 127÷3) የሚል መረዳት አለ። ነገር ግን ራስ ወዳድ የመሆን ዝንባሌና የናጠጠ ኑሮ ፍላጎት እየገዘፈ የሚሄድ መንፈስ የፍቅርና የማኅበረሰብነትን መንፈስ እየተጋፋ የሚሄድበት የሥልጣኔ ሂደት እያየለ መጥቶአል። በሌላ በኩል ጤናን÷ ልብስን÷ ትምህርትን እና አጠቃላይ ኑሮን አስመልክቶ እንክብካቤ ካልተደረገላቸው በአንድ ቤተ ሰብ ውስጥ ብዙ ልጆች መኖራቸው ብቻ የፍቅር ዋስትና ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ልጆችን የሚወልዱ ሰዎች ሁሉ ለልጆቻቸው ዓለማዊም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወት አስፈላጊ የሆነውን ኃላፊነት መወጣት አለባቸው። በእርግጥ የአካባቢውና አጠቃላዩ ማኅበረሰብ የልጆች መዋያ ስፍራን÷ የትንንሽ ልጆች ትምህርት ቤትን÷ የልጆች ጤና መከታተያ ክሊኒክንና አማካሪዎቻቸውን በሚመለከት ትልቅ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ትልቁ ኃላፊነት የሚወድቀው በወላጆች ላይ ነው። ጥሩ ትምህርት ቤትና ሥልጠና በጣም አስፈላጊ ይሁኑ እንጂ ከእነዚህ ነገሮች በተጨማሪ ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ከታናሽነታቸው ጊዜ ጀምሮ እንዲሰርጽ የሚያደርጉት መልካም ነገር ምሳሌነቱ በእጅጉ የጎላ ነው። ከእነዚህ ነገሮች መካከል ለምሳሌ በዓለም ላይ በሥርዓት መመላለስ÷ ሰዎችን ማክበር÷ ታማኝነት÷ መታተዝ÷ እውነተኝነት÷ ፍቅር÷ ተግዳሮት ባለበት ሁኔታ ውስጥ እንኳ ደስተኛ ሆኖ መገኘት ናቸው። በእርግጥ እነዚህን በጎነቶች በቅደም ተከተል ማስቀመጥ አይቻልም። ዋናው ነገር ወላጆች እነዚህን ችግሮች የሚፈቱበትን÷ የኑሮ ዘዬዎች ለልጆቻቸው የሚያሳዩበትና ለመልካም ነገር ልጆቻቸውን የሚያነሳሱበትን መንገድ በራሳቸው ሊፈልጉ ይችላሉ።

ልጆች በልጅነታቸው የሚመሳሰሉ ካልሆነ በስተቀር በመካከላቸው ትልቅ ልዩነት አለ። ስለ ሆነም ወላጆች ልጆቻቸውን

በመልካም አስተዳደግ ማሳደግና አንድ ቀን ፍሬ እንደሚሰጡ ትናንሽ አትክልቶች አድርገው እንክብካቤ ሊያደርጉላቸው ይገባል። ወላጆች ይህንን ብቻቸውን ለልጆቻቸው ሊያደርጉ አይችሉም። ስለዚህ ከዘመዶቻቸው+ ከወዳጆቻቸው እና ከማኅበረሰቡ ብዙ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። በሌላ በኩል ለልጆች እንክብካቤ ማድረግ የትምህርት ቤቶች+ ማኅበራዊ ተቋማት ወይም የአጠቃላዩ ማኅበረሰብ ኃላፊነት አድርጎ የመመልከት ስሕተት ይስተዋላል። በእርግጥ ማኅበረሰቡ ልጆችን የመንከባከብ ኃላፊነት ይኖረው እንጂ ልጆቻቸውን የወለዱት እነርሱ በመሆናቸውና የቅርብ ስለ ሆኑ ሁሉም ወላጆች በሕይወት እስካሉ ድረስ ትልቁ ኃላፊነት የሚወድቀው በእነርሱ ላይ ነው።

## የልጆች ትምህርት

ለልጆች የሚሰጠው ትምህርትና ሥልጠና ሁሉ ተግባራዊ ሊሆን በሚችልበት መንገድ የሚታቀድና የሚሆን መሆን አለበት። በዚህ ላይ ግን ብዙ ወላጆች አይሳካላቸውም። ጥሩ ስጦታ ያላቸውና ከፍተኛ ትምህርት የቀሰሙ ወላጆች ልጆቻቸው እንደ እነርሱ እንዲሆኑ ስለሚፈልጉ ከልጆቻቸው ተመሳሳይ ስኬትን ይጠብቃሉ። በዚህም ምክንያት ልጆቻቸው ለሚኖራቸው ሌላ ችሎታ ስፍራ አይሰጡትም። ብዙ ያልተማሩ ወላጆች ደግሞ እነርሱ ወዳልደረሱበት የእውቀት ደረጃ ልጆቻቸው እንዲደርሱላቸው ይመኛሉ። ይህ የወላጆች ፍላጎት ግን ከልጆቻቸው ስጦታና ችሎታ ጋር የማይጣጣም ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የልጆቻቸው ስጦታና ችሎታ ከሚፈቅደው በላይ እንዲያከናውኑ ልጆችን መግፋት ስሕተት ነው። እንዲሁም አእምሮአዊና መንፈሳዊ ጫናዎችን በልጆች ላይ ማሳደር ማለትም ልጆችን በስሕተታቸው ሁልጊዜ መውቀስ ርኅራኄ በሌለው ቃል ልጆችን መገሰጽ ሌላው ስሕተት ነው። ይህን ሁሉ ስሕተት ለማረም የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በጣም ጠቃሚ ነው። «ከሰማይ ከተሰጠው በቀር ማንም ምንም ሊቀበል አይችልም» (ዮሐ. 3፥27)።

ከቤተ ሰብ ፥ ከቤትና ከትምህርት ጋር የሚያያዙና አስደናቂ የሆኑ ነገሮች አሉ። አስገራሚ የሆነውም ነገር መልካም የሆነ ሁኔታ ገጽታ ባለው ቤት ውስጥ መልካም ያልሆነ የልጆች አስተዳደግ ሲታይ፤ በድሃ ቤተ ሰብ ውስጥ ያለው የልጆች አስተዳደግ ግን በእጅጉ መልካም ሆኖ መታየቱ ነው። እነዚህ እውነቶች ልጆች በሕይወት ዘመናቸው ምን ሊገጥማቸው እንደሚችል እርግጠኛ መሆን እንደማይቻል ያሳዩናል። ልጅን በማሳደግ በኩል ስኬታማ ለመሆን የሚያስችል ማረጋገጫ የለም። እያንዳንዱ ቤት «ችግር አምጪ ልጅ» ብቻ ሳይሆን «የጠፋ ልጅም» (ሉቃ. 15+11-13) ይኖረዋል። ስለዚህ ለሁላችን ማድረግ የሚኖርብን አንድ ነገር አለ። ይኸውም ባለን ስጦታ ሁሉ ማድረግ የምንችለውን ማድረግ፤ ለተሰጡን ልጆች ዕድገት በምናደርገው ጥረት የእግዚአብሔር እርዳታ እንድናገኝ መጸለይ ነው።

እዚህ ላይ ባለፉት ብዙ ትውልዶች ዘንድ ተቀባይነት

የነበራቸውን መርሆዎች መጥቀስ አስፈላጊ ይሆናል። በመጀመሪያ መልካም የልጆች አስተዳደግ በገንዘብ ወይም በሁኔታ በሚታይ ገንዘብ ብዛት አይመሰረትም። አንዳንዶች ይህ ይሆናል ብለው ያምናሉ። በዚህም ምክንያት ለልጆቻቸው አስጠኚ ይቀጥራሉ። ነገር ግን የልጆቻቸው ቤት በዚህ ዋስትና ሊኖረው አይችልም። ይልቁንም ይህ ጥረታቸው ተቃራኒ ውጤት ሊያመጣ ይችላል። ይህም ሊሆን የሚችለው ከሌሎች ልጆች ጋር ኅብረት የማድረግና አብሮ የመጫወት ልምድ ስለማይኖራቸው በራሳቸው ጉዳይ ላይ ብቻ የሚያተኩሩና የፈለጉትን ነገር አምጡ የሚል መንፈስ በሁለጣቸው ስለሚጎለብት በኅብረተሰቡ ዘንድ በተለመደው መንገድ ለመኖር የሚቸገሩ ሆነው ያድጋሉ።

ሁለተኛ፦ መልካም አስተዳደግ ወይም ትምህርት ሥልጠናና ትእዛዛትን በመቀበል ብቻ አይመጣም። መልካም አስተዳደግ ወይም ትምህርት በኃይል ወይም በመጫን አይመሰረትም። ይልቁንም የትብብርና ለልጆች ወይም ለተማሪዎች መልካም አርአያ የመሆን ጉዳይ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ለመልካም ወላጆች

ወይም አስተማሪዎች ጥሩ የሆነ ባለንጀራ አለ። እርሱም መልካም አርአያነት ነው። የቃል ትምህርት ማምጣት ያልቻለውን ውጤት ከቃል፣ ከተግባር፣ ከታማኝነት፣ ከርህራኄና ራስ ወዳድ ከመሆን ይልቅ መልካም አርአያ ከመሆን ይገኛል። በነዚህ መንገዶች የሚገኘው ፍሬ ብዙዎች በቃል ካስገኙት ውጤት ይልቅ የበለጠ ይሆናል።

ሦስተኛ፡ የትኛውም የትምህርት ዓይነት ወይም በማንኛውም ደረጃ የሚሰጠው ትምህርትና ሥልጠና ሁልጊዜ የመስጠትና የመቀበል ጉዳይ ነው። ራሱን ከፍ የሚያደርግ እንደ ጥሩ አስተማሪ የሚቆጠረው ለትንሽ ጊዜ ብቻ ሊሆን ይችላል። ትምህርት ሲጀምር «አሁን አንድ ነገር እነግራችኋለሁ» «በመሆኔ» «አሳያችኋለሁ» የሚል አስተማሪ ጥሩ አስተማሪ አይደለም፡ ፡ በተቃራኒው ግን «ይህንን ችግር ለማቃለል ማን ሊረዳን ይችላል» ወይም «አንድ ነገር አብረን ለማግኘት እንሞክር»

በማለት የሚጀምር አስተማሪ ተማሪዎቹ በእርሱ ላይ መተማመን እንዲኖራቸው ያደርጋል። ይህ መርህ በወላጆችና በልጆቻቸው መካከልም ተግባራዊ ይሆናል።

አራተኛ፡ የልጆችን መተማመን ማግኘት ከመልካም ወላጆች ምስጢር አንዱ ነው። ይህ ደግሞ ሳይከፈቱ ሊቀሩ የሚችሉ በሮች የሚከፈቱበት በር ሊሆን ይችላል፡ በሌሎች የትምህርት ጉዳዮች ለምሳሌ ውጤትን፣ የክፍል ደረጃን ሰርተፊኬትን ጨምሮ በሁሉም ቤተ ሰብ ማለት በድሃም ሆነ በሀብታም ቤት የሚደረስባቸው ብዙ ግቦች አሉ። እንደዚሁ ያሉ ግቦች በሀብታም ቤት ይሁን በድሃ ወይም ከፍተኛ ትምህርት ባላቸው ወይም ምንም ባልተማሩ ወላጆች ሊደረስባቸው ይችላሉ። እዚህ ላይ ትኩረት የሚሻው ነገር ፍቅር፣ መግባባት፣ ጥሩ አሳቢ መሆን እና መልካም ኅብረት ነው። እንደዚሁ ያለ መንፈስ የሚያደርጉባቸውና ይህንን መንፈስ የሚለማመዱ ልጆች በወላጆቻቸው ቤት ከሚያገኙት ሥልጠና በኋላ ከሰፊው ማኅበረሰብ ጋራ ኅብረት ለማድረግና ለመተባበር ዝግጁ ይሆናሉ።

ከአሥርቱ ትእዛዛት በአንዱ እንዲህ ተብሎአል፤ «እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር እድሜህ ይረዝም ዘንድ አባትህንና እናትህን አክብር» (ዘጸ. 20፥12)። እንደዚሁ ያለውን ትእዛዝ በሚቃረን መልኩ ብዙውን ጊዜ እንዲህ የሚል ክርክር አለ። «ወላጆች ክብር የማይገባቸው ሆነው ከተገኙ እንዴት ሊያከብራቸው እንችላለን?» እንዲህ የሚመስሉ ለየት ያሉ ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው መልስ ባለ ሦስት ፈርጅ መልስ ሊሆን ይችላል። መጀመሪያ አንዳንድ ጊዜ ከወላጆች አንዱ ወይም ሁለቱ ለየት ያለ ጠባይ የሚያሳዩ ወይም ከቶ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ግን ሊያስጨንቀን አይገባም። እንዲህ ያሉ ሰዎች በራሳቸው መንገድ ልጆቻቸውን የሚወዱበት እውነተኛ ፍቅር ሊኖር ይችላል። የወላጅ ፍቅር እንክብካቤ ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ የሚፈልግ ልጅ ከወላጁ የሚጎድለው ነገር ምን እንደሆነ ይዋል ይደር የሚረዳበትን ክፍተቱን የሚሞላበትን መንገድ ይገነዘባል።

ወላጆቻቸውን ለማክበር የሚጠራጠሩ ልጆች ወጣቶች በወላጆቻቸው ኑሮ ውስጥ ስለሚያዩት ጉድለት እውነታውን አይገነዘቡም። ይልቁንም የሚታያቸውን ነገር በወላጆቻቸው ቤት ያለው ድህነት ሆኖ «ከልጆች ሁሉ እኛ ብቻ ለምን እንዲህ ያለ ድሃ ወላጆች ኖሩን?» የሚል ጥያቄ ይበረታባቸዋል። እንደዚሁ ያለ አሳብ ያላቸው ልጆች የማያስተውሉት ነገር ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው ነገር ነው። ይኸውም ሀብታም ወላጆች በድንገት ድሃ የሚሆኑ ወይም በግብረ ገብ የሚዘቅጡ መሆናቸው ነው። እንደዚሁም ባለጸጋ የሆኑ ወላጆች ያላቸው ልጆች በወላጆቻቸው ሀብት ምክንያት ቀልቃቃ ሆነው በማደጋቸው ምክንያት በራሳቸው አቅም መኖር ከባድ ሊሆንባቸው ይታያል። ነገሩ እንዲህ የሚሆን ከሆነ የወላጆች ሀብት ምንን ያህል ልጆችን ሊረዳ ቻለ?

በተጨማሪም በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ወላጆችን ማክበር ተገቢ መሆኑን የሚገልጽ ነገር ሁልጊዜ ይኖራል። ከዚህ መርህ በስተጀርባ ያለው እውነታ ፍንትው ብሎ የሚታየው

ለወላጆች ሊሰጠው የሚገባው ክብር በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚሸፈን ከሆነ ነው። ይህ በሚሆንበት ሁኔታ ውስጥ ብዙ ልጆችና ወጣቶች ወላጆቻቸውን በቤት ውስጥ አብረው እንደሚኖሩ ደባል፣ የሚያስፈልጓቸውን ነገር አቅራቢ እንዲሁም ገንዘብ ሰጪ ብቻ አድርገው በሚመለከቱበት ጊዜ ነው። እንዲህ ያለው መንፈስ ወደ አንድ ቤተ ሰብ ሰርጎ በሚገባበት ጊዜ ያንን መንፈስ ማሸነፍ ከባድ ይሆናል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በአንድ ቤተ ሰብ ውስጥ ሲኖር ብዙ ነገሮችን መዳሰስ ሲያስፈልግ በተለይ ደግሞ የወላጆችንና የልጆችን መንፈሳዊና ሥነ ምግባራዊ ሁኔታ መፈተሽ አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ ቦታ የምናነሳውን ነገር አስመልክቶ በተለቀ የክርስትና ትምህርት ማጠቃለያ እንደተነገረው ማክበር ትሕትናን፣ አክብሮትን፣ ወላጆችን በትሕትና በአክብሮት መቀበል ብቻ ሳይሆን በልባችንና በሰውነታችን ጭምር ማክበርን፣ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ እነርሱ የበላዮቻችን እንደሆኑ አድርገን ማሰብ የሚሉትን አሳቦች በለማይዝ መውደድ ከሚለውም ቃል ይበልጣል። አንድ ክልብ

የምናከብረው ሰው እርሱን እንደ ከፍተኛ ተልቅ ሰው አድርገን ማሰብ አለብን። እንዲሁም ልጆች ወላጆቻቸው ምንም ያህል ዝቅተኛ ወይም ድሃ ቢሆኑ በእግዚአብሔር እንደተሰጡአቸው አድርገው እንዲያከብሩአቸው በልጆች ልብ ማሳደር አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ወላጆች በጠባያቸው ምክንያት የወላጅነትን ክብር ማጣት የለባቸውም። ስለዚህ ወላጆች በሰዋዊ ሁኔታቸው የትኛውም ዓይነት ድካም ቢታይባቸው በፈጠራቸውና ባቀማቸው እግዚአብሔር ምክንያት ሊከበሩ ይገባቸዋል።

## የወላጆች ቤት ልጆች ማኅበራዊና መንፈሳዊ ሕይወት የሚለማመዱበት ቦታ ስለመሆኑ

ወላጆች በመጀመሪያ ያለባቸው ግዴታ ልጆቻቸውን ይመለከታል። ነገር ግን ልጆች ከሌሎች ሰዎች ጋር በሚገናኙበት ጊዜ ወላጆች በዚህ ምክንያት የሚገናኙማቸው ደስታና ምቾት ማጣት ወዲያውኑ ብቅ ማለት ይጀምራል። እዚህ ላይ ወላጆች ልጆቻቸውን ከክፉ ባልንጀሮች ለመጠበቅ ሲሉ ከሌሎች ለይተው

በቤት ውስጥ በሚገዋል አይጋወጥንና ጉዳቱን ለመተንስ መሞከር መፍትሔ ሊሆን አይችልም። መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ልጆች መልካም ግንኙነት እንዲፈጥሩ፤ ምን መደረግና ምን መወገድ እንዳለበት እንዲያውቁ ልጆችን መርዳት ነው።

መልካም መንፈስ ያለበት ቤት በደስታ፤ በትብብርና በመተባበር ይገለጻና ወደ ውጭም ይንጸባረቃል። ይህ በመጀመሪያ የሚታወቀው ለዘመዶች፣ ለጎረቤቶች እና ለጎብኚዎች ሆኖ በተጨባይነት ደግሞ በመዋዕለ ሕጻናትና በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚታይ ይሆናል። በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የሚፈቱ ችግሮች የሚያኖሩ ሲሆኑ ከሚፈቱ ችግሮች መካከል ደግሞ ትምህርት ይገኛል። ከነዚህ ተግዳሮቶች የሚገኘው ትምህርት አማራጭ መፍትሔን መፈለግ፤ ትሕትና፤ ግልጽነት ለመተባበር ፈቃደኛ መሆን እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። አንድ ትምህርት ቤት ወይም ማኅበረሰብ አንድን ሕጻን ምንም እንዲሰለጥነው ባዶ ወረቀት ሆኖ ያገኘዋል ብሎ ማሰብ አይቻልም። ትምህርት ቤት ወይም

ማኅበረሰብ አንድን ሕጻን ምንም እንዲሰለጥነው ባዶ ወረቀት ሆኖ ካገኘው ምን መደረግ አለበት? በአሁኑ ጊዜ ትምህርት ቤቶችና ማኅበረሰቦች የሚቀበሉአቸው ሕጻናት በመጠኑም ቢሆን ለማኅበረሰብ ሕይወት የተዘጋጁ ናቸው የሚል አመለካከት አለ፤ ይህ ዝግጅት የሚጀምረው ከወላጆች ቤት ነው። በእርግጥ ልጆች ትናንሽ ቢሆኑም መሠረታዊ የሆኑ መርሆዎችን ከቤት ተምረዋል፤ ተለማምደዋልም። እነዚህም መሠረታዊ መርሆዎች ኅብረት ማድረግ፣ ትሕትና፣ ትክክለኛና ትክክል ያልሆነውን የማወቅ መሠረታዊ እውቀት ናቸው።

አንዳንድ ጊዜ ትናንሽ ወይም ያደጉ ልጆች ከወላጆቻቸው ሁለቱንም ወይም ከሁለት አንዱን በሞት፤ በፍቺና በክፉ አደጋ ያጡ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሁኔታዎች የሚያሳዝኑ ቢሆንም ልጆች ከማኅበረሰቡ መልካም ግንኙነት ውጭ የሆኑ ወይም የበታች አድርገው ራሳቸውን መቁጠር የለባቸውም። እንደዚህ ያሉ ልጆች በቅርብ ዘመድ ቤት፤ በግል ቤት ወይም በልጆች ማሳደጊያ ቤት

ወይም በጉዲፈቻ ወላጆቻቸውን የሚተኩ ቤተ ሰቦችን ሊያገኙ ይችላሉ። እንደዚህ ያሉ ልጆች ብዙውን ጊዜ መጀመሪያውን ክፉ አጋጣሚ በማወቅ የሚደረግላቸውን ድጋፍ በውስጠኛነት መንፈስ ተቀብለው ጥሩ ወጣቶችና የማኅበረሰቡ አካል ሊሆኑ ይችላሉ።

የወላጆችን ቤት አስመልክቶ እዚህ የተነገረው መልካምና አዎንታዊ ነገር በሲቪክስና በትምህርት ጉዳይ አስተሳሰብ ተቀባይነት አለው ማለት አይቻልም። የዚህ ዓይነት አሳብን የሚከተሉ ብዙዎች ሰዎች የሲዊሳዊውን የጆጆ ሮሳውን (1712-1778) አስተሳሰብ የሚከተሉ ሲሆኑ ይህ አሳብ እስከ አሁን ድረስ ትምህርትንና የልጆች አደገትን አስመልክቶ መሪ አሳብ ሆኖ ቀጥሎአል። ጆጆ ሮሳው በዚህ አስተሳሰቡ ውድቀት የደረሰበት ሆኖ እያለ እስከ አሁን ድረስ ብዙዎች የርሱን አስተሳሰብ ይዘው መቀጠላቸው አስገራሚ ነው። ሮሳው የራሱ ልጆች በሕፃንነታቸው ጊዜ ከማኅበረሰቡ ድጋፍ እስኪያስፈልጋቸው ድረስ የተለያቸውና

ብዙዎቹ የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ነቢያት ወላጆች ልጆቻቸውን ለማሳደግ ብቃት እንደሌላቸው አድርገው በመቆጣጠር ማኅበረሰቡ ልጆችን መንከባከብ አለበት ብለው ያስባሉ። ይሁን እንጂ ብዙዎቹ፣ በተለይም አምባገነን አመራር ያላቸው አገሮች ብዙ ጎልቶ የሆነ ውድቀትን አስተናግደዋል፤ ብዙውን ጊዜም ትምህርት ቤቶችንና ኅብረተሰቡን በኋላቀር ቀውስ ውስጥ ጨምረዋል። በከፋም መልኩም ለቤተ ሰብና ለልጆች ከተቀመጠው ግብ በእጅጉ ርቀዋል። በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ የትምህርት ቤት፣ የተቋማትና የኅብረተሰቡ መሠረት ስለ ተቃወሰ ውድቀቱ ፈጽሞ ሊያስገርም የሚችል አይደለም። የትምህርት ቤት፣ የተቋማትና የኅብረተሰቡ መሠረት ደግሞ የወላጆቻቸው ቤት በልጆች ላይ የሚያሳድረው መልካም አስተዋፅኦ ነው።

## የክርስቲያን ቤት

የክርስቲያን ቤት በብዙ መንገዶች እንደ ሌሎቹ መልካም ቤቶ

ሰቦች ሁሉ የሥርዓት፣ የመተባበርና የመረዳዳት መንፈስ ያለበት ቤት ነው። ይሁን እንጂ ከዚህ የሚያልፍ ነገር በክርስቲያን ቤት ይስተዋላል። ይኸውም በወላጆችና በልጆች መካከል እግዚአብሔር የፈጠረን፣ የሚንከባከበንና በሕይወት ሊመራን የሚፈልግ ሰማያዊ አባታችን ነው በሚለው እምነት ላይ የሚመሠረት መሆኑ ነው። ልጆች ከዚህ የሚማሩት፣ የሚለማመዱትና ለራሳቸውና ለሚቀጥለው ትውልድ የሚያስተላልፉት መልእክት እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው።

ክርስቲያን ባልሆኑት ዘንድ ክርስትና በልጆች ላይ ብዙ ጫና መፍጠር ነው በሚሉት መንገድ አይሁን እንጂ የክርስቲያን ቤተ ሰብ ቤት ከሌሎቹ ቤተ ሰብ ይለያል። ልዩነቱም በጋራ መግባባትና መተባበል፣ በፍቅር፣ በፈቃደኝነት እንዲሁም እንዱ ሌላውን በማገልገል ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው።

ይህ አባባል በግልባጭ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል። ይኸውም

ዘሊሆርዲንትሪ ሊያዘወግሩት የሚችለውን ነገር ይመለከታል። ክርስቲያን ወላጆች ልጆቻቸውን እንርሱ የሚፈልጉትን እንዲያደርጉ ለማስገደድ ሥልጣናቸውን በኃይል መጠቀሙን ማስወገድ ነው። ክርስቲያን ቤተ ሰብ እንዲህ ያለው መተኛ ሰው ወይም ዝና ያላቸው ሲሆን ይህ መግባ ሰማቸው እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። በእንዲህ ዓይነት መግባ ነገር የሚታወቅ ክርስቲያን ካለ ያ ሰው የክርስትና እምነት በቤት፣ በቤተ ሰብ፣ በትምህርት ቤትና በሥልጠና ሊኖረው የሚገባውን ትርጉም ያጣዋል። የአሠራር ትእዛዝ፣ ሥነ ሥርዓት፣ ቢሮክራ ሥልጣንና መቃዘዝ በሁሉም ስፍራና በክርስቲያን ቤተ ሰብ ውስጥ አስፈላጊ ናቸው። ልዩነቱ የሚታየው እነዚህ አስፈላጊ ነገሮች በሚተገበሩበት መንገድ ላይ ነው። ሥርዓት፣ ሥልጣንና መቃዘዝ ከፍቅር፣ ከጋራ መግባባት እና ለመተባበር ፈቃደኛ ሆኖ ከመገኘት ጋር የተቆራኙ ናቸው። ከቤት ውጭ ሰዎችን በግልና በማኅበረሰብ ደረጃ ለማገልገል በብዙ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተሳትፎ በሚያደርጉበት በዚህ ዘመናዊ ጊዜአችን ቤተ ሰብን በአጠቃላይ ክርስቲያን ቤተ ሰብን ደግሞ

በተለይ የሚገጥሙ አደጋዎች አሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ አስገራሚ የሚሆነው ክርስቲያኖች ለልጆቻቸው የሚናገሩትን ኃላፊነት የመርሳት አደጋ ነው። አደጋው የከፋ የሚሆነው አንድ በመልካም ክርስቲያን ቤተ ሰብ ውስጥ ያደገ ሰው «ወላጆቼ ለሌሎች ሰዎች ካላቸው ፍቅርና ከሚያደርጉላቸው እንክብካቤ የተነሣ እኔን አግልለውኛል፤ ረስተውኛልም» የሚል ወቀሳ ሲናገር ነው።

### በክርስቲያን ቤተ ሰብ ላይ የማረፍ በረከት

አስቀድሞ የተጠቀሱት አደጋዎችን ማስወገድ ቢቻል በሁሉም የክርስቲያን ቤተ ሰብ ላይ የሚወርድ በረከት አለ። ይህ በረከት ለወላጆችም ለልጆችም የሚሆን ሲሆን በመጪው ትውልድ ላይም አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚያመጣ ይሆናል። ይህም እግዚአብሔር በትእዛዙ የሚሰጠው ተስፋ ነው። እርሱም ለሚወዱትና ትእዛዙንም ለሚጠብቁ ለብዙ ሺህ ትውልድ

ምሕረትን የሚያደርግ አምላክ ነው የሚል ነው።

### ልጆች የሌላቸው ወይም ሳያገቡ የሚኖሩ ወንዶች ወይም ሴቶችስ እንዴት ናቸው?

በአንዳንድ ባህሎች አመለካከት አንድ ሰው እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ አለማግባቱ እንደ ውርደት ይቆጠርበታል። ይህ ግን ፈጽሞ ስሕተት ነው። እግዚአብሔር የበላይ ገዥ መሆኑን የምናምን ከሆነ እርሱ ሕይወታችንን በሙሉ ሲገዛና ሁሉም ነገር «ለበጎ እንደሚደረግ» መቀበል አለብን (ሮሜ 8+28)።

ስለዚህ ወንድ ወይም ሴት ሁሉ ማግባትና ልጅ መውለድ አለበት ብሎ ማሰብ ስሕተት ነው። በመጀመሪያ ብዙ የተጋቡ ባለ ትዳሮች በጋብቻቸው ውስጥ ልጅ ላይኖራቸው ይችላል። ልጅ ባይኖራቸውም ጋብቻቸው ለራሳቸውና ለሌሎች ብዙ ሰዎች በረከት ሊሆን ይችላል። በሌላው በኩል ደግሞ ልጆቻቸው ያስታጉ በሚገባ መንገድ የሚያድጉ በመሆናቸው በጉዘን በመመታት ልጅ ባልወለዱን ብሰው የሚጸጸቱ አሉ። ስለዚህ ብዙዎች እንደሚያምኑት

ልጅ መውለድ ትልቅ ደስታን ይሰጣል ብሎ ሁልጊዜ መናገር አይቻልም ብሎ መደምደም ይቻላል። ይልቁንም አንዳንድ ጊዜ ትልቅ ፈተና ነው።

ልጅ ስለማይወለድበት ጋብቻ አንድ ለማየት የማይቻል ወይም የማይታወቅ ነገር አለ። ይኸውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወደር የለሽ የልጆችና የወጣቶች አገልግሎት የሚሰጡ ብዙ መሪዎች መኖራቸው ሲሆን ከእነርሱም ብዙዎች ያላገቡና የራሳቸው ልጆች የሌላቸው መሆናቸው ነው። በትንሹ ቤታቸው አገልግሎት የመስጠት እድል ያላገኙ ሆነው ሳሉ በልጆችና በወጣቶች መካከል እንዲህ ያለ አገልግሎት ሲሰጡ የቻሉት ለምንድን ነው? ይህ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ትልቅ ምስጢር ነው። ይህን አሳብ ትንሽ እናብራራው። እንደዚህ ያሉ ሰዎች በራሳቸው ልጆች ፍቅር ምትክ የተለየ የአገልግሎት ስጦታ አግኝተዋል፤ ለሌሎች ሰዎች ልጆችና ወጣቶች የላቀ ፍቅር ይኖራቸዋል። ይህም በሕይወታቸውና በቤታቸው ባላገኙት ነገር ምትክ እግዚአብሔር ለእነርሱ የሚያደርገው ማካካሻ ነው።

የማያገቡትን ሰዎች አስመልክቶ ብዙ አነስተኛ ግምት የሚሰጣቸው ወይም የማይታወቁ ክርክሮች አሉ። ይኸውም ሆነ ብለው ላለማግባት የሚወስኑ ወይም አለማግባት የእግዚአብሔር ጥሪ ነው ብለው የሚያስቡ ሰዎች መኖራቸው ነው። እነዚህ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ጥቂትም ይሁኑ ብዙ ሌሎችን ሰዎች ወይም ማኅበረሰብን፤ ወይም መንፈሳዊ ወይም ምድራዊ ድርጅቶችን ለማገልገል የመረጡ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ የተነሣ ቤተ ሰብ ወይም ልጆች ይህንን አገልግሎት ከማከናወን ያሰናክሉኛል ብለው ያስባሉ። ይህንን መንገድ የመረጡ በመቶዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች እንዳሉ ከታሪክ መጥቀስ እንችላለን።

እዚህ የተጠቀሰውን ምሳሌ የጸጋ ስጦታ የተለያየ ነው ከሚለው ቃል ማሳየት ይቻላል። ይህንንም የሚያደርገው ደግሞ ለእያንዳንዱ ጸጋውን እንደ ፈቃዱ እያካፈለ የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው።

ከፍቅርና ከቤተ ሰብ ጋር ተያይዘው ካሉት ችግሮች አንዱ.

ለብዙ ባለትዳሮች ኀዘን ምክንያት የሚሆን አንድ ትልቅ ችግር አይተናል፡፡ እርሱም በጋብቻቸው ውስጥ ልጅ አለመውለድ ነው፡፡ እንዲሁህ ያሉ ጥንዶች የሚስማሙአቸውን ትናንሽ ልጆች ለማግኘት ወደ ሩቅ አገሮች ይጓዛሉ፡፡ አስገራሚ እውነታ ግን በማደጎ ከሚሰጡት ልጆች ይልቅ ተጥሪቻቸው የሚበዛ ገና ያልተወለዱ ሕጻናት በውርጃ መልክ መሞታቸው ነው፡፡

በየጎመሩ ቀጥሮራቸው ብዙ የሆነ ውርጃዎች መከሰታቸው ከብዙ የከፋ የዓለም ችግሮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህም በሚከተሉ ብዙ ምክንያቶች ይከሰታል፡፡ ይኸውም ፍቅርና ወሲብ የሚታዩት አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለአዲሱ ሕይወት ኃላፊነት

እንዳይኖራቸው ተደርገው ነው፡፡ ስለዚህ ማስወረድ እንደቀየ የጽንስ መከላከያ ተደርጎ ነው፡፡ ለውርጃ ‹‹ሌላ ልጅ ማሳደግ አንችልም የሚል የኢኮኖሚ ምክንያት ይሰጠዋል፡፡ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ውድ የሆኑ ቤቶችን መግዛትና ብዙ ወጪ የሚጠይቁ የእረፍት ጉዞዎችን ማድረግ እየቻሉ ሌላ ልጅ ማሳደግ አንችልም ማለታቸው በቂ ምክንያት አይደለም፡፡

ብዙ ኃላፊነት የጎደለው ‹‹የሕጋዊ ውርጃ›› አራማጆች እስከ አሁን መመለስ ያልቻሉት ጥያቄ አለ፡፡ እርሱም ‹‹እርስ በእርስ የሚዋደዱ አንድ ወንድና አንዲት ሴት የፍቅራቸው ውጤት የሆነውንና በማኅፀን ውስጥ በመጀመሪያ ሕይወት የዘሩበትን ነፍስ እንዴት ያጠፋሉ?›› የሚል ነው፡፡

የዓለም ማኅበረሰብ ወደ አእምሮው ተመልሶ ይህንን ጉዳይ እንደገና ማሰላሰል ይጠበቅበታል፡፡ ሁሉን አቀፍ የሆነችው ቤተ ክርስቲያንም ይህንን አሳብ ለማንቀሳቀስ የነቢይነት ድምጿን ማሰማት ይጠበቅባታል፡፡

# ምዕራፍ 11

# ሥልጣንና ፍትህ

## «ሥልጣን» ማለት ምን ማለት ነው?

አንድ ማኅበረሰብ ጥቅሙንና ሥራውን ለማስከበር አንድ ዓይነት ሥልጣን ያስፈልገዋል በማለት ብዙ ሰዎች ያሳስባሉ። እንዲህ ዓይነቱ ሥልጣን ለመሪዎችና ለባለሥልጣናት በሚሰጣቸው ጊዜም የራሳቸውን የግል ጥቅም እንዲጠብቁ ለእነርሱ ለማመቻቸት አይደለም። ባለሥልጣናት የግል ጥቅማቸውን የሚያሳድዱ ከሆነ ኅብረተሰቡ ምንም አይጠቀምም። ይልቁንም መሪዎችና ባለሥልጣናቱ ሥልጣኖቻቸውን ለአንድ ዓላማ ማዋል አለባቸው። [illegible]

[illegible] ሊባል ችግሮችን መቋቋምና መፍትሔ መፈለግ መሆን አለበት።

በአንድ ኅብረተሰብና በባለሥልጣኑ እጅ ያለው «ሥልጣን» ከአገር ወደ አገር ሊለያይ ይችላል። እርሱን በዚህ ቦታ በዝርዝር ማስቀመጥ አስፈላጊ አይደለም። ይሁን እንጂ የፖሊስ ኃይሉንና ፍርድ ቤቶችን እንደ ምሳሌ መጥቀሱ በቂ ነው። እነዚህ አካላት አንዳንድ ፓርቲዎች እንደሚያደርጉት የራሳቸውን ጥቅም ማስጠበቅ ሥራቸው አይደለም። የተወሰኑ አካላት የራሳቸውን ጥቅም የሚያስጠብቁበት አንዱ መንገድ ገንዘብና ጊዜን ለባለሥልጣናቱና ለሠራተኞች ጥቅም ብቻ በሚያውሉበት ጊዜ ነው። የተሰጣቸው ሥልጣን፣ ገንዘብና ሠራተኞቹ ኅብረተሰቡንና አባላቱን ለማገልገል ነው። በዚህ አገልግሎት ውስጥ መንግሥት፣ ሚኒስትሮች፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ ኃላፊዎችና የመሳሰሉት አገልጋዮች የሚሰጡ መሣሪያዎች ብቻ ናቸው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ሥልጣን የሚለው ቃል አሻሚ ነው። ለብዙ ሰዎች ሥልጣን በኅብረተሰቡ ድርጅቶችና ባለሥልጣናት

እንዲሁም በከሚኒሽነሮች፣ በፍርድ ቤትና በመሳሰሉት ሥራዎች ውስጥ በግልጽ የሚታየው ነው። አሁን ለምንነጋገርበት ርእስ ዓላማ ግን ሥልጣን የሚለው ቃል ሌላ ትርጉም ያለው ሲሆን እርሱም ከተቋማትና ከባለሥልጣናት በስተጀርባ ስላለው ሥልጣን ይሆናል። ይህ ሥልጣን ከሚታዩት ሥልጣናት፣ የሥራ ክፍሎችና መሪዎቻቸው እንዲሁም ከፍርድ ቤቶች ጀርባ ያለው ሥልጣን ነው። ከዚህም ቀጥሎ ይህ ከሥልጣን በስተጀርባ ያለው ሥልጣን ከየት ይመነጫል የሚለው ጥያቄ ነው። ይህ አስተሳሰቦች የሚለያዩበት ቦታ ነው። የሊበራሊስና የሶሺያሊስቶች አስተምህሮዎች ብዙ ክርክር የሚያደርጉበትም መነሻ ነጥብ ነው።

## መለኮታዊው መሰመር

[illegible]

እምነትና ልማዳዊ ሃይማኖትን ጨምሮ ክርስቲያን ባልሆኑ እምነቶች መካከል ተመሳሳይነት መኖሩ አስገራሚ ነው። ሬጅም እድሜ ካላቸው «ቀይ ሕንዶች» ይልቅ ለተፈጥሮና ለአካባቢ ጥልቅ ስሜት ያለውን ሕዝብ ማግኘት አስቸጋሪ ነው። እነዚህ ሕንዶች ቀጣይ ለሆነ የእንስሳት፣ የዛፎችና የአጽዋት ደኅንነት ኃላፊነት እንዳለባቸው ይቆጥሩ ነበር። ይህንንም ያሚያደርጉት «ለተፈጥሮ» «ለቅድመ አያቶችና» «ለታላቁ መንፈስ» ተጠያቂነት እንዳለባቸው ይገነዘቡ ስለ ነበረ ነው። ይህ በበኩሉ ተፈጥሮ ላይ ካላቸው ጥልቅ እምነትና ለእርሱም ያላቸውን ኃላፊነት ከመቀበላቸው የተነሣ ነው። በተቃራኒው በኩል ደግሞ ፈጣሪ መኖሩን የሚክዱ አስተሳሰብ እንመልከት። የዚህ አሳብ አራማጆች «ዝግመታዊ ለውጥ» ወይም «በአጋጣሚ የመጣ» የሚል አሳብ ያላቸው ወይም ለፍጥረተ ዓለም የመሰላቸውን ቦታ የሚሰጡ ክፍሎች ናቸው። እነዚህ ክፍሎች በማንም ፊት የባለአደራነት ተጠያቂነት እንደሌለባቸው የሚያምኑ ናቸው፣ (ሉቃስ 16፥2)። እንደዚሁ አሳብ አራማጆች ተጠያቂነት የሚመጣው «ከእግዚአብሔር ምክንያት»፣ «ድምፅ ከሚለባቸው

ሕዝብ ይሁንታ››፣ ‹‹የበራ አእምሮ ካላቸው መሪዎች›› ወይም አእምሮአቸው ከሚያመነጨው ማንኛውም አስተሳሰብ ብቻ ነው።

እነዚህ አስተሳሰቦች የሚያነሡት ጉዳይ ትልቅ ነው። ይኸውም ለአጭር ጊዜ ብቻ ሳይሆን ለቀናትና ለዓመታት ለኅብረተሰቡ ጥቅምና ደኅንነት የሚሆነው ነገር እንዴት ይመሠረታል? የሚለው ነው። ይህ ማለት አንድ ኅብረተሰብ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ፣ በታማኝነት፣ በትሕትና ከሁሉም በላይ ደግሞ በኃላፊነት እንዴት ይመራል የሚለው ጥያቄ ነው። ኃላፊነት የሚለው አሳብ የኅብረተሰቡ ሕይወት የሚያጠነጥንበት ማጠንጠኛ ዛቢያ ነው።

ኃላፊነት! ግን የማን?

መልሱ በመጀመሪያ የራሱ የሕዝቡ እና የመላው ኅብረተሰብ ነው። ስለዚህ እናንተ ትጸማውያን ገበሬዎች ‹‹ራሳችሁን

አታስጨንቁ››፣ የራሳቸው ነገር ብቻ ግድ የሚላቸውን መሪዎች ዓለም ተደፋ ብላ አስተናግዳለች፣ ይህ ይብቃ! ስለዚህ እነዚህ ‹‹በሥልጣን ላይ ያሉ›› በእውነት መልካምና ብቃት ያላቸው ከሆኑ ለዲሞክራሲያዊነት ሥልጣን መጋደል የለባቸውም። መታወቅ ያለበት ነገር እነርሱ ሰዎችና የሚሳሳቱ፣ ድካምም ያለባቸው ናቸው። ይልቁንም መልካም መስለው በሚታይ መንገድ ሁሉ ለሕዝባቸውና ከሕዝባቸው ጋር መሥራት የሚገባቸው ሲሆን በማያመጡት ውጤትና በሚታይባቸው ውድቀቶች ኃላፊነትን መውሰድ አለባቸው። መተማመንም የሚፈጠረው በዚህ ዓይነት መንገድ ነው። በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ሕዝባቸውን በዚህ ዓይነት መንገድ በሚያገለግሉበት ጊዜ ፈጣሪአቸውንም ያገለግላሉ። እነዚህ ሰዎች አማኞች፣ የማያምኑና እግዚአብሔርን የሚክዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ የራሳቸውን ስሜትና ሕሊና በመከተል የእግዚአብሔርን ዓላማ ያገለግላሉ። የሌሎች ሃይማኖት መሪዎችም ቢሆኑ ትክክለኛ የኃላፊነት ስሜት ካለ እንደ አገልጋዮቻቸው የጋራ ጥቅምን የሚያስገኝ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል አመራር የግል ጥቅም ለማግበስበስ ወይም ዘመዶችን፣ ወዳጆችን፣ የራስ

ቡድንን ወይም ፓርቲን ለመጥቀም ወይም «የራሱን ሥልጣን ለማስጠበቅ» ከሆነ አመራሩ በጣም መጥፎ ይሆናል። አመራሩ «በደመነፍስ»፣ «በመልካም አጋጣሚ» እና «ዕድገት በሚፈልጉ ኃይሎች» ሲጠየቅ የሚከናወን ከሆነ «ኃላፊነት» «አጋጣሚ» ወይም «መልካም ዕድል» ለሚሉት አሳቦች በፍሬን ይሰጣል።

## ሕግና ፍትህ

የንስማዊው ኅብረተሰብ ባለሥልጣናት ሥራቸውን በሚሠሩበት ጊዜ ሁለት መሪ የሆኑ መርሆዎችን መጠበቅ አለባቸው። እነርሱም ፍትህና የኅብረተሰቡ ዋስትና ናቸው። እነዚህ መርሆዎች እርስ በርሳቸው የተጋመዱና አብረው የሚሄዱ ናቸው። አንዱ ያለ ሌላው ሊኖር አይችልም። ስለዚህ የኅብረተሰቡ ዋስትና ያለ ፍትህ ሊገኝ የማይችል ሲሆን ፍትህ በበኩሉ

ለኅብረተሰቡ ዋስትና በሚያመቻች መልኩ ሊመራ እንዲሁም ኅብረተሰቡን በመቆጣጠር ማንኛውንም ኃይልን ሕገወጥ እንዳይሆን ማቆም ይኖርበታል። ፍትህ በማንኛውም መልኩ ምክንያት አልባና በማን አለብኝነት፣ በበላይነት መንፈስ ሊመራ አይገባም። የማን አለብኝነት መንፈስ ፊቱን ሲገልጥም በአገልጋይነት መንፈስና በእውነተኛ የሕዝባዊነት ስሜት መታረም አለበት።

ይህ ሁሉ ምክንያታዊ ሆኖ እንዲህ ብለን እንድናስብ ሊያደርገን ይገባል። ለመሆኑ ፍትህ ከየት ይመጣል? በተለይ የፍትህን ሥራ ለመምራት ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች «ትክክለኛ» የሆነውን ነገር እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? የመንግሥት ሚኒስትሮች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ኮሚሽነሮች፣ አቃቤያነ ሕግ ወይም ዳኞች ሁሉ የሚያምኑ ክርስቲያኖች መሆን አለባቸው ብለን እንደማናስብ መስማማት አለብን። የምንኖርበት ምድራዊውን ኅብረተሰብ አስመልክቶ እስከ ሆነ ድረስ በሕግ ሥራ ላይ የተሠማሩት ሁሉ አማኝ ክርስቲያን መሆን አለባቸው ብሎን ማሰብ አስፈላጊም አይደለም። «ሕግ የሚያዘው ነገር በልባቸው

ሲተፈጠረው ዓለም አስተደምሞውት ጥንቃቄ አድርጎአል። ሰዎች በእግዚአብሔር ቢያምኑም ባያምኑም የዓለማቱውን ኅብረተሰብ ጉዳይ በሚመለከት በሰው ልብ ውስጥ የሚሠራው የሕግ ሥራ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ስለሆነም በብዙ አገሮች ውስጥ እንደሚታየው ዓለማቀፉ ሕግ መልክም በሆነበት ሁኔታ፣ ባለ ሥልጣናት ሥራቸውን በተቀመጠው ሕግ፣ በሕሊናቸውና ከላይ በተቀመጡት ሁለት መርሆዎች ላይ ተንተርሰው እስከ ሠሩ ድረስ ሰዎች ሥራቸውን የሚያከናውኑት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እንዲህም እስከ ሆነ ድረስ ሰዎች በልባቸው የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ሕግ ይከተላሉ። ይህ ለአማኞችም ለማያምኑም በሚሆን መንገድ ሕጉን ተግባራዊ ማድረግ ነው። ይህንን አስመልክቶ ምንም የሚጋጭ አመለካከት ሊኖር አይገባም። ከዚህ አኳያ የኅብረተሰቡ መሪዎችና ዳኞች፣ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች ሁሉ የእምነት አቋማቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ ሊከበሩና [illegible]

[illegible] ሥልጣን ግዞት ውስጥ ሳያስገቡ ሁሉንም ጉዳይ በትክክለኛና እውነተኛ መንገድ ለመያዝ፣ እውነተኛው ነገር እውነተኛ ሆኖ እንዲቀር፣ ዳኞች ጥቁሩን ወደ ነጭ፣ ስሕተትን ወደ ትክክል በመለወጥ ቁንጮዎቹ ጥበቦቻቸውን ተጠቅመው ፍትህ እንዲጣመም ለማድረግ ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል» (ጉልቁ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ)። ማርቲን ሉተር በዚህ ቦታ የተናገረው ነገር ዳኞችን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ሌሎች እንዲሁም፣ እንደዚሁ እና በኅብረተሰቡ መካከል አገልግሎት እንዲሰጡ የተሾሙትን ሁሉ የሚመለከት ተመሳሳይ መንፈሳዊ ሥልጣን ነው።

## ሥልጣን የሚያስፈልግበት ሁኔታ

«ባለ ሥልጣናት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችላቸው የሚታይ ሥልጣን ያስፈልጋቸዋል» የሚለውን አነጋገር የሚቃወሙ አንዳንድ አስተሳሰቦች መኖራቸው ለብዙዎች አስገራሚ ሊሆን ይችላል። ይህንን አስተሳሰብ ለመቃወም የፖሊስና የመከላከያ ኃይሎች መኖር እንደ ዓይነት የሕዝብ አመፅ መኖሩን

ያመለክታል እስከ ማለት ጥግ ሄደዋል። አስተሳሰባቸውም የእነዚህ ኃይሎች መኖር የሕዝብን ቁጣ ያቀሰቅሳል በሚለው ክርክር ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ አስተሳሰባቸው በአንዳንድ ጽሑፎች ላይ እንኳ በተጨባጭ እውነት ላይ የተመሠረተ አይደለም። እንደዚህ ያለው አመለካከት በውሸት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ለማረጋገጥ ሁለት እውነታዎችን እንመልከት። የመጀመሪያው እውነታ የምንኖረው በምናባዊ ወይም በሕልም ዓለም ሳይሆን በተጨባጩ ዓለም ውስጥ መሆኑ ነው። በዚህ በተጨባጩ ዓለም ውስጥ የፖሊስ ወይም የመከላከያ ኃይል ኖረም አልኖረ ብዙ ክፉ ነገሮች አሉ። ሁለተኛ የሚሰረቅ ገንዘብ ወይም ንብረት ያላቸው በግልጽ የሚታዩና ያልተወሳሰቡ ማኅበረሰቦች አሉ። እንደዚህ ያሉ ማኅበረሰቦች ቋሚ ጠባቂ የሌላቸው ቢሆን እንኳ ያላቸውን ንብረት ለማስጠበቅ በተፈለገ ጊዜ የሚመጡ ጠባቂዎችን ሊጠሩ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነት ምሳሌ በምናነሳበት ጊዜ ጥበቃ አያስፈልገኝም ብሎ

የሚያስብ ማኅበረሰብ ካለ አስገራሚ ይሆናል። ወይም የጠባቂ መኖር ስርቆሽን ወይም ድብደባና ዝርፊያን ያነሣሣል የሚለው አስተሳሰብ አስገራሚ ሊሆን ይችላል።

ችግሩ ሌላም ጎን አለው። ይኸውም አንድ ሰው እንዲከፍል የሚፈለግበትን ግብር አልከፍልም ቢል «በቃ ይኸው ነው፤ ይህ ሰው አልከፍልም ካለ ምንም ማድረግ አልችልም» ብሎ እጁን የሚሰበስብ የማኅበረሰብ መሪ ማን ነው? ምናልባት እንደዚህ ያለ መሪ ላይኖር ይችላል። ካለ እርሱ የሚኖረው በምናብ ዓለም ብቻ ይሆናል። እንግዲህ እውነታው ሁሉም የማኅበረሰብ መሪ በመጀመሪያ የሚታይ ሥልጣን ወይም የሚታወቅ ሥልጣን፣ ሁለተኛ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ተግባራዊ የሚያደርግ ሥልጣን ያስፈልገዋል የሚል ነው። ይህ በሁሉም የዓለም ክፍል የሚታይ እውነታ ሲሆን ይህንን እውነታ የማይቀበሉና ሊረዱት የማይፈልጉ ጥቂት ሀሳባውያን አሉ።

የሚታወቅ ውጫዊ ሥልጣን የሌለው መንግሥት ወይም [illegible] ይሆናል። [illegible]

ለማስጠበቅ ያገለግላል። የሚታይ ውጫዊ ሥልጣን የሌለው መንግሥት አቅመ ደካማ ብቻ ሳይሆን ጥሉ ብሎም ወደ ሥርዓት አልበኝነት ይለወጣል። ስለተጻፈ ሕግ ሕዝቡ እስካልታዘዘው በሌላ ባለ ሥልጣናቱ ለማስፈጸም ኃይል ባይኖራቸው ሕጉ በወረቀት ላይ ብቻ ሰፍሮ ያለ ይሆናል፤ ምን ሊረዳ ይችላል? እንዲህ ሲሆን ማኅበረሰቡ ምንም ዳኛ ባልነበረበት የጥንቱ እስራኤል «ሁሉም ሰው በዓይኑ ፊት መልካም የመሰለውን ያደርግ» እንደነበረበት ዘመን ይሆናል (መሳ. 17፥6)።

ነገር ግን ፍትህ በሚፈለግበት ሁኔታ ውስጥ ብዙ እድሎች ይኖራሉ። በሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ሥልጣንን ያለ አግባብ የሚጠቀሙበት ከሆነ ምንም ሕግ በራሱ ዋስትና ሊሆን አይችልም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሁሉም ሰው የሚተማመነው በሕዝብ መንፈስ ውስጥ ባለው ግብረ ገብ ወይም ሞራል ብቻ ይሆናል። ሥልጣንን በአግባቡ [illegible]

ለማሳደግ ሦስት መንገዶች አሉ። በመጀመሪያ ነቶቹ የመጠበቅ መንፈስ በሕዝቡ ዘንድ መኖር አለበት። እንዲህ ያለ ንቃት ካለ ቢያንስ ከመንግሥት ባለሥልጣናት መካከል አንዱ የማስጠንቀቂያ ደወል ሊያሰማ ይችላል። ሁለተኛ እየተበላሸ የሚሄድ ፍትህ ሲኖር ሕዝቡ የተበላሸውን ነገር ለይቶ እንዲያውቅ ትምህርትና ሥልጣን ያስፈልገዋል። ሦስተኛ ፍትህ አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ፍትህን ለመጠበቅ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ዜጎች ብቻ ሳይሆኑ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጡ የማኅበረሰቡ አገልጋዮች ሁሉ የነቢይነት ድምፃቸውን ለማሰማት ዝግጁ መሆን አለባቸው። በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ የቤተ ክርስቲያን እረኞች «ዕውሮችና «የማያውቁ ውሾች» ኢሳ. 56፥10 ከሆኑ ለአገር ወዮላት።

## ቤተ ክርስቲያንና ፍትህ

ቤተ ክርስቲያንና ዓለማዊው አስተዳደር አንድ የጋራ ጥሪት ያላቸው ሲሆን እርሱም ሕግን መጠበቅ እንደሆነ ቀደም ተብሎ ተጠቅሷል (ገጽ 37)። ይህ እግዚአብሔር የተፈጠረውን

ዓለም በሥርዓት ለማስኬድና ለክፋ ነገር ቦታ ፈጽሞ እንዳይሰጥ የሚጠብቅበት የጥበቃ ሥራው ነው። ስለዚህ የዓለማዊው አስተዳደር ባለሥልጣናት ጥሩ ሕግ እንዲያወጡ፤ እንዲጠብቁና ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለመርዳት ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት አለባት። ሕጉን ተግባራዊ ወደ ማድረግ ስንመጣ ግን ቤተ ክርስቲያን ድምጿን ለማሰማት ካልሆነ በቀር ሥራው ሙሉ ለሙሉ የዓለማዊው አስተዳደር ድርሻ መሆን አለበት። (አባሪ ገጽ 37 ተመልከት)

ቤተ ክርስቲያን የነቢይነት ድምጿን በሚቃረን መንገድ በማንሳት በዚህ አሳብ ላይ ድክመት የምታሳይ መሆኗ አስገራሚ ነው። ይህም የሚሆነው ሰዎች ግልጽ በሆነ መንገድ ሥልጣንን ያለ አግባብ ሲጠቀሙበት አይታ በዝምታ በምታልፍበት ጊዜ ነው። ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ጊዜ ጣልቃ በመግባት ፖሊስና ፍርድ ቤቶች ሥራቸውን እንዳያከናውኑ እንቅፋት የምትፈጥርበት

ሁኔታ አለ።

ከላይ ያልነው ሳይሆን ቀርቶ የፍትህ አካሄዱ፤ የፍርድ አወሳሰኑ፤ ተመሳሳይ ጉዳዮች በተለያየ መንገድ መዳኘታቸው፤ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ አንድን ሰው ለመጥቀም ሆን ተብሎ ፍትህ ሲጣመም ስሕተት መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ባለ ሥልጣናት አመለከቱ እንበል። ይህ ሁሉ «ፍርድንና ጽድቅን አድርጉ፤ የተበዘበዘውንም ከአስጨናቂው እጅ አድኑ፤ መጻተኛውንና ድሃ አደጉን መበለቲቱንም አትበድሉ፤ አታግፉአቸውም፤ በዚህም ስፍራ ንጹሕ ደምን አታፍስሱ» የሚለው ቃል በቤተ ክርስቲያን የነቢይነት ሥልጣን ሥር ይወድቃል። በጥንታዊው የእስራኤል ነቢያት በየትኛውም ዘመን የሚጠቅመውን መልእክታቸውን ምሳሌ ይሰጡናል። አሞጽ ከእነዚህ ነቢያት አንዱ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ግን የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ግልጽ በሆነ መንገድ ለሕግ ተጠያቂዎች ወይም ከሳሾች በመሟገት በፖሊስ፤ በፍርድ ቤት ወይ በሌሎች ባለሥልጣናት ሥራ ውስጥ ጣልቃ

ሲገዙ ማየት አስገራሚ ነገር ነው፡፡ በእርግጥ እንዲህ ባለ ነገር ለምሳሌ በተከሳሾች ላይ ሕገወጥ እያያዝ ሲፈጸምባቸው ጣልቃ መግባት ትክክለኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በተከሳሾች ላይ የሚደረገው የክስ ሂደት በሕግ መሠረት በትክክለኛና ሰብዓዊነትን በሚያከብር መንገድ ከሆነ ጣልቃ መግባት ስሕተት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በብዙ አገሮች እንደዚህ ያለ ጣልቃ መግባት በተደጋጋሚ የሚታይ ነው፡፡ እንደዚሁም ክርስቲያኖች አደባባይ በመውጣት «ከፍትህ ይልቅ ለፍቅር» «ከከባድ ቅጣት ይልቅ ቀለል ያለ ፍርድ» እንዲሰጥ ጣልቃ ሲገቡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የፈለጉትን ለማግኘት ረብሻና ብጥብጥ ሲያነሱ ይታያል፡፡ ሌላው አስቸጋሪ ነገር ደግሞ «ፍቅር» ወይም «የይቅርታ ፍቅር» የሚጠየቀው በተመሳሳይ ጉዳይ ወንጀል ለሚገኙት ሰለባዎች ሁሉ ሳይሆን ለተለዩ ሰዎች ሆኖ መገኘቱ ነው፡፡ እዚህ ላይ ማስገንዘብ የምንፈልገው የቤተ ክርስቲያን ተወካዮች በግልም ሆነ በጋራ ነገሮችን ጥበብ በጎደለው መንገድ የሚያከናውኑ ከሆነ

[illegible] የሚፈጥሩ መሆናቸውን ነው፡፡ የክርስቲያኖችን ድምፅ ማሰማት ጥበብ ከጎደለውና ጥበቡና ከሌለው ጣልቃ ገብነት ጋር መደበላለቅ የሌለበት ሲሆን ፍትሃዊ የዳኝነትና ሕጋዊነት ያላቸውን የንሰማዊ አስተዳደሮችን ሥራ ማወክ የለበትም፡፡

ይህ ጉዳይ ሌላም ገጽታም አለው፡፡ ይኸውም «ወንጀሉ ከባድ ሆኖ ሳለ ቀለል ያለ ፍርድ ወይም ምሕረት የሚሰጥበት ሁኔታ» ሲኖር ጣልቃ መግባት ነው፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ሲሆን የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ይህንን ነገር ለማመልከት ጣልቃ መግባት የለባቸውም፡፡ ይህ ሥራ መመልከት ይልቁኑ የጠበቃውና የፍርድ ቤት ሰዎች ድርሻ ነው፡፡ በጥንቃቄ የተዘጋጁ ሕጎች ይህንን ጉዳይ የሚመለከት አንቀጽ አላቸው፡፡ ይህንን ጉዳይ የሚመለከቱ አንቀጾች በሕጉ ውስጥ ካልተካተቱ ጉዳዩ በሕግ አንቀጾች ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ንቃቱ ያላቸው ሰዎች ድርሻ ይሆናል፡፡ ስለዚህ እንዲህ ያሉትን ጉዳዮች አስመልክቶ በተደጋጋሚ ተቃውሞ ከማቅረብ ይልቅ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልና ጥበብ ያለበት

ሕግ እንዲኖር ከዋናዎቹ የፍትህ አካላት ጋር ተባብሮ መሥራት እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን ለተከሳሹም ሆነ ለተበዳዩ በሚጠቅም መልኩ ሕጉ እንዲሻሻል መሥራት ያስፈልጋል። እንዲሁም ለፍትህ ሥራ አካሄድ በየጊዜው ጣልቃ ከመግባት ይልቅ ለጋራ ዋስትና እንደዚሁም ተከሳሹ እንደገና የሚታደስበትን መንገድ ለመፈለግ አብሮ መሥራት አስፈላጊ ነው። ስለ አስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ግራ መጋባትን ያፈጥርና የቤተ ክርስቲያንን፣ የፍትህ አካላትን ክብር ዝቅ ያደርጋል።

## የፍትህ ሥርዓት ፍተሻ

የፍትህ ሥራ የሚፈተሸው በመጀመሪያ በፖሊስና በአቃቤ ሕግ ቅድመ ሥራዎች፣ ቀጥሎ በዳኞቹና ጉዳዩን በሚያመዛዝኑ ሰዎች በፍርድ ቤት በሚሠሩ የማጠቃለያ ሥራዎች ነው። በእነዚህም ነገሮች መሠረት ማኅበረሰቡ ጠንካራ ወይም ደካማ

[illegible] የሌለው መሆኑ ይፈተሻል። «የግንዛቤው» በቃላት ሳይሆን በመረጃ ላይ በተመሠረተ፣ ጥበብና ፍትህ ባለው አሠራር ይገለጻል። በነዚህ ነገሮች ላይ ሲኖር የሚገባው ጥበብ ሕግ የተከተለና ሁኔታዎችን በሚገባ ያገናዘበ መሆን አለበት። የጎለኛው አካሄድ ሕግን ማጣመም ወይም ማፋለስ ሳይሆን ሕግን የተከተለና በሁሉም አገሮች ተቀባይነት ያለውና «የመሠረታዊነትን» ምልክት የሚያሳይ አካሄድ ነው። የዓለም ማኅበረሰብ የእድገትና የሥነ ምግባር አቋም በነዚህ ነገሮች ቢፈተሽ በተወሰነ ደረጃ ሊረጋገጥ ይችላል። ዓለማዊው ማኅበረሰብ እንዲህ ወዳለ አቋም እንዲደርስ ክርስቲያኖች ሁሉና ቤተ ክርስቲያን መርዳት ግዴታቸው አድርገው ሊሰሩት ይገባል። ይህ አቋም ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ለሁሉም ሰው የምታስተምረው የሥነ ምግባር ክፍል ነው።

## ፍትህና ቅጣት

በእስረኞች የተፈጸሙባቸው፣ ምንም ብርሃን የሚያስገኙና

ጤና የሚጎድላቸው እስር ክፍሎች፣ ለታሣሪዎች ምንም ጥንቃቄ የማይደረግባቸውና የእስረኛው አካልና አእምሮ ቀስ በቀስ እየተጎዳ የሚሄድባቸው አሮጌው ዓይነት እስር ቤቶች እስከ ዛሬም ድረስ በአንዳንድ አገሮች ይገኛሉ። እስራትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በሙሉ በሕግ ገደብ ስለተደረገባቸው እንደዚህ ያለ እስራት በብዙ አገሮች ተከልክሎአል። እስር ቤቶች በቂ ቦታ ያላቸውና በጥሩ ሁኔታ በዕቃ የተደራጁ፣ ሰውነት የሚገነባ ምግብ የሚቀርብባቸው፣ ንጽሕናቸው የተጠበቀ፣ መዝናኛና ጠያቂ የሚጎበኝበት ሁኔታ የተመቻቸላቸው መሆን አለባቸው። እንደዚህ ዓይነት እንክብካቤ ባለበትም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ሁሉም እስረኞች የሚፈተሹበትና የእስራት ጊዜአቸው የሚቀንስበት ወይ የሚረዝምበት ጊዜ መኖር አለበት።

ሰዎች በእስር ቤት እንዲቆዩ የሚደረግበት ምክንያት ምንድን ነው? በዚህ ዝርዝር ውስጥ በሕግ ላይ የተመሠረተ አካሄድ እንከተላለን ለሚሉት መንግሥታት ከባድ በመሆኑ በሥልጣን ላይ ያሉ ባለሥልጣናት ተቃዋሚዎቻቸውን በእስር ቤት የሚያቆዩበትን ሁኔታ አናነሳም። ይልቁንም ሕግና ፍትህ የሚተገበርበትን ቦታ እንመልከት። እንደዚህ ያለ አሠራር ባለበት አገር የእስራት ምክንያት ዜጎችን ለመበቀል ሊሆን አይችልም። ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች ሁለት ናቸው። የመጀመሪያው የሕግ ዓለማ በፍርድ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ተቀባይነት ባላቸውና በሌላቸው ጉዳዮች መካከል ድንበር ለይቶ ማስቀመጥ መሆን አለበት። ከሰው ልጅ የጥንት ዘመን ጀምሮ ይህንን ማድረግ ይፈቀድልሃል፣ ያንን ማደረግ አይፈቀድልህም ብሎ ለሰዎች በቃል ብቻ መንገር በቂ ሆኖ አልተገኘም። በውስጣዊ ደመ ነፍሳችን ምክንያት ስሕተትን ለማድረግ ስለምንፈተን አንዳንድ ጊዜ ቃላት ከሚያስተላልፉልን መልእክት የጠነከረ ቃል ያስፈልገናል። በፍርድ ቤት የሚተላለፉ ውሳኔዎች በስሕተትና በትክክለኛ ነገር መካከል ድንበር የማድረጊያ መንገዶች ናቸው። ሁለተኛው የእስራት ምክንያት ወንጀል አድራጊው ከስሕተቱ የሚታረምበትን መንገድ መፈለግ ነው። ይህም ማለት አሳቡንና መንገዱን እንዲለውጥ

ማለት ነው። ሁለቱም ምክንያቶች በአንድ ማኅበረሰብ ጥረት ውስጥ የሚደባለቁ ናቸው።

በሕግ በሚሠራ አገር ሁሉም የፍርድ ቤት ክስ በሦስት መንገዶች መፍትሔ ያገኛል። ሦስቱ የመፍትሔ መንገዶች የሙታይ ጊዜ፣ የቅጣት ጊዜና የእስራት ጊዜ ናቸው። የሙታይ ጊዜ ማለት ቃሉ እንደሚያስረዳው የመፈተኛ ጊዜ ማለት ነው። የሙታይ ጊዜ የተጣለበት ሰው ጊዜውን በአግባቡ ከተጠቀመበት እስራት አይከተለውም። የሙታይ ጊዜ ትምህርት የማግኛ፣ የመሻሻይ እና በአጠቃላይ የመቋቋሚያ ጊዜ ነው። ወጣት ልጆችን ማሠር ጥበብ የሚጎድለው በመሆኑ ከተወሰነ የዕድሜ ክልል በታች ያሉ ልጆችን አስመልክቶ ሌሎች ሕጎችን መከተል አስፈላጊ ነው። እስራት የተፈጸመው ወንጀል ከባድ መሆኑን የማሳያ መንገድ ሲሆን ቅጣቶች ግን መካከለኛ መንገዶች ናቸው። እስራትም ቢሆን በአዎንታዊ መንገድ ሊታይ ይገባል። ይህ የሚሆነው [illegible]

[illegible] ለማድረግ ስለ ሆነ ነው። ስለዚህ እስራት የሚፈጸምበት ቦታ ጥሩና እስረኛው የሚታረምበት ቦታ መሆን ይገባዋል። አካላዊ ቅጣት፣ ማሰቃየት ፈጽሞ የተከለከለ ነው። ሁሉም የእስር ቤት ሠራተኛ ቀጥሎ ያለውን ማወቅ አለባቸው፤ ይህም ጤናማና በሥነ ሥርዓት የሚሠራ አእምሮ ያለው ሰው እስር ቤት ባሉት ዜጎች ላይ አካላዊ ድብደባ መፈጸምን እንደ ሥራ አድርጎ ሊሠማራበት የማይገባው መሆኑን ነው። እስረኞች ገና በፍርድ ሂደት ላይ እያሉ ተፈርዶባቸዋል። ከዚያ በኋላ አካላቸውንና ነፍሳቸውን መስበር ሳይሆን እንዲያገግሙ መርዳት ያስፈልጋል።

ከአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ እስር ቤቶች እስረኞች በሰብአዊ መንገድ የሚያዙበትና ደንበኞቻቸው የሚጠበቅበት ቦታ ለማድረግ ዓለም አቀፍ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። ይህም ጤንነታቸውን፣ መገናኛቸውን፣ ትምህርታቸውን እና መንፈሳዊ እንክብካቤያቸውን ያጠቃልላል። ይህን ንቅናቄም አቀፍ ድንጋጌ የሚያከብሩ ማኅበረሰቦችና አገሮች ከንሰም አቀፍ

ማኅበረሰብ የሥነ ምግባር ደረጃ ራሳቸውን ያገለሉ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። እንደዚሁም እነዚህን ድንጋጌዎች በቃልና በጽሑፍ ብቻ በመቀበልና ተግባራዊ በሆነ መንገድ በመከተል መካከል ልዩነት መኖሩን ማመልከት ያስፈልጋል።

## ከፍርድ ቤት ውሳኔዎች ጋር የተያያዙ አንዳንድ ችግሮች

በትክክል እና በስሕተት መካከል የልዩነት ድንበርን ማስመር እንደሚያስፈልግ ጠቅሰናል። ይህ የሚያደርገው ፍትሕን ለመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ከጽድቅም አንጻር ነው። የኋለኛው ቃል በስምን እንደ ሆነ በግልጽ ይነግረናል። እንደ እውነቱ ከሆነ የተሟላ ፍትሕን ማግኘት ፈጽሞ አይቻልም። አንድ ምሳሌ ይህንን ሊያሳይ ይችላል። በአንድ ከተማ መቶ የሚያህሉ ባይስክሎች ቢሰረቁ ከእነዚህ የሚገኙት በአማካይ ሰላሳ ወይም አርባ ያህሉ ብቻ ይሆናል። ለዚህ ስርቆት ሃያ ሌቦች ብቻ ወደ ፍርድ ቤት በመሰዱ ከእነዚህ ምናልባት አስሩ አምስቱ ብቻ ይከሰሱና አምስቱ

በማስረጃ እጦት ነፃ ይለቀቁ ይሆናል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ በዚያች ከተማ ያለው የፍትህ ሂደት ደካማ በመሆኑ የከተማው ነዋሪዎች በዚህ ምክንያት ሳይማረሩ አይቀርም ብለን ለመናገር እንፈተናለን። ይሁን እንጂ የፖሊስ፣ የአቃቤ ሕግና የፍርድ ቤት ሥራ ፍትህ ያለ ምንም እንከን የሚከናወንበት ሳይሆን ስሕተትና ትክክል ምን እንደሆነ የሚረጋገጥበት ትልቅ ሥራ ነው። በቤትና በትምህርት ቤት ስለ ታማኝነትና ስለ ስርቆት፣ አስመስሎ ስለ መሥራት እና ስለ ማጭበርበር መማርን ትምህርት ከመስጠት ጋን ለግን በእነዚህ ባለሥልጣናት በሚሠራው ሥራ ውስጥ በግልጽ የሚተላለፍ መልእክት አለ። እርሱም በሕዝቡ ማኅበረሰብ ውስጥ በጋራ አድናቆትን ሁላችንም ሕግ አክባሪዎች፣ ታማኞችና ትክክለኞች መሆን ይገባናል የሚል ነው።

ምናልባት አሥር ከመቶ ሌቦች ብቻ ቢያዙና በፍርድ ቤት ቢፈረድባቸው ወይም ሃምሳ ከመቶ ነፃ ንጹሐን ብቻ ቢፈረድባቸው ይህ ፍትህ ሊሆን ይችላልን? በማለት ብዙዎች ይህንን አሳብ

ሊታወስ ይችላሉ። ይህንን ጥያቄ እንዲህ ብለን ልንመልስ እንችላለን። ሁለት አመራረጦች አሉ። አንደኛው አማራጭ ሕግ አክባሪዎች ለመሆን ሁላችንም መጸጸት፤ አካሄዳችንን በእጅጉ መለወጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተቆጣጣሪ ፖሊሶችን፤ ጠባቂዎችን፤ ዘበኞችን፤ ከሳሾችን፤ ዳኞችንና ፍርድ ቤቶችን በእጅጉ ማብዛት ናቸው። «በእጅጉ ማለት ደግሞ ከአምስት እስከ አሥር እጅ ማለት ነው። ይህ በበኩሉ ብዙ ገንዘብ ይጠይቃል። በዚህ አካሄድ ወንጀል መቀነስ የሚቻለው ለአጭር ጊዜ ብቻ ሲሆን ይህ አካሄድ በሂደት ማኅበረሰቡን በድህነት ውስጥ ይጥላል። እንዴት ተብሎ ቢጠየቅ የፖሊስንና የዳኝነትን ሥራ ቀጣይ ለማድረግ ማኅበረሰቡን በተለያየ መንገድ ብዙ ወጪ ስለሚያስወጣው ነው። ለመሆኑ የሚፈለገው «ጥቅም» ምንድን ነው? በብዙ «ፖሊሳዊ አስተዳደር» ውስጥ መታወቅ ያለበት አንድ ነገር አለ። ይኸውም ብዙ ፖሊሶች፤ ጠባቂዎች፤ ዘበኞች በቂ ደመወዝ ስለማይከፈላቸው እነርሱ ራሳቸው ተመልሰው የድሃው ዜጎቻቸው «ደም መጣጭ»

ወንጀለኞች ይሆናሉ። እነዚህ ባለሥልጣናት ስለተሠራ ወንጀል ማንኛውንም ሰው ተጠያቂ አድርገው መያዝና በጉቦ መልቀቅ የየዕለቱ ትእይንት ይሆናል። ለአንድ ማኅበረሰብ ፋይዳ ከማክበር፤ ለሕግ ከመታዘዝና እርስ በእርስ ከመረዳዳት የተሻለ ሌላ አማራጭ የለም። ከእስራት ጋር ተያይዞ «ወንጀልን መከላከል» የሚል አባባል ድሮ ትኩረት ይሰጠው ነበር። ከዚህ የተነሣ አገላለጹ ሥርቃይን ጨምሮ ትብብ «የክፋ» ነበር። አሁን ግን ወንጀልን የመከላከሉ ጉዳይ እንዳለ ቢሆንም ለትብብት የሚሰጠው ትርጉም ከበፊቱ የተለየ ነው። አጥፊዎች ወንጀል ዋጋ እንደሚያስከፍል መረዳት አለባቸው። አጥፊው ራሱ ይህንን ለመረዳት የሚቸገር ከሆነ ቢያንስ ሌሎች ወንጀል ለመሥራት የሚፈተኑ ይህንን መረዳት ይገባቸዋል። ወንጀል በሂደት ትርፉ ከጉዳት ከመሆንም ባለይ አንድም ችግር የመፍቻ መንገድ አይደለም።

በይበልጥ የዘመነው ይህ ጊዜ በእስር ቤቶችና በተከሳሾች ትግር ላይ ያመጣው መሻሻል የለም። ብዙዎቹ እስረኞች ወደ እስር ቤት በተደጋጋሚ በመመርመር የተለመዱትንና አዳዲስ የወንጀል

ዓይነቶችን ለአዲስ ገቢ እስረኞች ለማስተማር ባለሙያ ይሆናሉ። ከዚህም የተነሣ እስር ቤቶች የቁማርና የአደንዛዥ እጽ መለማመጃ ቦታ ይሆናሉ። በዚህም ምክንያት ባለሥልጣናትና የህግ ፈቃጅ ድርጅቶች ጣልቃ በመግባት ተጨማሪ ማሻሻያዎችን ለማድረግና የሚቻል ሆኖ ሲገኝ ለእስር ቤቶች አማራጭ መንገዶችን መቀየስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶአል። እንደዚህ ያለውን መረጃ በሰፊው ማኅበረሰብ ውስጥ በማሰራጨ ብዙዎቹ አስቀድመው በሕይወታቸው አንድ ዓይነት ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ ያስፈልጋል።

ቅጣት ወይም እስራት የደረሰባቸው ሰዎች የቅጣቱ ጊዜ ካለፈ በኋላ ለወንጀላቸው «ቤዛ» እንደ ከፈሉ ብዙ ጊዜ ይናገራሉ። ይህ ለተከሰተውን ነገር ጥሩ የመግለጫ ቃል አይደለም። እነዚህ ሰዎች የተሰረቀውን ገንዘብ ወይም ነፍስ አያስገኙትም ከሆነ የገደሉትን ሰው ነፍስ ያልመለሱ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች ለማለት የሚፈልጉት ማኅበረሰቡ እንደዚህ ዓይነት ቅጣት ጥሎብኛልና እኔና ኅበረተሰቡ እኩል ነን፤ ጉዳዩም ተፈቶአል

ሊሉ ይችላሉ። ይህ ለተፈጸመው ቅጣት የሚሰጥ በጣም ተራ ትርጉም ቢሆንም አንድ እውነታ ሊኖረው ይችላል። ይኸውም የተቀጣው ተከሳሽ ጉዳዩ «ተፈጽሟል» ለማለት የሚፈልግ ከሆነ «እርሱ ወጥቶ አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» ማለቱ ነውና ይህ ሰው ትምህርት አግኝቶ ሕይወቱን እንደ አዲስ ሊጀምር ይችላል። ወንጀል ፈጻሚዎች ሁሉ ተስፋ የሚያደርጉት ነገር አለ፤ እርሱም ከሁሉም ሰው ጋር ኅብረት ወደሚያደርግበት ሕይወት ለመግባት አስፈላጊውን ተሐድሶ ማግኘት ነው። ከዚህ ሩቅ ልንሆን እንችላለን። ነገር ግን ወደዚህ አቅጣጫ ለመጓዝ መታገል ግዴታችን ይሆናል። ክርስቲያኖች ሁሉ ይህን ለማድረግ ግንባር ቀደም መሆን አለባቸው።

## የሞት ፍርድ

ይህንን ዓይነት ቅጣት አስመልክቶ ብዙውን ጊዜ የሚደረገው ክርክር ወንጀል ለመከላከል ትልቁ መሳሪያ እርሱ

ነው ማለት ነው። አስተሳሰቡም የዚህ ዓይነት ወንጀል ፈጻሚዎች ነፍሳቸውን እንደማያጡ በመመልከት ነፍስ ከመግደልና ከሌሎች አስቃቂ ወንጀሎች ይቆጠባሉ የሚል ነው። ነገር ግን የሞት ቅጣት የሚፈጸምባቸውን አገሮች የተመለከትን እንደ ሆነ ለሞት ቅጣት የምንሰጠው ይህ ትርጉም ትክክል አይሆንም። በነዚህ አገሮች ያለው የወንጀል ቁጥር ከሌሎቹ አገሮች እየቀነሰ ከመሄድ ይልቅ እያሻቀበ ይሄዳል። እንግዲያውስ የሞት ቅጣት እንዴት አድርጎ የወንጀል መከላከያ መንገድ ሊሆን ይችላል?

በሠለጠነው ዓለም የተከሳሽን ሕይወት ማጥፋት ተገቢ እንዳልሆነ ይታመናል። ይልቁንም የአንድን ሰው ክፉ ጠባይ ለማረቅ በጣም ተስማሚ ያልሆነ አፈጻጸም ነው።

ከዚህ የተሻሉ ብዙ መንገዶች አሉ። ከእስር ቤቶችና [illegible]

[illegible] የሆኑ ብዙዎች አሉ። ይህም የሚያበረታታ ነው። በተጨማሪም ወንጀለኛን ጨምሮ የሰው ልጅ ሁሉ የማትሞት ነፍስ አለው። ሕይወት እስካለችም ድረስ እንደዚህ ያለ ሰውም ተስፋ አለው። ስለዚህ ወንጀለኛ ሊታደስና የታረመ ሰው ወደ መሆን ሊደርስ ይችላልና ተደም ብለን የጠቀስነው «አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» (2 ቆሮ. 5፥17) የሚለው ቃል ተግባራዊ ሊሆንለት ይችላል።

# ምዕራፍ 12
# መከላከያና ጦርነት

## ለአገራችን የሚኖረን ፍቅር

የራሱን አገር የመከላከልና የጦርነት ጉዳይ ሲነሣ እነዚህን አመለካከቶች የሚደግፉና የሚቃወሙ በመኖራቸው ምክንያት ለመመለስ የሚያስቸግሩ ጥያቄዎች ይነሣሉ። የክርስቲያን ሥነ ምግባር በሚተነተንበትም ጊዜ እነዚህ ተመሳሳይ አስቸጋሪ ጥያቄዎች ይነሣሉ። ሌላው ችግር በንድፍ (ቲዎሪ) እና በተግባር መካከል ያለው ልዩነት ነው። ቲዎሪ ያርቃቂው በመጻፊያ ጠረጴዛው ላይ ተቀምጦ አመጽ በሌለበት ዓለም በምናቡ እየገለጸ [illegible]

ምንም ወታደራዊ ኃይል [illegible] ይሁን እንጂ በበሩ ወይም በመስኮቱ ትንሽ ድምፅ ቢሰማ ሌቦች ቤቱን ሰብረው የሚገቡ እየመሰለው አፋጣኝ የፖሊስ እርዳታ ይጠይቃል። ይህም ሁኔታ እንደዚህ ያለ ሰው ከአገሩ አጥታ ይልቅ ለራሱ ደኅንነትና ጥበቃ ቅድሚያ የሚሰጥ ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው። ይህ ዓይነቱ ሰው የፖሊስ እርዳታ ሲጠይቅ ፖሊሱ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት እጁን ወደ ቤቱ በመምጣት ከዘራፊዎች ጋር እንዲደራደር የሚፈልግ ይመስላል። በዚህ ዓይነት አመለካከቱ ይህ ሰው ቤት ሰርጎ ገቦችና ዘራፊዎች ለእርሱ በምናቡ ውስጥ ከሚታየው መደራደር ይልቅ አደገኛ የሆኑ ትጥቆችን ይዘው እንደሚመጡበት መጠራጠር የለበትም።

እንደዚህ ያሉ የመከላከያንና ማንኛውንም ወታደራዊ ኃይል የሚቃወሙ ሰዎች ራሳቸው የሚከተሉትን መመሪያ የሚቃወሙበት ሌላም መንገድ አለ። እነዚህ የወታደራዊ ኃይል ተቃዋሚዎች አገራቸውን በውጭ ወራሪዎች በምትጠቃበት ጊዜ ወራሪውን በመጋፈጥ ከሚዋጉትና በአገባቸው ከሚቃወሙት ጋር ሆነው አገራቸውን ለመከላከል ወታደራዊ ሥልጠና እንዲሰጥ

[illegible]

ፈጥነው የሚወተውቱ ናቸው። ከዚያስ ምን ይሆናል? እነዚሁ ሰዎች ነፉት በተመላው ጎሰም ውስጥ መሆናችንንና አንዱት አገር ደግሞ እንደዚሁ ላሉት ክፉቶች በኃይል ጭምር የመጨረሻ ግደብ ሊያደርጉላቸው የሚገባት መሆኑን ከቀደመው ዘመን ይልቅ በግልጽ የሚረዱባቸው ብዙ ሁኔታዎች ይኖራሉ። ይህ የሚሆነው ጥቂት የአድማ ቡድኖች ጸጥታውን እንዲቆጣጠሩ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ ራሱ የራሱን ፖሊስ በሚያስፈልግበት ጊዜ ነው። ክፋትና ጭካኔ በሰፈነበት በሚታይበት ጊዜ ሊሰሙና ሊሉት ክፉ አድራጊዎች ግዴት ለመከላከል ለመግደል ተዘጋጅተው በሚመጡ ሰንሰለትና ሌላ ብቻ ያለ መገኘት በቂ አይሆንም። ስለዚህ የፖሊስ ትጥቅ፣ አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ ትጥቁን መጠቀም ወንጀልን ለመከላከል ይጠቅማል።

አገራችንን ከጥቃት እንድንከላከል የሚያደርገን ምንድን

ነው? ቤታችንን፣ ሰፈራችንን፣ ከተማችንን ወይንም ክልላችንን የምንወደውን ያህል አገራችንንም መውደድ ያስፈልጋል። ከዚያም የሚያልፍ ነገር አለ። በእኛ አገራችን ውስጥ የጋራ የሆነ ቅርስ፣ ቋንቋ፣ ልማዶች፣ ታሪክ፣ ባህላዊ ሥራዎችና ልምምዶች አሉን። ሕዝባችን ምናልባት ለብዙ ትውልዶች በአገራችን ውስጥ ስለ ኖረ እነዚህ ብዙ ትውልዶች ወደ እኛ ያስተላለፉአቸው ብዙ ልምዶች በውስጣችን ሥርአው የተቀመጡ ናቸው። እንደዚሁ ባለ ሁኔታ ውስጥ የሚኖር ግንኙቱ አለ። ይኸውም እነዚህን ሁሉ ስሌሎች አስረክበን እንተመጣለን ወይ የሚል ይሆናል። ሌሎች ስንል እነርሱ እነ ማን ናቸው? በወታደር ሊወሩን ወይም በአየር ሊወጉን የሚመጡ፣ ምናልባ መጠለያ ለመፈለግ ከባዕድ አገር የሚመጡ ኮበለሎች አይደሉም። በውጭ ኃይል የሚላኩ የጠላት ኃይሎች ናቸው። እነዚህን ወራሪዎች የሚልኩ አገር ገዢዎች ምናልባት አገራቸውንና ሕዝባቸውን ሲረዱም ጊዜ ትንኮሳዊ ባልሆነ መንገድ የሚጠቀሙ ክፉ ገዢዎች ከመሆናቸው የተነሣ ሕዝቡን ያላዘኑ ሊሆኑ ይችላሉ። በሕዝቡ ዘንድ ያጡትን አርኪታ አትኩሮት ለማስለወጥና የሚያደርስባቸውን ጎሰም አተኩሮ ትችት

ለማስቆም ሲሉ በውስጣቸው የተደበቀውን ዓላማ ...ተደጋጋሚ

የወሰን ግጭት›› እና ‹‹በእነርሱ ወሰን ውስጥ የሚገኙትን አናሳ ዜጎቻችንን ስላጎሳቁሉ›› በሚሉ ሰበቦች በመሸፈን ጦርነት ይጀምራሉ። አገራችንን እንደዚህ ላሉት ወራሪ ገዥዎች በማጋለጥ እና ተጨማሪ መሬት፣ ሕዝብ፣ ተቋማት እና ፋብሪካዎችን ለእነርሱ አሳልፎ በመስጠት ምን ጥቅም ይገኛል?

## መሠረታዊ እውነቶች

መሠረታዊውን እውነት ለመረዳት መነሻ ነጥባችን እግዚአብሔር ፈጣሪአችን፣ አባታችን እና ጠባቂአችን ነው የሚለው አሳብ ነው። በመቀጠልም የምንኖርበትን አገር እና አብረን የምንኖረውን ሕዝብ የሰጠን እግዚአብሔር መሆኑን መቀበል አለብን። ይህም አገር በዚህ ዓለም ላይ መኖሪያ ቦታችን ነው። ስለሆነም ሁላችንም ይህንን የተሰጠንን አገር ወይም ምድር የመጠበቅ አደራ አለብን። በዚህም ምክንያት ሕዝባችን ነገን እና ቀጣዩን ዓመታት በዚህ በተሰጠን አገር ውስጥ መኖር ለመቻሉ ማረጋገጫ አለን? ወይ ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ነገን እና ቀጣዩን መጪ ዓመታት በሰላም ለመኖር ከፈለግን ዛሬ አገራችንን መጠበቅ ነው። መንገዶች፣ የባቡር ሐዲዶች፣ የመስኖ ዝርጋታዎች ለተሠሩበት ዓላማ እንዲውሉ መከታተል ብቻ ሳይሆን ሊያፈርሱአቸው ከሚፈልጉ ጠላቶችም መጠበቅ አለብን። ከጥንታዊው የቤተ ክርስቲያን ዘመን ጀምሮ ሰላም ለመኖር እንደሚያስችለን ‹‹የዕለት እንጀራ›› ተደርጎ ይታሰባል። ለዕለት እንጀራችን ‹‹ምግብ፣ ልብስና ሌሎች ነገሮች ብቻ ሳይሆን የሚያስፈለጉን አብረን በምንኖረው ሕዝብ መካከል በምናደርገው የየዕለቱ ሥራና ንግግር እንዲሁም የጎረቤት፣ የሕዝብ እና የእርስ በርስ ግንኙነት ውስጥ በሰላምና በጸጥታ መኖር ስንችል ነው። እነዚህ ሁለቱ ነገሮች ማደግና መስፋት የሚገባቸውን ያህል እንዳያድጉ በተረበሹ ጊዜ ለመኖር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ እየመነመኑ ይሄዳሉ። ከዚህ የተነሣ ጤናማ ሕይወት ሊቀጥል አይችልም። ስለዚህ እግዚአብሔር የዕለት እንጀራችንና ምቾትን ለእኛ ይሰጥ ዘንድ መሣሪያ አድርጎ ለሚጠቀምባቸው

መንግሥታዊ ተቋማትና ባለሥልጣናቱ መሳሰይ እጅግ አስፈላጊ ነው። ሁሉንም ነገር ከእግዚአብሔር በችሮታ የተቀበልን ቢሆንም እግዚአብሔር የተረጋጋና ቀጣይነት ያለው ሰላማዊ መንግሥት ባይሰጠን ከእርሱ ዘንድ የተሰጡንን ነገሮች በጸጥታና በደስታ ልንጠቀምባቸው አንችልም። መከፋፈል፣ ግልና ጦርነት ባለበት ቦታ የዕለት እንጀራ ከእኛ ይነጠቃል፤ ወይም ተመጥኖ በራሽን ይቀርብልናል። (ትልቁ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ)።

እነዚህ ነገሮች ከእኛ እንዴት እንደሚነጠቁ ማብራራት ቀላል ነው። ማብራሪያውም ሌባ ቤት ሰርስሮ ገብቶ ከሚሠርቅበት ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል ማቴ. 6፥19። ይህንን ነገር ኢየሱስ በትምህርቱ ግልጽ ካደረገው በላይ ግልጽ ሊያደርግ የሚችል ሰው ሊኖር አይችልም። ለጦርነት መንስኤ ምክንያት የሚሆነውና

በእግዚአብሔር የሚፈጠሩ፣ የማይፈለግ ክስተት አይደለም። ይልቁንም ሰው እግዚአብሔር ያቀደለትን መንገድ ትቶ ሌላውን መንገድ መከተሉን የሚያመለክት ነው።

ራሳችንን በጦር መሳሪያ ከማስታጠቅ ብንቆጠብና ያለውን ወታደርና የጦር መሳሪያ ብንቀንስ ጦርነቶች ሁሉ ይቀራሉ የሚለውን አሳብ የሚያራምዱ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ። ለዚህ ጉድለት አስተሳሰብ የሚሆኑ ሦስት ምሳሌዎች አሉ። በመጀመሪያ አገሮች ሁሉ የጦር መሣሪያዎቻቸውንና ወታደሮቻቸውን እንዲተዉ ማድረግ የሚችል ባለሥልጣን የቱ ነው? ተጠባባቂ ሠራዊት እንዲኖር የሚወተውቱ ካሉ የተጠባባቂ ጦር ሠራዊት ወንጀለኞች፣ ሌቦች አባላት ታጣቂዎች ናቸው? ከክፋት እና አገራቸውን አሳልፈው ለመስጠት የቆረጡ ናቸው? አያሰርቁም ወይ አይዋጉም? ከመካከላቸው ማንኛውም ሰው ይህንን እያደረገም ብሎ መገመት ይቻላል? እንግዲያውስ በሌላውም አገር ያሉ ሰዎች ከእነዚህ የተለዩ ሊሆኑ አይችሉም። አገራችንን በሚያጠቁ አገሮች ውስጥ የሚኖሩትንም ሕዝብ አስመልክቶ ያለው ነገር ይኸው ነው።

እነዚህ የጎረቤት አገር ሰዎች እጅግ ከመውረር፣ መሬታችንን

ከመንጠቅና በእኛ ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት የተለየ ሌላ ዓላማ አላቸው ብሎ ማሰብ ይቻላል? ይህንን ማሰብ አይቻልም። በተጨማሪ የጎረቤቶቻችን አገሮች ወይም የሌሎች አገር መሪዎች ከሁሉም ይልቅ ታማኞች ሊሆኑልን ይችላሉ? እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ የተረጋገጠ ዋስትና የሚሰጠን ወይም የታማኝነት ውል የሚፈርምልን ማንም የለም።

የጦር መሣሪያ ቅነሣን አስመልክቶ የሚቀርበው አንድ ደካማ ክርክር አሳማኝ አይደለም። እርሱም «ጠላታችን የጦር መሣሪያ እንደፈታን ቢያውቅ ይህንን ሁኔታ ተረድቶ በሰላም እንድንኖር ይተውናል» የሚል ነው። ሌላው እንዲህም ሊል ይችላል። «አንድ ሌባ የተቆለፉ ቤቶችና ያልተቆለፉ ቤቶችን ቢያገኝ ያልተቆለፉትን ቤቶች አክብሮ በሰላም ያልፋቸዋል» የሚል ክርክር ነው። ይህንን ሁኔታ የጦር መሣሪያውን ወደ ፈታው አገር

ሁኔታ ብናመጣው ያ አገር ምን ይደርስበት ይሆን? የዚያ አገር ጠላት በሌላ ወራሪ አገር ለመውሰድ ብዙ ጊዜ አይፈጅበትም። ለምን እንዲህ ይሆናል? በይፋ የሚቀርበው ዋና ሰበብ «ያህ ጎረቤት አገር ከአሁን ጀምሮ ለሌላ የውጭ ወራሪ ኃይል የተጋለጠ ስለ ሆነ ይህንን አገር ከውጭ ወራሪ ኃይል ለመከላከል ስለ ተገደድን ነው፤ ሌሎች አገሮች ይህንን አገር እንደ ከፍተኛ ግዛት ተጠቅመው እኛን እንዳያጠቁን ነው» የሚል ይሆናል። ሌላም ነገር ሊሆን ይችላል። መከላከያ የሌለውን አገር ሁለት ወይም ሦስት ጎረቤት ኃይሎች የዚያን አገር አንዳንድ ግዛቶች እየቆራረጡ ሊከፋፈሉት ይችላሉ። በእንደዚህ ሁኔታ ድንበሩን መከላከል ያልቻለ አገር ቀስ በቀስ ከዓለም አገሮች ካርታ ላይ ሊደመሰስ ይችላል። ይህ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የተከሰተ ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች ከዚህ ትምህርት ማግኘት ከባድ ይሆንባቸዋል።

## ከቅዱሳት መጻሕፍት የምንማረው ትምህርት

ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ በጥንቃቄ መመርመር አለብን።

በአንድ በኩል የመከላከል ጉዳዮችን በተመለከተ ምን ማድረግ

እንደሚናገርብን ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር መመሪያ ይሰጡናል ለማለት አያስችልም። በሌላ በኩል ቅዱሳት መጻሕፍት ራሳችንን አገራችንን መከላከል ይከለክሉናል ማለትም አይቻልም። ሁለተኛው ሐሳብ እንደ ዘጸአት 20፥13 እና ማቴዎስ 5፥39 ባሉት ክፍሎች የሚደገፍ እንደሆነ በየዘመናቱ ሲነገር ቆይቶአል። ነገር የኢየሱስ የተራራው ስብከት አንድ አማኝ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለውን ጉዳይ የሚፈታበትን መንገድ ያሳያል። እንደዚህ ያሉ መመሪያዎች የአገርና የሕዝብ ደኅንነት ጠባቂዎች በሆኑት በፓርላማ፣ በመንግሥታት እና በባለሥልጣናት ተግባራዊ የሚደረጉ አይደሉም። በተጨማሪም ቅዱሳት መጻሕፍት ራሳቸውን እንዲያብራሩ መፍቀድ ያስፈልጋል። እንዲህ ማለት አንድ ቃል በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ሌሎችን ቃላት በሚቃረን መንገድ መተርጎም የለበትም።

ስለ መከላከል በአጠቃላይ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት በምንመለከትበት ጊዜ ኢየሱስ መከላከል «እርቅን ከመጠየቅ» ወይም እጅን ከመስጠት ሌላው አማራጭ መሆኑን ተናግሯል ሉቃስ 14፥31-32። ኢየሱስም ይሁን ሐዋርያቱ በቅድስት አገር ውስጥ በተመላለሱ ጊዜ ብዙዎች ወታደሮች የወትድርና አገልግሎታቸውን እንዲያቆሙ አልነገሩአቸውም። መጥምቁ ዮሐንስ ከወታደሮች «እኛ ደግሞ ምን እናድርግ» የሚል ጥያቄ በቀረበለት ጊዜ «በማንም ግፍ አትሥሩ፤ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ፤ ደመወዛችሁም ይብቃችሁ» ብሎ የመለሰውን መልስ ከእርሱ በኋላ ኢየሱስም ሆነ ሐዋርያት ስሕተት እንደ ሆነ አልተናገሩም። በዚህ ዓይነት መንገድ እነዚህ ሰዎች ስለ መከላከል ወይም ስለ ጦርነት ያላቸው አመለካከት ከክርስትና ደቀ መዛሙርትነት ጋር ሊስማማ የሚችል ሐሳብ ነው። እንደዚሁም ቅዱሳት መጻሕፍት «ሥልጣን ከእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር ለማንም አይሰጥም» እና «ባለሥልጣን በከንቱ ሰይፍ አይታጠቅም» ብሎ በግልጽ ያስተምራሉ።

እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ ከመስመር የወጣ አመለካከት

ከመስመር የሚወጡ ነገሮች በተለያዩ ምክንያቶች ይከሰታሉ። እንዲያም የላላና የደበዘዘ የግንዛቤ አሳብ ነው። በመጀመሪያ አሳቡ «ነፃ መሆን» ከሚለው አመለካከት የሚመጣ ሲሆን ልዩ ልዩ ችግሮች መፍትሔ የሚያገኙት ከዚህ «ፍቅር» ከተገለለው አስተሳሰብ ነው የሚል ነው። ብዙዎቹ «ግብረ-ገብ ወይም ጦርነት የሌለበት» ማኅበረሰብ የሚሉት ጽንሰ አሳቦች ወደ «የብልጭታ ዘመን» (Age of Enlightenement) ያመለክታሉ። ይህም «የሰው አመክንዮ» (Reason of Man) የሚለው አመለካከት የብዙዎችን አእምሮ የተቆጣጠረበት ዘመን ነው። የዚህ አመለካከት አራማጆች ከነባሩ ልማዳዊ አመለካከቶች ለመላቀቅ ከዚሁ በማያንስ መልኩ ከቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ቃል ነፃ የሚወጡበትን አዲስ

መንገድ ለመፈለግ የመረጣትን ሚና ተጫውተዋል። ይህም በሆነ ጊዜ «በዓለማዊ አመራር» እና «በመንፈሳዊ አመራር» መካከል ምንም ልዩነት አልተደረገም ነበር። ምድራዊው አመራር የሚጠበቀው መሠረታዊ ዓለማዊ ሆኖ ሥራውን ያከናውን ዘንድ ትልቅ ሥልጣን ያለው ቢሆንም ሥልጣኑ ከእግዚአብሔር ነው። ምድራዊውን ባለሥልጣን ትጥቅ ማስፈታት ማለትም ምድራዊውና መንፈሳዊውን አመራር አጥፍቶ ሌላ ትርጉም በመስጠት ግማሽ ምድራዊ እና ግማሽ መንፈሳዊ ማድረግ የሚል አመለካከት ነው። እነዚህ ዓይነት የውሸት ትንቢት በሁሉም ዘርፎች የሚፈለገውን ሥራ ለማከናወን አያስችልም። መንፈሳዊ አመራር ሊሆን አይችልም፤ እንዲሁም ዓለማዊው መንግሥት ምድራዊ ሥልጣኑን ስለ ተቀማ ምንም ዓይነት ምድራዊ ሥራ ማከናወን አይችልም።

## የተለያዩ ጦርነቶች

እስከ አሁን ስንነጋገር የቆየነው ጦርነት በአጠቃላይ ትክክል

ነው ለማለት ሳይሆን እንዲያውም በተቃራኒው ተቀባይነት የሌለው

ነው ለማለት ተፈልጎ ነው። የዚህን አሳብ ሙሉ ማብራሪያ በዚህ ቦታ መስጠት አስቸጋሪ ስለሚሆን ጥቂት ዋና ዋና አሳቦችን ብቻ እናነሣለን።

ምን አንኳ ራስን ለመከላከል ነው ተብሎ የሚደረግ ቢሆንም በሁሉም ዓይነት ጦርነቶች ሁሉና ብዙ ነፍ ሰዎች ስለሚነኩና ይህ የጦርነት ምልክት ነው የሚል ሽፋን በመስጠት ብዙ የግፍ ድርጊቶች ስለሚከሰቱ አንድም ጦርነት በራሱ ትክክል አይደለም። ከእነዚህ የግፍ ድርጊቶች መካከል በጦር ምርኮኞች ላይ የሚፈጸም ጭካኔ፣ ዝርፊያና አስገድዶ መድፈር ሊጠቀሱ ይችላሉ። በዚህ አካሄዳችን በጦርነት ጊዜ መከበር ካለባቸው ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች ወጣ ያሉትን ድርጊቶች ሳናነሣ እናልፋለን። ይልቁንም በአጠቃላይ ሁለት ዓይነት ጦርነት መኖራቸውን የምንጠቅስ ሲሆን፥ እነርሱም መከላከልና ማጥቃት ናቸው። በእነዚህ ሁለት ዓይነት ጦርነቶች መካከል ያለውን ልዩነት ማየትና
[illegible]

[illegible]
እንዲ ከባድ የሆኑ ችግሮችም አሉበት። ይኸውም ብዙ የፖለቲካ መሪዎች በመከላከል ስም ወረራን የሚያካሂዱ በመሆናቸው ነው። ይህም የሚከናወነው ጥልቅ በሆነ የብሔርተኝነት ስሜት ተገፋፍተው ያለው ፕሮፓጋንዳ በማድረግ ነው። ፕሮፓጋንዳው የሚገነባው አጥቂው እንደ ተበዳይ ተደርጎ ነው። በዚህ ሂደት ሁሉም እንደ የሚያታልል አካሄድ አለ። ጥቂት የወታደሩ አባላት የሌላውን አገር ወታደር ልብስ አስመስለው በማስፋት ወይም ከድብቅ ያላ ንጋዴዎች ላይ በመግዛትና በመልበስ አንዳንድ የራሳቸውን አገር መንደሮች ያወድማሉ፤ ሰዎችን ይገድላሉ። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ሥራ የሚፈጽመው የፕሮፓጋንዳ ክፍሉ ይሆናል። የፕሮፓጋንዳ ክፍሉም «የጠላት ኃይል በንጹሃን ዜጎቻችን ላይ የሚፈጽመውን ተደጋጋሚ የታትና ግድያ በትእግሥት ማለፍ አንችልም» የሚል ልፋፋ ከተነዛ በኋላ «የእጸፋ ወጊያ» «ሀገር አገርን ለመጠበቅ የሚል ሰበብ የመከላከል ጦርነት» ይካሄዳል። እንደዚህ ያሉና መሰርሰር ያለባቸው የማስመሰያ ድርጊቶች በብዙ የዓለም ክፍሎች ተደጋግመው ይካሄዳሉ።

ሌላው አስቸጋሪ ነገር ለጥቃት የተጋለጠው አገር አንዳንድ ግልጽ የወረራ ምልክቶችን ሲያይ ወይም ጠላት በምድር ወይም በባሕር ወደ እርሱ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑን የሚያመለክት መረጃ ሲደርሰው ነው። በዚህ ላይ የጠላት አካሄድ ገና ይፋ ባይሆንም ግማሽ ያህል ወረራ ስለ ሆነ ጠላት የምድር ወይም የባሕር ድንበሩን እንዳያልፍ የማይፈቅድ መሆኑን ለመግለጽ ፖለቲካዊ ወይም ወታደራዊ ጥበብ ሊኖረው ይገባል። አብዛኛውን ጊዜ በዚህ ዓይነት ጦርነት ላይ የሚሳተፍ ሁሉ ጦርነቱ የመከላከል ጦርነት መሆኑን በግልጽ ያውቃል።

ከዚህ የሚያልፉ ሌሎች ችግሮችም አሉ። በዓለም አቀፍ ሕጎች መሠረት ብዙ ዓይነት የጦርነትና የጦር መሣሪያዎች ለምሳሌ አንዳንድ የጥይትና የቦንብ ዓይነቶች፣ የጋስ እና የኬሚካል የጦር መሳሪያዎች የተከለከሉ ናቸው። አንዳንድ ኬሚካሎች ሙሉ ለሙሉ መርዛማ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ የሚያፍኑ ወይም ዐይነ ሥውርነትን የሚያስከትሉ ናቸው። ኬሚካሎቹ የተለያዩ ቢሆንም አንድ የጋራ ጸባይ አላቸው። ይኸውም በቀረባቸው፣ ወይም በነካቸው እንደዚሁም ወደ ውስጥ በሰባቸው ሰው ላይ አደጋ ማስከተላቸው ነው። ከዚህ የከፋ ነገርም አለ። አንዳንድ አገሮች ጀርሞችን አራብተው በመያዣ ውስጥ ካከማቹ በኋላ ባሰኛቸው ጊዜ መያዣቸውን በመስበር በጠላቶቻቸው ግዛት ውስጥ ያሰራጫሉ። ከዚያም ጀርሞቹ የተለቀቁበት አገር ወይም በአቅራቢያው ያለው አገር ሕዝብ አደጋ ላይ ይወድቅና ተከታይ ትውልድንም በሚጎዳ ገዳይ በሽታ ይያዛል። በዚህ አደራረግ በአንድ ክፍለ ዓለም የሚገኘውን ሕዝብ በመላ ማጥፋት የሚቻልበት መንገድም አለ።

እስከ አሁን በሰውና በሥነ ሕይወት ታሪክ ውስጥ የተካሄደውና የተሰራጨው ዕድገት እንደሚያሳየው በእነዚህ በኩል ሊደርስ የሚችለውን ጦርነት በመከላከል ማቆም አይቻልም። ስለሆነም እነዚህ ጅምላ ጨራሽ መሣሪዎች በሰላሙ ጊዜ በሚፈበረኩባቸው ቦታዎች እንዲቆሙ መደረግ አላባቸው። ሳይንስ በአሁኑ ጊዜ በመስቀለኛ መንገድ ላይ ደርሶአል። ወታደሮች ወይም አዛዦቻቸው በዚህ ዓይነት ጦርነት መካፈልን እምቢ

እንዲሉ መጠየቅ ብቻውን በቂ አይደለም። ይልቁንም እምቢ ማለት ያለባቸው ሳይንቲስቶችና በኬሚካል ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሠሩ ረዳቶቻቸው ናቸው። ስለዚህ ጉዳዮች ለማሰብ ንቃት ያላቸው ሁሉ ከዚህ ዓይነት ጦርነት ጋር የተያያዙ ክፉ ነገሮችን ለማስቆም የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ አለባቸው። በሰላም ጊዜ ማንኛውንም ዓይነት ትብብር ማቆም ይቻላል። ጦርነት በተነሣ ጊዜ ግን ትብብርን ማቆም የከፋ ቅጣትን ከማስተናገድ በስተቀር ሌላ አማራጭ የለውም።

## የመከላከያ ዓለም አቀፋዊ ገጽታዎች

በአገሮች መካከል ያለውን ሰላም ለመጠበቅ የራሳችንን መከላከያ ከመገንባት ይልቅ በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ላይ መተማመን አለብን ተብሎ አንዳንድ ጊዜ ይነገራል። እንደ ዓለም አቀፍ ፖሊስ ኃይል ያሉ ተቋማት ተውስ ወጻለባቸው ቦታዎች ተልኮ፣ ካረጋጉ በኋላ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻን ውሳኔ

ይሰጡበት ተብሎ አሳብ ይቀርባል። ይህ ሁሉ መልካም መስሎ ቢታይም ሁኔታዎችን በሚከተለው መንገድ ሊገለጽ ይችላል። "ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ በአንድ ጉዳይ ላይ ወደ ስምምነት ደርሶ ኃይሎቹን አሰልፎ ወደ ሆነው ቦታ በሚልክበት ጊዜ ሂደቱ ከመጠናቀቁ የተነሣ ጦርነት አብቅቶ ያገኘዋል። በ1920 ተቋቁሞ በ1946 የፈረሰው የመንግሥታቱ ማኅበር እና በ1945 የተቋቋመው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በአንድ ላይ ያሳዩት እነዚህ ድርጅቶች የተፈለገውን ነገር ለመፈጸም አስፈላጊው ሥልጣን የሚጎድላቸው መሆኑን ነው። ቢሆንም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአባል አገራት የጋራ ጉዳዮችን ለመፈጸም ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ቢሆን ሰላምን ለመጠበቅ ለሚደረገው ተግባር ፍሬት አጋዥ መሣሪያ ነው።

## ወታደራዊ አገልግሎትን አለመቀበል

በአንዳንድ አገሮች አንዳንድ እንቅስቃሴዎች አሉ። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ማንኛውንም ጦርነትና ወታደራዊ አገልግሎትን

የሚታወሱ ወጣቶች ለጦርነት መሠልጠንና ወታደራዊ አገልግሎት መስጠት ከሕሊናቸው ጋር እንደማይስማማ በመግለጽ ይህ አባባቸው ተቀባይነትን አግኝቶ የሕዝቡን የአመለካከት ትኩረት እንዲስብላቸው ለማድረግ ራሳቸውን በማኅበር ያደራጃሉ:: በሌሎች አገሮች ደግሞ እንዲህ ዓይነት እንቅስቃሴ የሚያደርግ ተቋምም ይሁን ግላዊ ጥረት የለም:: ለዚህ ምክንያቶቹ ብዙ ሊሆኑ ጥቂቶቹ ሁሉንም የጦር መሣሪያ ዓይነት ይዞ መገኘት እና በማንኛውም መልኩ ቢሆን ሰውን መግደልን መቃወም ሊሆኑ ይችላሉ:: ግድያን ለመቃወም የሚሰጡት ምክንያት እላይ በገጽ 150 ላይ የተጠቀሰው ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን እነዚህ ተቃዋሚዎች ማኅበረሰቡ ከሚሰጠው ጥበቃ ተጠቃሚ ለመሆን የመብት ጥያቄ ያቀርባሉ፤ ይጠቀማሉም:: የሚፈልጉት ጥበቃ ደግሞ በፖሊሱ እጅ ባለው የጦር መሣሪያ ካልሆነ ሊያገኙት አይችሉም:: እንግዲያውስ በጦር መሣሪያ አማካይነት በሚሰጠው ጥበቃ ሥር የሚኖሩ ከሆነ እነዚህ ሰዎች የሚቃወሙት መሣሪያ ይዞ መገኘትን ነው ወይስ ግድያን ነው?

እዚህ ላይ ተቃዋሚዎቹ ከሁሉ የሰፋና የላቀ መርህ እንደሚከተሉ ለማለመን የጦር መሣሪያ መያዝን እና በእርሱ ላይ መደገፍን እምቢ ብንል በዓለም አገሮች መካከል ሰላም የሚያሰፍን አዲስ መግባባት እየሰፈነ የሚሄድ መሆኑን እናበስራለን ብለው ይናገራሉ:: ይህን ሲያደርጉ ብዙ ስሕተቶችን ይፈጽማሉ:: በመጀመሪያ አባባቸው ትክክል እንዲሆን በማለት «እኛ ትጥቅ ብንፈታ» «ጠላቶች» ሊሆኑን የሚችሉም «ትጥቃቸውን ይፈታሉ» በማለት አቋማቸውን ይሰፍራሉ:: እውነታው ግን «ጠላቶች» ሊሆኑን የሚችሉ ሁሉ እኛ ትጥቅ ስንፈታ እንደ ጥምጥ ይቆጥሩናል:: እነዚሁ ጠላቶች ሊሆኑን የሚችሉ ክፍሎች ስለ «ነፃነት» ስለ «ሶሻሊዝም» እና ስለ «ዲሞክራሲያዊ ጥቅም» የራሳቸው አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል:: ሁለተኛ በተቃዋሚዎቹ አእምሮ ውስጥ ስለ ሁለቱ «ሕጎች» የተደበላለቁ አባቦች አሉ:: እነዚህም ሕጎች ምድራዊና መንፈሳዊ ሕጎች ናቸው:: ምድራውያን ባለሥልጣናት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ

እንደ ቤተ ክርስቲያን ወይም ግለሰብ ክርስቲያን ማከናወን አይችሉም፡፡ ‹‹ሰይፍ በከንቱ አይታጠቅም›› በሚለው ቃል መሠረት አገር የሚመሩ ባለሥልጣናት ለመልካም ነገር ‹‹ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ›› ናቸው (ሮሜ 14÷4)፡፡ ይህ እርምጃ ግብር በማይከፍሉት ወይም ዳር ድንበርን ለክፉ አድራጊዎች ክፍት በሚያደርጉት ላይ ብቻ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ሦስተኛ የገዛ ሕሊናን ፍርድ በመከተልና መንፈሳውያን አሳቢዎች በመሆን በክፋት በተሞላውና ኃጢአተኛ በሆነው ዓለም ላይ የምንኖር መሆናችንን ማስተዋል ጥበብና መልካም ነው፡፡ ይህንን የዓለምን ክፋት ሰዎች ቀኝ ጉንጫችንን ሲመቱ የግራ ጉንጫችንን እንዲመቱ ሲናዞርላቸው ይተገበራል (ማቴ. 5÷39)፡፡ በግል ለየትኞቹም ዓይነት ክፉ አድራጊዎች ርኅሩኅ መሆን የምንችል ሲሆን ወደ ቤታችን ገብተው ሴቶቻችንና ልጆቻችንን ማጥቃት እስኪችሉ ድረስ ዝም እንድንላቸው ፈጽሞ መመሪያ አልተሰጠንም፡፡ ፍቅራችን እንዲሳቅበት የማንፈቅድ ከሆነ በራችንና አውድማችን ዳር ድንበራችን ሊሆኑ ይገባል፡፡ ምድራውያን ገዥዎች የሚመሩት አገር በሮችና አውድማዎች ጠባቂዎች ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነት ጠባቂዎች መሆን የሚያቅታቸውና የአገሪቱን በሮች ክፍት የሚያደርጉ ከሆነ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የአገሪቱ ዜጎች የውድቀታቸው ሰለባ ይሆናሉ፡፡ አገርን መከላከል አለመቻል ፍቅር ነው? ‹‹ዓለም አቀፋዊ መግባባት›› የሚገለጽበት መንገድ ነው? ‹‹ሰላምስ የሚያድግበት›› መንገድ ነው? አራተኛ የጦር መሣሪያና የጦርነት መንፈሳዊ ተቃውሞ በሁለት ሌሎች ግንባሮች ሊተገበር ይገባል፡፡ እነዚህ ሁለቱ ግንባሮች፦ የዓለም አቀፋዊ ግጭቶችንና የጦርነቶችን ጸባይ ግልጽ ማድረግ እና እነዚህን ዓለም አቀፋዊ ግጭቶች ለመፍታት የሚያስችሉ ሥራዎችን ለማጠናከር ስለ ትክክለኛና ስለ ስሕተት ጠለቅ ያለ የሥነ ምግባር ትምህርት መስጠት ናቸው፡፡ ይህም በብሔራዊ ስሜት ሽፋን ሥር ተሸሽጎ የሚካሄደው ተንኮል እና ከክፋትና ከክፉ አድራጊዎች በስተጀርባ ያለውን ክፉ ድርጊት በተገቢው መንገድ ለዓለም አቀፍ አካለት እንዲጋለጥ ማድረግን ይጨምራል፡፡

## በግለሰብ የሚደረግ ከባድ ውሳኔ

እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ እጅግ አስቸጋሪ ውሳኔ በአንድ ግለሰብ የሚወሰነው ግለሰቡ በሰላም ጊዜ ለወታደራዊ ሥልጠና በሚጠራበት ጊዜ አይደለም። እንደዚህ ያሉ ሥልጠናዎች በብዙ መንገዶች ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። ይኸውም ወታደሩ በአገር ውስጥ የእርዳታ ወይም ጦርነትን ለመከላከል በሚደረገው ዓለም አቀፍ አገልግሎት እና በመሳሰሉት ሥራ ላይ በመሠማራት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከባድ ውሳኔ ሊወሰን የሚገባው አንድ ግለሰብ አስቀድሞ በተጀመረው ወይም ሊጀመር በተቃረበው ጦርነት ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጥ በሚጠራበት ጊዜ ነው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ‹‹ይህ አገሬ ስለ ሆነ የታዘዝሁትን ብቻ አደርጋለሁ›› ማለት ብቻ በቂ ካለመሆኑም በላይ ይህን ያህል ቀላልም አይደለም። ይህንን ዓይነቱን ውሳኔ የሚቃወም ሕሊና ካለ ‹‹ለምንድን ነው?›› ብሎ ምክንያቱን መጠየቅ ያስፈልጋል። ተገቢው መልስ አስቀድሞ የተጀመረው ወይም ሊጀመር የተቃረበው ጦርነት ዓይነት ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል። በጽንሰ አሳብ ላይ ብቻ የተመሠረተ ውሳኔ ከመስመር ሊያወጣን ይችላል። ለመሆኑ ጦርነቱ ስለ ምንድን ነው? የጦርነቱስ ዓላማ? እዚህ ላይ ሁለት ምሳሌዎችን መመልከት ያስፈልጋል።

አንደኛው የአንድ አገር አገዛዝ ለብዙ ዓመታት መጥፎ ሆኖ ተቀባይነትና ድጋፍ በሚያጣበት ጊዜ ነው። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ መሪዎቹ በትናንሽ ምክንያቶች ከጎረቤት አገሮች ጋር ተደጋጋሚ ጦርነቶች እንዲነሡ ያደርጋሉ። በድንገትም ጥል ይፈጠርና ለአገሪቱ ሥጋት እንደ ሆነ ተደርጎ ይነገርና ጥሉ ወደ ትልቅ ጦርነት ይለወጣል። መሪዎቹም ‹‹እንደ አንድ ሰው ሆነን ጠላትን በመቋቋም የአገራችንን ነፃነት እናስጠብቅ›› በማለት የአገሪቱን ሕዝብ ይመጸናሉ። ፐሮፓጋንዳውና የሚጠቀሙባቸው ቃላት ዋጋ ቢስ መሆናቸውን ብዙዎች ቢያውቁም የፐሮፓጋንዳውን ባሉን ለማንሳፈፍ ድፍረቱ የሚኖራቸው ጥቂቶች ናቸው። ጥቂት ቀራጦች ማለትም ጥቂት ወታደራዊ መኮንኖች ‹‹ይህ ጦርነት ጠላትን ሰበብ በማድረግ ብሔራዊ ስሕተት ለመሸፈንና ሕዝቡን

ስለባ ለማድረግ የሚካሄድ ጦርነት እንጂ እውነተኛ ጦርነት አይደለም። በማለት በጦርነቱ ውስጥ ለመሳተፍና ለመዋጋት እምቢ ይላሉ። «ሰይጣንነት» ሲባል እስተደምጠውን በሥራ ላይ ባለው «የጦርነት ጊዜ ሕግ» መሠረት እንደዚህ ያሉ የጦር መኮንኖችና ወታደሮች በጅጉ ይቀጣሉ። ጉዳዩን በማስታተል ባለሥልጣናት መካከል የማጽዳት ሥራ ይካሄዳል። ጦርነቱ የተነገ ከሆነ ሕይወታቸውን የሚሠዉ ቢኖሩም ወደጎላ ላይ ጀግኖች ተደርገው የሚታሰቡ ጥቂት ሰዎች ይኖራሉ። በሌላ በኩል በጦርነቱ ድል በጠላት ላይ ቢገኝ ወይም ሽንፈት ቢመጣ ምን ሊከሰት ይችላል? በዚያ ዓይነት ጦርነት ውስጥ ለመሳተፍ እምቢ ያሉ ሰዎች በአገራቸው ታሪክ በታላቅ ጨለማ ውስጥ እንደሚበራ ብርሃን ተደርገው ይታያሉ። እነዚህ ሕይወታቸውን በከንቱ አሳልፈው ሰጥተዋል? ውጤቱ ምንም ይሁን ምን የክፉ መሪዎችን አካሄድ በመቃወም የተወሰደ የሕሊና ውሳኔ በለ ሆነ

ሕይወታቸውን በበጉ ደም ስለመሰከሩም፥ «እስከ ሞት ድረስ ነፍሳቸውን አልወደዱም» (ራእይ 12፥11)።

ሁለተኛው ምሳሌ፦ በይፋ በሚታወቀው መግለጫ ላይ እንደሚነገረው «ጦርነቱ ብሔራዊ ደኅንነትን ለማረጋገጥ» ነው። ይሁን እንጂ የጦርነቱ እውነተኛ ምክንያቶች ለእርሻ የሚሆን ለም መሬቶች፣ ለፋብሪካ የነዳጅ ዘይት ማውጫ መሬት፣ የማእድናት መሬቶች፣ ለጉልበት ኃይል ማግኘትና የመበዝበዝ አገልግሎት የሚውሉ የጎሳ ወገኖች ተፈላጊ ናቸው። ብዙ የተከበሩ አገሮች ከነዚህ ላላነሱ ምክንያቶች ወደ ጦርነት ገብተዋል። በብሔራዊ ጎትጎም ሽፋን የሚካሄደው የዚህ ዓይነት ዓለም አቀፍ ጦርነት ቅስቀሳ ዓላማ ለብዙዎች ግልጽ ከሆነ ይህንን አካሄድ በሚቻለው መንገድ ሁሉ የመቃወም የሕሊና ግዴታ በሁሉ ላይ የሚያርፍ ይሆናል። ይህም አካሄዱን የሚቃወሙ ቡድኖችን በማቋቋም፣ በራሪ የተቃውሞ ወረቀቶችን በማሰራጨት፣ የሕሊና ተቃውሞን በማቅረብ የሚካሄድ ነው። የመሪዎች ክፉ አካሄድ በጽሑፍ ሲገለጽ ቀላል ሲሆን ጉዳዩ በግልጽ በሚከሰትበት ጊዜ እንዴት ይሆን?

ስሕተቱ የሚፈጸመው በሰላም ጊዜ ራሳቸውን ‹‹የሕሊና ተቃዋሚዎች›› ብለው በሚጠሩት ነው፡፡ የተሳሳተና አስቀያሚ የሆነ ጦርነት በሚፈጠርበትና ወታደራዊ የአስተዳደር ሕግ በሚደነገግበት ጊዜ እነዚሁ የሕሊና ተቃዋሚዎች ተቃውሞ እያቀርቡ ይሆናል፡፡ ምናልባትም ከመፍራት የተነሣ በዚህ ዓይነት አደገኛ ጦርነት ውስጥ አንዳንዴም ምንም መከላከያ የሌላቸው ሲቪሎች በሚጠቁበት ጦርነት ውስጥ ይሳተፉ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ የቀረቡ ምሳሌዎች ምን መንገድ መከተል እንደሚገባን የሚያሳዩ ሳይሆኑ በጽንሰ አሳብና በተግባር እንዲሁም በመናገርና በተግባር በሚደረገው መካከል ያለውን ትልቅ ልዩነት ለማመልከት ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ የመከላከያ፤ የወታደራዊ አገልግሎትና ጦርነት ጉዳዮች የጦርነት ደወል በተደወለበት ጊዜ ሳይሆን በሰላም ጊዜ የሚመከርባቸውና ውሳኔ የሚደረግባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ጦርነቱ በተነሳ ጊዜ ስለ እነዚህ ጉዳዮች ማሰብ የዘገየ ጉዳይ ይሆናል፡፡ የጦርነቱ ጊዜ በአንድ ወይም በሌላ ጊዜ የድርጊት ጊዜ ይሆናል፡፡

## በእነዚህ ጉዳዮች ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ድርሻ

እነዚህን ጉዳይ በሚመለከት ቤተ ክርስቲያን በአንድ ወይም በሌላ የስሕተት መንገድ ላይ ትወድቅ ይሆናል፡፡ የፕሮፓጋንዳ ሥራ የሚሠራ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን እርሱን ተከትላ ጦርነት ናፋቂዎችን ታበረታታና ትባርክ ይሆናል፡፡ ወይም ግልጽና ድብቅ የተቃውሞ ዓላማ ካላቸው ክፍሎች ጋር ትወግን ይሆናል፡፡ ሁለቱም መንገዶች ስሕተት ናቸው፡፡ ነገሮች ሁሉ መታየት ያላባቸው ከጦርነቱ ዓይነት አንጻር ነው፡፡ በአሳብና በተግባር መካከል ያለው ልዩነትም መታሰብ አለበት፡፡ በተለይም ቤተ ክርስቲያን መንስኤ ምክንያት ነው ተብሎ በሚነዛው ፕሮፓጋንዳና ‹‹እውነተኛ›› ምክንያት መካከል ያለውን ልዩነት መመርመር አለባት፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ለብሔራዊ ጥቅም ነው ተብሎ በሚነገረው ነገር በስተጀርባ ግልጽ የሆነ ራስ ወዳድነትን፤ ስስታምነትንና የሥልጣን ጥመኝነትን እናገኛለን፡፡ ዓላማው ይህ

ክሆን ወደ ጦርነት ከመግባቱ በፊት የእንግሊዙ ሕዝብ ሲነገረው ይገባል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከየትኛውም አካል ይልቅ በብሔርተኝነት ጉሮጉ ጋንንና በእውነተኛ የዜጎች ፍቅር፤ እስፈላጊ በሆነው የራስን አገር መከላከልና በጎረቤት ወረራ መካከል ያለውን ልዩነት መለየት አለባት፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ቤተ ክርስቲያን የማይሰካለት ክሆነ የመሪነት ሚናዋ ወዴት አለ?

ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊና አስቸኳይ የሆነ ሌላም ነገር አለ፡፡ ይኸውም በዚህ ዓለም ይሁን በሚመጣው የሰው ሕይወት ትልቅ ዋጋ ያለው መሆኑን በሁሉቱም ድንበሮች ላይ ለሚኖሩ ሕዝቦች ክብደት ተሰጥቶት መነገር ያለበት መሆኑ ነው፡፡ የሰው ሕይወት መጠበቅና በጨካኝ መሪዎች ፍላጎት ሳይሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በራሳቸው የሕይወታቸው ባለቤት በሆኑ ሰዎች ፈቃድ ሕይወታቸውን ለአገራቸው ለመስጠት የተጠሩ መሆናቸው

በመሆኑ ጊዜ መስዋዕትነት ... የሆኑ ክርስቲያኖች ስለ እውነትና ስለ ክርስቶስ ሕይወታቸውን አሳልፈው በመስጠት የታሪክን አካሄድ ለውጠዋል፡፡ ክርስቶስም «ደቀ መዝሙር ከመምህሩ፥ ባሪያም ከጌታው አይበልጥም፡፡ ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ፥ ባሪያም እንደ ጌታው መሆኑ ይበቃዋል» (ማቴ. 10፥24-25) ባለ ጊዜ ያደረገው ይህንኑ ነበር፡፡ «ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» (ዮሐ. 15፥13)፡፡

## በድህረ ጦርነት ጊዜ

ማንኛውንም ዓይነት ጦርነት መቃወምና በሚቻለው መንገድ ሁሉ የጦርነትን ሀሳቦች መርዳት በነ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ሁሉ ግዴ ነው፡፡ በቀድሞ ዘመን ለስደቶች የነበረው የማምለጫ መንገድ እንደ ብቻ ነበር፡፡ እርሱም በቅርብ ያለውን ድንበር አልፎ ወደ ጎረቤት አገር መሰደድ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን የተሻሻሉ የመጓጓዣ ዘዴዎች ስላሉ ከሌላኛው የዓለም ጫፍ

ችግሩም ብዙ ገጽታዎች አሉት። ረሃብ፥ በሽታ፥ የሰብአዊ መብት መጣፋት፥ ሰብአዊ እርዳታ ፍለጋ፥ በተቀባዮችና አገሮች መካከል ትብብር አስፈላጊ መሆን እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። የተሰደዱ ችግሮችም ሊኖሩ ይችላሉ። ችግረኞች አዲሱ አገራቸው እንዲሆን ወይም ሊፈልጉትና ስደተኞችን በመቀበል ወይም ተወቀው አገር ለመድረስ ብዙ ድንበሮችንና ውቅያኖሶችን ያቋርጣሉ። አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን «ስደኞች» ብለው የሚጠሩ ሰዎች ከአገራቸው ለመልቀቅ የሚያስገድዳቸው አስቸኳይ ምክንያት ላይኖራቸው ይችላል። ይልቁንም ኢኮኖሚውን በመጠቀም በተሰደ በኢኮኖሚ ምክንያት የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ሊሰደዱ ይችላሉ። የስደተኞችን ጉዳይ አያያዝ ውስብስብ የሚያደርገውም ይህ ነው። ስደተኛው የቱ እንደ ሆነ የቱ ስደተኛ እንዳልሆነ ሊያረጋግጥ የሚችል ማን ነው? እንደዚሁም ስደተኞቹ ከአገራቸው ለመውጣት በሚሞክሩበት ጊዜ ለራሳቸው ንግድ በሚፈልጉ ሰዎች እጅ ይወድቃሉ

[illegible] ይወድቃሉ። በዓመት ወደ [illegible] ብርቱ ትግር ሆኖ በየአገሩ የሚታየው ችግር ይህ ነው።

## ጦርነቶች ሁሉ ወደ ፍጻሜ ሲመጡ

በብዙ የመልካም ምኞት ባለቤቶችና በጎ አድራጊዎች መካከል የሚነገር አንድ ነገር አለ። እነዚህ ወገኖች «ጦርነቶች ሁሉ መቆም» እንዳለባቸው ትልቁ ጠንጋታቸው ነው። ይህ ሐሳባቸው መልካም ይሁን እንጂ በተጨባጭ እውነት ላይ የተመሠረተ አይደለም። እንዲህ ዓይነት አባባሎች በዓለም ያለውን ክፋትና ሰው የሚገኝበትን ተጨባጭ ሁኔታ በትክክል አያገልጹም። ክፋት እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ይኖራል። የዓለም መጨረሻም ከመምጣቱ በፊት ክፋት እየባሰበት ይሄዳል ማቴዎስ 24። ስለዚህ ነገር ምን ማድረግ እንችላለን? ኢየሱስ ተስፋችሁ ማለት እንችላለም፤ እርሱ ጦርቶች እንደሚኖሩ ይናገር እንጂ እኛ ጦርነትን ጨርሰን እናጠፋለን ብለን መኩራራት አንችልም። በእርግጥ ጦርነቶችን ማገድ፥ ወይም ማምከን፥

ወይም የሚያስከትለውን የከፋ ውጤት መቀነሰ ግዴታችን ነው። እንደዚሁም ዓለም አቀፍ ግጭቶችን ለማስወገድ ጦርነትን እንደ መሣሪያ አድረገን መጠቀምን ማስወገድ አለብን። ጦርነትን ለማስወገድ ምንም ነገር ብናደርግ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ጦርነቶች ይኖራሉ።

ክርስቲያኖች እንደመሆናችን ምን ማድረግ አለብን? የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን አካላት እንደመሆናችን መጠን ሊከሰቱ ስለሚችሉ ዓለም አቀፍ ግጭቶችና ቀደም ተብሎ ስለ ተካሄዱት ጦርነቶች ተጨባጭ የሆነውን ትምህርት መስጠት አለብን። በትምህርታችንም የሁሉም ክፋቶች ምንጭ ‹‹በጄኔራሎቹ›› ወይም እንደሚባለው ‹‹ለጦርነት በሚውለው ብሔራዊ በጀት›› ውስጥ ሳይሆን በእኛው በሰው ልጆች ውስጥ እንዳለ ለራሳችንና መድረስ ለምንችላቸው ሁሉ ማስተማር የመጀመሪያው ግዴታችን ይሆናል። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተሳሳተ ነገር ካለ ስሕተቱ በሰው ውስጥ ካለ አንድ ዓይነት ክፋት የተነሣ ይሆናል። ይህ እውቀት የመወሰን ሥልጣን ባላቸው ዘንድ ተቀባይነት ቢያገኝ ብዙ እሰጣገባዎችና ጦርነቶች ይቀሩ ነበር። በክፉ ቀን ለመቃወም ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ጦር ዕቃ ሁሉ አንሡ (ኤፌ. 6÷13) ተብሎ እንደ ተጻፈ ተገቢው ክርስቲያናዊ ትምህርትና መረጃ ብዙዎች የሕይወታቸውን መንፈሳዊ መሠረት እንዲፈልጉ ይረዳቸዋል።

# ምዕራፍ 13

# አብዮት

አብዮት ስሜትን በሚያነቃቃ ብርሃን ወይም ልብስ ውስጥ የተሸፈነ ነው። ሰዎች አብዮት ናፋቂዎች በሚሆኑበት ጊዜ አብዮቱ በጥቂት ጀግኖች መሪነት በኅብረተሰቡ መካከል ያለው ክፋት የሚወገድበት፤ አዲስ ዘመን ለሕዝቡ የሚመጣበት፤ ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ የሚበለጽግበትና ደስተኛ የሚሆንበት እንዲሁም ስለ ሆነለት ነገር የሚያመሰግንበት አስደናቂ ለውጥ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ።

ብዙ አብዮቶች ፍትህ አልባውንና ሙስናን ማስወገድን፤ አላስፈላጊ ጦርነቶችን እና የመሳሰሉትን ማቆምንና የተሻለውን ለውጥ ማምጣትን ዓላማው ባደረገ ራእይ የተጀመሩ ናቸው። አንዳንድ አብዮቶች ደግሞ ዝርዝር በሆኑ ተጨባጭ እቅዶች የተጀመሩ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ የአብዮቱ መሪዎች ሕዝቡን የሚያነቃቁ አሳቦች ያላቸው የቀን ሕልመኞች ይሆኑና ‹‹የአገሩ ታዳጊዎች›› ‹‹የሰፊው ሕዝብ ጀግኖች›› ተብለው እስከ መጠራት ይደርሳሉ። አብዮቱ ሲከሰት ግን የጀመሩትን ለመቈጣጠር ችግር ውስጥ ይገባሉ። ከዚህ የተነሣ አብዮቱን ሲጀምሩ ላላለሙት ነገርም መሳሪያ ይሆኑና የተነሡለትን ዓላማ በሚያበላሽ አሠራር ውስጥ ይወድቃሉ። አብዮቱም እንደ ጎርፍ በራሱ መንገድ የሚሄድ ይሆናል።

## ሰፊው ሕዝብ እንዴት ወደ ስሕተት እንደሚመራ

አብዮትን በመደገፍ ከሚደረጉት ተገቢ ክርክሮች አንዱ የተለመደውና እንዲህም የሚገለጽ ነው። እርሱም ‹‹በአንድ አገር ውስጥ ያለው ነገር ምንም ዓይነት የለውጥ ተስፋ የሌለውና አስፈሪ ከሆነ፤ ለአገራቸው ሕዝብ የሚያዝኑና ሊታደጉአቸው ቃል የሚገቡ ከሆነ የአብዮቱን መሪዎች መከተል ትክክል አይደለምን?›› የሚል

ነው። እዚህ ላይ እጅግ ደካማው አመለካከት ሕዝቡ በአብዮቱ መሪዎች ቃላት፣ ዝንባሌ፣ ስሜትና ተስፋ ላይ መመርኮዙ ነው። ነገሩን በግልባጩ ማየትም መልካም ነው። አብዮቱ «ደም፣ ላብና እምባ» ከሕዝቡ የሚጠይቅ መሆኑን ስለሕዝብ የሚናገር መሪ የት አለ? ለብዙ ዓመታት በሚቆይ ከባድ ሥቃይ፣ ረሃብ እና ቦርነት እንዲሁም ከበፊቱ በከፋ ሁኔታ ውስጥ እንደሚያልፍ መሪው ለሕዝብ አስቀድሞ ያናግራል? አብዛኛውን ጊዜ መሪው ቀደም ብሎ ለሕዝብ የሚናገረው ተቃራኒውን ነው። ሕዝቡ እርሱን ቢከተለው ሥቃይ እንደሚያበቃና በምትኩ የበለጸገ ጊዜ እንደሚመጣ ቃል ይገባል።

የአንድ አብዮት ዓላማ ምን እንደ ሆነ እስኪደረስበት ድረስ ለማወቅ አይቻልም። የከሸፉ አብዮቶችን ከተመለከትን ውጤታቸው አብዮቶቹ ከመጀመራቸው በፊት ከተነገሩላቸው ዓላማ የተለየ [illegible]

[illegible]

መሆኑን [illegible]
ምክንያት ግልጽ ምቀኝነት፣ የሥልጣን ጥመኝነት እና አንዳንድ ሰዎችን ለመበቀል ነው። በሌላ በኩል የተሳካላቸውን አብዮቶች ስንመለከት ደግሞ ዓላማቸው ወይም ግባቸው ሥር ነቀል የሆነ ለውጥ አያመጡም። ከተገባው ተስፋ አንድም አይፈጸምም፣ ይልቁንም ቀደም ብለው የነበሩ ሠራተኞችና ድሆች ኑሮአቸው እየከፋ ይሄዳል። አብዛኛውን ጊዜ የሚታየው ወገናዊነት፣ ሙስና ከእርሱም ወደ አዲሶቹ መሪዎች መዛወሩ ብቻ ነው።

የአብዮቱ ጀግኖች የውሸት ተስፋ ሲጋለጥና የውሸት ደመኝ ሲገለጥ ማንኛውም ሰው ሊያይ የሚችለው ምን እንደ ሆነ ማብራራት አስፈላጊ አይደለም። ከአብዮቱ በኋላ ምን ይከሰታል? ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው የተለመደው መልስ «የተሻለ ሆኖ ያገኘው ምንም ነገር የለም፣ ይልቁንም የነበሩ ችግሮቻችን ከበፊቱ ይልቅ የተባባሱ ከመሆናቸውም በላይ ብዙ አዳዲስ ችግሮችም ተጨምረዋል» የሚል ይሆናል።

«ለውጦች» በብዙ አብዮቶች ፕሮግራሞች ውስጥ ስለ ተካተቱ እንደዚህ ያሉ መረጃዎች ስለ አብዮቶች መሰጠቱ [illegible]

የሚገርም ነው። ከዚህም የተነሣ ሌላም ጥያቄ ሊጠየቅ ይገባል።

ከብዙ አብዮቶች በኋላ ምንም የተሻለ ለውጥ የማይመጣ ከሆነ ታዲያ ሕዝብ ለምን ሥቃይና መከራ ይደርስበታል? አብዮት ስለሚያስከትለው ውጤት መረጃ ቢኖራቸውም ብዙዎቹ «ለውጥ» ለማምጣት ብቻ አዲስ የአብዮት እንቅስቃሴ ይጀምራሉ። አብዮቱ ሲታቀድ «ለምን?» ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል። ለተሻለ ወይስ «ለከፋ» ውጤት? በጣም ብዙ የሆኑ ሕዝቦች ከአብዮቱ በኋላ በመሠረቱ ሁሉም የተዘረፉ፤ አዳዲስ ሰዎችን ትላልቅ ማንኪያና ሹካ የያዙ መሪዎች በሥልጣን ላይ መቀመጣቸውን ይመለከታሉ። ሕዝቡ የከበዱ ችግሮች ሁሉ ይወድቃል። በእርግጥ ከአብዮቱ በኋላ ለውጥ ይኖራል። ነገር ግን ለውጡ በራሱ ምንም ችግር አይፈታም። ጉዳዩ የሚያስመሰግነው አብዮቱ ከመጣው ውጤት አንጻር ነው።

## ፖለቲካዊ አብዮት በጤናማ ሂደት የለውም

የትኛውም ሰብዓዊ ማኅበረሰብ ያለ ፍትህና ሥነ ሥርዓት ሊኖር አይችልም። እንደዚህ ያለው ሂደት ደግሞ ሕጎች፣ ፍርድ ቤቶች፣ ፖሊስ እና ሥርዓትን የሚከተል የሕዝብ መንግሥት አስፈላጊዎች ናቸው። ነገር ግን የሚሠራ ሕግ ሳይኖር ሕዝብ ለማን ሊታዘዝ ይችላል? ወይም ሥነ ሥርዓት ያለው ነገር ከየት ሊመጣ ይችላል? አብዮት ሲከሰት አብዛኛውን ጊዜ ቀድሞ የነበሩት ሕግጋት በሰሚሽሩ አዲስ ሕግ እስከሚወጣ ድረስ ሰዎች ሊከተሉአቸው የሚገባቸው ሕጎች አይኖሩም። እንግሊዛውያን ሰው እንዴት አድርጎ ያለ ሕግ ሊኖር ይችላል? መልሱ ከአብዮቱ በኋላ «የወታደር አስተዳደር ሕግ» ወይም የአብዮቱ መሪዎች «በአዋጅ» አገሪን ያስተዳድራሉ ማለት ነው። ይህም ማለት የመሪዎቹ ቃላት እንደ ሕግ የሚያገለግሉበት አሠራር ይሰፍናል ማለት ነው።

ስለሆነም ሕዝቡ የሚሠራ ሕግ ወደሌለበት፣ ተገቢው ነገር ምን እንደሆነ ማንም ወደማያውቅበት፣ በሕግ መሠረት የሚሠሩ ፍርድ ቤቶች ወደሌሉበት ወደዚህ ሁኔታ እንዴት ሊደርስ ይችላል? የአብዮቱ አቀጣጣዮችም ሆኑ አሳባቸውን የሚደግፉ ሌሎች ሰዎች

ሕግ እስተድምሮውን ተግናአልና ከእንግዲህ ወዲህ ፍትህ በእጁሩ የለም ሊሉ ይችላሉ። እነርሱ ይህን ያበሉ እንጂ ተቃራኒውን የሚናገሩ ብዙዎች ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ድክመቶች ስላሉ በሕጉት በተደጋጋሚ ይፈጸማል። የአብዮቱ ጀማሪዎች አብዮቱን ወይም በእነርሱ ላይ የተላለፈውን የፍርድ ቤት ውሳኔ ሰበብ ያደርጋሉ። ወደ ወኅኒ ቤት እንዳይወርዱም ሥርዓቱንና ፍርድ ቤቶችን በሙሉ ለመገልበጥ መሣሪያቸውን ይናገራሉ። በዚህም ምክንያት የራሳቸውን ጥቅም ለመጠበቅና ለደጋፊዎቻቸው እርካታ ለማስገኘት ሲሉ ፍትህን ከመጠበቅ ይልቅ ነባሩን ሥርዓት ይገለብጣሉ።

ይህንን አስመልክቶ አብዮቱን በማግኘን የሚነገረውን የሚቃረኑ ሐቆች አሉ። አብዛኛውን ጊዜ ስለ አብዮቱ ጎልማ ሲነገር ፍትህን፣ ሰላምንና ሥርዓትን ያለበትን አመራር ለማምጣት [illegible]

[illegible]
ከአብዮት በፊት በነበረው ሥርዓት ሁከት ችግር ቢኖርበትም በአብዮቱ ምክንያት የበለጠ እየተባባሰ ስለሚሄድ ጭቆና ሕዝብ ከአብዮቱ የሚያገኘው ጥቅም ምንድን ነው?

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ አለ፡ «የፍትህ ሥራ የተቋረጠ» መሆኑን በትክክልና በእርግጠኝነት የሚገነዘበው ማን ነው? እንደዚህ ሰፊና አስቸጋሪ የሆነውን ለመመርመር ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ምን ዓይነት ናቸው? የፍትህ ሥራ ተቋረጠ የሚለው አባባል ሕጉ ተቀባይነት አጣ የሚለውን አሳብ የሚይዝም ነው። ይህም ሙግት ሲፈጸም ዕትዳቸውን በሚነድፉበት ጊዜ መጀመሪያ የሚጠቀሙበት ክርክር ነው።

አብዮት ቢያንስ 75% አዲስና የተሻለ ነገር ቢያመጣ ለአብዮቱ የሚሰጠው ድጋፍ የበለጠ ከብዶት ይቀረፋል። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው የዚህ ተቃራኒ ነው። በአብዮቱ ወቅትና ከአብዮቱ በኋላ ሕግና ሥርዓት እየተባባሰ ይሄዳል። ይህ የሕግና የሥርዓት መበላሸት ተመልሶ መሻሻል እስከሚጀምርበት ድረስ ይዘልቃል። እንዲህ ከሆነ አብዮቱ ስለ ሕጋዊነትና ሥርዓት ለለው-

## የአብዮትን መጀመር የሚቃረኑ ተጨማሪ አሳቦች

አንድ መሪ ሕዝቡ ወደ አጠቃላይ ግራ መጋባትና ሕገ አልባነት የሚገባበትን አብዮት የሚጀምር ከሆነ ይህ አካሄድ እንዴት ሊደገፍ ይችላል? አብዮት ማለት አብዛኛውን ጊዜ ለመቈጣጠር የማይቻሉ ኃይሎች መለቀቅ ማለት ነው። በእንደዚህ ሁኔታ ውስጥ አብዮቱን የመቀልበስ ዓላማ፤ በአብዮቱ ውስጥ ሌላ አብዮት መፍጠር እና በድንገት በአዳዲሶቹ መሪዎች መካከል የሚካሄድ መፈንቅለ መንግሥት ሊከሰት ይችላል። ይህንን በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ቀጥሎ ያለውን ምሳሌ እንመልከት።

በችግር ጊዜ በትክክል በሚሠራ ዲሞክራሲ ውስጥ የተሻለ ዲሞክራሲን ለመመሥረት በሚደረገው ጥረት ውስጥ አንዱ መሪ ከሌሎቹ አይሎ ይወጣና እንደ ዋና መሪ ሆኖ ነጥሮ ይወጣል። በዚህን ጊዜ አብዮቱ ከታለመለት ግብ ተቃራኒ ወደ ሆነው አቅጣጫ ያመራል። በብዙ አብዮቶች ውስጥ የሚታየውም ይኸው ይሆናል። ውጤታቸው አስቀድሞ ከተነገረላቸው ውጤት ውጭ ይሆናል። ሌላው አስደንጋጭ ምልክት ቀጥሎ ያለው ነው። አብዮት ማድረግ እንደሚቻል እየተነገረ ባለበት ጊዜ ‹‹አንደበትን ሊገራ ማንም አይችልም፤ የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፉት ነው›› ያዕቆብ 3፥8 እንደተባለ ሁሉ ምላሳቸው ያልተገራ ሰዎች ይፈለጋሉ። ሕዝባቸውን ወደ አብዮቱ ለመውሰድ የሚፈልጉ ሰዎች አብዮቱ እስኪጠነክር ድረስ ዓላማቸውን በምስጢር ይይዛሉ። እንግዲያውስ እነዚህ በቅድሚያ የማይታዩ ኃይሎች በአብዮቱ ጊዜ ተግባራዊ የሚያደርጉትን አሳብ ግልጽ እንዲያደርጉት እንዴት ማድረግ ይቻላል? የሚል ጥያቄ አለ።

ከክርስቲያናዊ አመለካከት አንጻር ሁለት ነገሮች ትኩረት ሊደረግባቸው ይገባል። አንደኛው ‹‹ከእግዚአብሔር ካልተሰጠ በቀር ሥልጣን የለም፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው›› ሮሜ 13፥1 የሚለው ነው። አንዳንድ ጊዜ ይህንን ማመን ከባድ ቢሆንም በቀዳሚው ብልሹ አስተዳደር ላይ በማመፅ እርሱን በሌላ የከፋ አስተዳደር ለመተካት የሚፈልጉ ‹‹ይህንን ለምን አደረግን›› ብለው ራሳቸውን መጠየቅ አላባቸው።

ስሕተታቸውን ባዩና በተቀበሉ ጊዜም አዳዲሶቹ መሪዎች ተደላድለው ስለ ተቀመጡ ለውጥ ለማምጣት ማድረግ የሚችሉት ምንም ነገር አይኖራቸውም። አብዮት እንዲጀመር መታገሉ የማይረዳቸው ከሆነ ሕዝቡ ምን ማድረግ ይችላል? እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ 1 ቆሮ. 14÷33 ስላልሆነ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም ለሰላማዊ ለውጥና መሻሻል ደረጃ በደረጃ መሥራት ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትእግሥት በማጣት በመሪዎቹ ላይ የሚያምጹ በሚቀጥለው ትውልዶች ውስጥ መሻሻልን ሳይሆን ብዙ የሆኑ ቀጣይ አብዮቶችን የሚያስተናግዱ ይሆናሉ። ስለዚህ በክርስቲያናዊም ሆነ በዓለማዊ አመለካከት እንዲህ ብሎ መደምደም ይቻላል። ጠንካራ ምክንያት ከሌለ አብዮት መጀመር ምንም ተቀባይነት የለውም።

## አብዮት ተቀባይነት የሚኖረው በምን ሁኔታ ውስጥ ነው?

በአንድ አገር ውስጥ ያሉ ሁኔታዎች ሁሉ እየተባባሱ ወደ ውድቀት የሚደርሱባቸው ሁኔታዎች አሉ። ይህም ማለት ሕግና ሥልጣን አይኖሩም ማለት ነው። ‹‹ከጫካ ሕግ›› በስተቀር ምንም ሕግ የሌለበት ጊዜ ይሆናል ማለት ነው። ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ ለውጥ ፈልጎ እያለ ምንም ነገር ከባለሥልጣናት ሳይታይ ሲቀር አንድ ነገር መደረግ አለበት። ምናልባት ብዙዎች ‹‹ይህንን አገር ሊታደግ የሚችለው አብዮት ብቻ ነው›› ይሉ ይሆናል። ይሁን እንጂ አማራጭ ይኖራል። በዚህን ጊዜ አገሪቱን የማንቀሳቀስና እንደገና የመቅረጽ አመራር ሊወስዱ የሚችሉ የተከበሩ ግለሰቦች መኖር አስፈላጊ ነው። ይህ አብዮት ሳይሆን የአገሪቱ አዲስ መወለድ ነው። እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ጥቂቶች ባልሆነ አገሮች ውስጥ ተከስተዋል። እንዲህ ባሉ ለውጦችና አብዛኛውን ጊዜ አብዮት ብለን በምንጠራው ክስተት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? በአብዮት ውስጥ እውነታዎች ባለ ብዙ ፈርጅ ትርጉም ይሰጣቸዋል። ይህም ማለት ከሁሉም እውነታዎችና መረጃዎች በመነሣት ወደ ልዩ ልዩ መደምደሚያዎች ይደረሳል ማለት ነው። ‹‹አዲስ ልደት›› ተብሎ በሚጠራው ክስተት ውስጥ ግን

ብዙ ትርጉም የሚሰጠው ነገር አይኖርም። በተጨማሪም ከዚህ በፊት እንደታየው ሁሉ አብዮት ጀመሪ የሆኑ ሰዎች ለሚመሩት እንቅስቃሴ ብዙ ትርጉም የሚሰጡት በልዩ ልዩ ምክንያቶች ነው። አንድ አገር በውድቀት አፋፍ ላይ በሚሆንበት ጊዜ ያንን አገር እንደገና እንዲያሰራራ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ግን የተለየ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ አዳዲስ የሆኑ መሪዎች ራሳቸውን የመረጡ ሳይሆኑ ሌላ ምርጫ ስለታጣ ለአገሩ የሚያስፈልገውን የጥገና ለውጥ ለማምጣት በሕዝቡ ጥሪ የተደረገላቸው ናቸው። እነዚህ አዳዲስ መሪዎች ምንም የተደበቀና ግልጽ ያልሆነ ዓላማ የሌላቸው ናቸው።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያለ ሕዝብ አብዮት በሚመስል እንቅስቃሴ ውስጥ ራሱን የሚያገኝበት ነጥብም አለ። ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ቀውስ በሚፈጠሩበት ጊዜ አንዳንድ ክፉ የሆኑ ኃይላት ብቅ የሚሉበት ክፍተትም ይኖራል። ለራስ ጥቅምና ሥልጣን የሚደረግ ሩጫም አለ። በብጥብጡ ውስጥ ከአንዳንድ ጠላቶች ጋር የነበረውን የቆየ ጉዳይ የማስተካከል እድሎች ይኖራሉ ብለው የሚያስቡም ብዙዎች ይኖራሉ። እንደዚሁም ከጅምሩ ጥንቃቄ ካልተደረገ ወንበዴዎች ወይም ለተቃውሞ የወጣ ሕዝብ ሥልጣን በእጁ የሚያደርግበት ሁኔታም ይኖራል።

## አብዮቶች ሁሉ የማያስፈልጉ እንዲሆኑ የሚደረግበት መንገድ አለ?

አስፈላጊ የሆኑ፤ የማያጠራጥር ዓላማና ስኬት ያላቸው፤ ለሕዝቡም የተጠበቀውን መልካም ውጤት የሚያመጡ አብዮቶችን ምሳሌ ማግኘት አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ አብዮቶች ባይኖሩ በዓለም ላይ የተሻለ ነገር እናደርጋለን ብለን ለመናገር እንፈተናለን። ይሁን እንጂ ብዙ አብዮቶች ይከሰታሉ። ይህም የሚሆነው ለምን እንደ ሆነ ማብራራት ቀላል ነው። ለአብዮት መፈጠር ሁለት ምክንያቶች አሉ። እነርሱም በአንድ በኩል በብዙ የዓለም ክፍሎች ላይ ብዙ ክፉ ገዥዎች በመኖራቸው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በአብዮት ውስጥ ወደ ሥልጣን ቢመጡ የተሻሉ መሪዎች

እንደሚሆኑ የሚያስቡ የሥልጣን ጥመኞች በመኖራቸው ነው። በእነዚህ በሁለቱ መሪዎች በስተጀርባ አንድ የሚያመሳስላቸው ነገር አለ። ይህም ከሚመሩት ሕዝብ ጋር የሚጋሩት በሰው ልጆች ሁሉ ውስጥ ያለው ነፋት ነው። ይህም ማለት ምንም እንኳ ብዙ መልካም ነገር ቢኖራቸውም ሕዝቡ በልባቸው ውስጥ ሰብአ [illegible] አስተሳሰቦች የተጋለጡ መሪዎች ይኖረዋል ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ በአብዮቱ አማካይነትም ይሁን በሰላማዊ ሂደት ውስጥ ራስ ወዳድ ያልሆኑ ፍጹማን መሪዎችን ለማግኘት መጠበቅ ከንቱ ድካም ይሆናል።

በአዲስ አብዮት ሰበብ የሚፈጠረውን አደጋ ለመከላከል ምን መደረግ አለበት? በመጀመሪያ ስለ መንግሥትና ስለ ዜግነት ጥሩ ትምህርት እንዲኖረን ያስፈልጋል። በአንድ ወይም በሌላ አገር ውስጥ ዜጎች ነን። በዚህም ስለ ራሳችን ጉዳይም ሆነ ስለ ማኅበረሰቡ ኃላፊነት አለብን። አንድ ስሕተት በተፈጸመ ተግባር [illegible] ነው በማለት በስልጣናቸው ገዢዎችን

ተጠያቂ የማድረግ አደጋ አለ። ነገር ግን «እነርሱ» «እኛ» የተለዩ አለመሆናቸውን ማስታወስ ይኖርብናል። ምክንያቱም ልክ እንደ እኛው የማኅበረሰባችን አካል ስለ ሆኑ ነው። ስለዚህ የእነርሱ ኃላፊነት የእኛ ቢሆን በተጋለጡበት ደግሞ የእኛ ኃላፊነት የእነርሱ ነው። ዜጎች ሁሉ ባለሥልጣኖቻቸውን ከመተቸት ይልቅ እንደ የበላይነታቸውና ሕሊናቸው መሪነት በሥነ ታቂ ቢሆኑ መሪዎቻቸውን ቢያግዙ ለአብዮት መንስኤ የሚሆኑ ምክንያቶች ሁሉ ይወገዳሉ። ተቃውሞዎች ቢኖሩ ሕዝቡን ለአመጽ የሚያነሣሡ ከሉ እውነተኛና እውነተኛ ያልሆነ ነገር የቱ እንደ ሆነ ለይተን ማወቅ አለብን። አንድ ነገር በእውነት ስሕተት ሆኖ ከተገኘ ፈውስና ለማግኘት መፍትሔ መፈለግ ይኖርብናል። አብዮትን መፍራት የቀን ሕልም ብቻ ሳይሆን እጅግ አስቸጋሪ የሆነውን ሁኔታ ያውም የማያውሩ፤ የከፋ ሁኔታን የሚያስከትል በመጨረሻም ወደ አደገኛ ሁኔታ የሚጨምር ሁኔታን እንደ መፍራት ነው። አብዮት አብዛኛውን ጊዜ ተከፋፋይነትና አደገኛ መሣሪያ ነው። ከተጨማሪ ሁሉም ከሆነ እንዲት ተግባራዊ እንደሚሆን፤ በተግባራችን እጅ መሣሪያ ሥር እንደሚወድቅ ማንም

ሊያውቀው አይችልም፡፡ በተጨማሪም ከቊጥጥር ውጭ ከወጣ ለመፊወስ የብዙ ትውልዶችን ዘመን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

## የክርስቲያኖችና የቤተ ክርስቲያን ልዩ ጥሪ ወይም ግዴታ

ከላይ በገጽ 50 የተገለጸው የሁለቱ ማለትም የምድራዊውና የመንፈሳዊው ሕግ መርሆ እዚህም ላይ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ አብዮትን መምራት ወይም ሕዝቡ አብዮት እንዲጀምር መምከር የክርስቲያኖች ወይም የቤተ ክርስቲን ሥራ አይደለም፡፡ የመጀመሪያውና ዋናው የቤተ ክርስቲያን ሥራ ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው ሮሜ 13÷1 ለሚለው ቃል ትኲረት መስጠት ነው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች የሚመለከት ሁለተኛው መርህ በመሪዎች ድርጊት ውስጥ ጤናማ ያልሆኑና ኢ-ፍትህ የሆኑ ነገሮች ሲከሰቱ ጨዋነት በተሞላበት መንገድ በጽናት ለመሪዎቹ መንገር አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም አብዮትን ለመከላከል ዋስትና ያለው አካሄድ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፤ ካህናት ወይም ካህናት ልሆኑ ሰዎች የነቢይነት ድምፅ በማሰማታቸው ወደ ወኅኒ ቤት ቢጣሉ ይህ የሚሆነው ሥራቸውን በመሥራታቸው ብቻ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ቤተ ክርስቲያን ስሕተትን በመቃወም ድምጿን የማታሰማ ከሆነ ክፋትን እያየች ዝም በማለትዋ ክፉ ሥራ ከሚሠሩት ጋር በመቈጠር ተጠያቂ ትሆናለች፡፡

እንዲሁም አብዮቱ በሚካሄድበት ጊዜም ሆነ ከአብዮቱ በኋላ የሚከሰት ክፋት ሲኖር ቤተ ክርስቲያን የተቃውሞዋን ድምፅ ለማሰማት ዝግጁ መሆን ይጠበቅባታል፡፡ ይህንን የሚታደርግበት ሁለት ምክንቶች አሉ፡፡ አብዮቱ ቢከሽፍና ክርስቲያኖችና ቤተ ክርስቲያን ደም ሲፈስና ሌላም የጭካኔ ተግባር ሲፈጸም አይተው የማይቃወሙ ከሆነ የንጹሐንን ደም ራሳቸው እንዳፈሰሱ ተደርጎ ደሙ በእጃቸው ላይ ይሆናል፡፡ እንደዚሁም አብዮቱ በመጀመሩ ሂደት ወይም ባስከተለው ስሕተት ውስጥ ተሳታፊ እንደሆኑ ተደርገው ይጠረጠራሉ፡፡

ሁሉንም አጠቃለን ብናየው ሰውዮን በማኅበረሰቡ ውስጥ ወይም በግለሰብ ላይ ለማምጣት አብዮትን እንደ መሣሪያ ከመጠቀም ይልቅ ሌላ አማራጭ አለ። እርሱም ሰላማዊ ንቃትና ትብብርን ለጋራ ግብ መጠቀም ነው። ይህም ግብ በዚህ ትድለት በሚበዛበት ዓለም ውስጥ እስከ ተቻለ ድረስ ፍትሐዊና ትክክለኛ የሆነ ማኅበረሰብ መገንባት መሆን አለበት።

# ምዕራፍ 14

## ትምህርትና ሥልጠና

የባህልና የሥልጣኔ ጉዳዮች በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ አንዳንድ ችግሮችን ይፈጥራሉ። በብዙ የሰው ሕይወት ውስጥ እንደሚሆነው ሁሉ እዚህም ላይ «በዓለም ውስጥ በመሆን» እና «ከዓለም በመሆን» መካከል ጠባብ መተላለፊያ መንገድ አለ። (ከላይ ገጽ 75ን ተመልከት) በዓለም ላይ መኖር ክርስቲያኖችንም ጨምሮ ከሁሉም ዜጋ ብዙ ነገርን ይጠይቃል። ክርስቲያን መሆን ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ለመረዳት ደግሞ እውቀትን ይጠይቃል። እውቀት የሚመጣው በአንድ ወይ በሌላ መንገድ ከትምህርትና ከሥልጠና ብቻ ነው። ጥሩ ዜጋ መሆን በሁሉ በመንግሥት ላይ የተመሠረተ ሆኖ አንዱ ሌላውን ማገልገልን ይጠይቃል።

ትምህርት አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ማንበብን የሚማሩበት መንገድና ከመጽሐፍት ብቻ የሚገኝ ነገር አድርገው ይረዱታል፤ ይለማመዱታልም። እንደዚህ ያሉ በሕብረቶች በብዙ አገሮች የክፋት ሥር ሆነው ግድለሽነትን፤ ለውጤት ብቻ መጓጓትን፤ ወይ አንዳንድ የትምህርት ተቋማት ለመግባት መሽቀዳደምን እና ለአንዳንድ የአስተማሪነት ቦታዎች መራኮትን አስከትለዋል።

ሁሉም የትምህርት ዓይነትና ደረጃ ኃላፊነትና ዓላማ ያለው መሆን አለበት። መማርና ማጥናት በራሳቸው ግቦች አይደሉም። አንድን ነገር ለመረዳትና ለማወቅ ራስን ማዘጋጀትና ሌሎችንም እንዲረዱና እንዲያውቁ ለማድረግ እንዲሁም ሁሉንም በማጣመር ለማኅበረሰብና ለሰዎች ሁሉ ጠቃሚ ሆኖ መገኘት አስፈላጊ መሆኑን በተለይ ሊረዳ ይችላል። ትምህርት አብዛኛውን ጊዜ በሕብረት የሚከሰትበትና ሁለተኛው ኃላማው የሚገኝበት ቦታ ሊሆን ይችላል። አንድ የሂሳብ ተማሪ የቢዝነር ወረቀቱ ላይ አተርቸር እየተመለከተ ባለበት ሁኔታ ውስጥ አንድ ፈረንጅ በዚህ አስቸጋሪ ሥራ ለምን ራሱን እንዳጠመደ ጠየቀው።

ተማሪው ሲመልስ የዩኒቨርሲቲ ድግሪውን ለማግኘት ሲል ይህንን እንደሚያደርግ ነገረው፡፡ «የዚህ ድግሪ ጥቅሙ ምንድን ነው?» የሚል ቀጣዩ ጥያቄ ነበር የገጠመው፡፡ መልሱም «የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ሂሳብ እንዳስተምር ይህ ድግሪ አስፈላጊ ነው» የሚል ነበር መልሱ፡፡ «እነርሱስ ለምን ይህ ትምህርት አስፈለጋቸው?» የሚል ቀጣዩ ጥያቄ ነበር የቀረበለት፡፡ «እርሱ የእኔ ጉዳይ አይደለም» ነበር መልሱ፡፡ እዚህ ላይ አንድ የተሳሳተ ነገር መኖሩ ግልጽ ነው፡፡ እዚህ ላይ ትምህርቱ፣ ጥናቶቹ እንደዚሁም ፈተናዎቹ በራሳቸው ግብ ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ተማሪው በተራው አስተማሪ ሆኖ አዳዲስ ተማሪዎች የሚያስተምር መምህር ሊሆን ነው፤ ግን ለምን? ማኅበረሰቡና ሌላው ተራው ሰው ለፍሬው የት ነው? ትምህርቱ ተግባራዊ የሚደረግበት ከክፍሉ ውጭ ላለው ሕዝብ ጠቃሚ የሚሆንበት እምነ ላይ ነው? ትምህርትና ሥልጠናን አስመልክቶ መረሳት የሌለባቸው ችግሮች ቀጥሎ ያሉት ናቸው፡፡ እነርሱም ትምህርትና ሥልጠና

ለምን ይጠቅማሉ? ለምንስ ዓላማ ያገለግላሉ? የሚሉ ናቸው፡፡

የትምህርት ሁሉ የመጀመሪያ ዓላማ ግለ ሰብኣዊ ነው፡፡ እርሱም ለተጨማሪ ጥናቶችና ሙያዊ ክህሎት መሠረት የሚሆነውን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማግኘት ነው፡፡ በቀደመው ዘመን በ«ሦስት የእንግሊዝኛ ፊደላት «R» መነሻ ስለሚጀምሩ ቃላት የሚደረገው ብዙ ውይይት ነበር፡፡ እነዚህ ሦስቱ አነጋገሮች አስቂኝ ከሆኑት የእንግሊዝኛ አጻጻፍ የተገኙ ናቸው፡፡ እነርሱም «reading, writing, እና rithmetic» ናቸው፡፡ በእርግጥ እነዚህ መሠረታዊ የትምህርት ዓይነቶች ለሁሉም ዓይነት እውቀትና ሳይንስ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ስለዚህ ዕድሉን በሚገኝበት ቦታ ሁሉ እነዚህን መሠረታዊ እውቀቶችን በወጣትነት እድሜ መቅሰም እና ወላጆችም ልጆቻቸው እንደዚሁ ያለውን እውቀት እንዲያገኙ መርዳት ሥነ ምግባራዊ ግዴታ ነው፡፡ ይህ ግዴታ አሁንም ይቀጥላል፡፡ በየትኛውም የዓለም ክፍል ባሉ አገሮች የሚገኙና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ሁሉ ቢያንስ የመጀመሪያ ትምህርት ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ እንዲሆን የማድረግ ግዴታ

አለባቸው። ክርስቲያኖችና ቤተ ክርስቲያን ለአንድ ቡድን ወይም የማኅበረሰቡ መደብ ቢያንስ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያገኘ እድል እንዲደርሰው የሚያደርግ ማንኛውም እንቅስቃሴ እንዲኖር መሥራትና ማቀድ አለባቸው። ክርስቲያኖች እንደ መሆናቸው መጠን ጉዳዩ ተጨማሪ ሥራና ጊዜ የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ እንኳ ከዚህም ያለፈ ዓላማ ሊኖራቸው ይገባል። ሁሉም ዜጎች የሚስማሙበትን ሦስቱን «R» ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ዓላማ ማሟላት ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት መስጠትም ዓላማቸው መሆን አለበት።

## ትምህርትና «ቃሉ»

እንደ ማንኛውም ሌላ ሰው ሁሉ ክርስቲያኖችም ዜጎች ሁሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እንዲያገኙ የሚያበረታቱበት ምክንያት አላቸው። ክርስቲያኖች የቃሉም እውቀትና ሥልጠናን

አብዝተው የሚፈልጉበት ሌላም ምክንያት አላቸው። የቃሉም እውቀት የሚለው ቃል መጻፍና ማንበብ ችሎታን የሚያጠቃልል አሳብ ይመለከታል። እነዚህ ቃላት ሁሉ የክርስቲያንን መሠረታዊ እምነት የሚነኩ ናቸው። ይኸውም እግዚአብሔር ራሱን በቃሉ ለእኛ የገለጸበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው። ስለዚህ የክርስቲያን መሠረታዊ እውቀት የቅዱሳት መጻሕፍትና በውስጣቸው የተጻፈው ቃል ለእኛ ለክርስቲያን ማኅበረሰብ ምን ማለት እንደሆነ መታወቅ አለበት። በእርግጥ ያለ ምንም የማንበብ ችሎታ ክርስቲያን መሆን ይቻላል። ነገር ግን የሚኖረን ልምምድና መስጠት የምንችለው አገልግሎት ውስን ሊሆን ይችላል።

ለክርስቲያኖች ማንበብን፣ መጻፍን፣ ትምህርትን እና እውቀትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሁሉ ላቅ ባለ መልኩ «ከቃሉ» ጋር የተቆራኙ ናቸው። በመጀመሪያ ደረጃ ያለ ፊደላትና ቃላት ትምህርት የሚባል ነገር ነው። ያለ አሳብ፣ ያለ ማብራሪያዎች፣ ያለ ሐረጎች፣ ያለ ዐረፍተ ነገሮች እና ያለ

ሰጥሰው አንድን ነገር መረዳት አይቻልም። በገቅተኛ ደረጃም ይሁን በከፍተኛ ሳይንሳዊ መንገድ ከሰዎች ጋር ለምናደርገው ግንኙነት እነዚህን ነገሮች አስፈላጊዎች ናቸው። የእነዚህን ነገሮች ሥረ መሠረት በንመለከት ድምፆችና ቃላት አሉ። በአእምሮ ወይም በመጽሐፍት ሁሉን ያለው እውቀት በገዘምታም ይሁን ገላ ባለ ድምፅ ያለ ቃላት ሊገለጽ አይችልም። የክርስትና የመጀመሪያው ምንጭም እንዲህ ይላል። «በመጀመሪያ ቃል ነበር።» «ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ።» (ዮሐ. 1፡1-14)። ይህ በእግዚአብሔር፣ በፍጥረት፣ በደኅንነት፣ በሰው እና በሰው ኅብረት መካከል ያለው ግንኙነት የተለየ የክርስትና ጠባይ ነው። ይህም በአንድ በኩል በቃላትና በንባብ፤ በሁሉም ዓይነት መልክም እውቀቶች፤ በክርስትና እምነትና ሥነ ምግባር መካከል ያለውን ልዩ ትስስር ለክርስቲያኖች የሰየል። ሁሉም በአንድ ላይ ሲጣመሩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

ወይም በክርስቲያኖች መካከል መግባባት እንዲኖር መሟገት እንደማይቻል ግልጽ ይሆናል። ይልቁንም የክርስትናን እምነት በማቃረን ወይም በሚያጠፉና እምነቱንና ግብረ ገባዊ አቋሙን በሚያበረታቱ እውቀት መካከል ያለውን ልዩነት ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል። ቤተ ክርስቲያን ለእውቀትና ለትምህርት የምታደርገውን ጥረት በሁለት መንገድ ልናየው እንችላለን። ይኸውም እነዚህን ነገሮች ማመቻቸትና ማበረታታት፣ ሁለተኛ ዓለም በመላ በተቻለ መጠን ቃሉን ማለትም ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያገኙና እንዲረዱ ማድረግ ናቸው።

## የትምህርት አስፈላጊነት

የትምህርት አስፈላጊነት ትልቅ ነው። ከዚህም የተነሣ ሌሎች የሰው ሕይወት ጉዳዮች ቅሉ እስኪባሉ ድረስ የትምህርትን አስፈላጊነት ማጉላት ቀላል ነው። አንዳንድ ጊዜ ጥሩ ትምህርት ያገኙና በሥራዎቻቸውና በደረሱበት ደረጃ ምክንያት በኩራት ያበጡ ሰዎችን እናገኛለን። ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች የሚረሱትዋቸውን

የሚያስቀርብሩን ይሆናሉ። ምክንያቱ ደግሞ አንድ የሚጎድላቸው ነገር በመኖሩ ነው።

ይህ ምሳሌ የራሱ ተጓዳኝ አለው። አንዳንድ ጊዜ መጠነኛ የሆነ ምናልባትም ለመጀመሪያ ደረጃ እንኳ የማይበቃ ትምህርት ያላቸውን ሰዎች እናገኛለን። እነዚህ ሰዎች አረጋውያን ከሆኑ ምናልባት ሁለት ወይ ሦስት ዓመታትን ብቻ በትምህርት ቤት ያሳለፉ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚሁ ሰዎች ምናልባት በሕይወት ዘመናቸው ፍጹም መልካም የሆኑ ነገሮችን ያደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንዶቹ በልዩ ልዩ መስኮች ለማኅበረሰባቸው ወደር የሌለው ሥራ የሠሩ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህስ እንዴት ሊገለጽ ይችላል? የዚህን ጉዳይ ጥቂት ገጽታ ለመጥቀስ ያህል ሦስት ወይም አራት ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። በመጀመሪያው የትምህርት ዓመት በጥሩ ሁኔታ የተማሩት ትንሽ ትምህርት በኋላም ላለው ሰፊ እውቀት የመሠረቱ ቁልፍ ይሆንላቸዋል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ጨርሶ ወደ ትምህርት ቤት ሳይገቡ የሚገነዘብ ችሎታ ያዳበሩ አንዳንዶች ሰዎች አሉ። ይህ ሊሆን የሚችለው በአጋጣሚያቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከፍለ ጊዜ የገባበ ትምህርት እንዲማሩ የተደረገ እንደሆነ ነው። ሁለተኛ ለመማር የተከፈተ አእምሮ ሊኖር ነው። እንዲህ ዓይነት ዝንባሌ አንድን ሰው በአድናቆት እንዲሞላ፤ ያስደነቁትን ነገሮች እንዲለይና ወደ እውቀትና ልምምድ እንዲለውጣቸው ይረዳዋል። በዚህ ዓይነት ዐይን የሰውነት መብራት ትሆናለች (ማቴ. 6፥22)። ሦስተኛ እንዲህ ባለው አቋም ውስጥ ትሕትናና ጥንካሬ እየጎለበተ ይሄዳል። ይህም ሁኔታ አንድ ሰው ችግሮችን እንዲቋቋምና ከከንቱ ተገዳዳሪዎቹም በላይ ራሱን ቀና እንዲያደርግ ይረዳዋል። አራተኛ ለሰዎች ሁሉ ከፍ ያለ ፍቅር መኖር አለበት። እንዲህ ካለ ፍቅር ውጭ ያለውና በራሱ በኩል ድክመቶች ያሉበት ሰው በአንድ ወቅት እርሱን ያገለገሉትን ጨምሮ ሰዎችን ሁሉ ለማገልገል ራሱን ሊሰጥ አይችልም።

እዚህ የተባለው ነገር የትምህርት ፕሮግራሞችን

ለማኅበረሰባቸው ከመስጠት ለሚያዘጋጁ ወይም ትምህርትን ለሚታወሱ ሰዎች ጓደኛ ሊሆን አይችልም። አንዳንድ ለየት-ያሉ ሁኔታዎችን በተለይም ብዙ ዕውቀት ሳይኖራቸው በመልካም ሥራቸው ርቀው የሄዱትን ሰዎች ስናነሣ እነዚህ ሰዎች ልዩ መሆናቸውን ማስታወስ ይኖርብናል። ስለዚህ ትምህርት በራሱ የመጨረሻ ግብ አይደለም። ይልቁንም ለአንድ ጎለማ መሣሪያ መሆኑን ማሰብ ያስፈልጋል። ይህም ዓላማ ድርብ ነው። አንደኛው ጥሩ ተማሪ፣ ጥሩ ጠባይ ያለው እና ጥሩ ዜጋ ለመሆን ዕድገትና ሥልጠና፤ ሁለተኛ ማኅበረሰቡን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በክልልና በብሔራዊ ደረጃ ለማገልገል የተዘጋጀ ዜጋ ሆኖ መገኘት ናቸው። እንዲህ ዓይነት መንፈስ ከመጀመሪያው ጀምሮ በተማሪዎች ውስጥ ካልሠረጸ ወደ ኋላ ላይ ሊመጣ አይችልም። በምትኩ ተማሪዎች ትምህርትን የሚማሩትና የሚያጠኑት ለራሳቸው ስስታምነትና በእውቀት ውስጥ ለሚከሰተው ከንቱነት ብቻ ይሆናል።

## ከመልካም ትምህርት ጋር የተቆራኙ ኃላፊነት

አብዛኛውን ጊዜ ይህ የትምህርት ድርሻ ችላ የሚባል ወይም የሚረሳ ነው። ትምህርት ማለት በተከታታይነት ለአገልግሎት መዘጋጀት መሆኑን ቀደም ብለን አይተናል። እንግዲያውስ ይህ እንዴት ይረሳል? ይህ የሚከሰተው ተማሪው ከአንድ ክፍል ወደ ሌላው ክፍል፤ ከአንድ ትምህርት ቤት ወደ ሌላው ትምህርት ቤት ምናልባትም ወደ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ በሚሸጋገርበት ጊዜ ነው። ይህ ሁሉ ሲጠናቀቅ ምናልባትም ተማሪው ትምህርቱን ለመቀጠል ወደ ውጭ አገር ይሄዳል። ተማሪው ትምህርቱንአጠናቆ ወደ አገሩ ተመልሶ ሕዝቡን ወይም ዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ቢያገለግል መልካም ነው። ነገር ግን በዚህ ሂደት መካከል አንድ ነገር ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ሊያመራ ይችላል። ይኸውም አንድ ሰው ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ለራሱ ጥቅም ብቻ ያዋለ እንደሆነ ነው። ይህ ዓይነቱ ሰው በትምህርቱ ሁሉ «ከፍተኛ ወደ ሆነው ሥራ» ወይም «ከፍተኛ ደመወዝ» ለማግኘት የሚያስችሉትን [illegible]

[illegible]

ደመወዞች የአገሩን ችግሮች ለመፍታት ካልዋሉ ጉግሉና ጥሪቱ ምን ጥቅም አለው? ከሕዝቡ አንጻር ስናየው ደግሞ የተማረው ሰው ጀርባውን ለሕዝቡ የሚሰጥ ከሆነ ሰዎቹ ግብር ከፍለው ይህንን ሰው እስከ ከፍተኛ ደረጃ ድረስ ለምን አስተማሩት? እንደዚህ ያለ ተማሪ እንዲህ ብሎ እውነቱን ቢናገር መልካም ነው፤ «ጥበብን፣ እንዲሁም እብደትንና ሞኝነትም ለማወቅ አእምሮዬን ተጠቀምሁ» ጥበብን በዚህ መንገድ ማግኘት «ነፋስን እንደ መከተል ነው» (መክብብ 1፥17)።

የብዙ ዓመታት ትምህርት የመጨረሻ ውጤቱን ሥራና ደመወዝ የማግኛ መንገድ አድርጎ ማየት ይቻላል። ይህ አመለካከት ግን ራስ ወዳድነት ብቻ ነው። ከዚህም የከፉ መንገዶች አሉ። ይህንን አሳብ ለመግለጽ ሁለት ምሳሌዎችን ብቻ መጥቀስ ይበቃል። አንድ የቴክኖሎጂ ተማሪ ከሃያ ወይም ከሰላሳ ዓመታት ተከታታይ ትምህርት በኋላ አደገኛ የሆነውን የልጆች

መጫዎቻ አሻንጉሊት በሚያመርት ትልቅ ፋብሪካ ውስጥ ትልቅ ሥራ ያገኛል እንበል። ይህ ትልቅ ፋብሪካ የሚያመርታቸው አሻንጉሊቶች አደገኛ ስለ ሆኑ በአንዳንድ አገሮች ተከልክለዋል። ይሁን እንጂ እነዚሁ አሻንጉሊቶች በማያሰልና በገቡ አሁንም ወደ ብዙ አገሮች መላካቸው ቀጥሏል። እንግዲያውስ ይህ ኢንጂኔየር ወይም ሥራ አስኪያጅ እርሱን ለማስተማር አገሪቱ ያወጣችውን ያህል አገሩን ወይም ዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ያገለግላል ወይ? አይደለም። ይህ ሰው ከፍተኛ ደመወዝ እየተከፈለው አውዳሚ ሥራ ይሠራል። ሌላው ምሳሌ የፍልስፍናና የሥነ ጽሑፍ ተማሪ ከረጅም ጊዜ የአካዳሚ ትምህርት በኋላ የአንድን ወጣት ማኅበረሰብ ግብረ ገብ የሚያበላሽ ሥነ ጽሑፎችን ለሚያወጣ ማተሚያ ቤት ተቀጥሮ ይሠራል እንበል። ይህ «ትልቅ ገንዘብ» የሚሰበሰብበት ሥራ ነው። የዚህ ሰው የከፍተኛ ትምህርት ውጤት ይህ ከሆነ በጣም ረጅም ለሆነ ጊዜና ውድ የትምህርት ወጪ ከማኅበረሰቡ የተሰጠው የተማረው ለምንድን ነው? ማኅበረሰቡ ከዚህ ዓይነት ሰው ያገኘው ትርፍ ምንድን ነው? አጥፊ ሥራ ትርፍ ነው ማለት ይቻላል?

ትምህርትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ጥብቅ ሕጎችን በማውጣት፣ ተማሪዎች ምን መማር እንደሚገባቸውና የጥናታቸውን ውጤት ለምን አገልግሎት መጠቀም እንደሚገባቸው በመቆጣጠር ብቻ የሚወሰኑ አይደሉም። እንደዚሁ ዓይነት አሠራሮች በፍጹማውያን መንግሥታት አገሮች ምንም ውጤት አላስገኙም፤ በሌላ በየትም አገር አይሠሩም። በአንዳንድ አገሮች እንደዚህ ባሉ የመቆጣጠሪያ የሥራ ክፍሎች ብዙ የጭካኔ ሥራዎች ተሠርተዋል። ነገር ግን በአገራችን ያለውን ትምህርት ለመለካም ውጤት ለመጠቀም ያለው መንገድ አንድ ብቻ ነው። ያም መሠረታዊም ይሁን ከፍተኛ ትምህርት መልካም ለሆነና ለተከበረ ዓላማ ይውል ዘንድ ለኅብረተሰቡ ጠባይ ማረፊያ የሚሆን ሥልጠና የሚሰጥ እና ለማኅበረሰቡ አገልግሎት እንዲውል የሚያደርግ የሥነ ምግባር ግብ እንዲኖረው ያስፈልጋል።

**ሌላው የኃላፊነት ገጽታ**

ይህ ኃላፊነት የሕዝብ ትምህርት ቤቶችንና ሌሎች ትምህርትና ሥልጠናን የሚያካሂዱ ተቋማትን ውስጣዊና የየዕለቱን እንቅስቃሴአቸውን የሚመለከት ነው። ትምህርት የአእምሮና የመደበኛ እውቀት ጉዳይ ብቻ ባለመሆኑ ሁሉም ነገር ሞራላዊ ገጽታም ይኖረው ዘንድ ግድ ነው። በእርግጥ ትምህርት አካልን፣ አእምሮን፣ ነፍስንና መላውን የሰው ማንነት ይይዛል። በዚህ ሁሉንም ተማሪዎች በመንፈሳዊ እና በሥነ ምግባራዊ አቋም እንዲጸኑ እና ለእድገታቸው ሙሉ ኃላፊነት ይሸከሙ ዘንድ ቤተሰቦቻቸውን ማገልገልና ከሰዎች ሁሉ ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው መርዳት የሁሉም ትምህርት ቤቶችና ተቋማት ዓላማ መሆን አለበት።

ይህንን አስመልክቶ የብዙ ትምህርት ቤቶችና ተቋማት በሁለት መንገዶች አይሳካላቸውም። እነዚህም መንገዶች ችላ ማለትና ሆን ተብሎ የሚፈጸሙ ስሕተቶች ናቸው። የመጀመሪያውን አከል ስንመለከት ለተማሪዎች ክትትል አለማድረግ ቢሆን በትምህርት

የሚያይበትና የሚያውቅበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህም መጥፎ ድርጊት የሚታወቀው እንደ ተማሪ ትምህርት ቤቱን ለቆ ወደ ሌላ ቦታ በሚሄድበት ጊዜ በተድላም ትምህርት ቤቱ በነበረበት ጊዜ መጥፎ ድርጊቶች ሲከሰቱ ጣልቃ ገብቶ ለማስተካከል ጥረት የሚያደርግ ሰው እንዳልነበረ በሚናገርበት ጊዜ ነው። እንደ ሰው ስለዚያ ጉዳይ አንድን መምህር በሚጠይቅበት ጊዜ አስተማሪው «እስከምናውቀው ድረስ ይህ መጥፎ ነገር የለም» ብሎ ይመልሳል። በዚህን ጊዜ ትምህርት ቤቱ የመልካም ባሕርይ መማሪያ መሆኑ ቀርቶ ለንጥቃት ተቃራኒው ነገር የሚስተናገድበት ቦታ ይሆናል።

ሁለተኛው የተጠቀሰው ነገር የሚከሰተው አስተማሪያቸው ወይም ቢያንስ ከእነርሱ ጥቂቶቹ በትምህርት ቤቱ ለሚታዩት መጥፎ ልማዶች ተጠያቂዎች ናቸው። እንዲህ ያሉ መጥፎ ልማዶች በትምህርት ቤቱ የሚከሰቱና አስተማሪዎች ከሥነ ምግባር አኳያ መጥፎ የሆነውን ነገር ለልጆች የሚያስተምሩ ከሆነ

እንደዚህ ባለ ቦታ የሚሰጠው ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ የወደቀ ለመሆኑ ምልክት ነው። ይህም ማለት ትምህርት ቤቱ ገንቢ ሥራ ከሚሠራበት ቦታ ይልቅ አፍራሽ ድርጊት የሚካሄድበት ቦታ ሆኗል ማለት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የምንማራቸው ሁለት ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪዎችና የአስተማሪዎች ቦታ ሳይሆን ማኅበረሰቡ በሙሉ የሚሳተፍበትና ኀላፊነትንም የሚጋራበት ተቋም ሊሆን ይገባል። ሁለተኛ በሁሉም ማኅበረሰብ ውስጥ ሰዎች የትምህርት ሥራ ባሕርይን የሚቀርጽ፤ ሥነ ምግባርን የሚያስይዝ እና ግላዊ ታማኝነትን በሚመለከታቸው አካላት ዘንድ ጥራቱን ከፍ የሚያደርግ ሥራ አድርገው ሊመለከቱት ይገባል።

ከጥንት ዘመን ጀምሮ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እንደተገኘው ሐሰተኛ ወይም አታላይ እውቀት ያስታብያል፤ እውነተኛ ፍቅር እና እውቀት ይገነባል (1 ቆሮ. 8÷1)። እንደዚሁም «እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ» እንደ ሆነ ይታወቃል (ምሳሌ 1÷7)። እነዚህ ቃላት በእርግጥ በዚህ ዓለም ለወጣት የሚያስችለውን ጥልቅ እውቀት ያስመክታሉ።

# ምዕራፍ 15

## ሥነ ጥበብና ሳይንስ

በመላው ዓለም ተጨማሪ ትምህርት ቤቶችና ትምህርት ይኖሩ ዘንድ ከፍተኛ ጥያቄ አለ። ጥያቄውም ፈጽሞ አርካታ የሌለው ይመስላል። ያለ ትምህርት ቤቶች በብዙ ቦታዎች ነባራዊው ሕይወት የደኸየ ወይም ከነጭራሹ እንደሌለ ይቆጠራል። የብዙ ታዋቂ ሰዎችን ታሪክና ባህል ብንፈትሽ ይህንን አሳብ የሚያጠናክር ሆኖ እናገኘዋለን። በማንኛውም የዓለማችን ክፍል ከሚገኙ ታላላቅ የባህል መዘክሮች ውስጥ አንዱን ብንጎበኝ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ከመከፈታቸው ከመቶ ዓመታት እንዲያውም ከሺ ዓመታት በፊት የተሠሩ ሥነ ጥበባት እና እደጥበባት የሚያስደምሙ ናቸው። ታዲያ ይህ ሁሉ እውቀትና ስጦታና ተሰጥዎ ከየት ሊመጣ ቻለ?

ስዚህ መልሱ መስጠት ያለበት ከራሱ ከሕዝቡ የጠለቀ ውስጣዊ መንሻ ስብዙ ምዕተ ዓመታት ከተካበተው ልምዳቸው፥ ከቤተ ሰባዊ ምስጢር፥ ከመናፈያ መንደርና ከማኅበራዊ አደረጃጀት ነው የሚሆል ይሆናል። ይህ ሁሉ ደግሞ ችሎ ሲባል ወይም ሲታሰብ የሚያደገበው የትምህርትና የሥልጠና ዓይነት ነው። መደበኛው የትምህርት አሰጣጥ እነዚህን እንዲቱ ሆኖ ከተዋቀረና ብልሃት በንደለው ጎደሬ ሀሳብ ወይም ከሞላ ጎደል በስተኋላ በመጣው የንንቀሳ እምነት እነዚህን ሁሉ የሚያሰንት ከሆነ ባሕላዊው እመራር አደጋ ውስጥ እየወደቀ ነው።

### ተረትና ምሳሌ

እዚህ ላይ የተባለውን ነገር ተግዳሮት በሚያቀርበት መልኩ ማሳየት ይቻላል። በዓለም ላይ በሚገኙና በሚታወቁ ሕዝቦች ሁሉ ዘንድ ብዙ የተለያዩ ዓይነት «ወጎች»፣ «ተረቶች» ወይም «አፈ ታሪኮች» አብዛኛውን ጊዜ «ተረትና ምሳሌ» በሚል ምሁራዊ አባባል ይቀርባሉ። ይህ ቃል በአብዛኛው ታሪካዊ ግንዛቤ የሚሰጡ አባባሎችን፣ ወጎችን ብቻ የሚያመለክት

ሳይሆን የሕይወትን ጥበብ አብዝቶ የሚዳስስ ነው ። ይሁንና እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር በ.ኖር በተለያዩ ሕዝቦች መካከል የሚገኙ የአብዛኛዎቹ መረጃዎች መነሻቸው ምንም ዓይነት መደበኛ ትምህርት ቤቶች ያልነበሩበት ዘመን መሆኑ ነው ። ወጎቹ፡ ተረቶቹና አፈ ታሪኮቹ በትርፍ ጊዜ በቤትና በቤተ ሰብ ውስጥ እንዲሁም ከሥራ ጋር ተያይዞ በመስክና በመሥሪያ ማምረቻ ቦታዎች ወዘተ... በቃል እየተተረኩ ከትውልድ ወደ ትውልድ የመጡ ናቸው። እነዚህ ወጎችና ተረቶች በብዙ ዓይነት መልኩ እጅግ የተለያዩ ናቸው ። ስለዚህ የነዚህን ነገሮች ፍሰትና ያለደረጃን ተጽዕኖ በመመርመር የሕዝቦችን ፍልስፍና ማጥናት ይቻላል። ይህንን የከበረ መዝገብ በምናጠናበት ወቅት የምንማረው ሌላ ነገር ደግሞ ትሕትናን ነው። ይህንን በተመለከተ ተረትና እጅግ ኋላ ቀር ሁኔታ ውስጥ የነበሩ እነዚህ ያልተማሩ ሕዝቦች እነዚህን ድንቅ የሥነ ጽሑፍ (ምንች በቃል ብቻ) እና የሕይወት

እኛ ልናደርግ የምንችለው ዋጋ ያለው አስተዋጽዖ ምንድን ነው?

ስለሆነ፡ ጎላማችን አንዳንድ የክርስቲያን ሥነ ምግባር መርሆዎች ስንተነትን በተለይ ልዩ ትኩረት የሚሰጡ ሁለት ሁኔታዎች መኖራቸውን እንመለከታለን። የመጀመሪያው በእንክብካቤ የመያዝ አስፈላጊነት ነው። ይህም ማለት ከአባቶች ትውልዶች የወረስናቸው ብዙ ጠቃሚ ነገሮች መጥፋት አይደርስባቸውም ማለት ነው። ይህ እውነታ መላውን የጎሳዎችን ሕዝቦች ያመለክታል። ከነዚህ ልንታደጋቸው የሚገባ ብዙ የከበሩ መዛግብት አሉ። ይህንን ማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። በእርግጥ በተረትና ምሳሌ ውስጥ ያሉ ነገሮች ሁሉ ጠቃሚ ናቸው ማለት አይደለም።ከዋሉ ጎደል የማይጠቅሙ ብዙ ነገሮች የመኖራቸውን ያህል እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችም አሉ።

የዚህ ነገር ሁለተኛው ጎን ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ነው። አብዛኛውን ጊዜ ወጎችና ተረቶች የሚተረኩት በመልካምና ክፉ መካከል እየተደረገ ስላለው የማያቋርጥ ትግል ነው። በዋናው

ዘርዘር ባለ መልኩ በሚተረከው አማላይ ተረት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ‹‹ልብ በል›› የሚል የስነ ምግባር ማስታወሻ አለ። አንዳንድ ጊዜ ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላ ትውልድ የሚተላለፉ እንዲህ ዓይነት ተረቶች ሕይወት ምን እንደሆነች ምን ዓይነት ኃላፊነትም እንደያዘች ፍንጮችን ይሰጡናል። በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ውስጥ ያሉ ሁኔታዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው በነዚህ የተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ክርስቲያኖችም ባሉበት አካባቢ መስራት ያለባቸው አስፈላጊ ነገሮች፤ የቱን መንከባከብ እንደሚኖርባቸውና የተረከቡትን ይህን የከበረ ጥሪት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ማሰብ አለባቸው።

## ሥነ ጥበብና አካባቢ

ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት በዓለም ላይ የነበሩትን ጥንታውያን የሥነ ጥበብ ዓይነቶችን ብንመለከት በአዎንታዊ መልኩ የምንናገርላቸው ብዙ ነገሮች አሉ። እነዚህ ጥንታውያን ሥነ ጥበባት በአካባቢ ደኅንነት ላይ ያላቸውን ጠቃሚነት ከሌላው ባላነሰ መንገድ ልዩ ትኩረት ልንሰጥበት ይገባል። በጥንት ጊዜ ሁሉም ነገር የሚሠራው ከአላቂ ቁሳቁሶች ስለነበረ በመጨረሻ ላይ ምንም ነገር በማይቀርበት ሁኔታ በሁሉም ነገር መልሰው መላልሰው ይጠቀሙ ስለነበር ከሞላ ጎደል ምንም ዓይነት የቆሻሻ ክምር አልነበረም። ይህንን ሁኔታ ዛሬ በዓለም ሀገሮች ሁሉ የዓለምን ገበያ ካጨናነቁ የፋብሪካ ምርቶች ጋር አነጻጸር። ላለፉት ጥቂት አሥርት ዓመታት የዓለምን ገበያ የተቆጣጠሩት እነዚህ ነገሮች ‹‹ገዝተህ ተጠቀምና ጣለው›› ለሚል አስተሳሰብ እንዲስማሙ ሆነው የተመረቱ ነበሩ። እንዲህ ዓይነቱን አስተሳሰብና ይህን መሰል ሥልጣኔ በመደገፍ የሚደረጉ ክርክሮች ቀጥሎ ከተመለከተው ሐቅ ጋር ሲነጻጸሩ ፍጹም ውድቅ ይሆናሉ። በታላላቅ ከተሞች ዙሪያ የቦታ እጥረት አለ። የዚህን ምክንያት አሳንሰን ማየት የሌለብን ሲሆን እርሱም ለቆሻሻ ክምርና ለፋብሪካ ዝቃጭ የሚሆን ሰፊ አካባቢ በማስፈለጉ አይደለም። የአየር÷ የመሬትና የከርሠ ምድርን ውኃ መመረዝን ሳንጠቅስ የሚመጡ

ትውልዶች በተለየ መልኩ የሚወርሱአቸውና ሊታመን በማይችል መልኩ በብረት፣ በመስተዋት ወይም በፕላስቲክ ውስጥ የሚገኙና ፈጽመው ሊወገዱ የማይችሉ የገዳቃዊ ቁልሎችን ጉዳይ ነው። ከነዚህ ከተጠቀሱት ምርቶች ሁሉ በስተጀርባ ይህ መተኪያ የሌለው የምድራችን የተፈጠሮ ሀብት በታሪክ ውስጥ በአንደ-ወቅት እሱም የተወሰኑ ሽማቾች ይኖሩ በነበረበት ወቅት ለሰው ልጅ ጥቅም የሚሰጡ ነበር። ከራሷ ከመሬት ጋር ከአፈሯ፣ ከማዕድናቷ፣ ከእፀዋቷ፣ ከእንስሳት፣ ከአየርና በውስጧ ካሉ ማንኛውም ነገር ጋር አብሮ መኖርን እስካልተለማመድን ድረስ በህልና ሥልጣኔን በተመለከተ ሊያሰጠመን የሚችል አንዳችም ነገር የለም። ይህን በተመለከተ ያሉት ትሁልዶች አስተማሪዎቻችንና አሠልጣኞቻችን መሆን ይችላሉ። አብዛኛውን ጊዜ ‹‹ጥበብ›› ተብለው የሚጠሩትን ብዙዎቹን ነገሮች ልቆ የሚሄደው ይህ ዓይነት ጥበብ ነው።

## ቤተ ክርስቲያንና ባህላዊ ሕይወት በአጠቃላይ

ባህላዊ ኑሮዎች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተወሰኑ አደጋዎች ይደቅናሉ። እነርሱም ‹‹ዓለማዊ›› የመሆን አደጋ ማለትም በዓለማዊ ነገሮች፣ እንቅስቃሴዎችና አመለካከቶች መጠመድ ነው። በነዚህም የእግዚአብሔር መንግሥት/ሥራና ዘላለማዊ አመለካከቶች ቸል ሊባሉ ወይም ከነጭራሹ ሊረሱ ይችላሉ። ይህንን አደጋ ሁልጊዜ ልብ ልንለውና በተቻለን መንገድ ሁሉ ልንዋጋው የሚገባን ነው። ይህ ከተደረገ ቤተ ክርስቲያንና ክርስቲያኖች ሁሉ እያንዳንዱ በተጠራበትና በተመደበበት በታ-በከፍተኛ ቅንነትና ትጋት ሊሠሩ ይችላሉ። ‹‹ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች›› (ዮሐ. 9፥4)። በመንፈሳዊ ነገሮች ላይ ማተኮር ዓለማዊ ግዴታን ችላ ለማለት እንደማክኛ ሊቀርብ አይችልም። ይልቁንም የአንድን ሰው ዓለማዊ፣ መንፈሳዊና ዘላለማዊ የሥራ ድርሻውን እንዲሁም እግዚአብሔር ለእነዚህ ሁሉ ግዴታዎች ያስተመጠው ዓላማ ምን እንደሆነ በገናዘበ መልኩ እና በአጠቃላይ

ለባህልና ሥልጣኔ በእጅጉ የደከሙትን አካቢያን ያሰፉ ብዙ-
ትውልዶችን እንደገና ዞር ብሎ መመልከቱ አስፈላጊም ጠቃሚም
ነው። የእነርሱ ፈጠራና ክንዋኔ በዛሬው ኑሮአችን ውስጥ
እየተጠቀምንባቸው ያሉት ነገሮች ሁሉ መሠረት ናቸው። በዚህ
ንጥብ የእኛ ግዴታ ምን መምሰል እንዳለበት በአጭሩ በዚህ
መንገድ ሊገለጽ ይችላል።

የክርስትና ጥሪያችንና ተልእኮአችን በባህላዊ ኑሮአችንና
አካባቢያችን ላይ እንቅፋት ሊሆን አይገባውም። ይልቁንም
የእግዚአብሔርን ስጦታ በአግባቡ ለመጠቀም በመሻትና በመተባበር
ለወገኖቻችን አገልግሎትና ደኅንነት እንዲሁም ለሰው ልጅ ሁሉ
ብልጽግናና ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሆን ማገልገል ጥሪያችንና
ግዴታችን ነው። በዚህ ዓለም ለመኖር እስከተጠራን ድረስ
‹‹ከዓለም ሳንሆን›› ‹‹በዓለም›› የመኖር ትክክለኛው ትርጉም ይህ
ብቻ ነው።

ይህ ችግር በዚህ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ ወደተነሳው
ንጥብ መልስ ይወስደናል። እርሱም መደበኛ ትምህርት በሌለበት
ሁኔታ አብዛኛውን ጊዜ ብዙች ያለው ባህላዊ ኑሮ እንዴት ሊገኝ
ቻለ? የሚለው ነው። ለዚህ መልሱ እውነተኛ ባህላዊ ሕይወት
ሁሉ የተመሰረተው በዳበረው አእምሮ ላይ ነው። ከዚህ ውጭ
ግን ኑሮ ባህላዊ ኑሮ ሁሉ ውጫዊ፣ ፈጠራ፣ ምርት፣ ፋብሪካ፣
ግብይት፣ ንግድና ትርጓ፣ ብቻ በሆነ ነበር። የአእምሮ ኩትኩታና
በዚህ ውስጥ ያሉት መንፈሳዊ ሂደቶች ካልተካተቱበት ያኔ
የምንገናኘው ነገር ቢኖር ባህልንና ሥልጣኔን ማዛባት ብቻ
ይሆናል። ለምሳሌ የሸመናን፣ የጥልፍ ሥራን፣ የቅርጫትን፣
የሸክላ ሥራና የመሳሰሉትን የዕደ-ጥበብ ሥራዎችን ብንመለከት
በጭጽም ለማምረት ብቻ ወይም ገንዘብ ለመሰብሰብ ብቻ ሆኖ
የሚሠሩ አልነበሩም። ‹‹ጥበብ›› ከሆነ ደግሞ የመማር ውጤት
ነው። ከሰፊው ትውልድ የመወረስ ጉዳይ ነው። የፍቅር
ጉዳይ ነው። ዕቃውን የመውደድ፣ ውበቱን የማድነቅ፣ ራሱን
ሥራውን የማክበር ጉዳይ ነው። ይህን ማግኘት የምንችለው

ከምንም ዓይነት ዕቃ ይሠራ እየሠራና እየተጠቀመበት ያለውን ነገር የሚያሽሞነሙነውን እውነተኛውን የኪነጥበቡን ሰው ስንመለከት ነው። ይህን በመሰለው ፍቅር ውስጥ ከዚህ ቀስ ጋር መቼ፣ የትና በምን ዓይነት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችልና እንዲሁም ወደ ፊት የሚሰጠውን አገልግሎት ታሳቢ የሚያደርግ አስተሳሰብ ይኖረዋል። እነዚህን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ እስካስገባን ድረስ የንብረት የአገልግሎትና የእውነተኛ ጥበብ ሁኔታዎች ከዚህ ውጪ ይሆናሉ። ያኔ አብዛኛው የሚንበረከቡትን ሕይወት አልባ፣ የሠዐሊ ምርትና ፍጆታ ብቻ ይሆናል። ከዚህም በላይ ለቆሻሻ ክምር የሚሆኑ ዕቃዎችን አስተዋጽዖ ማድረግ ብቻ ይሆናል። ይህንን ነገር ከአእምሮ ዕድገት በሽገርም በጥልቅ መፈተሽ ይቻላል። ከክርስትና አተያይ አንጻር እምነትና ቅድስናን እንዳስሳለን። ከዚህም አንጻር ሰው ራሱ የሸክላ አንድ ክፍል ነው። ይህ የሆነው ግን በታላቁ ሸክላ ሠሪ እጆች ነው። ወይም በሌላ መልኩ ሰው በታላቁ የቅርጫት ሠሪ እጆች

የተሠራ ጎንሽ ሥር ወይም በእግዚአብሔር የተሸመነ የነበር ትንሿ ሰበዝ ነው። ይህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ቃል የተወሰደና የቆየ አስተሳሰብ ነው። «ተነሥተህ ወደ ሸክላ ሠሪው ቤት ውረድ፥ በዚያም ቃሌን አሰማሃለሁ። ወደ ሸክላ ሠሪው ቤትም ወረድሁ፥ እነሆም፥ ሥራውን በመንኰራኵር ላይ ይሠራ ነበር። ከጭቃም ይሠራው የነበረ ዕቃ በሸክላ ሠሪው እጅ ተበላሸ፤ ሸክላ ሠሪውም እንደ ወደደ መልሶ ሌላ ዕቃ አደረገው።» ኤር. 18፥2-4 ላይ ይህ ወገኖቻችንን በማገልገል በፈጣሪያችንና በአባታችን በእግዚአብሔር እጅ ጠቃሚ መሣሪያዎች እንሆን ዘንድ ሁላችንም ልንማረው የሚገባ መሠረታዊ ትምህርት ነው። «ለሸክላ» ሠሪው እንዲሚስማማ ሆነን መልሰን መላልሰን ከተቀረጽን እርሱ እንደሚያደርግ በሚፈልገው መንገድ ለማገልገል የተገባን እንሆናለን። ከእኛ የሚፈለገው ነገር ትሕትናና ራስን ገዢ የሚያደርግ እምነት ብቻ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ትሕትናና እምነት ካለ የቆሻሻ ክምር ሳይሆን ዘላቂና ታላቅ የሆነ ነገር ሊፈጠር ይችላል።

ቤተ ክርስቲያን ለማኅበረሰቡ ባህላዊ ጉሮን እስካላበረከተች ድረስ «የምድር ጨው» «የዓለም ብርሃን» መሆንዋ ይቀራል (ማቴ. 5÷13-16)። እነዚህ ቃላት ክርስቲያኖችን ሁሉ በግል ይመለከቱአቸዋል።

## «የሥነ ጥበብ» ተግባራት

«ሥነ ጥበብ» የሚለው ቃል ብዙ የተለያዩ ትርጉሞች አሉት፤ ወይም «ሥነ ጥበብ» ዘርፉ ብዙ ነው። ስለ ሥነ ምግባር ስንነጋገር በመላው ዓለም የሚተገበሩ እንደ የእጅ ሥራ፥ ቅብ፥ ቅርፃ ቅርፅ፥ ሙዚቃ፥ ሥነ ጽሑፍ ወዘተ... ያሉትን እንቅስቃሴዎች ታሳቢ በማድረግ ነው። ይህ አርእስት ብዙ ጉድፈ አሳብና ተግባር የሚያቅፍ ስለ ሆነ እዚህ የምናተርበው በአጭሩ ብቻ ይሆናል። በዚህ ቦታ ላይ ተጨማሪ ዝንባሌ ያላቸው ተማሪዎች ወይም ቡድኖች ካሉ በመስኩ የተጻፉትን መጻሕፍት

ዝርዝር መጻሕፍትን እንዲያነቡና እንዲያውቁ እንመክራለን።

በብዙ የዓለም ክፍሎች የውበትን ምንነት የሚወክሉ ወይም የሚጨምሩ የተለያዩ ሥነ ጥበባት የሚገለጹባቸው ልማዶች ነበሩ። ቋሚ የሥነ ጥበብ ሥራዎችን ለምሳሌ በቅብ ሥራዎች፥ በቅርጻ ቅርጽ ወይም በሥነ ሕንጻ መልክ የተሠሩትን በምናጠናበት ወቅት በእርግጥ የሚያስተላልፉት አንድ መልእክት አለ።

እንደዚሁ ዓይነቱ ሥራዎች አብዛኛውን ጊዜ ውብ ናቸው፤ አንዳንድ ጊዜም ሲበዛ ውብ ናቸው። ሆኖም ውበት ማለት ምን እንደሆነ የሚገልጸው የሥነ ጥበብ አተራረብ ምሉዕነቱ እጥጋቢ አይደለም። ጎልቶ በወጣ ሥራቸው የተጠቀሱትንና ሌሎች የሥነ ጥበብ ዓይነቶችን ለምሳሌ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ የሠፈሩትን ብንመለከት እነዚህ ሥራዎች የውበትን ምንነት «ጥሩ ነገር» ማለት ምን እንደሆነ ወዘተ... ለመግለጽ የሚታይ፥ የሚነበብ ወይም የሚደመጥ ነገር በመፍጠር ላይ ብቻ ራሳቸውን አልገደቡም። ብዙ ጊዜ እጅግ ወደ ውስጥ ሰርስሮ የሚገባ

ሰይጣናዊ ገለጻም አለው። ውብ ወይም ጥሩ ገለጻ በተለይ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የተጋነነ ወይም በጎብረ ተለማት ያሸበረቀ ከሆነ የሚሰጠው ስሜት ጣፋጭ የሚመስል ነገር ግን ሐሰት የሆነ ነው። ለምሳሌ ይህን ነጥብ በተመለከተ ሊተቹ የሚገባቸው ብዙ መጻሕፍት አሉ። እነዚህ መጻሕፍት ስለ ሰዎች ሕይወት ወይም በሰዎች መካከል ስላለው ጉሮ ወይም ፍቅርና አገልግሎት የሚሰጡት ስዕል እውነተኛ አይደለም። እውነተኛ ካልሆነ ደግሞ ሌላ ምን ሊሆን ይችላሉ? ከነዚህ ባነሰ መልኩ በደበዘዘ ወይም «በነጭና ጥቁር» ቀለማት የተቀቡ አብዛኞቹ «የክርስትና» ሥነ ጽሑፎች በሰላ ትችት ውስጥ ሊወድቁ ችለዋል። እናም እንደ ደካማ ሥነ ጥበብ ተደርገው ተፈርጀዋል።

መሐሉ ያጠላበት ክፉል መልካምና መጥፎ የሆነውን የሰውን ልጅ እውነተኛ የሕይወት ገፅታ መወከል ያለበት በመሆኑ የሰውን ልጅ ትግል የሚወክል መሆን ይኖርበታል።ይህ እንዴት መደረግ አለበት የሚለው የሚወሰነው እንደ ጉዳዩ ተጨባጭ

ሁኔታ ነው። እኛ ሁላችን የምንኖርበት ዘመን ልጆችና ትውልድ ነን። የምንጽፋቸው መጻሕፍት በጥንታውያን የግሪክ ወይም የሮማውያን ጸሐፍት ዘይቤ ሊሆን አይችልም። ወይም እንደ ሚካኤል አንጀሎ ዓይነት ሕንፃ መገንባት አንችልም። ሁላችንም ከጥላ ኃይል የምንወሰነው በተካንበትና አንባቢዎቻችን ወይም ተመልካቾቻችን ወዘተ... በሚኖሩቸው መረዳትና ይሁንታ ነው። ከሚኖርበት መንደር፥ ቀበሌ ወይም ከተማ ወይም ካለበት ደረጃ በላቀ ሁኔታ ራሱን ከፍ ለማድረግ፥ አሻግሮ ለማየት፥ የእያንዳንዱ አርቲስት፥ የእያንዳንዱ አንባቢ፥ የእንዳንዱ ተመልካች ወይም ያሉበት ትውልድ ጭምር ግዴታ ነው። ስለሆነም ሥነ ጥበብ በሁሉም ቦታና በሁሉም አዲስ ትውልድ ዘንድ ሊወረስ፥ ሊጠናና እንደ ገና በአዲስመልክ ሊቀረጽ የሚገባው ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ሥነ ጥበብ ከዚህ በፊት ሌሎች የሠሩትን የመገልበጥ ነው ማለት አይደለም። እንደዚያ ከሆነ ሥነ ጥበብ ሁሉ ቅጂ ወደ መሆን ወይም ቅርጽ የሚያወጣ

ማገዝን ወደ መሆን ደረጃ ይወርዳል፤ ማለት ነው። እውነተኛ ሥነ ጥበብ ሁሉ ከፈጠራ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት። ይህ ማለት እንደ ፍጥረት ሙሉ በሙሉ አዲስ ነገር መፍጠር ማለት ሳይሆን ቀድሞውኑ በተፈጠረው ዓለም የሚገኙትን ነገሮችና አስተሳሰቦች በመጠቀም በነዚህ ቁሳቁሶች አማካይነት አዲስ ያልተመደ ነገር መፍጠር ማለት ነው። ይህ ሥራ በተለይ ጊዜንና ዘላለማዊነትን አስመልክቶ ከሰው ልጅ ሁኔታ+ ከአካባቢውና ከአኗኗሩ በመነሣት የሰው ልጅ ከመልካምና ከክፉ ጋር የሚያደርገው ትግል በአሁንና በሚመጣው ዘመን ካለውና ከሚመጣው ተስፋ ጋር ተያይዞ መሠራት ይኖርበታል።

## የሥነ ጥበብ ፍንገጣ

እንደዚሁ ዓይነቱ ፍንገጣ ብዙ ነው። እዚህ ላይ ሁሉንም መዘርዘሩ አስፈላጊ አይደለም። ነገር ግን እነዚህ ነገሮች በእውን

ያሉና ብዙ ጉዳዮችን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ መገለጹ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ጥቂት ምሳሌዎችን ብንጠቅስ እንኳ ይህ ዓይነቱ «ሥነ ጥበብ» የመጥፎና የእውነታ ካባ የደረበ መሆኑን ያሳየናል። ለዚህም ከሥነ ጽሑፍ ዘርፍ አንድ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ምንም ዓይነት አማራጮችን ሳያቀርብ እንዲሁ የማይረቡና ብልሹ ነገሮች የሚተረኩበት ሥነ ጽሑፍ ሰው ለንዋየ ፍቅር ብቻ ያለውን ነውረኛነት እንዲናፍቅ የሚያደርግ ነው። ውበት፥ እውነት ወይም ምስጋና ሊቸረው የሚገባ ነገር ማለት ምን እንደሆነ የሚያሳይ ምንም ነገር ከሌለበት እንዲሁ ሰዎች በክፋት ላይ እያነፈሱ ያለውን ትግል ፍንገጣው አድርጎ የሚያሳይ ከሆነ እውነት አትምርም፤ ግንዛቤም የለውም። ስለዚህ ወደ አንድ ወገን ብቻ ያጋደለ ጉዳይ ብቻ ይሆናል። ሌላ ምሳሌ ደግሞ ሙዚቃ ዘርፍ መውሰድ ይቻላል። አንዳንድ የሙዚቃ ዓይነቶች አፈጣጠራቸው፥ ለዛቸውና ትንበራቸው ከአደንዛዥ እጾች አጠቃቀም ጋር በተጥቃ የተያያዙ ናቸው።ይህ ደግሞ ሥነ ጥበብ ሊባል አይችልም። ደግሞም በተጠና ስልት ወጣቶች አቅላቸውን ወደሚያስት ደረጃ ወይም እስከ «ፈለክፍት» የሚያደርስ የሙዚቃ ዓይነት አለ።

በእንዲህ ዓይነቱ ሙዚቃ ውስጥ ‹‹ምን ጥበብ›› የለም ማለት በቂ ነው። ይልቁንም ይህ በብዙዎች ላይ አካላዊ፣ አእምሮአዊና መንፈሳዊ ጉዳቶችን የሚያስከትሉ አደገኛ መሳሪያዎች የመጠቀም ጉዳይ ነው።

## የቤተ ክርስቲያን ልዩ ተግባር

በመላው ዓለም ሁሉንም አህጉራትና ክፍለ ዘመናትን ብንመስድ እንደ ቤተ ክርስቲያን በምን ጥበብ ላይ የሠሩ የሉም። እነዚህ ሥራዎች በሁሉም መስክ ያሉትን እውነተኛና ውብ ምን ጥበባትን፣ ምን ጽሑፍን፣ ሙዚቃ፣ ስዕል፣ ትቦችና ምን ግንባታዎችን ያካተቱ ናቸው። ይህ ሥራ ዛሬም ድረስ አላቋረጠም። ሰው ምን እንደሆነ፣ የውበት ምንነት፣ በመልክምና በክፉ መካከል ያለው ትግል ምን እንደሆነ ይግምም በአሁኗ ዓለም የተንሰራፋውን አገዛዝና ክብሩን እንዲሁም የእግዚአብሔር ዘለአለማዊ መንግሥትና የሰው ልጅ የተጠራለትን እጹብና ድንቅ ግብ

ለዓለም ለማሳየት ሲባል ይህ ሥራ በሊሎች መስኮችም መቀጠል አለበት። የሚነገሩና የሚጻፉ ቋንቋዎች እንዲሁም ‹‹የምን-ጥበባት›› ውበት ለማሳየት የሚያገለግሉ የታወቁ መገለጫዎች ሁሉ ለዚህ ዓላማ በእርግጥ ያስፈልጋሉ።

## የሳይንስ ተግባር

የትምህርቱ ዓይነት ምንም ይሁን ምን የሳይንስ ጥናት ‹‹እውነትን መፈለግ›› ነው የሚለው አባባል ከጥንት ዘመን ልማድ ጋር በሚስማማ መልክ ብዙ ጊዜ ይገለጻል። እየተነገረለት ያለው ሳይንስ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ለተቃራኒ ዓላማ እስካልቆመ ድረስና ከምር እውነትን የሚፈልግ ከሆነ ይህንን ሐቅ መካድ አይቻልም። እንዲህ ዓይነቱ ባለ ሁለት ቢላዋ መንትያ ዓላማዎች ሳይንሳዊ ምርምሮችን በሚደግፉ ወይም ለዚህ ሥራ የራሳቸው ተቋማት ባላቸው አንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ። ንግድ የወለደ የሚሊሳቡ፣ የቋንቋ ትምህርት፣

ቁጥሮቹንና የመሳሰሉ የትምህርት ዓይነቶችን በተመለከተ ምንም ዓይነት አዲስ የለውም። ወደ ኬሚስትሪና የሕክምና የትምህርት ዓይነቶች ስንመጣ ግን በምርምር ዘርፎች ያሉ ነገሮች ሁሉ ፈጽሞ የተለዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። በውስጡ ጥያቄዎችን ብቻ ሳይሆን ስለ ራሱ ስለ ሕይወትና በራሱ በሕይወት ላይ ተገቢ ያልሆነ ምርምርን የሚያካትት ከሆነ ግን እነዚህ የምርምር ሥራዎች ሲበዛ አደገኛ ይሆናሉ።

ቀድሞውኑ የሳይንስ ቴክኖሎጂ ጎኑ በሰውና በአካባቢ ላይ ብዙ ችግሮችንና መዘዞችን አምጥቷል። የመሣሪያዎችና የማሽኖች ጌታ ሰው ነው ወይስ በቃራኒው ነው የሚለው ነገር አልፎ አልፎ አነጋጋሪ ሆኗል። ይህን ጉዳይ ለማብራራት አንድ ምሳሌ ማንሳት ብቻ ይበቃል ። ከአእምሮና ከማሰብ ችሎታ አንጻር ኮምፒዩተሮች የሰው ልጅ ጠላት እየሆኑ መጥተዋል። አንድ ዜጋ ከግል ሥራው ጋር በተገናኘ የተሳሳተ መረጃ ወይም አሉባ

ቢቀርብበትና ቅሬታውን ይዞ ወደሚመለከተው የመንግሥት ወይም የንግድ ቢሮ ቢሄድ የሚሰጠው መልስ ይህን ሊመስል ይችላል፤ «እናዝናለን ምንም ማድረግ አንችልም አንዴ ከምፒዩተር ውስጥ ስለገባ ኮምፒዩተሩ ያስተመጠው መረጃ ነው።» ባለ ጉዳዩ ዜጋ እንዲህ በማለት አቤቱታውን ይቀጥላል «ጉዳዩል ነህ የኔም ቅሬታ ይኸው ነው» እንዲህ ዓይነቱ የተሳሳተ መረጃ ወደ ኮምፒዩተሩ መግባት አልነበረበትም። የተሰጠው መረጃ ስሕተት መሆኑን የሚያረጋግጥልኝ ሠነድ በእጄ ይገኛል። ከዚያም የቢሮ ሠራተኛው «መረጃው ወደ ኮምፒዩተር ገብቷል ማለት አይገባህም እንዴ?» በማለት ጉዳዩን በግልፅ መልስ ይመልስለታል። ይህ ተቀባይነት የሌለው መልስ ነው። ይህን ሠራተኛ ጅንን ብሎ ደግሞም ባልሠለጠነ መንገድ እንዲህ ዓይነቱን መልስ እንዲሰጥ ማን አስተማረው? የሠራተኛው አነጋገር ስሕተቱን የሚፈጽመው ራሱ ፍርድ ቤቱ ሆኖ እያለ የኮምፒዩተሩ ሁሉን የመጨረሻው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እንደሆነ ዓይነት ነው። ባለመዘገበው ስሕተት ምክንያት የተቸረው «ሳይንስ» እንዲህ በመሰለው ጉዳይ መከራከሪያ ያገኛልን?

የሳይንስ ቴክኖሎጂ ስኬት እውን የሆነው ከዘመነ ኮምፒዩተር ረጅም ዓመታት በፊት ነው። ብዙዎቹ ስኬቶች ለሰው ልጅ ጥቅምና በረከት ውለዋል። ነገር ግን ሁሉም ይህን አድርገዋል ማለት አይደለም። ከከሰል+ ነዳጅና ከዘይት የሚወጣው ቃጠሎ አንዳንድ ከተሞችና አካባቢዎች ሊሸከሙ ከማይችሉት በላይ ዘበቢ አየርን እየበከሉት ነው። ኬሚካሎችን ከመጠቀማችን የተነሻ በብዙ መንገድ የእርሻዎቻችን ውበት ወደዚህ ደረጃ እየደረሱ ነው። ስለሆነም የምንመገባቸው ምግቦች አደገኛና እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ወደማይበሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። አሁንስ በቃህ እስካላልነው ድረስ ሳይንስ ምን ያህል ርቀት እየወሰደን ይሆን?

በእርግጥ አደጋዎቹ ብዙ ናቸው። ስለዚህ ቸል ልንላቸው አይገባም። ይህን አደጋ የመግፉን አደጋ መቋቋም የምንችለው ሰብዓዊ ኃላፊነት በማሳየት ብቻ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ኃላፊነት ሊመጣ የሚችለው በተፈጠረው ዓለም ውስጥ ያለፈ ሰው ድርሻ

ምን እንደሆነ በሚያመለክት የጠለቀ እውቀት አማካኝነት ብቻ ነው። ሰው በሁሉም ነገር ገዢ ወይም «ጌታ» አይደለም። የሰው ልጅ የዓለም አገልጋይ ተብሮ ነው። ባለንበት ዘመን ሁሉም ሰው «እየፈጠረ» ያለው ነገር በብዙ መንገድ አስደንጋጭ ነው። የኒውክሌየርን አደጋ ብንጠቅስ ይህ ቃል ለአንድ ላልተረዳ ሰው ምንም ትርጉም ላይሰጠው ይችላል። በየዕለቱ የሚሆኑትን ሌሎች ነገሮችን ብንጠቅስ ግን ብዙዎች ይረዱታል። በሰዎች ምርምርና የማራባት መሣሪያዎች አማካይነት ተፈጥሮአዊ ፍሰቱ መቆጸም የማይችሉ ዓሳማዎች አሉ። በዚህ ዘዴ የተራባው ወንዱ ዓሳማ ጀርባዎቹ ረጅምና እቅመ ቢስ በመሆኑ ለሴርያ ሴትዋ ዓሳማ ላይ መውጣት አይችልም። ይህ ዓይነቱ የአረባብ መንገድ የሚያነሩ የሰው ልጅ ሥራ አይደለም። ይልቁንም የሰው ልጅ ለንጉሣ ሥጋ ገድንና ለገንዘብ ያለውን ፍቅር ብቻ የሚገልጽ ነው። የከብቶች ሥቃይም ከዚህ ያነሰ አይደለም። በልዩ የማራባት ዘዴ አማካኝነት የተፈጠሩ ላሞች በጣም የተለቁ የጡት ቀጥት አላቸው። የወተት ምርታቸውም እጅግ ብዙ ነው። መራት ለመንሳት ምንም ያህል ያልተፈው የጡት ቀጥታቸው በጉለ

የእግሮቻቸው ኮቴ ጉዳት ይደርስበታል። ስለሆነም እንዲህ መሰሉን ላሞች የግት ቋት ወደ ላይ አቅሮ የሚይዝ ከረጢት መሰል ነገር ይደረግላቸዋል። ከብቶችን በማዳቀሉ ተግባር ሌላው ልዩ ነገር የጥጃዎችን እርባታ የሚመለከተው ነው። በቅርጽም ሆነ በመጠን ከተለመደው ጤናማ አካል የተለዩ በመሆናቸው ላሞቹ በተፈጥሮአዊ መንገድ አይወልዱአቸውም በዚህ ፈንታ ከማኅፀን እንዲወጡ የሚደረገው በቀዶ ጥገና ነው። ሰዎች ባስመዘገቡት ስኬት ሳቢያ ላሞቹ የተሸከሙት ጠባሳ በግልጽ የሚያሳየው ነገር ..."የሰው ልጅ እድገት".. ምን ያህል ወደ ፊት እየተራመደ ነው? የሰው ልጅ እስከ ምን ድረስ በተፈጥሮ በተገኘው ሕይወት ላይ እያፌዘ ይኖራል?

## ለሕይወት ክብር መስጠት ወይም አለመስጠት?

በሕክምናው ዓለም አንድ ሐኪም በተቻለው አቅም ሁሉ ሕይወትን ለማዳንና ለመንከባከብ ሲባል ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሥነ ምግባር ደንብ አለ። ከጊዜ በኋላ ግን ይህ የሥነ ምግባር ደንብ ውርጃን አስመልክቶ በሚወጡት ሕጎች ወይም አንድን ሰው ከሥቃይ ለመገላገል በሚል ሰበብ በሐኪሞች ውሳኔ እንዲገደል በሚወጡ ሕጎች ምክንያት ጥርጣሬ ላይ ሲወድቅ ወይም ሲጣስ ይታያል። አሁንም በዚሁ ሂደት ውስጥ ከዚህ የባሰ ነገር ሊመጣ ይችላል። እርሱም ሕይወትን ሁሉ ለመቆጣጠር ምክንያት የሚሆኑ የዘር አስተላላፊ (Hereditary Factors) እና በራሂያን (Genes) ላይ እየተደረገ ያለው ጥልቅ ጉብኝት ነው። ለመነሻያህል በግልጽ እንደሚነገረው ከሆነ ሳይንቲስቶች የተወሰኑ በሽታዎችን ለመፈወስ ይቻላቸው ዘንድ ተለያዩ ዘዴዎችን እየሞከሩ መሆናቸውን ለሕዝብ እየገለጹ ነው። ይሁንና ይህ መግለጫ ያንን ዘዴ በመጠቀም የሆነ ጉድለት አለባቸው በሚል ሰበብ ወይም ሊጣርባቸው ይችላል በሚል ሥጋት ብቻ በእናቶቻቸው ማኅፀን ያሉትንና ገና ያልተወለዱ ልጆችን የማይፈለጉ ብለው ስለሚፈርጇቸው አደራረጉ እርስ በእርስ የሚጋጭ ነው።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሁሉ በቅርብ ጊዜ ውስጥ በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ምን መደረግ ይችላል የሚለው ነገር ቀድሞውኑ በብዙ ዓይነት መልኩ በእፀዋትና እንስሳት ላይ እየተተገበረ ይገኛል። በነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ውስጥ እያደገ በመሄድ ላይ ያሉ አስቸጋሪ እርከኖች አሉ። ከጥንት ዘመን ጀምሮ የተሻሉ ምርቶችን ለማግኘት የእህል ዘሮችን የመምረጥ ብዙ ዓይነት ዘዴዎችን ይጠቀሙ እንደነበር ይታወቃል። በዘሮች ጥራት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ አንዳንድ መንገዶች እንደነበሩ ይታወቃል። እዚህ ላይ ብዙ ችግሮች ይነሳሉ። በአሁኑ ወቅት ሳይንቲስቶች ለዚህ ስርወ-ውርስ ምክንያት የሆኑትን እፀዋትን ፍራፍሬዎችንና ወዘተ... ጥራት ለመለወጥ እንዲሁም ደግሞ ከሞላ ጎደል አንድን እፅ ወደ ሌላ ለመለወጥ በበራሄ ላይ እንዴት ተጽዕኖ ማድረግ ወይም እንዴት መለወጥ እደሚቻል እንኳ ሳይቀር እስከ ማወቅ ደርሰዋል። ይህ ነገር ዛሬ ላይ ሊያስደንቅ ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ ወደፊት ሊመጣ ስላለው ነገር የመጀመሪያው ማሳያ ብቻ ነው። የምርትን ብዛትና ሌሎች ሀብቶችን ለማሳደግ የእንስሳትን በራሄ ከእፅዋት ጋር ማቀያየር ተችሏል። የዚህ ማብቂያው እስከምን ድረስ ነው? ሰው ኃላፊነትስ ጣልቃ የሚገባው የቱ ላይ ነው? በሌሎች ላይ በራሄ ተወስዶ ወደ ሰው ወይም ከሰው ወደ እንስሳት ተዛውሮ ቢዳቀል ምን ሊፈጠር ይችላል? እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጥያቄ በዚህ መልኩ ሊቀመጥ ይችላል። እርሱም ሕይወትን በመፍጠርና በሕይወት ላይ በመቀለድ መካከል ያለው ድንበር የቱ ጋ ነው? የሚል ነው።

እስካሁን ድረስ ሳይንስ ብዙ ስቃይና ጉዳት በማድረሱ ከባድ ጥፋት ሠርቶአል።ይህንን ጥፋት ወደፊት ገፍቶ ከመሄድ የሚገታው ማነው? ፍጥረታትን በእንክብካቤ ለመያዝ ዝግጁነት ወይስ በተቃራኒው ለማጥፋት እየተዘጋጀን ነው? የሚለውን አነጋጋሪ ጉዳይ በእርግጥ መልሰንና መላልሰን ማጤን በእጅጉ አስፈላጊ ነገር ነው። ሕይወትን በተመለከተ እየተደረገ ካለው ምርምር በስተጀርባ ያለው ድብቅ ዓላማ ምን ይሆን የሚለው ይህ

ጥያቄ ደግሞ ደጋግሞ መቅረብ ይኖርበታል። ይህንን አስመልክቶ በቅንነትና በግልጽነት ያልተገነዘበው ነገር ሕይወትን ለመፍጠር ወይም አዲስ ኅይነት ሕይወትን የመፍጠር ፍላጎትና ውሳኔ ይሆናል። ሀቁ ይህ ከሆነ እንግዲህ ሁለት የጥንት ዘመን ጥያቄዎች ዛሬ ላይ ሲደገሙ ነው ማለት ነው። ሁሉም ጥያቄዎች እጅግ አስፈላጊ ግን ደግሞ አደገኛ ናቸው። እነርሱም «መልካሙንና ክፉውን የሚያስታውቀውን ዛፍ» መብላት በእርግጥ ተከልክሎ ነበርን? ደግሞስ ከዚህ ዛፍ መብላት «እንደ እግዚአብሔር መልካሙንና ክፉውን እንድታውቁ ነው» ዘፍጥ. 2÷17፡ 3÷15 የሚለውን ሁጢት አይሰጥምን? እነዚህን ሳይንሳዊ ጉዳዮችን በፈሰገ መልኩ ብንፈትሻቸው ለሰው ልጅ ያልተገለጠ እውቀት አለ። ሰው ይህንን ለማግኘት ቢሞክር ወይም በዚህ ነገር ላይ ቢያተኩር ብዙ ርቀት መጓዝ ሊኖርበት ነው። ይህን ጎጂ ነገር እንደማስያ ለማንሳት ያህል ሳይንቲስቶች ልዕለ-ሰብ (Super man) ለመፍጠር በሚል አስተሳሰብ እያደረጉ ያለውን ጨዋታ መጥቀስ ብቻ ይበቃል። ይህን ነገር እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፍጥረቱ ወቅት እንዲ አላደረገውም። እንዲህ ዓይነቱን ሥራ ለመሥራት የሚያስብ በኃጢአት የወደቀ ሰው ብቻ ነው።

በእውነት በምክንያታዊነት፣ በቅንነትና በንጹሕ ሕሊና እንዲሁም የተፈጥሮና የሰው ልጅ ደኅንነትን በተመለከተ ሳይንስ ጥቅም ላይ ቢውል ወይም ቢተገበር ብዙ ነገሮችና ጉዳዮች ሊወገዱ ይችላሉ። እነዚህም ጉዳዮች ወደ አንድ ጎን ማዘንበል፣ መመጻደቅና መታበይ፣ ስስትና አፍቅሮተ ንዋይ፣ ማቴሪያሊዝም ወይም አፍቅሮተ ሀብት ናቸው። አንድ አንድ ሰብአዊ ፍጡር የሰይጣን የእጁ ሥራዎች ከመሆን ፊታቸውን ከቀየሩን ሁሉም ሰው የሰይጣንን ሥራ ያበረታታል፤ ይደግፋልም ። የሰይጣን ጥቅሙና የተንሰራፋው ታላቅ ስኬት ሊነድ አይችልም። እጅግ አስፈላጊው ነገር ጌታ ወይም ልዕለ-ሰብ ለመሆን ሳይሆን የፍጥረትና የሰው ልጅ አገልጋይ ለመሆን ቅን ፍላጎት መኖር ነው።

## የክርስቲያኖችና የቤተ ክርስቲያን ተግባር

በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን የግሏ የሆነ የተለየ ሳይንስ የላትም፡፡ ሆኖም ግን በራሱ በእግዚአብሔር ቃልና በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የተገለጠ በእምነት ላይ የተመሠረተ የማይነቀነቅ ጽኑ እውነት አላት፡፡ እውነትን ከልብ የሚፈልግ ማንም ሰው እንደ ቤተ ክርስቲያን ጠላት አይቆጠርም ‹‹ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንም ለማድረግ አንችልም›› (2 ቆሮ. 13÷8)፡፡ ይሁንና በዚህ የእውነትን ፍለጋ ውስጥ አንዳንድ ገቺ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ጥቂቶችን ለመጥቀስ ያህል የምንሠራው ሰብዓዊ ማኅበረ ሰብ ለመገንባት ነው ወይስ ለማፍረስ ? የምንሠራው ለደኅንነትና ለአገልግሎት ነው ወይስ ለጥቂት ሰዎች ብቻ ሀብትና ንዋይ ለማጋበስ ነው ? የምንሠራው ለተፋጠነና ትርፋማ ገቢ ነው ወይስ ኋላ ላይ ሊከሰት ለሚችል ኪሳራ? የምንሠራው አሁን በፍጥነት ዝናን ለመቀዳጀት ነው ወይስ ካልተሳካልን የሥራችን ውጤት እየጎመራ ሲሄድ ውሎ ሲያድር ለሚመጣ በጣም አስከፊ ገጽታ? መልካሙን አውቀን ለመሥራት ንጹሕ የህሊና ድጋፍ አለን ወይስ በ1 ጢሞ. 4÷2 ላይ እንደተጠቀሰው ‹‹በገዛ ህሊናቸው ደንዝዘው እንደተቃጠሉ ውሸተኞች›› እየሠራን ነው? በዚች አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ‹‹ሳይንስ›› ተጨማሪ ዝርዝር ማስረጃዎች ለማቅረብ አይቻልም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በዚህና በተመሳሳይ ርእሶች በተለይም ከክርስቲያን አተያይ አንፃር በስፋት የተጻፉ መጽሐፍትን እንዲያነቡ ይመከራል፡፡

# ምዕራፍ 16

## ሥራና ወሮታው

ከውድቀት በኋላ ያለው የሰው ልጆች ሁኔታ በድካም፥ በእሾህና በአሜኬላ ሊገለጽ ይችላል (ዘፍ. 3፥17-18)። ቀለል ያለ ሕይወት ለመኖር የሚተጉ እንዲህ ያሉ ሰዎች በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በቀላሉ ወይም ምንም ሳይለፉ ብዙ ለማግኘት በሚል የዕለት ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ይጥራሉ።

በዚህ እጅግ በሠለጠነ ዘመን ላይ ሥራን በሚመለከት ብዙ ለውጦች ተደርገዋል። የሰውም የኑሮ ጫና ለማቃለልና የዕለት እንጀራን ያለ ብዙ ልፋት ለማግኘት ሲባል ብዙ ማሽኖች ተፈልስፈዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ይህንን የመሰለ ሌላ ጠቃሚ

ነገርም ተከስቷል። እርሱም ማሽኖቹ ብዙ ሰዎችን ተክተው የሚሠሩ በመሆናቸው ብዙ ሰዎችን ሥራ አልባ አድርጓቸዋል። በኢንዱስትሪ የበለፀጉ አገሮችን የኑሮ ሁኔታ በተመለከተ በአንድ በኩል ከዚህ በፊት ባልታየ መንገድ ለብዙ ሰዎች የዕለት እንጀራ አስገኝቶአል፤ ብዙዎችንም የዕለት እንጀራ አሳጥቶአል።

ሀብታሞችም ሆንን ድሆች እየኖርንባቸው ያሉት ሁኔታዎች ምንም ይሁኑ ምን ሁላችንንም የሚያሳስቡ ብዙ ጥያቄዎች አሉ። እነዚህ ጥያቄዎች ከዕለት እንጀራችን፥ ከሥራ ወሮታው ወይም ከዋጋው፥ ከገንዘብ ከምቾት፥ ከካፒታልና ከአገዛዙ ዘይቤ ጋር የሚገናኙ ናቸው።

### የየዕለቱ ሥራችን ጥሩ ነው

በአቅመ አዳም የደረሰ ማንኛውም ጤነኛ ሰው ምንም ዓይነት ተግባር ወይም ሥራ የለውም ብሎ ማሰብ ፈጽሞ አይቻልም። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ካለ እርሱ ህልመኛ፥ ሥራ ፈት ወይም ሰነፍ ሰው መሆን አለበት። እዚህ ላይ ማሰብ ያለብን

ማንኛውንም ዓይነት የዕለት ሥራዎችን መሥራት የሚይችሉትን አካል ጉዳተኞችን ብቻ ነው ። በሌላ በኩል ላይ እንደተገለፀው ሁሉ እንደዚሁ ያሉ ሰዎችም ቢሆኑ የተወሰኑ ኃላፊነቶችን በመውሰድ ራሳቸው ያሉበት ሁኔታና የማኅበረሰባቸው ሕይወት ትርጉም ያለው እንዲሆን የተወሰኑ ነገሮችን ማበርከት ይችላሉ። ሥራ የአንድ ዜጋ መደበኛ ኑሮ ነው፤ ሥራ ግዴታ ነው፤ ከዚህም የተነሣ ሥራ የእያንዳንዱና የሁሉም ጉዳይ ነው። በአሁኑም አጠቃላይ ሕግ የመልካም ማኅበረ ሰብ አባላትን ሁሉ ያመለክታል።

እኛ ሁላችንም እንደምናከናውነው የተጠራንበት ከዚህ ሥራ በስተጀርባ ያለው ዓላማ ምንድነው? በእርግጥ ከዓላማዎቹ አንዱና ዋናው ሁልጊዜ የራሳችንንና የቤተ ሰባችን የዕለት ተዕለት ኑሮ ማሸነፍ። ሰው ሁሉ ማንኛውንም ዓይነት ሥራ መሥራት አይችልም። እናም የአንድ ቤተ ሰብ አባል እያንዳንዱ አራሽ፣ ምግብ አብሳይ፣ የሕፃናት ተንከባካቢ፣ የፋብሪካ ሠራተኛ፣

የቢሮ፣ የሐኪም ቤት ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ሊሆን አይችልም። አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎች ተደልድለው መከፋፈል አለባቸው። እነዚህ በአንድነት ሲዋሐዱ የቤተ ሰቡን አባላት ኑሮ ለማሸነፍና በተቻለ መጠን ሕይወታቸው በመልካም መንገድ እንዲገፋ ያግዛሉ።

ይሁን እንጂ ሥራችን ቤተ ሰባችንን በመንከባከብ ግዴታ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ከሆነ ፍጹም ስሕተት ይሆናል። እያንዳንዱ ቤተ ሰብ ከሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ጋር የተቆራኘ ነው። በእርሻ ማሳ የሚመረተውን፣ በገበያ የሚሸጠውን፣ በፋብሪካ የሚመረቱና በማከማቻዎችና በመደብሮች የሚሸጡትን፣ በትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ትምህርቶችን፣ በብዙ ቢሮዎችና ችሎቶች ወዘተ... ውስጥ የሚሠሩ ሥራዎችን ስናስብ ይህ እውነት ግልጽ ይሆንልናል። እንደነዚህ ዓይነቱ ሥራዎች ሁሉ አጋዥ፣ አገልግሎት ሰጪና ተደጋጋፊ ናቸው። ይህ ማለት በቅንነት የሚሠራ እያንዳንዱ ነገር ተግባራዊና ትርጉም ያለው እንዲሆን የሚያደርግ ሠራተኛ የኅብረተሰብ የኑሮ አካል ነው።

በአሉታዊ ይሁን በአዎንታዊ መልኩ ስለ ገንዘብ አጋነን ብናወራ ችግር የለውም። ምናልባት በንለም ውስጥ በአንድ ወይ በሌላ መልኩ ሕይወቱን ለመምራት በገንዘብ የማይገለገል የማኅበረሰብ ክፍል አይኖርም። ንብረትን በተመለከተ ቀደም ሲል በገፅ 89 ላይ ተብራርቶአል። በዚህ ክፍል ውስጥ ገንዘብ ስለሥራ የሚከፈል ዋጋ ነው በሚለው ክፍል ላይ ማተኮር ይኖርብናል። እዚህ ላይ ሊነሡ የሚችሉ እጅግ ከባድ ችግሮች የገበሬው ማኅበረሰብ በኢንዱስትሪው ማኅበረሰብ እየተተኩ የመምጣታቸው ጉዳይ ነው። እንዲህ ሲሆን ችግሮቹ እየተባዙ የሚሄዱ ይመስላል። የኢንዱስትሪው ማኅበረሰብ ኑሮ በአብዛኛው የተመሠረተው በገንዘብ ገበያ ለውጥ ላይ ሲሆን የግብርናው ማኅበረሰብ በጣም የተለመደውን መደበኛ ሕይወቱን ከጥላ ጎደል በወቅቶች መፈራረቅ ይመራል። የፋብሪካ ሠራተኞች ያመረቱት

ዕቃ ዋጋ ቢረክስ እባ ፈንታቸው ምን ሊሆን ይችላል? ለምርት የሚውል ጥሬ ዕቃ ዋጋ ቢንርና ሸማቾች ደግሞ በፈንታቸው አልቆ ገበያ ላይ የዋለውንና ዋጋው ያሻቀበውን ምርት ለመግዛት አሻፈረኝ ቢሉ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? ኑሮው በኢንዱስትሪ ሥራ ላይ የተመሠረተው ማኅበረሰብ በየጊዜው በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ብዙ ችግሮች ቢያጋጥሙት ፈጽሞ የሚያስደንቅ አይሆንም።

በዚህ በመጠኑም ቢሆን አዲስ በሆነው ዓለም ውስጥ ለተራው ዜጋ እንግዳና በተለሉ ችላ ሊሏቸው የማይቻለው በርካታ ችግሮች አሉ። ‹‹ሥራውን ጠብቆ ለማስኬድ›› ይቻለው ዘንድ ‹‹ሥራ ላይ የዋለን መዋዕለ ንዋይ››+ ‹‹ወለድ›› እንዲሁም የሚጠበቀው ‹‹ትርፍ›› ይህንና ይህን የመሳሰሉ ብዙ ተጨማሪ ነገሮችን ለመሸፈን እንዴት አድርጎ ነው ራሱን ሊያበቃ የሚችለው? በእርግጥ ብዙ ሰዎች ከእንዲህ ዓይነቱ ነገሮች ጋር በሚገባ ላይተዋወቁ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱንም ሁሉ በማናናቅ ‹‹ትርፍ›› ለምን ይኖራል?፤ እነዚህ ሰዎች ለምን ገዢ ብለው ሥራቸውን አይሠሩም? ሊሉ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱ

አስተያየት በሚገባ የታሰበበት አይደለም። በነዚህ የሚጠቀሙ ሰዎች እነዚህን ውድ ማሽኖች የሚገዙት ወይም ሞያተኞችን የሚቀጥሩት በራሳቸው ገንዘብ ነው። እንዲሁም ምርቱንስ የሚሸጡት ጥሬ ዕቃውንና የጉልበት ዋጋን ታሳቢ ባደረገ ተመን ብቻ ነው። አሁን በሥራ ላይ ያለውን ማሽን በአዲስ መተካት ካለበት ማን ነው የሚገዛው? በተጨማሪም ግብር የሚከፍለው ማን ነው? ለተቀጣሪዎቹ ደመወዝ የሚከፍል ማን ነው? ከባንኮች የተወሰደውን ብድር የሚከፍለስ ማን ነው? በማብርሪያም ሆነ በማተሚያ ቤት ወይም በመሰል ዘርፎች የሚሠራው ሥራ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ረብ ያለው መሆኑ ሊካድ የማይችል ሐቅ ነው። ይህም ማለት በሸቀጥ ወይም በገንዘብ ወይም ደግሞ በላቀ ሙያዊ አነጋገር ትርፋማና ወሮታ የሚያስገኝ መሆን ይኖርበታል ማለት ነው። እንዲህ ካልሆነ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይዘጋል። ታዲያ ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከላይ በተጠቀሰው አገባብ መሠረት የማይከፈልባቸው ብዙ ዓይነት

ሥራዎች መኖራቸው የግድ ይሆናል። እዚህ ላይ የፖሊስን፣ የጎዳናን፣ የሆስፒታሎችንና የሕክምና ክፍሎችን፣ የምክር አገልግሎት ሰጪዎችን፣ የከተማ ጽዳት ዲፓርትመንቶችን ወዘተ... ሥራዎች ታሳቢ ማድረግ እንችላለን። በአንድ ወይም በሌላ መልኩ እነዚህ ሥራዎች ሁሉ ሊኖሩ የግድ ነው። እነዚህ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ወጪያቸውን የሚሸፍኑበት የራሳቸው የሆነ ገንዘብ ስለሌላቸውና ምንም ዓይነት ትርፍ ስለማይሰበስቡ ከሌሎች የሥራ ዘርፎች በሚገኝ ገቢ ሊደገፉ ይገባቸዋል። ይህም ማለት ከሌላው ማኅበረ ሰብ ግብር በመሰብሰብ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ መንገድ የሚሰበሰብ ገንዘብ ደግሞ እንደ ብክነት ሆኖ ሊቆጠር አይገባውም። እነዚህ የተጠቀሱት የአገልግሎት ዓይነቶችና ከእነርሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች አገልግሎቶች እንድን ዜጋ በአካልና በነፍስ ብቁ ሆኖ እንዲኖርና እንዲሠራ ያደርጉታል። እናም እነዚህን የመሳሰሉ ሥራዎች ሁሉ በማኅበረሰቡ ኢኮኖሚ ውስጥ በምንም መንገድ እሴታዊ ሚና አይኖራቸውም። ይልቁንም ሲበዛ አዎንታዊ ናቸው።

በማኅበረ ሰቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ብዙ ችግሮች ስላሉና ብዙ ስሕተቶችም በቀላሉ ስለሚሠሩ ባለፉት ሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ እጅግ ጥሩ ሊባሉ ስለሚችሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ሥርዓቶች ላይ ብዙ ውይይቶች ተደርገዋል። ችግሮቹ በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠነጥኑት ሥራና ወሮታው በሚል ዙሪያ ነው።

## ሁለት የተለያዩ ሥርዓቶች

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት አብዛኞዎቹ ችግሮች እያደጉና እየበለጸጉ የመጡት ብዙ አገሮች ኢንዱስትሪያዊ እየሆኑ ከመምጣታቸው ጋር የተቆራኘ ነው። ብዙ ጊዜ ካፒታሊዝም በአብዛኛው የግል ካፒታሊዝም በመባል የሚታወቀው ብዙ የአመለካከት ጎራዎችን ያሳተፈ ጉዳይ ነው። የዚህ አመለካከት [illegible]

[illegible] ነቀይ ፍሰትንና ትርፍን ወዘተ... ሥራ ላይ ለማዋል ትክክለኛ ብቃት ያላቸው ግለሰቦች ናቸው ብለው ያምናሉ። ይህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች ትርፍ ከፍተኛውን ሚና እንደሚጫወት ቢያምኑም ሌላ ፍላጎት ካላቸው ጋር ሆነው ለምሳሌ (ኮምፓኒዎች ወይም በኮምፓኒዎች ማኅበራት ከሚደራጁና አንድ ዓይነት ፍላጎት ካላቸው ብዙ ግለሰቦች ጋር በመሆን ለማኅበረ ሰቡ የጋራ ጥቅም ሊያበረክቱ እንደሚችሉም ያምናሉ። ምንም እንኳ እነዚህን ሀሳቦች የሚደግፉ ብዙ ሀቆች ቢኖሩም በተቃራኒው ደግሞ ብዙ ማለት ይቻላል። ሁሉም ግለሰቦች ከሞላ ጎደል ራስ ወዳድ ቢሆኑና ለራሳቸው ገቢና ትርፍ ለመሥራት ብቻ ቢያልሙ ድምሩ ወይም የመጨረሻው ውጤት እንዴት አድርጎ ለብዙሀኑ ተስማሚና ጥሩ ሊሆን ይችላል? ይህ ነገር አልፎ አልፎ መከሰቱን መካድ አይቻልም። ይሁንና ሊከሰት እንደሚችል እንዴት አድርጎ ማረጋገጥ ይቻላል? ብዙ ግለሰቦችና ቡድኖች እንዲሁም አብዛኛውን ጊዜ ማኅበረሰቡ በሙሉ ገንዘብ፣ ካፒታልና ትርፍ ወዘተ... በሚያመጡት መዘዝ ምክንያት ይሰቃያሉ።

የካፒታሊዝም ታሪክ ሰብአዊ ስቃይና ያስየለት ድህነት ውጤት ምን እንደሚመስል በብዙ ምሳሌዎች ያሳየናል። በጣም የተስመደውና በብዙ አገሮች የሚታየው የወጣቶችና የታዳጊ ሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ ከምሳሌዎቹ አንዱ ነው። ቀደም ሲል ስለ ሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ ጠቅሰናል (ገጽ 94 እና ተከታዩ)። እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት እንዴት ይፈቀዳል? በነዚህ አገራት ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ሕግና ማኅበራዊ ሥርዓት ምን ዓይነት ነው? መልሱ ሥርዓቱ ይለያያል የሚል ይሆናል። ነገር ግን በጋራ የሚጋሩአቸው ነገሮች አሉአቸው። እነርሱም ግንዛቤ ካፒታልና ትርፍ ናቸው የሚል ነው።

የካፒታሊዝም ሌላኛው ገጽታ እንደ እውነቱ ከሆነ በማንም ሀገር የማይፈለጉ ነገር ግን እየተበራከቱ የሚፈበረኩ ዕቃዎች ናቸው። በተቃራኒው ደግሞ እነዚህን የመሳሰሉት ብዙ ሸቀጦች አደገኛ ወይም መርዛማ ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ከመጠን በላይ ተፈላጊ ናቸው። ታዲያ እንዴት ነው የሚሸጡት?

በካፒታሊስቶቹ «ገበያ መፍጠር» እየተባለ በሚጠራ አገላለጽ መሠረት መሥራት አስፈላጊ ይሆናል። ይህ የሚሠራው እጅግ ውድና ብዙ ጊዜ ተደጋጋሚ በሚተርብ የማስተዋወቅ ዘዴ ነው። የሚሰራጩት በፖስተሮችና በራሪ ወረቀቶች ብዛት በአውሮፓ ነፋስ አምዶች ዙሪያ ትርንጎዎች ላይ የሚበተኑ ትብሎችን ይመስላሉ። ስለእንዲህ ዓይነቱ ማስታወቂያ የሚከፈለው ወጪ የተጠቀሰውን የዕቃውን ዋጋ ያንራል። በኢንዱስትሪ በበለጸጉ አገሮች የሚኖረው አብዛኛው ሕዝብ ለማስታወቂያ የሚውሉ ቁሳቁሶች ላይ የእንጨቱንና የወረቀቱን መሥሪያ እንጨቶችን ብክነት እንደ አንድ ምሳሌ በማሳየት በማንሳት ይህን መሰሉን ሥራ በብርቱ ይቃወማል፤ በዚህም ይህን ጥፋት ለማስቆም የሚቻልበት መንገድ ባለመኖሩ ተስፋ ይቆርጣል። ሁኔታው እንደ ግዙፍ ሰው ከድንክዬ ሰው ጋር የሚያደርገው ትግል ዓይነት ሆኖ ይሰማቸዋል። ይህም ማለት ተራ ዜጎችና ግብር ከፋዮች ከግዙፍ አምራች ኩባንያዎች ጋር ባለንብረቶችና ከእነርሱ ጀርባ ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር መፋለም ማለት ነው።

የበዛ ፍትህ አልባነት፥ ብክነትና ከንቱነት በሰፈነበት ሁኔታ መጀመሪያ በሠራተኞችና በቀን ሙያተኞች እንዲሁም ነገሮች እየተበላሹ በመሄድ ላይ መሆናቸውን በተገነዘቡ ሌሎች ብዙ ሰዎች መካከል አለመረጋጋት በመኖሩ ተቃውሞ መነሣቱ የተለመደ ነው። ይህ ሁኔታ ነው እንግዲህ ለሶሺሊስታዊነትና ለኮሚኒስት ንቅናቄዎች ምንጭ የሆነው። በቀጣይ ጊዜአትም በሌሎች የሥራ መስኮች ለሦስት በባለርስቶችና በመሬት አልባ ድሆች መካከል የተነሣሱ ትግሎች በብዙ አገሮች በተመሳሳይ ሁኔታ በተደጋጋሚ ሲከሰቱ ቆይተዋል። ከዚህ የተነሳ ካፒታሊስቱ ሥርዓት ሌላ አማራጭ ለመሻት የሞከሩ የሰራተኛ መሪዎችና የኅብረተሰብ ጥናት ባለሙያዎች ሊፈጠሩ ችለዋል። የዚህ አመለካከት አቀንቃኞች አድማ ከካፒታሊስቱ ጋር አቻነት ያለው ነው። ምንም እንኳ ስያሜው ከጊዜ ወደ ጊዜ ከአገር አገር ቢለያይም በአብዛኛው ሶሺሊዝምና ኮሚዩኒዝም በሚል የተለያየ

ግጽታም አለ። በዚህኛውም ሥርዓት ውስጥ ኅንዘብ ካፒታልና ወለድ ትርፍና ደሞዝ ሊቀር የማይችል ነገር ስለሆነ ሶሺሊዝምና ኮሚዩኒዝም እንደ መንግሥታዊ ካፒታሊዝም ሊጠሩ ይችላሉ። እንዲህ ዓይቱ ሥርዓት እየተተገበረ ያለው በኮሚኒስት ሀገሮች ሲሆን ሶሺሊስት አገሮች ደግሞ ቅይጥ ኢኮኖሚን ምርጫቸው አድርገዋል። በኮሚዩኒዝም ፊሎሶፊ ዓለም በሚመራ ማኅበረሰብ ውስጥ መንግሥት የሁሉም ንብረትና የካፒታል ብቸኛ ባለቤት ነው። በመርህ ደረጃ የግል ኢንተርፕራይዞችና ካምፓኒዎች ሁሉ በቁጥጥሩ የሚገኙ ሲሆን በአነሩሩ ኮሚዩኒዝም አንድ ደግሞ እንዲህ ዓይነት ነገሮች የተከለከሉ ናቸው። ማንም ሰው በራሱ የሚሆን ምንም ዓይነት ሰድል ወይም ትርፍ ማግኘት አይፍርበትም። ከዚህ ይልቅ ሁሉም ነገር መንገ ያለበት ቢያንስ በዕንሰ ሀሳብ ደረጃ መንግሥት በሚሰለው አካል አማካይነት «የሠራተኛው መደብ» ወይም «በላብ አደሩ» ስም ነው። «ማንም ሰው የሌላው ሰው ደም መጣጭ እንዲሆን ስለማይፈቀድለት» ምንም ዓይነት ትርፍ ማግኘት ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

ይህ በአብዛኛው የሚታየው መስሉ ቢታይም ሀቁ ግን የሚያሳየው ከዚህ የተለየ ነው። በኮሚኒስት አገሮች ውስጥ የሠራተኛው መደብ ደኅንነት አለመኖር አብዛኛውን ጊዜ በግልፅ የሚታይ ነገር ነው። የሠራተኛው ሁኔታ እጅግ ሲበዛ አስከፊ ነው፤ ይህንና ደግሞ ማንኛውም ዓይነት አድማ የተከለከለ በመሆኑ ምንም ዓይነት ብሶት መስማት አይቻልም። ስለዚህ የሚሰጠው ማብራሪያ እራሱን ገላጭ ነው። እርሱም «ማኅበረሰቡ በሙሉ የሚተዳደረው በራሱ በሠራተኛው መደብ በመሆኑ አድማ ለመምታት ምንም ዓይነት ምክንያት አያስፈልገውም» የሚል ነው። የሚመረቱ ዕቃዎች ዋጋ አብዛኛውን ጊዜ ርካሽ ነው ስለሆነም አምራች ኩባንያዎች የሚንቀሳቀሱት በኪሳራ ነው። ሆኖም ለነሱ ይህ ችግራቸው አይደለም። ምክንያቱም መንግሥት ድጎማ ያደርግላቸዋልና ነው። ለዚህ የሚውለው ገንዘብ ደግሞ የሚሰበሰበው ሸማቹ በሚገዛቸው ብዙ ዓይነት ዕቃዎችና ሸቀጦች ላይ በሚጣል ቀረጥ አማካይነት ነው።

ረጋ ብሎ ሁኔታውን ላጤነ ሰው ይህ ሥርዓት የተገነባባቸውና ከካፒታሊስቱ ጋር የሚጋሯቸው ብዙ ስሕተቶች እንዳሉት መገንዘብ አይሳነውም። ከስሕተቶቹ አንዱ ሥርዓቱ ሰውን በተፈጥሮው ብልሹና ሕገወጥ መሆኑን አለመገንዘቡ ነው። ግለሰቦች የግል ተቋማትን ማቋቋምና መምራት አይችሉም ከተባለ በኮሚኒስት ሥርዓት ሥር ያሉትንና ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡትን ለምሳሌ ግዙፍ የንግድ ተቋማትን ወይም ሁሉንም የንግድ ተቋማት በተግባራቸው ሥር የሚስተዳድሩትን ኢንዱስትሪዎች እንዴት አድርገው ሊመሩ ይችላሉ? የኢንዱስትሪዎቹ መሪዎች ከበላይ አካል ትእዛዝ የሚቀበሉ ከሆነ ይህ ፈፅሞ ሊሆን የማይችል ነገር ነው ምክንያቱም እነዚህ «የበላይ» አካላት ራሳቸው የሚመረጡት የመጨረሻ ጫፍ ላይ ባለ ግለሰብ ወይም በጥቂት ቡድኖች በተመሳሳይ መንገድ ስለሚሆን ነው። ይህ ምንም ዓይነት አቅም የሌለው «የሠራተኛው ክፍል» «ከገዥው መደብ» በምን ያህል ርቀት ላይ እንዳለ የሚያሳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪም እነዚህ በ«ሕዝባዊ ዲሞክራሲ» ሽፋን ከእነርሱ በፊት የነበሩትን

በመፈንቅለ መንግሥት ወይም በሴራ ገልብጠው ሥልጣን ላይ የወጡ ቡድኖች የሚሠሩት በሕዝብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ወይም የሕዝቡን ደኅንነት የሚያስጠብቅ ስለመሆኑ ምን ዋስትና ይኖራል? እንዲያውም በተቃራኒው ከአገር አገር የሚታየው የሀገር ሀብት ብክነት የኢ-አስተዳደር ሕጋዊነትና የሕዝብ ሥቃይ እየበረታ መሄዱን መመልከቱ በቂ ማስረጃ ነው።

በመላው ዓለም ጎልቶ የሚታይ ተመሳሳይ ነገር ቢኖር የካፒታሊዝምን ወይም የኮሚኒዝምን ሥርዓት በመምረጥ መከተል ያለው ስሕተት ነው። ስለዚህ ከነዚህ ሥርዓቶች ውጤት የተነሳ በጣም የበዙ ስሕተቶች ሊያንሰራሩ ችለዋል። በካፒታሊስቱ በኩል ከሚታዩ መሠረታዊ ስሕተቶች ውስጥ አንዱ ሰው በራሱ መልኩም ስለሆነ የተጣለበትን ኃላፊነትና ሥራ በከፍተኛ ብቃት የመወጣት ችሎታ አለው የሚለው እምነት ነው። ይሁንና ግን ይህን ኃላፊነት በነፃነት ፊት ነው የሚወጣው ተብሎ የሚታሰበው

ጉዳይ በሚገባ አልተብራራም። ስለዚህ የካፒታል ባለንብረቶችን ወይም ባለአክሲዮኖችን አስመልክቶ እንዲህ ዓይነቱ ኃላፊነት ቢኖር ኖሮ ብዙዎችን ሊያረካ እንደሚችል ይገመታል። ተደጋግሞ በሥራ ላይ የዋለው ሌላው ስሕተት ደግሞ ብዛት ያላቸው የራስ ወዳዶች ስብስብ መልካም ፍቃድ ያለውና ራስ ወዳድ ያልሆነ የሆነ አደራጅ ካምፓኒ ሊፈጥር ይችላል የሚለው እምነት ነው። እንዲሁም በካፒታሊዝም ውስጥ ካሉት እጅግ አስቸጋሪ ነገሮች አንዱ ሥርዓቱ የተገነባው በቁስ አስላፊነትና ሲሆኑም በትርፍ ማግበስበስ ላይ ነው። በኮሚኒስቶች በኩል ያለው ሁኔታም ቢሆን ከዚህ የተሻለ አይደለም እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ የከፋ ነው። በብዙ አካባቢዎች ሰዎች «የሠራተኛው መደብ አምባ ገነንነት» እስከተመሰረተ ድረስ አንድ ሰው መልካም ይሁን መጥፎ ግድ እንደማይሰጣቸው ይታወቃል። ይህ አስተምህሮ በብዙ አገር ያሉ ሠራተኞችን አንድ ቀን አዲስ ሥራ ለመሆን እንበቃ ይሆናል ወይም ቢያንስ በመንግሥታችን አስተዳደር ውስጥ ተሰሚነት ይኖረናል የሚል እምነት እንዲያድርባቸው አድርጓል። ግን ሁላቸውም ይታለላሉ። በማንኛውም የኮሚኒስት ሀገሮች

ውስጥ ሠራተኞች ፈፅሞ አስተዳድረው አያውቁም። ሥልጣን ለመጨበጥ የሚቋምጡ ከሆነ «በሰፊው ሕዝብ ላይ የኀብር ጥቃት በመሰንዘር ከመንገዳችን ላይ ዞር ለማድረግ እናመነታም» የሚል ርእሰ-መሪዎቻቸው የታጠቁት በሁኖር መሳሪያ እንደያዙ አልገባቸውም ማለት ነው። መቶ ዓመት ሊደፍን ምንም ያህል እስካልቀረው ድረስ አንድ ደርዘን በሚሞሉ አገሮች ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ለረዥም ጊዜ ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም በሚሉ የበዙ ባዶ ተስፋዎች አማካይነትና አስተምህሮ አገዛዝ ሥር ሆኖ በጥቂቶች በጭካኔ ሲገዛና ሲማቅቅ ኖሯል።

ድኅነው

የፖለቲካው ሥርዓት ምንም ይሁን ምን በማኅበረሰቡ ውስጥ ምን ጊዜም ድኻ ይኖራል። እጅግ አሳሳቢው ነገር የደሃ ሕዝብ መኖር ሳይሆን ችግሩ ድህነትን በተመለከተ ምን ማድረግ [illegible]

[illegible]

በየዘመኑ ሁሉ ኅብረተሰቡን ለማረጋጋት እና ሰዎችን በሕይወት ለማኖር እነሰም በዛም እዚህም እዚያም በሚደረጉ እርዳታዎች ረሃብተኞችን የሚመግቡና ለድሆች «የሚመጸወቱ» ከጥላ ጎደል የተደራጀ ሥርዓት ነበር። ምንም እንኳ ይህ በአብዛኛው «መልካም» ተግባር ቢሆንም ከበስተጀርባው ግን ድህነትን አይነኬ የሚያደርጉ ብዙ ምክንያቶችን የሚጋብዝ ነው። ይህ በምንም መልኩ አጥጋቢ አይደለም። በዚህ ጉዳይ ላይ የኮሚኒስት ሥርዓት አዋጪ ያለው መፍትሔ ጥሩ የሚባል አይደለም። ሥራ አጥ የለም እያሉ በአደባባይ ይመጻደቃሉ። ይህ ፖሊሲአቸው እጅግ መናኛ በሆኑ ዘዴዎች ይተገበራል። ፋብሪካዎች፣ መስሪያ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ወዘተ... ፈለጉም አልፈለጉም በሠራተኞች እንዲታጨቁ ይገደዳሉ። የሚሰጠው ሥራ እና ክፍያው እዚህ ግባ የማይባል ነው። የታሪኩ ሌላው ገጽታም ቢሆን ምንም የተሻለ አይደለም። መላውን ሕዝብ ከዓመት ወደ ዓመት «ለሠራተኛው መደብ» ሊመጣ በሳለው ገነታዊ ሕይወት ብሩህ ተስፋ የመግቡታል።

በነዚህ አገሮች የሚኖረውን ሰፊውን ደሃ ሕዝብ ሁሉም ሰው ከካፒታሊስቶች ቀንበር ከተላቀቀና ሁሉም ሥራውን ካገኘ ሁሉም ሰው ይበለጽጋል በሚለት እየደጋገሙ ይደሰኩሩለታል። ያን ጊዜም ‹‹መደብ አልባ›› ኅብረተሰብ ይፈጠራል ይላሉ። ይህ ግን በሦስተኛውም የኮሚኒስት ሀገር ሲሆን አልታየም። ሌላው ቀርቶ ‹‹ሞዴሎች›› ወይም ‹‹የሠራተኛው ሕዝብ ምድረ ገነት›› ነን በሚሉትም ዘንድ አልሆነም። ከአንድ ወይም ሁለት ትውልድ የኮሚኒስት አገዛዝ በኋላ እንደታየው የማይጠቅሙ ብዙ-ሥራዎች ላይ የፈሰሰው የሀገር ሀብት እንዲሁ በከንቱ ባክኗል፤ መሪዎቻቸው በቅንጦት ሲኖሩ ድኅነት ግን በእጅጉ ይጨምራል። ሰፊው ህዝብ ተራ መኖሪያ ቤትና የዳቦ ያለህ እያለ ሲጮህ እነሱ ግን የሚያምሏሉና የሚያብረቀርቁ የበጋ ወራት የእረፍት ቤቶችና ግዙፍ ቪላዎች ወይም ውድ ባለግንብ ቤቶች አንዳንድ ጊዜም ቁሳቁሶቻቸው በወርቅ ያሸበረቁ የነሱ መታጠቢያ ክፍሎች ያላቸው [illegible]

[illegible]

የድሆች ጉዳይ ልዩ ትኩረት ማግኘት ይኖርበታል። ችግሮቻቸውም በተቻለ መጠን ፍጹም የተለየ መፍትሔ ይሻል። እያንዳንዱ ድሀ ሰው ለገዛ ራሱ ባልንጀራና ለማኅበረሰቡ የተለየ ስጦታና የተወሰነ ኅላፊነት ያለው የማኅበረሰቡ አስፈላጊ አባል ሆኖ መቁጠር ይኖርበታል። ይህ ንይነቱ የግለሰብ ስጦታ በማኅበረ ሰቡ ዘንድ ካልታወቀና ተቀባይነት ካላገኘ ማኅበረሰቡ-ራሱ በማኅበራዊና በመንፈሳዊ ድኅነት እንዳይጠቃ ያስፈራል። እያንዳንዱ ተራና ቅን ሥራ ትንሽ መስሎ ቢታይ ወይም ቢገመት-እንኳ ለሠራው የዕለት እንጀራውን የሚያስገኝ እንጂ የማንም ችሮታ እንዳልሆነ አውቀንና ዋጋ ሊጠው የሚገባ ነው። ሰዎች ለሠሩት ሥራ ተገቢው ዋጋ ባይከፈላቸው ይህ የአሠሪው ስሕተት-ብቻ ሳይሆን የመላው ማኅበረሰብም ስሕተት ነው። የሠራተኛው ገቢ በጣም አናሳ ስለሆነና ምንም የሚያበረክተው ነገር ስለሌለው ማኅበረሰቡ ለዕድገቱ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚገባውን አንድ ጥሩ ደጋፊ ያጣል። ‹‹ባለ አንድ ሳንቲም ገጽታ ሁለት ሳንቲሞች ሆኖ አያውቅም›› ይህም የጉጉሀ ሠራተኞች ክፍያ ርካሽ እስከሆነ

ድረስ የአባባሉን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡ ትጉህ ሠራተኞች ተገቢውን ክፍያ ቢያገኙ ኖሮ ገንዘባቸው በገበያ ውስጥ ሊዘዋወር በቻለ እንዲሁም ዜጎቻቸውንና ማኅበረሰቡን በጠቅላላ ሊያግዝ በቻለ ነበር፡፡ እንዲሁም አዳዲስ የሥራ መስኮች በተፈጠሩ እና ማኅበረሰቡንም ለብዙ የሥራ ዓይነቶች ብቁ እንዲሆን ባስቻሉት፣ ድኅነትም ይንሰራፋል፡፡ ይህ ሐቅ በሁሉም ማኅበረ ሰብ ውሰጥ ሊጠና የሚገባው ነው፡፡

## የቤተ ክርስቲያን ተግባር

ቤተ ክርስቲያን በነዚህ ኢኮኖሚያዊ፥ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሥርዓቶች ላይ የሚደረገውን ውይይት በተመለከተ ወገናዊ መሆን ፈፅሞ አይቻላትም፡፡ ስለሆነም ኮሚኒዝምን ተቃውማ ከካፒታሊስቱ መወገን ወይም የዚህን ተቃራኒ ማድረግ አይኖርባትም፡፡ ቀደም ሲል በዚህ ምዕራፍ ላይ እንደተገለፀው ሁሉ በሁለቱም ሥርዓቶች ውስት ብዙ የአስተሳሰብና የተግባር እንከኖች ስላሉ አንደኛውን ወይም ሌላኛውን መወገን ትልቅ ስሕተት ይሆናል፡፡ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ቤተ ክርስቲያን ለጌታዋና ለመሪዋ ታማኝ መሆን ይገባታል፤ በዚህም መንፈስ ሆና የማስተማርና የመገሰፅ የነቢይነት ግዴታዋን መወጣት የኖርባታል፡፡

አንዱ ግዴታዋ ሰው በተፈጥሮው ኃጢአተኛ መሆኑን ማሳየት ነው፡፡ ይህ ማለት በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ያሉ ታማኝና ቅን የሚመስሉን ሰዎች ሊፈተኑና ስሕተት ሊፈጽሙ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በማኅበረሰባችን ውስጥ ጉዳያችንን እንዲፈጽምልን ወይም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እንዲመራን ብለን በማንም ሰው ላይ ፍጹም የሆነ እምነት መጣል አይገባንም ማለት ነው፡፡ ይልቁንም በመሪዎችና ባለሥልጣኖች ላይ ቁጥጥር ሊኖር ይገባል፡፡ አንድ ሰው ባለሥልጣን እንኳ ቢሆን እርሱ ራሱ ለጥ ብሎ የሚገዛለት አንድ ዓይነት ገዢ ሕግ መኖር አለበት፡፡ በአንድ ግለሰብ ወይም በጥቂት ግለሰቦች እጅ የተያዘ አምባገነንነት

ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም። በእንዲህ ዓይነቶቹ ሥርዓት ውስጥ መኖር የሰውን ክብር ይነካል።

ይህ በተመሳሳይ መልኩ ሁሉንም ዓይነት የንግድና የሥራ መስኮችን ይመለከታል። «ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ስለሆነ» (1 ጢሞ. 6፥10) ጥቂቶች በሀብት፥ በገንዘብና በአብዛኛው ሕዝብ ላይ የማይገሰስ ልጓን ከጨበጡ ለሕዝቡ እጅግ አሰቃቂ አደጋ ይሆንበታል። አንድ ግለሰብ በቀናነት በእንዲህ ዓይነቱ ሥልጣን ላይ ሊቀመጥ ይችል ይሆናል፤ ይሁንና ግን በዚህ ዓይነቱ ሥራ ላይም ሆኖ ሥልጣኑን ተከትለው ሊመጡ የሚችሉ ፈተናዎች እጅግ ብዙ ናቸው ። ነገሮችን በማጣመምና ጥቁሩን ነጭ ነጩን ጥቁር በማድረግ ሁልጊዜ እውነትን አዛብቶ ማቅረብ ይቻላል። በመሆኑም አስከፊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ እንደ መልካም ተግባርና ለሰዎች ጥቅም እንደተደረጉ ይገነቱና ልግስና ተደርገው ሊቀርቡ ይችላሉ። እዚህ ላይ ቤተ ክርስቲያን የበዛ

ኃላፊነት ይኖርባታል። ይህ ማለት በማይረቡና ትርኪምርኪ በሆኑ ተራ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን ታማኝነት፥ ፍትሀዊነትና የፅድቅ ሥራዎች ለአደጋ ከተጋለጡ «ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ማሰማት» ይኖርባታል ማለት ነው። ከላይ ( በገፅ ---) እንደተገለጠው ሁሉ ጨዋነት፥ ታማኝነት፥ የድሆች መብት እና ወዘተ... በከፍተኛ ተቋማት በግልጽ ከተጣሱ ፍትህና የጽድቅ ሥራዎች ወደ ጎን ከተገፉና ከተረገጡ የቤተ ክርስቲያን የውግዘት ድምፅ ከፍ ብሎ መሰማት ይኖርበታል።

አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተቃውሞ ቢያሰማና የዚያች አገር የፖለቲካ መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን ሰዎች ቢያስሩና ብዛት ያላቸውን ተቋሞቿን ቢዘጉ ምን ይሁን? በቤተ ክርስቲያን በኩል ጉዳዩ በእውነትና በትጋት የቀረበ ሆኖ አስከፊ ስደት ቢደርስባት እንኳ ሁኔታው ተረታች ማለት አይደለም። ይህም የሚሆነው የራሱዋንና የሌሎች ብዙ ሰዎችን ነፍስ አድናለችና ነው። ይህ አንድ፥ አሥር፥ ሀያ፤ ወይም ሰላሳ ዓመት ሊፈጅ ይችል ይሆናል። ያን ጊዜ ደግሞ

ነገሮች ሁሉ ተመልሰው ጤነኛ ሊሆኑ ይችላሉ። የተዘራው ዘር ለመከሩ ፍንጎ ሁኔታንና ጽድትን እንዳጸቁል። እዚህ ላይ የተጠቀሱ ጉዳዮችን በተመለከተ ቤተ ክርስቲያን የእውነትና የጽድቅ ጠበቃ መሆን ብቻ ይኖርባታል እንጂ በምንም ዓይነት መልኩ በፖለቲካ ተጽዕኖ ሥር መውደቅ አይኖርባትም። በአምባ ገነን ግለሰብ እጅ በጥይት ተመቶ የተገደለ አንድ ጀግና ሊቀ ጳጳስ ቢሞትም በታሪክና በሰዎች ሕሊና ውስጥ ለዘላለም ሕያው ሆኖ ሲኖር አምባ ገነኑ ግን ምንም እንኳ በሕይወት ያለሁ «ጎበዝ» ነኝ ብሎ ቢያምንም በቁመ ግን መንፈሳዊ ሞትን ሞቷል፣ ወይም በቁመ የሞተ ነው።

በብርቱ ምስጢር የሚከናወነው ሌላው የቤተ ክርስቲያን ግዴታ የነፍሳት እንክብካቤ ነው። በዚ እንክብካቤ የሚያገኙ በሥቃይ ሕይወታቸውን የሚገፉና የማኅበረሰቡ አካል የሆኑ ግን የማይታወቁ አያሌ ድሆች ሁልጊዜም ይኖራሉ። ለምሳሌ እነርሱን

የሚያዝናናቸው የለ/ በድሆች የሚገዙበት ሰውነ እንዲኖር ብቻ ባለው መልኩ በግልጽ በመሥዋዕት ልንረዳቸው እንችል ይሆናል። ይህን መሰል ብዙ ጉዳዮች በመኖራቸው እንደዚህ ዓይነቱን ነገሮች በታደርግ «በጥትህ መለከት ማስነፋት» (ማቴ. 6፡2) ብልህነት አይሆንም። ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ሰዎችን የምንረዳ አገልግሎት በመስጠትና የግል እገዛ በማድረግ ወይም ተጨማሪ እርዳታ ወደሚያገኙበት ሰዎች ወይም ተቋማት በመውሰድ እገዛ ማድረግ ይቻላል። በእርግጥ እንደ «ርኅሩኅ ማዳኛዎች» የሚቋቋሙ የበጎ ሥራ እርዳታ ዓይነት እዚጋ ሊኖር ይችላል። ቤተ ክርስቲያን ያሰማሰበሰ ከዚህ የበለጠ መሥራት ትችላለች። ቤተ ክርስቲያን ፍቅር ካላት ይኖራትም ዘንድ ግድ ነውና እውነተኛውንና «የፍቅር ተግባሮችን» የሚያስገኘውን ልግስና ለማድረግ መንገዱ ተና ይሆንላታል፣ እነዚህም «የፍቅር ሥራዎች ናቸው»

በተንቀሳቃሽ የኢየሩሳሌም ታላላቅ ካቴድራሎችና እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስና በሐዋርያቱ ከተነገሩት በተጓዳኝ ማርቲን

ሉተር በትልቁ የክርስትና ትምህርት መጽሐፉ ውስጥ የተናገረውን ደግሞ እንጥቀስ፡

«በየዕለቱ በሚያገኘው ሰንቲም የዕለት ጉርሱን የሚገፋ (ዛሬም እንደነዚህ ዓይነቱ ብዙ ሰዎች አሉ) አንድ ደሃ ሰው ወደአንተ ቢመጣ እያንዳንዱ ሰው ባንተ መልካም ፈቃድ ብቻ ይኖር ይመስል አጥንቱን ሰርስር እስኪሰማው ከፍ ዋጋ አድርገህ ብታመናጭቀው እንዲሁም ያለ ምንም ውለታ መስጠት ሲገባህ በትምክህትና በትእቢት ብትናገረው ተሸማቆና ተኮራምቶ እያዘነ ይሄዳል፡፡ አቤት የሚልበት ስለሌለው በጩኸትና በለቅሶ ወደ ሰማይ ይማፀናልና ከዚህ ተጠንቀቅ፡፡ ይህ ከራሱ ከሰይጣን የሆነ ነውና አሁንም ደግሜ እልሃለሁ ተጠንቀቅ፡፡ይህ መታተትና የጻር ድምፅ ባንተና በመላው ጎሰም ላይ ከባድ እዳ ወይም ሸክም ሳያመጣ እንዲሁ በከንቱ አይቀርም፡፡ ምክንያቱም ይህ እንባ ልባቸው በሃዘን ለተሰበረ ድሆች ወደሚራራው ወደ እርሱ ይደርሳል፣

እርሱም ሳይበቀልላቸው አይተውምና ነው፡፡ ግን ይህን ብትንቅና እልኸኛ ብትሆን በራስህ ላይ የምታመጣውን መንገድ ልብ ብለህ እይ፤ በዚህ መንገድ ስኬታማ ብትሆንና ብትበለጽግ በመላው ዓለም ፊት እግዚአብሔርንና እኔን ውሸታሞች ብለህ ለመጥራት ይቻልሃል››

በምድራዊ ነገሮች የፖሊቲካው ሥርዓት ወዘተ... የሚፈጸመውን እነዚህን ስሕተቶች መጠቆም የሌተ ክርስቲያንን የእያዳንዱ ክርስቲያን እንዱ ግዴታ ቢሆንም ከግዴታዎች ሁሉ የበለጠ ትልቁ ግዴታ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ ትልቁ ግዴታ ወይም ኃላፊነት በየዕለቱ በቤታችን በአጥቢያችን በትምህርት ቤቶችና በየሥራ መደባችን ላይ ሆነን የምንሰራው ሥራ ነው፡፡ በእነዚህ ቦታዎች ላይ የእግዚአብሔርን የተቀደሰ ፈቃድ ማስተማርና ማብራራት እንዲሁም በተቻለ ሁሉ የተሰጠ ለማድረግ መሞከር ተግባራችን ነው፡፡ የሕግና የወንጌል ትምህርት ለሁሉም ክርስቲያኖችና በአጥቢያችን ለሚገኙት የኅብረተሰብ ክፍል በሚገባ ከተሰጠ ብዙ ነገሮች በእርግጠኝነት

ሊከሰቱ ይችላሉ። በሥልጣንና በሀብት አማካይነት የሚመጡ ሁሉም ዓይነት ፈተናዎች በሚገባ ይጋለጣሉ፤ ለጋራ ብልፅግና ሲባል ዜጎች ሁሉ ሲያበረክቱ የሚገቡ ግዴታዎችም ተብራርተው ይቀርባሉ። የግለሰቦችና የማኅበረ ሰቡ ሁሉ ደኅንነት ለብዙዎች በጥሪ መልክ ይቀርባሉ። እንዲህ ዓይነቱ ትምህርትና ልባዊ ምክር ብዙ የከፋት ሥራዎችን ያስቀራል፤ እንዲያውም እስከነጭራሹኑ እንዲወገዱ ያደርጋል። በዚህ መንገድ ቤተ ክርስቲያን በዘዴና በብልሀት ጠንክራ ካስተማረች መላው ማኅበረሰብና አብዛኛው ዜጋ ይጠቀማል፤ ይበለጽጋልም።

እዚህ ላይ አንድ እርምጃ ወደፊት መሄድ እንችላለን። ባለፉት ትውልድ ውስጥ ክርስቲያኖች በተሻለና በግልጽ መንገድ ግዴታቸውን ተወጥተው ቢሆን ኖሮ ካፒታሊዝምና ኮሚኒዝም የሚባሉ ጤናማ ያልሆኑ ነገሮችን ማስወገድና በዓለም የታሪክ መድረክ ላይ ፈጽሞ እንዳይታዩ በተቻለ ነበር። አሁን ግን ከታዩ ዘንዳ ምን መደረግ እንዳለበት ማሳየቱ የቤተ ክርስቲያንና የክርስቲያኖች ተግባር ነው። ይህም በዓለም የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ እንዴት በአግባቡ መኖር እንዳለባቸው የሚያሳየውንና የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን ሕግንና ወንጌልን ማቅረብ ነው። እዚህ የተጠራነው በማንም ላይ ጌታ ለመሆን ወይም የማንም ባሪያ ለመሆን አይደለም። የፈለገው ዓይነት ገፅታ ይኑራቸው ሰይጣንንና አምባ ገነኖችን ለማገልገል አይደለም፤ ይልቁንም እዚህ የተጠራነው ለመኖር÷ ለመሥራትና ለማገልገል ነው። እናም በዚህ ሁሉ ውስጥ እንደ አንድ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ጓደኛሞች ‹‹ጎረቤታሞች›› ወንድማማችና እኅትማማች እንድንሆን ነው።

## ምዕራፍ 17

# ክርስቲያናዊ ምስክርነት

በክርስቲያኖች ሁሉ ዘንድ በቃልና በአካሄድ የሚደረግ ምስክርነት የሥነ ምግባራቸው አንዱና ዋነኛው አካል በመሆኑ ይህ ክፍል በመጀመሪያው ርእስ ላይ መቀመጥ ነበረበት። ሌላው መንገድ ደግሞ እያንዳንዱን ምዕራፍ «በዚህ ምዕራፍ የተነገሩ ሁሉ ቀጥሎ በተመለከቱት መንገዶች ለክርስትና ምስክርነት ሊውሉ ይችላሉ...» በሚል ማጠቃለያ መቋጨት ይቻላል። ይሁንና ግን የክርስትና ምስክርነት ዘርዘር ባለ መንገድ በቅድሚያ ነጥብ በነጥብ ሊቀርብ ይችላል የሚል ግምት ሊያሳድር በሚችል ይህ የኋለኛ ዘዴ በመጠኑም ቢሆን አደጋ ያለው ሆኖ ነበር። ይህ ዘዴ ምንም እንኳ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጊዜ እየተተገበረ ያለ ይሁን [illegible]

[illegible] እያንዳንዱ ዝርዝር መመሪያ ወይ የይስሙላ ንድፍት ሥነ ምግባር የሚያስመራ ከመሆኑም ሌላ ፈሪሳዊነትም ነው። እንዲህ ዓይነቶቹ ሥነ ምግባሮች መጥፎና ክፉን የመለየት ክህሎት-ተበሉ ይጠራል። በክርስትና ሥነ ምግባር ውስጥ የሚያስፈልገን በእያንዳንዱ ጥቃቅን ጉዳይ ላይ የሚቀርብ ዝርዝር ማብራሪያ ሳይሆን አቅጣጫ ጠቋሚ መርሆዎችን ነው። እንዲህ ዓይነቱ መርሆዎች በሌሎች የክርስቲያን ሥነ ምግባር ጉዳዮች በጥብቅ የሚፈለጉ ከሆነ ለክርስቲያን ምስክርነትም ያላቸው አስፈላጊነት ከዚህ ያነሰ አይሆንም።

### ክርስቶስን መምሰል

ይህ ቃል ብዙ ጊዜ የክርስቲያን ምስክርነት ከሚለው አጠቃቀም ጋር ይመሳሰላል። ይሁን እንጂ በተለይ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በተገናኘ «መምሰል» የሚለው ቃል በቀላሉ አለመገንዘብን ይፈጥራል። በእያንዳንዷ የየዕለቱ ሕይወታችን ክርስቶስን «ለመምሰል» እንጥራለን የሚለው አሳብ ወይ በስተ-

መንገድ ይወስደናል። ስለሆነም ይህ አመለካከት ስሕተት ነው። ምክንያቱም የክርስትና እምነትና ሕይወት ሥርዓታዊነት ሆኖ የሕግ ጉዳይ ብቻ ሆኖ እንዲቀር ከማድረግ ጋር የሚመሳሰል ስለሚሆን ነው። ከዚህ በተጨማሪ አገልግሎታችን ከክርስቶስ አገልግሎት የተለየ በመሆኑ በዚህ መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስን መኮረጅ ስሕተት ይሆናል። እርሱም ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ልጅና የዓለም አዳኝ ነው። አብዛኛው ምድራዊ ሕይወቱ በመሲህነት አገልግሎቱ የተጠመደ ነበር። ይኸውም በመጀመሪያ ለሚያምኑበትና ለማያምኑት ሁሉ ተስፋ የተገባው መሲህ ወደ ዓለም መምጣቱን በማስተማርና በማሳየት ነበር። የመሲህነቱ ሥራ ደግሞ የተገለጠው በሥጋዌ፣ በሞቱና በትንሣኤው ነው። በእነዚህ ጉዳዮች ማንም እርሱን ሊከተል አይቻለውም። በእርግጥ ክርስቲያኖች ስለእነዚህ ነገሮች ሊመሰክሩ ይችላሉ፤ ግን በተግባር በማሳየት ሊመስሉ አይችሉም።

እነዚህ ጉዳዮች በተለየ ግልጽ በሆነ መንገድ በቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ተብራርተዋል "የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና።" (1 ጴጥ. 2፥21)። እዚህ ላይ በተለይ በግልጽ የሚታየው ክርስቶስን የመምሰል አስተምህሮ ከሌሎች አስተምህሮዎች ተነጥሎ ሊታይ አይችልም። ስለዚህ ክርስቶስን መምሰል በክርስቶስ ሥጋዌ፥ ሞትና ትንሣኤ አማካይነት በተገኘው ድነትና የቤዛነት ትምህርት ጋር አብሮ መሄድና በዚህም ላይ መመሥረት ይኖርበታል። በዚህ መሠረት ላይ ያልቆመ ክርስቶስን መምሰል ሙሉ በሙሉ ሐሰት ይሆናል።

ስለዚህ "ክርስቶስን መምሰል" የሕግና የመታዘዝ ጉዳይ ብቻ አይደለም። በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ሁሉም ያየነውንና የተረዳነውን እንደ ትእዛዝ ወስደን በሕይወታችን ሁሉም ማከናወን አለብን ማለት መሆን የለበትም። ይልቁንም ክርስቶስን መምሰል በክርስቶስ ላይ እምነታችንን ማኖርና ከዚህ እምነት የሚፈልቀውን ሕይወት መረዳት ነው። እነዚህን ቃላት መረዳት ከራሱ ከክርስቶስ

ትምህርት ጋር የሚጣጣም ነው። «ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው ብታምኑ ነው» «እናንተ ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ» (ዮሐ. 6፥29፤ 15፥27)።

## እውነትን መፈለግና ስለ እውነት መመስከር

እንደ ቅድስና፥ ጽድቅና ፍቅር ወዘተ... ሁሉ እውነትም በተመሳሳይ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። የእግዚአብሔር እውነት የተገለጠልን በቃሉና በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በሰው ውስጥ እምነትንና የቅድስና ሕይወትን ለመፍጠር ይሠራል። መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል። እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል በማለት ክርስቶስ ተስፋ ሰጥቷል ዮሐ. 14፥26 ይህ «ወደ እውነት ሁሉ» የሚመራውንና ክርስቶስን እንድናከብር የሚያግዘን ነው (ዮሐ. 16፥13-14)።

እውነት የክርስትና አስተምህሮ መሠረት እንደ ሆነ ሁሉ በተመሳሳይ መንገድም ለክርስትና ምስክርነትና ለሥነ ምግባር መሠረት ሊሆን ይገባል። «ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንንም ማድረግ አንችልም» (2 ቆሮ. 13፥8)። ሥነ ምግባራችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ያነገበ ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስና ትምህርቱ ደግሞ መሠረት ሊሆነው ይገባል። በመሆኑም የእግዚአብሔርን ቃል በቸልታ ማለፍ የማይቻል ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል አስፈላጊነት በብዙ መንገድ ማረጋገጥ ይቻላል። በክርስቶስ ሳያምኑ በክርስቶስ የሚሆን ሕይወት ወይም ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ሊኖር አይችልም። በአንጻሩ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና በቅዱስ ቃሉ አማካይነት ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ካላደረገ በስተቀር እንዲህ ዓይነቱ በክርስቶስ የሚሆን ሕይወት ሊኖር አይችልም። በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠን ተስፋ ይህ ነው፤ «በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» (ዮሐ. 8፥31-32)።

እውነት የድነትና የነፃነት መሣሪያ ብቻ አይደለም። በግላችን ለመኖርም ሆነ ከሌሎች ጋር በኅብረት ለመኖር የሚያስችለን እጅግ በጣም ጠቃሚ መሣሪያም ነው። ይህንንም ደግሞ በእለታዊ መልክ ማሳየት ይቻላል። በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት በሕይወቱ ውሸትን የመሠረት ብሎ የያዘ አንድ ሰው ቢያጋጥመን ይዋል ይደር እንጂ በሁሉም ነገር ይህ ሰው በስሕተት መንገድ ላይ መሆኑን እንረዳለን። በመጨረሻም ይህ ውሸቱ ሊረዳውም ሆነ ሊያድነው አይችልም። እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ የተሳካለት ቢመስል እንኳ ከሞተ በኋላ ፍጹም ውድቀት የሚደርስበት ይሆናል። ይህ ሐቅ አንድ አስገራሚ ትምህርት ይሰጠናል። ለማከናወን የምንመኘውን የምናከናውነው «በእውነት ብቻ ነው» ሥነ ምግባራዊ ሕይወታችንን መሠረት ያለበት መርህ ይህ ነው። ይህ ደግሞ ክርስቲያኖች ለሚኖሩበት ማኅበረሰብ ማበርከት ከሚችሉአቸው ትልቅ ነገሮች መካከል አንዱ ነው። ጌታውም «ለእውነት መመስከር» (ዮሐ. 18፥37)።

እውነት ማንኛውንም ዓይነት የሕይወት ዘርፍ የሚመለከት ጉዳይ ነው። የክርስቲያኖችን ሕይወት ገላጭ መሆን ያለበት ውሸት ሳይሆን እውነት ነው። እውነት በእምነትና በክርስቶስ ያለውን ምሉዕ ሕይወት «ሕያው የሆነ ሕይወት» በሚል ሊገለጽ የሚችል ባለ ብዙ ዘርፍ ነው (2 ቆሮ. 5፥17፤ 3 ዮሐ. 14፥6)። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ስለ እውነት ምን ያህል ጊዜ መመስከር አለብን? ለማንና በምን ዓይነት መንገድ መመስከር አለብን? የሚሉ ብዙ ጥያቄዎች መፍትሔዎቹን ማወቅ የግድ ይሆናል።

ከሁሉ አስቀድሞ «ሁልጊዜ እውነት መናገር» እና «ሁልጊዜ መናገር» በሚሉት ቃላት መካከል ትልቅ ልዩነት መኖሩን መረዳት ይገባል። ይህ ማለት ምንም ነገር ከመናገራችን በፊት፥ መናገሩ ራሱ አስፈላጊ ወይም ብልህነት ነው ወይ ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። ምክንያቱም ሁሉም ሁኔታዎችን ሳያጤኑ የሚናገሩ ምናልባትም አስፈላጊ ብቻ ሳይሆኑ አደገኛና ጎጂ ቃላትን የሚሰነዝሩ ሰዎች በሰንበሩ ብዙ

አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ የተነገረው ነገር ተጠባቂ ያልተባለውን ትርጉም እንዲሰጥ በሚደረግበት ሁኔታ ውስጥ እውነተኛ ቃላት እንኳ አልፎ አልፎ አላስፈላጊ የሚሆኑበት ጊዜያት አሉ። ብዙ ነገሮች እውነት ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይሁንና ግን ካለው ሁኔታ የተነሳ በጊዜውና በቦታው መናገሩ አስፈላጊ አይሆንም። በሌላ በኩል ሁኔታዎች የተለዩ ከሆኑ መናገሩ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ይህ ከጥንት ጀምሮ የሚታወቅ ነው። «ለሁሉም ዘመን አለው ... ዝም ለማለት ጊዜ አለው ለመናገርም ጊዜ አለው» (መክ. 3፥1-7)።

## ንግግር፥ እውነትና ፍቅር

የሚነገሩ የማይደመጡ ብዙ ነገሮች አሉ። ይሁንና ግን በእንተ የሚዘነጋውን ጊዜና ፍሬ ቢስ ይዘታቸውን በዓለብ ጉዳት አልባ አለመሆናቸውን ለመጠርጠር ብዙ ምክንያቶች ይኖሩናል።

ንግግሮቻችን ሁሉ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት መመዘኛዎች መፈተሽ ይኖርባቸዋል፤ እውነት ነው ወይ? አስፈላጊ ነው ወይ? ከፍቅር ጋር የሚስማማ ነው ወይ? በዚህ መንገድ ቢፈተሹ ሳይነገሩ የሚቀሩ ብዙ ብዙ ነገሮች ይኖራሉ።

በዚህ ላይ ተቃራኒውን ማየት ይኖርብናል። «እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎ ቢሆን፥ ምስጋናም ቢሆን እነዚህን አስቡ» (ፊልጵ. 4፥8)። ይህ የአነጋገራችንና የአስተሳሰባችን ይዘት ነው። ሆኖም እነዚህ ነገሮች በአጃችን ላይ ላይኖሩ ይችላሉ። በተለመደው የማጣጣም ልምዳችን የምናውቀው ላይሆን ይችላል። እነዚህ በሊቃርያው የተጠቀሱት መልካም ነገሮች የሚንጸባረቁት እምነታቸውን በክርስቶስ ላይ ለማሳደር በተዘጋጁና ሕይወታቸውን ከዚህ እምነት ጋር በሚገጥሙ ክርስቲያኖች ላይ ነው። ይህም ቅድስና ተብሎ ይጠራል።

አነጋገራችንን በተመለከተ ክርስቶስ ባስተማረው ትምህርት ብዙ ጊዜ እየተሳሳትንበት ያለውን አባባል ይጠቁመናል፤ እንዲህም ይላል፦ «እኔ እላችኋለሁ፤ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ ከቃልህ የተነሳ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኮነናለህ» (ማቴ. 12፥36-37) እዚህ ላይ ሰዎች ሌሎች ቃላትን በነፃነት ልንጠቀምባቸው እንችል ዘንድ ማስወገድ ያለብን ቃላት የትኞቹ መሆን እንዳለባቸው ግምታቸውን ለማስቀመጥ ጥረት አድርገዋል። ይህ ብስለት የጎደለውና ወደ ፈሪሳዊነት አስተሳሰብ የሚወስድ የተሳሳተ መንገድ ነው፤ ምክንያም እንዲህ ከሆነ የተከለከሉትን ቃላት ብቻ ትተን ሌሎቹን ቃላት ለመጠቀም ነፃነት እንዲሰማን ስለሚያደርግ ነው። በእርግጥ ክርስቶስ ፍጹም በተለየ ሌላ ነገር ላይ ማተኮር ነበረበት። ለምሳሌ ንግግሮቻችን ሥራዎቻችንን ይመስላሉ፤ በውስጣችን ያለው ነገር የሁኔታችን ማረጋገጫ ነው (ማቴ. 15፥18-20)፤ ስለሆነም ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን

ግንኙነት ያሳያል በማለት ይናገራል። እንዲሁም ደግሞ ከራስ ወዳድነት የመነጩ ስለሆኑና እውነተኛ ፍቅር የጎደላቸው በመሆናቸው አሲያም ከእውነተኛ ፍቅር ጋር የተቆራረጡ ስለሆኑ ነው በማለት ተናግሯል። ከእውነተኛ ፍቅር ጋር የተቆራረጡትን በተመለከተ መጽሐፈ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በልባችን ውስጥ የሆነውን ተግባርም መንፈሱ በውስጣችን ከፈጠረው ፍቅር የተነሣ በውጫዊ ሁኔታችን የተገለጠው የራሱ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። ይህም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ስፍራዎች ላይ በግልጽ ተመልክቶአል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በእርግጥ «በቃል» እና «በሥራ» መካከል የጎላ ልዩነት ሊኖር አይችልም። ልክ እንደ ሥራው ሁሉ ቃላትም በሰው ውስጥ ያለውን ነገር የሚገልጹ ናቸው። እንዲህ ማለት ደግሞ ከስተጀርባቸው በክርስቶስ የሆነ እውነተኛ እምነትና ለባልንጀራ እውነተኛ ፍቅር ከሌለ የአንድ ክርስቲያን ቃላት ፍሬ ቢስ ወይም ከንቱ ናቸው ማለት ነው። እዚህ ላይ «እምነት» ማለት ንጹሕ አሳቢ አመለካከት ወይም ቅንስ አሳብ ወይም አእምሮ ወሰድ ላይሆን «መታመን፦ በእርሱ

ላይ መደገፍ፡፡ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ እምነት እግዚአብሔር ያለ ሥራ በክርስቶስ ጽድቅ ይቆጥርለታል ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ እምነት እግዚአብሔር በክርስቶስ ለሚያምን ሰው ሁሉ ያለ ሥራ ጽድቅን ይቆጥርለታል (ሮሜ 4፥6) ወይም በሌላ መንገድ እንደተገለጸው «የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣል፥ ጻድቅ በእምነት ይኖራል» ተብሎ እንደ ተጻፈ (ሮሜ 1፥17) በሚገል ተገልጾአል።

## ለክርስቶስ መመስከርን በተመለከተ ያሉ ሁለት የግል ፈተናዎች

ከፈተናዎቹ አንዱ በአንድ ተራ ቤጋ ላይ በሕይወት ዘመን አንድ ጊዜ ወይም አልፎ አልፎ ሊገጥመው የሚችል ፈተና ነው። ፈተና ብዙ ሰዎችን ፈጽሞ ላይጋጥማቸው ይችላል። ይህ [illegible]

[illegible] የሚደርሰው ትእዛዝ ሊሆንው ይችላል። በጉዳዩ ላይ በችሎቱ የተሰየሙ ዳኞች የነገሩ እውነት ይቅርና ሐሰት እንዲሆን ሀቁን ለማወቅ በሚያደርጉት ማጣራት በከፍተኛ ደረጃ የሚተማመኑት በምስክሮቹ እውነተኛነት ላይ ይሆናል። ከዚህ አንጻር የተሰጠ ምስክርነቶች እውነትነት ከሌላቸው ትክክል ውሳኔ ላያገኝ ይችላል፤ ወይም የተሳሳተ ውሳኔ ሊሰጠው ይችላል። በችሎት ላይ ሐሰትን መናገር በራስ ላይ ከባድ መዘዝን ሊያመጣ ይችላል። ከሌሎች ሁሉ ይልቅ ለአንድ ክርስቲያን ሊከድ የማይችለው ግዴታ ቃሉን ሊሰጥ እውነቱን መናገር ነው። አንድ ምስክር ስለ ተጠየቀው ነገር የሚያውቀው ምንም ነገር ከሌለ ስለዚህ ነገር የማያውቀው ነገር የለም ብሎ መናገር አለበት። ነገር ግን ለችሎቱ የሚያውቀውን ነገር መናገር አለበት። የሚሰጠው መልስ ለሁሉም ወገን አድሎ የሌለውና ፍጹም እውነት ነው እያለ መናገር አለበት። አንድ ክርስቲያን በችሎት ላይ መናገር ያለበት እውነት ብቻ የሚሆነው የሉተራውያን የእምነት መግለጫ ነው።

ምስክርነትን በተመለከተ ሌላው ፈተና ሁልጊዜ ሁሉንም ሰው የሚያጋጥም ፈተና ነው። ይህ ዓይነቱ ፈተና ‹‹ክብርን›› እና ‹‹መልካም ዝና›› በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ያርፋል። የሌሎችን ሰዎች ክብርና ዝና መጉዳት ፍጹም ስሕተትና አሳፋሪ መሆኑን ማወቅ ለእኛ ጠቃሚ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? እነዚህን ነገሮችን በተመለከተ ማርቲን ሉተር በትልቁ የክርስትና ትምህርት መጽሐፍ እንዲህ ሲል አብራርቶአል። ‹‹ከግል ሰውነታችን÷ ከትዳር አጋራችን÷ ከጊዜአዊ ጥሪታችን በበለጠ የምንሳሳለትና እንዲኖረን የምንፈልገው (ያልጎደፈ ቅን ሥምና የማይገሰስ የመልካም ዝና አንጸባራቂ ምስክርነት) ነገር አለ፤ እርሱም ክብርና መልካም ምስክርነት ነው። በሰው ሁሉ ፊት በውርደትና ግልጽ ጥላቻ መመለስ ፈጽሞ ልንሸከም የማንችለው ነገር ስለ ሆነ››። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የሰዎችን ስም ማጥፋትና ሐሜት ሰምተን እናም በበኩላችን እርሱኑ ማራገብ ኃጢአትን መሥራት ቀላል ያደርገዋል። ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶ ማርቲን ሉተር ጽሑፉን በሚከተው መንገድ ይቀጥላል፤ ‹‹በሐሰት መመስከር የአንደበት ሥራ እንጂ ሌላ ምንም ሊሆን ስለማይችል ሁላችንንም የሚያሳስበን (በባልንጀራ ላይ በሐሰት መመስከር) ትእዛዝ ባልንጀራን በጣም በመቅረብ ለመጉዳት የሚደረገውንና በአንደበት የሚሠራውን ኃጢአት መከላከል ነው›› ነው።

ይህ ምዕራፍ ብዙ ሰዎች የተሰማሩበትን የተሳሳተ የሥነ ምግባር ጉድለትን የሚያሳይ ምዕራፍ ነው። የሚያሳየውም የባልንጀራቸውን ክብር ከመጠበቅ የጎደሉና አብዛኛውን ጊዜ የባልንጀራቸውን ‹‹ክብርና መልካም ዝና›› ለመጉዳት ያለ የሌለ ኃይላቸውን መጠቀማቸውን ነው። እዚህ ላይ ብዙዎች ‹‹ባልንጀራዬ ከተሳሳተስ እንዴት ሊሆን ነው?›› በማለት የተቃውሞ አሳብ ሊያነሱ ይችላሉ። ለዚህ ተቃውሞ መልሱ ቀላል ነው፤ ‹‹በሐሜት÷ በሹክሹክታወይም ስሙን በማጥፋት ባልንጀራህን ማቅናት ትችላለህን? ይህ ምን ዓይነት ፈውስ ሊሆን ይችላል?›› በሚል ጥያቄ የሚመለስ ይሆናል።

## ባልንጀራችን ተሳስቶ በሚገኝበት ጊዜ

አንድ ሰው ስሕተት ፈጽሞ ቢገኝ አንዳንድ ሰዎች ለመውሰድ የሚያስቡት እርምጃ ስለ ተሠራው ስሕተት ማራገብና ስለተሳሳተው ሰው ወሬ ማናፈስ ብቻ ነው። በእርግጥ ይህ ፈጽሞ ልቡን ይሰብር ይሆናል እንጂ በምንም መልኩ አይረዳውም። ይሁን እንጂ ይህንን ዓይነት ሰው በእርግጥ ልንረዳው የምንችልበት መንገድ አለ። ይህ እንዲህ በማለት በኢየሱስ ተብራርቷል፤ «ወንድምህ ቢበድልህ ሂደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው። ቢሰማህ ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው። ባይሰማህ ግን በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገሩ ሁሉ እንዲጸና ደግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ። እነርሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት። ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ» (ማቴ. 18፡15-17)። ይህ ቃል በሚከተለው መንገድ በበለጠ ተብራርቶአል፤ «እዚህ

ላይ ይህንን አግባብ የሌለውን አስከፊ ነገር በንቃት መከላከል ትችል ዘንድ ምላስህን እንዴት መግራት እንደሚኖርብህ የሚያሳይ አጭር በጣም ጠቃሚና የላቀ ትምህርት ቀርቦልሃል። እንግዲህ ባልንጀራህን በሚመለከት ለብቻው ወስደህ በመምከር ሊድንና እንዲሻሻል አድርገው እንጂ የጎዳት ወሬ እያዛመትህ በሌሎች ዘንድ እርሱን ለማማት እንዳትበጋጅ ይህ ሕግ ይሁንልህ። በተመሳሳይም አንድ ሰው እገሌ ይህን ወይም ያንን አደረገ ብሎ ቢያወራልህ ያወራልህን ነገር እርሱ ራሱ በዐይኑ አይቶ ከሆነ ሂድና ከስሕተቱ እንዲታረም ምከረው ብለህ ትምህርት ስጠው። አለበለዚያ ግን ምላሱን ይሰብስብ» (ገላቴ የክርስትና ትምህርት)።

## ግዴታ አማራጭ በሚሆንበት ጊዜ

አንዳንድ ጊዜ የክርስቲያን ምስክርነት ግዴታ ስንል ክርስቲያኖቹ እንደ ነገር ግዴታም መሆን አለበት በሚል አረዳድ ሲገለጽ ቆይቶአል። ከላይ (በገጽ 203 እና ተከታዩ) እንደተመለከተው

ይህ ስሕተት ነው። እዚህ ላይ እንደ ማንኛውም ንግግር ሁሉ ዝምታም በራሱ የመናገር ግጼታ ሆኖ ሊቆጠር እንደሚችል አጽንዖት መስጠት ይኖርብናል።

ከሁሉ አስቀድሞ ለነፍሳችንና ለሥጋችን ጥቅም ሲባል የእረፍት፣ የፀጥታና የዝምታ ሰአትና ጊዜ ሊኖረን እንደሚገባ ትኩረት ማድረግ የግድ ይሆናል።እንዲሁም ስላለንበት ሁኔታ ሀሳብና ስሜት በጥሞና ለማጤን እድል ስናገኝ ከሰዎቹ ተገልሎ ለብቻ መሆን አስፈላጊ ይሆናል። ሁላችንም የተለያየን ሰዎች እንደመሆናችን ሁሉ ማንኛውም ሰው እርዳታና ምክር ለመለገስ በሚጓጉ ለፍላፊዎች ሳይረበሽ ራሱን አግልሎ በጽሞና ጊዜውን የማሳለፍ መብት አለው። በማኅበራዊና ኅብረተ ሰባዊ ሕይወታችን ውስጥ እርዳታና የምክር አገልግሎት ማግኘት አስፈላጊ መሆኑ እርግጥ ነው። ይሁንና ግን ይህ ምንጊዜም ሊሆን የሚችለው እርዳታው በሚያስፈልገው ሰው ሁኔታና ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ መሆን ይኖርበታል።

የዝምታ አስፈላጊነት ደግሞ ውስጣዊ ማንነታችንን የሚመለከት ነው። በውስጣችን ያለውን ሀሳብ ስሜት ፈተናና የሕይወት ልምድ ላገኘነው ሰው ሁሉ መግለጡ የሚመከር አይደለም። ለምሳሌ እምነትንና አለማመንን በመሳሰሉ ዘርፎች ላይ ያለውን ተሞክሮ ማስተዋል በጎደለው መንገድ መነገር የሌለባቸው ናቸው። ለማይመለከተው ሰው ቢነገር እነዚህ አስተሳሰቦችና ቃላቶች ብዙ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ። እጅግ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በውስጣችን መያዝ ያሉብን ነገሮች መኖር እንዳለባቸው በዘመናት ውስጥ የኖሩና ቊጥራቸው ቀላል የማይባል ክርስቲያኖች ያመኑበት ጉዳይ ነው። እርዳታና ማጽናኛ የሚያሻን ከሆነ ከሁሉ አስቀድሞ እነዚህ ነገሮች እምነት በሚጣልባቸው አንድ ወይም ጥቂት ሰዎችና በቂ ተሞክሮ ባላቸው ክርስቲያኖች በጣም በጥንቃቄ መያዝ ይኖርባቸዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ቀላል ምሳሌ ማንሣነት ብቻ ይበቃል። የጌታ እናት ማሪያም ከብስራቱ ዕለት ጀምሮ ትልቅ ምስጢር በልቧ ይዛ

ቀይታለች። ምናልባት ምስጢሯን ያካፈለችው ለዮሴፍና የቅርብ ዘመዷ ለሆነችው ለኤልሳቤጥ ብቻ ሊሆን ይችላል። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አማካይነት የእግዚአብሔር ዕቅድ በሷና በልጇ በኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ሲገለጥ ብቻ ነበር የሆነውን ሁሉ ለሁሉም ሰው በይፋ የገለጠችው። በዚህ መካከል ባሉት ዓመታት ውስጥ ለምሳሌ በልጇ ላይ ሲዘባበቱበትና ያለ ርኅራኄ ሲያሰቃዩት ብዙ ስቃይ አሳልፋለች። ሉቃስ በዚህ ጉዳይ ላይ የተሟላ ማስረጃ ያለው ወንጌላዊ ስለነበር ‹‹የዓይን ምስክሮች›› የነበሩትን በደቂቁ (ሉቃ. 1፡1-2) መዝገቡን በግልጽ አስፍሯል። ይህ ሐቅ የሚያሳየው ነገር ቢኖር ወቅቱ የማይፈቅድ በመሆኑ ማርያም በልቧ የነበረውን አውጥታ እንደነገረችው ነው።

የዝምታ አስፈላጊነት ሌላው ገጽታ ደግሞ በሚስጥር ለመያዝ ቃል የገባንላቸውን ነገሮች የሚመለከት ነው። ይህ [illegible]

[illegible]
በጣም ጥብቅ ግዴታ ነው።ለምሳሌ በኑዛዜ ወቅት በተነገሩት ጉዳይ ላይ እንኳ እንዲህ ብሎ ነገሩን በግልጽ ጉራ ከሚነዙ ለፍላፊ ቀሳውስት ገና በበለጠ ደረጃ ጥቂት ነገሮች የቤተ ክርስቲያንን ክብር ይጎዳሉ።እንዲህ አይነቱ አሰራር በሦስት ምክንያቶች እጅግ በጣም የሚያፈርብ ነው። አንደኛ የሰጠውን የእምነት ቃል በግልጽ መጣስ ነው፤ ሁለተኛ እንዲህ ዓይነቱ ካህን በማይታዎቹ ውስጥ ቀዳሚ የሆነውን ነገር የመፈጸም ብቃት ማለትም ኑዛዜን የመቀበልና በዚህ ላይ እቀን የመገንዘብ ብቃት የሌለው መሆኑን በሰሚዎቹ ፊት በግልጽ የሚያሳይ ነው። ሦስተኛ ኑዛዜን ይፋ ያደረገውን ይህንን ካህን ይሁን ሌሎቹን ካህናት ምስጢር የመጠበቃቸውን ጉዳይ ማን ሊያምን ይችላል?

ሌላው የዝምታ ዓይነት ደግሞ ለአያያዝ የሚያስቸግር ግላዊና መንፈሳዊ ነገሮችን የሚመለከት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ዝምታ የሚታየው በተፈጥሮአቸውና በዐበያቸው የተነሳ ከሰው ጋርግንኙነት በማያደርጉ ሰዎች ዘንድ ነው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በዚህ ነገር እንደሚጨነቁ፤ ከዚህ የሚወጡበትን

መንገድ ግን አለማግኘታቸው የታወቀ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ እነርሱን መርዳትና ለመምከር የጎረቤቶቻቸው ግዴታ ይሆናል። ችግራቸው ምን እንደ ሆነ ለመናገር ይዘጋጁ ዘንድ አእምሮአቸውና ልባቸው እንዲከፈት እርዳታ መለገስ እጅግ በጣም ጥንቃቄ የሚሻ ተልዕኮ ነው። የክርስቲያኖች ኅብረት ሊሰጣቸው የሚችለውን እርዳታ ይቀበሉ ዘንድ መርዳትና ብዙ ጊዜ ያላገኙትን በረከት እነርሱም በተራቸው ሌሎችን እንዲረዱ ለማድረግ ማገዝ ደግሞ ግዴታ ነው።

ለብዙዎች ለመቀበልና ለመተግበር እጅግ የሚከብድ የዝምታ ዓይነት አለ፤ ይህም ስለ ጎረቤታቸው ያዩትንና የሰሙትን ነገር በዝምታ የመጠበቅ አስፈላጊነት ነው። እዚህ ላይ የዝምታን አስፈላጊነት መስማት ለሚፈልግ ሁሉ ‹‹መመስከር›› ከሚለው ፍላጎት ጋር ደህና አድርጎ የሚላተምና የሚያምም ነው። ‹‹ሥልጣን ከሌለው በስተቀር ኃጢአት ሲሠራ ቢያየው እንኳ ማንም ሰው ጎረቤቱን በአደባባይ ሊፈርድበትና ሊገስጸው እንደማይፈቀድለት ልብ ማለት ይገባናል። በኃጢአት መፍረድና ኃጢአትን በማወቅ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። በእርግጥ ታውቅ ይሆናል፤ ግን መፍረድ አትችልም። ወዳጄ ኃጢአት መሥራቱን በእርግጥ ሰምቻለሁ፤ በዐይኔም አይቻለሁ፤ ይህንን ኃጢአቱን ለሌሎች ሪፖርት ለማድረግ ግን ሥልጣን የለኝም። አሁን ለመፍረድና ለመወሰን ከተጣደፍኩ እርሱ ከሠራው በበለጠ በኃጢአት ወድቄአለሁ ማለት ነው። ግን በሚሰጥህ ሥልጣን አማካኝነት ለመዳኘትና ለመቅጣት እስከምትበቃበት ቀን ድረስ ኃጢአቱን የምታውቅ ቢሆን እንኳ ሌላ ምንም ሳታደርግ ዐይኖችህን ወደ መቃብር አዙራቸውና ከደናቸው›› (ትልቁ የክርስትና ትምህርት)

## ለውጭው ዓለም የምንመሰክርባቸው ልዩ ልዩ መንገዶች

ደካማና የተሳሳቱ መንገዶች እንዳሉ ሁሉ ጥሩ መንገዶችም አሉ። ቦታውና ጊዜው ምንም ይሁን ምን ትክክለኛና ጥሩ መንገድ ‹‹በእናንት ስላለው ተስፋ ምክንያት›› ነው።

(1 ጴጥ. 3፥15)። እነዚህ ቃላት የተነገሩት ጠላትን እንዲያፈሩ ይልቁንም በልባቸው «ክርስቶስን እንደ ጌታ ያክብሩት» ዘንድ፣ ክርስቲያኖችን ለመገሠጽ ነው። በዚህ ዓይነት መንገድ የሚቀርብ የመመስከር ሰይፍ ከፍርሃትና ድፍረት ከማጣት የተነሳ ሊበላሽብን ይችል ይሆናል። በአንጻሩ ደግሞ ለማያምኑ ሰዎች ክርስትናን መመስከር ምን ትርጉም እንደሚሰጣቸው ባለመረዳታችን ምክንያት ሊበላሽ ይችላል። ስለ ሆነም ብዙ ቃላት መደርደር፥ ስለ ራሳችን፥ ስለ ስሜታችን፥ ስለ ተሞክሮአችን ወዘተ... ብዙ ማውራት ምን ጊዜም ስሕተት ነው። ወይም «ሃይማኖታዊ» ለመምሰል መሞከር ወይም ፍጹም የተለየ አማኝ ለመምሰል መጣር በአብዛኛው «የከንዓን ልሳን» በመባል በሚታወቀው የድምጽ ዘይቤ በመጠቀም ሥክ ባሉና ተፈጥሮአዊ ባልሆነ ድምጽ በመጠቀም ስለ ክርስቶስና ስለ እምነት በመስበክ እውነተኛ ማንነታችንን መደበቅ መቻያም ሊሆን ስሕተት ነው። እንዲህ

ዓይነቱ አነጋገር ጥቂቶችን ለማግለል የሚችል ስለሆነ አብዛኛው ሰው ግን ከፈሰት፥ ከአታላይነትና ከግብዝነት ጋር ስለሚያያዝ አሉታዊ ስሜት ያሳድራል።

ክርስቲያን መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ልብ ብንል በክርስቶስ የሆነ እምነት፥ ለእርሱና ለሥራው ክብር መስጠት ማለት ነው። የክርስትና ምስክርነት ማለት ከሁሉ አስቀድሞ ስለ ክርስቶስ ፤ስለ መንግሥቱና ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ነው ማለት ትክክል ይሆናል። ቃላትንና የድምጽ አጠቃቀምን በተመለከተ በሚገናኛቸውም ሁኔታ ውስጥ በተሰጠን ተፈጥሮ አዊ መንገድ ብቻ መናገር ይመረጣል። የራስ ያልሆነ እንዲህ ዓይነቱ የፈጠራ ድምፅና የተጋነዘ ቃላት ድርደራ የሚማርከው ቀድሞውኑ በውጭ ያሉ ሰዎች ከራሳቸው ዘይቤ ጋር የሚለያዩ ስለሆነ እነርሱን ለመማረክ የምንጠቀመው ምንም ነገር የለም። በውጭ ያሉትን ሰዎች ለመማረክ የበለጠ ከራሳቸው የቃላት አጠቃቀም ጋር በእጅጉ የሚጣጣም ዘይቤ መፍጠር እንችላለን።

እንዲሁም ዕቅዳችን ብዙ ቃላት ከመደርደር ይልቅ

ጥቂት ቃላትን ለመጠቀም አፅንኦት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በጥና ሁኔታ የተረቡ ምንምን ቃላት ጥያቄ የመፍጠር ኃይል አላቸው፡፡ ለጥያቄዎቹ የሚሰጡት መልሶችም እኛ ለመናገር ከምንሠማው ብዙ ቃላት በበለጠ ለአድማጮች አጥጋቢ መልሶችን ይሰጣሉ፡፡

በመጨረሻም ለማቅረብ ያሰብነው የምስክርነት አቅድ የተንዛዛ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ አትኩሮ ቀድሞውኑ የታወቀ ይሆንና የቃሎቻችንን ተጽዕኖ ያሳንስ ይሆናል፡፡ በዚህ ፈንታ ራሱን በራሱ የሚገልጸውን እድል መጠቀም የተሻለ ይሆናል፡፡ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ክርስቲያን ጥበብና ብርታት እንዲሰጠው እግዚአብሔርን ከተማጠነ ጌታ የገባውን ተስፋ እንደሚፈጽምለት ይገነዘባል፤ «የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ» (ማቴ. 10+19)፡፡

[illegible]

[illegible]

ጌታን ለመመስከር የሚያስችላቸውን አጋጣሚዎች መፍራት አይኖርባቸውም፡፡ በዓለማዊ ማኅበረሰብ ይሁን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸው ሥልጣን ምንም ይሁን ምን ይህ የክርስቲያኖች ሁሉ ግዴታ ነው፡፡ ይህ ተግባር «ለባለሙያዎቹ» ማለትም ለካህናቶቻቸው ወይም «ለወንጌላውያን» ወይም በሙያው ለተካኑ የሁድን ሠራተኞች ብቻ የሚተው ከሆነ ስሕተት፥ የሐሰት ትምህርትና ተግባር ይሆናል፡፡

## የክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ ምስክርነት

«የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት» በማለት ፈንታ ብዙ ጊዜ «ትዳሴ» በማለት እንጠቀማለን፡፡ የዚህ ቃል አጠቃቀም የትዳሴ ተርጓሚ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የሚሰጡትን ሁሉ ስብከትንም ጨምሮ የሚያጠቃልል መሆን ይኖርበታል፡፡ «ትዳሴ» ማለት «ሰዎችን ማገልገል» ማለት ነው፡፡ ምንም እንኳ ይህ ሐቅ በአብዛኛው

ትክክለኛ አረዳድ ባያገኝም የወንጌል አማኝ ክርስቲያኖች ቅዳሴ ወይም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በአካባቢያችን ለሚገኘው ኅብረተሰብ÷ ››ለሕዝቡ›› የሚመሰክር መሆን ይገባዋል። በዚህ ጓደኝነት መንገድ ተነጋግረናል፤ ሠርተናልም (ሐ.ሥ. 2፥2-41፤ ማቴ. 5፥13-16)።

ከቃሉ ትርጉም እንደምንረዳው ‹‹ሕዝብን ማገልገል›› የሚል ትርጉም ያለው ‹‹ቅዳሴ›› ሌላም ጎንዮሽ አለው። በኦርቶዶክስ ትውፊት አማኒያኑ መመስከር÷ ለዕለቱ የተመደቡ ክፍሎችን ማንበብ፣ ፀሎት÷ ስብከት ወዘተ... አስፈላጊነት ከሌሎች ክፍሎች ጋር አብሮ መንዝ ይኖርበታል። እርሱም በግሪክ ‹‹ዲያኮኒያ›› ማለትም የቤተ ክርስቲያን ሥራ ነው። የቃሉን ምስክርነት ሊሠሩ ያልቻሉትን ነገሮች ‹‹መልካም ሥራዎች›› ብዙ ጊዜ ሊሠሩ መቻላቸውንና ተደም ሲል ለእግዚአብሔር ቃል ልባቸውን በግልፅ [illegible]

[illegible] የዘመናት ታሪክ ውስጥ ብዙ ጊዜ የተረጋገጠ ነው። ይህ ሐቅ በዘመናት ሁሉ ውስጥ ያሉትን ክርስቲያኖች እንዲህ በማለት ያስባለ። ቃላት በእውነተኛ ፍቅርና ከዚህ ጋር የሚሄዱት የፍቅር ሥራዎችን ማፍለቅ ካልቻሉ ዋጋ ቢስ ናቸው። በዚህ ነገር ላይ የሐዋርያው መልእክት እጅግ ጠንካራና ግልጽ ነው፤ ‹‹በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሺዋሺዋ ጸናጽል ሆኛለሁ›› (1 ቆሮ. 13፥1) ‹‹ወንድሞቼ ሆይ እምነት አለኝ የሚል ግን ሥራ የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?›› ‹‹እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው›› (ይሁዳ 2፥14-17)።

ስለሆነም በራሱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በሐዋርያቱ ትምህርት ካልተነሳሳና በዚህ ላይም ካልተመሠረተ የማንኛውም ክርስቲያን ምስክርነት በአግባቡ ሊሠራ አይችልም።

# ምዕራፍ 18

# በሕይወት መንታ መንገዶች ላይ

## መንታ መንገዶች የት ናቸው?

ሰዎች የት እንደሚደርሱ በቅድሚያ ሲያውቁ አይችሉም። እንዲሁም ደግሞ ማንም በቅድሚያ ሊመርጣቸው አይችልም። ሕን እንዲህ ነው፤ ይሆናል ብለን ባልገመትነው ሁኔታ መንታ መንገድ ላይ እንደርሳለን። አንዳንድ መምረጥ ሲኖርብን የሚያጋጥሙን ግን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ የተሳሳተ ምርጫ አናደርግና ስሕተቶቻችንን እንገነዘባለን። ከዚያም ወደዚያው መንታ መንገድ ተመልሰን የተሻለውን መንገድ እንመርጣለን።

በዚህ መንታ መንገድ ላይ ምርጫው ምን ይሆናል? ምርጫው በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ የተለመዱና ተራ ነገሮች ሊሆኑ ይችላል። ነገር ግን እውነተኛ መንታ መንገዶች ሁልጊዜ በሕይወታችን ስለሉ አስፈላጊ ነገሮች ማለትም እንደ መለወጥ ወይም በእግዚአብሔር ስለማመን ከዓለም፣ ከእግዚአብሔር አንዱን ስለ መምረጥ+ ወደ እግዚአብሔር ስለ መመለስ ወይም እግዚአብሔርን ስለመተው እነዚህን የመሳሰሉትን ነገሮች የሚመለከቱ ናቸው። እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ምርጫዎች ስቃይ ሊያስከትሉ ይችሉ ይሆናል። ምርጫው አልፎ አልፎ «በሥቃይ የለሽ ሕይወት» «በሥቃይ ሕይወት» መካከል ሆኖ ሊገለጥ ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ምርጫ አቀራረቡ በተሳሳተ መንገድ ቢሆንም የሚቀርብልን ግን ከታላቁ ጠላት ነው። ሐሰተኛ መንገዱን የሚያስተዋውቀው ምንም ሥቃይ እንደሌለው የክርስቶስ መንገድ ግን የሚያስቃይ መንገድ አድርጎ ነው። ጉዳዩን እንዲህ አድርጎ የማቅረቡ ዘዴ ውሉ ሳይደር ፍጹም የተለየ ሆኖ ይገኛል። ጠላት እንድንወድቅ ወይም በክርስቶስ ላይ ያለንን እምነት እንድንተው

ካደረገ ኋላ ላይ ተመልሰን ቅሬታ የማቅረብ እድል አይኖረንም። የጥፋት መንገድ የመረጠውን ሰው «እኛ ምን አግዶን? አንተው ተጠንቀቅ» ይሉዋል (ማቴ. 27፥4)።

አንዳንዶቻችን ወደነዚህ መንታ መንገዶች ብዙ ጊዜ እንመለሳለን። አንዳንዶቹ ግን አልፎ አልፎ ሊሆን ይችላል። ይሁንና ግን በመሠረቱ ቀጥተኛ ከባድ ምርጫ ይጋጥመናል። ምርጫው ስለ ምን ይሁን ምን ሁኔታዎችንና የሚያስከትሉትን ውጤቶች መገንዘብ ያሻል። እንዲህ ዓይነቱ የመረዳት ችሎታ በቀላሉ አይገኝም። ይህ ሊገኝ የሚችለው በአንድ መሠረት ላይ በተገነባው ክርስትናና «መንገድ፣ እውነትና ሕይወት» ብሎ ራሱን ከሚጠራው ከእርሱ ጋር በኅብረት በመኖር ነው (ዮሐ. 14፥6)።

## ከእውነትና ከሐሰት አንዱን ለመምረጥ

ይህን የመሰሉ ብዙ መንታ መንገዶች አሉ። ለምሳሌ አንድ የተፈጠረ አደጋ ብናይ የታመመ ሰው ብንጎበኝ ኖሮ፥ በወራሪዎች ወይም በጠላት ጦር እጅ ወድቀን ምርመራ ቢደረግብን ምንድነው የምንደርገው? ወይም በክርስትና መመሪያ መሠረት ምን ማድረግ አለብን? እያንዳንዱን ጉዳይ ይፋ ለማድረግ የሚፈቀድልን እስከ ምን ድረስ ነው? ከተናገርንስ ቃሎቻችንን እንዴት ከእውነት ሕግጋት ጋር ማጣጣም አለብን? በንግግራችን ውስጥ ከእውነት ሕግጋት ጋር የሚጣጣሙ የቃላት አጠቃቀማችን እንዴት መሆን አለበት? በእርግጥ እንደዚህ በመሳሰሉ ሁኔታዎች ውስጥ በብዙ ዓይነት መንገድ ሊተገበሩ የሚችሉ ሥራዎች አሉ። አንዳንዶቹ መንገዶች ትክክል ሲሆኑ አንዳንዶች ደግሞ ስሕተት ናቸው። የመጀመሪያው መንታ መንገድ በመናገርና በዝምታ መካከል ያለ ምርጫ ነው። ለመናገር ከወሰንን ጥያቄው እንዴት እንናገር? የሚል ይሆናል። የሚደረገው ንግግር አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም የለየለት ሐሰት ይሆናል።

ብዙ የፍልስፍናና የሃይማኖት አመለካከት ጎራዎች እዚህ ላይ የተጠቀሱትን ዓይነት ጉዳዮች በዋናነት በሦስት መንገዶች ሲያስተናግዱ ኖረዋል። በመጀመሪያ መንገድ የቀረበው አስተያየት ውጤት ምንም ይሁን ምን መናገርና እውነቱን መናገር ብቻ ነው ይላል። ይህ ለብዙዎች መልካም መስሎ ቢታይም ግን ከእውነተኛውና ተመሳሳይ ጉዳዮች አንጻር ሲታይ አብዛኛውን ጊዜ ከፍተኛ ጉዳት አለው። ሁለት ምሳሌዎችን በማቅረብ ይህንን ጉዳይ ማሳየት ይቻላል። የአልጋ ቁራኛ የሆነ አንድ ሰው ጎብኝቼ በመመለስ ላይ እንዳለሁ አንድ የሆነ ሰው አጋጥሞኝ ስለ ታመመው ሰው የጤና ሁኔታ ቢጠይቀኝ እውነቱን መናገር ስለሚገባኝ ሊሞት እያጣጣረ ነው ብዬ እመልስለታለሁ። በእርግጥ ሕመምተኛውን ሰው በጎበኘሁበት ወቅት እኔም ራሴ በጥሩ ስሜት ውስጥ አልነበርሁም። ሁሉም ነገር የጨለመ በሚመስልበት ሁኔታ ውስጥ ወቅቱ ለራሱ ለሕመምተኛውም ቢሆን የከፋ ነው። እዚህ ላይ እያስታመሙ ከነበሩት ሰዎች ከተሰነዘሩት ጥቂት ቃላት በስተቀር ከሐኪሞች ያገኘሁት ቀጥተኛ መረጃ አልነበረም። ከዚህም የተነሳ ስለ ሕመምተኛው ሁኔታ ለጠየቀኝ ግለሰብ የሰጠሁት መልስ «በትንንሽ» ና ለእኔ እስከገባኝ ድረስ በስንበር እያጣጣረ ነው ብዬ መለስኩለት። በሚቀጥለው ቀን ግን የሕመምተኛው ዘመዶች የተፈራው እንዳልደረሰና ሕመምተኛው እያገገመ እንዳለ ተነገሩቸው። በዚህ ጊዜ ውስጥ እኔ የሰጠሁት መረጃ ወሬው ተዛምቶ ከአብዛኛው ሰው ጆሮ ደርሶ ኖሮ አንዳንድ ሰዎች በቀብሩ ሊታደሙ መዘጋጀት ጀምረዋል። ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለው እርግጠኛ ሆኜ ባልናገርም «እውነቱን እውነት ብቻ» መናገር ግድ ይለኛል በሚል ስሜት ነበር። ምንም እንኳ በዚህ መንገድ መቅረቡ ጭራሽ አስፈላጊ ባይሆንም ይህ ስለ ራሱና ስለ ንግግሩ የቀረበው ታሪክ አንድ መቶና አንድ ሺ ጊዜ የሚሆን የማንም ሰው ታሪክ ነው።

ሁለተኛው ምሳሌ በብዙ አሳዛኝ ምክንያቶች የተነሳ አንድ አገር በጠላት ኃይሎች ወይም በአብዮታውያን ኃይሎች በከፊል ቢወረር ሊከሰት የሚችለውን ነገር የሚያሳይ ነው። የአገር ጉዳ

ለማድረግ ሆኖ ባልኩበት ሰዓት እንዴት እንስተኛ የሰው ቁጥር የያዘች ግብረ ኃይል አጋጠመችኝ። የኃይሏ አባሽ መኮንን ጠጋ ብሎ አገሬ አገሌ የሚባሉ ሰዎች የት ይገኛሉ ብሎ ጠየቀኝ። እንግዲህ መንታ መንገድ ላይ ነኝ ማለት ነው። በትርቡ ባገኘሁት መረጃ መሠረት እንዴህ በሚባል መንደር ውስጥ ተሸሽገው ይገኛሉ ብዬ በመልስለት ውጤቱ አተባሰው ቦታ ሄደው ሊያገኙት አለመቻላቸው ነው። ከዚህም የተነሳ በወሰዱት የበቀል እርምጃ የመንደሯን ነዋሪዎች በጥይት ደበደቡ፤ ቤቶቻቸውንም በእሳት አጋዩ። ግን «እውነትና እውነት ብቻ» መናገር የለብኝም እንዴ? ታዲያ እውነት የት ነበረች? ተፈላጊው ሰው በመንደሯ ውስጥ እንዳለደረ መገመት ነበረብኝ። አሁን በኋ የሚደረብ መልስ ምክንያት ቁጥሩ የበዛ ሰውና የመንደሯ ሕይወት ጠፍቶአል። ግን ለምን ዓላማ? ይህ በዓለም ውስጥ በሚገኙ ብዙ ቦታዎች ላይ የደረሰ ነገር ነው።

ሁለተኛውና በብዙዎች የተረበው መንገድ አሻሚ ተርጉም ሊሰጡ የሚችሉ ቃላትን በመጠቀም በአጠቃላይና በተዛማጅ መልክ መናገር ብቻ ነው የሚል ነው። ከዚህ የአነጋገር መንገድ በስተጀርባ ያለው ዓላማ ቃሎቹ በፈለገው መንገድ ቢተረጎሙም የተነገረው ነገር ውሸት ነው ለማለት በለማያስችል ነው። በሁሉም ነገር ላይ «እኔ ያልኩህ እንዲህ አልነበረም ወይ» ለማለት ይችላል። ነገር ግን ማንም ቅን ሰው ይህንን ዘዴ በመጠቀም እርካታ ማግኘት ስለማይችል ይህንን መንገድ መጠየቁ ይፍርበታል።

ሦስተኛው መንገድ ሆን ተብሎና ታስቦበት የሚደረግ ውሸት ነው። «ነጭ ውሸት» በመባል ይታወቃል። የዚህ አሳብ ደጋፊዎች እንዲህ ይላሉ «እውነት ብናገር አማራጩ ምን ይሆናል? እውነት ብናገር በአንድ ሰው ወይም በብዙ ሰዎች ላይ ጉዳት እንዲደርስም ጥጉ ማድረስ ነው፤ ብዋሽ ግን ብዙዎችን ከዚህ አደጋ አተርፋለሁ» በተጨማሪም ይህንኑ ሀሳባቸውን አሳብ በማጠናከር «እንዲያውም እውነተኛ ጠላት እውነቱን ማወቅ የለበትም» ይላሉ። «በነጭ ውሸት» ላይ የተፈጠሩ ክርክሮች ሁሉ ደካማ ናቸው። እስቲ ሁለት ነጥቦችን ብቻ ልብ ብለህ እናስተዝን።

ሰዎች ስለ ታመመው ሰው የተናገርኩት ውሸት መሆኑን ሲረዱ ታማኝነቴ ምን ሊሆን ይችላል? የጠላት ኃይል ስለ ጠየቀኝ ሰው በሰጠሁት መልስ ሰውየው ባልተሸሸገበት መንደር ውስጥ እኔ ግን እዚያ ነው ያለው ብዬ ብነግራቸው ምን ሊፈጠር ይችላል? ጠላት በመንደሯ ውስጥ አሰሳ ቢያካሄድና ልፋቱ ከንቱ መሆኑን ሲያውቅ የበቀል እርምጃ አይወስድም? ታዲያ ‹‹ነጭ ውሸት›› በረከቱ ምን ላይ ነው?

በነዚህ በሦስቱ የአመለካከት ጎራ አቀንቃኞች መካከል ያለው እንካ ሰላንቲያ ማለቂያ የለውም። ስለዚህ ጥያቄውን እንዳለ ከሌላ አቅጣጫ ማየቱ ተገቢ ይሆናል።

## ከእውነትና ከሐሰት አንዱን መምረጥ የግድ ሲሆን የሚኖረን ምርጫ

በአብዛኛው በአስገዳጅ ሁኔታዎች የተነሳ የሚፈጠሩ ብዙ ውሸቶች ፍጹም አስፈላጊ አለመሆናቸውን መገንዘብ ይኖርብናል። በዚህ ሁኔታ ሥር የሚወድቁ ብዙ ሰዎች ብዙ ይለፈልፋሉ። ማንኛውንም ጥያቄው የማይመለከታቸው መሆኑን ቢያውቁም ለመመለስ ዝግጁ ናቸው። አንድ ሰው ተገቢ መረጃ በእጁ ላይ ከሌለ መልካም ሕግ በሚያዘው መሠረት ይህንን አላውቅም ብሎ መናገር አለበት። አንድ ምሳሌ ብቻ ለማንሳት ያህል ወደ ‹‹የአልጋ ቁራኛ›› ስለነበረው ሕመምተኛ ሰው ጉዳይ እንመለስ ‹‹እውነትንና እውነቱን ብቻ ለመናገር›› ራሳችንን አሳምነን ከሆነ በድንገት በመባነን እጃችን ላይ ያለው እውነታ ከታመነ ምንጭ ስለ ማግኘታችን ምንም ዓይነት አስተማማኝ መረጃ የሌለን መሆኑን እንገነዘባን። ስለዚህ በመጀመሪያ ራሳችንን ቀጥሎ ሌሎችን አሳሳትን ማለት ነው። ይህን ከመሳሰሉ ሌሎች ምሳሌዎች አንድ አጠቃላይ ማስጠንቀቂያ እንውሰድ፤ ማንም ሰው በማንኛውም ጊዜ በማያውቀው ጉዳይ ላይ ቃሉን እንዲሰጥ አይጠበቅበትም እና ነገሩ እንዲህ ከሆነ ደግሞ እሱም በቅንነት ስለጉዳዩ የማውቀው ነገር የለም ማለት ይኖርበታል።

ሊያጋጥሙን የሚችሉ ሁሉንም ዓይነት ምሳሌዎች እዚህ ላይ ማንሳት ስለማንችል ጥቂት አጠቃላይ ሕጎችን ብቻ እንጥቀስ፡፡ በመጀመሪያ እውነት ፣ ፍቅርና ጽድቅ ሁሉ በእግዚአብሔር ውስጥ ያሉና በአንድ ባሕርዩ የተዋሀዱ መሆናቸውን ሁላችንም መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ስለዚህ በእርሱ ዘንድ «በመዞርም በመለወጥም የተደረገ ጥላ የለም»፡ ያዕ1፡17፡፡ ክርስቲያኖች ከሆንን ይህ ዓይነቱ ኅብረት በውስጣችን ሊኖር ይገባል፡፡ በሕይወት መንታ መንገዶች ላይ ብንሆን እንኳ በውስጣችን በእውነትና በሐሰት መካከል በጭራሽ ለውጥ መኖር የለበትም፡፡

ሁለተኛ፡ ይህ ከመጀመሪያው ሀሳብ ሠርጾ የሚወጣ ነው፡፡ ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ለመውጣት ሲባል ውሸትን እንደ አማራጭ መውሰድ በፍጹም አይገባም፡፡

ሦስተኛ፡ ውሸት ላለመናገር ሁልጊዜ አማራጭ አለ፡፡ የእውነት ጠበቃ ሆነን ለመቆም የማይቻለን ከሆነ መፍትሔው

በተለየ መልኩ የሚደረግ ዝምታ ነው፡፡ ይህ ሁልጊዜ ቀላል መንገድ አይደለም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከራሱ ከንግግሩ በበለጠ ከፍ ያለ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል፡፡

አራተኛ፡ ማንኛውም ሰው ሌላውን ሰው ወክሎ እነዚህን ችግሮች መፍታት እንደማይችል ለሁላችንም ግልጽ ሊሆን ይገባል፡፡ ሁሉም ሰው የራሱን ምርጫ የማድረግና ለዚህም ኃላፊነቱን መውሰድ ይኖርበታል፡፡ «አንድ ድርጊት ከተፈጸመ በኋላ አዋቂ መሆን» ሁሉም ቀላል ነው፡፡ አንድ ሰው በዚህ መንገድ አዋቂ ኖኖ ብሎ ካለፈ፣ ሁሉ ሊያደርግ ግን መሰላቱን ከተገነዘበ መልቶቹንና መፍረድ የተመልካች ወይም የውጭ ሰው ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲሁም ደግሞ እንዲህ ዓይነቱን ስሕተትና ኃጢአት በተመለከተ የተሰናከሉትን ለእግዚአብሔር የጸጋው ዙፋን መስጠት ይኖርብናል፡፡

## በኃጢአት መንታ መንገዶች ላይ

ከመንታ መንገዶች መካከል የኃጢአትን የመሰለ የለም፡፡

ምክንያቱም ከዚያ መነሻ ላይ መድረሻ ወደ ‹‹ጨለማ መንገድ›› ‹‹በክፉ መደሰት›› ‹‹የተጣመመ አካሄድ›› ወዘተ... ነውና (ምሳ. 2÷13-15)፡፡ ይህ ሁሉ ክፉ ነገር ሲጀምር እንደ ቀልድ አድርጎና የዋህ መስሎ በመቅረብ ነው፡፡ እውነተኛ ማንነቱ ሲገለጥ ግን ተጠቂውን ቀድሞውኑ ወደ ክፉ መንገድ የወሰደው መሆኑ ግልጽ ይሆናል፡፡

እግዘአብሔር ማንንም በክፉ አይፈትንም (ያዕ. 1÷12-15)፡፡ ግን በሁሉም አዋቂነቱና መካርነቱ ለተወሰነ ጊዜ ክፉ ነገሮች እንዲከሰቱ ሊፈቅድ ይችል ይሆናል፡፡ ያ መንገድ ምን ሊያመጣ እንደሚችል በማሳያት በፈተና የወደቀውንና ሌሎችንም ይረዳ ዘንድ ከችግሩ እንዲላቀቅ ያበረታዋል፤ ራሱን እንዲከላከልም ያስታጥቀዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን በፈተናው ሰው በስሕተት ጎደና መጓዙን ይቀጥላልና ከፈተናው የሚወጣው የቆሰለ ልብ ይዞ ይሆናል፡፡

በፈተና እንድንወደቅ ከሚገፋፉን ሰዎችና ቦታዎች ጋር ራሳችንን ማላመድ የሚመከር አይደለም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በኃጢአት መውደቅና በኋላም በውጤቱ መሰቃየት ካልሆነ በስተቀር ከነዚህ የሚመጣ መልካም ነገር የለም፡፡ ምንም እንኳ በእውነት ኃጢአታቸውን የሚናዘዙ ይቅርታን ቢያገኙም በፈተና መጫወት የሚመርጡና በዚህም ውስጥ የሚመላለሱ ሁሉ የመዳን ተስፋ የላቸውም፡፡

በሌላ በኩል አንድ ሰው በኃጢአት መውደቁን ከተገነዘበና የድፍረት አስተሳሰቦቹ ካበቁ ወደ እግዚአብሔር መልሶ የሚወስደውን መልካሙን መንገድ መፈለግ ይቻላል፡፡ እዚህ ላይ ሌላ መንታ መንገድ አለ፡፡ ወደ ተጨማሪ ኃጢአትና በመጨረሻም ወደ ተስፋ መቍረጥ የሚመራ አንድ መንገድ አለ፡፡ ነገር ግን በሚያስደንቅ ሁኔታ በዳዊት እንዲህ በሚል ሁኔታ የተገለጠ መንገድ አለ ‹‹ኃጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ፤ በደሌንም አልሸፈንኩም›› (መዝ. 32÷1-5)፡፡ ይህም በክርስትና ውስጥ ከሚገኙ አብይ ነገሮች ማለትም ከንስሐ÷ ከኑዛዜና ከይቅርታ

ሁሉም እንዲሁ ስለሆነ ምንም ጥርጥር የለውም። ከነዚህ መንፈሳ መንገዶች ሁሉም እንዲሁ ወደ ሕይወት፣ ወደ ተለወጠ ሕይወት፣ ወደ ሕይወት ኃይላትና ሕያው ተስፋ ይመራናል።

ምንም እንኳ ተደም ሲል የኃጢአት ይቅርታ የተገኘ ቢሆንም በብዙ ነገሮች ላይ አዲስ መንፈሳ መንገድ ይኖራል። በዚህ መንፈሳ መንገድ ላይ ችግሩ በተራራዎቹ የኃጢአት ውጤቶች ላይ ምን መደረግ? አለበት የሚል ነው። በተሰበረ ልብ የሆነ ትህትና ፈቃደኝነት ሊኖረው የሚገባ ነው። ከኃጢአት ጋር በተያያዘ ስሕተት የሆነውን ለማረም መሞከር ነው። አንድ ሰው ወይም አንዳንድ ሰዎች ከኃጢአት ጋር በተያያዘ ሥቃይ፥ ውድመት ወይም ጉዳት ደርሶባቸው ሊሆን በየትም ቦታና በተቻለ መጠን እነዚህ ነገሮች ፈውስ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ጉዳዮቻቸው የበዛና የተለያየ በመሆኑ ዝርዝሩን እዚህ ላይ ማስፈር አይቻልም። ይሁንና እንጂ በአንድ ሰው ላይ የሆነ ጉዳት መድረሱን በመንፈስ [illegible]

[illegible]
አለበት። አስፈላጊ ሆኖ ካገኘነውም ተሞክሮ ያለውን ክርስቲያን ካህን የምክር አገልግሎት መጠየቅ አለበት። ፊቱን በዚህ መንፈሳ መንገድ ላይ ማግኘት የሚያስገኘን ይሆናል። ግን ዳግም በዚህ ነገር ላይ አጥንቶቹውን መንገድ መፈለግና በእርሱ ላይ መመላለስ በእርግጥ አስፈላጊ ነው። ለበለጠ ወደ ጤናማ መንፈሳዊነትና ሕይወት የሚመራ ይህንን የመሰለ መንገድ ብቻ ነው። ሌላው የመንገድ ምርጫ አያስብ እነዚህን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ያስተማረውን ሙሉ በሙሉ በመጻረር የሚሄድ ነው። ክርስቶስ በእግዚአብሔር መሰዊያ ፊት ቀርቦ በኃጢአት የተጎዳውን ሰው ምሳሌ ይገልፃል፤ ይህ ሰው «ወንድሙ» የሚያጉረመርምበት የሆነ ጉዳይ ነበረው። ስለዚህ አያስብም ወደ ባልንጀራው ሄዶ እንዲታረቀው ነገረው (ማቴ. 5፡23-24)

## በምድራዊ አገልግሎት መንፈሳ መንገዶች ላይ

በሰው ኑሮ ውስጥ አንዳንድ መንፈሳ መንገዶች በፍርሃትና በጭንቀት በማስተሉት መንገዶች ይገለጣሉ፤ «ምን እንሆናለን?»፣

«ምን እንጠጣለን?»፥ «ምን እንለብሳለን?» (ማቴ. 6፥31)። የሰማዩ አባታችን ይህ ሁሉ እንደሚያስፈልገን ስለሚያውቅ ከዚህ ሸክም ራሳችንን ነፃ እናድርግ። ከመድኃኒታችን የበለጠ ስለዚህ ጉዳይ በአጽንዖት ያስተማረ ሌላ ማንም የለም (ማቴ. 6፥32)። ሆኖም ይህ ሁሉ አጠራጣሪ ስለማይሆንብን ሁላችንም ወደዚህ ዓይነቱ የሕይወት መንታ መንገድ መምጣታችን የማይቀር ይሆናል። በዚህ ዓይነቱ መንታ መንገድ ያለን ብቸኛው መንገድ፥ «እርሱ ስለ እኛ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ እንጣል» የሚል ነው (1 ጴጥ. 5፥7)።

በዕለት ተዕለት ሁኔታዎች ውስጥ የሚያድግ ማንም ሰው ስለ ትምህርትና ትምህርት ቤት፥ ስለ ሥራ ቅጥር፥ ስለ አገልግሎት ወዘተ... ጥያቄ ሲነሳ መምረጥ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቃል። ብዙ ወጣት ሰዎች ኋላ ላይ የሚያስቡትና የሚያስታውሱት በመንታ መንገዶቻቸው ላይ ዓይነተኛ ስፍራ የነበራቸውን እነዚህን ጥያቄዎች ነው። የፍቅር መተጫጨትና

የጋብቻ ጥያቄ በአንድ ላይ ሲመጣ በብዙ ምክንያቶች የተነሳ ለመምረጥ የበለጠ አስቸጋሪ ይሆናል። በዚህ ላይ ለወጣቶች ብርቱ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። ወላጆች፥ መምህራን፥ የትምህርት ቤት ባለሥልጣናት፥ አንጋፋ ባልንጀሮች፥ ቀሳውስትና አጥቢያዎች ተገቢውን ትምህርትና የመምከር አገልግሎት በመስጠት የድርሻቸውን ቢወጡ ትክክለኛውን መንገድ ለመምረጥ በጣም ቀላል ይሆንላቸዋል። በእርግጥ የመጨረሻው ምርጫ የሚገኘው በባለጉዳዮቹ እጅ ላይ ቢሆንም በተቻለ መጠን እንዲነቁ ትምህርትና ምክር በተገቢው መንገድ ከተሰጣቸው ሁሉም ነገር ቀና ይሆንላቸዋል።

የሙያ ሥራን በተመለከተ ማንኛውም ሰው ተሰጥዎውን ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም መጓጓት ይኖርበታል። በድንገት በመሀል ትምህርታቸውን ያቋረጡ ወይም ባለማስተዋል ያለጊዜአቸው ጋብቻ በመፈፀም እድላቸውን ያበላሹ ሰዎች በኋለኛው የሕይወት ዘመናቸው ላይ ወደነዚህ ነገሮች ለመድረስ እንደማይችሉ ይገነዘባሉ። በእርግጥ ሁሉም ስሕተትና ኃጢአት

ይቅር ሊባል ይችላል። ግን ገና በጠዋቱ ያጋጠመህ የመንታ መንገድ ምርጫህ የተሳሳተ ባይሆን ኖሮ ብዙ መሥዋዕት አትከፍል ነበር ብለህ ከተቆጨህ በሕይወት ዘመንህ ሁሉ ልትሸከም የማትችለው ሸክም ሆኖ ይኖራል። እንደነዚህ ዓይነት ስሕተቶችን እንዴት ማስወገድ ይቻላል? ለአንድ ክርስቲያን መልሱ ሁለት ዓይነት ሊሆን ይችላል። አንደኛ መንገድህን ለመምረጥ አትቸኩል፤ ጉዳዩን በጥሞናና በእርጋታ አስበበት፤ እንዲሁም ተሞክሮ ያላቸውን፣ ታማኝ የሆኑ ሰዎችን ምክር ልብ በል። ሁለተኛ አስፈላጊ ነው የምትለውን ምርጫ ከማድረግህ በፊት ጊዜ ወስደህ ባለመታከት እርዳታውንና ምሪቱን ለመጠየቅ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፤ እንዲሁም በገባው ተስፋ መሠረት ይመራህ ዘንድ በእርሱ ላይ ተማመን። «እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል» (1 ዮሐ. 5፥14)።

አዲስ ጥሪ ሲደርስን

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በነቢያትን፥ በሐዋርያትና በደቀመዛሙርት ሕይወት እንደ ተፈጸመው ሁሉ ዛሬም በብዙዎች ሕይወት ውስጥ የሚፈጸም ነው። ዛሬ ባለንበት ዘመን ላይም ቢሆን መንፈሳዊና ምድራዊ ነገሮችን አስመልክቶ አዲስ ጥሪ ለሰዎች ይደርሳል። ለተራ ዓለማውያን ሰዎች ይህ ጥሪ በአብዛኛው ገቢና ክብርን የሚመለከት ጥያቄ ያስነሳል። ለክርስቲያኖች ግን ከምንም ነገር በላይ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድና ባልንጀራዎቻቸውን፣ ማኅበረሰባቸውን እንዴት ማገልገል እንደሚችሉ የሚያነሳ ጥያቄ ነው። ሁሉም ነገር በዝናና በሚያስገኘው ትርፍ ከተለካና ከተወሰነ ጉዳዩ ጥልቀት በጎደለው መንገድ የሚያዝና ምናልባትም ወደ በረከት አልባነት የሚወስድ ነው። ጉዳዩ ሁልጊዜ በሕይወት የሚገኘው መንታ መንገድ ነው። ውጤቱን በተመለከተ ክርስቲያኖች መጠየቅ ያለባቸው እንዲህ በማለት መሆን አለበት፡ «በፊቴ በር ተከፍቶልኛል» (2 ቆሮ. 2፥12)። እንዲሁም ይህን በመሳሰሉ ሌሎች ጥያቄዎች ላይ እርግጠኞች ባንሆን ወይም ውሳኔ ላይ መድረስ ቢሳነን በጉዳዩ ስራ ተሞክሮ ያላቸውን

ክርስቲያኖች የምክር አገልግሎት መጠየቅና ከዚሁ ጎን ለጎን ከሁሉም በላይ እርዳታውንና ምሪቱን እንዲሰጠን ጌታን መማጸን ይመከራል።

## በሁከትና በትግል ውስጥ

በዚህ ጉዳይ ላይ የክርስትና ትምህርት ሚዛናዊ አጥፍና ድርብ ነው። በአንድ በኩል ወሳኞች እኛው እስከሆንን ድረስ «ሰላምን እስከፈለግን» ድረስ «ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም እንድንኖር» ይመክረናል (ሮሜ 12፥18፡ 14፥19)። በሌላ በኩል ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ይነግረናል «በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም» (ማቴ. 10፥34)። እነዚህ ሁለት ነገሮች በአንድ ላይ ሊሄዱ ይችላሉን? በእርግጥ ጉዳዩ ራሱ ሁለት ገጽታ አሉት። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰላም ንጉሥ ነው። ነገር ግን ወንጌሉና መንግሥቱ ወደ ማኅበረሰቡ ሲገባ ተቃውሞና

እምቢታ አስነሳ። ስለሆነም በመቀጠል እንዲህ ሲል ተቃውሞው በተላቸ መልኩ ይገለጻል አለ። «በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ» (ማቴ. 10፥22)።

ታዲያ በሁሉም ነገር በክርስቲያኖች ላይ የተነሳና እንዲደርሱም እስከ ጥላቻ የደረሱ እነዚህ ጠላቶች እነ ማን ናቸው? ከሁሉ አስቀድሞ «ቃላቱ ዘንዶ» «ያ የተደመሰሰ እባብ» «ዲያቢሎስና ሰይጣን የሚባለው ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው» ትልቁ የእግዚአብሔር ጠላት ነው (ራእ. 12፥9)። ሁለተኛው ዓለም ነው። ዓለም ቃል እንደሚያሳየው ሁሉሚታዩና የተፈጠረው ዓለም ማለት አይደለም። ከዚህ ይልቅ ከእግዚአብሔር የራቀ እርሱን ተ መንግሥቱንና አገልጋዮቹን የሚጠላ «ኃጢአተኞችን» ማለት ነው። ሦስተኛው በራስ በሰው ውስጥ ያለው ክፋት ነው። ይህ ክፋት ደግሞ በተለመዱና አማኝ ክርስቲያኖች በሆኑትም ዘንድ የሚገኝ ነው። ለዚህም ነው በራሳቸው ውስጥ ሳይቀር ትግል የሚያደርጉት። ይህ ክፋት ሁልጊዜ «ሥጋዊ» ተብሎ ይጠራል፡፡ራሱንም የሚገልጠው ከእግዚአብሔር ጋር በጠላትነት

በመቃወም ነው፡፡ «ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም፤ በእርግጥ ሊገዛ አይችልምም» (ሮሜ 8፥5-6፤ 7፥21-23)፡፡

ብዙ ሰዎች በክርስትናና በተከታዮቹ ላይ የሚደርሰው ስደት ያለፈ ታሪክ ነው ብለው ያምናሉ፤ ይህ ግን ፍጹም ስሕተት ነው፡፡ በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው ክፉ ስደት፣ መከራ፣ እስርና ግድያ አሁንም አለ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰቆቃ ካለፉት ምዕተ ዓመታት በበለጠ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ላይ ተንሰራፍቶ ይገኛል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ነገር እስካሁን ባይደርስብንም ይዋል ይደር እንጂ የማይቀር ስለ ሆነ ተዘጋጅተን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ በክርስቶስ ለሚታመን ማንኛውም ሰው ስደት የማይቀርለት ስለሆነ ተከታዮቹ ሁሉ ሊደርስባቸው ላለው መከራ ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ «የእግዚአብሔር ቃል በሚሰበክበት፣ ተቀባይነት በሚያገኝበት፣ በሚታመንበትና በሚያፈራበት በዚያ ስፍራ ቅዱስ መስቀሉ ሳይገለጥ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው ሰላም አለኝ

ብሎ አያስብ፤ ይልቁንም ምንም ይሁን ምን በዚህ ምድር ላይ ያለውን ይዞታ፣ ክብር፣ ቤትና ንብረት፣ ሚስትና ልጆች እንዲሁም ሕይወትን አደጋዎችን መጋፈጥ አለበት፡፡ ተግዳሮቱ ጽናትንና በማንኛውም መልኩ የሚደርስብንን መከራ በትዕግሥት መቀበልና ያገኛቸውን ነገሮች በጸጋ መቀበልን ስለሚጠይቅ ሥጋችንና አሮጌውን እኛም የሚጎዳ ነው» (ትልቁ የክርስትና ትምህርት)

## በዚህ ትግል ውስጥ ያሉ ውስብስብ ነገሮች

አንዳንድ ጊዜ ጓደኞቻችንና ጠላቶቻችን እነ ማን እንደሆኑ ማወቅ እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ነጥብ ላይ መሳሳቱ ቀላል ነው፡፡ ተቃዋሚ ወይም ጠላት መስሎ የሚታየን ሰው ከፍርሃት የተነሳ በስውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር» ዮሐ. 19፥38 ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከእኛ ጋር በአንድነት ከጌታ ማእድ የተካፈለ የጌታ ደቀመዝሙር እንደ ሆነ የሚገመት አንድ ሰው በጌታውና በእሱ ላይ እግሩን ያነሳና ለጠላት አሳልፎ የሚሰጥ አስመሳይ ደቀመዝሙር ሊሆን ይችላል መዝ. 41፥9፤

ዮሐ. 1፥10-17፡፡

በችኮላ ተነሳስተን ማንንም ሰው እንደ ወዳጅ ወይም እንደ ጠላት ለመቍጠር ድምዳሜ ላይ መድረስ አይኖርብንም። በሌላ በኩል ማንንም በጥድፊያ የልብ ወዳጅ ለማድረግ መጣደፍ የለብንም። ምን ዓይነት ባሕርይና ተግባቦት እንዳለው ጊዜ ወስዶ መፈተሹ ያስፈልጋል።

ቢቻለን በእኛ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር ይቻለን ዘንድ (ሮሜ 12÷18)። ሰላምን ለመጠበቅ ከተቃዋሚዎች ወይም ከጠላት ጋር እንዴት ነው መገናኘት የምንችለው? ከሁሉ አስቀድሞ ሁለቱን ጥያቄዎች ማለትም ጉዳዩንና ይህ ጉዳይ የሚመለከተውን ግለሰብ ለያይተን ማስቀመጥ ይገባናል። ይህ ማለት ጉዳዩ የሚመለከተውን ሰው ሳናጠቃ ወይም ሳንጎዳ ጉዳዩን ግን መደገፍ ወይም ማውገዝ መቻል አለብን ማለት ነው። ጉዳዩ በሚያስከትለው መዘዝና ችግር መሃል ብንሆን እንኳ በነገሩ ላይ ጠንካራ አቋም መያዝ ይገባናል። ይሁንና ለባለ ጉዳዩ ወንድማዊ አገልጋይ መሆን አለብን። በሌሎች በርካታ ጉዳዮች ላይ እንደሆነው ሁሉ በእኛ በኩል በራሳችን ላይ ችግር የሚያመጣ እንዲሁም የደገፍነውን ወገን ሊጎዳ እንደሚችል ማስታወስ ይገባናል። በሌላ በኩል መናገሩ ግድ ሆኖ ከተገኘ ንግግሩ ግልጽ÷ ተአማኒና አስተማማኝ እንዲሆን ያስፈልጋል።

ታዲያ ‹‹ለሰላም ሲባል›› መግባባት ላይ መድረስ እንዴት ይቻላል? ጌታችንና መድሃኒታችን የሚያስፈልገንን ሁሉ መልስ ሰጥቶናል። ግላዊ መግባባትን በተመለከተ ብዙ ርቀት መሄድ እንችላለን (ማቴ. 5÷38-48)። ክርክራችን ስለ ክርስቶስ÷ ስለ እምነታችንና ስለ እውነት ሲሆን÷ ግን አቋማችን ፈጽሞ የተለየ ይሆናል። እውነት የእኛ አይደለችም። ስለ እርሷ መደራደርም ሆነ እርሷን አሳልፈን መስጠት አንችልም። ይልቁንም ‹‹ስለ ወንጌል ሃይማኖት፤ አብራችሁ እየተጋደላችሁ÷ በአንድ መንፈስ እንድትቆሙ ... በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ›› (ፊልጵ. 1÷27-28)።

በእግዚአብሔር ሰላም ማግኘት መሠረታችን÷ መንፈሳዊና

ዘላለማዊ ተስፋችን ነው። እነዚህ ያሉ ውጊያና ትግል ሲገኙ ወይም ሊጠበቁ አይችሉም። እነርሱም የአንድ ክርስቲያንና እንዲሁም የመላው ቤተ ክርስቲያን ሁኔታዎች ናቸው። ይህ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን የሚሹ ሁሉ ሊቀበሉት የሚገባ ጥሪ ነው። «ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ፤ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለም።» (ዕብ. 12፥14)።

## የክርስትና እምነት አቋምን መግለጽ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ

በክርስቲያን ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ምእመናን በቤተ ሰብ፥ በትምህርት ቤት፥ በሥራ ክርስቲያን የአምልኮ አገልግሎት፥ በቤተዘመድና በጓደኞች ኅብረት ውስጥ የእምነት መግለጫ የሕይወታቸው አንዱ አካል ነው። በቦታው ላይ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ጥቂት በሆኑና በሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ተከበው

ቢኖሩ ጉዳዩ የተለየ ይሆናል። አንድ ክርስቲያን በተለየ ወቅት በአንድ ወይም በሌላ መንገድ እምነቱን ማሳወቅ አስፈላጊው ነው። አንድ አማኝ በአሳብ የሰሸነፉ ወይም ወሬ በማነሳሳት መንገድ በግል ተነሳሽነት ሳይሆን ይልቁንም እምነቱን ማሳወቁ ሁኔታው በሚፈቅድበት ጊዜ በትሕትናና በግልጽና በትክክለኛ መንገድ መደረግ አለበት። ሁሉም ዓይነት በሚያቷዊነት፤ ተፈጥሮአዊ ያልሆነ የድምፅ ቅላጼ ወይም ባሕርይ ማሳየት ደካማ መላ ነው።

ስለ እምነታችን በሚጠይቁን ሰዎች ዘንድ ድምፃችንን ከፍ አድርገን የክርስትናን እምነት መግለጽ የሚያስፈልገንበትና የሚጠየቅበት ጊዜም አለ። ይህን እውነታ ለማሳየት በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰውን ምሳሌ መመልከት እጅግ ጠቃሚ ነው። ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በደረሱ ጊዜ ባለሥልጣናቱ «በኢየሱስ ስም ፈጽሞ እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዙአቸው።» (የሐዋ. 4፥18)። ይህንን የሚመስል ሁኔታ ሲያጋጥም ብዙ ክርስቲያኖች ክልከላውን ተገቢ አድርገን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት

የሚገባ እንደሆነ ቁረጡ። እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም›› (የሐዋ. 4÷19-20)። በቤተ መቅደስ ውስጥ ትምህርታቸውን በድጋሚ ባቀረቡበት ወቅት እንደገና ታስረው ‹‹በዚህ ስም እንዳታስተምሩ!›› ተብለው ለፍርድ በቀረቡበት ወቅት አሳባቸውንና ተግባራቸውን በዝርዝር በገለጹበት መንገድ ላይ እንዲህ ተብሎ ተብራርቷል፤ ‹‹ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል›› በማለት መለሱላቸው (5÷28-29)።

ዛሬ ላይ ሁኔታዎች የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ። በባለሥልጣናት÷ በገዢዎች÷ በዘመዶቻችን÷ በጓደኞቻችን÷ በሥራ ባልደረቦቻችን ወይም በሌሎች ሰዎች አማካይነት የክርስትና እምነታችንን ማስታወቅ አስፈላጊያችን ይሆናል። ሁኔታዎች ከተለመደው ርቀው በሚሄዱበት ሁኔታ ላይ ያሉትን ክፍት መንገዶች ወደ ሁለት ዝቅ ማድረግ ይቻላል። እነርሱም እምነታችንን እርግፍ አድርጎ መተው ወይም በእምነታች ጸንቶ መቆም፤ ትእዛዛቸውን ማክበር ወይም አለማክበር ናቸው። ይህ ከሚገጥሙን መንታ መንገዶች ሁሉ የመጨረሻው ዓይነት እንደሆነ ተደርጎ መገመት ይኖርበታል።

እዚህ ላይ የተጠሉት ጉዳዮች ባለሥልጣናት ራሳቸው ተሳስተውና ሌሎች ሕጎችን በተለይም የእግዚአብሔርን ሕግ የሚቃረኑ ነገሮችን እንድንፈጽም የሚያዙንን የሚመለከቱ ናቸው። ከዚህም በላይ ማንም ሰው በአለቆቹ ላይ ለማመፅና ይህንንም በተግባር ለማሳየት ምቹ አጋጣሚዎችን መጠበቅ አይኖርበትም። ከዚህ ይልቅ ልክ ሐዋርያቱ እንዳደረጉት ሁሉ ጉዳዮቹ ራሳቸውን የሚገልጹ ይሆናሉ።

የዚህ መከራ ውጤት ሥቃይ ከሆነ ሥቃዩ ትልቅ ሀዘንን ለማሳየት ‹‹ይህን የመሰለ ክፉ ነገር ለምን ሊደርስብኝ ቻለ›› እያለ በማጉረምረም ወደ ፈተና ይወስደናል። እዚህ ላይ በድጋሚ የሐዋርያቱን ትምህርት ማስታወስ ይገባናል፤ ‹‹እነርሱም ስለ ስሙ (ኢየሱስ) ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለተቆጠሩ ከሸንጎ ፊት ደስ እያላቸው ወጡ›› (ሐዋ. 5÷41)።

በሥቃይና ወይም በፈተና መንታ መንገዶች ላይ።

የሚደርሱብን የሥቃይ ዓይነቶች የተለያዩና ብዛት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ጤናችንን፣ ኑሮአችንን፣ ቤተ ሰባችንን፣ ዘመዶቻችን ወዘተ... የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ የደረሰብንን ሥቃይ በአሳባችን ከሚገባው በላይ አጋኖ የማቅረብ ፈተና ይኖራል። ይሁን እንጂ በሌሎች ላይ ሊደርስ ካለው ጋር ሲነጻጸር ያነሰ ሊሆን ይችላል።

እግዚአብሔር በሥቃዮቻችን ውስጥ ምንም ድርሻ የለውም ብሎ ማሰብ ፍጹም ስሕተት ይሆናል። ይልቁንም ሥቃይ ሲደርስብን በእርሱ ፈቃድ የሆነ ነው። የደረሰው ሥቃይ ለሠራነው ስሕተትና ለመረጥነው ኀጢአት ከእርሱ የተላለፈብን ቅጣት ሊሆን ይችላል። የእርሱን ማስጠንቀቂያዎች ችላ ብንል ለሚደርሱብን ነገሮች እንዘጋጃለን። ይህ የኃጢአተኞችንና የክፉዎችን መንገድ

ላለመከተል (መዝ. 1፥1) ደግመን ደጋግመን ራሳችንን ማስገንዘብ ያለብን ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ ግን አጽንዖት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ስለ ኃጢአትና ስለ ቅጣት የሚሰጠው ትምህርት በራሳችን ላይ ብቻ የሚሠራ መሆን እንዳለበት እንጂ በሌሎች ላይ የሚደርሰው ሥቃይ ከኃጢአታቸው የተነሣ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ቅጣት ነው ብሎ መናገር የተለየ ጉዳይ መሆኑ ነው። ይህንን መናገር ያለብን ጉዳዩ ከመጨረሻው ጽንፍ ሲደርስ ብቻ ነው። ለምሳሌ ‹‹አስታቲኖ›› የሚገጥማቸው ዕጣ ፈንታችንን፤ በተመለከተ የደረሰብንን መከራና ሥቃይ በንመለከት አልፎ አልፎ ገምዛዛ አስተሳሰብና መራት ይለማን ዘንድ እንፈተናለን። የደረሰብንን ችግር በተመለከተ የተወሰኑ ሰዎችን ለምሳሌ ቤተ ሰባችንን ወይም ጎረቤቶቻችንን ለመውቀስ እንፈተናለን። አንዳንድ ሰዎች ስለ ገጠማቸው ዕጣ ፈንታ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ‹‹ባለሥልጣናት›› ወይም ‹‹የሥራ ኃላፊዎችን›› መውቀስ ይመርጣሉ። እንዲሁም አንድ አማኝ ክርስቲያን ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑትን ወይም ሁሉንም እና ሌሎች የበዙትን ለማድረግ ይፈተን ይሆናል። እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩት በሁሉም ዓይነት ሥቃይና መከራ ውስጥ

እግዚአብሔር ሊናገር የፈቀደውን ለመስማት መዘጋጀቱ እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ ነው። በሆነው ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ መሻት እርሱ ሊሰጠን ያሰበውን ትምህርት መማር የምንችለውና የሚፈልገው መንገድ ላይ ለመሆን ምሪቱን ማግኘት የሚቻለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።

## ሥቃይና እምነት

በእርግጥ በሁሉም ዓይነት መከራ ውስጥ ትእግሥት ማሳየት መልካና ምስጋና ሊቸረው የሚገባ ነገር ነው። ይሁን እንጂ ከዚህ በበለጠ አስፈላጊ የሆነ ነገር አለ፤ እርሱም እምነት ነው። መከራ እንኳ ቢሆን ተዘጋጅተንበትና ፈቅደን ለመቀበልና ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት የምንችለው በእምነት ብቻ ነው። ይህ የክርስቲያን ትልቅ ምስጢር ነው፤ ይህም ‹‹የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ ጸንቶአልና›› (ዕብ. 11÷27)። እንደሚለው ነው።

እምነትን ከጠቀስን ዘንድ ሌላው ነገር ተከትሎ መምጣቱ የግድ ነው። ለአንድ ክርስቲያን ሥቃዩ ሁሉ ከክርስቶስ ጋር የተቆራኘ መሆን ይኖርበታል። የሚድረስብን መከራ ከክረስቶስ ጋር ካልተቆራኘ የራሳችን ብቻ ይሆናል፤ ምክንያቱም መከራን መቀበል ያለ እምነት ከሆነ በሥራችን ካገኘነው ነገር ጋር ብቻ የተያያዘ ይሆናል። በሌላው በኩል በሁሉም ሥቃይ በእውነተኛ መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር የምንሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ የሆነ ማስተዋል በመካከላችን ሲኖር ነው።

የዚህ እምነት ሌላው ጎን ፍቅር ነው። በመከራ ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔርን መውደድ ከባድ ነገር ነው። ይሁን እንጂ የክርስቲያኖች ሁሉ መንገድ መሆን ይኖርበታል። ‹‹እግዚአብሔርን ለሚወዱ እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን›› (ሮሜ 8÷28)። ይህ ደግሞ ለማግኘትና ለማወቅ የሚከብድ ግን አንዴ ራሱን ከገለጠ ደግሞ አስደናቂ ልምድ የሆነ የክርስትና ትልቁ ምስጢር ነው። ‹‹ነገር ግን መከራ

ትዕግሥትን እንዲያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን፥ ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ አውቀን በመከራችን ደግሞ እንመካለን። የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም» (ሮሜ 5፥3-5)።

## በአስቸጋሪ ውሳኔዎች መንታ መንገዶች ላይ

አንዳንድ ጊዜ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን ለመወሰን በማሰብ እንዲህ ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን «ለመወሰን ከባድ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሕይወት ራሱዋ ውስብስብ የሆነው ለምንድን ነው?» ለዚህ ዋናው መሠረታዊው መልስ የሚሆነው የምንኖረው ፍጹም ባልሆነና ኃጢአተኛ ዓለም ውስጥ በመሆኑ ምክንያታዊነታችንና ውሳኔአችን ፍጹም አስተማማኝ ባለመሆናቸው ነው። «ከዕውቀት ከፊሉን እናውቃለን» እናም «በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን»

(1 ቆሮ. 13፥9-12)።

እነዚህን አስቸጋሪ የሆኑ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ዓለማዊና መንፈሳዊ አውዶችን መለየት ነጥቦችን ይሆናል። የተማሩ ሰዎች እያንዳንዱን ጉዳይ እንዴት መምረጥና መወሰን እንደሚኖርብን ሰፊ መመሪያ የሚቀርጹልን ከሆነ የሚሰጠን ጥቅም የለም። በተወሳሰበው የዓለም ሁኔታዎች ውስጥ ሌላ አቅጣጫ ለመያዝ ወይም በእሳብ በማፈንገጥ ማለትም ለክርስትና መሠረታዊ መርሆች ሌላ ትርጉም በመስጠት ለራሳችን እንዲስማሙ አድርገን ለመወሰድ ብዙ በሮች ይኖራሉ።

እያንዳንዱ አስቸጋሪ ውሳኔ የራሱ የሆነ ልዩ ምግባራዊ እንደምታ አለው። በተለመደ ሁኔታ ትክክለው መልካም ተብሎ ሊጠራ የሚችል መንገድ ማግኘት የማይቻል ነገር ነው። ያን ጊዜ መልካም መስሎ ይታይ የነበረው መንገድ እንኳ እንደተጠበቀው ላይሆን ይችላል። ይህንን ችግር አስመልክቶ አንዳንድ አስባውያን «የግጭት ውሳኔ» የሚባለውን አሠራር ጠቁመዋል፤ ይህም ማለት «አነስ መልካም ከሆነው ተግባሩ የሚመነ…

የሚሊሰውን እሳቤ ማመላከታቸው ነው። በክርስትና ማብራሪያ መሠረት ይህ ጉዳይ በሚከተለው መንገድ ሊታወቅ ይችላል፤ ... በየጎንታቱና በየግዛና ከታሰበና የእግዚአብሔርን እርዳታና ምሪት ለማግኘት በእውነትና ፍጹም በሆነ ቅንነት ጸሎት ከተደረገ በኋላ ውሳኔ ለመስጠት ጊዜው ደረሰ ማለት ነው። ያን ጊዜም ትክክል ነው ብሎ ያመነበትን አድርጎ። እርዳታውን ጠይቋልና አሁን የምትመርጠው ሌላ ነገር አይኖርም። በዚህ ጉዳይ ላይ የመጨረሻና ወሳኝ ድምዳሜ ላይ ይደረሳል፤ ይህም የእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነትና ጥበቃው ነው። የሰማይ አባታችን ሕይወት ያላቸውን ፍጥረታት ሁሉ አዕዋፋትና አበባዎችንም ጭምር ይንከባከባል። ስለሆነም እንዲህ በማለት ምክንያታዊ ጥያቄ ያቀርብልናል፤ ‹‹እናንተስ ከእነርሱ አትበልጡምን?›› (ማቴ 6+25-34)። ይህንን በተመለከተ ትርጉሙ እንዲህ ሊሆን ይገባል፤ ... እጅግ በጣም አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ብንሆንም እግዚአብሔር

ስለሆነም የምንፈልገውን መቋጫ ሊሰጠን ሁልጊዜም ዝግጁ ነው። ምናልባት ይህ በቀላሉ ሊገኝ አይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ ‹‹የሚለምን ሁሉ ይቀበላል፤ የሚፈልገውም ያገኛል›› (ማቴ. 7+8)።

## የክርስቶስ ሕይወት ምሳሌነት

እነዚህን ሁሉ ጥንካሬ ቁልፍ አድርጎ የሚያሳየንን ምሳሌ በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ውስጥ እናገኛለን። ሥቃዩንና ሞቱን ከሰብዓዊ አመለካከት አንጻር በማያወላውል በዝርዝር መልኩ ብንመለከት በዓለም ውስጥ ጥቂት ነገሮች የበለጠ ትርጉም የለሽ ይሆኑብናል። ከመንፈሳዊ ጎናቸው አንጻር በጥልቀት ቢፈተሹ ግን እነዚሁ ነገሮች እጅግ የላቀ ትርጉምና እንዲያውም ዘለዓለማዊ የሆነ አስፈላጊነት አላቸው። በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ ስለ ነበሩ መንታ መንገዶች በዳሰሰ እና ሁልጊዜ እንደምናደርገው ሁሉ እርሱም ‹‹ሁሉም ነገር ለምን አስቸጋሪ ሆነብኝ? መልካም መስሎ የሚታይ አንድ መንገድ ለምን አይታይም›› ብሎ በተናገረ

ነበር። ነገር ግን ይህን የመሰለ አንዳችም ነገር ከአፉ አልወጣም። የተነገሩትም ቃላት ፍጹም የተለዩ ነበሩ፤ «አሁን ነፍሴ ታወከች» እንዲሁም «ነገር ግን የምጠመቃት ጥምቀት አለች፤ እስክትፈጸም ድረስ እንዴት እጨነቃለሁ?» ነበር ያለው (ዮሐ. 12፥27፤ ሉቃስ 12፥50)። እነዚህን ቃላት ተከትሎ እርሱ የተናገራቸውን በሁለት ቃላት ማጠቃለል ይቻላል፤ እነርሱም «እንደ ፈቃድህ ይሁን» ማቴ. 26፥42 እና «እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ» ዮሐ. 17፥4 የሚሉ ናቸው።

እንዲህም ስለ ሆነ በሁሉም መከራ ውስጥ ከፍርሃትና በአንዳንድ የሕይወታችን መንታ መንገዶች ላይ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ውሳኔዎችን ማድረግ ካለብን በእግዚአብሔር ጥበቃና አባታዊ ፍቅሩ መታመን ይኖርብናል። ከዚያም ደግሞ በሁሉም ነገር ውስጥ የሚመራን አንድ መንገድ እንዳለ ማመን ይገባናል። ይህ በሌሎች መንገዶች መካከል አንዱ የሆነ መንገድ አይደለም።

ያለው ብቸኛ መንገድ እርሱ ብቻ ነው፤ ስለሆም፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ዮሐ. 14፥6።

ምንም እንኳ በሁሉም ችግሮች ውስጥ አንድ መንገድ ብቻ እንዳለ ብንረዳም ይህ ማለት ግን ሁልጊዜም ይህንን መንገድ እንመርጣለን ወይም እንከተላለን ማለት ቀስትና አይደለም። ከዚህ ይልቅ ሌላ መንገድ ለመምረጥ በኃጢአትና በውድቀት ውስጥ ልንገባ እንችል ይሆናል። የሚገርመው ግን እንደዚህ ለመሰሉ ሁኔታዎች ደግሞ የእግዚአብሔር ተስፋዎች የተረጋገጡ መሆናቸው ነው። ያን ጊዜ ተስፋዎቹ ከሕይወት መንታ መንገዶች ውስጥ አንዱን የስሕተት መንገድ ለመረጠው ኃጢአተኛ የይቅርታ መንገድ ያሳዩቃል። «ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው» (1 ጢሞ. 1፥15)።

## ምዕራፍ 19

## ሕይወትና ሞት

### ሕይወት አጭር ናት

«ሰው ከንቱን ነገር ይመስላል ዘመኑ እንደ ጥላ ያልፋል» መዝ. 144፥4። ስለዚህ «ቀን ሳለ» (ዮሐ. 9፥4) ሁላችንም ስለ ሕይወት ግብ ማሰብ ይኖርብናል። ሕይወት በራሱዋ ግብ አይደለችምና መኖር ወይም ለተወሰነ ጊዜ እዚህ መሆን ራሱ በቂ ነው ብለን ማሰብ አይኖርብንም። ስለሆነም ሕይወት የተወሰነ ትርጉም፥ የተወሰነ ይዘትና ግብ ሊኖራት ይገባል። በሰዎች መደበኛ ኑሮ ውስጥ በተወሰነ መልኩ ሌሎች ሰዎችንና ማኅበረሰቡን ለማገልገል የሥራ ጥሪ ዕድል መኖር አለበት።

በእንደዚህ ዘመናዊ ሕይወት ጥድፊያ ያለው ጊዜ የንመቃትና የቀናት ቍጥር አይደለም። ጊዜው ረዘመም አጠረም ለማናቸውቃቸው ሰዎች እንኳ ሳይቀር ትልቅ ጥቅም ሊኖረው ይችላል። ሕይወትን በተመሳሳይ የተሳሳተ አንድ የጋራ ግንዛቤ አለ፤ ለምሳሌም ያህል ሰዎች ስኬትንና ደስታን፥ ሀብትንና ተደማጭነትን የሚያገናኙት፤ ሕይወት የበለጸገና ትርጉም ያለው ሕይወት ነው ብለው ያስባሉ። ይህን የመሳሰሉ አስተሳሰቦች ሁሉ ከክርስቶስ ትምህርት ጋር የሚቃረኑ ናቸው። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሚመዘኑት በሚያስገኙት መንፈሳዊና ዘላለማዊ ነገር ነው። ስለሆነም ዋናውና ትልቁ ቁም ነገር ረዢም ዓመታትን ማስቆጠር ወይም ብዙ ሀብት ማካበት ሳይሆን ራሱን «ሕይወትን» መኖር ነው።

ሕይወት ለሰው ልጅ የተቸረችው በዘይር ወይም በሌላ አነጋገር በአደራ መልክ የተሰጠች ናት። ስለዚህ ሰው ለሕይወቱና ከእርሷም ለተገኙ ውጤቶች ተጠያቂ መሆኑን እግዚአብሔር ይናገራል (ማቴ. 25፥14-30)። የሕይወት ጥቂና የክርስቲያን

ሕይወት ይዞት በሦስት መንገዶች ሊገለጽ ይችላል። ይህም ከክርስቶስ ጋር መኖር ሌሎችን ለማገልገል መኖርና የሚመጣውን ዘላለማዊ ሕይወት ለመኖር መዘጋጀት ነው። አንድ ክርስቲያን በዚህ መንገድ ከተመላለሰ ከዚህ ዓለም ቢለይ እንኳ በሕይወቱ ዘመን ያስገኘው አገልግሎትና በረከት በሰዎች መካከል ጸንቶ ይኖራል።

የሕይወትን አጭርነት ከተገነዘብን ይህን ዓለም የምንሰናበትበት ጊዜ ሲደርስ ዝግጁነታችን ምን ይመስላል? በማለት ራሳችንን በተደጋጋሚ መጠየቅ ይኖርብናል። እዚህ ላይ የሚጠቀስ ውጫዊ ሕግ አይኖርም። እጅግ ተመራጭ መንገድ በቃሉ መሠረት በጸሎት፥ በክርስትና ኅብረት፥ በቅድስናና በአገልግሎት ጥሪ እምነታችን በሰዎች መካከል በሚኖረን የዕለት ተዕለት ክርስትና ሕይወት ነው። «በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና፤ ነገር ግን ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን።» የሚለውን የዕብ. 13፥14 ቃል ስለምናውቅ ጌታ በሚጠራን በማናቸውም ጊዜ በዚህ መንገድ ለመሰናበት ዝግጁዎች እንሆናለን።

## መጨመርና መቀነስ

ከጌታ ጋር በእውነተኛ ኅብረት ወደፊት የሚራመድ ክርስቲያን ሁልጊዜ እምነቱ፥ መንፈሳዊ ጥንካሬውና ቅድስናው እየጨመረ ይሄዳል ብሎ ማመን ለፈተና የሚጋብዝ ነው። እንደዚሁ ሊሆን አይችልም። በዚህ ፈንታ አንድ እውነተኛ ክርስቲያን በመጨመር ፈንታ እንዲያውም በየስ ሁኔታ እየቀነሰ መሆኑ ሊሰማው ይችላል። እንደ መጥመቁ ዮሐንስ አባባል ጌታችንና መድኃኒታችን ከእኛ ይልቅ ዘንድ የሚገባው ስለ ሆነ እኛ ግን ማነስም ሲገባን ነው (ዮሐ. 3፥30)።

ይሁንና ክርስቲያኖች ራሳቸው በጉልበት ካልሆነ ሊገነዘቡ የማይችሉትን እድገት እንዳለ ሊያውቁት ይገባል። ሌሎች ደግሞ እምነትን፥ ቅድስናን፥ «መልካም ሥራዎችን» በተመለከተ

መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ቃል ምን ዓይነት ተግባሮች እንዳከናወኑ ይመለከታሉ። እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ የሚከናወነው ቀደም ሲል ባለፉበት ሕይወታቸው ውስጥ ምናልባትም እንደ አሉታዊ ተሞክሮ ብቻ አድርገው የሚመለከቱት ፈተናንና ውድቀትን ነው። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስ የተለየ አሳብ ነው የሚሰጠን፡- ‹‹የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት›› (ያዕ. 1÷2-3)። እንዲህ ዓይነቱ ትምህርት በክርስትና ተሞክሮ በሚገባ ተመስክሮአል፡- ‹‹እኛ ክርስቲያኖች ሰይጣን ከእኛ ርቆ ያለ ይመስል ማንም ሰው ያለ ጥንቃቄ በግድ የለሽነት እንዳይመላለስ ይልቁንም ሁል ጊዜ ሊደርስብን የሚችለውን ጥቃት እያሰብን ሳያቋርጥ በየዕለቱ የሚደርስብንን ፍላጻ እያሰብን ይህንንም ለመመከት ራሳችንን ማዘጋጀት የኖርብናል። ምንም እንኳ አሁን ንጹሕ÷ ታጋሽ÷ ቸር÷ ለጋሽና ጽኑ እምነት ቢኖረኝም በዚች ደቂቃ ላይ እንኳ ሰይጣን ልቋቋመው የማልችለውን ፍላጻውን ወደ ልቤ እየወረወረ ይኖኛል። አንዱ ፈተና ሲያበቃ ሌላ አዲስ ፈተና ብቅ ስለሚል እርሱ ደከመኝና ሰለቸኝን የማያውቅ ጠላት ነው›› (ትልቁ የክርስተና ትምህርት)።

የመንፈሳዊ ጥንካሬ መላላት ጉዳይ ብዙ ጊዜ ከዕድሜ መግፋት ጋር የተሳሰረ ነው። ብዙ ጊዜ እንደሚታመነው እምነት÷ ቅድስናና መንፈሳዊ ጥበብ እንዲሁም በሁሉም በጽናት እየጎለበቱ የሚሄዱት ከዕድሜ መጨመር ጋር በተቆራኘ ነው። ይህ ሊሆን ይችል ይሆናል፡ ነገር ግን ሁልጊዜም እንደዚያ ነው ማለት አይደለም። በዕድሜ የገፉ ሰዎች ብዙ ጊዜ ነገሮችን ከአንድ ጎን ብቻ የሚመለከቱና ብስጩዎች ናቸው። ለምሳሌ ‹‹ሁሉም ነገር ድሮ ቀረ›› በማለት በተለያዩ ነገሮችና ጉዳዮች ላይ ብዙ ጊዜ ቅሬታ ይሰነዝራሉ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በዕድሜ ለገፉ አዛውንቶች ልዩ ፈተና የሚሆንባቸው ለምሳሌ በሚረባውም በማይረባውም መነጫነጭና ማኩረፍ እንዲሁም ለስስት በቀላሉ መጋለጥ ነው። ይህን የመሳሰሉ የባሕሪ ፈተና ከድካም÷ ከሕመምና መጃጀት ጋር ተደማምሮ ከመጣ በውስጣቸው እየጨመረ የሚመጣውን

እምነትና ቅድስና በቀላሉ ማግኘት ይከብዳል። ይህ ሁሉም ክርስቲያኖች ከልጅነት ዕድሜአቸው «መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል» 1 ጢሞ 6፥12 የሚለውን ከባድ ትምህርት በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ መማር ይኖርባቸው ዘንድ የተገባ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

## ሕመምና ሥቃይ

ሕመም እንደምንገነዘበው ሕዝብ ሁሉ አማኝ ክርስቲያኖችንም የሚያጠቃ ነው። ልጆቹ ስለሆንን በሙሉ እምነት ወይም እንዲህ ዓይነቱ አደጋ ቢገጥመን ከዚህ ክፉ ነገር እንዲታደገን መማጠንና ከሁሉም ሕመምና ሥቃይ ነፃ እንዲያደርገን እግዚአብሔርን መለመን ትክክል የተባለ እምነትና አስተምህሮ ነው። ጥቅም እንዲፈውሰንና ወደ ሙሉ ጤንነት ይመልሰን ዘንድ የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ለማግኘት እንድንጸልይ በእርግጥ ተፈቅዶልናል። ይህ ሁሉ ተፈቅዶአል፤ ይቻላልም። ይሁንና ግን

ይህን የመሰሉ ልመናዎች ሁሉ መቅረብ ያለባቸው ኢየሱስ ወደ ሰማያዊ አባቱ በጸለየበት መንፈስ መሆን ይኖርበታል። «አባቴ ሆይ ይህች ፅዋ ሳልጠጣት ታልፍ ዘንድ የማይቻል እንደሆነ ፈቃድህ ትሁን» (ማቴ. 26፥42)።

ይህ ደግሞ በውስጡ አናልፍ ዘንድ ወይም እንስፕ ዘንድ የተጠራንበትን ሁሉንም ዓይነት ሥቃይና መሥዋዕትነት ይመለከታል። ማስተዋል በጎደለው መንገድ ሥቃይንና መሥዋዕትነትን ለመቀበል ቁርጠኞች መሆናችንን ቅጽበታዊ ተስፋ በመስጠት ስለ ሥቃይና መሥዋዕትነት መናገር ይቻላል። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የቅዱስ ጴጥሮስ የሕይወት ምሳሌ ገላጭ ነው (ሉቃ. 22፥31-34)። ከዚህ ዓይነቱ ጥድፊያ ይጠብቀን ዘንድ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ይኖርብናል። ሕመም+ ፈተና+ ችግር+ ሥቃይና አጉል ጀብደኝነት ልንቋቋም የማንችላቸው ነገሮች ናቸው። እነዚህ ነገሮች በተለየ መንገድ በትሕትናና በእምነት በጥንቃቄ መያዝ አለባቸው። እንዲህ ካደረግን ችግር ሲገጥመን፣ እንዲሁም የእርሱ ጊዜ ሲደርስ እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ

ውስጥ ይመራናል፤ ይረዳናልም። ሁኔታው ሁልጊዜ የጀግንነት ተቃራኒ ይሆናል። ምናልባትም ይህን በመሰለው ሁኔታ ውስጥ በቃልና በተግባር የተገለጸው የእግዚአብሔር መልስ እጅግ በጣም የሚስማማ ነው፥ ‹‹ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና›› (2 ቆሮ. 12፥9)።

## ‹‹የማይድን›› በሽታን መጋፈጥ

በተለይ የተወሰነ ደረጃ ላይ ከደረሱ ‹‹ሊድኑ የማይችሉ›› ተብለው የሚታሰቡ አንዳንድ በሽታዎች አሉ። ከራሱ ከበሽታው አስቸጋሪነት በተጓዳኝ ሌሎች አንዳንድ አስቸጋሪ ሁኔታዎች አሉ። በመጀመሪያ ‹‹የማይድን›› በሽታ ብሎ ለመፈረጅ የሚያበቃን ምንም ዓይነት አስተማማኝ ሕግ የለም። ሁለተኛ የበሽታውን ባህሪ በተመለከተ ለሕመምተኛው ወይም ለቅርብ ዘመዱ ምን ብለን መናገር ይኖርብናል የሚለው ጉዳይ ብዙ ጊዜ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው።

ማንም ሰው በግድ የለሽነት ‹‹ሊድን የማይችል›› የሚለውን ቃል መጠቀም አይገባውም። በነዚህ ጉዳዮች ላይ የቃላት አጠቃቀማችን ጥንቃቄ የተሞላ መሆን ይኖርበታል ለማለት ከበቂ በላይ የሆኑ ምክንያቶች አሉን። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በቀላሉ ሊድን በሚችል ተራ የዕለት በሽታ ይሞታሉ፤ በአንጻሩ ደግሞ ዶክተሮችና መላው ቤተዘመድ ተስፋ በቆረጡበት ሁኔታ በከባድ ሕመም የሚሰቃዩ ሰዎች ከሕመማቸው አገግመው ሲድኑ ይስተዋላሉ። ይህ በማንኛውም ጊዜና ለማንኛውም ነገር ተዘጋጅተን መጠበቅ እንዳለብን የሚያሳይ ነው። የመጀመሪያውና ከሁሉም በላይ በሕይወትና በሞት ላይ ሥልጣን እንደሌለን ሁላችንም ማመን ይኖርብናል። ሁለተኛ እግዚአብሔር በሚልከውና እርሱ እንዲሆን በሚፈቅደው መካከል ልዩነት እንዳለ መገንዘብ ያሻናል። እግዚአብሔር ክፉ ነገር በላያችን ላይ አያደርስም፤ ግን ከባድ ወይም ክፉ የሚመስል ነገር እንዲደርስብን ሊፈቅድ ይችላል። እዚህ ላይ ይህንን ልብ ማለት ያስፈልጋል ‹‹እግዚአብሔርንም ለሚወዱ ነገር ሁሉ ለበጎ ነው›› (ሮሜ 8፥28)።

አንድ አማኝ ክርስቲያን «የማይድን» ተብሎ በሚጠራ በሽታ ሲሰቃይ «የክብር ተስፋ» (ቈላ. 1፥27) የሆነውን ክርስቶስን፥ እምነቱንና ተስፋውን ለመመስከር እጅግ ምቹ አጋጣሚ ይሆንለታል። የማያምኑት ብዙዎች ደግሞ በሥቃይ ውስጥ ያለ ክርስቲያን አሸንፎ የሚመሰክረውን ደስታና ጽናት ሲመለከቱ ይደንቃቸው ይሆናል። ይህ «በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን» (ሮሜ 8፥37) የሚለውን ያሳያል። «ከማይድን» በሽታ ጋር በተያያዘ የሚነሣው ሌላው ጥያቄ ክርስቲያኖች አንድን በሽታ ለመፈወስ የእግዚአብሔርን ባሕታ ጉብኝት መጠየቅ ተፈቅዶላቸዋል ወይ የሚል ነው። «የእምነት ጸሎት ድውዩን ያድናል፤ ጌታም ያስነሣዋል» (ያዕ. 5፥15) የሚለው ቃል በእምነት ለሚፈወስም ይሁን በእምነት ለሚጸልይ ሰው ያላቸው ተግባራዊነት እርግጥ ነው። ቃሉ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሲያስተምረን «ፈቃድህ ትሁን» የሚለውን የክርስቶስን ቃል ለመቀበል መጠቀስ አይኖርበትም። በሁሉም

ሁኔታዎች ውስጥ ድርብ ትሕትና ይኖረን ዘንድ የግድ ነው። መጀመሪያው ትሕትና ሕመምተኛውን ያፈውሰው ዘንድ እርዳታውንና ምህረቱን በመሻት እግዚአብሔርን ስንማፀን፣ ይኸው ጸሎታችን በእርሱ ፊት የሠመረ ሲሆን ሁለተኛው አሁን ይጠራው ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ ሕመምተኛው በደስታ ወደ መንግሥቱ ለማያት ይገባ ዘንድ በሰላም እንዲያሰናብተው ስንጸልይ ነው።

«የእምነት ጸሎት» በሐኪም ቤት የሚሰጠውን የሕክምና ዕርዳታ ወይም የዚህ ዓይነቱን ሕክምና የሚተካ አንድ አማራጭ እንደሆነ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። የመናፍቅ አባዜ የተጠናወታቸው ክርስቲያኖች አንዳንድ ጊዜ በዚህ ዓይነት መንገድ ሲሠሩ ይታያል፤ ይህም አድራጎታቸው የክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያን በእጅጉ እየጎዳ ነው። እነዚህን ሁሉ መንገዶችና ስጦታዎች የሰጠን እግዚአብሔር ራሱ ስለ ሆነ እምነትና ጸሎት የሕክምና ዕርዳታ አማራጮች አይደሉም። ስለሆነም ማንም ሰው በሕመሙ የመዳን ወይም ተዶ ጥንና ክፍል ውስጥ «የእምነት

ጸሎት፥ ከማድረስ ሊገታን አይችልም። ክርስቲያኖች ሁሉ ይህን አጋጣሚ እንደ ልዩ ዕድል ሊቆጥሩትና መንገዶችን ሁሉ ሊጠቀሙበት ይገባል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን እንደ ፈቃዱ ይፈጽም ዘንድ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ ይኖርባቸዋል። ይህ ሁሉ እንዲህ ተብሎ በተጻፈው የሐዋርያው ትምህርት መሠረት ነው፦ «እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛ የእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ፤ እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት» (1 ጴጥ. 5፥6-7)።

## ትዕግሥትና ምስጋና

በሕይወት ዘመናችን በብዙ የሥጋት፥ የትግል፥ የአደጋና መዓት ወዘተ... እና በመጨረሻም የሞት ወቅቶች ውስጥ እናልፋለን። ይህ ግን ሊደንቀን አይገባም፤ ምክንያቱም ሐዋርያው ነገሩን እንዲህ በማለት ያጠቃልለዋልና ነው፦ «የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋል» (ዕብ. 10፥36)። እጅግ የከበዱ ችግሮች የሚያጋጥሙን ገና ከጧቱ ይሁን ወይም በሕይወታችን ማብቂያ ላይ፥ በመጀመሪያው ይሁን ወይም ማለቂያው ላይ አስቀድሞ የሚያውቅ ማንም የለም። ቢያንስ ከውጫዊ አይታ አንጻር ሞት ራሱ ለአንዳንዱ ከባድ ለሌላው ደግሞ ቀላል ሆኖ ይታይ ይሆናል። እዚህ ላይ እነዚህን ነገሮች ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ማግኘት ጋር በማነጻጸር ማየት ይኖርብናል፥ መከራ ሁሉ በሕይወት ዘመናችን ውስጥ «በፍጻሜው ዘመን» (ዳን. 12፥9) ወይም ዋጋችንን ተከትለው ይምጡ አይምጡ የሚለውን በቅድሚያ ማወቅ ፈጽሞ አንችልም። ጉዳዩ ምንም ይሁን ምን ነቅቶ መጠባበቅ አስፈላጊ ነው፦ «ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ» (ማቴ. 24፥42)። እነዚህ ሁሉ ሀቆች አንድን ነገር በግልጽ ይነግሩናል፥ «ጽናት ይኖርህ ዘንድ ያስፈልጋል»። ስለዚህ ክርስቲያኖች ሁሉ አንዱ ለሌላው እንዲህ ብሎ በማበረታታት ሊነግረው ይገባል፦ «እኛ

ግን ነፍሳቸውን ሊያድኑ ከሚያምኑት ነን እንጂ ወደ ጥፋት ከሚያፈገፍጉት አይደለንም›› (ዕብ. 10፥36-39)።

በመከራና በሥቃይ ውስጥ ሆነውም እንኳ በክርስቲያኖች ብልህና ትክክለኛ ባህሪ ውስጥ አመስጋኝነት አለ። እንድም እምነታችንና ፍቅራችን እየቀነሰ መሄዱ ለራሳችን ይታየናል፤ አሊያም ጥቂት እርምጃዎችን ወደፊት የተራመድን መሆናችንን ተስፋ እናደርጋለን። ስለሆነም ለሁሉም ነገር እግዚአብሔርን ማመስገን ይኖርብናል። ይህም ሕመምን፥ መከራንና ማንኛውንም ዓይነት ሥቃይ የሚመለከት ነው። በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ማለፍ ቢኖርብንም በነዚህ ሁኔታዎችም ውስጥ እያለን ምንም ዓይነት ነገር ቢሰማን በኃያሉ እግዚአብሔር እጆች ውስጥ መሆናችንን ሊሰማን ይገባል፤ ያን ጊዜ ደግሞ ልንደርስበት የማንችልን እንደ ሰቆቃወ ኤርምያስ ብዥ ይኖራል፦ ‹‹ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሳ ነው፤ ርኅራኄው አያልቅምና

ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤ ታማኝነትህ ብዙ ነው፤ ነፍሴ እግዚአብሔር ዕድል ፈንታዬ ነው፤ ስለዚህ ተስፋ አደርገዋለሁ አለች›› (ሰቆ. ኤር. 3፥22-24)።

ስለ ሕይወትና ስለ ሞት ያለው እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት በቀላሉ የሚገኝ አይደለም። ዕድሜ ሳይለይ በሁሉም ሰዎች ዘንድ ሊገኝ ይችላል። ይህ የሚገኘው በዕውነት ክርስቲያኖች ዘንድ ነው በማለት አፍ ሞልቶ መናገር አይቻልም። በአንጻሩ ነገሩ የግል ጉዳይ ነው፤ የጸጋና የቅድስና ፍሬም ነው፤ ስለሆነም በዕድሜ ቁጠራ ላይ የተመሠረተ አይደለም። ይህ በጸሎት ተግተን መሻት ያለብን መንፈሳዊ ስጦታ ነው። የሚመጣውም ‹‹ከትዕግሥትና የመጽናናት አምላክ›› ነው (ሮሜ 15፥5)።

### የመሞት ጥበብ

የጥንት ሮማውያን ስለ ‹‹የመኖር ጥበብ›› እንደ ተናገሩ ሁሉ ስለ ‹‹መሞት ጥበብም›› ተናግረው ነበር። በተጨማሪም ከዚህ ጋር የተቆራኘ ስለ አባባልም ያላቸው ሲሆን እርሱም ‹‹ለመሞት

የተገባህ መሆንህን አስተውል›› ይላል። ሌሎች ሰዎች ዘንድ እንደሆነው ሁሉ እነርሱም ያለ ፍርሃት ሞትን የሚጋፈጡና ከነ ክብራቸው የሚሞቱ ሰዎችን ድፍረት ያደንቃሉ።

ይህ ሁሉ እንደ ዋዛ የሚነገር ቢሆንም በአንድ ሕይወት ውስጥ መተግበር እጅግ ሲበዛ አስቸጋሪ ነው። አካላዊና አእምሮአዊ ጥንካሬ ካለ ጀግንነት እንደ ዕውቅናና ዝና ያሉትን ክብር የሚያጎናጽፍ ከሆነ በሕይወቱ ዘመን ጀግና መባል አንድ ነገር ነው። ግን ሕመምና የረዘመ ሥቃይ ኃይላችንን ሁሉ አሟጦ በሚጨርስበት ሁኔታ ውስጥ ጀግና መሆን ፍጹም የተለየ ነገር ነው።

አሁን ልክ እንደ ሌላው ጥበብ ሁሉ ግን በቀላሉ ልንማር ስለማንችለው ረጅምና ብዙ ልምምድ ስለሚጠይቀው የመሞት ጥበብ እንመለከታለን። ከሞት ጋር በተገናኘ ምንም ነገር መማር ወይም መተግበር የማይቻል ሆኖ ሊታይ ቢችልም ይቻላል። በእርግጥ የምንሞተው አንዴ ብቻ ነው፤ ይሁን እንጂ በሕይወት ዘመናችን ውስጥ በከባድ ሕመም ስንያዝ÷ ጓደኞቻችንና ዘመዶቻችን ሲታመሙ ወይም ከባድ አደጋ ሲደርስባቸው ወይም በሥቃይና በጣር ውስጥ ያሉ ሰዎች አልጋ ዳር ሆነን በምንመለከትበት ጊዜ ከሞት ጋር እንጋፈጣለን። ይህ ሁሉ ስለ ሕይወትና ስለ ሞት አብዝተን እንድናስብ እንዲሁም አንድ ቀን ከዚች ሕይወት የምንሰናበት መሆኑን እንድናስብ ዕድል የሰጠናል።

ሞታችንን በተመለከተ ዋናው ጥያቄ ‹‹መቼ›› ይሆናል የሚለው ሳይሆን ትልቁ ጥያቄ ‹‹እንዴት›› የሚለው ነው። እነዚህ ጥያቄዎች የመሞትን ጥበብ በጥልቀት የሚመለከቱ ስለሆነ ‹‹እንዴት›› የሚለው ጉዳይ በምን ዓይነት በሽታ ወይም አደጋ ልንሞት እንችላለን የሚል አይደለም። በዚህ ፈንታ በጣም አስፈላጊ የሆነና ከሌሎች ሁሉ ልዩ የሆነው ጉዳይ እንዲህ የሚል ነው÷ የሞታችን ምክንያት ምንም ይሁን ምን የሞታችን ቀን በፈለገው ጊዜ ቢመጣ ለሞት ዝግጁዎች ሆነን ያገኘናል ወይ? ይህን ሕይወት ተሻግረን ለማለፍና ገና ወዳላየነው ዓለም ለመግባት

ተዘጋጅተናል ወይ? ይህ «ብልብ ጥበብን እንድንማር ዘመናችን ይረዝም ዘንድ» (መዝ. 9፥ 12) የሚለው ቃል ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ የሚያሳየን ነው።

## የመጨረሻችን ቀንና ሰዓታት

ብዙ ጊዜ ሰዎች የመጨረሻቸው ቀናትና ሰዓታት እንዴት እንዲሆን እንደሚፈልጉ ይነግሩናል። አንዳንዶቹ ሞታቸው በድንገት ወይም በጥቂት ቀናት ሕመም ቢሆን ይመርጣሉ። አንዳንዶች በሞታቸው ወቅት ኅሊና የሚያሳጣ መድኃኒት ቢወስዱ ይመርጣሉ አንዳንዶች ደግሞ በሙሉ ስሜት ሕዋሳቶቻቸው ሆነው ሞታቸውን ለመቀበል ይመርጣሉ።

በአንድ ወይ በሌላ መንገድ በጣም ቀላሉን ነገር እንኳ ማድረግ ስለማንችል ይህን የመሰሉ አስተሳሰቦች ሁሉ ከንቱ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰቦች አደገኛ

ናቸው። በሞት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነትና መንፈሳዊ ስፍራ እንድንም በሚቶቻችን ሙሉ በሙሉ በኑሮዋችንን ሥር ናቸው ወይም አይደሉም ከሚለው በጣም ጠቃሚ ከሆነው ከዚህ ነገር ሊያወጡን ይከጅሉናቸዋል። እጅግ ትልቁ ቁምነገር ከእግዚአብሔር ወይም ከሰው ጋር ያላወራረድነው ነገር የለም። ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ መሰዊያው ፊት ከመቅረባችን በፊት ከሰዎች ጋር እንዴት ነገሮችን ማስተካከል እንዳለብን እጅግ በሚያስደንቅ መንገድ አስተምሯል (ማቴ. 5፥21-26)። ይህ ደግሞ በሞታችን ጊዜ ያላስተካከልናቸውን ጉዳዮች የሚመለከት ወሳኝ ነገር ነው። ለመሆኑ በከፍተኛ ሕመም እየተሰቃየን፣ ሕሊናችንን ስተንና በሞት አፋፍ ላይ ሆነን እንዴት ነው ነገሮችን የምናስተካክለው? በሌላ በኩል «ቢቻላን በእኛ በኩል» (ሮሜ 12፥18) ግጭቶችንና አለመግባባትን የመሳሰሉ ሌሎችንም ነገሮች ሁሉ አስተካክለን ከሆነ ይቅርታን ሰጥተንና ይቅርታ ከሰጠን የሕመማችን መጨረሻ ሊቀጥል ይችል ይሆናል ግን ጊዜ ዶስ የሚሆን ከሆነ ደግሞ በመጨረሻም እንሞታለን። ውጫዊው ሁኔታችን ምንም ይሁን ምን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን

ግንኙነት በተመለከተ የሚቀይሩት ምንም ነገር የለም በኃጢአት ይቅርታ ውስጥ እንመላለሳን በእጆቹ ዕቅፍ ውስጥ ነንና በሰላም እናንቀላፋለን።

በመላው ዓለም በሚገኙ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንደሚሰራበት ከሆነ የሞታችን ጊዜ መድረሱን ካመንና ዕድሉ ከተገኘ የጌታን ሥጋና ደም ለመውሰድ መጠየቅ የተለመደ ነገር ነው። በመሞት ላይ ላለ አንድ ክርስቲያን በዚህ መንገድ ጌታን መገናኘቱና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጀመሪያዎቹ ደቀ መዝሙርቱ ‹‹ነገር ግን እላችኋለሁ÷ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሮ አልጠጣውም (ማቴ. 26÷29)። በማለት በሰጠው ተስፋ መሰረት መጪውን ጊዜ አሻግሮ መመልከት እጅግ መባረክ ነው። እንዲሁም ደግሞ ከተቻለ ሚስት ወይም ባል ወይም ልጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች በሕመምተኛው አልጋ ዙሪያ ተሰባስበው ይህን ቅዱሱ ማዕድ በአንድነት መቍረስ መቻል እንዴት ያለ ትልቅ በረከት ነው። የሆነ ሆኖ በሆነ ምክኒያት በተጠቀሰው መንገድ ቅዱስ ቊርባን ማክበር የማይችሉ ከሆነ እንደ መጥፎ ዕድል ሊቆጠር አይገባውም። እንዲህ ያሉ አጋጣሚዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ማሳደር ነው። ሞት አልጋችን ላይ ሆነን ይህን መሰሉን አገልግሎት ወይም ሌላ አገልግሎ ብናገኝም እምነት ግን እዚያው እቦታዋ ላይ ነች።

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሕያው እምነት ከሌለን በስተቀር መሞት አስቸጋሪ ነው። ያለ እርሱ መሞት ያለ ‹‹ሕያው ተስፋ›› መሞት ነው። (1 ጴጥ. 1÷3፤ ቲቶ 1÷2)። በሌላ በኩል ደገም ‹‹በጌታ መሞት›› ከባድ አይደለም። ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁአን ናቸው። መንፈስም አዎን ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል›› (ራእ. 14÷13)።

# ምዕራፍ 20

## ወደ ዘለዓለማዊ ግብ መጓዝ

የምናቅደውና የምንከውነው እያንዳንዱ ሥራ ዓላማ አለው፤ መነሻና ፍጻሜም አለው። ሕይወትም ከዚህ የተለየ አይደለም። የራሱ ዓላማና ፍጻሜ አለው። እውነተኛ ግቡን የመታ ሕይወት ከሆነ ፍጻሜ ማለት አለቀለት፤ አበቃለት ማለት አይደለም።

ሁልጊዜ እግዚአብሔር ራሱን በቃሉ በገለጠበት መሠረት ብቻ መሆን ካለበት የክርስትና ምልከታ አንጻር እግዚአብሔር የሕይወታችን መጀመሪያ ነው። ወይም እርሱ ከጅማሬውም በፊት የነበረ ነው። «ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ እኔም እንደ ሆንሁ ታስተውሉ ዘንድ እናንተ የመረጥሁትም ባሪያዬ ምስክሮቼ [illegible]

[illegible] ከእኔም በኋላ አይሆንም» (ኢሳ. 43፥10)።

ስለ እግዚአብሔር የቀረበው ይህ እውነታ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በብዙ ኀይላት መንገዶች ተገልጿአል። የነዚህ ሁሉ ገለጻዎች ቁና ማዕከላዊ መንገድ (ዮሐ. 14፥6) ብቻ ሳይሆን «አልፋና ኦሜጋ፥ የመጀመሪያና የመጨረሻው» (ራእ. 21፥6) ተብሎ የተጠራው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልብና አእምሮ ሊረዳው እስከሚችል ድረስ በእግዚአብሔርና በሰው ውስጥ ያለውን፥ ከየት እንደመጣን፥ ምን እንደሆንና ወዴትስ ልንሄድ እንደምንችል ገልጦልናል።

በመሆኑም ግባችን የት እንደሆነ ጥርት ባለ መንገድ እንዲህ በማለት ነግሮናል፥ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐ. 3፥16)። «እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን

የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘለዓለም ሕይወት ናት›› ዮሐ. 17÷3፡፡ በሁሉም የክርስትና አስተምህሮዎችና የእምነት መግለጫዎች ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሚል በአንድ ቃል ብቻ የተጻፈ ‹‹ቃል›› ‹‹ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ›› ዮሐ. 1÷14 በሚለው ቃል ውስጥ ሚካተት ነው፡፡

እንዲሁም እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የሥነ ምግባር መርሆችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ተቀብለናል፡፡ ቀደም ባሉ ምዕራፎች ውስጥ እንደቀረበው ‹‹መንገድ›› የሚለው እንደ ‹‹እውነትና›› ‹‹ሕይወት›› ሊገለጽ ይችላል፡፡ በሕይወት ውስጥ የክርስቲያን አካሄድና አኗኗር የሚመሠረተው በጌታና አዳኝ ላይ ስለሚሆን የምንጠቀመው ቃል አንዱን ወይም ሌሎችን እንደ ‹‹ልብ›› ‹‹ሕሊና›› ‹‹ፍቅር›› ወይም እንደ ‹‹ጎረቤት›› ‹‹ኅብረት›› ‹‹ማኅበረሰብ›› ‹‹መልካም ሥራዎች›› ወዘተ... የመሳሰሉት ነገሮችን በግንዛቤ ውስጥ እናስገባለን፡፡ ስለሆነም በክርስትና ሥነ ምግባር ውስጥ ሊካተት የሚችል ሁሉም ነገር ከክርስቶስ ጋር በጥብቅ የተቆራኘና በእርሱ ዙሪያ የሚያጠነጥን መሆን አለበት፡፡ እርሱ ‹‹አልፋና ያሜጋ ነው›› ነው የሚለው በክርስት እምነት ብቻ ሳይሆን የክርስትና ሥነ ምግባርንም የሚያካትት ነው፡፡ ስለዚህ ሞት አገዛዙ ፍጻሜ ወደሌለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ዘላለማዊው ዓለም የሚያስገባ በር ብቻ ስለ ሆነ የክርስቲያን ሕይወት መነሻው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ ፍጻሜው ግን ይህ ነው አይባልም፡፡

## በመንገዱ ላይ የሚያጋጥሙ ፍንገጣዎች

እግዚአብሔር የሁሉ አባትና ረዳት መሆን ይገባዋል፡፡ የእርሱ መኖሪያም የሰዎች ሁሉ ግብ መሆን ይገባል (ዕብ. 13÷14፤ ዮሐ. 14÷2)፡፡ እነዚህ አሳቦች እግዚአብሔር ቀደም ብሎ በሰጠው ተስፋ መሠረት በመንገድ ላይ ለሚያጋጥም ችግርና መከራ ሁሉ እርዳታና መጽናናትን ይሰጣሉ፡፡ ‹‹መኖሪያህ

የዘለዓለም አምላክ ነው፣ የዘለዓለም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው›› (ዘዳ. 33÷27)። ይህ እያለ ሰዎች በልባቸው መጥፎና አጅግ ጎጂ ነገሮችን በመሸጉ ሰንቆቹ ከመልካሙ መንገድ እንዲፈነገጡ መመልከት አስገራሚ ነው። በቀድሞ ዘመን ከእውነተኛ መንገድ ይልቅ ማፈንገጥን የመረጡ ብዙ ሰዎች እንደ ነበሩ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሰፍሮ እናገኛለን። በዚህ መሠረት ባለጠጋውን ወጣት (ሉቃስ 18÷18-27) ‹‹ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር›› ይለብስ የነበረውን ባለጠጋ ሰው (ሉቃ. 16÷19-31) የአስቆሮቱ ይሁዳን፣ (ዮሐ. 12÷6፤ ማቴ. 26÷14-16) ዴማስን (2 ጢሞ. 4÷10) እና ሌሎች ብዙዎችን እናገኛለን። ዛሬ ድረስ የነዚህን ሰዎች ዱካ እየተከተሉ ያሉ ብዙዎች መኖራቸው የሚያሳዝን ነው። ‹‹ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ›› (1 ቆሮ. 10÷12)።

እንደ ገንዘብ፣ የትንበት ሰተውች፣ የሌሎትና ዝር

የመሳሰሉትን ጥቂት ነገሮችን እዚህ ላይ ብንጠቅስ ማንም ሰው ለማግኘት የሚፈልጋቸውና በአብዛኛው የተለመዱ ነገሮች ተደርገው የሚቆጠሩ ናቸው። ‹‹የተለመዱ›› በሚለው ዝርዝር ውስጥ ዕለት ተዕለት የሚፈጸሙ ብዙ ነገሮች አሉ። አሁን ባለንበት ክፍለ ዘመን ላይ ግብረ ሶዶማዊነት ከዚህ በፊት ባልታየ መልኩ በዝርዝር ውስጥ ለመካተት በቅቶአል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የዚህ ጉዳይ አንዱ ገጽታ በትክክለት ሊፈተሽ የሚገባው ነገር ነው። የዚህ አዲስ ዘይቤ ወይም ‹‹ነዚያት›› ላስፋከሉአቸው ሰዎች የወደፊት ዕጣ ኃላፊነት የማያስጨንቃቸው የጉዳዩ ብርቱ አቀንቃኞች ናቸው። የዚህ አስደንጋጭ ነገር ሰለባዎች ለሚሰጡት የመጨረሻ መልስ በእኔ ውትልህም ዓይነት ትክሻ መነትነት ወይም ‹‹በነገሩ ላይ ምን ማለት እንደፈለጋችሁ የተማባባን አልመሰለኝም›› ወይም ‹‹ውሴቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ማንም የተገነዘበ አልነበረም›› ወዘተ... የሚል የሥላት ይትርጓሜ ይሆናቸዋል።

ይህን መሰሉ ክስተት ብዙ ጊዜ በስፖርት ዘርፍም ይስተዋላል። በዚህ ዘርፍ ውስጥ አንድ ክስተት ከታየ ከገንዘብ

ጋር የተያያዘ አንድ ነገር አለ ማለት ነው። የሐዋርያው ቃል ለዚህ ጉዳይነቱ ነገር የሚስማማ ሆኖ እናገኘዋለን፡ «ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና» (1 ጢሞ. 6፥10)። ይህ በድሮ ዘመን ጥሩና ጤናማ የነበረው እንዲሁም ከማኅበረሰቡ መካከል ወጣቱን ያነቃቃ የነበረው ስፖርት ዛሬ በገንዘብ ኃይል ተጽዕኖ ሥር እንዲወድቅ ስለ ተደረገ አውዳሚ ሲሆን ጥራቱል ሰባሪ ሄደቱም ዘር እንዲተፋፋፉ አድርጎታል። ምሳሌዎቹም እጅግ የበዙ ናቸው። በብዙ የስፖርት ክለቦች ውስጥ ተጨዋቾችና ደጋፊዎቻቸው በአደንዛዥ ዕጾች ኃይል ሰጪ ንጥረ ነገሮችና የቁማር አጭበርባሪዎች ጠንካራ ክንድ ሥር እየወደቁ ነው። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ አንዲት ድሃ አገር ምርጥ የእግር ኳስ ተጫዋቾችን በውድ ዋጋ ከሌላው አገር እየገዛች ነው። በተመሳሳይ ጊዜ ተጫዋቾቹን በውድ ዋጋ ለሌላው ድሃ መንግሥት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በመመደብ ሰብዓዊ ዕርዳታ ሲያደርግ ይታያል። በዚህ ላይ ሥነ አመክንዮና መልካም ሥነ

ምግባር የት ነው ያሉት?

የዚህ ችግር ሌላው ገጽታ ደግሞ አለ። በአሁኑ ጊዜ ለስፖርት እየተባለ በሚመደበውና እጅግ አስፈላጊ ለሆኑ ነፃ ትምህርትና ባህል የሚመደበው ገንዘብ መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። አትራቢው ይህንን እውነታ በምሳሌ አስደግፎ እንደሚከተለው ያቀርባል። የግሪክ ቋንቋ ስመ ጥር የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ወርሐዊ ክፍያ ከአንድ የእግር ኳስ ተጫዋች ክፍያ በእጅጉ ያነሰ ነው። «ይህ አስቴኝ አይደለምንን?» አለ። ጥያቄው የቀረበለትም ሰው «አይ ከአንተ ጋር አልስማማም፤ ለመሆኑ በአንድ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ቀጥታ ወደ 100,000 የሚጠጋ ሕዝብ በደስታና በፌንጠዚያ ሲጮህ ሰምተህ ታውቃለህን?» በማለት መለሰለት። በሁለተኛው መልስ ሰጪ አሳብ መሠረት ሁሉም ነገር የሚለካውና የሚመዘነው በጊዜአዊ ስሜት፥ ደስታ፥ ገንዘብና ሐሴት ብቻ ነው። ስለ ዝነኛው የእግር ኳስ ተጫዋች መጻኢ ጊዜ የተጠቀሰ አንድም ነገር የለም። ከቡድኑ «ቢተነስ» ወይም የተጫዋችነት ዘመኑ ቢያበቃና ይኸው ይጮህለት የነበረው ሕዝብ

አሁን ደግሞ ድምጹን ከፍ አድርጎ «እስጠማለሁ፤ ተያረው» እያለ ቢሮክህበት ምን ሊሆን ነው? ምናልባት ዕድሜው በሃያዎቹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ይህ ዘንጭ ተማሪ ከዩድኑ መስኑበት ብቻ ሳይሆን በፊሊፕ የዕጽ ሱሰኛ ወይም ቁማርተኛ ስለሚሆን እንዲዚህም በዚህ በታላቁ የእንግሊዝ ኪስ ከሰብ ውስጥ በዕድሜ ትንሹ ከሆነው ልጅ ይልቅ እጅግ ድሃ ስለሚሆን በሕይወቱ ሁሉ እየተሽማቀቀና እያነሰ ይሄዳል። ምናልባትም በሰጋ ዕድሜው በሰው ሁሉ ተረስቶና አስታዋሽ አጥቶ በአንድ አልባሌ ቦታ ሞቶ ሊገኝ ይችላል። በዓለም እጅግ የከበረውን የክበር-ቤዎች የፈረስ እሽቅድምድም ክለብ የመማቢያ ቴኬት በነፃ የሚላክላቸው እነዚያ የተደሞ «ክክቦች» እየተባሉ ይንቆለጳጰሱ የነበሩ ወጣቶች ፍጻሜና የምድራዊ ሕይወት ድምዳሜ ይህን ይመስላል። እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች የስፖርት ዓይነቶችን በተመለከተም በመቶዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። ዛሬም በሆን ይህ ከስተት በሁሉም ጎስም «በአዲሶቹም»

አገሮች ሳይቀር እየተሠራበት ይገኛል። የዚህ አሳዛኝ ነገር ሌላው ገጽታ ደግሞ የስለባዎቹ ወላጆች እመራሮች ክለቦችና አጋሮች ሁሉ የገዛ ራሳቸውን ሥነ ምግባር፥ እንዲሁም የሚመለከተውን ሁሉ ሊያስተምሩ ግድ ይላቸው የነበረውን ሥነ ምግባር ችላ በማለታቸው ያልተሳሳቸው ከንቱዎች ሆነዋል።

በወይ ፊት ሕይወታቸው ስለሚጠትመውኣቸው መንፈሳዊና ሥጋዊ ነገሮች ላይ ጭብጥ ማሰያገ ሲገባቸው ለንስስብ አገቢያቸ ተጫዋቾች የሚሰጠውን የተለመደ ቃል በመጠቀም ወርቁን ለማግኘት ፋይዳ ያለው ግብ ላይ መድረስ በመሆኑ ለእግቢው የመጨረሻ ግቡ እንደ ሆነ ያስገነዝባሉ። ፋይዳ ያለው ግብ ላይ መድረስ ከሌተቻለ ጥቅሙ ምን ላይ ነው? በዚህ መንገድ ሀብቶችን ማጋበስ በዚህና በሌሎች ሊፈትኑት በሚችሉ ነገሮች ላይ ከዚህ በፊት ለወጣቶችና አዛውንቶች ይሰጥ የነበረውና ትርጉም ያለው ምክር ጋር ፈጽሞ የሚጋጭ ነው። «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?»

በዚህ ጉዳይ ዝናን ያተረፉ ወይም የተሳካላቸውና ሀብታም የሆኑ የብዙ ሰዎች ችግር በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶአል። በአንዳንድ የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎች ውስጥ መሰል የሆነ አተራረብ ሥፍር ይገኛል። በዳዊት መዝሙር ከሥራዎች አንዱን በመዝሙር 73 ላይ የተፈጠሩና ስለ ክፉ ሰዎች ምኞት በሰፊው የተብራራበት ክፍል ነው። በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ምኞትና ውጤቶቹ በጥቂት አስደማሚ ቃላት እንዲህ ተብለው ተገልጸዋል፤ «ክፉዎች ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው ገለባ ናቸው» (መዝ. 1፥4) «ኃጥእን ከፍ ከፍ ብሎ እንደ ሊባኖስ ዝግባም ለምልሞ አየሁት፤ ብመለስ ግን አጣሁት፤ ፈለግሁት በታውንም አላገኘሁትም» (መዝ. 37፥35-36)።

የእንዲህ ዓይነቱ ክፉት ምሳሌ ከሥነ ጽሑፍ፥ ከመዝገኛ፥ ከስፖርትና ከሁሉም ኅብረተሰብ ክፍል ለመዘገ

ይቻላል። በመልካም ቀኖች ውስጥ እንዲህ ማለት በጣም ቀላል ነው። «እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል? በልዑልስ ዘንድ በውኑ እውነት አለ?» (መዝ. 73፥11) ወይም «እግዚአብሔር የለም» (መዝ. 14፥1)። መልካም ቀኖች ካለፉና ሀብታምና ታዋቂ ሰው ተሰናክሎውን፥ ቆንጆነትውን፥ ጉልበቱን፥ ሀብቱን፥ ዝናውን ወዘተ... ሲያጣ ሁሉም ነገር የተለየ ይሆናል። ያን ጊዜ ልክ እንደ ጠፋው ልጅ ባልንጀሮች ሁሉ (ሉቃ. 15፥14-16) የዚህም ዓለም ጓደኞቹ፥ ደጋፊዎቹና አድናቂዎቹ ጥለውት ይሄዳሉ። እንዲህ ከመሰሉ ሰቆቃዎችና ከእግዚአብሔር የመለየት ምኞት እንድንመለስ እርሱ ራሱ እንዲህ ሲል ነግሮናል፤ «የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጕብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ፤ ደስ አያሰኙኝም በለህ የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ» «የብር ድሪ ሳይበጠስ የወርቅም ኩስኩስት ሳይሰበር ማድጋም በምንጭ አጠገብ ሳይከሰከስ፥ መንኰራኵርም በጉድጓድ ላይ ሳይሰበር፥ አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፥ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ» (መክ. 12፥1፤ 6-7)።

ከዓለም ሳይሆን በዓለም

ቀደም ሲል (በገጽ 75 እና ተከታዩ) ላይ ተነስቶ የነበረው ይህን ርዕስ እንደገና በድጋሚ እዚህም ላይ መታየት ያስፈርበታል። በክርስትና ሥነ ምግባር ውስጥ ያሉ ሁሉም ሲባሉ በሚችሉ ነገሮችና ችግሮች ይህን ርዕስ በሰፊው እንዳስስ የሚያስዳስሱ ናቸው። «እኛ አገራችን በሰማይ ነውና» (ፊልጵ. 3፥20) የክርስትና እምነት ዘለዓለማዊ ግብ ከዓለሙ ለጋሪ ማንነታችንና «ገረቤታችን» እንደማሉት ይሁል ዘንድ እምነታችን በዚህች ምድር ላይ ሊተገበር ይገባዋል። በዓለም ተኑሮ ግን ከዓለም ለሆን ይህ «ሁለቱም... እና» የሚለው መሳከራ ተግባርም ችግርም ነው። እንዲህም በመሆኑ ይህ ለብዙዎች የሚያሰናክል ዓለት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሩጫቸውን በመልካም ሁኔታ ጀምረው የነበሩ ብዙዎች ከመልካም መንገድ የመውጣታቸው ጉዳይ ነው።

ይህ ችግር ፊቱ ባለና ክርስቲያናዊ በሆነ መንገድ እንዲታ

ላለፉት ሁለት ወይም ሦስት ምዕተ ዓመታት የለውጥ ዓላማን እንግዳ ደፈጃ በደፈጃ ወይ ጋራ መማባበት ፍቅርና ኅብረት ለመድረስ ከሃይማኖት ድርጅቶችና እንግባብነት ካላቸው ሌሎች አካላት ጋር መተባበር ይኖርበታል በማለት ሲያስገነዝቡ ነበር። በዚህ ዓይነት መንገድ መላው የሰው ልጅ ፆታ ነቀል ለውጥ ከመጣ እዚህች ምድር ላይ የእግዚአብሔርን መንግሥት የማቋቋም ዓላም መፍጠር ስለሚቻል፡ «መንግሥተ ሰማያት» እዚሁ ስለምትኖር ዘለዓለማዊ መንግሥት ሰማይ መሆት አስፈላጊ አይሆንም በማለት ያስቡ ነበር። እንዲህ መሰል አስተሳሰቦች እጅግ አደገኛና ከኢየሱስ ወንጌልና እርሱ ካስተማረን ዘለዓለማዊ እይታ ጋር የማይስማሙ ናቸው። እዚህ ላይ ለተጠቀሱ አሳቦች ደግሞ በተግባር ያልተፈተሹ ተልልቅ መሰናክሎች አሉ። እነርሱም ለምሳሌ፡- «የውርስ ኃጢአትንስ» ምን ገጠመው? የኃጢአት ዝንባሌያችን ስለ መሸነፍስ? እግዚአብሔርን ከበክ መጠጠራቸው የተበው ደንጋና ልቦች ተዳይስ? መልካምንና ክፉን በሚለያየው የመጨረሻ ፍርድ በተመለከተ ምን የተፈጠረ ነገር አለ? የሚሉ ናቸው።

እውነታው የወደቀውን ዓለምና የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ አንድ የተመሳጠነና አኩል ወደ ሆነ ማኅበረሰብ ወይም መንግሥት አምጥቶን ለማዋሐድ ሥልጣን አልተሰጠንም። ይልቁንም የምድራዊው ማኅበረሰብ አባላትና መንግሥት ዜጎች ሆነን ለጥቂት ጊዜ እዚህ ምድር ላይ መኖር አለብን። ይህ ችግራችን ነው፤ ይሁን እንጂ ትግላችንና ግዴታችን ሲሆን እርሱም ከበድና አደገኛም ነው። ቢሆንም በእግዚአብሔር ጸጋ «በመጥፎና ጠማማ ትውልድ መካከል ያለ ነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባችሁ የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ በእነርሱም መካከል እንደ ብርሃን ልጆች እንታይ» (ፊልጵ. 2÷15)

ስለ መጨረሻው የፍርድ ቀንና ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወት ለማወቅ ያለውን ክርስቲያናዊ ትምህርት ሳይነቡ ከ‹ዓለም›ና ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር በተያያዘ እነዚህን ያልተፈቱ ችግሮችን ወይም ተግባራዊ ችግሮችን ለመገንዘብ መፍትሔ ለመስጠት አይቻልም። የሕይወት መሠረታችንን በሕይወት

ጉዞ ውስጥ መንገዳችንና ዘለዓለማዊ ግቦችን የምናገኘው ሕይወታችንን በዘለዓለም ምልከታ አንጻር ብቻ ከተመለከትነው ነው። እንዲሁም የስነ ምግባር ችግርን ለማቃለል ዘለዓለማዊ እይታ ያስፈልገናል። ጉዳዩም ዓለማዊ በሆኑ የፍልስፍናና የሥነ ምግባር ትምህርት ቤት ያሉ ምሁራን ለዓለማዊ ምክንያቶች ብቻ ሰንል ለምን ለጋብቻ፥ ትሑታን እና ለሰው ልጆች አባቢዎችና እንዲሁ ለሌላው መሥዋዕት እስከ መክፈል የተነገደደንበት ጉለማ ምን እንደ ሆነ ለማወቅና ለመግለጽ ትልቅ ችግር አለባቸው። ትንታኔአቸውን እንደ ፈለጉ ተያያዞው ቢያቀርቡም ከምላ ኃይል የሚያቀንቅኑት ማግኘት በማይገባን «ትርጉም» ዘረፋ ነው። የዚህም ትርጉም «ያስከፍላል» የሚል ነው። ይህ እነርሱ እንደሚሉት «ከሁሉ» እንደሚመጣ የሚታሰብ ከሆነ ሳላማዊው ተቀባይነት ስለሚኖረው ከምላ ኃይል ሥነ ምግባርን ከትርጉሙ ራስ ወዳድነት እንደር የሚመለከት ነው። በእነርሱ በኩል የሚታይ ከፍተኛ ችግር ነው። እግዚአብሔርና ዘለዓለማዊው ጉለም ከሌሉ ራሱን አለመውደድ ለምን አስፈለገ? ለምንስ ነው የአገልጋዮችን ጉሮሮ

እንተን እኛን ደስ የሚያሰኝ ነገር እንዲሠራ የምናስገድደው? (ማቴ. 18፥23-35)

ሐዋርያት በአዛብ ከተማዎች ተገኝተው እጅግ በጣም ጠቢባን በነበሩ የአቴናና የቆሮንቶስ ፈላስፎች መካል በነበሩበት ወቅት ያቀረቡት መልእክት ስለ ክርስቶስ ትንሣኤና «በዓለም ሁሉ» ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ነበር (ማቴ. 25፥31-45፤ ሐዋ. 17፥23-31፤ 1 ቆሮ. 1፥18-25፤ 2፥1-5)።

## የሚመጣው ዓለም

የክርስቶስ ትንሣኤ፥ የሙታን ትንሣኤና እርሱን ተከትሎ የሚመጣው ታላቁ ፍርድ በሁሉም የሰው ልጅ ሕይወት ላይ ሚያርፍ ዘላቂ አሻራ ናቸው። «መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (ሐዋ. 4፥12)። ይህ እውነታ በተመሳሳይ መንገድ ሁሉንም ኅብረተሰብ እንደሚመለከት ሁሉ እንዲሁም ሕይወታቸውን ባንድነት አገልግሎታቸውንና ኅብረታቸውን ይመለከታል።

ይህ ማለት ደግሞ የኅብረተሰብ፥ የክርስቲያንና የቤተ ክርስቲያን ሥነ ምግባር በተወሰነ መልኩ ከመጨረሻው ማለትም፤ ከሙታን ትንሣኤና ከዘላለማዊው ፍርድ ጋር የሚገናኝ ነው። ይህ እውነታ በብዙ መንገዶች ይገለጻል። የክርስቶስ ሐዋርያት ይህ እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ «የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ» (ዕብ. 3፥14) በማለት አመልክተዋል። ብዙዎች «የመምጣቱ የተስፋ ቃል ወዴት ነው?» (2 ጴጥ. 3፥4) እያሉ በንቀት የተሞሉ ጥያቄዎችን በማቅረብ ሊያሾፉትን ቢሞክሩም ሐዋርያው ግን ጌታ «ስለ እናንተ ይታገሣል» (2 ጴጥ. 3፥9) በማለት ያስረዳል።

ብዙ ተቃዋሚዎች ስለ ብዙ ነገሮች ለሚጠይቁት ጥያቄ የሚሰጣቸውን መልስ አምነው ከመቀበላቸው በፊት ሰፊና የተብራራ ዝርዝር መልስ ማግኘት ይሻሉ። ጥያቄዎቻቸውን

ሙሉ ለሙሉ መመለስ አንችልም። በተመሳሳይም ለጠላቶቻችን ጥያቄዎች ሁሉ መልስ መስጠት አስፈላጊ አይደለም። ሰውን፥ ሕይወትን፥ ሞትን፥ ትንሣኤን እና መድኃኒታችንን የሚመለከቱ ዋና ዋና ጥያቄዎችን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት መመለሱ ለሁላችንም፣ በቂ ነው። ያን ጊዜም ወደ ፊት አሻግሮ ማየት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከፊታችን ያለው መንገድ ግልጽ ይሆናል።

ክርስቲያን ለመሆን ከፈለግን «ተከተሉኝ!» (ዮሐ. 1፥44፤ ማቴ. 9፥9) ከሚለው የኢየሱስ ጥሪ በኋላ ያለው መንገድ አንድ ብቻ ነው። ኢየሱስን የሚከተል አንድ ክርስቲያን ባለማቋረጥ እንዲህ በማለት ይታመናል፤ ይናዘዛልም፡ «በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክቱን እፈጥናለሁ» (ፊልጵ. 3፥12-14)።

## የክርስትና ሥነ ምግባር ማጠቃለያ

ቀደም ባለፉት ምዕራፎች ውስጥ የሠፈሩትን ጉዳዮች ወደ ኋላ መለስ ብለን ብናይ ሙሉ በሙሉ ግለሰባዊ በሆነ የክርስትና ሥነ ምግባር መካከል ምን ያህል ሰፊ ልዩነት እንዳለ እንደገና እንገነዘባለን። የክርስትና ሥነ ምግባር ገና ከመሠረቱና ከጅማሬ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን በመታዘዝ ትንሣኤ በፍርድ ቀንና በዘላለም ሕይወት ላይ የተገነባ ነው። ከክርስትና እምነትና ሥነ ምግባር ጋር ተቃራኒዎቹ የሆኑ በማስተ-መደመም ለሚሻ ማንኛውም ሰው አስተዳዩም ይህን መሠረታዊ ሐቅ ከግምት ማስገባት ይኖርበታል። እዚህ ላይ ሁሉም ነገር የተመሠረተው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ዙሪያ ነው ብሎ መናገሩ ትክክል ነው። ይህንን በተራ ምሳሌ ማሳየት ይቻላል። አንድ ሞት ተምሳሌት አድርገን ከጥንት ዘመን የሠራበነው ነው። ሕይወት አበቃለት! ሁሉም ነገር አለፈ፤ ተፈጸሞአል የሚል መልእክት የያዘ የተሰበረ ምሶሶ ምልክት ላይ ይህ የክርስትና ምልክት አይደለም። በክርስትና በኩል የተለየ ምልክት (እርምጃ) አለን። እርሱም መስቀል ነው። ይህ መስቀል የእኛ ሥቃይና ሞት ምልክት አይደለም። ይልቁንም የክርስቶስ ምልክት ነው። ሥቃዩ

ክርስቶስ ለሞላው የሰው ልጅ ሲል የመሞቱና የክብር ትንሣኤው ምልክት ነው። ስለዚህ መስቀሉን ከሰባራው ምሰሶ በተቃራኒ የድል አርማችን አድርገን እንቀበለዋለን። «በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ሐሴት እናደርጋለን» (ገላ. 6፥14)፤ «ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው» (1 ቆሮ. 1፥18) እንደ ማለት ነው።

ድሉ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሆነ በዚህ መንገድ ወደፊት አሸንፈን በእምነት ዘለዓለማዊውን ዓለም ማየት እንችላለን። ይህ «ተስፋ» ተብሎ ሲጠራ የክርስቲያን ተስፋ ነው ማለት ነው። ተስፋው «የተዘጋጀልን ተስፋ» ነው። «ይህም ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን፤ እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደ መጋረጃውም ውስጥ የገባ ነው። ኢየሱስ ስለ እኛ ቀድሞ ሆኖ ገባ» (ዕብ. 6+19-20)።

አምንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት ይኖረው የሆን? አንድ ጠላት አባባል ውጤቱ አሉታዊ ይሆናል ነው መልሱ። ዘለዓለማዊ ሕይወት፥ ድነትንና ዘላለማዊ ደስታን በማመልከት ያሉት፤ አስተሳሰቦች ሁሉ ከንቱ ብሬት ሰብዓዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ክርስቲያኖች በምድራዊ ጉዳይ ባላቸው ተሳትፎት ላይ አሉታዊ ዝንባሌ ያሳድርባቸዋል ይላሉ። ይሁንና ግን ታሪክ የሚሰጠው ምስክርነት ከዚህ የተለየ ነው። ገና ከጅምሩ በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ምዕተ ዓመታት ላይ በክርስቲያኖች የበጎ አድራጎት ሥራና እንዲሁም በራሳቸው በአሕዛቦች መካከል በሉ ምቀኛ ሰዎች በማያሳዩት ተግባር አህዛቦች ይደነቁ ነበር። ክርስቲያኖች በዓለማዊ ነገሮች ላይ አሉታዊ ለማድረግ የሚጸየፉትን ያደርጉ ነበር። ክርስቲያኖች እንደ ቆሻሻ በየመንገዱ ይወረውሩ የነበሩትን ሰዎች አስከሬን በየዕለቱ ሲቀብሩ የመሰብሰባቸው ነገር አህዛቦችን ያስደምማቸው ነበር። ክርስቲያኖች ይህን የሚያደርጉት ለሙታን ትንሣኤውን የክብር ቀብር ለማድረግና መንገዶቹም የጸዱ እንዲሆኑ ለማድረግ ነበር ሁለተኛው ምላሽ ክርስትና ለመነካከስያው ዘመን አሁርጋ የበኀል ዕድገት ያመጣው ምንድን

ነው? በአገልግሎት በትምህርት በሆነ አድራጎት ዘርፎች ላይ ቤተ ክርስቲያን በበረከቱ ትው የሰበተ አስተዋጽኦ ነው። ሦስተኛ ምሳሌ ያለፉት ሁለት ወይም ሦስት ምዕተ ዓመታት እንደ ምሳሌ ሊወሰዱ ይችላሉ። ባርነትን ከማስወገድ በስተጀርባ እንዲሁም በብዙ ትላልቅ ማኅበራዊ ተቋማት ምሥረታ በስተጀርባ የነበረው አንቀሳቃሽ ኃይል ማን ነበር? በመንቃቃት በተቃኙ ክርስቲያን ድርጅቶች ግንባር ቀደም ማን ነበር? እዚህ ላይ በጀርመን በአገ ኦገስት ሄርማን ፍራንክ፣ በቴዎደር ፊሊደንደር ባሉ በመሳሰሉ ጉልቶችን ሰዎችና በሌሎች ተመርተው የተከፈቱትንና በራሳቸው የተመሩትን ተቋማትን ማስታወስ ይገባናል። በእንግሊዝ ጋርሰማውንና መንግሥትን ሳይቀር ለመቀስቀስ የተገደደበት አዲስ ማኅበራዊ አገልግሎትና ማኅበረሰቡን እንደገና የማዋቀር እርምጃ እንዲወሰድ ያደረገው የፋና ወጊዎቹ እማኝ ክርስቲያኖች የዊሊያም ዊልበርፎርስና ፍሎሬንስ ናይቲንጌል ሥራ ነበር። ታማኝ ክርስቲያኖች ለዓለማዊው ማኅበረሰባቸው ሥነ ምግባራዊና

ማኅበራዊ ዘርፍ ወደፊ የበዘ [illegible] ይህንንም ያደረጉት በለዓለማዊ ተስፋቸውን በጽናት እንደያዙ ነበር።

## ጥያቄው ሲቀለበስ

ጥያቄውን ቀልብሰን በሚከተለው መንገድ ብናቀርበው እስካሁን የተባለውን ነገር ሊያረጋግጥ ይችላል። በሌሎች አገሮችም እንደሚታየው ሁሉ በአሁኑ ጊዜ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል ከናቁ የነፍሳቸውን ድነትና ዘለዓለማዊ ተስፋቸውን ችላ በማለት ይልቁንም በዓለማዊ ነገሮችና በማኅበራዊ ሥራዎች ላይ ብቻ ቢጠመዱ ሊያገኙ የሚገባቸውን ማግኘት ይችላሉ? በአጠቃላይ መልሱ መሆን ያለበት በጭራሽ አይሆንም ነው። በማናቸውም ጊዜና ስፍራ የሚከናወኑ ይህ ዕድገ ቤተ ክርስቲያንን ተሳትፎ ገቶ ያደርጋል። በነዚህ ነገሮች ላይ የነበሩትን ተጽዕኖዎች በማገርም መልክ ይተንበላል። ማኅበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከአንድ ወይም ከሁለት ምዕተ ዓመታት በፊት በአውሮፓ ቤተ

ክርስቲያን ውስጥ ከነበረው ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር በኋለኛው ዘመን ላይ የተገኘው ውጤት በመጠኑም ገቶ ለ ነበር። የህ ነገር በተጨማሪ የሚያረጋግጥልን ዘለዓለማዊ አመለካከት የሚደክምና ጨርሶ የሚጠፋ ከሆነ ሥነ ምግባራዊና ኅብረተሰባዊ ጥንካሬ እየተጨፈጨፈ ኄዶ በመጨረሻም እንደሚጠፋ ነው። ስለዚህ ጌታችን አሁንም ቤተ ክርስቲያኑን እንዲህ በማለት ይገስጻል፦ «ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና። እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው አወስዳለሁ» (ራእ. 2፥4-5)።

## ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ ይሁን

ለአንድ ክርስቲያን በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ ከሁሉም በላይ ሁለት ነገሮች እጅግ በጣም አስፈላጊው ናቸው።

የመጀመሪያው ነገር እርሱ በሁሉም ይከብር ዘንድ «በሕይወት ቢሆን ወይም በሞት» (ፊልጵ. 1፥20) ክርስቶስን መያዝ ነው። ይህ የመጀመሪያው ነገር በተሟላ መንገድ እንዲህ ተብሎ ተገልጾአል «ክርስቶስን አገኝ ዘንድ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለውን ጽድቅ አይደለም» (ፊልጵ. 3፥8-9)። ሁለተኛውና አንድ ክርስቲያን በዚህ ዓለም በሚኖርበት ወቅት እጅግ በጣም አስፈላጊው ነገር «ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ መኖር» ነው (ፊልጵ. 1፥27)። ይህ ለማያምኑ ሰዎችም ምስክርነት ነው።

እዚህ ላይ የተነሳው ሕይወት ትርጉም እዚህ እንድንኖር በደረስን ጥሪ መሰረት በዓለም የምንኖር ይሁን እንጂ ከዓለም ሳይሆን አለመሆን ማለት ነው። ማንም ሰው ይህን ዓለም ከመሰናበቱ በፊት በዚህ ተግባር ውስጥ ማለፍ አይችልምና፤ ይልቁንም ይህ ተግባር ሁል ጊዜም ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል። ስለዚህ በክርስቶስ አዲስ መሆን በየቀኑ ሕይወት ውስጥ ባለማቋረጥ

መቀጠል አለበት። ይህ ማለት «በአእምሮ መንፈስ» መታደስ «እውነትም በሚሆን ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው» መልበስ ነው (ኤፌ. 4፥23-24)። ይህ ሥራ የሚሠራው በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ነው። አንድ አማኝ ባለማቋረጥ ኃጢአቱንና ውድቀቱን ያስተውል ዘንድ የሕግንም ተግባር ያነቃቃል። እንዲሁም በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔርን ጸጋ ያውቅና ይቀበል ዘንድ ወንጌሉ ደግሞ ይሠራል።

ይህ ተግባር እስከ ምን ያህል ጊዜ ድረስ መቀጠል አለበት? መጽሐፈ ስምምነት እንዲህ በማለት ይሰጣል። «ይህ መቀጠል ያለበት «ኃጢአተኛውን ሰውነት ሙሉ በሙሉ ከላያችን ላይ እስክናስወግድና የሕግ ስብከቱ+ ዛቻውና ቅጣቱ ዋጋ የሌለው እስከማይሆንበት ጊዜ ድረስና ጠቀሜታው ፍጹም ሳልሆነ ሟች ሕይወት ብቻ ስለሆነ የሥጋዊነቱም አስፈላጊነቱ እስከሚያበቃበት፤ የሰው ልጅ በትንሣኤው ፍጹምና አዲስ እስከሚሆንበት ቀን ድረስ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ሲያዩት በውስጣቸው በሚኖረው የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል አማካይነት እግዚአብሔርን (የሰማዩ አባታቸውን) ቅዱስ ፈቃድ ባልተበረዘ ደስታ ያለ ምንም ጭንቀትና ያለ አንዳች ክልካይ በሙሉ ልብ+ በፍጹም ንጽሕና በቃል ለዘለዓለም ሊሰሩት ያደርጋሉ»።

ክርስቲያኖች ቢያምኑና በዚህ ወንጌል ቢመላለሱ የብርሃን ልጆች ይሆናሉ፤ በብርሃንም ይመላለሳሉ (ዮሐ. 12፥35-36፤ ኤፌ. 5፥8)። ክርስቶስን መያዣውን የሚያቀምጡ ከሆነ ይህን ያደረጉት ራሱን በማመስገን መንፈስ አይደለም። ይህ ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ በመታመንና በቃልና በሥራ እርሱን በማወደስ ነው። እርሱ ራሱ መንገድና ሕይወት ስለ ሆነ (ዮሐ. 14፥6) በቃሉና በመንፈሱ እንዲሁም በቅድስት ቤተ ክርስቲያን አማካይነት በሕይወት መንገድ ይመራቸዋል።

ስለዚህ «የተወደድክ አባታችን ሆይ፤ በመጀመሪያ ወንጌል በዓለም ሁሉ በተገለጠው መንገድ ይሰበክ ዘንድ ቃልህን ስጠን፤

ይህ ቃል ደግሞ በመጨረሻ ላይ የሰይጣን መንግሥት ተወግዶ በፍጹም ቅድስናና ዘለዓለማዊ በረከት እንኖር ዘንድ ኃጢአት፥ ሞትና ሲኦል ድል ሆነውና ጠፍተው በቃልና በመንፈስ ቅዱስ አማኑኤልነት መንግሥትህ በመካከላችን ትሆን ዘንድ ከእኛ ጋር እንዲኖርና እንዲሠራ የእምነት ይሁንታ ይሁንልን።

ከጥንት ለነበረ፥ አሁንም ላለ፥ ለወደፊትም ለዘለዓለም ለሚኖር ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ይሁን፤ አሜን!